# መድሎተ አሚን ፡

## የሃይማኖት ሚዛን ።

መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ

ተ ዘ ጋ ጀ ።

ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በነገሡ ፡ በ፴፫ኛው ፡
ዘመን ፡ መንግሥት ።

ብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ የኢትዮጵያ ፡
ፓትሪያርክ ፡ በነበሩ ፡ በ፫ኛው ፡ ዓመት ።

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በትንሣኤ ፡ ዘጉባኤ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፶፬ ዓ. ም.

አዲስ አበባ ነሐሴ ፩ ቀን ፲፱፻፶፮ ዓ/ም
በድጋሚ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡

ኢትዮጵያውያን ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ አመዛዝነው ፡ ብልሚና ፡ ሳቂያ ፡ ያለው ፡ መኾኑን ፡ የሚረዱበት ፡ ስለኾነ ፡ የሃይማኖት ፡ ሚዛን ፡ ተብሎ ፡ ተሰየመ።



# ግርማዊ ሆይ ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አካላዊ ፡
ተዋሕዶ ፡ የምታምነው ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ አባ ፡ አየለ ፡ የተባሉ ፡ ካቶሊ
ካዊ ፡ መነኵሴ ፡ የኦርቶዶክስን ፡ ባህል ፡ በማከሰስ ፡ የካቶሊክን ፡ ባህል ፡
በማሞገስ ፡ የጻፉትን ፡ መጽሐፍ ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኦርቶ
ዶክስና ፡ በሮማ ፡ ካቶሊክ ፡ መከከል ፡ ያለውን ፡ የመለያየት ፡ ባህል ፡ ገል
ጮና ፡ አብራርቼ ፡ የጻፍኩትን መድሎተ ፡ አሚን ፡ የተባለውን ፡ መጽሐፍ ፡
አበረከታለሁ ።

ከዚህም ፡ ቀደም ፡ በ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ፡ም ፡ ዘመንፈስ ፡ አብርሀ የተባለ ፡ ፕሮ
ቴስታንት ፡ ተግሣጽና ፡ ምክር ፡ በሚል ፡ መጽሐፍ ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ ሕገ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ በመንቀፍ ፡ አባቶቻችን ፡ ነቢያት ፡ ሐዋርያት ፡ ጻድ
ቃን ፡ ሰማዕታትን ፡ በመዝለፍ ፡ የጻፈውን ፡ ጽሑፍ ፡ ምክንያት ፡ በማድ
ረግ ፡ በፕሮቴስታንትና ፡ በኦርቶዶክስ ፡ መከከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ገልጠ፡
ለማሳየት ፡ የጻፍኩትን ፡ ኰኵሐ ፡ ሃይማኖት ፡ የተባለውን ፡ መጽሐፍ ፡ ማበ
ርከቴን ፡ አስታውሳለሁ ።

እኒህ ፡ ኹለቱ መጻሕፍቶች ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ትክክለኛ ፡ መፅነት ፡ ያስ
ገኛቸው ፡ ፍሬዎች ፡ ናቸው ። ይህን ፡ የምልበትን ፡ ምክንያትም ፡ በሚከተለው
መሥመር ፡ እገልጻለሁ ።

ሰው ፡ በተፈጥሮው ፡ ኹሉም ፡ በአካለ ፡ ሥጋ ፡ ቅርጹ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡
ያንዱ ፡ ካንዱ ፡ የማይገጥም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ኅብረ ፡ መልክዕ ፡ እንዳለው፡
በመንፈሱም ፡ በኩል ፡ እንደዚሁ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ሕዋሳቶቹን ፡ እንደ ፡

ንጉሥ ፡ ኸኛ ፡ የሚገዛና ፡ የሚያዝዝ ፡ ያንዱ ፡ ከንዱ ፡ የማይገጥም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ያለው ፡ ልቡና ፡ አለው ።

ስለዚህ ፡ የኹሉም ፡ አሳቡና ፡ ምኞቱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ የለውን ፡ አምልኮቱን ፡ በተሻለና ፡ በተጣራ ፡ አነጋገር ፡ ገልጦ ፡ አስተምሮ ፡ ዋጋውን ፡ ለማግኘት ፡ ሲኾን ፡ በአሳቡና ፡ ባስተያየት ፡ አንዱ ፡ ከንዱ ፡ ካለመገጣጠሙ ፡ የተነሣ ፡ ኹሉም ፡ በየበኩሉ ፡ በሃይማኖት ፡ አገላለጥ ፡ በሕግና ፡ በባህል ፡ ተለያይቶና ፡ ተበታትኖ ፡ ይታያል ።

ኹሉም ፡ በየበኩሉ ፡ እውነተኛው ፡ ሃይማኖት ፡ እኔ ፡ የያዝኩት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ያነኑ ፡ ለማጽደቅ ፡ ከመጣጣር ፡ በቀር ፡ በሰላማዊው ፡ መንገድ ፡ ተጨዋውቶ ፡ ሐሳብ ፡ ለሐሳብ ፡ ካለመለዋወጡና ፡ ካለመግባባቱ ፡ የተነሣ ፡ አንዱ ፡ የሚለውን ፡ ሌላው ፡ ሳይረዳው ፡ በመፈራራትና ፡ በመኳረፍ ፡ ተለያይቶ ፡ ይኖራል ።

ይህንም ፡ ለማለት ፡ ያበቃኝ ፡ ዶክቶር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፋቸው ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ ችግርና ፡ አሳብ ፡ ድንግርግር ፡ የሚነሣው ፡ በሕርይና ፡ ህላዌ ፡ የሚሉት ፡ ቃላት ፡ ትርጕማቸው ፡ ያልተወሰነ ፡ በመኾኑ ፡ ነው ። ከውጭ ፡ አገር ፡ ተተርጕመው ፡ በመጡትና ፡ በክፍላቸው ፡ ከሚገኙ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ የሃይማኖት ፡ ባህል ፡ እውነተኛውን ፡ አሳብ ፡ አገኛለሁ ፡ ማለት ፡ ዘበት ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ጽፈዋል ። ከኢትዮጵያውያን ፡ መምህራን ፡ ጋራ ፡ እየተገናኙ ፡ ቢጨዋወቱ ፡ ኖሮ ፡ እንዲህ ፡ ከማለት ፡ ሳይደርሱ ፡ በተረዱት ፡ ነበረ ።

በእኛም ፡ በኩል ፡ እንደዚሁ ፡ ከቶሊካውያን ፡ ከሚሉት ፡ ባህል ፡ ብዙ ፡ የማይገባን ፡ ነገር ፡ አለ ። ቃል ፡ ለቃል ፡ ብንጨዋወት ፡ ወይም ፡ እንዲህ ፡ እንዳሁኑ ፡ በጽሑፍ ፡ ብንገናኝ ፡ ሲኾን ፡ እንስማማ ፡ ነበረ ፡ ወይም ፡ ለመለያየታችን ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ እናገኝለት ፡ ነበረ ፡ ለማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጉባኤ ፡ ኒቅያን ፡ ጉባኤ ፡ ኤፌሶን ፡ ጉባኤ ፡ ቍስጥንጥንያን ፡ ሌሎችንም ፡ ጉባኤያት በመዘንጋት ጉባኤ ፡ ሳይቆም ፡ ክርክር ፡ ሳይደረግ ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ መለያየት ፡ መጣ ፡ ለማለት ፡ አይደለም ።

ይልቁንም ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የተነሡ ፡ ነገሥታት ፡ በየጊዜው ፡ በሃይማኖት ፡ ካልመሰላችሁን ፡ በማለት ፡ በውስጣቸው ፡ የሚተዳደሩትን ፡ ሰዎች ፡ ሲያሠቃይዋቸው ፡ ይኖሩ ፡ እንደነበረ ።

ልዩ ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ያላቸውም ፡ ሰዎች ፡ ነገሥታቱን ፡ ከመፍራታቸው ፡ የተነሣ ፡ ባህላቸውንና ፡ አስተያየታቸውን ፡ በቃልም ፡ በጽሕፈትም ፡ ሳይገልጡ ፡ ደብቀው ፡ ይኖሩ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

ግርማዊነትዎ ፡ ግን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንደራሴ ፡ እንደ ፡ መኾንዎ ፡ መጠን ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃጥእ ፡ ጻድቅ ፡ አማኒ ፡ መናፍቅ ፡ ሳይል ፡ ኹሉንም ፡ በዝናም ፡ አብቅሎ ፡ በፀሐይ ፡ አብስሎ ፡ እንደሚመግብ ፡ ግርማዊነትዎም ፡ በመንግሥትዎ ፡ ሥር ፡ የሚተዳደረው ፡ ሕዝብ ፡ በትክክል ፡ መብቱ ፡ ተጠብቆ ፡ የሚኖርበትን ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አቋቋሙለት ። በሃይማኖትም ፡ በኩል ፡ ካባ

ቶችም ፡ ከአብርሀ ፡ ወአጽብሐ ፡ ጀምሮ ፡ ሳይቋረጥ ፡ ተያይዞ ፡ የወረደው አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ ልደት ፡ በተዋሕዶ ፡ ከበረ ፡ የሚል ፡ ኦርቶዶክሳዊ ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ በ፳ ፡ በ፳፫ ፡ በ፻፳፮ ፡ አንቀጽ ፡ እንደገለጹ ፡ ሌሎችም ፡ በመንግሥትዎ ፡ ጥላ ፡ ተጠልለው ፡ የሚኖሩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ባህል ፡ የያዙ ፡ ሰዎች ፡ የሕሊና ፡ ነፃነት ፡ እንዳያጡ ፡ በማሰብ ፡ በ፴፫ኛው ፡ አንቀጽ ፡ መብታቸው ፡ ተጠብቆላቸዋል ። ስለዚህ ፡ ከመንግሥቱ ፡ ሃይማኖት ፡ በአፍኣ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ሥጋት ፡ ጠፍቶላቸው ፡ ፍርሃት ፡ ርቆላቸው ፡ ሰውረው ፡ የያዙትን ፡ ባህላቸውን ፡ በቃል ፡ ሊናገሩት ፡ በጽሕፈት ፡ ሊገልጹት ፡ ቻሉ ።

እኛም ፡ በግልጥ ፡ ከቃላቸው ፡ ሳንረዳው ፡ በግምት ፡ እንዲህ ፡ ይላሉ ፡ አሉ ፡ እንዲህም ፡ ይላሉ ፡ አሉ ፡ እያልን ፡ እናማ ፡ የነበረውን ፡ በጽሕፈት ፡ ተገልጾ ፡ ስላገኘነው ፡ እውነቱን ፡ እውነት ፡ ሐሰቱን ፡ ሐሰት ፡ እያልን ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ቻልን ።

ደግሞ ፡ ከእኛ ፡ በላይ ፡ ያሉ ፡ ሊቃውንት ፡ በበለጠ ፡ አብራርተውና ፡ አስፋፍተው ፡ እንደሚጽፉ ፡ ተስፋ ፡ አለን ። ወደፊት ፡ የሚመጣውም ፡ ትውልድ ፡ የግራ ፡ ቀኛችንንም ፡ ጽሑፍ ፡ በመመልከት ፡ አመዛዝኖ ፡ የሚጠቅመውን ፡ መርጦ ፡ እንደሚይዝ ፡ እናምናለን ። በዚህም ፡ አኳኋን ፡ አንዱ ፡ ያጎደለውን ፡ አንዱ ፡ መልቶት ፡ አንዱ ፡ ያጣመመውን ፡ አንዱ ፡ አቅንቶት ፡ ሲገኝ ፡ በመግባባት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወደ ፡ ጥንት ፡ አንድነቷ ፡ እንድትመለስ ፡ እንመኛለን ።

ስለዚህ ፡ በአርእስቱ ፡ እኒህ ፡ መጻሕፍቶች ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ትክክለኛ ፡ መሪነት ፡ ያስገኛቸው ፡ ፍሬዎች ፡ ናቸው ፡ አልኩ ።

የግርማዊነትዎ ፡ መልካም ፡ መሪነት ፡ ባስገኘው ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመግባባት ፡ ደርሳ ፡ አንድነቷን ፡ አግኝታ ፡ ሌላውን ፡ ወገን ፡ ወደ ፡ ወንጌላዊት ፡ ጉባኤ ፡ ለመሰብሰብ ፡ በቅታ ፡ ለማየት ፡ ያብቃን ።

አሜን ።

ለዚህ ፡ እነጋገርና ፡ አሳብ ፡ ተስማሚ ፡

መወድስ ።

ዕሪና ፡ መዓልት ፡ ሕዝብ ፡ እምከመ ፡ ተሠርዐ ፡ ሌሊት ፡ ዘስሕተ ፡ ወመዓልት ፡ ዘለበወ
ለዘመንከ ፡ ዘበቱ ፡ ማዕረረ ፡ ዕሪና ፡ ፃዕደወ ።
ከመ ፡ በዕሩይ ፡ ይትካፈልዎ ፡ ሕገ ፡ መንግሥትከ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ዜነወ
ወሕገ ፡ ዕሪና ፡ ዘተመጠወ ፡ ኅቡዓቲሁ ፡ ከሠተ ፡ ማዕነ ፡ ፍርሃቱ ፡ ኀበ ፡ አስሐወ ።
ባሕቱ ፡ እንበለ ፡ ሕግ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ሀልወ ።
በዘያስተሐይጽ ፡ ሕሊናሁ ፡ መድሎተ ፡ አሚን ፡ ተደለወ ።
ንባበ ፡ ዳዊት ፡ ጽድቅ ፡ ከመ ፡ ኢይኩን ፡ ሕስወ ።
እመኒ ፡ ሐሳውያን ፡ ይዔምፁ ፡ መዳልወ ።
ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘለከ ፡ ኖኅተ ፡ ገነት ፡ ተርኅወ ።
እመኒ ፡ ሐሳውያን ፡ ይዔምፁ ፡ መዳልወ ።



የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል መርዕድ

አዝማች አስፋ ወሰን ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት
ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ።

# ማውጫ ፤


| | |
|---|---|
| መቅድም | ፲፯ |
| መግቢያ | ፳፪ |
| ማቅረቢያ | ፳፫ |
| የደራሲው ፡ ዐጭር ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ | ፳፯ |
| መልስ ፡ የሚሰጥበት ፡ መቅድም | ፳፰ |
| ደራሲው ፡ የጠቀሷቸው ፡ መጻሕፍት ፡ | ፴፩ |
| በኢትዮጵያ ፡ የሚታመነው ፡ ባሀል ፡ | ፴፯ |
| እውነተኛው ፡ ምክንያት | ፵፭ |
| ኢትዮጵያ በእስክንድርያ ፡ ስለመመራቷ | ፵፱ |
| ስለግብጻዊው ፡ ጳጳስ ፡ ሥራና ፡ ሥልጣን | ፵፱ |
| ነገሥታቱ ፡ በሃይማኖት ፡ ስላላቸው ፡ ሥልጣን | ፶፭ |
| ስለ ፡ ዕጨጌው ፡ ሥልጣን | ፶፮ |
| ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ የተለየችው ፡ መቼ ፡ ነው | ፷፪ |
| ልዩ ፡ ልዩ ፡ አስተያየቶች ፡ | ፷፫ |
| በይኾናል ፡ የሚገለጹ ፡ አሳቦች | ፷፱ |
| ስለ ፡ ፱ ፡ ቅዱሳን ፡ አመጣጥ ፡ | ፷፭ |
| የኬልቄዶንን ፡ ጉባኤ ፡ የመቃወም ፡ ምልክት | ፸፪ |
| ስለኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ አስተያየት ፡ | ፸፯ |
| በጉባኤ ፡ ስለተደረገው ፡ ታሪክ ፡ ስሕተት | ፺ |
| አካላዊ ፡ ተዋሕዶን ፡ ሲተረጕሙ ፡ የሚያገቧቸው ፡ ቃላት | ፻፲፭ |
| የቃሎች ፡ ምርመራ ፡ | ፻፲፰ |
| የኬልቄዶኑን ፡ ውሳኔ ፡ ይቀበላሉ ፡ ስለሚሉት ፡ | ፻፳፭ |
| የኢትዮጵያውያንና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰባኪዎች ፡ ክርክር | ፻፴፯ |
| የካቶሊክ ፡ ሰባኪዎች | ፻፴፱ |
| የመጀመሪያ ፡ ክርክሮች ፡ | ፻፵፪ |
| በ፲፮፻ ፡ በ፲፯ኛ ፡ ፻ ፡ የተደረጉ ፡ ክርክሮች ፡ | ፻፵፰ |
| አሳቦችና ፡ ምስክሮች | ፻፶፯ |
| በአምልኮና ፡ በሃይማኖት ፡ የሚገኝ ፡ ትምርት | ፻፷ |
| ስለክርስቶስ ፡ ቅብዐት ፡ ክርክር | ፻፷፱ |
| ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ | ፻፷፱ |
| የተገለጡ ፡ አስተያየቶች | ፻፺፭ |
| የርስ ፡ በርስ ፡ ክርክሮች | ፻፺፪ |
| ስለቅኔዎች | ፻፺፰ |
| የመጨረሻ ፡ ፍርድ | ፪፻፲፭ |
| ጠቅላይ ፡ መደምደሚያ | ፪፻፲፯ |
| ማጠቃለያ ፡ አሳብ | ፪፻፳፱ |

# መቅድም ፡፡

## ከመልአከ ፡ ብርሃን ፡ አድማሱ ፡ የተዘጋጀ ።

መቅድም ፡ ማለት ፡ ለሚመጣው ፡ ነገር ፡ መሪ ፡ ፊታውራሪ ፡ በር ፡ ከፋች ፡ ማለት ፡ ነው ።

ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ይደልዎ ፡ ለዘያነብብ ፡ ቅድመ ፡ ይዝክር ፡ ስሞ ፡ ለበዓለ ፡ መጽሐፍ ፡ ወእምዝ ፡ ያንብብ ፡ ወይምሀር ።

መጽሐፍ ፡ ለሚመለከት ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ የደራሲውን ፡ ስምና ፡ ታሪክ ፡ ማወቅ ፡ ከዚያ ኀ በኋላ ፡ መጽሐፉን ፡ ማንበብ ፡ መተርጐም ፡ ይገባዋል ፡ ብሎ ፡ እንደነገረን ፡ እኔም ፡ አስቀድሜ ፡ ስሜንና ፡ አድራሻዬን ፡ ቀጥዬም ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ለመጻፍ ፡ ያሰብኩበትን ፡ ምክንያት ፡ እያከታተልኩ ፡ እጽፋለሁ ።



እኔ ፡ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ አድማሱ ፡ ጀንበሬ ፡ የተወለድኩበትና ፡ ያደግሁበት ፤ የተማርኩበት ፡ ሀገሬ ፡ በጎጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ዲማ ፡ ጊዮርጊስ ፤ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ ተብዬ ፡ የተሾምኩበት ፡ ብቸና ፡ ጊዮርጊስ ነው ።

ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ለመጻፍ ፡ ያሰብኩበት ፡ ምክንያት ፡ ዶክተር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የተባሉ ፡ ካቶሊካዊ ፡ መነኵሴ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ የምታምነው ፡ ትምርት ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ተነሥተው ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፈዋል ። ይህም ፡ መጽሐፍ ፡ የዶክተርነት ፡ ማዕርግ ፡ ለመቀበል ሊቅነታቸውን ፡ ለማስመስከር ፡ የጻፉት ፡ እንደ ኾነ ፡ ታውቋል ።

ፍሬ ፡ ነገሩም ፡ ኢትዮጵያ ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ስላልነበረች ፡ በልዮንና ፡ በዲዮስቆሮስ ፡ መከከል ፡ የተደረገውን ፡ ታሪክ ፡ ሳታውቀው ፡ እንደ ጠፍ ፡ ከብት ፡ ለግብጽ ፡ መናጆ ፡ ኾና ፡ ትነኰዳለች ፡ እንጂ ፡ በህሏ ፡ ከካቶሊክ ፡ በህል ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነውና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሮም ፡ ካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥር ፡ ትተዳደር ፡ የሚል ፡ ነው ።

ይህነኑም ፡ እውነት ፡ ለማስመሰል ፡ ከውጭ ፡ ሀገር ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ መጽሐፍ ፡ በብዙ ፡ ጠቅሰዋል ፡ ዐፄ ፡ ካሌብና ፡ ፱ቱ ፡ ቅዱሳንም ፡ ካቶሊካውያን ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ለማስረዳት ፡ ሞክረዋል ።

የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ መንግሥትና ፡ ቤተ ፡ ክህነትም ፡ ለማለያየት ፡ ሊቃውንቶቿንም ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ለማጣላት ፡ በብዙ ፡ ጥረዋል ። ምናልባት ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ለተመለከተው ፡ እውነት ፡ ይመስለው ፡ ይኾናል ። ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ አይቶ ፡ መልስ ፡ ሳይሰጡ ፡ ዝም ፡ ማለት ፡ የቀደሙ ፡ አባቶቻችንን ፡ እንደ ፡ ማስወቀስ ፡ ክብርን ፡ እንደ ፡ መቀነስ ፡ ሀገርን ፡ እንደ ፡ መበደል ፡ ራስን ፡ እንደ ፡ መግደል ፡ ኾኖ ፡ ስለታየኝ ፡ ተመልካች ፡ ነገሩን ፡ ያመዛዝንበት ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ጻፍኩ ፤ ስሙንም ፡ መድሎተ ፡ አሚን ፡ ብዬ ፡ ሰየምኩት ። ነገሩን ፡ ለማመዛዘን ፡ የሚረዳ ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ መነሻና ፡ ውሳኔ ፡ ማወቅ ፡ ስለሆነ ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፎ ፡ ያገኘሁትን ፡ ታሪክ ፡ መቅድም ፡ አድርጌ ፡ እጽፋለሁ ።

## ፩ኛ ፡ ስለ ፡ ካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ መነሻ ፡ የሚገልጽ ፡ ታሪክ ።

አውጣኪ ፡ የተባለ ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ ውስጥ ፡ ያለች ፡ ያንዲት ፡ ገዳም ፡ መነኵሴ ፡ ነበረ ። እርሱ ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋው ፡ ረቂቅ ፡ ነው ሕማም ፡ ሞት ፡ አይስማውም ፡ ብሎ ፡ አስተማረ ።

አውሳብዮስ ፡ የሚባል ፡ የንስጥሮስ ፡ ጠበቃ ፡ በቍስጥንጥንያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ በፍላብያኖስ ፡ ላይ ፡ ከሰሰው ፤ ፍላብያኖስም ፡ ፴ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ሰብስቦ ፡ አውጣኪን ፡ ገዝተው ፡ ፍላብያኖስና ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳቱም ፡ አውጣኪን ፡ ከገዘቱ ፡ በኋላ ፡ የርሱን ፡ ቱሳሔ ፡ አጠፋን ፡ ብለው ፡ የንስጥሮስን ፡ ክህደት ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ አደሱት ፡ አውጣኪም ፡ ያላገባብ ፡ ተገዝቻለሁ ፡ ፍርድ ፡ ይታይልኝ ፡ ሲል ፡ ለንጉሡ ፡ ለቴዎዶስዮስ ፡ አቤት ፡ አለ ።

ወደ ፡ ልዮንም ፡ ፍላብያኖስ ፡ ያስጎጢአት ፡ ገዘተኝ ፡ ብሎ ፡ ላከ ። ልዮንም ፡ ለአውጣኪ ፡ ይድረስ ፡ ከከበረ ፡ ልጁ ፡ ከአውጣኪ ፡ ለነገርኸ ፡ ብልሃት ፡ ፈልጌ ፡ እስክተናልህ ፡ ድረስ ፡ አይዞህ ፡ በለህበት ፡ ሃይማኖት ፡ ጽና ፡ ብሎ ፡ ላከበት ። ንጉሥ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ግን ፡ የአውጣኪን ፡ አቤቱታ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ ከእስክንድርያ ፥ ዩልያኖስ ፡ ዘኢየሩሳሌምን ፤ ድምኑስ ፡ ዘአንጾኪያን ፤ እስጢፋኖስ ፡ ዘኤፌሶንን ፡ አስጠራ ። እነዚህም ፡ ተሰብስበው ፡ ፻፶ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ጨምረው ፡ የገዘትክበትን ፡ ምክንያት ፡ መጥተህ ፡ ንገረን ፡ ብለው ፡ ከፍላብያኖስ ፡ ዘንድ ፡ ላኩበት ።

ፍላብያኖስም ፡ የነርሱን ፡ ጥሪ ፡ እንቢ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ልዮን ፡ ዘሮም ፡ ዘንድ ፡ አድነኝ ፡ ተማፅኘብሃለሁ ፡ ሲል ፡ ላከ ። ልዮንም ፡ ለአውጣኪ ፡ አይዞህ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ላከበት ፡ ለፍላብያኖስም ፡ አይዞህ ፡ ብሎ ፡ ላከበት ፡ በዚህ ፡ ፍላብያኖስ ፡ ከጉባኤው ፡ አልመጣም ፡ ብሎ ፡ ቀረ ። የተሰበሰቡትም ፡ ፻፷ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ከቅዱስ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ጋራ ፡ ኸነው ፡ አውጣኪን ፡ ሃይማኖትኽ ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ።

እርሱም ፡ ከሀደቱን ፡ በልቡ ፡ ደብቆ ፡ ሃይማኖቴ ፡ የ፫፻፲፰ ፡ ሊቃውንት ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፡ አላቸው ፤ ወዲያውም ፡ ነአምን ፡ በ፩ ፡ አምላክ ፡ ብሎ ፡ ሐመ ፡ ወሞተ ፡ ወተቀብረ ፡ ወተንሥአ ፡ እስከሚለው ፡ ድረስ ፡ አነበበ ፡ ቱሳሔ ፡ ብዬ ፡ መናገሬንም ፡ አላውቅም ፡ አለ ። ዲዮስቆሮስ ፡ የተሰበሰቡትን ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ምን ፡ ይኹን ፡ ትላላችሁ ፡ አላቸው ። ዩልያኖስ ፡ ዘኢየሩሳሌም ፡ አውጣኪ ፡ አሁን ፡ ከፊታችን ፡ የታመነበት ፡ ሃይማኖት ፡ የ፫፻፲፰ ፡ ሊቃውንት ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፡ ከግዝቱ ፡ ይፈታ ፡ ከሹመቱ ፡ ይግባ ፡ አለ ።

ድምኑስ ፡ ዘአንጾኪያም ፡ እኔ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ አውጣኪን ፡ መግዘቴ ፡ ፍላብያኖስ ፡ ቢልክብኝ ፡ ነው ፤ አሁን ፡ ግን ፡ በወረቀት ፡ ጽፎ ፡ ያቀረበው ፡ በኒቅያ ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነውን ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፡ አለ ።

እንደዚኹም ፡ እስጢፋኖስ ፡ ዘኤፌሶን ፡ ከምእመናን ፡ ይቀላቀል ፡ አለ ። ከርሱም ፡ ቀጥሎ ፡ ጸላስዩስ ፡ ዘቂሣርያ ፡ ይግባ ፡ ሲል ፡ ፈረደ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የቀሩት ፡ ከየአገሩ ፡ የተሰበሰቡ ፡ አበው ፡ እንደዚሁ ፡ ፈረዱ ። እነርሳቸው ፡ ከፈረዱ ፡ በኋላ ፡ ቅዱስ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ተነሥቶ ፡ እናንተ ፡ እንዲህ ፡ ከፈረዳችሁ ፡ እኔም ፡ ይህነን ፡ የተቀደሰውን ፡ ጉባኤ ፡ ፍርድ ፡ እቀበላለሁ ፡ አውጣኪ ፡ ከግዝቱ ፡ ይፈታ ፡ ከሹመቱ ፡ ይመለስ ፡ ስል ፡ ፈርጃለሁ ፡ አለ ።

ደግሞ ፡ ያውጣኪ ፡ መነኰሳት ፡ ጥፋታችንን ፡ ሳናውቅ ፡ ፍላብያኖስ ፡ ገዘተን ፡ ብለው ፡ ለጉባኤው ፡ ለቤት ፡ አሉ ። ቅዱስ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ከጉባኤ ፡

ጋራ ፡ ኸና ፡ እናንተን ፡ እንጠረጥራችኋለን ፡ የምታምኑትን ፡ ሃይማኖት ፡ ግለ ጡልን ፡ አላቸው ፡ መነከሳቱም ፡ በሮቱፀትና ፡ በዚች ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ ከተማ ፡ ፻፶ው ፡ ሊቃውንት ፡ በወሰኑት ፡ ሃይማኖት ፡ እናምናለን ፡ አሉ ። ዲዮስቆሮስም ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ እንደሉሎቹም ፡ አበው ፡ ቅዱሳን ፡ እምነት ፡ አድርጋችሁ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ታምናላችሁን ፡ አላቸው ። አዎን ፡ እናምናለን ፡ አሉ ። ዩልያኖስ ፡ ዘኢየሩሳሌም ፡ በእውነተኛው ፡ ሃይማኖት ፡ ከመኑ ፡ ከምእመናን ፡ ይቀላቀሉ ፡ ቢል ፡ ፈረደ ። የቀረውም ፡ ጉባኤ ፡ ይህ ንን ፡ ፍርድ ፡ ተቀብለነዋልና ፡ አለ ። በመጨረሻ ፡ ቅዱስ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ የአውጣኪንና ፡ የመነከሳቱን ፡ ሃይማኖት ፡ አይተን ፡ ከምእመናን ፡ ይቀላ ቀሉ ፡ ካልን ፡ እስኪ ፡ ፍላብያኖስን ፡ በክርስቶስ ፡ እንዴት ፡ እንደሚያምን ፡ እንጠይቀው ፡ አለ ። ከጉባኤው ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ ቢጠየቅ ፡ በንስጥሮስ ፡ ሃይ ማኖት ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለቱን ፡ ገለጠ ። የተሰበሰቡት ፡ ፻፴፯ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ከቅዱስ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ጋራ ፡ ኾነው ፡ ፍላብያኖስን ፡ ከ፫ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ጋራ ፡ ገዘቱት ፡ ከሹመቱ ፡ ሻሩት ፡ ወዲያውም ፡ በሥላሴ ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የማይል ፡ ግዝተኛል ፡ ሲሉ ፡ ወሰኑ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እኒህ ፡ የተ ወገዙት ፡ ሰዎች ፡ ሮም ፡ ከልዮን ፡ ዘንድ ፡ ሔደው ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ያንተን ፡ ሥልጣን ፡ በመጋፋት ፡ አንተን ፡ ሳይጠይቅ ፡ ካንተ ፡ ሳይማከር ፡ አንተ ፡ በሌለኽበት ፡ በገዛ ፡ ሥልጣኑ ፡ ጉባኤ ፡ ሠርቶ ፡ የቍስጥንጥንያውን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ፍላብያኖስንና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩትን ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ አው ግዞ ፡ ለያቸው ፡ ከሹመታቸው ፡ ሻራቸው ፡ በታላቂቱ ፡ ሀገር ፡ በሮም ፡ የተ ሾምከው ፡ በሊቀ ፡ ሐዋርያቱ ፡ በጴጥሮስ ፡ ወንበር ፡ የተቀመጥከው ፡ አንተ ፡ እያለህ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ እንዲህ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ይገባዋልን ፡ እርሱ ፡ ምን ድን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ነገር ፡ ሠሩበት ፡

ልዮንም ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ተቈጣ ፡ ተናደደ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ መርቅያንም ፡ ፪ ባሕርይ ፡ የሚለውን ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ በጿኤ ፡ ፍና ፡ በማለት ፡ እያቅናና ፡ የዲዮስቆሮስ ፡ ሃይማኖት ፡ ግን ፡ የቀናች ፡ እን ዳይደለች ፡ ጽፎ ፡ እኒህ ፡ ተወግዘው ፡ የተሻሩትም ፡ ሰዎች ፡ ጉባኤ ፡ ተደ ርጎላቸው ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ እንዲያስረዱ ፡ ሲል ፡ ላከ ።

ይህችም ፡ መልእክት ፡ ለመርቀያን ፡ ደረሰችው ። መርቅያንም ፡ በንስጥ ሮስ ፡ ሃይማኖት ፡ ያምን ፡ ነበርና ፡ እኒያ ፡ የተወገዙት ፡ ሰዎች ፡ ሔደው ፡ ንስጥሮስ ፡ ከተሰደደበት ፡ ሀገር ተመልሶ ፡ ስለሃይማኖቱ ፡ እንደገና ፡ ይጠየቅ ፡ ሲሉ ፡ ለመኑት ። ንጉሡም ፡ ንስጥሮስ ፡ ከተሰደደበት ፡ ሀገር ፡ ከአክሚም ፡ ይምጣ ፡ ብሎ ፡ መላክተኛ ፡ ላከ ። ንስጥሮስ ፡ ግን ፡ ታሞ ፡ ተኝቶ ፡ ይድናል ፡ ብለው ፡ ቢጠብቁትም ፡ አልዳነም ፡ ወዲያው ፡ ሞተ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እኒህ ፡ ሰዎች ፡ ጉባኤ ፡ ይደረግልን ፡ ብለው ፡ አሳሰቡና ፡ በ፫፻፲፰ ፡ ሊቃውንት ፡ አጠፌታ ፡ ፮፻፴፮ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ተሰበሰቡ ። እኒኽውም ፡ መለከውያን ፡ ተብለዋል ፤ መለከውያንም ፡ ማለት ፡ የንጉሥን ፡ ፈቃድ ፡ የሚፈጽሙ ፡ ማለት ፡ ነው ። ልዮን ፡ ግን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክ ፡ ወሰብእ ፡ ፍጹም ፡ በ፪ ፡ ፍና ፡ እምድኅረ ፡ ተዋሕዶ ፡ በ፪ቱ ፡ ህላዌያት ፡ ክርስቶስ ፡ ከተዋሐደ ፡ በኋላ ፡ በ፪ ባሕርይ ፡ በ፪ ፍና ፡ የተለያየ ፡ አምላክና ፡ ሰው ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፎ ፡ ልኮ ፡ ቀረ ።

ይህንን ፡ ደብዳቤ ፡ ጉባኤው ፡ አክብሮ ፡ ሲቀበል ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ብቻ ፡ አልቀበልም ፡ አለ ፡ ንጉሡ ፡ መርቅያን ፡ ያለቃኽን ፡ የልዮንን ፡ ክታብ ፡ ለምን ፡ አትቀበልም ፡ አለው ። ዲዮስቆሮስም ፡ ሲመልስ ፡ ሳጥናኤል ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ ነበረ ። ቢክድ ፡ ቀረበት ፡ ከሹመቱ ፡ ተሻረ ፡ ከማዕርጉ ፡ ተዋረደ ። ልዮንም ፡ እንደዚሁ ፡ አባቶቻችን ፡ በወሰኑት ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንቶ ፡ ቢገኝ ፡ በእውነት ፡ አለቃዬ ፡ ነበረ ፡ ሃይማኖት ፡ ከለወጠ ፡ ግን ፡ አለቃዬ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ጠማሩን ፡ ቀደደውና ፡ እስኪነግሩኝ ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ ቤት ፡ የተጠራ ፡ እንደ ፡ ሰውነቱ ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ እንደ ፡ አምላክነቱ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ ፤ እንደ ፡ ሰውነቱ ፡ ነው ፡ አሉት ። ውኃውንስ ፡ ወይን ፡ ያደረገ ፡ እንደ ፡ ሰውነቱ ፡ ነውን ፡ ቢላቸው ፤ እንደ ፡ አምላክነቱ ፡ ነው ፡ አሉት ። እንግዲያስ ፡ እንደ ፡ ሰውነቱ ፡ የተጠራው ፡ እንደ ፡ አምላክነቱ ፡ ውኃውን ፡ ወይን ፡ ካደረገ ፡ ተአምራትን ፡ የሚያደርግ ፡ በፈቃዱ ፡ መከራ ፡ የሚቀበል ፡ ክርስቶስ ፡ መለኮቱ ፡ ከትስብእቱ ፡ ትስብእቱ ፡ ከመለኮቱ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነዋ ፡ አለ ።

ደግሞ ፡ ከኤጲስ ፡ ቆጶሳቱ ፡ አንዱ ፡ ልዮን ፡ ለክርስቶስ ፡ አንዱ ፡ ተአምራት ፡ የሚያደርግ ፡ አንዱ ፡ መከራ ፡ የሚቀበል ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ አሉት ፡ ይላል ። ከዚህ ፡ ሌላ ፡ መለኮት ፡ መከራ ፡ ተቀበለ ፡ ተብሎ ፡ ሊነገር ፡ አይገባም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ አለ ። ዲዮስቆሮስ ፡ ሲመልስ ፡ አባቴ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ የመለኮትና ፡ የትስብእት ፡ ተዋሕዶ ፡ እንደ ፡ እሳትና ፡ እንደ ፡ ብረት ፡ ተዋሕዶ ፡ ነው ፤ ብረትና ፡ እሳት ፡ ተዋሕደው ፡ በመዶሻ ፡ ሲመቱ ፡ እሳቱ ፡ ከብረቱ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዶ ፡ ብትሩን ፡ በሚቀበልበት ፡ ጊዜ ፡ ሕማሙ ፡ ለብረቱ ፡ ይሰማዋል ፡ እንጂ ፡ ለእሳቱ ፡ እንደ ፡ ማይሰማው ፡ የመለኮትም ፡ መከራ ፡ መቀበል ፡ እንደ ፡ ዚህ ፡ ነው ፡ ብሏል ፡ አለ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የቀናችቱ ፡ እውነተኛይቱ ፡ ሃይማኖት ፡ የዲዮስቆሮስ ፡ ናት ፡ እያሉ ፡ አሰምተው ፡ ተናገሩ ። ንጉሡ ፡ ግን ፡ እንግዲህ ፤ ከዚህ ፡ ኹሉ ፡ ጉባኤ ፡ ለሃይማኖት ፡ ሠሪ ፡ መሪ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ነህን ፡ አለው ። ሌሎቹም ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ የእኛም ፡ ቃላችን ፡ እንደ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ አሉ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ተቈጥቶ ፡ ተነሣ ፡ ጉባኤውም ፡ ተበተነ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ አውግዞ ፡ የለያቸው ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳት ፡ ግርማኽን ፡ ከላለየኹውና ፡ ካላዋረድኩው ፡ ጉባኤውን ፡ የሚፈታው ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ነው ፡ አሉት ። ሌሎቹ ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ አይኾንም ፡ ከዚህ ፡ ከጉባኤው ፡ ውስጥ ፡ ኸማግሎችንና ፡ ታላላቆችን ፡ ሰዎች ፡ መርጦ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ከዲዮስቆሮስ ፡ ጋር ፡ ጠርቶ ፡ መልከም ፡ በመናገር ፡ በትሕትና ፡ ፈቃዱን ፡ ይግለጽላቸው ፡ ቃሉን ፡ ተቀብለው ፡ ወደርሱ ፡ ሃይማኖት ፡ ቢመለሱ ፡ መልከም ፡ ነው ፤ አንመለስም ፡ ቢሉ ፡ ግን ፡ የንጉሥን ፤ ትእዛዝ ፡ ማንም ፡ ሊለውጠው ፡ አይችልም ፡ አሉት ። ንጉሡም ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዲዮስቆሮስን ፤ የቍስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አናጦልዮስን ፤ የአንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ መቅሲሞስን ፤ የኢየሩሳሌም ፡ ኤጲስ ቆጶስ ፡ ዑብላንዮስን ፤ የኤፌሶን ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ ማርቆስን ፤ ከኤጲስ ፡ ቆጶሳቱ ፡ ውስጥ ፡ ፫ት ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ሰብስቦ ፡ በንጉሡ ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ፰ ወንበር ፡ አዘጋጀ፤ ንግሥቲቱ ፡ ብርክልያም ፡ በመጋረጃ ፡ ውስጥ ፡ ኹና ፡ የሚነጋገሩትን ፡ ትሰማ ፡ ነበረ ። ከንጉሡ ፤ ባለሟሎች ፡ አንዱ ፡ ተነሥቶ ፡ ከዚህ ፡ የተሰበሰባችሁ ፡ አባቶች ፡ ሆይ ፡ ንጉሥ ፡ ይወዳችኋል ፡ ጸሎታችሁን ፡ በረከታችሁን ሊቀበል ፡ ይሻልና ፡ እንቢ አትበሉት ፡ አታሳዝኑት ፡ አላቸው ።

ዲዮስቆሮስ ፡ ሲመልስ ፡ እኛም ፡ እጅግ ፡ እንወደዋለን ፡ መልከም ፡ ጤና፡ ከረጅም ፡ ዕድሜ ፡ ጋር ፡ እንመኝለታን ፡ እነሆ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥቱን ፡ ክብሩን ፡ ሰጥቶታል ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ያልሰጠው ፡ ነገር ፤ የለም ፡ ይህ ፡ ይበቃዋል ፡ ዕዳ ፡ በደል ፡ እንዳይኾንበት ፡ በሃይማኖት ፡ ነገር ፡ እንዳይገባ ፡ እንመኝለታለን ፡ አለ ። በዚህ ፡ ነገር ፡ ብዙ ፡ ከተመላለሱ ፡ በኋላ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ንጉሥ ሆይ ፡ የልዑንን ፡ ቃል ፡ አትስማ ፡ ያባቶቻችን ፡ ሃይማኖት ፡ የቀናችናትና ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አትሻ ፡ አለው ። ንግሥቲቱ ፡ ብርክልያ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ በቀደመችቱ ፡ ሃይማኖት ፡ ላይ ፡ ሊጨመርበት ፡ ወይም ፡ ሊቀነስላት ፡ የማይሻ፡ መኾኑን፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ተቈጥታ ፡ እነሆ ፡ በአውዶክስያም ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ እንዳንተ ፡ ያለ ፡ ዕቡይ ፡ ትዕቢተኛ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ፤ ለአንተም፡ በርሱ ፡ ያደረሰ ፡ ይደርስብሃል ፡ አለችው ። እናትሽ ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅን፡ ብትበድለው ፡ ምን ፡ ተጠቀመች ፡ እግዚአብሔር ፡ በጽኑ ፡ ሕማም ፡ ስላሠቃያት፡ ከመቃብሩ ፡ ሔዳ ፡ አልቅሳ ፡ ሥርየት እስክትለምንና ፡ በድኑን ፡ አምጥታ ፡ በዚህ ፡ ቦታ ፡ እስክትቀብረው ፡ ድረስ እግዚአብሔር ፡ በጽኑ ፡ ሕማም ፡ እንዳሠቃያት ፡ ኋላም ፡ ይቅር ፡ እንዳላት ፡ አታውቂምን ? አንችም ፡ እነሆ ፡ ከፊትሽ ፡ አለሁልሽ ፡ የወደድሽውን ፡ አድርጊ ፡ አንችም ፡ እርሷ ፡ እንደተጠቀመች ፡ ትጠቀሚያለሽ ፡ አላት ።

ንግሥቲቱ ፡ የእናቷን ፡ ነገር ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ የእናቷ ፡ ነገር ፡ አበሳጭቷት ፡ አጅዋን ፡ በመጋረጃው ፡ አዝልቃ ፡ ኹለት ፡ ጥርሶቹ ፡ እስኪረግፉ ፡ ድረስ ፡ ደበቀችው ፤ ገጨችው ፤ መታችው ፡ ከዚያ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ እየተነሡ ፡ ገሚሶቹ ፡ ሰደቡት ፤ ገሚሶቹ ፡ ጽሕሙን ፡ ነጩት ፡ ርሱም ፡ የተሰበረውን ፡ ጥርሱን ፡ የተነጨውን ፡ ጽሕሙን ፡ ሰብስቦ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖቴ ያገኘኝት ፡ ፍሬ ፡ ናትና ፡ ጠብቋት ፡ ብሎ ፡ በእስክንድርያ ፡ ላሉ ፡ ምእመናን ፡ ላከላቸው ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳቱ ፡ ከቁስጥንጥንያ ወጥተው ፡ ጉባኤው ፡ በኬልቄዶን ፡ እንዲኾን ፡ አዘዘና ፡ ጉባኤው ፡ በኬልቄዶን ፡ ኾነ ፡ ወዲያውም ፡ ከሮ ተሟ ፡ ቃል ፡ ፩ ፡ አካል ፡ ማለትን ፡ ጨምሮ ፡ እንደ ፡ ንፅጥሮስ ፡ ባህል ፡ በኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በኹለት ፡ ፈቃድ ፡ አምላክ ፡ ወሰብእ ፡ ብሎ ፡ ልዮን ፡ የጻፈውን ፡ አስመስሎ ፡ ጻፈና ፡ ይህንን ፡ ሃይማኖት ፡ የተቀበለ ፡ በሹመቱ ፡ ጸንቶ ፡ ይኑር ፡ በክብር ፡ ላይ ፡ ክብር ፡ ይጨመርለት ፡ ይህን ፡ አልቀበልም ፡ የሚል ማን ፡ ከሹመቱ ፡ ይሻር ፡ በሹመቱም ፡ ሌላ ፡ ይተካበት ፡ ሲል ፡ አወጀ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ወደ ፡ ጉባኤው ፡ ቢገባ ፡ እኒያን ፡ አውግዞ ፡ የለያቸውን ፡ ሰዎች ፡ ከጉባኤው ፡ መካከል ፡ ተቀምጠው ፡ አገኛቸው ።

እኒህን ፡ ተወግዘው ፡ የተለዩትን ፡ ሰዎች ፡ ከጉባኤ ፡ መካከል ፡ እንዲገቡ ፡ ማን ፡ አሰናበታቸው ፤ አንተስ ፡ አብላንዮስ ፡ እኒህን ፡ ሰዎች ፡ ለማውገዝ ፡ ከእኔ ፡ ጋር ፡ ተስማምተህ ፡ የጻፍከው ፡ ጽሑፍ ፡ ያለ ፡ አይደለምን ፡ አለ ፡ ከኤጲስቆጶሳቱ ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ እየተነሡ ፡ ይህንን ፡ ትእዛዝ ፡ ያዘዘ ንጉሡ ፡ ነው ። እኛ ፡ አይደለንም ፡ አሉ ፡ ዲዮስቆሮስም ፡ ይህ ፡ ጉባኤ ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ቢኾን ፡ እኔም ፡ እትባበር ፡ ነበር ፡ ስለንጉሥ ፡ ብላችሁ ፡ ከኾነ ፡ እንደ ፡ ወደዳችሁ ፡ አድርጉ ፡ ብሎ ፡ ወጥቶ ፡ ሔደና ፡ ካንድ ፡ ሥፍራ ፡ ተቀምጠ ፡ እስኪ ፡ የሚደረገውን ፡ አይታችሁ ፡ ንገሩኝ ፡ ብሎ ፡ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ ላከ ፡ ጉባኤውም ፡ የንጉሡን ፡ ትእዛዝ ፡ ሰምቶ ፡ ከብዙ ፡ ክርክርና ፡ ጭቅጭቅ ፡ በኋላ ፡ የንጉሡን ፡ ቁጣ ፡ በመፍራት ፡ ነገሩን ፡ ተቀበለው ። ዲዮስቆሮስ ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ጉባኤው ፡ የንጉሡን ፡ ቃል ፡ በመቀበል ፡ ከተስማማ ፡ እኔ ፡ ብቻዬን ፡ ምን ፡ አደርጋለሁ ፡ የተፈራረማችሁበትን ፡ ላኩልኝና ፡ ልፈርም ፡ ብሎ ፡ ላከ ።

እነርሱም ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ላኩለት ፡ እርሱም ፡ አባቶቻችን ፡ ባቆዩን ፡ በቀናችቱ ፡ ሃይማኖት ፡ ላይ ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡ የጨመረ ፡ ወይም ፡ የቀነሰ ፡ ቢኖር ፡ ለዚህም ፡ ረዳት ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ውጉዝ ፡ ነው አውግዤዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ጽፎ ፡ ፈርሞ ፡ መለሰላቸው ። ኤጲስቆጶሳቱ ፡ ብዙ ፡ አዘኑ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ጉባኤዎቹ ፡ ንጉሡን ፡ ከመፍራታቸው ፡ የተነሣ ፡ ነቂጣ ፡ የተባለ ፡ ከመኳንንቱ ፡ አንዱ ፡ ለጓደኞቹ ፡ ለመኳንንቱ ፡ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ቢያዝዘኝ ፡ ከዲዮስቆሮስ ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ጉባኤ ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ እንኳ ፡ ሳላሳርፍበት ፡ ይህችን ፡ በትር ፡ በማሳየትና ፡ በማስፈራራት ፡ ብቻ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት በነዳሁት ፡ ነበረ ፡ አለ ፡ ይባላል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ታስሮ ፡ ተግዞ ፡ ወደ ፡ ደሴተ ፡ ጋግራ ፡ ሔደ ፡ እትኩ ፡ የምትባል ፡ አገር ፡ ኤጲስ ቆጶስ ፡ አባ ፡ መቃርስም ፡ አብሮት ፡ ተሰደደ ። ከምሥራቅ ፡ ሀገር ፡ የመጡ ፡ አራት ፡ ኤጲስቆጶሳት ሸሽተው ፡ አመለጡ ። ዲዮስቆሮስም ፡ በዚያው ፡ እንደታሰረ ፡ ሞተ ፡ የሚል ፡ ታሪክ ፡ እናገኛለን ፤ ኢትዮጵያ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ባትኖርም ፡ መምህሯን ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ ተከትላ ፡ ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጀምራ ፡ ከሮም ፡ ካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተለየች ፡ ናት ።

፪ኛ ፡ ይህ ፡ የካቶሊክ ፡ ባህል ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በምን ፡ ጊዜ ፡ እንደመጣና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ በምን ፡ ዓይነት ፡ እንደተቃወሙት ፡ የሚገልጽ ፡ ታሪክ ።

ኢትዮጵያን ፡ ግራኝ ፡ መሐመድ ፡ በወረራት ፡ ጊዜ ፡ ዐፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ከፖርቱጊዝ ፡ መንግሥት ፡ ርዳታ ፡ ጠይቀው ፡ እርሳቸው ፡ ተሞቱ ፡ በኋላ ፡ በፖርቱጊዞች ፡ ርዳታ ፡ ግራኝ ፡ ድል ፡ ኾና ኢትዮጵያ ፡ ሙሉ ፡ ነፃነቷን ፡ አግኝታ ፡ መንግሥቷን ፡ በትክክል ፡ ማቋቋምዋ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ተልኮ ፡ ፓርቱጊዞችን ፡ ለርዳታ ፡ ያመጣው ፡ ቤርሙዲዝ ፡ ከኢትዮጵያ ግዛት ፡ ገሚሱ ፡ ለፖርቱጊዝ ፡ መንግሥት ፡ ይሰጥ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም፡ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ አቡን ፡ ከእስክንድርያ ፡ መምጣቱ ፡ ቀርቶ ፡ ከሮም ፡ ይምጣ ፡ እኔም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አንደኛ ፡ መጀመሪያ ፡ ሮማዊ ፡ ጳጳስ ፡ ልኹን ፡ ብሎ ፡ ዐፄ ፡ ገላውዴዎስን ፡ ጠየቀ ። ዐፄ ፡ ገላውዴዎስም ፡ ሊቃውንቱን ፡ ሰብስበው ፡ ምን ፡ እናድርግ ፡ ብለው ፡ ጠየቁ ። የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንትም ፡ ፍርድ ፡ በቃ ፡ ይስጡን ፡ እንከራከርና ፡ ሮማውያን ፡ ቢረቱን ፡ እንልቀቅላቸው ፡ ብንረታቸው ፡ ይልቀቁልን ፡ አሏቸው ። ንጉሡም ፡ ፈቅደው ፡ ጉባኤ ፡ ተደረገ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ አፈ ፡ ጉባኤ ፡ ዝክሪና ፡ ጳውሊ ፡ ኾኑ ።

ጳውሊም ፡ በኀጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ፀዲጥ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አጠገብ ፡ የሚገኝ ፡ የደብረ ፡ ጽሙና ፡ ገዳም ፡ ሊቃውንት ፡ ናቸው ።

ኢትዮጵያውያን ፡ ሮማውያንን ፡ ሀገራችሁ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ሃይማኖታችሁስ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ጠየቋቸው ።

ሮማውያን ፡ ሲመልሱ ፡ ሀገራችን ፡ ሮም ፡ ነው ፡ ሃይማኖታችንም ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ ጠባይዕ ፤ አንዱ ፡ የመለኮቱ ፡ አንዱ ፡ የትስብእቱ ፡ እንላለን ። ሁለተኛም ፡ ወልድ ፡ ከአብ ፡ ያገሳል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ከወልድ ፡ ያንሳል ፡ እንላለን ፡ አሏቸው ።

ኢትዮጵያውያን ፡ ሲመልሱ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ምን ፡ አለ ፡ እስኪ ፡ አስረዱን ፡ አሏቸው ።

ሮማውያን ፡ ሲመልሱ ፡ እርሱው ፡ ራሱ ፡ ወልድ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሕልፈተ ፡ ዓለም ፡ የሚኾን ፡ መቸ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁት ፡ መላእክትም ፡ ቢኾኑ ፡ ወልድም ፡ ቢኾን ፡ ከአብ ፡ በቀር ፡ ያችን ፡ ዕለት ፡ ያችን ፡ ሰዓት ፡ የሚያውቃት ፡ የለም ፡ ብሏል ። ስለዚህ ፡ አብ ፡ መለኮት ፡ ስለኾነ ፡ ያውቃል ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ግን ፡ መለኮት ፡ ስላልኾኑ ፡ አያውቁም ፡ እንላለን ፡ እናንተ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ትሉታላችሁ ፡ አሉ ፡ አባ ፡ ዝክሪ ። ሲመልስ ፡ ምስቱን ፡ አካላት ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ፩ ፡ አምላክ ፡ የምንላቸው ፡ አብን ፡ ልብ ፡ ወልድን ፡ ቃል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ እስትንፋስ ፡ ብለን ፡ በአብ ፡ ልብነት ፡ ያስባሉ ፡ ያውቃሉ ፡ በወልድ ፡ ቃልነት ፡ ይናገራሉ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እስትንፋስነት ፡ ሕያዋን ፡ ኾነው ፡ ይኖራሉ ፡ ለየራሳቸው ፡ ልብ ፡ ቃል ፡ እስትንፋስ ፡ የላቸውም ፡ በማለት ፡ ነው ።

ልብ ፡ ቃል ፡ እስትንፋስ ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በልቡ ፡ አስቦት ፡ ዐውቆት ፡ ለመናገር ፡ ጊዜው ፡ ባለመድረሱ ፡ ሰዓት ፡ እየጠበቀለት ፡ ሰውሮ ፡ የያዘውን ፡ ነገር ፡ ጊዜው ፡ ባለመድረሱ ፡ ምክንያት ፡ በቃሉ ፡ ሳይናገረው ፡ ቢቆይ ፡ ቢጠየቅም ፡ ዛሬ ፡ አልናገረውም ፡ ቢል ፡ እያውቀውም ፡ እንደማይባል፤ ወልድም፡ያችን፡ዕለት፡ያችን፡ሰዓት ፡ ከአብ ፡ በቀር ፡ ወልድ ፡ አያውቃትም ፡ ማለቱ ፡ ያችን ፡ ዕለት ፤ ያችን ፡ ሰዓት ፡ የምትገለጽበት ፡ ጊዜው ፡ እስኪደርስ ፡ በልቤ ፡ በአብ ፡ ሰውሬ ፡ አቆያታለሁ ፡ እንጂ ፡ ዛሬ ፡ በቃልነቴ ፡ አውጥቼ ፡ አልናገራትም ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የማያውቃት ፡ ኾኖ ፡ አይደለም ፤ እንዲህስ ፡ ባይኾን ፡ የከዊን ፡ ስማቸውና ፡ ግብራቸው ፡ ተፋልሶ ፡ አብ ፡ ቃል ፤ ወልድ ፡ ልብ ፡ በተባሉ ፡ ነበረ ፡ አለው ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሮማውያን ፡ መልስ ፡ አጥተው ፡ ዝም ፡ አሉ ።

<u>ኹለተኛ ፡ ጥያቄ ።</u>

ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ሮማዊ ፡ ተነሥቶ ፡ መለኮት ፡ ሥጋ ፡ አልኾነም ፡ ሥጋም ፡ መለኮት አልኾነም ፡ ሥጋ ፡ ለመለኮት ፡ እንደ ፡ ብረት ፡ ልብስ ፡ እንደ ፡ ጥሩር ፡ ኾነው ፡ መለኮትና ፡ ሥጋ ፡ ኅዳሪና ፡ ማኅደር ፡ ኾነው ፡ መለኮት ፡ የመለኮትን ፡ ሥራ ፡ ትስብእትም ፡ የትስብእትን ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡ ኖረው ፡ በዕርገቱ ፡ ጊዜ ፡ የለበሰውን ፡ ሥጋ ፡ አውልቆ ፡ በ፫ኛው ፡ ሰማይ ፡ አኑሮት ፡ በየማን ፡ አብ ፡ በዘባነ ፡ ኪሩብ ፡ ተቀመጠ ። የዚህም ፡ ምሳሌው ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ለጦርነት ፡ ወደ ፡ ስልፍ ፡ ሲገባ ፡ የጦርነት ፡ ልብስ ፡ ይለብሳል ፤ ሲዋጋ ፡ ውሎ ፡ ድል ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ የለበሰውን ፡ የጦር ፡ ልብስ ፡ አውልቆ ፡ ከግምጃ ፡ ቤቱ ፡ ሰቅሎ ፡ ልብሰ ፡ መንግሥቱን ፡ ለብሶ ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ እንደሚቀመጠው፡ ያለ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ትስብእቱን ፡ ከመለኮቱ ፡ ጋራ ፡ በአባቱ ፡ ቀኝ ፡ አያስቀምጠውም ፡ አለ ።

አባ ፡ ዝክሪ ፡ ሲመልስ ፡ ነፍስ ፡ ርቀቷን ፡ ሳትለቅ ፡ ሥጋ ፡ ግዙፍ ፡ ውሱን ፡ መኾኑን ፡ ሳይለቅ ተዋሕደው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዲኾኑ ፡ መለኮት ፤ ምልአቱን ፡ ስፍሐቱን ፤ ርቀቱን ፡ ሳይለቅ ፡ ትስብእትም ፡ ግዘፉን ፤ ውሱንነቱን ፡ ሳይለቅ ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ፡ ባሕርይ፡ ኾኗል ፡ እንጂ፡ እንደ ፡ ልብስና ፡ እንደ ፡ ገላ ፡ አይደለም ፡ አለ ።

ሮማዊ ፡ መለኮት ፡ ከደረሰበት ፡ ኹሉ ፡ ይህ ፡ መዋቲ ፡ ትስብእት ፡ ደረሰ ፡ ትላለህን ፡ አለ ።

አባ ፡ ዝክሪ ፡ ሲመልስ ፡ እኔስ ፡ መለኮትና ፡ ትስብእት ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ ስለኾኑ ፡ መለኮት ፡ በሥጋ ፡ ውሱን ፡ ግዙፍ ፡ ኾነ ፤ ትስብእትም ፡ በመለኮት ፡ ምሉእ ፡ ስፉሕ ፡ ረቂቅ ፡ ኾነ ፡ እላለሁ ፤ ትስብእት ፡ ከመለኮት ፡ ተለይቶ ፡ በ፫ኛው ፡ ሰማይ ፡ እንዳልቀረ ፡ በየማን ፡ አብ ፡ በዘባነ ፡ ኪሩብ ፡ እንደተቀመጠም ፡ ሲያስረዳ ፡ አሚሃ፡ትሬእይዎ ፡ ለወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ እንዘ ፡ ይነብር ፡ በየማነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሏል ። በክበበ ፡ ትስብእት ፤ በግርማ ፡ መለኮት ፡ ዳግም ፡ እንዲመጣ ፡ ሲያስረዳም ፡ ወእመ ፡ ይመጽእ ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ በስብሐተ ፡ አቡሁ ፡ ወኵሎሙ ፡ መላእክቲሁ፡ ምስሌሁ ፡ ብሏል ፡ ይህ ፡ ንባብ ፡ በቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ መጻፉን ፡ ታምናለህ ፡ ትክዳለህ አለው ። ሮማዊ፤ መልስ ፡ አጥቶ ፡ ዝም ፡ አለ ።

## ፫ኛ ፡ ጥያቄ ።

ሮማዊ ፤ እኔ ፡ ክርስቶስን ፡ ፍጡር ፡ እለዋለሁ ፡ አለ ።

አባ ፡ ጳውሊ ፡ ሲመልስ ፡ ክርስቶስን ፡ ፍጡር ፡ የሚል ፡ ንባብ ፡ ከምን ፡ ታገኛለህ ፡ አለው ።

ሮማዊ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከኾነ ፡ ከሳምራዊት ፡ ውኃ ፡ እስኪለምን ፡ ድረስ ፡ ለምን ፡ ተጠማ ፡ ከላይ ፡ ያለው ፡ ሐኖስ ፤ ከታች ፡ ያለው ፡ ውቅያኖስ ፡ በማሃል ፡ እጁ ፡ ሲኾን ፡ አምላክ ፡ ይጠማልን ፡ አለ ።

አባ ፡ ጳውሊ ፡ ሲመልስ ፡ ፍጡር ፡ ከኾነ ፡ የእግዚአብሔርንስ ፡ ስጦታ ፡ ዐውቀሽ ፡ ቢኾን ፡ ይህ፡ ውኃ ፡ አጠጭኝ ፡ ብሎ ፡ የሚለምንሽ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተገንዝበሽ ፡ አንቺ ፡ የሕይወት ፡ ወኃን ፡ አጠጣኝ ፡ ብለሽ ፡ በለመንሺው ፡ ነበረ ፡ እርሱም ፡ በሰጠሽ ፡ ነበረ ፡ ከዚህ ፡ ወኃ ፡ የሚጠጣ ፡ ኹሉ ዳግመኛ ፡ ይጠማል ፤ እኔ ፡ ከምሰጠው ፡ ወኃ ፡ የሚጠጣ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ እኔ ፡ የምሰጠው ፡ ወኃ ፡ ለዘለ ዓለም ፡ ሕይወት ፡ ሊኾነው ፡ ከውስጡ ፡ ሲመነጭ ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፡ ዳግመኛ ፡ አይጠማም ፡ ለምን፡ አላት ፡ አለው ።

## ፬ኛ ፡ ጥያቄ ።

ሮማዊ ፡ አምላክ ፡ ከኾነ ፡ አልዓዛርን ፡ ወዴት ፡ ቀበራችሁት ፡ ብሎ ፡ ለምን ፡ ጠየቀ ፤ የተቀበ ረበትን ፡ ባላወቀውም ፡ ነበረን ። ኹለቱ ፡ ዕውራንስ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ይቅር ፡ በለን ፡ ባሉት ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ትሻላችሁ ፡ ብሎ ፡ ለምን ፡ ጠየቃቸው ፡ የሚሹትን ፡ ባላወቀውም ፡ ነበረን ፡ አለ ።

አባ ፡ ጳውሊ ፡ ሲመልስ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዳምን ፡ አይቴ ፡ ሀሎከ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ፡ ይላል ፡ ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፱ ። ሙሴንም ፡ ምንት ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ፡ ይላል ፡ ዘፀ ፡ ፬ ፡ ፪ ። እግዚአብ ሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መጠየቁ ፡ አዳም ፡ ያለበትን ፡ ቦታ ፡ አጥቶት ፡ ሙሴም፡ በእጁ ፡ ምን ፡ እንደያዘ አላውቀው ፡ ብሎ ፡ ይኾን ፡ አይደለም ፡ ይህም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ጥያቄ ፡ ነው ። ብዚያውስ ፡ ላይ ፡ ፍጡር ፡ ከኾነ ፡ አልዓዛር ፡ አልዓዛር ፡ ነዓ ፡ ፃእ ፡ አፍአ ፡ እመቃብር ፡ ብሎ ፡ ሊያሥነሣው ፡ እንደምን ፡ ቻለ ፡ በደረቅ ፡ ግንባርስ ፡ ዐይን ፡ ሊፈጥር ፡ እንደምን ፡ ቻለ ፡ አለው ።

ሮማዊ ፤ ይህን ፡ የመሳሰለስ ፡ ቅዱሳን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የኾኑ ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ ያደርጋሉ ፡ አለ ።

አባ ፡ ጳውሊ ሲመልስ ፡ ቅዱሳን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ተአምራት ፡ ቢያደርጉ ፡ የእርሱን ፡ ስም ፡ ጠርተው ፡ በስሙ ለኢየሱስ ፡ ናዝራዊ ፡ ተንሥእ ፡ ወሑር ፡ እያሉ ፡ ነው ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፫ ፡ ፮ ፡ ፱ ፡ ፴፭ ፡ ፲፮ ፡ ፲፰ ።

እርሱ ፡ ግን ፡ እኢዝዘከ ፡ ፃእ ፡ እምኔሁ ፡ እያለ ፡ በገዛ ፡ ሥልጣኑ ፡ ነወና ፡ ቅዱሳን ፡ ከሚያደር ጉት ፡ ተአምራት ፡ ጋራ ፡ ሲነጻጸር ፡ አይገባውም ፡ አለ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሮማዊ ፡ መልስ ፡ አጥቶ ፡ ዝም ፡ አለ ።

## ፭ኛ ፡ ጥያቄ ።

ስሙን ፡ ልዮን ፡ የሚሉት ፡ አንድ ፡ ሮማዊ ፡ ተነሥቶ ፡ ወልደ ፡ አብ፡ ከሰማየ፡ ሰማያት፡ ወርዶ፡ ሥጋ ፡ ማርያምን ፡ በለበሰ ፡ ጊዜ ፡ ሰይፍ ፡ በስገባው ፡ እንዲከተትና ፡ እንዲቀመጥ ፡ አደረበት ፡ እንጂ ፡ አልተዋሐደውም ፡ በ፴ ፡ ዘመኑ ፡ በዮርዳኖስ ፡ በተጠመቀ ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ሲቀመጥ ፡ መለኮቱ ፡ ከትስብእቱ ፡ ተዋሐደ ፤ የጸጋ ፡ አምላክ ፡ ሆነ ፡ መዋቲ ፡ ትስብእትም ፡ የማይሞት ኾነ ፡ ከ፴ ፡ ዘመን ፡ በፊት ፡ የጸጋ ፡ አምላክ ፡ ስላልሆነ ፡ አምላካዊ ፡ ሥራ ፡ አልሠራም ፤ ከተጠመቀ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ የጸጋ ፡ አምላክ ፡ ስለሆነ ፡ ወኃውን ፡ ወይን ፡ አደረገ ፡ ብዙ ፡ የአምላክነት ፡ ሥራ ፡ ሠራ ፡ አለ ።

እንደዚኹውም ፡ በንግድ ፡ ምክንያት ፡ መጥቶ ፡ እስክንድርያዊ ፡ መስሎ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚኖር አንድ ፡ ሰው ፡ ተነሥቶ ፡ እዓዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፡ እናንተ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ በለበሰ ፡ ጊዜ ፡ በማኅፀነ ፡ ማርያም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀብሎ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ሆነ ፡ ትላላችሁ ፡ በማ ኅፀን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ሲቀበል ፡ ያየው ፡ የለም ። ሮማውያን ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ፴ ፡ ዘመን ፡ በሰብ አዊ ፡ ግብር ፡ ኖሮ ፡ ሲጠመቅ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ እያየው ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ስለተቀመ ጠበት ፡ የጸጋ ፡ አምላክ ፡ ሆኖ ፡ የአምላክነት ፡ ሥራ ፡ ሠራ ፡ ይላሉና ፡ ከእስክንድርያ ፡ ሃይማኖት ፡ የሮማ ፡ ሃይማኖት ፡ ትሻላለች ፡ አለ ።

አባ ፡ ጳውሊ ፡ ሲመልስ ፤ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ ለእመቤታችን ፡ ሲያበሥራት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ይመጣል ፡ የአብም ፡ ኃይሉ ፡ ይጋርድሻል ፡ ካንቺ ፡ የሚወለደውም ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡ የልዑል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ይባላል ። ብሎ ፡ ፫ቱም ፡ አካላት ፡ በማኅፀነ ፡ ማርያም ፡ እንደ ፡

አደሩ ፡ ተናግሯል ። ማደራቸውም ፡ አብ ፡ ለአጽንዖ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለአንጽሖ ፡ ወልድ ፡ ለለቢስ ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ፫ቱ ፡ ኹሉ ፡ ለለቢሰ ፡ ሥጋ ፡ ያደሩ ፡ አይምሰልህ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መለኮት ፡ ርቀቱን ፡ ለቆ ፡ ሳይገዝፍ ፡ ሳይለወጥ ፡ ትስብእትም ፡ ግዘፉን ፡ ለቆ ፡ ሳይ ረቅ ፡ ሳይለወጥ ፡ እንደ ፡ ነፍስና ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ሆነ። ወልድ ፡ ለለቢሰ ፡ ሥጋ ፡ ማለት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አብ ፡ ለአጽንዖ ፡ ማለትም ፤ ሰማይ ፡ ምድር ፡ የማይወስ ኑትን ፡ ምሉእ ፡ ስፉሕ ፡ ረቂቅ ፡ መለኮትን ፡ እመቤታችን ፡ በጠባብ ፡ ማኅፀን ፡ እንድትችለው ፡ አጸናች ማለት ፡ ነው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለአንጽሖ ፡ ማለትም ፡ ትስብእትን ፡ ከአዳም ፡ መርገም ፡ አንጽቶ ፡ ቀድሶ ፡ ለተዋሕዶተ ፡ መለኮት ፡ የበቃ ፡ አደረገው ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህን ፡ በማኅፀን ፡ በረቂቅ ፡ ምሥ ጢር ፡ የሠሩትን ፡ አምላካዊ ፡ ሥራ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ወልድ ፡ ባጭር ፡ ቁመት ፡ በጠባብ ፡ ደረት ፡ ተወስኖ፡ ሲጠመቅ ፡ በመታየት ፤ አብ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ በማሰማት ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በርግብ ፡ አምሳል ፡ ወርዶ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ አብ ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የመሰ ከረለት ፡ ወልድ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በጣት ፡ ጠቅሶ ፡ እንደ ፡ ማሳየት ፡ በመመስከሩ ፡ ገልጸውታል ፡ እንጂ ፡ እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ ፴ ፡ ዘመን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተለይቶት ፡ ኖሮ ፡ በዮርዳኖስ ፡ አደረበት ፡ ማለት ፡ አይደለም ፡ አለ ። ያ ፡ ሮማዊ ፡ መልስ ፡ አጥቶ ፡ ዝም ፡ አለ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ገላውዴዎስ ፡ አባ ፡ ዝክሪንና ፡ አባ ፡ ጳውሊን ፡ እኔ ፡ የክርስቶስ ፡ ባሪያ ፡ ሃይማኖቴ ፡ እንደ ፡ ሃይማኖታችሁ ፡ ኦርቶዶክስ ፤ እስክንድርያዊ ፡ ነው ፤ ይህንንም ፡ እናንተ ፡ ታውቁ ልኛላችሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እኛ ፡ የሕክምናና ፡ የተግባረ ፡ እድ ፡ ትምህርት ፡ የለንም ፡ ሮማውያን ፡ ብዙ ፡ ጥበብ ፡ ያውቃሉና ፡ ይህን ፡ ጥበባቸውን፡ እስኪያስተምሩን ፡ ድረስ ፡ በሀገራችን ፡ እንዲቆዩ ፡ ፈቃዳ ችሁ ፡ ይኹን ፡ ሲል ፡ ለመናቸው ።

አባ ፡ ዝክሪ ፡ የተባለው ፡ መነኩሴ ፡ ተነሥቶ ፡ እናንተ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ እሊህ ፡ ሮማውያን በሀገራችን ፡ ይቀመጡ ፡ ካላችሁ ፡ ወደፊት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ የሚያደርስባትን ፡ ነገር ፡ ልንገራችሁ ፡ እኒህ ፡ ሰዎች ፡ ከእኅቶቻችን ፡ ከልጆቻችን ፡ ይወልዳሉ ፡ እኒያ ፡ ልጆች ፡ በድብቅ ፡ ያባቶቻቸውን ፡ የካቶሊካውያንን ፡ ትምህርት ፡ ይማራሉ ፡ እኛ ፡ ወገኖቻችን ፡ መስለውን ፡ ቅስና ፡ ዲቁና ፡ ስንሾማቸው፡ የመምህርነት ፡ ማዕርግ ፡ ስንሰጣቸው ፡ ውስጥ ፡ ውስጡን ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ እያስተማሩ ፡ ሃይማኖታችንን ፡ ይለውጧታል ፡ ይህም ፡ የተናገርኩት ፡ ነገር ፡ አይቀርም ፡ ፫ ፡ ነገሥታት ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡ ፬ኛው ፡ ንጉሥ ፡ ከወደ ፡ አረማውያን ፡ ሀገር ፡ መጥቶ ፡ ይነግሣል፡ በርሱ ፡ ጊዜ፡ ይፈጸማል ሲል ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ካ፺ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ዐ፺ ፡ ፋሲል ፤ ካ፺ ፡ ፋሲል ፡ ዐ፺ ፡ ሚናስ ካ፺ ፡ ሚናስ ፡ ዐ፺ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ካ፺ ፡ ሠርፀ ፡ ድንግል ፡ ዐ፺ ፡ ያዕቆብ ፡ ካ፺ ፡ ያዕቆብ ፡ ዐ፺ ፡ ሱስ ንዮስ ፡ ዐ፺ ፡ ሱስንዮስ ፡ ከጋላ ፡ ሀገር ፡ መጥተው ፡ ነገሡ ። በ፬ኛው ፡ ንጉሥ ፡ በዓ፺ ፡ ሱስንዮስ ፡ ጊዜ የአባ ፡ ዝክሪ ፡ ትንቢት ፡ ተፈጸመ ። በዓ፺ ፡ ሱስንዮስ ፡ ጊዜ ፡ የተደረገውን ፡ ታሪክ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በሚ ገኘው ፡ በም ፡ ፮ ፡ በክፍል ፡ ፪ ፡ በቍ ፡ ፬ ፡ በሰፊው ፡ የጻፍነው ፡ ስለኾነ ፡ ከዚህ ፡ ሊጻፍ ፡ አላስፈለገም ።

እነሆ ፡ ፭ኛ ፡ ልዮንና ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ የተለያዩበትን ፡ ታሪክ ፡ ፪ኛ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ወደ ፡ ኢት ዮጵያ ፡ ሲገቡ ፡ የሞከሩበትንና፡ ኢትዮጵያውያንም ፡ ተከራክረው ፡ የመለሱበትን ፡ ታሪክ ፡ አባቶቻ ችን ፡ ካቆዩን ፡ የታሪክ ፡ መጻሕፍት ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ጽፌላችኋለሁ ። ይህም ፡ ከአባቶቻችን ፡ የተ ገኘው ፡ ቅርስ ፡ ጠቃሚ ፡ መኾኑን ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በትውልድ ፡ የሚደርሱ ፡ የሚታዩና ፡ የሚሰሙ ፡ ነገሮች ፡ ኹሉ ፡ ከሞና ፡ ትምህርት ፡ የሚቆጠሩ ፡ ናቸው ። ብለው ፡ አስረድተ ውናል ፡ ሐምሌ ፡ ፲፮ ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ቀ - ኃ - ሥ ።

ዶክተር ፡ አባ ፡ አየለም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የተደረገውን ፡ እውነተኛውን ታሪክ ፡ አያውቁትም ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ ታሪክ ፡ የሚያስነቅፍና ፡ የሚያስለውጥ ፡ ያቀረቡት ፡ መረጃ ፡ የለም ።

ይህን ፡ ታሪክ ፡ የሚያስለውጥ ፡ ታሪክ ፡ ቢኖራቸው ፡ ኖሮ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፋቸው ፡ ውስጥ ፡ ሳይጠቅሱት ፡ ባልቀሩም ፡ ነበረ ።

ትውልድ ፡ ያልፋል ፡ አገርና ፡ ታሪክ ፡ አያልፍም ፡ አገርና ፡ ታሪክ ፡ የሚታወቅም ፡ በትምህርት ነው ፡ ያለትምህርት ፡ የሚገኝ ፡ የዕለት ፡ ጥቅም ፡ ግን ፡ ተስፋ ፡ የሌለው ፡ ደካማ ፡ ነው ፡ መስከረም ፡ ፳፬ ፡ ፲፱፻፴፱ ፡ ዓ/ም ፡ ቀ - ኃ - ሥ -

እውነተኛ ፡ ትምህርት ፡ ጠቃሚነቱ ፡ ለራስም ፡ ለሀገርም ፡ ነው ፡ ያገርን ፡ ልማድ ፡ እያስንቅም ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ እያርቅም ፡ በባሕርይ ፡ ጠማምነት ፡ የተሸፈነ ፡ ትምህርት ፡ ግን ፡ ጎጂ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡ መጋቢት ፡ ፳፩ ፡ ፲፱፻፵ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቀ-ኃ-ሥ ። የሚለውን ፡ ንጉሣዊ ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ ተመርጉዘን ፡ ከባቶቻችን ፡ ያገኘነውን ፡ ባህል ፡ ንቆ ፡ ከመጣል ፡ እንጠበቅ ።

«በአእምሮ ፡ ጠንክሩ ፤ በሥራ ፡ ጠንክሩ ፤ በሃይማኖት ፡ ጠንክሩ ፤ የመጨረሻውን ፡ ዕድልና ፡ የድል ፡ አክሊል ፡ ትወርሳላችሁ ።» ሐምሌ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ/ም ። የሚለውን ፡ ንጉሣዊ ፡ መሪ ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ ከባቶቻችን ፡ በወረስናት ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንተን ፡ ተገኝተን ፡ የመጨረሻውን ፡ የድል ፡ አክሊል ፡ ለመቀዳጀት ፡ ያብቃን ፡ አሜን ።

# መግቢያ

መግቢያ ፡ ማለት ፡ መሪ ፡ ምልክት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ ወደ ማያውቀው ፡ ሀገር ፡ ልክ የሚሰድ ፡ ሰው ፤ ቢያገኝ ፡ አንድ ፡ መሪ ፡ ጨምሮ ፡ ቢያጣ ፡ የመንገዱን ፡ አኳኋንና ፡ የሀገሩን ፡ አቀማመጥ ፡ የሚደርስበትንም ፡ ቤት ፡ በቂ ፡ ምልክት ፡ አስጠንቶ ፡ ወይም ፡ የዚህኑ ፡ ካርታ ፡ ሰጥቶ ፡ ቢሰደው ፡ መላክተኛው ፡ ያለችግር ፡ ካሰበው ፡ ቦታ ፡ ይደርሳል ።

እንግዳ ፡ ድርሰትም ፡ የሚጽፍ ፡ ሰው ፡ ተመልካቾች ፡ ከመካከሉ ፡ ሲገቡ ፡ የመጽሐፉን፡አኳኋን ለማወቅ ፡ እንዳይቸገሩ ፡ መግቢያ ፡ በተባለው ፡ አርእስት ፡ ላይ ፡ የመጽሐፉን ፡ ጠባይ ፡ ያጸጻፉን፡ ድርጅት ፡ ዘርዝሮ ፡ ማሳየት ፡ ይገባል ፡ እንዲህ ፡ የኾነ ፡ እንደሆነ ፡ ተመልካቾች ፡ ያላንድ ፡ ችግር ፡ የመጽሐፉን ፡ ጠባይ ፡ ሊረዱት ፡ ይችላሉ ።

እኔም ፡ ይህን ፡ በመገንዘብ ፡ ተመልካቾች ፡ ያለአንድ ፡ ችግር ፡ ከግቡ ፡ እንዲደርሱልኝ ፡ በማለት ፡ የዚህን ፡ መድሐፍ ፡ ያጸጻፉን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በዚህ ፡ መግቢያ ፡ በተ ባለው ፡ አንቀጽ ፡ አንድ ባንድ ፡ ዘርዝሬ ፡ አሳያለሁ ።

፩ኛ/ ፤ የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ አካሔድና ፡ ጠቅላላ ፡ ድርጅቱ ፡ የፊተኛው ፡ ደራሲ ፡ ዶክተር ፡ አባ አየለ ፤ ለጻፉት ፡ ጽሑፍ ፡ እውነቱን ፡ እውነት ፡ ሐሰቱን ፡ ሐሰት ፡ እያሉ ፡ መልስ ፡ መስጠት፡ብቻ፡ ነው ።

፪ኛ ፤ ተመልካቾች ፡ መልሱ ፡ ልክ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ልክ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ለማመዛዘን ፡ እንዲመቻቸው ፡ አስቀድሜ ፡ የዶክተር ፡ አባ ፡ አየለን ፡ ጽሑፍ ፡ በሙሉ ፡ ጽፌ ፡ የኔን ፡ መልስ ፡ አስከትላለሁ ።

፫ኛ ፤ የዶክተር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ ንግግርና ፡ መልሱ ፡ ባንድ ፡ መልክ ፡ የታተመ፡ እንደኾነ፡ ንባቡ ፡ ተሰባጥሮ ፡ ተመልካቾችን ፡ እንዳያስቸግር ፡ በማለት ፡ የፊተኛውን ፡ ድርሰት ፡ በረቂቅ ፡ መልሱን ፡ በጉልህ ፡ አሳትሜዋለሁ ።

፬ኛ ፤ ዶክተር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ ለመጽሐፉ ፡ ከምዕራፍ ፡ በቀር ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ስላልሰጡት ፡ ቍጥር የለሽ ፡ በመሆኑ ፡ ለመመልከት ፡ ወይም ፡ ከውስጡ ፡ ለመጥቀስ ፡ አይመችም ፡ ነበረ ። እኔ ፡ ግን ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ ስለሰጠሁት ፡ ለመመልከትም ፡ ለመጥቀስም ፡ ቢኾን ፡ የተሻለ መልክ ፡ አግኝቷል ። ተመልካቾችን ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ መጽሐፉን ፡ እየመረመራችሁ ፡ እንድታመዛዝኑት ፡ አሳስባችኋለሁ ።

ዶክተር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ በመጽሐፋቸው ፡ ልባስ ፡ የሚገኘውን ፡ የመጽሐፉን ፡ መግቢያ ፡ ጽሑፍ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ የምታምነው ፡ ትምርት ፡ ብለውታል ።

መግቢያውን ፡ ሳይመረምሩ ፡ ከውስጠ ፡ ምሥጢሩ ፡ ልግባ ፡ ማለት ፡ ሣንቃ ፡ ሳይከፈት ፡ ከጓዳ ፡ ልገኝ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ የሚቈጠር ፡ ስለኾነ ፡ አስቀድመን ፡ ይህንን ፡ በመጽሐፉ ፡ መግቢያ ፡ ላይ፡ የሚገኘውን ፡ ቃል ፡ መመርመር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ የሚለው ፡ አነጋገር ፡ ካቶሊካውያን ፡ ክልኤ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ ስለኾኑ እንደኛ ፡ አነጋገር ፡ ሳይሆን ፡ እንደ ፡ እነርሱ ፡ አነጋገር ፡ መንገድ ፡ ይገኝለት ፡ ይኾናል ። አካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ የሚለው ፡ አነጋገር ፡ ግን ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ ተዋሕዶ ፡ ማለት ፡ ኹለት ፡ ወይም ፡ ከ፪ ፡ በላይ ፡ ብዛት ፡ ያላቸው ፡ ነገሮች ፡ ምንታዌን ፡ ብዛትን ፡ አጥፍተው ፡ አንድ መኾናቸውን ፡ የሚያሳይ ፡ ንግግር ፡ ነው ። እንደ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አነጋገር ፡ ከኹለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኾነ ፡ እንዳይባል ፡ ካቶሊካውያን ፡ አካል ፡ ለቃል ፡ እንጂ ፡ ለትስብእት ፡ የለውም ፡ ባዮች ፡ ናቸው ፤ ለትስብእት ፡ ያለው ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ይላሉ ።

አካለ ፡ ቃልና ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ተዋሐዱ ፡ እንዳይባል ፡ ባሕርይ ፡ በፍጹም ፡ አልተዋሐደም ፡ ባዮች ፡ ናቸው ። እንግዲህ ፡ ይህ ፡ አካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ የሚለው ፡ አነጋገር ፡ ማንነና ፡ ማንን ፡ ወይስ ፡ ምንንና ፡ ምንን ፡ አዋሐደ ፡ ይባላል ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ።

ነገሩ ፡ ተመርምሮ ፡ የሚሰጠው ፡ ውጤት ፡ ይህ ፡ ሲኾን ፡ ኢትዮጵያ ፡ በማትናገረው ፡ አነጋገር ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ የምታምነው ፡ ትምህርት ፡ ብሎ ፡ መናገር ፡ ሐሰትንና ድፍረትን ፡ የተመላ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

# ማቅረቢያ ።

## ከካርዲናል ፡ ኤውጀንዮስ ፡ የተሰጠ ።

### ካርዲናል ፡ ኤውጀንዮስ ፡ ቲሰራን ፡ ለሰጡት ፡ ማቅረቢያ ፡ መልስ ፡

፩/ ከመ ፡ ይኩኑ ፡ ፩ደ ፡ ዙሉሙ ፡ ዮሐ ፡ ፲፯ ፡ ፳፩ ፡ ሲል ፡ ክርስቶስ ፡ የተመኘው ፡ የክርስቲያኖች ፡ ሁሉ ፡ አንድነት ፡ እንዲፈጸም ፡ ለማድረግ ፡ የሚረዳ ፡ ማናቸውንም ፡ ሥራ ፡ በተቻላት ፡ መጠን ፡ ማደፋፈርና ፡ መደገፍ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዋና ፡ ተግባሯ ፡ መኾኑን ፡ ማንም ፡ አይስተውም ፡ ይህም ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈው ፡ ይህን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አሳብና ፡ ዓላማ ፡ በመከተል ፡ ስለኾነ ከ፳ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ መጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በጣልያንኛ ፡ ታትሞ ፡ ሲወጣ ፡ ማቅረቢያ ፡ እንዳደረግን በት ፡ እንደገና፡ባማርኛ፡ቋንቋ ታትሞ ፡ ሲወጣ ፡ ለሕዝብ ፡ የምናቀርበው ፡ ጥልቅ ፡ የኾነ ፡ ደስታ ፡ እየተሰማን፤ ነው ፡ ይኸውም ፡ ያሁን ፡ ማቅረቢያ ፡ በመጽሐፉ ፡ ውስጥ ፡ ሊተገለጸው ፡ አሳብ ፡ ማበረታቻ ፡ እንዲኾን ፡ ተብሎ ፡ የተደረገ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

፪/ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እርስ ፡ በርሷ ፡ ብትለያይ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እርስ ፡ በእርስዋ ፡ የምትለያይ ፡ መንግሥት ፡ ትጠፋለች ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ምሳሌ ፡ ይደርስባት ፡ ይኾን ፡ ከሚል ፡ ስጋት ፡ ላይ ፡ ይጥላል ፡ እንጂ ፡ ጠቃሚ ፡ አለመኾኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ ጥንቷ ፡ አንድ ፡ እንድትኾን ፡ ማሰብ ፡ ለዚህም ፡ አሳቢ ፡ ሲገኝ ፡ ማደፋፈርና ፡ ማበረታታት ፡ የተቀደሰ ፡ ተግባር ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ማድረግ ፡ የሚገባ ፡ ያ ፡ የሚያደፋፍሩት ፡ የሚያበረታቱት ፡ ሰው ፡ ኹለቱንም ፡ ወገኖች ፡ በሚዛናዊ ፡ ዐይን ፡ ተመልክቶ ፡ ኹለቱ ፡ የሚስማሙበትን ፡ መንገድ ፡ ይዞ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ አሁኑ ፡ ባለው ፡ መንገድ ፡ የተመሠረተውን ፡ አይደለም ። አሁን ፡ አባ ፡ አየለ ፡ ያቀረቡት ፡ ሐሳብ ፡በሁሉታችንም፡ወገን ፡ ቢኾን ፡ አባቶቻችን ፤ ተነጋግረውበት ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ ማስገኘቱ ፡ ቀርቶ ፡ ደም ፡ እስከመፋሰስ ፡ ደርሰው ፡ የተለያዩበትን ፡ ሐሳብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስምምነትን ፡ የሚፈጥር ፡ መልክ ፡ የያዘ ፡ ሌላ ፡ ሐሳብ ፡ አይደለም ። ይህም ፡ ሐሳብ ፡ ትክ ፡ ብሎ ፡ ሲመለከቱት ፡ እኔ ፡ ካባቶቼ ፡ ካቶሊካውያን ፡ መልእክተኞች ፡ እበልጣለሁ ፤ እናንተም ፡ ካባቶቻችሁ ፡ ታንሳላችሁና ፡ አባቶቻችሁ ፡ እንቀበለውም ፡ ብለው ፡ ደማቸውን ፡ ያፈሰሱበትን ፡ ባህል ፡ ተቀበሉኝ ፡ ማለታቸው ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ሐሳብ ፡ ያቀረበውን ፡ ሰው ፡ ይህማ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ቀርቦ ፡ ዋጋ ፡ ሳያገኝ ፡ የቀረ ፡ ነገር ፡ አይደለምን ፡ ቢቻልህ ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ ፈልግ ፡ እንጂ ፡ ይህስ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ተሞክሮ ፡ ሳይሆን ፡ ቀርቷል ፡ ተው ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ጠንክር ፡ ግፋ ፤ እያሉ ፡ ማበረታታት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ገደል ፡ ወድቄ ፤ ባሕር ፡ ጠልቄ ፡ ልሙት ፡ ቢል ፡ ጠንክር ፡ ግፋ ፤ መልካም ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እንደማበረታታት ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ፡

፫/አባ ፡ አየለ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘዓቢይ ፡ ዓዲ ፡ የደረሱት ፡ መጽሐፍ ፡ ተመሳሳይ ፡ የሌላቸው ፡ መሬ ፡ የኾኑትና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሀገራቸው ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ ለማሠልጠን ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ የሚለፉት ፡ ገናናው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ተመልክተው ፡ ያመሰገኑት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተተርጕሞ ፡ እንዲወጣ ፡ ምክራቸውንና ፡ ማበረታታቸውን ፡ ሰጥተው ፡ ለማተሚያ ፡ የገንዘብ ፡ ርዳታ ፡ ሰጥተው ፡ የደገፉት ፡ ሥራ ፡ መኾኑን ፡ በማወቄ ፡ ይህን ፡ ማቅረቢያ ፡ በንጽፍለት ፡ ደስታችን ፡ ወሰን ፡ የለውም ፡ ብለዋል ።

፫ ፤ የገንዘብ ፡ ርዳታ ፡ በመስጠት ፡ የደገፉት ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ ያሉትን ፡ የመጽሐፉ ፡ ባለቤት ፡ አባ ፡ አየለ ፡ በመቅድሙ ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ልግስና ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ አሳትሜ ፡ ለማውጣት ፡ በገንዘብ ፡ ስላገዙኝ ፡ በታላቅ ፡ ትሕትና ፡ አመሰግናቸዋለሁ ፡ ብለው ፡ ስለገለጡልኝ ፤ እኔም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ የገንዘብ ፡ ችግር ፡ ሲደርስበት ፡ የገንዘብ ፡ ችሮታ ፡ ሕዝብን ፡ ለሚያስተዳድሩ ፡ ነገሥታት ፡ ተገቢ ፡ ተግባራቸው ፡ መኾኑን ፡ በሰፊው ፡ ዘርዝሬ ፡ ጽፌአለሁ ፡ አባ ፡ አየለ ፡ በጸፉት ፡ መቅድም ፡ በቍ ፡ ፲፬ ፡ ይመልከቱ ። ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ተመልክተው ፡ ያመሰገኑት ፡ ብቻ ፡ ይኾን ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተተርጕሞ ፡ እንዲወጣ ፡ ምክራቸውንና ፡ ማበረታታቸውን ፡ ሰጥተዋል ፡ ያሉትን ፡ ግን ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፤ ሳይቀርቡም ፡ ቢኾን ፡ ርዳታ ፡ የተደረገላቸው ፡ አባ ፡ አየለ ፡ ያልሰሙትን ፡ ያልተናገሩትን ፡ ነገር ፡ እርስዎ ፡ የት ፡ ኾነው ፡ ሰሙት ፡ ብለን ፡ እንቀበልዎ ፡ በእውነቱ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሲያመዛዝኑት ፡ ለነገ ፡ ጸሐፊ ፡ መንገድ ፡ ለመጥረግ ፡ የታሰበ ፡ ዘዴ ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ስሜት ፡ የሌለው ፡ ስለሆነ ፡ ማንም ፡ እውነት ፡ ብሎ ፡ የማይቀበለው ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ።

፬/ ይህ ፡ ክቡር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ያደረሱት ፡ መጽሐፍ ፡ ከረጅም ፡ ዘመናት ፡ ጀምሮ ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ሮማን ፡ ለያይቶ ፡ የሚገኘውን ፡ ዋና ፡ ክርክር ፡ ለማቆም ፡ በጣም ፡ እንደሚረዳ ፡ ስለማያጠራጥር ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ አሳብ ፡ ማበረታታትና ፡ ርዳታ ፡ ሊያገኝ ፡ በእውነት ፡ የሚገባው ፡ ነው ብለዋል

፫ / ጥንቱንም ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ሮማን ፡ የለያያቸው ፡ ሮማ ፡ በአንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ ሠረጸ ፡ ባይ ፡ ስትኾን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይኸን ፡ የመሰለውን ፡ ባህል ፡ ከመጽሐፍ ፡ ያልተገኘ ፡ ነውና ፡ አልቀበለውም ፡ በማለቷ ፡ ነው ። አሁን ፡ አባ ፡ አየለ ፡ የጻፉትም ፡ መጽሐፍ ፡ ያኑኑ ፡ በንጉሤ ፡ ዘድንግልና ፡ በንጉሤ ፡ ሱስንዮስ ፡ ዘመን ፡ የካቶሊክ ፡ መልክተኞች ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን ፡ በቀል ፡ የሚያስታውሱትን ፡ መጻሕፍት ፡ እየጠቀሱ ፡ እናንተ ፡ የምትሉትን ፡ ባታውቁት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ ናችሁ ፤ ንጉሦቻችሁ ፡ ዓፄ ፡ ካሌብም ፡

ኹለት ፣ ባሕርይ ፣ ባይ ፣ ነበረ ፣ እያሉ ፣ ስድብን ፣ የተመላ ፣ ውሸት ፣ ከመናገር ፣ በቀር ፣ ከቅዱሳት ፣ መጻሕፍት ፣ ጠቅሰው ፣ ክርስቶስ ፣ ባንድ ፣ አካል ፣ ኹለት ፣ ባሕርይ ፣ መኾኑን ፣ መንፈስ ፣ ቅዱስ ፣ ከወልድ ፣ መሥረጹን ፣ አስረድተዋልን ፣ አላስረዱም ። ይህ ፣ እያያዝ ፣ ያለፈውን ፣ በቃል ፣ እያስታወሰ ፣ ክርክሩ ፣ እንዲቀጥል ፣ ከማድረግ ፣ በቀር ፣ ክርክሩን ፣ ለማቆም ፣ የሚረዳበት ፣ መንገድ ፣ ምንድን ፣ ነው ፤ እስኪ ፣ ያስረዱኝ ፤ እንደኔ ፣ አስተያየትስ ፣ ክርክሩን ፣ ለመቀጠል ፣ ካልሆነ ፣ በቀር ፣ክርክሩን ፣ ለማቆም ፣ ምንም ፣ አይጠቅምም ፣

፱/ ደራሲው ፣ በመጽሐፉ ፣ መጀመሪያ ፣ ክፍል ፣ አስደናቂ ፣ ስለኾነው ፣ ስለኢትዮጵያ ፣ ሃይማኖት ፣ ታሪክና ፣ ኢትዮጵያን ከመንበረ ፣ ጴጥሮስ ፣ ስለለይዋት ፣ አባዛዎች ፣ ምክንያቶች ፣ አትሐተው ፣ ይናገራሉ ፣
ብለዋል ፡

፱ / እናንተ ፤ ቁም ፣ ነገር ፣ አድርጋችሁ ፣ የያዛችሁት ፣ የጴጥሮስን ፣ ወንበር ፣ነው ፣ እኛ ፣ ግን ፣ ቁም ፣ ነገር ፣ አድርገን ፣ የያዝነው ፣ የጴጥሮስን ፣ ትምህርት ፣ ነው ፤ ስለዚህ ፣ ጴጥሮስ ፣ ካስተማረው ፣ ትምህርት ፣ ወጥተን ፤ አንገኝ ፣ እንጂ ፣ ከወንበሩ ፣ በመለየታችን ፣ አናዝንም ። የኢትዮጵያን ፣ ሃይማኖት ፣ ታሪክም ፣ በጌታችን ፣ በኢየሱስ ፣ ክርስቶስ ፣ ቃል ፣ ንግሥተ ፣ አዜብ ፣ ትትነሣእ ፣ አመ ፣ ዕለተ ፣ ፍትሕ ፣ ወትትፌትሐ ፣ ለዛቲ ፣ ትውልድ ፣ ተብሎ ፣ የተነገረላት ፣ ስለኾነ ፣ በአባ ፣ እየለ ፣ቃል ፣ ተነገረ ፣ ብለን ፣ ከምስጋና ፣ የምናገባው ፣ አይደለንም ።

፲/ ፀሐፊው ፣ ክፍል ፣ የኢትዮጵያ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ስለክርስቶስ ፣ ባሕርያት ፣ የምታምነውን ፣ ትምህርት ፣ የኬልቄዶን ፣ ጉባኤ ፣ ካስተማሩት ፣ ትምህርት ፣ ጋራ ፣ በማንፃቀ ፣ አመዛዝነው ፣ ካነጻጸሩት ፣ በኋላ ፣ የኹለቱም ፣ ባሀል ፣ በመሠረቱ ፣ ትክክል መኾኑን ፣ ያስረዳሉ ፣
ብለዋል ።

፲ / የኹለቱም ፣ ወገኖች ፣ ትምህርት ፣ ቃል ፣ ሥጋ ፣ ከነን ፣ ያልለቀቀ ፣ ስለ ፣ ኾነ ፣ በመሠረቱ ፣ አንድ ፣ መኾኑ ፣ አይካድም ፣ በኬልቄዶን ፣ ጉባኤ ፣ የተወሰነው ፣ ውሳኔ ፣ ግን ፣ አንድ ፣ ክርስቶስን ከኹለት ፣ ከፍሎ ፣ ኹለት ፣ ባሕርይ ፣ ኹለት ፣ ፈቃድ ፣ ከማለቱ ፣ በላይ ፤ ባሕርየ ፣ ትስብእቱ ፣ ለባሕርየ ፣ መለኮቱ ፣ መቸም ፣ መቼ ፣ ሲገዛ ፣ ይኖራል ፣ የሚል ፣ ስለኾነ ፣ ከኢትዮጵያ ፣ ባሀል ፣ ጋራ ፣ ሊነጻጸር ፣ በፍጹም ፣ አይችልም ። ከአባ ፣ እየለ ፣ መጽ ፣ ገጽ ፣ ፻፲፭ ፣ እይ ።

፲፩/ ቀጥለውም ፣ በላንዳንድ ፣ ትንንሽ ፣ ጉዳዮች ፣ ያለ ፣ ልዩነትን ፤ አስቀርተው ፣ እንደገና ፣ አንድነትን ፣ ለማስገኘት በበለጠ ፣ የሚረዱ ፣ ዘዴዎችን ፣ ያመለክታሉ ፣
ብለዋል ።

፲፩ / ከአንዳንድ ፣ ትንንሽ ፣ ጉዳዮች ፣ ያሏቸው ፣ የቶች ፣ ናቸው ፤ መንፈስ ፣ ቅዱስ ፣ ከወልድ ፣ ሠረጸ ፣ ማለትን ፣ ነውን ፤ ወይስ ፣ ጌታችን ፣ ኢየሱስ ፣ ክርስቶስ ፣ ለኹሉ ፣ አስተካክሎ ፣ የሰጠውን ፣ ሥጋውን ፣ ደሙን ፣ አበላልጦ ፣ ሕዝባዊ ፣ ሥጋውን ፣ ብቻ ፣ ይቀበል ፣ እንጂ ፣ ደሙ ፣ አይገባውም ፤ ካህናት ፣ ግን ፣ ሥጋውንም ፣ ደሙንም ፣ ይቀበሉ ፣ ብሎ ፣ መበየን ፣ ነው ፤ በዚያውስ ፣ ላይ ፣ ምነው ፣ ጌታችን ፣ ኢየሱስ ፣ ክርስቶስ ፣ ዘኬ ፣ ፈትሐ ፣ አሐተ ፣ እምእላ ፣ ትእዛዛት ፣ እንተ ፣ ተሐጽጽ ፤ ወይሜህር ፣ ከመዝ ፣ ለሰብእ ፣ ሕጹጸ ፣ ይከውን ፣ በመንግሥተ ፣ ሰማያት ፣ ወዘሰ ፣ ይሜህር ፣ ወይገብር ፣ ውእቱ ፣ ዐቢየ ፣ ይከውን ፣ በመንግሥተ ፣ ሰማያት ፣ ማቴ ፣ ፭ ፣ ፲፱ ።

ከኢህ ፣ ትእዛዞች ፣ አንዲቱ ፣ ታንሳለች ፣ ብሎ ፣ የሚያስተምር ፣ በመንግሥተ ፣ ሰማያት ፣ ያነሰ ፣ ይኾናል ፣ ከኢህ ፣ ትእዛዛት ፣ አንዲቱም ፣ አታንስ ፣ ብሎ ፣ ለራሱ ፣ የሚጠብቅ ፣ ለሌላውም ፣ የሚያስተምር ፣ ግን ፣ በመንግሥተ ፣ ሰማያት ፣ ታላቅ ፣ ይኾናል ፣ ያለው ፣ ቃል ፣ ተሠረዘን ፣ አልተሠረዘም ፣ ስለዚህ ፣ ክሕግ ፣ ውስጥ ፣ ይህ ፣ ትንሽ ፣ ነው ፣ ተብሎ ፣ የሚታለፍ ፣ የለም ።

፲፪/ የጴጥሮስ ፣ ተከታይ ፣ የኾኑት ፣ የሮም ፣ ርእሰ ፣ ሊቃነ ፣ ጳጳሳት ፣ ክርስቲያኖቻችን ፣ ኹሉ ፣ የሚያስተባብር ፣ ጠቅላይ ፣ ጉባኤ ፣ በቅርብ ፣ ጊዜ ፣ እንዲደረግ ፣ መታቀዱን ፣ ባስታወቁበት ፣ ባሁኑ ፣ ጊዜ ፣ አባ ፣ አየለ ፣ ተክለ ፣ ሃይማኖት ፣ የደረሱት መጽሐፍ ፣ ወደ ፣ አማርኛ ፣ ተተርጉሞ ፣ ታትሞ ፣ ሲወጣ ፣ በጣም ፣ የተመቸ ፣ ኾኖ ፣ ይታየናል ፣
ብለዋል ።

፲፪ / ይህ ፣ ወደፊት ፣ የሚታሰብ ፣ ምኞት ፣ ስለኾነ ፣ ሲደረግ ፣ ከማየት ፣ በቀር ፣ አሁን ፣ መልስ ፣ ሊሰጥበት ፣ አይገባም ፣ እግዚአብሔር ፣ ለማየት ፣ ቢያበቃን ፣ እናያለን ።

፲፫/ የካቶሊክ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ ኢትዮጵያን ፣ ኹልጊዜ ፣ በመልካም ፣ ዓይንና ፣ በል ፣ ፍቅር ፣ እንደተመለከተቻት ናት ፣ መቸውንም ፣ አንድነት ፣ እንዲገኝ ፣ ከመመኘት ፣ አቋርጣ ፣ አታውቅም ፣
ብለዋል ።

፲፫ / ሮማ ፣ ባዬ ፣ ዘድንግል ፣ ጊዜ ፣ ሰባኪዎቿን ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ልካ ፣ ንጉሡን ፣ ከሕዝብ ፣ አለያይታ ፣ ሰባኪዎቿን ፣ከንጉሡ ፣ ጋራ ፣ አስልፋ ፣ ሕዝቡንና ፣ ንጉሡን ፣ አዋግታ ፣ ንጉሡን ፣ አስገድላለች ።ባዬ፡ሱስንዮስም ፣ጊዜ ፣ ንጉሡን ፣ ከሕዝቡ ፣ አለያይታ ፣ የብዙ ፣ ክርስቲያን ፣ ደም ፣ አስፈ

ስላለች ። አሁንም ፡ በቅርቡ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወረራ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምትደበደብበትን ፡ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ መርዝ ፡ ባርካ ፡ መርቃ ፡ ሰዳ ፡ እንዳስደበደበቻት ፡ ታሪክ ፡ ይነግረናል ፤ ይህን ፡ ክፋትና ፡ ክውሰታ ፡ ቁጠሩትን ፤ በመልካም ፡ ዐይንና ፡ በልዩ ፡ ፍቅር ፡ ባትመለከታት ፡ በጠብ ፡ ዐይን ፡ ብታያት ፡ ምን ፡ ልታደርጋት ፡ ትችል ፡ ኖሯል ። አንድነት ፡ እንዲገኝ ፡ ትመኛለች ፡ የሚሉትስ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከመንበረ ፡ እስክንድርያ ፡ ለይቼ ፡ ከእግሬ ፡ በታች ፡ አድርጊያት ፡ እስክንድርያን ፡ ብቻዋን ፡ ሳላስቀራት ፡ አስቀርቻት ፡ እያለች ፡ የምትመኘውን ፡ ምኞት ፡ ለመፈጸም ፡ ብቻ ፡ አይደለምን ። ስሕን ፡ ወንጌል ፡ የምትቀረቀር ፡ ከኾነች ፡ ባጠገቧ ፡ አላህ ፡ አንድ ፡ ነው፡ አይወለድም ፡ አይወልድም ፡ የሚሉ ፡ እስላሞችና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሃይማኖት ፡ የያዙ ፡ ሕዝቦች ፡ አሉ ፡ እነዚያን ፡ አስተምራ ፡ አታሳምንም ፡ ኖሯልን ።

፱/ ኢትዮጵያ ፡ በበኩልዋ ፡ ከሮም ፡ ጋራ ፡ ለመታረቅ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በልብ ፡ ተመኝታለች ፡ ይህም ፡ ከታሪክ ፡ የሚታወቅ ፡ ከመኾኑም ፡ በላይ ፡ አባ ፡ አየለ ፡ በኹለቱ ፡ የመጽሐፋቸው ፡ ፊተኞች ፡ ምዕራፎች ፡ ውስጥ ፡ አደላድለው ፡ ያስረዱት ፡ ነው ። ብለዋል ።

፱ / ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ ለመታረቅ ፡ ከተመኘች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ማንም ፡ የማያዝዛት ፡ ራሷን ፡ የቻለች ፡ የወደደችውን ፡ ልትሠራ ፡ የምትችል ፡ ነፃ ፡ መንግሥት ፡ ናት ፤ ሮማውያንም ፡ በየጊዜው ፡ ለመምጣት ፡ እጃርጠው ፡ እያውቁም ፡ ለምን ፡ ግንባር ፡ ግንባራቸውን ፡ እያለች ፡ አሳፍራ ፡ መለስቻቸው ፤ በፍቅር ፡ አትቀበላቸውም ፡ ኖሯልን ። በዚያውስ ፡ ላይ ፡ የልብን ፡ ምኞት ፡ ማወቅ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ ለሰው ፡ ይቻለዋልን ፡ በልብ ፡ ተመኝታለች ፡ ያሉት ፡ ካቅም ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ንግግር፡ ነው ።

አባ ፡ አየለ ፡ በ፪ቱ ፡ የመጽሐፋቸው ፡ ፊተኞች ፡ ምዕራፎች ፡ አስረዱት ፡ የሚሉትም ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ በ፲፭ኛ ፡ ፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፈረንጂ ፡ ከተማ ፡ በተደረገው ፡ ጉባኤ ፡ አባ ፡ ኒቆዲሞስ ፡ የተባለ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ አለቃ ፡ የላኳቸው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መልእክተኞች ፡ ለጉባኤው ፡ ተካፋዮች ፡ ኾነው ፡ ተናገሩት ፡ የሚሉትን ፡ ቃል ፡ መኾኑን ፡ ተረድቼዋለሁ ። የዚህን ፡ መልስ ፡ ከዚያው ፡ አባ ፡ አየለ ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ ከጠቀሱበት ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ስንደርስ ፡ ተገቢውን ፡ መልስ ፡ የምሰጥ ፡ መኾኔን ፡ ከማስገንዘብ ፡ በቀር ፡ ከዚህ ፡ ላይ ፡ ልዘረዝረው ፡ አልፈቀድኩም ።

፲/ ከዚያ ፡ ዘመን ፡ ወዲህ ፡ የሮማው ፡ ርእስ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ኹሉ ፡ እንደገና ፡ ወደአንድነት ፡ ለመጥራት ፡ ያንበኛ ፡ ዐዋጅ ፡ አሰነግረው ፡ ጉባኤ ፡ የሚሰበስቡት ፡ ዛሬ ፡ መጀመሪያ ፡ ጊዜያቸው ፡ ነው ። ብለው ፡ ጥሪ ፡ መደረጉን ፡ ገልጠውልናል ።

፲ / ነገሩ ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ እንደሚያስገኝ ፡ ኾኖ ፡ ተመሥርቶ ፡ ከተገኘ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሐሳብ ፡ ነው ። ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመካከሏ ፡ ዲያብሎስ ፡ የዘራው ፡ እንክርዳድ ፡ ተነቃቅሎላት ፡ አንድ ፡ ኾና ፡ ለማየት ፡ ያብቃን ፡ እያልን ፡ ኹላችንም ፡ የምንመኘው ፡ ምኞት ፡ ነው ።

፩ / የደራሲው ፡ አጭር ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ተነሥተው ፡ በ፲፱፻፳፯ ፡ ዓ/ም መጋቢት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ተወልደው ፡ በተወለዱ ፡ በ፲፩ ፡ ዓመትዎ ፡ የሀገርዎን ፤ የኢትዮጵያን ፡ ባህልና ፡ ትምህርት ፡ ዘወር ፡ ብለው ፡ ሳያዩ ፡ በቀጥታ ፡ ከካቶሊክ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መግባትዎን ፡ ከ፲፱፻፴፯ ዓ/ም ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፵፯ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ ባለው ፡ ፳ ዘመን ፡ ውስጥ ፡ ካንደኛ ፡ ክፍል ፡ እስከ ፡ ዩኒቨር ሲቲ ፡ ያለውን ፡ ምድብ ፡ ትምህርት ፡ በየክፍሉና ፡ በየደረጃው ፡ እየተዘዋወሩ ፡ መማርዎን ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ለሊቅነትዎ ፡ ማስመስከሪያ ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ መጻፍዎን ፡ ነግረውናል ።

አንድ ፡ ሰው ፡ የሕይወት ፡ ታሪኩን ፡ በመሰለው ፡ ቢጽፍ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መከራከር ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ ስላልኾነ ፡ ይህን ፡ ወደጐን ፡ ትተነው ፡ ሊቅነትዎን ፡ ለማስመስከር ፡ የደረሱትን ፡ መጽሐፍ ፡ ወደመመርመር ፡ እንመለስ ። ይህን ፡ ሊቅነትዎን ፡ ያስመሰከሩበትን ፡ መጽሐፍ ፡ ብንመረምረው ፡ ፳ ፡ ዘመን ፡ የደከሙት ፡ ድካም ፡ ኹሉ ፡ የቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ምሥጢር ፡ ለማወቅ ፡ ሳይሆን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ባገኙ ፡ አጣ ፡ እያያዙ ፡ የጻፉትን ፡ ሰዎች ፡ ታሪክ ፡ ብቻ ፡ ለማወቅ ፡ መኾኑን ፡ ያስገነዝበናል ፡ ምክንያቱም ፡ ጥልቅ ፡ ምሥጢር ፡ ያለው ፡ የቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነን ፡ ምሥጢር ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ አንድ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ሳይጠቅሱ ፡ ከነዚሁ ፡ ከታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ መጽሐፍ ፡ ባገኙት ፡ ጥርቅም ፡ አነጋገር ፡ ብቻ ፡ ሳስረዳ ፡ ብለው ፡ ስለሞከሩ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ጠቅሶ ፤ ለማስረዳት ፡ ችሎታ ፡ ቢኖራቸው ፡ ይህን ፡ ባላደረጉም ፡ ነበረ ፡ በማለት ፡ ነው ። ይህን ፡ አኳኋን ፡ ከርስዎ ፡ አልፎ ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ አስረጅነት ፡ የዶክተርነት ፡ መዓርግ ፡ የፈቀዱልዎን ፡ ሊቃውንት ፡ ሳይቀር ፡ ሳያሳማ ፡ አልቀረም ።

፪/ ዶክተርነታቸውን ፡ ያስመሰከሩበት ፡ ጽሑፍ ፡ ታላቅ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ስለነበረው ፡ ባስተማሪዎቻቸው ፡ ፈቃድና ፡ ኪሳራ ፡ በጣልያንኛ ፡ ቋንቋ ፡ ታትሞ ፡ እንዲወጣ ፡ ተደረገ ።

ብለዋል ።

፫ / ይህ ፡ ነገር ፡ ምናልባት ፡ በካቶሊካውያን ፡ ዘንድ ፡ እንደቁም ፡ ነገር ፡ ተቈጥሮ ፡ ይኾናል ። ምክንያቱም ፡ ካቶሊካውያን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ትምህርትና ፡ ባህል ፡ ባለማወቃቸው ፡ ኢትዮጵያ ፡ አስቀድማ ፡ ካቶሊክ ፡ ነበረች ፡ እነዓፄ ፡ ካሌብ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ነበሩ ፡ ተብሎ ፡ የተጻፈው ፡ ቃል ፡ እውነት ፡ መስሎ ፡ ስለሚታያቸው ፡ ነው ። እኛ ፡ ግን ፡ በድፍረትና ፡ በመላ ፡ የተጻፉትን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪኮችና ፡ ቅኔዎች ፡ ባህሎችንም ፡ አጣርተን ፡ የምናውቃቸው ፡ ስለኾነ ፡ አብራርተን ፡ አስፋፍተን ፡ መልስ ፡ እንድንሰጥ ፡ ከማነቃቃት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ የተጨበጠ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ እንደሌለበት ፡ እናውቃለን ።

፬/ በምጥዋ ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ በየካቲት ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ/ም ፡ ለጥርጣሮ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መጽሐፉን ፡ ግጽ ፡ በረከት ፡ ባቀረቡላቸው ፡ ጊዜ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ተተርጉሞ ፡ እንዲታተም ፡ ፈቃዳቸው ፡ መኾኑን ፡ ስለገለጹላቸው ፡ ካንድ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ተርጕመው ፡ አሥመራ ፡ ላይ ፡ በጥር ፡ ፳፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፮ ፡ ዓ/ም ፡ አቀረቡላቸው ፡

ብለዋል ።

፭ / ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ወረቀቶቹን ፡ ገልበጥ ፡ ገልበጥ ፡ አድርጎ ፡ ወደማሃል ፡ ገባ ፡ ብሎ ፡ ሲያዩት ፡ ኢትዮጵያ ፡ የካቶሊክን ፡ ባህል ፡ ተቀብላ ፡ ፬ ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ ነበረች ፡ ነገሥታቶቿ ፡ እነዓፄ ካሌብም ፡ ካቶሊካውያን ፡ ነበሩ ፡ እያለ ፡ የሃይማኖቷን ፡ መሠረት ፡ ለማፋለስ ፡ ከመሞከሩም ፡ በላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ በሃይማኖት ፡ ጉዳዮችና ፡ ትምርቶች ፡ ውስጥ ፡ ያላቸው ፡ ሥልጣን ፡ ምንም ፡ የሕግ ፡ መሠረት ፡ የለውም ። እንደ ፡ ሕጉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መንፈሳዊ ፡ መሪ ፡ አቡኑ ፡ ናቸው ። ለነገሥታቱ ፡ በዚህ ፡ ሥልጣን ፡ ለመግባት ፡ ምክንያት ፡ የኾናቸው ፡ ንጉሣዊና ፡ ቅዱስ ፡ ከኾነው ፡ ከዳዊት ፡ ዘርዕ ፡ ይወርዳሉ ፡ ተብለው ፡ ስለሚታሰቡና ፡ በተቀደሰ ፡ ቅብዕ ፡ ስለሚቀቡ ፡ ነው ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ ተቀደሱ ፡ ሰዎች ፡ ታስበው ፡ ለሕዝብ ፡ ኑሮ ፡ ጸጥታና ፡ ዕርጋታ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ለሃይማኖት ፡ ጥበቃ ፡ እንደ ፡ ተላኩ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደራሲዎች ፡ ስለታዩ ፡ ነው ፡ ንጉሥን ፡ መቃወም ፡ ወይም ፡ ከመንግሥቱ ፡ ለማስለቀቅ ፡ መፈተን ፡ የቲቀደሰ ፡ ነገርን ፡ እንደማርከስ ፡ የሚቈጠር ፡ ነገር ፡ ነው ። የኢትዮጵያን ፡ ነገሥታት ፡ ሥልጣን ፡ የሚደግፉ ፡ ሁኔታዎችና ፡ የድሮ ፡ ባህሎችን ፡ ለማበርታት ፡ የተገበ ፡ ለማስመሰል ፡ የረዳም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለረጅም ፡ ዓመታት ፡ መንፈሳዊ ፡ መሪ ፡ በማጣቷ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ እያለ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሥልጣን ፡ በግፍ ፡ የነጠቁ ፡ በማስመሰሉ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትንና ፡ ቤተ ፡ ክህነትን ፡ ሊያለያይ ፡ የተነሣ ፡ መኾኑ ፡ እስኪገለጥ ፡ ድረስ ፡ በመግቢያው ፡ ላይ ፡ መጻሕፍት ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ አንድ ፡ ሃይማኖት ፡ አንዲት ፡ ጥምቀት ፡ ብቻ ፡ መኖራቸውን ፡ ሲያስተምሩ ፡ የክርስቶስ ፡ ተከታዮች ፡ የኾኑት ፡ የክርስቲያኖች ፡ ኹሉ ፡ መለዮ ፡ እንዲኾን ፡ የፈለገውና ፡ ያማጠነው ፡ አንድነት ፡ ይህን ፡ በመሳሰሉ ፡ በማይረቡ ፡ ነገሮች ፡ ተበታትኖ ፡ ማየት ፡ በጣም ፡ የሚያሳዝን ፡ ነው ። ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ዋና ፡ ዓላማው ፡ ይህን ፡ ኹላችን ፡ የምንመኘውን ፡ አንድነትን ፡ ማስገኘት ፡ ነው ፡ የወንጌልን ፡ መንፈሳዊ ፡ ሀብት ፡ ለመጠበቅና ፡ እርሱ ፡ ወደሚያመለክተው ፡ ከፍተኛ ፡ ዓላማ ፡

ለመድረስ ፡ ክርስቲያኖች ፡ እንዲያብሩና ፡ ኃይላቸውን ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ እንዲያደርጉ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ በመታየቱ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ አንድነት ፡ የፈለገ ፡ ይመስላል ። ግርማዊ ፡ ጃንሆይም ፡ የመላውን ፡ ዓለም ፡ ሰላም ፡ ፈላጊ ፡ ስለኾኑ ፡ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ የተጠቀሰውን ፡ ትንኮል ፡ ደብቀው ፡ በመግቢያው ፡ ላይ ፡ የሚገኘውን ፡ ሰላምን ፡ የሚመሠርት ፡ መኾኑን ፡ ብቻ ፡ ስለገለጹላቸው ፡ የክርስቲያንን ፡ አንድነት ፡ የሚመሠርት ፡ ከኾነ ፡ ከኢጣልያንኛ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ቢተረጐም ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ፈቅደዋል ፡ ብሎ ፡ ማመን ፡ ምናልባት ፡ ይቻል ፡ ይኾናል ፡ ወይም ፡ አይታመንም ።

፱/ ግርማዊነታቸውም ፡ በዚሁ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ በኾነው ፡ ሥራ ፡ ብዙ ፡ ተደስተው ፡ ለማሳተሚያው ፡ አስፈላጊ ፡ የኾነውን ፡ ገንዘብ ፡ በተለመደው ፡ ልግስናቸው ፡ ሰጡዋቸው ፡
ብለዋል ።

፲ / ይህ ፡ አነጋገር ፡ ከላይ ፡ እንዳተትነው ፡ መጽሐፉ ፡ በውስጡ ፡ የሰበሰበውን ፡ ጉድ ፡ ሳይገልጹ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድነት ፡ ጠቃሚ ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ሸፋፍነው ፡ ከኢጣልያንኛ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ መተርጐሙን ፡ ብቻ ፡ ቢነግሯቸው ፡ ተደሰቱ ፡ ቢባል ፡ ሊታመን ፡ የሚገባው ፡ አነጋገር ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድ ፡ ኾና ፡ ተስማምታ ፡ እንድትኖር ፡ የሚፈቅዱ ፡ ስለኾነ ፡ ነው ። ለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ማቅረቢያ ፡ ያደረጉልዎ ፡ ካርዲናል ፡ ኤውጀንዮስ ፡ ቲሰራን ፡ ግን ፡ እርስዎ ፡ ያልተናገሩትን ፡ ከርስዎ ፡ ያላገኙትን ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መጽሐፉን ፡ ተመልክተው ፡ አመሰገኑት ፡ ያሉት ፡ ቃል ፡ ለንገው ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊ ፡ በር ፡ ሊከፍቱ ፡ መንገድ ፡ ሊጠርጉ ፡ ከራሳቸው ፡ አንቅተው ፡ ተናገሩት ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሊቀበለው ፡ የማይችል ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ።

ለማሳተሚያው ፡ የገንዘብ ፡ ችሮታ ፡ አደረጉልኝ ፡ ለሚሉትም ፡ ተገቢ ፡ ሥራ ፡ መኾኑን ፡ በመቅድም ፡ በቍ ፡ ፲፩ ፡ ዘርዝሬ ፡ በሰፊው ፡ ስለጻፍኩ ፡ ያንን ፡ መመልከት ፡ በቂ ፡ ነው ።

መልስ ፡ የሚሰጥበት ፡ ከአባ ፡ እየለ ፡ የተጻፈ ፤

## መቅድም ።

፩/ ዶክተር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ ሲጽፉ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሁሉ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ኅብረት ፡ እንዲኖራቸው ፡ የግድ ፡ ነው ። መጻሕፍት ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ አንድ ፡ ሃይማኖት ፡ አንድ ፡ ጥምቀት ፡ ብቻ ፡ መኖሩን ፡ ሲያስተምሩን ፡ እኒህ ፡ ነገሮች ፡ እንዲያገኙ ፡ ጸንጾ ፡ ለየብቻው ፡ የኾነ ፡ ትርጉም ፡ እየተሰጣቸው ፡ መለየታቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡ ነገሩም ፡ አሳዛኝ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ካሳሰቡ ፡ በኋላ ፡ ለክርስቲያን እርስ በርስ መለያየት ፡ እንዳይገባ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ጽፏል ፡ በማለት ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲—፲፱ ፡ ጠቅሰዋል ።

ይህችም ፡ የቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ቃል ፡ ጌታችን ፡ መድኃኒታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በምሴተ ፡ ኀሙስ ፡ ቀኑ ፡ ቀሩ ፡ በበይናቲከሙ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ የመሰለ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አስገንዝበዋል ።

ይህንንም ፡ ካስገነዘቡ ፡ በኋላ ፡ ለኔ ፡ ደግሞ ፡ እኒህ ፡ ቃሎች ፡ በጸሮቹ ፡ ክርስቲያን ፡ ሆይ ፡ አንድነታችሁን ፡ ጠብቁ ፡ እንደሚሉ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ እንደገና ፡ እንዲገኙና ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ ጸሎ ፡ እርሱ ፡ እንደሚል ፡ ብርቱ ፡ ጥሪ ፡ ኾነው ፡ ይሰሙኛል ፡ ብለው ፡ የራስዎን ፡ ስሜት ፡ ገልጸዋል ።

፪/ እውነት ፡ ነው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ፩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወ፩ ፡ ሃይማኖት ፡ ወአሐቲ ፡ ጥምቀት ፡ ብሎ ፡ እንደነገረን ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ እንደኾነ ፡ ሃይማኖትም ፡ አንዲት ፡ ናት ፡ ጥምቀትም ፡ አንዲት ፡ ናት ። ይህ ፡ በክርስቲያን ፡ ዘንድ ፡ ኹሉ ፡ የሚካድ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ነገር ፡ ግን ፡ ኹሉም ፡ በየበኩሉ ፡ ሐሳቡን ፡ ያች ፡ አንዲት ፡ ናት ፡ የተባለችቱ ፡ ሃይማኖት ፤ እኔ ፡ የያዝኳት ፡ ናት ፤ ሌላው ፡ ተሳስቷል ፡ በማለት፡ላይ፡አሳርፎታል፡እንጂ፡ምናልባት፡እኔ፡ተሳስቸ፡ይኾን፡የሚል፡አይገኝም፡የክርስቲያንም ፡ ኹሉ ፡ ምኞቱና ፡ ፍላጎቱ ፡ በክርስቶስ ፡ ስም ፡ አምኖና ፡ ተጠምቆ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ለመውረስ ፡ ሲኾን ፡ እንዲህ ፡ ተለያይቶ ፡ መገኘቱ ፡ በጣም ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ ነው ። አሁንም ፡ ዶክተር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ እንዳሳሰቡት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በዘራት ፡ ንጽሕት ፡ የሃይማኖት ፡ ዘርዕ ፡ ላይ ፡ ዲያብሎስ ፡ በጨለማ ፡ መጥቶ ፡ የነሰነሰውን ፡ እንክርዳድ ፡ ነቅሎ ፡ ጥሎ ፡ አንድነት ፡ ለማግኘትም ፡ መጣጣር ፡ እጅግ ፡ የተቀደሰ ፡ ሐሳብ ፡ ነው ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ ሊቀበለው ፡ ይገባል ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ምኞት ፡ እኔ ፡ በላይ ፡ ነኝ ፤ ሌላው ፡ ከበታች ፡ ነው ፤ እኔ ፡ እውነተኛ ፡ ነኝ ፤ ሌላው ፡ ሐሰተኛ ፡ ነው ፤ እኔ ፡ አልሳሳትም ፡ ጠንቃቃ ፡ ነኝ ፡ ሌላው ፡ ስሑት ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ አስተያየት ፡ ያፈርስ ዋል ፡ ብዬ ፡ እሰጋለሁ ፤ የኾነ ፡ ኾኖ ፡ ፀቅሜ ፡ የፈቀደልኝን ፡ ያህል ፡ የምገልጸውንና ፡ የምገልጸው ማበትን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ [illegible] ፡ ዶክተር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ የጻፉት ፡ ግን ፡ ምንጩ ፡ ከሊቃውንት ፡ መጻሕፍት ፡ ሳይኾን ፡ ከታሪክ ፡ መጻሕፍቶች ፡ ብቻ ፡ የተሰበሰበ ፡ መኾኑ ፡ ቅር ፡ ማሰኘቱ ፡ አልቀረም ። ወደ ፡ ፊት ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የትናገሩት ፡ ኹሉ ፡ ከሊቃውንት ፡ መጻሕፍት ፡ የተያያዘ ፡ መኾኑን ፡ የሚያስረዱ ፡ ቢኾን ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ነው ።

፫/ የኢትዮጵያ ፡ ክርስቲያንና ፡ ካቶሊክ ፡ በሃይማኖት ፡ በሁሉ ፡ የማይስማሙበት ፡ ምንም ፡ ምክንያት ፡ መኖሩን ፡ ባለማ ወቅ ፡ ባልደረሰ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

፫/ ይህ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ይህ ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ መለያየት ፡ ነው ፡ ዋናውም ፡ ሌላ ፡ (ሀ) የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብ ፡ ብቻ ፡ ሠረጸ ፡ ስትል ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብም ፡ ከወልድም ፡ ሠረጸ ፡ ትላለች ።

(ለ) የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነፍስንም ፡ ሥጋንም ፡ ከእመቤታችን ፡ ነሣ ፡ ብላ ፡ ስታስተምር ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥጋ ፡ እንጂ ፡ ነፍስ ፡ አልነሣም ፡ ትላለች ።

(ሐ) የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለምእመናን ፡ ሥጋውን ፡ ከቀበለች ፡ በኋላ ፡ ደሙንም ፡ ስታቀብል ፡ ካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደሙን ፡ ለካህናት ፡ እንጂ ፡ ለምእመናን ፡ አታቀብልም ፡ በዚህ ፡ ኹሉ ፡ ይለያያሉ ፡ ሌላም ፡ ይሁን ፡ የመሰለ ፡ አይጠፋም ።

ከዚህ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የማስታውሰው ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡ ከዚህ ፡ አልፎ ፡ ብሎ ፡ በሚገኙት ፡ መሥመሮች ፡ ፲፪ኛው ፡ ርእስ ፡ ሊቃነ ፡ ለጳሳት ፡ ጥዮስ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ የማይስማሙ ፡ በግብጽ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በሶርያ ፡ በአርማንያ ፡ በሌሎችም ፡ አገሮች ፡ አሉ ፡ ብለዋል ፡ ብለው ፡ እንደገለጹት ፤ ይህን ፡ በመሳሰለው ፡ ባህል ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተለዩ ፡ እሊህ ፡ ኹሉ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብቻ ፡ አይደለችም ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ኹለቱም ፡ ወገኖች ፡ በየበኩላቸው ፡ ኦርቶዶክስ፡ካቶሊክ ፡ የሚል ፡ የመለዮ ፡ ስም ፡ ተሰጥቷቸዋል ፤ አሁን ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍም ፡ ውስጥ ፡ ካቶሊካውያንና ፡ ኦርቶዶክሳውያን ፡ የሚለያዩበት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፤ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚለያዩበት ፡ እያሉ ፡ ይጽፋሉ ። ይህ ፡ አያያዝ ፡ ብዙ ፡ በጎች ፡ ባንድነት ፡ ተሠማርተው ፡ ከሚለቀሙበት ፡ ቦታ ፡ ተኩላ ፡ ወይም ፡ ቀበሮ ፡ እንዲገን ፡ በግ ፡ ነጥላ ፡ አበራ ፡ እንደምትነጥቅ ፡ ኢትዮጵያንም ፡ ከኦርቶዶክሳውያን ፡ ጓደኞቿ ፡ ነጥሎ ፡ ለመንጠቅ ፡ የታሰበ ፡ ዘዴ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ጥርጣሬ ፡ በተመልካች ፡ ልቡና ፡ አሳድሯል ፤ ስለዚህ ፡ የአጻጻፍዎን ፡ አመራር ፡ ኢትዮጵያና ፡ ካቶሊክ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ካቶሊክና ፡ ኦርቶዶክስ ፡ የሚል ፡ ቢኾን ፡ የክርስቲያንን ፡ አንድነት ፡ ፈላጊ ፡ መኾናቸው ፡ ጎልቶ ፡ በታየና ፡ በተረጋገጠ ፡ ነበር ፡ እላለሁ ።

፬/ ፈተኞች ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ያስተምራሉ ፡ ጃኮቦ ፡ ግን ፡ በክርስቶስ ፡ ፪ ፡ ባሕርያት ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ሲሉ ፡ ያስተምራሉ ፡ ይህ ፡ ኹለቱንም፡ወገን ፡ ለያይቶ ፡ ያለ ፡ ጉዳይ ፡ ለመገመሪያ ፡ ሲገጥማቸው ፡ ለብዙዎቹ ፡ እንደሚመስላቸው ፡ ሊስማሙበት ፡ የማይቻል ፡ አይደለም ። ብለዋል ።



ይህ ፡ ሥዕል ፡ ሮማ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስን ፡ የቁልቁሊት ፡ ሰቅላ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስን ፡ በሰይፍ ፡ መትራ ፡ እንደ ፡ ገደለቻቸው
ያሳያል ። ሮማ ፡ ይህን ፡ ትሠራ ፡ በነበረበት ፡ በሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ ነዋ ፡ ማይ ፡ መኑ ፡ ይከልዓኒ ፡ ተጠምቆ ።
ውን ፡ እነሆ ፡ አለ ፤ መጠመቅን ፡ ማን ፡ ይከለክለኛል፡ብላ፡ በፈቃዷ ፡ ወንጌልን ፡ መቀበልን ፡ ጀምራለች ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፰ ፡ ፴፮-፴፰

፫ እንግዲህ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ያስተማሩ ፡ ፊተኞች ፡ ለሃይማኖተ ፡ ወን ጌል ፡ መደበኞች ፡ የኾኑ ፡ ሐዋርያትና ፡ ጉባኤ ፡ ኒቅያን ፡ ያቆሙ ፡ ሦስቱ ፡ መቶ ፡ አሥራ ፡ ስምንት ፡ ሊቃውንት ፤ እንዲሁም ፡ ጉባኤ ፡ ቍስጥንጥንያን ፡ ያቋቋሙ ፡ ፻፶ ፡ ሊቃውንትና ፡ ጉባኤ ፡ ኤፌሶንን ፡ የወሰኑ ፡ ፪፻ ፡ ሊቃውንት ፡ሲኾኑ ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ብለው ፡ ያስተ ማሩ ፡ ኹለተኞች ፡ በጉባኤ ፡ኬልቄዶን ፡ የተሰበሰቡ ፡ ካቶሊካውያን ፡ መኾናቸው ፡ የሚካድ ፡ አይ ደለም ።

እነሆም ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ጉባኤያት ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ ሲወስኑ ፡ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ በጉባኤው ፡ ተገኝታ ፡ አብራ ፡ መወሰኗ ፡ አይካድም ።

እንዲህ ፡ ከኾነ ፡ ካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የኀላና ፡ የተጨበጠ ፡ ነገር ፡ ሳትይዝ ፡ በይመስላልና ፡ በያሰኛል ፡ ያመጣችውን ፡ ባህል ፡ ትታ ፡ የፊተኞች ፡ በወሰኑት ፡መን ገድ ፡ ካልሄደች ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ ስምምነት ፡ በምን ፡ አኳኋን ፡ ይገኝ ፡ ይኾን ፤ የሐዋርያትን ፡ የሮቱ ፫ን ፡ ውሳኔ ፡ ለቆ ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ መመራት ፡ አግባብ ፡ መስሎ ፡ ይታያል ፡ ይኾን ፤ እንኳ ፡ ለእኔ ፡ አይታየኝም ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ሐሳብ ፡ ተቀባይ ፡ ያገኝ ፡ አይመስለኝም ።

፩/ ኹለቱን ፡ ወገኖች ፡ ማቀራረብ ፡ ቅርብ ፡ መኾኑን ፡ ስለተረዳሁ ፡ ይህ ፡ ጉዳይ ፡ የምመረምርበት ፡ መጽሐፍ ፡ ልደርስ አሰብኩ ፡ በመጽሐፉም ፡ ውስጥ ፡ ከኹሉ ፡ አስቀድሜ ፡ ላደርገው ፡ ያሰብኩት ፡ ይህን ፡ የሃይማኖት ፡ መለያየት ፡ ያመጡ ፡ ምክ ንያቶች ፡ እኒቱ ፡ መኾናቸውን ፡ ጠንቅቆ ፡ መመርመር ፡ ነው ።
ብለዋል ።

፪ / እውነት ፡ ነው ፡ ሰው ፡ ዐዋቂ ፡ ፍጥረት ፡ ነውና ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ማሰብ ፡ ማውጣት ፡ ማውረድ ፡ አስቦም ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ሲገኝበት ፡ በጽሑፍ ፡ መግለጥ ፡ ተገቢ ፡ ሥራው ፡ ነው ። ስለኾነም ፡ የተጻፈ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ከሰው ፡ ፊት ፡ መድረሱ ፡ አይቀርምና ፡ ሰው ፡ ይታዘበኛል ፤ እግዚአብሔር ፡ ይፈርድብኛል ፡ ብሎ ፡ ሐሳብን ፡ ለመደገፍ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ በሚዛናዊ ፡ አስተያየት ፡ ካልጸፉት ፡ ከምስጋናው ፡ የበለጠ ፡ ነቀፋና ፡ ትንቢት ፡ [illegible] ፡ የማይቀር ፡ ነውና ፡ [illegible] ፡ እንዲጠነቀቁ ፡ አሳስብዎታለሁ ፡ እንጂ ፡ ሐሳብዎስ ፡ መልካም ፡ ነው ።

፫/ ቀጥሎም ፡ የተረጋገጠና ፡ የጸኑ ፡ ማስረጃዎችን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህልና ፡ የካ ቶሊክ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ምን ፡ በሚያህል ፡ ደረጃ ፡ መራራቃቸውን ፡ የሚገልጽ ፡ የተረጋገጠ ፡ መምሪያ ፡ ስጥቻለሁ
ብለዋል ።

፬ / አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለትና ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ ዓላማው ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፤ ለሃይ ማኖት ፡ ነገር ፡ ከቅዱሳት ፡ ከአሥራው ፡ መጻሕፍትና ፡ አሥራው ፡ መጻሕፍትን ፡ በሰፊው ፡ ተርጕ መው ፡ አብራርተው ፡ ከሚያስረዱ ፡ ከመጻሕፍት ፡ ሊቃውንት ፡ በቀር ፡ ማንኛውም ፡ ጽሑፍ ፡ ሊያ ስረዳ ፡ አይችልም ፡

አሁን ፡ የተረጋገጡና ፡ የጸኑ ፡ ማስረጃዎች ፡ ብለው ፡ የጠቀሷቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ኹሉ ፡ የታሪክ ፡ መጻሕፍት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ከብሉያት ፡ ከሐዲሳት ፡ ከሊቃውንት ፡ የተጠቀሰ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ የለም ። እንግዲህ ፡ የሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ አንዳንድ ፡ ሀገር ፡ ጐብኝዎች ፡ በጻፉት ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ማስረ ዳትስ ፡ መረዳትስ ፡ እንደምን ፡ ይቻላል ። ተቀባዩስ ፡ ማነው ፤ እኔ ፡ በእውነቱ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ መሠረ ታዊ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሚቀበለው ፡ ይገኝ ፡ አይመስለኝም ።

፭/ ፲፪ኛው ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ፕዮስ ፡ ይህ ፡ መለያየት ፡ አብዛኛውን ፡ ስለሃይማኖት ፡ ሲናገሩ ፡ ከሚያገቧቸው ፡ አንድ ፡ ትርጕም ፡ ከማይሰጣቸው ፡ ቃሎች ፡ የተነሣ ፡ ነው ፤ በዛሬ ፡ ዘመንም ፡ ቢኾን ፡ አንዳንዶች ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ የማይስማሙ ፡ በግብጽ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በሶርያ ፡ በአርማንያ ፡ በሌሎችም ፡ ሀገሮች ፡ የሚገኙ ፡ ማኅበሮች ፡ ስለ ፡ ጌታችን ፡ ሥጋዌ ፡ የሚይዙትን ፡ ባህል ፡ ሲገልጡ ፡ ከቀና ፡ መንገድ ፡ የወጡ ፡ የሚያስመስላቸው ፡ አብዛኛው ፡ ያነጋገራቸው ፡ ልዩነት ፡ ነው ። እንዲሁ ፡ ብሎ ፡ ለማሰብ ፡ የሚያስችልም ፡ የሥርዓት ፡ አምልኮና ፡ የሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ መጻሕፍቶቻቸው ፡ ናቸው ፡ አሉ ።
ብለዋል ።

፮ / (ሀ) ትርጕም ፡ ከማይሰጣቸው ፡ ቃሎች ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ ለሚሉት ፡ ትርጕም ፡ የማይሰ ጣቸው ፡ ቃሎች ፡ የትኞች ፡ እንደኾኑ ፡ ቢታወቅ ፡ ኖሮ ፡ ምናልባት ፡ የሚቻል ፡ ቢኾን ፡ ትርጕማ ቸው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ለመግለጽ ፡ ይታሰብበት ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ ስላልተገለጹ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ ሊሰጣቸው ፡ አልተቻለም ።

(ለ) ከቀናው ፡ መንገድ ፡ የወጡ ፡ የሚያስመስላቸው ፡ ያነጋገራቸው ፡ ልዩነት ፡ ነው ፡ስለ ሚሉት ፡ ግን ፤ ይህ ፡ አስተያየት ፡ በእኛም ፡ ዘንድ ፡ አለ ። ለእኛም ፡ ካቶሊካውያን ፡ ከቀናው ፡ መንገድ ፡ የወጡ ፡ መስለው ፡ የሚታዩን ፡ ከአነጋገራቸው ፡ ልዩነትና ፡ ከሥርዓተ ፡ አምልኳቸው ፡ ልዩነት ፡ የተ ነሣ ፡ ነው ።

ስንኳን ፡ በክርስቶስ ፡ ያመነ ፡ ክርስቲያን ፤ ሰው ፡ ከሆነ ፡ ከሃይማኖተ ፡ ወንጌል ፡ በአፍኣ ፡ ያሉ ፡ ማናቸውም ፡ ቢኾን ፡ አምላክ ፡ ፈጣሪ ፡ መኖሩን ፡ የማያምን ፡ የለም ፡ ኹሉም ፡ በየራሱ ፡ በሃይማኖት ፡ ተለያይቶ ፡ የሚኖር ፡ እግዚአብሔርን ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ ያገለገልኩ ፡ እየመሰለው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ልበድል ፡ ብሎ ፡ የሚኖር ፡ አይገኝም ።

ለምሳሌ ፡ እስላሞች ፡ አላህ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ አይወርድም ፡ አይወለድም ፡ አይታመምም ፡ አይሞትም ፡ አላህ ፡ ከሞተ ፡ ዓለሙን ፡ ማን ፡ አጸናው ፡ ከርሱ ፡ በላይስ ፡ ምን ፡ ኖሮ ፡ ገደለው ፡ እያሉ ፡ ወንጌልን ፡ አንቀበልም ፡ ማለታቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአዳም ፡ ያደረገውን ፡ ቸርነት ፡ ካለማወቃቸው ፡ የተነሣ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ አከበርነው ፡ አገለገልነው ፡ ብለው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማዋረድ ፤ ብለው ፡ አይደለም ።

እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ መግባባትና ፡ መስማማት ፡ የሚገኘው ፡ ኹሉም ፡ በየበኩሉ ፡ እውነተኛው ፡ ሃይማኖት ፡ እኔ ፡ የያዝኩት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ማለቱን ፡ ትቶ ፡ የሌላውንም ፡ አስተያየትና ፡ አመራር ፡ በቅን ፡ ሕሊና ፡ በመመልከት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ ኢያያዝ ፡ አይደለም ።

፬/ እንግዲህ ፡ ኢትዮጵያውያኖችና ፡ ካቶሊካውያንን ፡ ለያይቷቸው ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ ትልቅ ፡ ነገት ፡ ሊሰጠው ፡ የማይገባው ፡ የቃሎች ፡ ልዩነት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፡
ብለዋል ።

፭/ የቃል ፡ መለያየትን ፡ እንደ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ አድርገው ፡ ገምተውታል ፤ የፍቅር ፡ መሠረቱ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ መኾን ፡ የጥል ፡ መሠረቱ ፡ የቃል ፡ መለያየት ፡ አይደለምን ፡ እስመ ፡ እምተረፈ ፡ ልብ ፡ ይነብብ ፡ አፍ ፡ እንዲል ፡ አንደበት ፡ የሚናገር ፡ ከልቡና ፡ የመነጨውን ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ በልብ ፡ አንድ ፡ መኾን ፡ የሚታወቀው ፡ በአነጋገር ፡ ነውና ፡ የቃል ፡ መለያየት ፡ እንደ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ የሚቈጠር ፡ አይደለም ፤ በዚህስ ፡ ፈንታ ፡ የቃል ፡ ልዩነት ፡ የሚጠፋበትን ፡ መንገድ ፡ መፈለግ ፡ በጣም ፡ የተሻለ ፡ ነው ።

፮/ የክርስቲያን ፡ መለዮ ፡ ሊኾን ፡ የተፈለገው ፡ አንድነት ፡ በማይረቡ ፡ ነገሮች ፡ ተበታትኖ ፡ ማየት ፡ በጣም ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ ነው ። ብለዋል ።

፯/ ይህ ፡ አነጋገርዎ ፡ ሰውንም ፡ እግዚአብሔርንም ፡ የሚያሳዝን ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነውና ፡ ኹላችንም ፡ በየበኩላችን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድ ፡ የምትሆንበትን ፡ ብናስብ ፡ መልካም ፡ ነው ።

፰/ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ዋና ፡ ዓላማው ፡ ኹላችን ፡ የምንመኘውን ፡ አንድነትን ፡ ማስገኘት ፡ ነው ፡ እኔም ፡ ይህ ፡ ኅብረት ፡ እንዲፈጸም ፡ ጠቃሚ ፡ ኾኖ ፡ የታየኝን ፡ ምክር ፡ እየገለጽኩ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ መዋሉ ፡ የሚመራ ፡ መንገድ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ እመለከቻለሁ ፡ ብለዋል ።

፱/ አንድነትን ፡ ለማግኘት ፡ መመኘትዎ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ ነበረ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አመራርዎ ፡ ምኞትዎን ፡ የሚደግፍ ፡ ኾኖ ፡ አልተገኘም ፡ ምክንያቱም ፡ ያንኑ ፡ የለመዱትን ፡ አዲሱን ፡ የካቶሊክን ፡ ባህል ፡ ከማነጋገሥ ፡ በቀር ፡ ጥንታዊውን ፡ የኦርቶዶክስን ፡ ባህል ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ የማያየው ፡ በመኾኑ ፡ ነው ።

፲/ የወንጌልን ፡ መንፈሳዊ ፡ ሀብት ፡ ለመጠበቅና ፡ እርሱ ፡ ወደሚያመለክተው ፡ ከፍተኛ ፡ ዓላማ ፡ ለመድረስ ፡ ክርስቲያኖች ፡ እንዲያብሩና ፡ ኃይላቸውን ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ እንዲያደርጉ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ብለዋል ።

፲፩/ የሚተባበሩበትን ፡ መንገድ ፡ አድልዎ ፡ በሌለበት ፡ ዘዴ ፡ ማዘጋጀት ፡ ያስፈልጋል ፡ እንጂ ፡ ሐሳብዎ ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ በዚህ ፡ የማይተባበር ፡ ክርስቲያን ፡ አይገኝም ።

፲፪/ በተለይም ፡ በዚኽ ፡ ዘመናችን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሃይማኖታዊ ፡ ብቻ ፡ ሳትኾን ፡ ፖለቲካዊውንም ፡ አንድነቷን ፡ በማጥፋት ፡ ኀበቀሏ ፡ አሳቦች ፡ ወደ ፡ ኾነው ፡ መከፋፈል ፡ ላይ ፡ ከመውደቅ ፡ ልትድን ፡ የፈለገች ፡ እንደኾነ ፡ ከልፋት ፡ ዘመናት ፡ ይልቅ ፡ ዛሬ ፡ በጽኑነት ፡ እየታገለች ፡ ለብዙ ፡ ዘመናት ፡ የተከላከለችለትንና የጠበቀቻቸውን ፡ መንፈሳዊ ፡ ሀብቷን ፡ ለመጠበቅ ፡ ልጆችዋንና ፡ ኃይሎችዋን ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ልትሰበስባቸው ፡ እንደሚገባ ፡ አስተዋይና ፡ አዋቂ ፡ ልብ ፡ ያለው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ይረዳዋል ።

ይህን ፡ መንፈሳዊ ፡ ሀብት ፡ ለመጠበቅ ፡ መተባበር ፡ የውጭ ፡ ሀገሮችን ፡ ደግነትና ፡ ልግት ፡ ማረጋገጥ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ከኹሉ ፡ የበለጠው ፡ ሀገራችን ፡ ታሪክ ፡ ምዕራፍ ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ አጽንታ ፡ መያዝዋ ፡ መኾኑን ፡ እንዲሁም ፡ የአፍሪቃ ፡ ክፍል ፡ የክርስትና ፡ የታመነና ፡ የማይበገር ፡ ምሽግ ፡ መሆንዋን ፡ እያንዳንዱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ኹልጊዜ ፡ ሊያስታውሰው ፡ የሚገባው ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ለአባቶቹና ፡ ለያቆብ ፡ የተገባ ፡ ለመኾን ፡ የሚፈልገው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ ያገሩ ፡ ያለፉ ፡ ዘመናት ፡ የተመሰገነ ፡ ታሪኳን ፡ ለመቀጠልና ፡ እያደር ፡ እንዲገኝ ፡ ለማድረግ ፡ መጣጣር ፡ አለበት ፡

ብለው ፡ ከልብ ፡ የሚገባ ፡ ነገር ፡ ተናግረዋል ፡፡

፲፩/ ይህ ፡ ምክር ፡ በእውነቱ ፡ ማንም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ክብሩን ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲል ፡ በደስታ ፡ የሚቀበለው ፡ ልባዊ ፡ ጥልቅ ፡ ምክር ፡ ነው ፤ ይህን ፡ ምክር ፡ በመስጠትዎ ፡ በጣም ፡ አመሰግንዎታለሁ ፡፡ ይልቁንም ፡ የሐሳብዎ ፡ አመራር ፡ ኢትዮጵያ ፡ የካቶሊክን ፡ ባህል ፡ እንድትቀበል ፡ ለማግባባት ፡ መኾኑ ፡ ሲታወቅ ፡ ለአባቶቹና ፡ ለአያቶቹ ፡ የተገባ ፡ ለመሆን ፡ የሚፈልገው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ ያገሩ ፡ ያለፉ ፡ ዘመናት ፡ የተመሰከረ ፡ ታሪኳን ፡ ለመቀጠልና ፡ እያደር ፡ እንዲገኝ ፡ ለማድረግ ፡ መጣጣር ፡ አለበት ፡ ያሉትን ፡ ቃል ፡ ምንም ፡ እድገትዎና ፡ ትምህርትዎ ፡ በካቶሊክ ፡ ቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ቢኾን ፡ ዘርዎና ፡ ትውልድዎ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ስለኾነ ፡ ኢትዮጵያዊነትዎ ፡ አስገድዶ ፡ ያናገረዎ ፡ ይመስለኛል ፡ እንጂ ፡ የያዙትን ፡ ዓላማ ፡ በገዛ ፡ እጅዎ ፡ ለመጣል ፡ አስበው ፡ የተናገሩት ፡ አይመስለኝም ፡፡

እኔም ፡ በበኩሌ ፡ ይህን ፡ መልካም ፡ ምክርዎን ፡ በመደገፍ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የሆነ ፡ ኹሉ ፡ አባቶቹ ፡ ባዒ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከመሐመዳውያን ፡ ከእነግራኝ ፡ ባዒ ፡ ሱስንዮስና ፡ ባዒ ፡ ዘድንግልም ፡ ዘመን ፡ ከካቶሊካውያን ፡ ከነአልፎንሱ ፡ ከነመፀልም ፡ ጴጥሮስ ፤ አሁንም ፡ በቅርቡ ፡ ከነአባ ፡ ማስያስ ፡ ከነአባ ፡ ያዕቆብ ፡ ጋራ ፡ እየተጋደሉ ፡ ያቆዩትን ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖቱን ፡ ለመጠበቅ ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ የማይበገር ፡ ምሽግ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ የጠነከረ ፡ አንድነትን ፡ እንዲያገኝ ፡ እየተመኘሁ ፡ ምንም ፡ የማያውቀው ፡ ባይኖር ፡ ኢትዮጵያውያንና ፡ ካቶሊካውያን ፡ የሚለያዩበትን ፡ ባህል ፡ ለመግለጽ ፡ እሞክራለሁ ፡ እርሱዎም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ስለኾኑ ፡ ከዚህ ፡ አድንድነት ፡ እንዳይለዩ ፡ እመኝልዎታለሁ ፡፡

፲፪/ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ስጽፍ ፡ ባይኔ ፡ ፊት ፡ ያደረግሁት ፡ ዓላማ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ የተረሳውን ፡ ክርክር ፡ እንደገና ቀስቅሼ ፡ ለማንሣት ፡ ሳይኾን ፡ ክርክሩ ፡ በጥልቅ ፡ ተመርምሮና ፡ ተጠንቶ ፡ የመግባባት ፡ መንፈስ ፡ እንዲፈጠርና ፡ እንዲነግሥ ፡ ማድረግ ፡ መኾኑን ፡ ላስታውቅ ፤ እፈልጋለሁ ፡

ብለዋል ፡፡

፲፫ / እኛ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በቃልም ፡ ካባቶቻችን ፡ የምንሰማው ፡ በታሪክም ፡ ተጽፎ ፡ የምናነበው ፡ ካቶሊካውያን ፡ በየጊዜው ፡ እየመጡ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለማግባት ፡ መሞከራቸውን ፡ ኢትዮጵያውያንም ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ አናስገባም ፡ በማለት ፡ በመጡበት ፡ አኳኋን ፡ እያሳፈሩ ፡ መመለሳቸውን ፡ ነው ፡፡ አሁን ፡ ግን ፡ እርስዎ ፡ የሚጽፉልን ፡ አጸጻፍ ፡ ካቶሊካውያን ፡ መርታታቸውን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ መረታታቸውን ፡ በጠቅላላው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የነበሩ ፡ ነገሥታቱም ፡ ሊቃውንቱም ፡ ካቶሊካውያን ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ የሚያመለክት ፡ ነው ፡፡

እንግዲህ ፡ የተረሳውን ፡ ክርክር ፡ ለመቀስቀስ ፡ አይደለም ፡ የሚሉ ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ ሳትሰጡ ፡ አዎን ፡ አዎን ፡ ብላችሁ ፡ ተቀበሉኝ ፡ ለማለት ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ የኖረው ፡ ነገር ፡ ተጠቅሶ ፡ መልስ ፡ ሲሰጥበት ፡ ያለክርክር ፡ ይፈጸማል ፡ ብለው ፡ ያስባሉ ፡፡

በእውነቱ ፡ ለዚህ ፡ አነጋገርዎ ፡ ሌላ፡ግምት ፡ ከመስጠት ፡ በቀር ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ልቀበለው ፡ አልቻልኩም ፡፡ የመግባባት ፡ መንፈስ ፡ የሚፈጠርና ፡ የሚነግሥ ፡ ትሕትናን ፡ በተመላ ፡ አነጋገር ፡ እውነተኛውን ፡ የቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ቃል ፡ በመለዋወጥ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ያልኾነውን ፡ ኾነ ፡ ያልተደረገውን ፡ ተደረገ ፡ እያሉ ፡ አስመስሎ ፡ በመጻፍ ፡ አይደለም ፡፡

፲፬/ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ የምታነቡ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡ የድሮ ፡ ዘመናት ፡ መከራከርን ፡ በወገኑ ፡ ትታችሁ ፡ እዚህ ፡ በቀና ፡ አሳብ ፡ እምቀቻችው ፡ ያለሁትን ፡ ማስረጃዎች ፡ በታላቅ ፡ ማስታዋልና ፡ እርጋታ ፡ መርምራችሁ ፡ እውነትከየትኛው ፡ ወገን ፡ ጋራ ፡ እንደምትገኝ ፡ ልትፈርዱ ፡ አደራ ፡ እላችኋለሁ ፡ እውነትን ፡ ካገኛችኋትም ፡ በኋላ ፡ የሰውን ፡ ይሉኝታ ፡ ሳትፈሩ ፡ ያዙዋትና ፡ እመንፈሳዊ ፡ ነፃነት ፡ ላይ ፡ እስክታደርሳችሁ ፡ ድረስ ፡ አትተዋት ፡፡

ብለዋል ፡፡

፲፭ / የድሮ ፡ ዘመን ፡ መከራከርን ፡ በወገኑ ፡ ትታችሁ ፡ ማለት ፡ እርስዎ ፡ የድሮውን ፡ ዘመን መከራከር ፡ ሳያነሱ ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ ቢፈጥሩ ፡ ነበረ ፡፡ በቅን ፡ አሳብ ፡ አመጣኋቸው ፡ የሚሏቸውን ፡ መረጃዎችም ፡ በታላቅ ፡ ማስተዋልና ፡ እርጋታ ፡ ብንመረምራቸው ፤ ያነኑ ፡ የድሮውን ፡ ክርክር ፡ እየጠቀሱ ፤ የካቶሊክን ፡ ባህል ፡ የሚያጐለምሱ ፤ የኦርቶዶክስን ፡ ባህል ፡ የሚያኮስሱ ፡ ኾነው ፡ አግኝተናቸዋል ፡፡ የሰጡባቸውም ፡ አስተያየት ፡ በተውሶ ፡ ያገኙትን ፡ ባህል ፡ ለማጽደቅ ፡ በአድልዎ ፡ የተሰጠ ፡ አስተያየት ፡ እንጂ ፡ ሚዛናዊ ፡ ትክክለኛ ፡ አስተያየት ፡ ኾኖ ፡ አላገኘነውም ፡፡

እንዲህ ፡ እውነተኛ ፡ አስተያየት ፡ አለመኾኑን ፡ ስናውቅ ፡ እርስዎን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ ብቻ ፡ አዎን ፡ እውነትዎ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ካልተቀበልንዎ ፡ በቀር ፡ ተገቢውን ፡ መልስ ፡ የምንሰጥዎ ፡ ከኾነ ፡ ያ ፡ ክርክር ፡ የሚቀርበት ፡ ምን ፡ መንገድ ፡ ይገኛል ፡ ብለው ፡ ያስባሉ ፡፡ ልባችን ፡ እያወቀው ፡ አዎን ፡

አምን ፡ ብንልምትም ፤ እውነት ፡ ከየትኛው ፡ ወገን ፡ ጋራ ፡ እንደምትገኝ ፡ ልትፈርዱ ፡ አደራ ፡ እላች ኋለሁ ፡ ብለው ፡ የጣሉብን ፡ አደራ ፡ ይፈርስብናል ፡ ስለዚህ ፡ በውድም ፡ በግድም ፡ ቢኾን ፡ የክርክሩ ፡ መልስ ፡ የሚቀርብበት ፡ መንገድ ፡ አላገኘንም ።

ኹለተኛም ፡ እውነትን ፡ ካገኘችኋት ፡ በኋላ ፡ የሰውን ፡ ይሉኝታ ፡ ሳትፈሩ ፡ ያዟት ፡ በማለትም ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ እውነተኛነትን ፡ ሳንረዳ ፡ የሰውይሉኝታ ፡ ፈርተን ፡ የያዝናት ፡ አስመ ስለው ፡ ተናግረዋል ። ይህንስ ፡ ነገር ፡ ዮሐንስ ፡ በመልእክቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ በም ፡ ፫ ፡ በቍ ፡ ፪ ፡ አኃዊነ ፡ ይእዜሰ ፡ ደቂቀ ፡ እግዚአብሔር ፤ ንሕነ ፡ ወዓዲ ፡ ኢተዐውቀ ፡ ለነ ፡ ምንተ ፡ ንከውን ፡ ብሎ ፡ እንደ፡ ነገረን ፤ ፍጻሜያችን ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ገና ፡ አልታወቀልንም ፡ እንጂ ፡ ዛሬስ ፡ ኹላችንም ፡ በየበ ኩላችን ፡ እኔ ፡ የያዙኩት ፡ እውነት ፡ ነው ፤ እኔ ፡ በበለጠ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አምነዋለሁ ፡ በማለት ፤ ያነኑ ፡ የያዝነውን ፡ ባህል ፡ ለማጽደቅ ፡ በየበኩላችን ፡ ከመጣጣር ፡ በቀር ፡ ሃይማኖቱን ፡ ለሰው ፡ ይም ሰል ፡ ብሎ ፡ ሰውን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ነኝ ፡ ካቶሊክ ፡ ነኝ ፤ ወይም ፡ ተዋሕዶ ፡ ነኝ ፤ ጸጋ ፡ ነኝ ፤ ቅበዐት ፡ ነኝ ፤ የሚል ፡ ይኖር ፡ አይመስለኝም ። የኾነ ፡ ኾኖ ፡ ይትወላወል ፡ ሰብእ ፡ እም ጊዜ ፡ ልደቱ ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ።

ሰው ፡ ከተወለደበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ ድረስ ፡ ሲያወጣ ፡ ሲያወርድ ፡ ሲያወ ላውል ፡ ይኖራል ፡ እንዲል ፡ (ሃይ ፡ አበ) ፡ ማውጣት ፡ ማውረድ ፡ ይኾንን ፡ አይኾንን ፡ ማለት ፡ የማ ይቀር ፡ ነውና ፡ እርስዎም ፡ በበኩልዎ ፡ እውነትን ፡ የሚፈልጉበት ፡ ቦታ ፡ የታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ መጽ ሐፍ ፡ መኾኑ ፡ ቀርቶ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ መርምረው ፡ እውነት ፡ ከየትኛው ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ እንዲረዱትና ፡ እውነትን ፡ በቅን ፡ ልቡና ፡ እንዲከተሏት ፡ እኔም ፡ በበኩሌ ፡ አደራ ፡ እልዎ ታ ለሁ ።

፲፬/ ይህን ፡ አጭር ፡ መግቢያ ፡ ከመፈጸም ፡ በፊት ፡ ከኹሉ ፡ አስቀድሜ ፡ እጅግ ፡ ለተወደዱ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታችን ፡ ለግር ማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ልግሥና ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ አሳትሜ ፡ ለማውጣት ፡ በገንዘብ ፡ ስላገዙኝ ፡ በታላቅ ትሕትና ፡ አመሰግናቸዋለሁ ፡
ብለዋል ።

፲፭ / እግዚአብሔር ፡ ኹሉም ፡ ፍጥረቱና ፡ ተገዢው ፡ ስለኾነ ፡ ኃጥእ ፤ ጻድቅ ፤ እማኒ ፤ መና ፍቅ ፡ ሳይል ፡ ዕንጨት ፡ ጠርበው ፡ ደንጋይ ፡ አለዝበው ፡ ጣዖት ፡ ለሚያመልኩ ፡ ሰዎች ፡ ሳይቀር መዓልትንና ፡ ሌሊትን ፡ ክረምትንና ፡ በጋን ፡ እንዲያፈራርቅላቸው ፡ ዝናም ፡ ለዘርዕ ፡ ጠል ፡ ለመከር ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ንጉሥም ፡ እግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ አገዛዙን ፡ በጸጋ ፡ የሰጠው ፡ ምስለኔው ፡ እንደ መኾኑ ፡ መጠን ፡ ምንም ፡ ሰው ፡ እንደመኾኑ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የኾነ ፡ የሃይማኖት ፡ ስልት ፡ ቢኖረው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሃይማኖትን ፡ ይዘው ፡ በውስጡ ፡ ለሚተዳደሩት ፡ ሰዎች ፡ የሃይማኖት ፡ መብታቸውን ፡ ጠብቆ ፡ ባስፈላጊው ፡ መንገድ ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ ርዳታ ፡ ማድረግ ፡ የተቀደሰ ፡ ክርስቲያናዊ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ ማናቸውንም ፡ የሃይማኖት ፡ ስልት ፡ ይዞ ፡ በሃይማኖት ፡ ከማይመስለው ፡ ንጉሠ ፡ ሥር ፡ የሚተዳደር ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ችግሩን ፡ ለሚያስተዳድረው ፡ ንጉሥ ፡ ቢያመለክት ፡ በሃይ ማኖት ፡ ተመሳሳይ ፡ አለመሆኑ ፡ ከንጉሡ ፡ የሚደረግለትን ፡ ችሮታ ፡ የሚያስቀርበት ፡ አይደለም ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ሲያሳትሙ ፡ ችግርዎን ፡ ለግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ አመልክተው ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ በተለመደው ፡ ሰፊ ፡ ችሮታቸው ፡ ያደረጉልዎን ፡ የገንዘብ ፡ ርዳታ ፡ ሳይዘነጉ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በማስታወስዎ ፡ አመሰግንዎታለሁ ።

ከዚህም ፡ አያይዘው ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ሲያዘጋጁ ፡ በማንኛውም ፡ ረገድ ፡ ርዳታ ፡ ላደረጉልዎ ፡ ሰዎች ፡ ምስጋና ፡ ማቅረብዎ ፡ ተገቢ ፡ ነገር ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፪

ደራሲው ፡ የተመለከታቸውና ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የጠቀሳቸው ፡ መጻሕፍት ።

### አርእስት ።

፩ኛ ፤ ማስጠንቀቂያ ።
፪ኛ ፤ ምንጮች ፡ አጭር ፡ መግለጫ ።
፫ኛ ፤ መጻሕፍቶች ፡ ናቸው ፡ ብለዋል ።
፩ኛ ፤ ከነዚህ ፡ ከ፫ ፡ አርእስቶች ፡ ለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ መገኛ ፡ ምንጭ ፡ የኾኑትን ፡ መጻሕፍቶች ፡

ብቻ ፡ መርምሮ ፡ የትኞች ፡ መኾናቸውን ፡ ለመረዳት ፡ እፈልጋለሁ ፡ የቀሩትን ፡ አርእስቶች ፡ ግን ፡ መመርመር ፡ አስፈላጊ ፡ መስሎ ፡ አልታየኝም ።

፪/ ይህን ፡ ሥራ ፡ ለማዘጋጀት ፡ በተመለከትናቸው ና ፡ በጠቀስናቸው ፡ መጻሕፍት ፡ በኩል ፡ የተጠቀምንባቸው ፡ ምንጮችና ፡ መጻሕፍቶች ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ብቻ ፡ መኾናቸውን ፡ እናሳስባለን ፡ ስለዚህ ፡ በዚህ ፡ የምናወጣው ፡ የመጻሕፍት ፡ ዝርዝር ተርታ ፡ እኛ ፡ የተመለከትናቸውና ፡ በመጽሐፋችን ፡ ውስጥ ፡ የጠቀስናቸው ፡ ብቻ ፡ ነው ።
ብለዋል ።

፫/ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ለማዘጋጀት ፡ የጠቀሷቸው ፡ መጻሕፍት ፡ አብዛኛዎቹ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ታሪክ ፡ጸሐፊዎች ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥተው ፡ የሃይማኖት ፡ ክርክር ፡አንሥተው ፡ የነበሩ ፡ የኢጣልያ ፡ ተወላጆች ፡ ከጻፏቸው ፡ መጻሕፍት ፡ የተጠቀሰ ፡ መኾኑን ፡ ተረድተናል ።

፬/ በቀጥታ ፡ ለውጥናችን ፡ የማይረዱ ፡ ወይም ፡ ምስክሮች ፡ ያልቁንም ፡ በኢጣልያ ፡ ወረራ ፡ ጊዜ ፡ በችኮላ ፡ የተጻፉትን ጎደሎ ፡ የኾኑትን ፡ መጻሕፍቶች ፡ የወገን ፡ አሳብ ፡ ስለሚገለጥባቸውና ፡ ለመሰበኪያ ፡ ተብለው ፡ በከረምት ፡ እንደሚበቅል እንጉዳይ ፡ የተደረሱ ፡ መኾናቸውን ፡ ስላወቅን ፡ ትተናቸዋል ።

የኢትዮጵያ ፡ ነገሮችን ፡ መርማሪ ፡ የሆነው ፡ ሊቁ ፡ የኢጣልያ ፡ ተወላጅ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ስለነዚህ ፡ መጽሐፎች ፡ ሲናገር ፡ የ፲፱፻፴፭ ፡ ፴፮ ፡ ዓ/ም ፡ ኹኔታዎች ፡ በያይነቱ ፡ መጻሕፍቶች ፡ ኹለተኛ ፡ ሦስተኛ ፡ እስከ ፡ ዐራተኛ ፡ ጊዜ ፡ የታተሙ ፡ የማይረቡ ጥርቅሞች ፡ ከብዙ ፡ ዓመቶች ፡ እንደሚገባቸው ፡ ተረስተው ፡ የነበሩ ፡ እትሞች ፡ እንደገና ፡ እንዲወጡ ፡ አደረጉ ፡ እንዲሁም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲያልፉ ፡ አገሩን ፡ ካዩ ፡ ወይም ፡ ጥቂት ፡ ከተቀመጡበት ፡ በኋላ ፡ የጻፍዋቸው ፡ የችኮላና ፡ የላይ ፡ ላዩ ፡ የኾኑ ፡ ወሬዎች ፡ ታሪኮችን ፡ የያዙ ፡ መጽሐፎች ፡ እንደ ፡ ጥሩት ፡ ወኅ ፡ እንዲጎርፉ ፡ አደረጋቸው ፡ ይላል ፡
ብለዋል ።

፭/ የኢጣልያው ፡ ተወላጅ ፡ ኮንቲ ፡ ሮስኒ ፡ ይህን ፡ በመናገሩ ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ተናግሯል ፤ ይህን ፡ ነገር ፡ እኔም ፡ የምደግፈው ፡ ነኝ ። ምክንያቱም ፡ አንድ ፡ የማውቀው ፡ ነገር ፡ ስላለ ፡ ነው ፤ ባፄ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ እየዞረ ፡ ሀገር ፡ የሚጎበኝ ፡ አንድ ፡ ፈረንጅ ፡ መጥቶ ፡ ነበረ ። ካንዱ ፡ ሀገር ፡ ወዳንዱ ፡ ሀገር ፡ ሲዘዋወር ፡ በያደረበት ፡ መንገድ ፡ የሚመራ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ባላገር ፡ ይታዘዝለታል ። በየመንገዱ ፡ ያገኘውን ፡ እንጨት ፡ ኹሉ ፡ ይህ ፡ ዕንጨት ፡ ስሙ ፡ ማን ፡ ይባላል ፡ እያለ ፡ እየጠየቀ ፡ ይጽፋል ። አንዱን ፡ እንጨት ፡ ይህ ፡ ዕንጨት ፡ ምን ፡ ይባላል ፡ ቢለው ፡ ያ ፡ ባላገር ፡ የዕንጨቱን ፡ ስም ፡ የማያውቅ ፡ ኾኖ ፡ እንጃ ፡ አለው ። ፈረንጁ ፡ ግን ፡ ቋንቋ ፡ ካለማወቁ ፡ የተነሣ ፡ የዕንጨቱን ፡ ስም ፡ የነገረኝ ፡ መስሎት ፡ እንጃ ፡ የሚባል ፡ ዕንጨት ፡ ብሎ ፡ ጽፎ ፡ ሔደ ። ክቡር ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይም ፡ ቋንቋ ፡ ያላወቁ ፡ ሰዎች ፡ የኢትዮጵያን ፡ ታሪክ ፡ ማበላሸታቸውን ፡ ዋዜማ ፡ በተባለው ፡ መጽሐፋቸው ፡ አስታውሰውታል ።

በዚህም ፡ ላይ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ባላጋራነቱ ፡ ታውቆ ፡ ደምሲፋሰስ ፡ የኖረን ፡ የሀገርን ፡ ሕዝብ ፡ አጥቅቶ ፡ ስሙን ፡ ለመደምሰስ ፡ ክብሩን ፡ ለመቀነስ ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ ሲያገኝ ፤ ከቀድሞም ፡ ታሪኩ ፡ የተበላሸ ፡ ነበር ፤ እኛ ፡ አደስነው ፤ ቀደስነው ፡ ብሎ ፡ ለመዋሸት ፡ እንዲመች ፡ ታሪኩን ፡ አበላሽቶ ፡ ስሙን ፡ አጥፍቶ ፡ መጻፍ ፡ የታመነ ፡ ነገር ፡ ስለኾነ ፡ ይህን ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ የተናገረውን ፡ እውነተኛ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ተቀብየዋለሁ ።

እንግዲህ ፡ ወደርስዎ ፡ ጽሑፎች ፡ እንመለስ ። እኚህ ፡ እርስዎ ፡ ተመለከትኳቸው ፡ ተጠቀምኩባቸው ፡ የሚሏቸውም ፡ ጽሑፎች ፡ የተጻፉ ፡ የወረራው ፡ ስልቱ ፡ ልዩ ፡ ይኹን ፡ እንጂ ፡ ሮማውያን ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ላይ ፡ የሃይማኖት ፡ ወረራ ፡ አድርገው ፡ ሊቃውንቶቿና ፡ ምእመናኖቿ ፡ የበረቱት ፡ በሚታረዱበት ፡ የፈሩት ፡ በሚሰደዱበት ፡ ጊዜ ፡ ስለኾነ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ካስታወሳቸው ፡ ጽሑፎች ፡ ልዩነት ፡ አላቸው ፡ ብለን ፡ የምንቀበላቸው ፡ አይደለንም ፤ ምክንያቱም ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ጽፈው ፡ ካቆዩልን ፡ ጽሑፎች ፡ ጋራ ፡ ከመጣላት ፡ በቀር ፡ የማይተባበሩ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ።

፮/ ለዚሁ ፡ ውጥን ፡ ይረዱኛል ፡ ብለው ፡ የጠቀሱዋቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ ፩ኛ ፡ ሰዓታት ፡ ዘሌሊት ፡ ወዘነግህ ፡ ፪ኛ ፡ ክብረ ፡ ነገሥት ። ፫ኛ ፡ መጽሐፈ ፡ ምሥጢር ፡ ፬ኛ ፡ መጽሐፈ ፡ ምሥጢር ፡ ዘሰማይ ፡ ወዘምድር ፤ ፭ኛ ፡ ስንክሳር ፮ኛ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፤ ፯ኛ ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፤ ፰ኛ ፡ ተአምኖተ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘጎላውዴዎስ ፡ ንጉሠ ፡ ኢትዮጵያ ፤ ፱ነኛ ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ፲ረኛ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነገሮች ፡ የጸፉ ፡ ምዕራባውያን ፤ ፲፩ኛ ፡ በሮማ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ የሚገኝ ፡ የላዛሪስቱን ፡ መልእክተኛ ፡ ነገር ፡ የያዘ ፡ ፲፪ኛ ፡ አባ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘመምሳሕ ፡ ፲፫ኛ ፡ ምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ፲፬ኛ ፡ መዝገበ ፡ ሃይማኖት ፡ ፲፭ኛ ፡ ባጭሩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ሊቃውንቶቿ ፡ እንደ ፡ ጻፉት ፡ ፲፮ኛ ፡ አባ ፡ ተስፋ ፡ ሥላሴ ፡ ላዛሪስታ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ የሚል ፡ ማኅተም ፡ የታተመበት ፡ በውስጡ ፡ እስከ ፡ ፳፩ ፡ ክፍል ፡ የደረሰ ፡ ልዩ ልዩ ፡ አንቀጽ ፡ ያለው ፡ ፲፯ኛ ፡ ቅኔ ፡ ፲፰ኛ ፡ አሥመራ ፡ የሚታተም ፡ የካቶሊካውያን ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፱ነኛ ፡ ፍኖተ ፡ ብርሃን ፡ የተባለ ፡ ወርኃዊ ፡ ጋዜጣ ፡ ፳ ፡ አባ ፡ ጋስፒሪኒ ፡ ገ ፡ ማ ፡ የጻፉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፤ እንደኾኑ ፡ ገልጸዋል፤ሌሎችም ፡ እኒህን ፡ የመሳሰሉ ፡ አይታጡም ።

፩ ከውጭ ፡ ሀገር ፡ ተጸፉ ፡ ለሚሏቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ያለኝ ፡ አስተያየት ፡ በዚሁ ፡ በያዝነው ፡ ምዕራፍ ፡ በ፪ና ፡ በ፫ ፡ ቍጥር ፡ እንደ ፡ ገለጽኩት ፡ ነው ።

ከኢትዮጵያ ፡ ተገኙ ፡ ስለሚሏቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ግን ፡ ደገኛው ፡ የቃል ፡ ሥጋ ፡ ኾነ፡ ምሥጢር፡ የተመሠረተ ፡ እናንተም ፡ እኛም ፡ በማንንቅፋቸው ፡ አክብረን ፡ በተቀበልናቸው ፡ በብሉያት ፡ በሐዲሳት ፡ ነው ።

፪ተኛም ፡ በብሉይ ፡ በሐዲስ ፡ የተነገሩትን ፡ ቃላት ፡ የረቀቀውን ፡ አጉልተው ፡ የተሰወረውን ፡ አፍታተው ፡ የሚያስረዱ ፡ ስለኾኑ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በደንብ ፤ ተቀብላ ፡ ስታነባቸው ፡ ስትተረጕማቸው ፡ የሚኖሩ ፡ መጻሕፍት ፡ ሊቃውንት ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ አፈወርቅ ፤ ቄርሎስ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፤ መጽሐፈ ፡ ቅዳሴ ፤ እንዲሁም ፡ መጻሕፍተ ፡ መነኮሳት ፤ ፊልክስዩስ ፤ ማሬ ፡ ይስሐቅ ፡ አረጋዊ ፡ መንፈሳዊ ፡ ናቸው ።

ከነዚህ ፤ ዘለው ፡ ደገኛውን ፡ የቃል ፡ ሥጋ ፡ ኾነን ፡ ምሥጢር ፡ በታሪክ ፡ መጻሕፍቶችና ፡ በቅኔዎች ፡ እንዲሁም ፡ በጋዜጦች ፡ ላስረዳ ፡ ማለትም ፡ እጅግ ፡ ያሳዝናል ፡ ፭ዱ ፡ የተባለውን ፡ አጋዝ ፡ ለክርስቶስ ፡ እየቀጸለ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፩ ፡ ባሕርይ ፡ ፩ ፡ ህላዌ ፡ አሐቲ ፡ ጠባይዕ ፡ ፩ ፡ አካል ፡ የሚል ፡ ንባብ ፡ አሁን ፡ በጠቀስኳቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ኹሉ ፡ በብዛት ፡ ይገኛል ።

ይህ ፡ የጀመሩት ፡ ውጥን ፡ እውነተኛ ፡ ኾኖ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ የምትል ፡ መኾኗን ፡ በኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ የሚያስረዱ ፡ ከኾነ ፡ አሁን ፡ ከጠቀስኳቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ክልኤቱ ፡ የሚል ፡ አጋዝ ፡ ለክርስቶስ ፡ ቀጽሎ ፡ ፪ቱ ፡ ባሕርይ ፡ ፪ቱ ፡ ጠባይዕ ፡ ፪ቱ ፡ ፈቃድ ፡ የሚል ፡ ንባብ ፤ አይጠቀሱም ፡ ነበርን ፤ ውጥንዎ ፤ እውነት ፡ አለመኾኑን ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ያስረዳል ፡ በእኛ ፡ ዘንድስ ፡ ስንኳን ፡ እኒህ ፡ የጠቀስኳቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ሌሎችም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ አገኘኋቸው ፡ የሚሏቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ቅኔዎች ፡ ሳይቀሩ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ከማለት ፡ የወጡ ፡ አይደሉም ። እርስዎ ፡ ግን ፡ የግእዝና ፡ የአማርኛን ፡ ስልት ፡ ጠንቅቀው ፡ ካለማወቅዎ ፡ የተነሣ ፡ ሌላ ፡ ትርጉም ፡ ሊሰጧቸው ፡ ይሞክራሉ ፡ ይህንንም ፡ ስንደርስበት ፡ አስረዳዎታለሁ ።

፭/ በታሪክ ፡ ነገሮች ፡ ዓመተ ፡ ምሕረቱን ፡ ዕለቱን ፡ አስተካክለው ፡ ከማያመጡ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ ይልቅ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነገር ፡ መርማሪዎች ፡ የጻፉትን ፡ መረጥኩ ፡
ብለዋል ።

፮ / ኤውሮፓውያንና ፡ እኛ ፡ በቍጥር ፡ ምንም ፡ ባንገናኝ ፡ ሒሳቡ ፡ ከዚያው ፡ የማይወጣ ፡ ከዚያው ፡ የሚያደርስ ፡ ስለኾነ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ የምቃወመው ፡ የለኝም ።

## ም ዕ ራ ፍ ፡ ፫ ።

በኢትዮጵያ ፡ የሚታመነው ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ መንሻና ፡ ምክንያት ።

ለዚህ ፡ እንቀጽ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የኾኑ ፡ ፰ ፡ አርእስቶች ፡ ሰጥተውታል ። መልሳቸውን ፡ በየአርእስቶቹ ፡ ለይተን ፡ ለይተን ፡ እንሰጥበታለንና ፡ ጠንቅቀው ፡ ይመልከቱ ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሮማ ፡ የተለየችበት ፡ ምክንያት ፡ አርእስቶች

፩/ የትምህርት ፡ ልዩነት ፡ ነውን

፪/ እውነተኛው ፡ ምክንያት

፫/ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በእስክንድርያ ፡ መንበረ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ስለመመራቷ ፡

፬/ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይመጣ ፡ ስለነበረው ፡ ግብጻዊ ፡ ጳጳስ ፡ ሥራና ፡ ሥልጣን ፡

፭/ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ውስጥ ፡ ስላላቸው ፡ ሥልጣን

፮/ ስለ ፡ ዕጨጌ ።

፩/ በኢትዮጵያ ፡ የሚታመነው ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ አስቀድሞ ፡ ሳያውቁት ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ መኾኑን ፡ ጠንቅቆ ፡ ለመረዳት ፡ አስቸጋሪ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ የማይቻል ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ምርመራውን ፡ ከመጀመር ፡ በፊት ፡ ያለፉትን ፡ የታሪክ ፡ ኹኔታዎች ፡ ማየት ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ይህ ፡ ቢደረግ ፡ ስለኹለቱ ፡ የክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ መዋሐድ ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በተወሰነው ፡ ትምርት ፡ ፊት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያላት ፡ አስተያየት ፡ እያያዘ ፡ የሚለውን ፡ የንግግራችንን ፡ እርእስት ፡ በትክክል ፡ ለመወሰን ፡ ይረዳናል ፡

ብለዋል ።

፩ / ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ከ፬፻፶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ መኾኑ ፡ ሲታወቅ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ተነሣ ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ እንግዳ ፡ ደራሽ ፡ አስመስሎ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ተነሣ ፡ ብሎ ፡ መጻፍ ፡ እንደ ፡ ማደናገርና ፡ እንደ ፡ ማሳሳት ፡ የሚቆጠር ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ነገሩስ ፡ እውነት ፡ ነው ። ማናቸውም ፡ ነገር ፡ ቢኾን ፡ ሥሩ ፡ መነሻው ፡ ካልታወቀ ፡ ጫፉን ፡ ይዞ ፡ ተነሥቶ ፡ መልስ ፡ ልስጥበት ፡ ቢሉ ፡ መልሱ ፡ የተበላሸ ፡ መኾኑ ፡ አይከድም ። ስለዚህ ፡ ወደኋላ ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡ ያለፈውን ፡ ታሪክ ፡ መመልከት ፡ ተገቢ ፡ ነገር ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ ላሰብኩት ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ ያስገኝልኛል ፡ ብሎ ፡ ያለፈውን ፡ ታሪክ ፡ እውነተኛውን ፡ መንገዱን ፡ አስለቅቆ ፡ ልብ ፡ በወደደው ፡ መንገድ ፡ ቢመሩት ፡ አተኩሮ ፡ የሚመለከተው ፡ ሰው ፡ ሲያገኝ ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ኾኖ ፡ መቅረቱን ፡ እንዳይዘነጉ ፡ ስል ፡ በትሕትና ፡ አስገነዝብዎታለሁ ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

## የትምህርት ፡ ልዩነት ፡ ነውን? ።

፪/ ከላይ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ ከ፮ቱ ፡ አርእስቶች ፡ ባንደኛው ፡ አርእስት ፡ የትምርት ፡ ልዩነት ፡ ነውን ፡

ብለው ፡ ጥያቄ ፡ አቅርበዋል ።

፪ / አሁን ፡ እርስዎ ፡ በሚቀጥሉት ፡ መሥመሮች ፡ የክብር ፡ መበላለጥ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ እስታወሱን ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ እንደምናውቀውስ ፡ የትምህርትና ፡ ያነጋገር ፡ መለያየት ፡ ነው ።

፫/ ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ ተለይታ ፡ የምትገኝበትና ፡ ሌሎች ፡ የምሥራቅ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የተለዩበት ፡ ምክንያት ፡ አንድ ፡ አደለም ። ክርስቶስ ፡ የተከላትን ፡ ማኅበር ፡ አንድነቷን ፡ በታትኖ ፡ ያስኰፋቁና ፡ መለያየት ፡ የትምርት ፡ ልዩነት ፡ ነው ፡ መባሉ ፡ የማይረባ ፡ ማማሃኛ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ምክንያት ፡ አይደለም ፡ እውነተኛውስ ፡ ምክንያት ፡ አንዳንዶቹ ፡ የምሥራቅ ፡ አበምኔቶችና ፡ ፓትርያርኮች ፡ በክብር ፡ ፍላጎት ፡ ተንተንተው ፡ ከሮማው ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ጋራ ፡ የመበላለጥና ፡ የመወዳደር ፡ መንፈስ ፡ አድሮባቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እናውቃለን ፡

ብለዋል ።

፫ / ይህ ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ የሚያሳዝን ፡ ነው ፡ ኢትዮጵያ ፡ በዚህ ፡ ውስጥ ፡ የለችም ፡ ቢሉም ፡ በሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ በሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ መበላለጥ ፡ መመርመር ፡ አስፈላጊ ፡ ኾኖብኛል ።

ምናልባት ፡ የምሥራቅ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ከሮሙ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ እንወዳደር ፡ ቢሉ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አንትሙሰ ፡ ኢትሰመዩ ፡ ረቢ ፡ እስመ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ መምህርክሙ ፡ ወአንትሙሰ ፡ አኃው ፡ ኵልክሙ ፡ ወኢትረስዩ ፡ አበ ፡ በዲበ ፡ ምድር ፡ እስመ ፡ ፩ዱ ፡ ውእቱ ፡ አቡክሙ ፡ ሰማያዊ ፡ ወኢትሰመዩ ፡ መምህራነ ፡ እስመ ፡ ፩ ፡ ውእቱ ፡ መምህርክሙ ፡ ክርስቶስ ።

እናንተስ ፡ ኹላችሁም ፡ ወንድማማቾች ፡ ናችሁ ፡ ስለዚህ ፡ አባታችሁ ፡ አንዱ ፡ ሰማያዊ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለኾነ ፡ ምድራዊ ፡ አባት ፡ አታብጁ ፡ መምህራችሁም ፡ አንድ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነውና ፡ ምድራዊ ፡ መምህር ፡ አለን ፡ አትበሉ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ይገድፋቸው ፡ ይኾናል ፡ ማቴ ፡ ፳፫ ፡

ኟ ፡ ኸረ ፡ የሮሙ ፡ ርእስ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ እኔ ፡ ከበላያችሁ ፡ ልኹንና ፡ እናንተ ፡ እግሬን ፡ እያሻ ችሁ ፡ ከበታቼ ፡ ተቀመጡና ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ በሉኝ ፡ የሚልበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድን ፡ ነው ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘይፈቅድ ፡ እምኔክሙ ፡ ይኩን ፡ ሊቀ ፡ ይኩንክሙ ፡ ላእከ ።
ከናንተ ፡ አለቃ ፡ ሊኾን ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ አገልጋይ ፡ ተላላኪ ፡ ይኹንላችሁ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፡ እንጂ ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ ሰርም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ይገዛ ፡ ብሏልን ፡ አላለም ።

ምናልባት ፡ ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ ረዐይኬ ፡ አባግዕየ ፤ ረዐይኬ ፡ መሐስዕየ ፡ ብሎ ፡ መላልሶ ፡ የሾመው ፡ የቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ መንበር ፡ ስለኾነች ፡ ነው ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ይቀርብለት ፡ ይኾናል ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥ ሮስና ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ሮማ ፡ ገብተው ፡ ወንጌልን ፡ ቢያስተምሩ ፡ የቍልቍሊት ፡ ሰቅላ ፡ በሰይፍ ፡ መትራ ፡ ገላቸዋለች ፡ እንጂ ፡ አክብራ ፡ ተቀብላቸዋለችን ፡ አልተቀበለቻቸውም ።

ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በግፍ ፡ ብትገላቸውም ፡ ዐፅማቸው ፡ ያረፈበት ፡ ቦታ ፡ ስለኾነች ፡ ልትከ በር ፡ ይገባታልና ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ የተሾመው ፡ ከኹሉ ፡ በላይ ፡ ሊኾን ፡ ይገባዋል ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ይከተል ፡ ይኾናል ።

ይህም ፡ የሚያስከብር ፡ ከኾነ ፡ እግዚአ ፡ ጴጥሮስ ፡ አምላከ ፡ ጴጥሮስ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተ ሰቀለባት ፡ የተቀበረባት ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ከኹሉ ፡ በላይ ፡ ተከብራ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሷ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ መባል ፡ በተገባው ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሊላክ ፡ ሊያገለግል ፡ እንጂ ፡ ሊላኩት ፡ ሊያገለግሉት ፡ አልመጣምና ፡ እናንተስ ፡ ኹላችሁም ፡ ወንድማማች ፡ ናችሁ ፡ ብሎ ፡ ትክክለኝነትን ፡ ከማስተማር ፡ በቀር ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ ይገዛ ፡ አላለም ።

እንግዲህ ፡ አሁን ፡ እንደ ፡ መረመርነውና ፡ እንደ ፡ ተረዳነው ፡ ይህ ፡ መለያየት ፡ የመጣ ፡ በት ምርት ፡ ልዩነት ፡ ሳይኾን ፡ በክብር ፡ ፍላጎት ፡ ነው ፡ ካሉ ፡ የሮም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ክብሯን ፡ ለመ ጠበቅ ፡ ስትል ፡ የክርስቶስን ፡ መንጋዎች ፡ እንደ ፡ በታተነቻቸው ፡ ታውቀ ፡ ተረዳ ፡ ማለት ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ የምሥራቅ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ከሮም ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ጋራ ፡ ትክክለ ኝነት ፡ ቢያገኙ ፡ አይለያዩም ፡ ነበረ ፡ የሚል ፡ ስሜት ፡ ስላሳደረብን ፡ ነው ።

፮/ ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስትለይ ፡ ግን ፡ ታሪኳን ፡ ብንመለከተው ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ አናገኝበትም ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ ትምርት ፡ ለመለየት ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማዋን ፡ አምርታ ፡ የተነሣችበት ፡ ጊዜ ፡ መቼውንም ፡ አይታወቅም ፡ ምናልባት ፡ በ፲፮ኛ ፡ ፻ ፡ ዓ/ም ፡ የፖርቱጋል ፡ ካቶሊክ ፡ መልክተኞች ፡ ፈጽመው ፡ የተባረሩበትን ፡ ሰዶት ፡ በማስታወስ ፡ ካህ ኑም ፡ ዓለሙም ፡ ተባብሮ ፡ የካቶሊክን ፡ ሃይማኖት ፡ ያስወገደበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ለማሰብ ፡ የሚ ፈትን ፡ ይገኝ ፡ ይኾናል ፡ ብለው ፡ እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ በሚያጠራጥር ፡ ጉዳና ፡ መርተውታል ።

ይህንም ፡ በሚያጠራጥር ፡ ጉዳና ፡ ያመጡትን ፡ ሐሳብ ፡ እውነተኛ ፡ ለማስመሰል ፡ ቢሉ ፡ የእውነት ፡ መሠረት ፡ ያላቸው ፡ ጸሐፊችና ፡ ምስክሮች ፡ መልክተኞችን ፡ ካስወገዱ ፡ ምክንያቶች ፡ ውስጥ ፡ የሃይማኖት ፡ ልዩነት ፡ በፍጹም ፡ አለመገኘቱን ፡ ያረ ጋግጣሉ ፡ ብለው ፡ እነዚህን ፡ ጸሐፊች ፡ ሲዘረዝሩ ፡ ፩ኛ ፡ መልክተኞቹን ፡ ያባረረው ፡ ንጉሥ ፡ ፋሲል ፡ ለአልፎንሱ ፡ በሰጠው ፡ መልስ ፡ በኢትዮጵያውያንና ፡ በመልክተኞቹ ፡ መካከል ፡ ዋና ፡ የክርክር ፡ ምክንያት ፡ ኾና ፡ ስለነበረው ፡ ስለክርስቶስ ፡ ኹለት፡ ባሕርያት ፡ ነገር ፡ ሲናገር ፡ በግልጥ ፡ መልእክተኞቹ ፡ ይሰብኩት ፡ በነበረውና ፡ ኢትዮጵያውያኖቹ ፡ በሚያምኑት ፡ ትምህርት ፡ መሐከል ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ የለም ፡ ብሏል ።

ከመልክተኞቹ ፡ ጋራ ፡ ላለመስማማትና ፡ እነርሱ ን ፡ ለማባረር ፡ ዋና ፡ ምክንያቶች ፡ ከትምርት ፡ አለመስማማት ፡ በፍጹም ፡ ልዩ ፡ የኾኑ ፡ ሌሎች ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ፡ እነዚኽውም ፡ ለምእመናን ፡ በወይን ፡ ጠጅ ፡ መልክ ፡ አለማቍረባቸው ፡ ግጽውን ፡ መለወጣቸው ፤ ጥምቀትንና ፡ የክህነትን ፡ ማዕርግ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መስጠታቸው ፡ ይህንንም ፡ የመሳሰሉ ፡ ሌሎች ፡ መኾናቸውን ገልጠዋል ። ብለዋል ።

፱ / መለያየትን ፡ መገናኘት ፡ ይቀድመዋል ፡ ኸረ ፡ ለነገሩ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ የተለየችበት ፡ ጊዜ ፡ መቼ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የሚጠይቁ ፡ አስቀድሞ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ሮማ ፡ በፍቅር ፡ የተገናኙበት ፡ ጊዜ ፡ አለን ። የጠቀሷቸው ፡ መረጃዎች ፡ ኹሉ ፡ በጥል ፡ መገናኘታቸውን ፡ እንጂ ፡ በፍቅር ፡ መገና ኘታቸውን ፡ አያስረዱም ።

(ሀ) የፖርቱጋል ፡ ካቶሊክ ፡ መልክተኞች ፡ መባረራቸውን ፡ እያመኑ ፡ ካህኑም ፡ ዓለሙም ፡ ተባብሮ ፡ አላባረራቸውም ፡ ብለው ፡ የሰጡት ፡ ግምት ፡ ኹሉም ፡ ተባብሮ ፡ ያባረራቸው ፡ መኾኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ ስለኾነ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ግምት ፡ ነው ።

(ለ) ንጉሥ ፡ ፋሲል ፡ መልክተኞች ፡ ይሰብኩት ፡ በነበረውና ፡ ኢትዮጵያውያኖቹ ፡ በሚያም ኑት ፡ ትምህርት ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ የለም ፡ ብሏል ፡ ለሚሉት ፡ ዓፄ ፡ ፋሲል ፡ ይህን ፡ መናገራቸ ውን ፡ እኛ ፡ አናውቅም ። ምናልባት ፡ እርስዎ ፡ እንዳሉትም ፡ ዓፄ ፡ ፋሲል ፡ ይህን ፡ ተናግረው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ነገሩ ፡ የተቀራረበ ፡ መስሏቸው ፡ የራሳቸውን ፡ አስተያየት ፡ ተናግረው ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በመባባል ፡ ተከራክረው ፡ ካቶሊኮች ፡ አልተባረሩም ፡ አላሉም ።

(ሐ) ከመልክተኞቹ ፡ ጋራ ፡ ላለመስማማትና ፡ እነርሱን ፡ ለማባረር ፡ ምክንያት ፡ የኾኑ ፡ ሌሎችም ፡ አሉ ፡ ስለሚሉት ፡ እኒህ ፡ ምክንያቶች ፡ አንድ ፡ ባሕርይና ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በመባባል ፡ ለተነሣው ፡ ክርክር ፡ ማዳበሪያ ፡ መኾናቸውን ፡ ያስረዳል ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ሮማ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ መስማማታቸውን ፡ አያስረዳም ። ቀድሞ ፡ በፍቅር ፡ መገናኘትና ፡ መስማማት ፡ ሳይኖር ፡ መቸ ፡ ተለያዩ ፡ ብሎ ፡ መጠየቅ ፡ ማጭበርበር ፡ ማስመሰል ፡ ማደናገር ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ጥያቄ ፡ አይደለም ።

፮/ እንግዲህ ፡ በሙሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ይህች ፡ ከሮማ ፡ ተለይታ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለፍዋን ፡ ወይም ፡ በግልጥ ፡ እርሱን ፡ መቀበሏን ፡ የሚያስረዳ ፡ ወይም ፡ የተለየችበትን ፡ ጊዜና ፡ ዘመን ፡ የሚነግር ፡ ጽሑፍ ፡ አይገኝም ፡ ብለዋል ።

፯/ በውነቱ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ማደናገርን ፡ ያዘለ ፡ ንግግር ፡ ነው ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ ወንጌልን ፡ ካስተማረበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ ድረስ ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ባሉ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ኹሉ ፡ ሮማም ፡ ሳትቀር ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ብቻ ፡ ሲነገር ፡ ኖሮ ፡ በጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ ጊዜ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ መፈጠሩ ፡ የማይካድ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ይህንም ፡ ርስዎ ፡ ራስዎ ፡ ሲያስረዱ ።

(ሀ) ፈተኞቹ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ያስተምራሉ ፡ ኹለተኞች ፡ ግን ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ሲሉ ፡ ያስተምራሉ ፡ ብለው ፡ በገጽ ፡ ፲፪ ፡ መሥመር ፡ ፩ና ፡ ፪ ፡ መስክረዋል ።

(ለ) ይህንኑ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ከጉባኤ ፡ ኒቅያ ፡ በኋላ ፡ በ፫፻፶፩ ፡ ወይም ፡ በ፫፻፸፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ግድም ፡ በጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ከመፈጠሩ ፡ በፊት ፡ ፍሬምናጦስ ፡ ከእስክንድርያ ፡ አምጥቶ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሰበከላትና ፡ እንደተቀበለችው ፡ በገጽ ፡ ፶፬ ፡ አረጋግጠው ፡ መስክረዋል ። በገጽ ፡ ፶፯ም ፡ ይህንኑ ፡ ደግመው ፡ መስክረዋል ።

(ሐ) ኢትዮጵያ ፡ ከእስክንድርያ ፡ በተቀበለችው ፡ ባንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ጸንታ ፡ የኖረች ፡ መኾኗንም ፡ በክርስትናዋ ፡ አዲስ ፡ የነበረችው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በፊት ፡ ይታመን ፡ የነበረውን ፡ መምህራንና ፡ ሊቃውንት ፡ በተራቀቀ ፡ መርምረውት ፡ በኋላ ፡ አነጋገር ፡ ያልተወሰነውን ፡ የሃይማኖት ፡ ትምርት ፡ ይዛ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ቆመች ፡ ቀረች ። ስለዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለ ፡ አካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ ትምህርት ፡ ዛሬም ፡ ቢኾን ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነውን ፡ ትምህርት ፡ ሳትቀበል ፡ ከጉባኤው ፡ በፊት ፡ ከዛሬው ፡ ልዩ ፡ በኾነና ፡ ባረጀ ፡ አነጋገር ፡ ይታመንበት ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ታምናለች ፡ እንጂ ፡ አነጋገሯን ፡ በተራቀቀ ፡ አሻሽላ ፡ ከቀድሞው ፡ ዘመን ፡ ምንም ፡ አለወጠችም ፡ ብለው ክርስትናን ፡ ከተቀበለችበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምራ ፡ አሁን ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ እስከ ፡ ጻፉበት ፡ ፲፱፻፶፩ ዓ ፡ ም ፡ ድረስ ፡ ካንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ያልተናወጠች ፡ መኾኗን ፡ አረጋግጠው ፡ መስክረዋል ፡ ገጽ ፡ ፩ ።

(መ) የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ የምታምነው ፡ ትምህርት ፡ ባሳቡና ፡ ባገላለጡ ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በፊት ፡ ልክ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ኹሉ ፡ ያምኑት ፡ እንደነበረው ፡ ነው ። ይህም ፡ ትምህርት ፡ ለንስጥሮስ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ለአውጣኪም ፡ ባህል ፡ ፈጽሞ ፡ ተቃራኒ ፡ በመኾኑ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ካስተማረውና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በደምብ ፡ ባትወስነው ፡ በዠሉ ፡ ዘንድ ፡ ይታመን ፡ ከነበረው ፡ ትምህርት ፡ ፈጽሞ ፡ የተስማማ ፡ ነው ፡ ብለዋል ፡ ገጽ ፡ ፭፩ ።

(ሠ) ሮማና ፡ ኢትዮጵያ ፡ መቸም ፡ ቢኾን ፡ ከጥል ፡ በቀር ፡ ፍቅር ፡ የሌላቸው ፡ መኾናቸውን ፡ ሲያረጋግጡ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቅ ፡ ሰላም ፡ አልብነ ፡ ምስለ ፡ ሰብአ ፡ ሮሜ ፡ ወለሰብአ ፡ ሮሜ ፡ ምስሌነ ፡ ኢሀለዎሙ ፡ ሰላም ፡ የሚለውን ፡ መወድስ ፡ ቅኔ ፡ በገጽ ፡ ፲፭ ፡ ጠቅሰውልናል ።

እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ጥያቄዎ ፡ ሕጋዊ ፡ እውነት ፡ ጥያቄ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ በፊት ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ በፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ተቀብላ ፡ እስከ ፡ ዛሬም ፡ በዚያው ፡ ጸንታ ፡ እንዳለችና ፡ ከሮምም ፡ ጋራ ፡ ከመጀመሪያ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ በጸብ ፡ ላይ ፡ ያለች ፡ መኾኗን ፡ እንዲህ ፡ መላልሰው ፡ እንዳስረዱ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይንም ፡ ባህል ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ተቀበለች ፡ ብለው ፡ ባስረዱ ፡ ነበረ ። ጥያቄዎ ፡ እውነትን ፡ የጨበጠ ፡ ሕጋዊ ፡ አለመኾኑ ፡ በዚህ ፡ ይታወቃል ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ጥያቄዎ ፡ ምናልባት ፡ እንዲህ ፡ እንደርስዎ ፡ የሀገሩን ፡ ሥርዓት ፡ አምልኮና ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ አስቀድሞ ፡ ሳያጠና ፡ ወደ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ የተሳበ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ለካስ ፡ ኢትዮጵያ ቀድሞ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ ኖራለችሳ ፡ የሚል ፡ ጥርጣሬ ፡ ለማሳደር ፡ ብቻ ፡ ይጠቅምዎ ፡ እንደ ፡

ኾነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ውስጡን ፡ ገብቶ ፡ ሲያዩትስ ፡ እንዲህ ፡ ፍሬቢስ ፡ ኾኖ ፡ ይገኛል ።

## ፪ኛ ፡ ክፍል ።

## ዕውነተኛው ፡ ምክንያት ።

፩/ ይሁን ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡ ኢትዮጵያም ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተለይታ ፡ መገኘቷ ፡ የማይካድ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ የፈጠሩና ፡ ወደ ፡ ርሱም ፡ ያደረሷት ፡ ምክንያቶች ፡ የቶቹ ፡ ናቸው ፡ በማለት ፡ ጥያቄዎን ፡ ቀጥለዋል ።

፩ / የዚህ ፡ ጥያቄ ፡ መልሱ ፡ አጭር ፡ ነው ፤ እውነተኛው ፡ ምክንያት ፡ ሮማ ፡ ከመጻሕፍት ፡ ሳይኾን ፡ በይመስላልና ፡ በያሰኛል ፡ ብቻ ፡ በሐሳቧ ፡ ገምታ ፡ የወሰነችውን ፡ የ፪ ፡ ባሕርይ ፡ ባህልና ፡ ሌሎችንም ፡ ውሳኔዎቿን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባለመቀበሏ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፪/ ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ ተለይታ ፡ የምትገኘው ፡ ሳታውቀውና ፡ ሳትፈልገው ፡ ነው ። ብለዋል ።

፪ / ኢትዮጵያ ፤ ከሮማ ፡ ጋራ ፡ ጠቡን ፡ ካልፈለገችው ፡ ሮማ ፡ በየጊዜው ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ ለማለት ፡ አቋርጣ ፡ አታውቅም ። መጥታም ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ያልተገኘ ፡ በይመስላልና ፡ በያሰኛል ፡ ብቻ ፡ የተመሠረተ ፡ ባህሏን ፡ ለመንዛት ፡ መሞከሯ ፡ አልቀረም ። ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ በተገኘ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ በመጣችበት ፡ ዐይነት ፡ መልስ ፡ እየሰጠች ፡ ለምን ፡ ትመልሳታለች ? በፍቅር ፡ አትቀበላትም ፡ ኖሯልን ይህ ፡ ንግግር ፡ ከስሕተት ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ስሕተት ፡ ነውና ፡ ያርሙት ።

፫/ ከዚህ ፡ ጉዳት ፡ ላይ ፡ ያደረሳት ፡ ከሮማ ፡ በጣም ፡ መራቋ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

፫ / ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ፡ብትለይ ፡ ያገኛት ፡ ጉዳት ፡ ምንድነው ፡ ባትለይስ ፡ ታገኘው ፡ የነበረው ፡ ጥቅም ፡ ምንድነው ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ያው ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ ያወቀው ፡ የሮማ ፡ ምኞት ፡ ሳይፈጸም ፡ ቀረ ፡ ብለው ፡ ከሚሰማዎ ፡ ኃዘን ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የሚያሳስብዎ ፡ ነገር ፡ የለም ።

፬/ ከእውነተኛይቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፈጽመው ፡ ለመለየቷ ፡ ሲሉ ፡ እስላሞችና ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ የፈጠሩባት ፡ ብዙዎች ፡ የውጭ ፡ ችግሮች ፡ ናቸው ፡ ብለዋል ።

፬ / የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ተለይታ ፡ እውነተኛ ፡ የምትኾንበት ፡ ሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሐሰተኞች ፡ የሚኾኑበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድነው ፡ ካቶሊክ ፡ በመባሏ ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ ሌላ ፡ ምክንያት ፡ አላት ፡ ካቶሊክ ፡ በመባሏ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ካቶሊክ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ማለት ፡ የግሪክ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ። ትርጓሜውም ፡ ካቶሊክ ፡ ማለት ፡ እንተ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ጉባኤ ፡ ዘሐዋርያት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ኦርቶዶክስም ፡ ማለት ፡ ርትዕት ፡ ሃይማኖት ፡ ማለት ፡ ነው ።ወደ ፡ አማርኛም ፡ ቢመልሱት ፡ እንተ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ጉባኤ ፡ ዘሐዋርያት ፡ ማለት ፡ በሐዋርያት ፡ ስብከት ፡ ያመነች ፡ የተሰበከች ፡ ከኹሉ ፡ በላይ ፡ ያለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ማለት ፡ ነው ።

ይህም ፡ ምሥጢሩ ፡ በሐዋርያት ፡ ትምህርት ፡ በክርስቶስ ፡ አምኖ ፡ ክርስቲያን ፡ የተባለውን ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ኦድርጎ ፡ አጠቃሎ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አማልክትን ፡ ያመልኩ ፡ ከነበሩ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ በላይ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ ታላቅና ፡ ታናሽ ፡ አለ ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ርትዕት ፡ ሃይማኖት ፡ ማለትም ፡ የቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ ማለት ፡ ነው ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ (ካቶሊክ ፡ መባል ፡ የሚገባው ፡ ኦርቶዶክስነትን ፡ ማለት ፡ የቀናች ፡ ሃይማኖትን ፡ ይዞ ፡ ለሚገኝ ፡ ክርስቲያን ፡ ኹሉ ፡ ነው ፤ እንጂ ፡ ላንድ ፡ ክፍል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብቻ ፡ የተሰጠ ፡ ስም ፡ ወይም ፡ የመዓርግ ፡ ስም ፡ አይደለም ፤ ስለዚህ ፡ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ብትኾን ፡ ኦርቶዶክስነትን ፡ ማለት) ፡ ርትዕት ፡ ሃይማኖትን ፡ ከለቀቀች ፡ ካቶሊክ ፡ መባል ፡ አይገባትም ።

ከሮማ ፡ የለዩዋት ፡ እስላሞችና ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ናቸው ፤ ያሉትም ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው፡ርሷ፡ራሷ፡ተመራምራ፡ ይህ ፡ ባህል ፡ በያሰኛል ፡ በይመስላል ፡ የመጣ ፡ ከመጻሕፍት ፡ ያልተገኘ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ ብላ ፡ ብትንቅፈውና ፡ ባትቀበለው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ፈቃደኛማ ፡ ከኾነች ፡ ርሷ ፡ ራሷ ፡ ሮማ ፡ መሔድ ፡ ባይቻላት ፡ በየጊዜው ፡ ከዚህ ፡ ድረስ ፡ እየመጡ ፡ የሚጎተጉቷትን ፡ ካቶሊካውያንን ፡ ለምን ፡ ታባርራቸዋለች ፡ አክብራ ፡ አትቀበላቸውም ፡ ኖሯልን ።

፭/ ይህ ፡ የምንለው ፡ ታሪኩን ፡ በመመርመር ፡ ኾነ ፡ እንዲሁም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተለይታ ፡ በነበረችበት ፡ ዘመናት ፡ ውስጥ ፡ ቀነሥታቷ፡አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ምዕራብና ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ሊልኳቸው ፡ የቻሉ ፡ መልእክተኞች ፡ በተናገሩዋቸው ፡ ቃሎች ፡ መሠረት ፡ እውነት ፡ መኾኑ ፡ ይታወቃል ፡ ብለዋል ።

፲ / ታሪኳን ፡ በመመርመር ፡ ያሉት ፡ ይህ ፡ ታሪክ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የማታውቀው ፡ ካቶሊካውያን ፡ የጸፉት ፡ ታሪክ ፡ በመኾኑ ፡ ልንቀበለው ፡ አንችልም ። መልእክተኞቿ ፡ ተናገሩት ፡ ለሚሉት ፡ ከበታው ፡ ከንግግሩ ፡ ላይ ፡ ስንደርስ ፡ መልስ ፡ እንሰጥበታለን ፡ ይቆይ ።

፲፩/ በእውነትም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታሪክ ፡ ጠንቅቀን ፡ ብንመለከትና ፡ ብንመረምር ፡ ከካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተለየችበትን ምክንያት ፡ የሚገልጽና ፡ የሚያስረዳ ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ ከትምርት ፡ ልዩነት ፡ ይልቅ ፡ አንዳንዶቹ ፡ የውጭ ፡ ኹኔታዎች ፡ መኾናቸውን ፡ እንረዳለን ። ከነዚህም ፡ ምክንያቶች ፡ ዋናዎቹ ፡ ያገሩ ፡ መራራቅና ፡ በክርስትና ፡ ልጅነት ፡ ሳለች ፡ ከሮም ፡ ተለይታ ፡ በካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዋና ፡ ጠላቶች ፡ ተከባ ፡ መቅረትዋ ፡ ነው ። ብለዋል ።

፲፪ / (ሀ) ኢትዮጵያን ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የማያገናኛት ፡ የባህል ፡ አለመስማማትና ፡ የልብ ፡ መራራቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሀገር ፡ መራራቅ ፡ አይደለም ፡ የልብ ፡ መራራቅ ፤ እንጂ ፡ የሀገር ፡ መራራቅ ፡ ፍቅርን ፡ ሊያስቀር ፡ አይችልምና ፡ በዚህ ፡ አይጠራጠሩ ።

(ለ) በክርስትና ፡ ልጅነት ፡ ሳለች ፡ ተከባ ፡ ቀረች ፡ ለሚሉት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ክርስትናን ፡ ከተቀበለችበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምራ ፡ ከግብጻውያን ፡ ጋራ ፡ በባህልም ፡ በሃይማኖትም ፡ ተባብራ ፡ መኖሯ ፡ የማይካድ ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ባለፈው ፡ ጥያቄዎ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አስቀድማ ፡ ከሮማ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ኖሯት ፡ ኋላ ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ የሄደች ፡ አስመስለው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ በርግጥ ፡ የተለየችበት ፡ ጊዜ ፡ መቸ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ጠይቀው ፡ ነበረ ።

እኔም ፡ ኢትዮጵያና ፡ ሮማ ፡ ምን ፡ ግንኙነት ፡ አላቸውና ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ይጠይቃሉ ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ሰጥቸዎ ፡ ነበረ ፤ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገና ፡ በክርስትና ፡ ልጅነት ፡ ሳለች ፡ በእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተከባ ፡ መቅረቷን ፡ ካረጋገጡ ፡ ባለፈው ፡ መሥመር ፡ ያቀረቡት ፡ ጥያቄ ፡ ስሕተት ፤ እኔ ፡ የሰጠሁዎ ፡ መልስ ፡ እውነት ፡ መኾኑን ፡ ይገንዘቡልኝ ።

፲፫/ ከሮማ ፡ ለመለየት ፡ ያደረሳት ፡ ከእስክንድርያ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥር ፡ ኾና ፡ በእርስዋ ፡ ስትመራ ፡ የነበረች ፡ መኾንዋ ፡ ነው ብለዋል ።

፲፬ / ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ በመለየቷ ፡ እንዳልተጎዳች ፡ በእርግጥ ፡ ታውቃለች ፡ በመለየቷ ፡ ተጎዳች ፡ እያሉ ፡ የሚያወሩ ፡ እርስዎ ፡ ብቻ ፡ ነዎ ፡ ስለዚህ ፡ በእስክንድርያ ፡ ስትመራ ፡ መቆየቷ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ከመጣ ፡ ስሕተት ፡ ጠብቋታል ፡ እንጂ ፡ የጎዳት ፡ ነገር ፡ የለምና ፡ በዚህ ፡ አይዘኑባት ፡ ግድ ፡ የለም ።

፲፭/ ሮማንና ፡ ኢትዮጵያን ፡ የምታገናኝ ፡ ድልድይ ፡ የነበረችው ፡ ግብጽ ፡ ከእስላሞች ፡ እጅ ፡ ወድቃ ፡ የእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወዳንድ ፡ ባህል ፡ ባለፈች ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ከክርስቲያን ፡ አገሮች ፡ ኹሉ ፡ ተለይታ ፡ ለብቻዋ ፡ ቀረችና ፡ እጅግ ፡ በጠና ፡ እጅግም ፡ በሚያስጨንቅ ፡ ምስቅል ፡ ጉዳና ፡ ላይ ፡ ተገኘች ፡ ብለዋል ።

፲፮ / ኢትዮጵያ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ በርግጥ ፡ የተቀበለችበት ፡ ጊዜ ፡ አይታወቅም። በማለትዎ ፡ ይህ ፡ ንግግር ፡ ኢትዮጵያ ፡ አስቀድማ ፡ የ፪ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ተቀብላ ፡ የነበረች ፡ ለማስመሰል ፡ ነውን ፡ እያልን ፡ ስንደነቅ ፡ እስክንድርያም ፡ በሌላ ፡ ባህል ፡ ኖራ ፤ ወዳንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ያለፈችበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡ ማለትዎና ፡ ይኸውም ፡ በእስላሞች ፡ እጅ ፡ በመውደቋ ፡ የመጣባት ፡ አስመስለው ፡ በመናገርዎ ። ጽሑፍዎን ፡ ኹሉ ፡ ከሌላ ፡ ግምት ፡ ላይ ፡ ጥሎታል ።

ግብጽ ፡ ከእስላሞች ፡ እጅ ፡ በወደቀች ፡ ጊዜ ፡ የእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወዳንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ አለፈች ፡ ብለው ፡ እስክንድርያን ፡ ላንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ እንግዳ ፡ እንዳያደርጓትማ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምሮ ፡ ከሐዋርያት ፡ ከ፫ቱ ፡ ፻ ፡ ተያይዞ ፡ የመጣ ፡ በተራቀቆና ፡ በፍልስፍና ፡ አነጋገር ፡ ያልተሻሻለ ፡ መኾኑን ፤ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ግን ፡ በ፬፻፶፩ ፡ ዓ/ም ፡ በጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ በተራቀቆና ፡ በፍልስፍና ፡ አነጋገር ፡ ተሻሽሎ ፡ የመጣ ፡ መኾኑን ። ይህንኑም ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ አልቀበለውም ፡ ብሎ ፡ መለየቱን ፡ በዚህ፡መጽሐፍዎ በገጽ ፡ ፫ ፡ መላልሰው ፡ አረጋግጠው ፡ ጽፈውልን ፡ የለምን ፤ ከመቸው ፡ ረሱትና ፡ እስክንድርያን ፡ ላንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ እንግዳ ፡ ያደርጓታል ።

፲፯/ እጅግ ፡ በሚያስጨንቅ ፡ ምስቅል ፡ ጉዳና ፡ ላይ ፡ ተገኘች ፡ ያሉትንም ፡ ሲተረጕሙ ፡ እናቷ ፡ የኾነችውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዕድል ፡ መከተል ፡ ወይም ፡ በምኽኘ ፡ ውስጥ ፡ በጠላቶቹ ፡ እንደተከበበ ፡ ለብቻዋ ፡ ተለይታ ፡ በእስላም ፡ አጥቂነት ፡ ያስማጸረጥ ፡ እየተከላከለችና ፡ እየታገለች ፡ መኖር ፡ ከኋህ ፡ ከኹለቱ ፡ አንዱን ፡ መምረጥ ፡ ግድ ፡ ኾነባት ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ጊዜና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ከእስክንድርያ ፡ ካንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ ባንድ ፡ በኩልም ፤ ከእስላሞች ፡ አደጋ ፡ ተጣለባት ፡ ብለዋል ።

፲፬ / ይህ ፡ አነጋገርዎ ፡ እውነቱን ፡ ከሐሰት ፡ ሐሰቱን ፡ ከእውነት ፡ ቀላቅሎና ፡ አሰባጥሮ ፡ የያዘ ፡ አደናጋሪ ፡ ንግግር ፡ ነው ፡፡ ስለኾነም ፡ ነገሩ ፡ የጎላ ፡ ስለኾነ ፡ እውነቱን ፡ ከሐሰቱ ፡ ለይቶ ፡ አንጠር ጥሮ ፡ ማስረዳት ፡ ይቻላል ፡፡ ነገሩም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ፡ በዓፄ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዘመነ ፡ መን ግሥት ፡ በእስላሙ ፡ ግራኝ ፡ ወረራ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሚያስጨንቅ ፡ ምስቅል ፡ጉዳና ፡ ላይ ፡ መገኘቷ ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ እንዲኹም ፡ በዚያው ፡ ጊዜ ፡ ለጦር ፡ ርዳታ ፡ የመጡ ፡ ፖርቱጋሎች ፡ ካቶሊካውያን ፡ ስለነበሩ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ላንድ ፡ አንድ ፡ ሰዎች ፡ ለማስተማር ፡ ሞክረዋል ፡፡

በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ዓፄ ፡ ዘድንግልን ፡ ከሕዝቡ ፡ አሊያይተው ፡ ደም ፡ አፋሰዋል ፤ ንጉሡንም ፡ አስገድለዋል ፡፡ እንዲሁም ፡ ዓፄ ፡ ሱስንዮስንም ፡ በዚሁ ፡ በ፪ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ አሳስተው ፡ የብዙ ፡ ክርስቲያን ፡ ደም ፡ አስፈስሰዋል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ ይሙ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ከምትል ፡ ከኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ ጋር ፡ የተቀላቀለ ፡ ስለኾነ ፡ ነገሩን ፡ ሊታገሠው ፡ ባለመቻሉ ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ታጥቆ ፡ ተነሣባቸው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ ፈሰሰ ፡፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ በሚያስጨንቅ ፡ ምስቅል ፡ጉዳና ፡ ላይ ፡ መውደቋ ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡፡ ቢኾንም ፡ ጀግናው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ፲፭ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ከግራኝ ፡ ጋራ ፡ ተከላክሎ ፡ ክርስትናውን ፡ ሳይለቅ ፡ መንግሥቱን ፡ ሳያስነጥቅ ፡ በነፃነቱ ፡ ኮርቶ ፡ እንደ ፡ ተገኘ ፡ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ሊያስማ ፡ የሞከረውን ፡ ንጉሥ ፡ አስጨንቆ ፡ አስጠብቦ ፡ ፋሲል ፡ ይንገሥ ፡ ሃይማኖት ፡ ይመለስ ፡ የሚል ፡ ዐዋጅ ፡ እንዲነግርና ፡ መንግሥቱን ፡ እንዲለቅ ፡ አድርጎታል ፡፡

ይህንን ፡ መርዝ ፡ የነዙ ፡ እነአልፎንሱንም ፡በዓፄ ፡ ፋሲል ፡ ጊዜ ፡ ተጠራርገው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ እንዲወጡ ፡ አድርጓቸዋል ፡፡ ይህ ፡ የነአልፎንሱ ፡ መባረር ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እጅግ ፡ በሚያስጨንቅ ፡ ምስቅል ፡ጉዳና ፡ ላይ ፡ መገኘቷ ፡ እርግጥ ፡ ነው ፤ እውነተኛው ፡ ታሪክ ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡

ይህንኑም ፡ ሊረዱ ፡ ቢወዱ ፡ የርስዎ ፡ ወገን ፡ አባ ፡ ጋስፒሪኒ ፡ የጻፉትን ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ገጽ ፡ ፻፳፭ና ፡ ፻፳፯ ፡ ይመልከቱ ፡፡

በኢትዮጵያ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ በእስክንድርያ ፡ ካንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፤ ባንድ ፡ ወገንም ፡ ከእስ ላሞች ፡ አደጋ ፡ ተጣለባት ፡ ያሉት ፡ ንግግርስ ፡ ስንኳን ፡ እንደርስዎ ፡ ያለ ፡ መዓርጋትን ፡ ኹሉ ፡ ደራ ርቤ ፡ ይዤዋለሁ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ሊናገረው ፡ ማንም ፡ ተርታ ፡ ሰው ፡ ሊናገረው ፡ የማይገባ ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡፡ ኢትዮጵያና ፡ እስክንድርያ ፡ ባንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ተስማምተው ፡ ከመኖር ፡ በቀር ፡ የተቀያየሙበት ፡ ጊዜ ፡ በፍጹም ፡ የለም ፡፡

፲፭/ ነገር ፡ ግን ፡ በጀግንነት ፡ ስለተጋደለች ፡ የሠለጠኑት ፡ የግብጽና ፡ የሰሜን ፡ አፍሪቃ ፡ የክርስቲያን ፡ ሀገሮች ፡ ከእስላም፡ ቀንበር ፡ ሥር ፡ አንገታቸውን ፡ ሲደፉ ፡ እርሷ ፡ ለብቻዋ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ በኩል ፡ በመጀመሪያ ፡ እር ምጃዋ ፡ ብትኖር ፡ ጠንክራ ፡ ስለተቃወመች ፡ የካቶሊክን ፡ ትምርት ፡ በመላው ፡ ለብዙ ፡ ዘመናት ፡ ለመያዝ ፡ የክርስቲያንንም ፡ ሃይማኖት ፡ ለመጠበቅ ፡ ቻለች ብለዋል ፡፡

፲፮ / ኢትዮጵያ ፡ መቸም ፡ መች ፡ ቢኾን ፡ ያልሞከረችውን ፡ ነገር ፡ ለማስመሰል ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ በኩል ፡ በመጀመሪያ ፡ እርምጃዋ ፡ ብትኖር ፡ የካቶሊክን ፡ ትምህርት ፡ በመላው ፡ ለብዙ ፡ ዘመናት ፡ ለመያዝ ፡ ብለው ፡ ያስጠጉባት ፡ ንግግር ፡ ብቻ ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌሎች ፡ ሀገሮች ፡ ከእስላም ፡ ቀንበር ፡ ሥር ፡ አንገታቸውን ፡ ሲደፉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሃይማኖቷን ፡ ጋሻ ፡ አድርጋ ፡ ጠንክራ በመዋጋቷ ፡ በየጊዜው ፡ ከተነሡባት ፡ከእስላሞችና፡ከካቶሊኮች፡እግር፡ ሥር አንገቷን ፡ ሳትደፋ ፡ በነጻነቷ ፡ ኮርታ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ሃይማኖቷን ፡ አጽንታ ፡ መኖሯ ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡፡

፲፯/ ኢትዮጵያ ፡ ባለማድረግ ፡ ክርስትናቸውን ፡ ይዘው ፡ ከሚኖሩ ፡ ከጥንታውያን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አንዲት ፡ ናት ፡ በአፍሪቃም ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ እርሷ ፡ ብቻ ፡ ናት ፡ ክርስትና ፡ ዛሬም ፡ ቢኾን ፡ የመንግሥቷን ፡ ደንበኛ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፡ ብለዋል ፡፡

፲፰ / ኢትዮጵያ ፡ ከክርስትና ፡ ሃይማኖትም ፡ በፊት ፡ ከመላው ፡ ዓለም ፡ አስቀድማ ፡ አምል ኮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከቤተ ፡ እስራኤል ፡ የተቀበለች ፡ ሀገር ፡ ናት ፡ ማለትንና ፡ ክርስትና ፡ ባሉት ፡ ላይ ፡ የኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ የመንግሥቷ ፡ ደንበኛ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ግልጥ ፡ አድርገው ፡ ይናገሩት ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ንግግርዎ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ የምቃወመው ፡ ንግግር ፡ የለኝም ፡፡

፲፱/ ኢትዮጵያ ፡ ያለፈቃዷ ፡ ደርሶባት ፡ ከነበረው ፡ መለየት ፡ ወይም ፡ ብቸኝነት ፡ ለመውጣት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጥራለች ፡ ከሮማም ፡ ጋር ፡ ለመገናኘትና ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለመቀላቀል ፡ ፈትናለች ፡ ብለዋል ፡፡

፲፯ / ለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ማቅረቢያ ፡ የጻፉልዎ ፡ ካርዲናል ፡ ኤውጅንዮስ ፡ ቲሰራንም ፡ በዚሁ ፡ በጽሑፋቸው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ ጋራ ፡ ለመታረቅ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በልብ ፡ ተመኝታለች ፡ ብለው ፡ ጽፈዋል ። ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ ያለፈቃዷ ፤ የተለየች ፡ አይደለችም ፤ የተለየች ፡ በፈቃዷ ፡ ነው ፤ ኋላም ፡ ከሮማ ፡ ልትቀላቀል ፡ መፈተን ፡ የለባትም ፡ የኹለታችሁም ፡ ቃል ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ሐሰት ፡ መኾኑንም ፡ ለመታረቅ ፡ ብዙ ፤ ጊዜ ፡ በልብ ፡ ተመኝታለች ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ያስረዳል ፤ ያስረዳል ፡ የምንልበትም ፤ ምክንያት ፡ ያንዱን ፡ ምኞት ፡ አንዱ ፡ ሊያውቀው ፡ ስለማይችል ፡ ነው ።

፲፰/ የሮማውያንም ፡ አርእስተ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ወደ ፡ እውነተኛው ፡ እረኛ ፡ በረት ፡ ለመመለስ ፡ ሊሉ፡ሰባኪያንን ፡ በመላክ ፡ ያባትንት ፡ አሳብ ፡ አልጎደለባቸውም ፡ ብለዋል ።

፲፰ / ጠላት ፡ ወይም ፡ ባላጋራ ፡ ሌባ ፤ ባለቤት ፡ መንቃቱንና ፡ መተኛቱን ፤ በሩ ፡ መጥበቁንና ፡ መላላቱን ፡ ለማወቅ ፡ ሲል ፡ ሊያጠቃው ፡ የፈለገውን ፡ ሰው ፡ በየጊዜው ፡እንዲጐበኝ ፡ የሮማ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትም ፡ በየጊዜው ፡ ሰላዮችና፡ጉበኞች ፡ እየሰደዱ ፡ ኢትዮጵያን ፡ መሰለላቸው ፡ አልቀረም ። ቢኾ ንም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ንቅተው ፡ ተግተው ፡ ባጭር ፡ ታጥቀው ፡ ማለት ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ አው ጥተው ፡ እልባት ፡ አልበው ፡ ስለጠበቋቸው ፡ በመጡበት ፡ አኳኋን ፡ እንደ ፡ ፍላጻ ፡ ልብ ፡ በሚሠነ ጥቅ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ግንባር ፡ ግንባራቸውን ፡ እያሉ ፡ መልሰዋቸዋል ፡ እንጂ ፡ እነርሱን ፡ በፍቅር ፡ የተቀበሉበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ። ስለኾነም ፡ በመጡበት ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፡ በመንግሥት ፡ ፖለቲካ ፡ እየገቡ ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ መለያየትን ፡ እየፈጠሩ ፡ ደም ፡ ማፋሰሳቸው ፡ አልቀረም ። እንግዲህ ፡ ለተንኮል ፡ የተሠ ራውን ፡ ተማባር ፡ ወረታ ፡ አድርጎ ፡ መቍጠር ፡ ይገባልን ፡ አይገባም ።

፲፱/ የግብጽ ፡ ሡልጣኖች ፡ ከኢትዮጵያ ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ ለማጥፋት ፡ ሲሉ ፡ የእስክንድርያም ፡ ፓትርያርኮች ከእውነተኛይቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለማራቅ ፡ ሲሉ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ወደሮማ ፡ እንዳይሔዱ ፡ ሮማውያንም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ እንዳይመጡ ፡ መንገድ ፡ ዘጉባቸው ፡ ብለዋል ።

፲፱ / እስክንድርያና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ባንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ስለተስማሙ ፡ ባንድ ፡ ግብጻዊ ፡ ጳጳስ ፡ አማሃይነት ፡ ብቻ ፡ እየተገናኙ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ግብጻውያን ፡ በብዛት ፡ መጥተው ፤ ወይም ፡ ኢት ዮጵያውያን ፡ በብዛት ፡ ሄደው ፡ ተገናኝተው ፡ አይደለም ። እንደዚኸውም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እየተ ላኩ ፡ ወደሮማ ፡ ይሄዱ ፡ ነበረ ፡ ብለዋል ። ሮማውያንም ፡ በየጊዜው ፡ መምጣታቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡ ለምን ፡ እየመለሱ ፡ እያባረሩ ፡ ሰደዷቸው ፤ የሃይማኖት ፡ ግንኙነት ፡ ባይኖር ፡ አይደለምን ፡ የሃይማኖት ፡ ግንኙነትማ ፡ ቢኖር ፡ እነዚያኑ ፡ የተላኩትን ፤ አክብረው ፡ አይቀበሏቸውም ፡ ነበርን ፡ ግብጻውያን ፡ መንገድ ፡ በመዝጋታቸው ፡ ተራራቁ ፡ የሚሉት ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ሮማና ፡ ኢት ዮጵያ ፡ የተራራቁ ፡ በሃይማኖትና ፡ በባህል ፡ ባይስማሙ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፳/ ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ የሚያስረዳ ፡ ወደ ፡ ፈረንጳ ፡ ጉባኤ ፡ የተላኩት ፡ የኢትዮጵያ ውያን ፡ መሪ ፡ ኾኖ ፡ ሔዶ ፡ የነበረ ፡ ጴጥ ሮስ ፡ ዲያቆን ፡ የተባለ ፡ በርእስ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳቱ ፡ በእውጅንዮስ ፡ ፩ኛ ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ መስከረም ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ እጅግ ፡ ብፁዕ ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፡ ባንተ ፡ ፊት ፡ የሚመጡ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ አንተን ፡ ዳግማዊ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆነህ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በኃጢአተኞች ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ የምትኖረው ን ፡ ለማየት ፡ ስላበቃቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብዙ ፡ ምስ ጋና ፡ ሊያቀርቡለት ፡ ይገባቸዋል ፡ የሚል ፡ ሰፊ ፡ ንግግር ፡ ጠቅሰዋል ።

፳ / ይህ ፡ ንግግር ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ወይም ፡ ከመላው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፤ የተላከ ፡ ነው ፡ ቢባል ፡ ኖሮ ፡ ለሐሳብዎ ፡ ደጋፊ ፡ ይኾናል ፡ ተብሎ ፡ በተገመተ ፡ ነበር ፡ ያውም ፡ ቢኾን ፡ የዚሁ ፡ ቃል ፡ ቀሪ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሲገኝ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ካልኾነ ፡ ግን ፡ ያንድ ፡ መላክተኛ ፡ ስሕተት ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ ሊኾን ፡ አይችልም ። ይህንንም ፡ ስል ፡ እርስዎ ፡ ጽሑፉን ፡ አየሁት ፡ ብለው ፡ ሲመሰክሩ ፡ እኔ ፡ ባላየሁት ፡ ነገር ፡ ማስተባበሉ ፡ ቅር ፡ ስላለኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በእውነቱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ይህን ፡ ይናገራል ፡ ብዬ ፡ አላምንም ።

ምክንያቱም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ዛሬ ፡ አምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ በጠፋበት ፤ አምልኮተ ፡ እግዚአ ብሔር ፡ በተስፋፋበት ፤ ወንጌል ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ በተዘረጋችበት ፡ ጊዜ ፡ ይቅርና ፡ ቀድሞም ፡ ቢኾን ፡ ከልደተ ፡ ክርስቶስ ፡ በፊት ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ ተካክሎ ፡ ጣዖት ፡ ያመልክ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ንግሥተ ፡ አዜብ ፡ ንጉሥ ፡ ሰሎሞንን ፡ከጐበኘችበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ኢታምልክ ፡ ባዕደ ፡ አምላከ ፡ ዘእንበሌየ ። ዘያመልክ ፡ በፍጡር ፡ ርጉም ፡ ውእቱ ፡ የምትል ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ ጠንቅቀው ፡ ያወቁ ፡ ስለኾኑ ፡ ማን ንም ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ ክርስቶስ ፡ ነህ ፡ ብለው ፡ ያምኑበታል ፡ ተብለው ፡ የማይገመቱ ፡ በመኾናቸው ፡ ነው ። ይህንንም ፡ በመርድ ፡ አዝማች ፡ ዘሚካኤል ፡ ቅኔ ፡ ልንረዳው ፡ እንችላለን ።

ዓፄ ፡ ኢያሱ ፡ ከጐንደር ፡ ተነሥተው ፡ ሸዋን ፡ ሊጐበኙ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ የሸዋ ፡ ሰዎች ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ተቀብለዋቸዋል ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሸዋው ፡ መስፍን ፡ መርድ ፡ አዝማች ፡ ዘሚካኤል ፡ ቅኔ ፡ ሲያበረክቱ ፡ እንዲህ ፡ ብለዋል ።

በእስተናሥኦ ፡ ማኅሌት ፡ ወበይባቤ ፡ ኢያሱ ፡ ንጉሥ ፡ ተቀበልናከ ፤ እመሰ ፡ ይደሉ ፡ እግዚኦ ፡
እምወሀብናከ ፡ ሰጊደ ።
ወእምረሰይናከ ፡ አምላከ ፡ ዋሕደ ።

ባሕቱ ፡ አምላክ ፡ ዘእምቤትከ ፡ ተወልደ ።
ውስተ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ አመ ፡ ወረደ ።
በቅድመ ፡ ሙሴ ፡ ወአሮን ፡ ይቤ ፡ ገሃደ ።
እንበሌየ ፡ ኢታምልኩ ፡ ባዕደ ፡ ብለዋል ።

የዚህም ፡ ቅኔ ፡ ትርጓሜ ፡ ባጭሩ ፡ ኢያሱ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ በማኅሌትና ፡ በዕልልታ ፡ ተቀበልንህ ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ ከቤተ ፡ ዳዊት ፡ የተወለደ ፡ አምላክ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ በሙሴና ፡ በአሮን ፡ ፊት ፡ ከኔ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አታምልኩ ፡ ብሏልና ፡ አይገባም ፡ እንጂ ፡ የሚገባስ ፡ ቢኾን ፡ እንደ ፡ አምላክ ፡ አድርገን ፡ በሰገድንልህ ፡ ነበረ ፡ ማለት ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ በወታደርነት ፡ ደረጃ ፡ ያሉት ፡ መስፍን ፡ የአምልኮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ አድርገው ፡ ሲጠነቀቁ ፡ በማዕርገ ፡ ክህነት ፡ ያለ ፡ ዲያቆን ፡ ይህን ፡ ተናገረ ፡ ቢባል ፡ አመዛዛኝ ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ሊቀበለው ፡ አይችልም ። ደግሞ ፡ መለስ ፡ ብለን ፡ የሮማው ፡ ርእስ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዳግማዊ ፡ ክርስቶስ ፡ ነህ ፡ ብለው ፡ ቢያመሰግኑት ፡ ይገባኛል ፡ ብሎ ፡ ወዶ ፡ መቀበሉን ፡ ትክ ፡ ብሎ ፡ ሲመለከቱት ፡ አእምሮን ፡ በመገረም ፡ ያፈዛል ።

እንግዲህ ፡ በሮማ ፡ መንበረ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የተቀመጠው ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ኹሉ ፡ በየተራው ፡ ዳግማዊ ፡ ክርስቶስ ፡ ሣልሳዊ ፡ ክርስቶስ ፡ ራብዐዊ ፡ ክርስቶስ ፡ ይባላል ፡ ማለት ፡ ነውን ወይስ ፡ ለአባ ፡ አውጋንዮስ ፡ ብቻ ፡ የአምላክነት ፡ ምልክት ፡ ታይቶለት ፡ የተሰጠ ፡ እድል ይኾን ። ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነገር ፡ ክሌሜንት ፡ የተባለ ፡ የሮም ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት እግዚአብሔር ፡ የሰማይንና ፡ የምድርን ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ሰጠኝ ፡ ብሎ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ተውህበ ፡ ሊተ ፡ ኵሉ ፡ ኵነኔ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ።

የሰማይ ፡ የምድር ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጠኝ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ የመሰለ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ እንዳሳወጀ ታሪክ ፡ ይነግረናል ፡ ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፲፰ ።

በእውነቱ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ለመረመረው ፡ ሰው ፤ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሞቱት ፡ ዘመዶቻችሁ ፡ ከሲኦል ፡ የሚወጡበት ፡ የኃጢአት ፡ ስርየት ፡ ግዙ ፡ እያለች ፡ ቲኬት ፡ በገንዘብ ፡ ትሸጣለች ፡ ብሎ ፡ ማርቲን ፡ ሉተር ፡ የጻፈው ፡ እውነት ፡ ይኾንን ፡ ወደ ፡ ማለት ፡ የሚያደርስ ፡ ኾኖ ፡ ይታያል ። ይህን ፡ ጽሑፍ ፡ ይጠቅማል ፡ ብሎ ፡ ከማኖር ፡ በፍጥነት ፡ ቀዶ ፡ መጣል ፡ ለሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባጠፈታ ፡ በጠቀማት ፡ ነበረ ።

የእኛስ ፡ አባቶች ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ለስማቸው ፡ ገብሩ ፡ ወሐዋርያሁ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚል ፡ ቅጽል ፡ ይሰጡታል ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ አይንጠራሩም ፡ ቢያመሰግኗቸውም ፡ አይቀበሉትም ። እኛ ፡ ልጆቻቸውም ፡ እንደዚሁ ፡ ስማቸውን ፡ በምንጠራበት ፡ ጊዜ ፡ ገብሩ ፡ ወሐዋርያሁ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚል ፡ ቅጽል ፡ እንሰጣቸዋለን ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ አንደፍርም ።

ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ይጠቅማል ፡ ብለው ፡ በመጥቀስዎ ፡ እያፈርኩ ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ አሳፋሪ ፡ ቃል ፡ የሚጽፍ ፡ የለም ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መልስ ፡ ልሰጥበት ፡ አልፈቅድም ። ምክንያቱም ፡ ወበእንቲአክሙ ፡ ይፀርፉ ፡ አሕዛብ ፡ ላዕለ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተባለው ፡ ቃል ፡ ይደርስብናል ፡ ብሎ ፡ በመፍራት ፡ ነው ።

፳፱/ በ፲፱፻፵፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ጳጋ ፡ ዘአብ ፡ የተባለ ፡ መላከተኛ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለተለየችበት ፡ ሲናገር አባቶቻችን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከተመሠረተችበት ፡ ከመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ጀምረው ፡ የሮማውን ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ጳጳስ ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ተቀበሉት ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ፡ ዛሬም ፡ ቢኾን ፡ እኛ ፡ የክርስቶስ ፡ እንደራሴ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፡ ልንታዘዝለት ፡ ዝግጁዎች ፡ ነን ፡ መንገዱ ፡ እጅግ ፡ የራቀ ፡ ባይኾንና ፡ ብዙ ፡ መሰናክልም ፡ ባይኖርበት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በተመላለስን ፡ ነበር ፡ አሉ ፡ ብለዋል ።

፴ / እውነት ፡ ነው ፡ ኋላ ፡ ልዮን ፡ በጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ እስኪያመጣ ፡ ድረስ ፡ ሮም ፡ በኦርቶዶክስነቷ ፡ ጸንታ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ ታስተ

ምር ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ የዓለም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ኹሉ ፡ የሮሙን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ያከብሩት ፡ እንደነበረ ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ኋላ ፡ ግን ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ ባመጣ ፡ ጊዜ ፡ ቀለውት ፡ ስለተ ለያዩ ፡ ቀርቶበታል ። ይህም ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ያነኑ ፡ የቀድሞውን ፡ በመጥቀስ ፡ የራሱን ፡ ሐሳብ ፡ ተናግሮ ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አልተናገረም ። ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መንገድ ፡ ባይርቀን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንመላለስ ፡ ነበረ ፡ አለ ፡ ተብሎ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ ነበረች ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ።

፳፫/ እንግዲህ ፡ ታሪኩን ፡ በመመርመር ፡ ኾነ ፡ ወይም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ራሳቸው ፡ በተናገሩት ፡ ምስክርነት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ትምርት ፡ ለመሸፈት ፡ በቀጥታ ፡ ምንም ፡ እንዳላበረች ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ክርስቲያንም ፡ መለየቷ ፡ ሳታውቀውና ፡ ሳት ወደው ፡ እንደኾነ ፡ በግልጽ ፡ ይረዳል ፡ ብለዋል ።

፳፬ / (ሀ) ታሪኩን ፡ በመመርመር ፡ ስለሚሉት ፡ እውነተኛው ፡ ታሪክ ፡ ከላይ ፡ በመቅድሙ ፡ እንደ ፡ ገለጽነው ፡ በ፬፻፡ ሱስንዮስ ፡ ጊዜ ፡ የሮም ፡ ካቶሊካውያን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሊቃውንትና ፡ ምእመናን ፡ ማሳረዳቸው ፤ በ፬፻ ፡ ፋሲል ፡ ጊዜም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ተጠራርገው ፡ መውጣታቸው ፡ ነው፤ በስ ተቀረ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ስንኳን ፡ ታሪኳን ፡ ቋንቋዋን ፡ አጥርተው ፡ የማያውቁ ፡ ሰዎች ፡ በየሀገራቸውና ፡ በየቋንቋቸው ፡ ጽፈው ፡ ያስቀመጡት ፡ ኢትዮጵያ ፡ የማታውቀው ፡ ታሪክ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ ነበረች ፡ ሊያሰኛት ፡ አይችልም ፤ ታሪክ ፡ እውነተኛ ፡ ሊኾን ፡ የሚቻለው ፡ የሚተረክለት ፡ የታሪኩ ባለቤት ፡ ዐውቆት ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተቀብሎት ፡ ሲገኝ ፡ ነው ።

(ለ) ኢትዮጵያውያን ፡ ራሳቸው ፡ በተናገሩት ፡ ምስክርነት ፡ ለሚሉት ፡ መሰከሩ ፡ የሚኋቸው ፡ ሰዎች ፡ ምስክርነታቸው ፡ በቂ ፡ አለመኾኑን ፡ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ አስረድቸዋለሁ ።

(ሐ) የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ለመሸፈት ፡ አላበረችም ፡ ስለሚሉት ፤ ይህ ፡ ንግግር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ለንጉሥ ፡ አልገዛም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ እገሌ ፡ ሸፈተ ፤ ተብሎ ፡ የሚነገር ፡ ንግግር ፡ ነው ። በወንጌል ፡ ሕግ ፡ ያመነ ፡ ኹሉ ፡ ተካክሎ ፡ ለክርስቶስ ፡ ይገዛል ፡ እንጂ ፡ አንዷ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላንዷ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ልትገዛ ፡ አያዝዝም ። እንግዲህ ፡ እርስዎ ፡ የእገሌ ፡ ሀገር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተገዛች ፡ የእገሌ ፡ ሀገር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሸፈተች ፡ ብሎ ፡ ለመናገር ፡ እንደምን ፡ ደፈሩ ፡

እውነትም ፡ ያ ፡ ዲያቆን ፡ ለአባ ፡ አውጋንዮስ ፡ አንተ ፡ ዳግማዊ ፡ ክርስቶስ ፡ ኾነህ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በኃጢአተኞች ፡ መካከል ፡ ትኖራለህ ፡ ብሎ ፡ የአክብሮት ፡ ምስጋና ፡ ቃል ፡ አቀረበለት ፡ ያሉትን ፡ ተገቢ ፡ ምስጋና ፡ አድርገው ፡ ተቀብለውታል ፡ መሰለኝ ። አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ርስ ፡ በር ሳቸው ፡ ባይስማሙ ፡ ተለያዩ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ሸፈተ ፡ ማለት ፡ ያልታረመ ፡ ንግግር ፡ ስለኾነ ፡ ንግግርዎን ፡ ያርሙ ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መልስ ፡ ሊሰጥበት ፡ የሚገባው ፡ አይደለም ።

(መ) ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መለየቷ ፡ ሳታውቀውና ፡ ሳትወደው ፡ ነው ፡ ስለሚሉት ፡ ካላወቀችው ፡ ካቶሊካውያን ፡ ለሚያቀርቡላት ፡ ጥያቄ ፡ ኹሉ ፡ ተገቢውን ፡ መልስ ፡ እየሰጠች ፡ ለምን ፡ ታሳፍራቸዋለች ፤ መለየቷንስ ፡ ካልወደደችው ፡ ካቶሊካውያን ፡ ጳጳስ ፡ ሳይቀር ፡ ይዘው ፡ መጥ ተው ፡ ነበረ ፡ ደም ፡ እስከ ፡ መፋሰስ ፡ ድረስ ፡ ደርሳ ፡ ለምን ፡ ጠራርጋ ፡ አስወጣቻቸው ፡ አትቀበላቸ ውም ፡ ኖሯልን ፡ ግን ፡ ከለከላት ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ተመራምራ ፡ ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተመለሰችቱን ፡ ኋላም ፡ ያስተማራት ፡ ሐዋርያ ፡ ሳይኖር ፡ በፈቃደ ፡ ሐዋርያ ፡ አስመጥታ ፡ ጥምቀትን ፡ ቊርባንን ፡ የተቀበለች ፡ ኢትዮጵያን ፡ ሳታውቀው ፡ ነው ፡ ሳትወደው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ለጻፉት ፡ የተመለከተውን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ኹሉ ፡ የሚያናድድ ፡ የሚያቋጭ ፡ ንግግር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ስምምነት ፡ የሚስብ ፡ መንገድ ፡ አይደለም ፤ የምታምነውን ፡ ሃይማኖት ፡ የምትናገረውን ፡ ነገር ፡ አታውቅም ፡ ማለት ፡ አብድ ፡ ዝንጉዕ ፡ ብሎ ፡ መስደብ ፡ መኾኑን ፡ አያውቁምን ።

፳፭/ መለየቷ ፡ ያለዕውቀት ፡ መኾኑን ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ሌላም ፡ መረጃ ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ያቀረቡት ፡ መረጃ ፡ በጠቅላላው ኢትዮጵያውያን ፡ ከሮማ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ከመላው ፡ ዓለም ፡ ክርስቲያኖች ፡ ተለይተው ፡ ስለነበሩ ፡ አስክንድርያ ፡ ከእስላሞች ጋራ ፡ ተስማምታ ፡ ጋርዳባቸው ፡ ከነበረው ፡ መጋረጃ ፡ ወዲያ ፡ ይደረግ ፡ የነበረውን ፡ በእርግጥ ፡ ማወቅ ፡ አይቻላቸውም ፡ ነበረ ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ስለኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የሚያውቋቸው ፡ ጥቂቶችና ፡ የተቀራረጡ ፡ ወሬዎች ፡ ከአስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ መላክተኞች ፡ ያገኟቸው ፡ ናቸው ። ግብጻውያን ፡ ከሮማ ፡ ፈጽመው ፡ ሲለይዋቸውና ፡ ከራሳቸው ፡ ጋራ ፡ ሲያስሯቸው ብለው ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነውን ፡ እውነተኛውን ፡ ትርጉሙን ፡ እንዳያውቁት ፡ በድንቁርና ፡ ጨለማ ፡ ደብቀው ፡ ያዟቸው ።

ይህም ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የሚጣሉ ፡ መጻሕፍትን ፡ አስተርጉመው ፡ እየዘሩ ፡ ያልኾነውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አስመስለው ፡ አሳመኗቸው ።

ስለዚህ ፡ ዲዮስቆሮስን፡በእውነት ፡ ጀግና ፡ የሃይማኖት ፡ ሰማዕት ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ያለፍርድ ፡ የተገፋ ፡ ለቀናችው ፡ ሃይማኖት ፡ ደጋፊ ፡ ተብሎ ፡ ከታላላቆች ፡ ቅዱሳን ፡ ሲቈጠር ፡ ልዮንን ፡ ርኩስ ፡ የኬልቄዶንንም ፡ ጉባኤ ፡ ማኅበረ ፡ አብዳን ፡ ብሎ ፡ እስከ ፡ መጥራት ፡ ደረሱ ፡ ስለዚህ ፡ ልዮን ፡ ጳጳስንና ፡ ንስጥሮስን ፡ አንድ ፡ አድርገው ፡ ያወግዟቸዋል ፡ የሚል ፡ ነው ።

፳፬ / (ሀ) ኢትዮጵያ ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ አለመኖሯና ፡ ከሌሎችም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ተለይታ ፡ መኖሯ ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ይህም ፡ የኾነበት ፡ ምክንያት ፡ በሀገሩ ፡ ርኀቀት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ግብጻውያን ፡ ከልክለዋት ፡ አይደለም ። እንዳትገደድስ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከማንም ፡ መንግሥት ፡ ሥር ፡ ያልወደቀች ፡ ነጻ ፡ መንግሥት ፡ መኾኗ ፡ በኹሉ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ ነው ።

በመንፈሳዊም ፡ በኩል ፡ በእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሥር ፡ መተዳደሯ ፡ እርስዎ ፡ በ፵፭ ኛው ፡ ገጽ ፡ በመሥመር ፡ ፮ ፡ እንደ ፡ ገለጹት ፡ ለተቀደሰው ፡ ለኒቅያ ፡ ጉባኤ ፡ ፮ኛ ፡ ቀኖና ፡ ለመታዘዝ ፡ ብቻ ፡ ፈቅዳ ፡ ያደረገችው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ያስገደዳት ፡ ኖሮ ፡ አይደለም ።

ኢትዮጵያ ፡ ብሉይ ፡ ኪዳንን ፡ ከዓለም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አስቀድማ ፡ በቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ጊዜ ፡ ተቀብላለች ። ሐዲስ ፡ ኪዳንንም ፡ በፈቃዷ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስን ፡ ልካ ፡ አስመጥታ ፡ ተቀብላለች ። ሃይማኖት ፡ የተወሰነ ፡ በብሉያትና ፡ በሐዲሳት ፡ ስለኾነ ፡ ብሉያትንና ፡ ሐዲሳትን ፡ እያነበበች ፡ እየተረጐመች፡ ሃይማኖቷን ፡ ጠንቅቃ ፡ ሕገ ፡ ክርስትናን ፡ ጠብቃ ፡ ትኖራለች ፡ ከሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ባትገናኝ ፡ የሚቀርባት ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ወጥቶ ፡ በይኾናል ፡ በይመስላል ፡ የሚነተቸው ፡ ትችት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ በመለየቷ ፡ እትጠጠትበትም ፡ የተጎዳችው ፡ መጎዳት ፡ የለም ።

ለ/ ግብጻውያን ፡ ከራሳቸው ፡ ጋራ ፡ ሲያስሯቸው ፡ በድንቁርና ፡ ጨለማ ፡ ደብቀው ፡ ያዟቸው ።
ስለሚሉት ።

በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የተጻፈውን ፡ ተመልክቶ ፡ በሊቃውንት ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነውን ፡ ሰምቶ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ማመን ፡ ድንቁርና ፡ ጨለማ ፡ መስሎ ፡ ከታየዎ ፡ ለአይሁድኒ ፡ ይመስሎሙ ፡ ዘንጌገ ፡ ወለዓረሚኒ ፡ ይመስሎሙ ፡ ዘነአብድ ፡ ወለነሰ ፡ ለእለ ፡ ድኅነ ፡ ክርስቶስ ፡ ኃይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ። ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፳፫ ። እያልን ፡ ስድቡን ፡ ከመታገሥ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ የምንሰጠው ፡ መልስ ፡ የለንም ።

ሐ/ ዲዮስቆሮስን ፡ ቅዱስ ፡ ብለው ፡ ሲያከብሩ ፡ ልዮንንና ፡ ንስጥሮስን ፡ አንድ ፡ አድርገው ፡ ያወግዟቸዋል ፡
ስለሚሉት ።

ነገሩ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ ቅዱስ ፡ ብንለው ፡ ልዮንንና ፡ ንስጥሮስን ፡ አንድ ፡ አድርገው ፡ በሌላ ፡ አስተያየት ፡ ያይዋቸዋል ። ምክንያቱም ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ በጉባኤ ፡ ሐዋርያት ፤ በጉባኤ ፡ ኒቅያ ፡ በጉባኤ ፡ ኤፌሶን ፡ በጉባኤ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ በተወሰነው ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ከምትል ፡ ከኦርቶዶክስ ፡ ሃይማኖት ፡ ሳይናወጥ ፡ በዚያው ፡ ጸንቶ ፡ሲያገኙት ፡ ንስጥሮስና ፡ ልዮን ፡ ምንም ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ በማለት ፡ ትንሽ ፡ ቢለያዩ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ተስማምተው ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ስላገኟቸው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ኹሉ ፡ የንስጥሮስንና ፡ የልዮንን ፡ አንድነት ፡ በየጊዜው ፡ በሚቀኙት ፡ ቅኔ ፡ ይገልጹታል ።

ለዚህም ፡ ማስረጃ ፡ ፩ኛ ፡ አለቃ ፡ ውድነህ ፡ እሸቴ ፡ የተባሉ ፡ ጎጃም ፡ ዲማ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የነበሩ ሊቅ ፡ እንዲህ ፡ ብለዋል ።

ነሥተ ፡ ልዮን ፡ እምድኅረ ፡ ሐነጸ ፡ በንጽሮ ፡ አካል ፡ ዋሕድ ፡ ምንታዌ ፡ ሕንጻ ፡ ማኅደሩ ።
እስመ ፡ ኢከሠተ ፡ ልዮን ፡ ትእምርተ ፡ ጸብዑ ፡ ወፍቅሩ ።

ለንስጥሮስ ፡ እርኩ ፡ ወቈርሎስ ፡ ፀሩ ።
ይቤለነሂ ፡ ንስጥሮሳዊ ፤ አዕጹቀ ፡ ድማኅ ፡ ዘይት ፡ ርቱዕ ፡ ይሰበሩ ።
ሰብአ ፡ ሮምስ ፡ አዕራሬነ ፡ በጽዋዐ ፡ ክህደት ፡ ሰክሩ ።
ጣዕመ ፡ ስቴ ፡ ወይን ፡ ሃይማኖተነ ፡ እስከነ ፡ ወለጡ ፡ ወእምረሩ ።

እምጣነ ፡ ንስጡር ፡ ወልዮን ፡ ዘመሳብከተ ፡ እብን ፡ ተጋብሩ ።
ያገምሩ ፡ በበክልኤ ፡ እንዘ ፡ አሐደ ፡ ኢያገምሩ ።

ኹለተኛውም ፡ የዲማ ፡ ተወላጅ ፡ የኾኑ ፡ የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ባለቤት ።
እመ ፡ ሖረ ፡ ኬልቄዶን ፡ ሕማማ ፡ ለጢሮስ ፡ ልበ ፡ ንስጡር ፡ ንስጥሮሳዊ ፡ ወልዮን ፡ ዓመፃ ፡ (ምንታዌ) ፡ እመ ፡ ይትናገሩ ፡ ባቲ ።
ገብረ ፡ ለአካለ ፡ ቃል ፡ እኅትነ ፡ ዛቲ ።

ብሂለ ፡ ዝንቱ ፡ ወልድየ ፡ ማዕፆ ፡ ዘኢያርኅዎ ፡ መዋቲ ።
ወይን ፡ ርባዕ ፡ ዘኢይሰቴ ።

እስመ ፡ አካለ ፡ ቃል ፡ እኅትነ ፡ ንስቲት ፡ ይእቲ ። ወአጥባት ፡ ምንታዌ ፡ አልባቲ ፡ ብለዋል ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ንስጥሮስና ፡ ልዩን ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ተባባሪዎች ፡ መኾናቸውን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በእርግጥ ፡ ያምናሉ ።

እንግዲህ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነውን ፡ ውሳኔ ፡ እያውቁትም ፤ የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ የነገሯቸው ፡ የተቆራረጡ ፡ ጥቂቶች ፡ ወሬዎች ፡ ናቸው ። ያሉትን ፡ ወደ ፡ መመርመር ፡ እንመለስ ።

አሁን ፡ ትክ ፡ ብለን ፡ የምንመለከተው ፡ ስለክርስቶስ ፡ የሚነገረውን ፡ የቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነን ፡ ምሥጢር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ ልዮን ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፡ ወይም ፡ አውጣኪ ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፡ ንስጥሮስ ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፡ ማለትን ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ አግብተን ፡ የምንመለከተው ፡ አይደለንም ።

ምክንያቱም ፡ እኛ ፡ ሃይማኖታችንን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጽሐፍት ፡ መርምረን ፡ ተረድተን ፡ ይጠቅመናል ፡ ብለን ፡ ከመያዝ ፡ በቀር ፡ በሰው ፡ የማንመራና ፡ በደባልነት ፡ የማንነዳ ፡ በመኾናችን ፡ነው ፡ በርስዎም ፡ በኩል ፡ ሐሳብዎ ፡ እንደዚሁ ፡ ቢኾንልኝ ፡ እወዳለሁ ። በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ብንመረምር ፡ ለክርስቶስ ፡ ፩ ፡ የሚል ፡ አኃዝ ፡ ብቻ ፡ ሲቀጽሉለት ፡ በብዛት ፡ እናገኛለን ፡ እንጂ ፡ ፪ቱ ፡ የሚል ፡ አኃዝ ፡ ሊቀጽል ፡ አንድም ፡ አናገኝም ።

ከሐዋርያት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ ድረስ ፡ በተደረጉት ፡ ጉባኤያት ፡ ኹሉ ፡ የተወሰነችቱ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተነገረችቱ ፡ አርቶዶክስ ፡ ርትዕት ፡ ሃይማኖት ፡ የተባለችቱ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ነበረች ፡ እናውቃለን ፤ እርስዎም ፡ ያውቃሉ ። ይህን ፡ ኑም ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍዎ ፡ በገጽ ፡ ፲፪ ፡ ፊተኞቹ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ያስተምራሉ ፡ ብለው ፡ አረጋግጠዋል ። ይህም ፡ ንግግርዎ ፡ እውነተኛ ፡ መኾኑን ፡ ለመረዳት ፡ በየቱ ፡ ዐበይት ፡ ጉባኤያት ፡ የተወሰነውን ፡ ውሳኔ ፡ እንመርምር ።

(ሀ) አርዮስ ፡ ወልድ ፡ ፍጡር ፡ በመለኮቱ ፡ ባለጊዜ ፡ በኒቅያ ፡ የተሰበሰቡ ፡ ፫፻፲፰ ፡ ሊቃውንት ፡ በእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በእለእስክንድሮስ ፡ አፈጉባኤነት ፡ ተከራክረው ፡ ከረቱት ፡ በኋላ ፡ ወነአምን ፡ በ፩ ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ ዋሕድ ።

ለአብ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ በሚኾን ፡ በጌታ ፡ ባንድ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እናምናለን ፡ ብለው ፩ዱን ፡ ቀጸሉለት ፡ እንጂ ፡ ፪ቱ ፡ ብለው ፡ አልቀጸሉለትም ።

ይህነንም ፡ ሲቀጽሉለት ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ወንጌልን ፡ ሲያስተምር ፡ አንስ ፡ እብለክሙ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ እላችኋለሁ ፡ በማለት ፡ ራሱን ፡ በአንድ ፡ ጾታ ፡ መናገሩን ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ ወ፩ ፡ እግዚእ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስ ፡ ዘኰሉ ፡ በእንቲአሁ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፮ ። በእንተ ፡ ፩ ፡ ብእሲ ፡ ዘውእቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋሁ ፡ ለ፩ ፡ ብእሲ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፲፭ ፡ ፲፮ ። ያለውን ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ከራሳቸው ፡ አንቅተው ፡ አይደለም ።

(ለ) መቅዶንዮስ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሕፁፅ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ የተሰበሰቡ ፡ ፻፶ ፡ ሊቃውንት ፡ በእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በጢሞቴዎስ ፡ ዘአልቦ ፡ ጥሪት ፡ አፈ ፡ ጉባኤነት ፡ ተከራክረው ፡ ረተውት ፡ የሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ ሲወስኑ ፡ ወነአምን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚእ ፡ ማኅየዊ ፡ ዘሠረጸ ፡ እምአብ ። ከአብ ፡ በሠረጸ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እናምናለን ፡ አሉ ፡ አንጅ ፡ (ወእምወልድ ፡ ) ከወልድም ፡ የሠረጸ ፡ ብለው ፡ አልጨመሩም ። ይህንም ፡ ሲናገሩ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መንፈስ ፡ ጽድቅ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምኀበ ፡ አብ ፡ ውእቱ ፡ ሰማዕትየ ፡ ዮሐ ፡ ፲፭ ፡ ፳፮ ።

ከአብ ፡ የሠረፀ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እርሱ ፡ ምስክሬ ፡ ነው ፡ ያለውን ፡ ይዘው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዲያው ፡ ከልቡናቸው ፡ አመንጭተው ፡ አይደለም ።

(ሐ) ንስጥሮስ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባለ ፤ ጊዜ ፡ በኤፌሶን ፡ የተሰበሰቡ ፪፻ ፡ ሊቃውንት ፡ ምንም ፡ ንስጥሮስ ፡ ከጉባኤው ፡ አልቀርብም ፡ ቢል ፡ በቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ አፈ ፡ ጉባኤነት ፡ በነገሩ ፡ ከተስማሙበት ፡ በኋላ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ወሰኑ ፡ እንጂ ፡ በአካልም ፡ በባሕርይም ፡ ቢኾን ፡ ፪ ፡ የሚል ፡ ቅጽል ፡ አልሰጡትም ። ይህም ፡ እርግጠኛ ፡ ቃል ፡ መኾኑን ፡ ርስዎ ፡ ራስዎ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ስለክርስቶስ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ የምታምነው ፡ ትምህርት ፡ በአሳቡና ፡ በአገላለጡ ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በፊት ፡

ልክ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ኹሉ ፡ ያምኑት ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ነው ። ይህም ፡ ትምርት ፡ ለንስጥሮስ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ለአውጣኪም ፡ ባህል ፡ ፈጽሞ ፡ ተቃራኒ ፡ በመኾኑ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ካስተማረወና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በደንብ ፡ ባትወስነው ፡ በኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ይታመን ፡ ከነበረው ፡ ትምህርት ፡ ፈጽሞ ፡ የተስማማ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በገጽ ፡ ፳፭ና ፡ ፳፮ ፡ አረጋግጠዋል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የድንበር ፡ ሽማግሌ ፡ ከኹለት ፡ ጥለኞች ፡ መካከል ፡ ገብቶ ፡ አንተም ፡ ይህን ፡ ተውለት ፤ አንተም ፡ ይህን ፡ ልቀቅለት ፡ ብሎ ፡ እንደሚገላግል ፡ የሮማውም ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ልዮን ፡ በቄርሎስና ፡ በንስጥሮስ ፡ መካከል ፡ ገብቶ ፡ ከንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ አግብቶ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ማለትን ፡ አውጥቶ ፡ ከቄርሎስ ፡ ባህል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ማለትን ፡ ይዞ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ ሠርዞ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ ቢሰብክ ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ይህማ ፡ አባቴ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ንስጥሮስን ፡ ተከራክሮ ፡ የረታበት ፡ ንስጥሮስ ፡ የተወገዘበት ፡ አይደለምን ፤ ንስጥሮስ ፡ የተወገዘበትን ፡ ሃይማኖት ፡ በከፊል ፡ አልቀበልም ፡ ብሎ ፡ መለየቱን ፡ ነግረውናል ። እርስዎም ፡ እውነተኛው ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የወሰነው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በገለጹት ፡ ጽሑፍዎ ፡ ላይ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ በክልኤ ፡ ባሕርያት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መስክረዋል ።

እንግዲህ፡የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ እኛን ፡ ከሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለይተው ፡ ከራሳቸው ፡ ጋራ ፡ ለማሰር ፡ ብለው ፡ የነገሩን ፡ ሐሰተኛ ፡ ወሬ ፡ የትኛው ፡ ፡ ነው ፤ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ከተወሰነውስ ፡ ከፍለው ፡ ያስቀሩብን ፡ የትኛው ፡ ቃል ፡ ነው ፤ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤስ ፡ ባንድ ፡ አካል፡ ኹለት፡ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ምን ፡ ያለውን ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ተነሣና ፡ ፡ ለአንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ፪ቱ ፡ የሚባል ፡ አኃዝ ፡ ሊቀጽልለት ፡ ቻለ ፡ እስኪ ፡ ያስረዱኝ ።

እንግዲህ ፡ የሚለየየን ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ክርስቶስን፡፩ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ ስለኾነ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ፪ ፡ ባሕርያት ፡ ፪ቱ ፡ ፈቃድ ፡ ብሎ ፡ለክርስቶስየሚቀጽልለት፡ ንባብ ፡ ይስጡንና ፡ እንቀበልዎ ። በስተቀር ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዐውቃ ፡ ጠንቅቃ ፡ ያደረገችውን ፡ ነገር ፡ ሳታውቀው ፡ ሳትወደው ፡ ነው ፡ እውነተኛውን ፡ ውሳኔ ፡ አላገኘችውም ፡ እያሉ ፡ ማውራት ፡ ብቻ ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ አይደለም ።

፳፭/ ይኸም ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ እነርሱ ፡ የሚያምኑት ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ በሌሎችም ፡ ሀገሮች ፡ እንደሚታመን፡አድርገው ፡ ይዘውታል ፡ ብለን ፡ ለመጠራጠርም ፡ ያስደፍረናል ፡
ብለዋል ።

፳፮/ እኛ ፡ ይህን ፡ ባህል ፡ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የተወሰነ ፡ በ፫ቱ ፡ ጉባኤያትም ፡ የታመነ፡ ኾኖ ፡ አግኝተነው ፡ ተስማምተን ፡ ይዘነዋል ። ሌሎችም ፡ ይህንን ፡ ባህል ፡ ኪያዙ ፡ ያልለቀቁ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መኖራቸውን ፡ እናምናለን ። ምናልባት ፡ ደግሞ ፡ እርስዎ ፡ እንዳሉት ፡ ይህንን ፡ ባህል ፡ የተዉ ፡ ማኅበሮች ፡ ቢኖሩ ፡ የራሳቸው ፡ ጉዳይ ፡ ነው ፡ እኛን ፡ የሚያሳስበንና ፡ የሚያስጨንቀን ፡ ነገር ፡ አይደለም ።

፳፯/ ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ ከተለየችባቸው ፡ ዋናዎቹ ፡ ምክንያቶች ፡ አንድ ፡ ተብሎ ፡ የሚቈጠረው ፡ ከእስክንድርያ ፡ መንበረ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሥር ፡ መኖሯ ፡ ነው ።

እናቷ ፡ የኾነችው ፡ የእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሮማ ፡ ባትለይ ፡ ኖሮ ፡ ተለይታም ፡ ሳለች ፡ በጠና ፡ እኳኋን፡መንገዱን ፡ አግዳ ፡ ከሮማ ፡ ጋራ ፡ መገናኘትን ፡ ፈጽማ ፡ ሳትነሣት ፡ ኖሮ ፡ ዛሬ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በእርግጥ ፡ ከሮማዊቷ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተነጥላ ፡ አትገኝም ፡ ነበረ ።
ብለዋል ።

፳፰/ ኢትዮጵያ ፡ ከሮማና ፡ ከግብጽ ፡ ከሌሎችም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አስቀድማ ፡ በእእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ ተመራምራ ፡ ከልደተ ፡ ክርስቶስ ፡ በፊት ፡ ሃይማኖተ ፡ ኦሪትን ፡ የተቀበለች ፡ ስለኾነች ፡ የተነገረውን ፡ ትንቢት ፡ የተቈጠረውን ፡ ሱባኤ ፡ ታውቅ ፡ ነበረና ፡ ክርስቶስ ፡ በተወለደ ፡ ጊዜ ፡ ተስፋ ፡ መድረሱን ፡ ሥጋ ፡ መልበሱን ፡ ዐውቃ ፡ ለማጥመቅ ፡ ለማቍረብ ፡ ሥልጣነ ፡ ክህነት ፡ ያለው ፡ አባት ፡ ላኩልን ፡ ስትል ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ላከች ፡ እንጂ ፡ ግብጻውያን ፡ በሐዋርያነት ፡ መጥተው ፡ አስተምረው ፡ ያሳመኗት ፡ ሀገር ፡ አይደለችም ። ኢትዮጵያ ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ከጥንት ፡ ጀምራ ፡ ራሷን ፡ የቻለች ፡ ስለሆነች ፡ እስክንድርያ ን ፡ በርትዕት ፡ ሃይማኖት ጸንታ ፡ ብታገኛት ፡ ተከተለቻት ፡ እንጂ ፡ ይህስ ፡ ባይኾን ፡ አትመስላትም ፡ ነበረ ።

ሮማና ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተለያዩ ፡ በሀገር ፡ ርቀትና ፡ የእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡መንገዱን ፡ ዘግታ ፡ መገናኘት ፡ በመከልከሏ ፡ ምክንያት ፡ ከኾነ ፡ እነሆ ፡ ዛሬ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከግብጽ ፡ ተወላጅ

ጳጳስ ፡ ማስመጣቷ ፡ ቀርቶ ፡ ራሷን ፡ ችላ ፡ ከተወላጆቿ ፡ ጳጳስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ፓትርያርክ ፡ ለመሾም ፡ ችላለች ፡ ከሮማና ፡ ከሌሎችም ፡ ሀገሮች ፡ ጋራ ፡ በአየርም ፡ በባሕርም ፡ ቢኾን ፡ ያለችግር ፡ ለመገናኘት ፡ ች ለች ፡ አሁን ፡ አትቀበላትም ፡ ኖሯልን ፤ የለም ፡ ይህ ፡ የሚናገሩት ፡ ኹሉ ፡ ማስመሰል ፡ ማታለል ፡ ነው ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ አይደለም ።

## የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ስለ ፡ መመራቷ ፡ ምንጭ ።

፩/ የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ከጥንት ፡ ጀምረው ፡ በሕግም ፡ ኾነ ፡ በተግባር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ነበራቸው ፡ በታሪክ ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ እውነቱም ፡ ከ፲፭፻ ፡ ዓመት ፡ የሚበልጥ ፡ የኢትዮጵያን ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የመሩት ፡ አቡኖች ፡ ኹልጊዜ ፡ በእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ የተመረጡ ፡ ግብጻውያን ፡ ነበሩ ፡ ብለዋል ።

፩/ ግብጻውያን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገቡበት ፡ ምክንያት ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ገለጽኩልዎ ፡ መኾኑን ፡ እንዳይዘነጉብኝ ፡ አሳስበዎታለሁ ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ንግግርዎ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ የማስተባብልዎ ፡ ነገር ፡ የለኝም ። ስለሆነም ፡ ከዚህ ፡ ላይ ፡ ሳላስታውስዎ ፡ የማላልፈው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡ ባለፈው ፡ ንግግርዎ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አስቀድማ ፡ በሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ይዛ ፡ ቆይታ ፡ ኋላ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ለመያዝ ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተላለፈች ፡ በማስመሰል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ ተለይታ ፡ ወዳንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ማለፏን ፡ ወይም ፡ በግልጥ ፡ እርሱን ፡ መቀበልዋን ፡ የሚያስረዳ ፡ ወይም ፡ የተለየችበትን ፡ ጊዜና ፡ ዘመን ፡ የሚነግር ፡ ጽሑፍ ፡ አይገኝም ፡ ብለው ፡ ነበር ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ ይህንን ፡ ቃልዎን ፡ ለውጠው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ክርስትናን ፡ ካመነችበት ፡ ከመጀመሪያው ፡ ፬ ፡ ዓመት ፡ ጀምራ ፡ በእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ መመራቷን ፡ ይናገራሉ ፡ ከኒህ ፡ ከኹለቱ ፡ ቃሎችዎ ፡ የሚታመን ፡ እውነተኛ ፡ መስሎ ፡ የሚታየው ፡ የትኛው ፡ መኾኑን ፡ እንዲገልጡልኝ ፡ እለምንዎታለሁ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ እውነተኛው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ያሁኑ ፡ ንግግርዎ ፡ እንደኾነ ፡ አምናለሁ ።

፪/ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ከግቤ ፡ ብርሃን ፡ ሰላማ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጥምቀትን ፡ ለመስበክ ፡ ሥልጣን ፡ ክህነትን ፡ ከእስክንድርያ ፡ መንበረ ፡ ሊቀ ፡ ፡ ጳጳሳት ፡ እንዳመጣና ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በቂ ፡ ባልኾነ ፡ ምክንያት ፡ ኢትዮጵያን ፡ በመጨቆን ፡ ግብጻውያን ፡ ጳጳሳት ሲሾሙባት ፡ መኖርዎን ፤ በሰፊው ፡ አትተው ፡ ጽፈዋል ።

፪/ይህ ፡ ያስተዳደር ፡ ጉዳይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሃይማኖት ፡ ጉዳይ ፡ አይደለም ። ይኸውም ፡ አሁን ፡ ባለንበት ፡ ዘመን ፡ በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ብርታትና ፡ ትጋት ፡ በብፁዕ ፡ ፓትርያርክ፡ አባ ፡ ባስልዮስ ፡ ጸሎት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ስምምነት ፡ በመልካም ፡ አኳኋን ፡ በዜና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኅዳር ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶ ፡ ዓ/ም ፡ የተጻፈ ፡ ስለኾነ ፡ ያንኑ ፡ መመልከት ፡ ይበቃል ብለን ፡ አልፈነዋል ።

## ፬ኛ ፡ ክፍል ።

## ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይመጣ ፡ ስለነበረው ፡ ግብጻዊ ፡ ጳጳስ ፡ ሥራና ፡ ሥልጣን ።

፩/ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከእስክንድርያ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ ከመኖሯ ፡ የተነሣ ፡ ለመሪነት ፡ ከግብጽ ፡ ተሹመው ፡ የሚመጡ ፡ ጳጳሳት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያናቸውን ፡ ባህል ፡ አሳምረው ፡ ለማስተማር ፡ ችለው ፡ ይኾናል ። ስለዚህም ፡ በኹለቱ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መካከል ፡ ጥብቅ ፡ የኾነ ፡ የትምህርት ፡ ተመሳሳይነት ፡ ይገኝ ፡ ይኾናል ፡ ብለው ፡ የሚያምኑ ፡ አይታጡም ፡ ይኾናል ፡ አንዳንዶችስ ፡ እንኳ ፡ እንዲሁ ፡ በግልጥ ፡ የሚሉ ፡ አሉ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ይህ ፡ የማይታመን ፡ መስሎ ፡ ቢታይ ፡ ግብጻዊውን ፡ አቡን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ሃይማኖትን ፡ በሚያይ ፡ ትምርት ፡ ውስጥ ፡ እንዳይገባ ፡ በሕግና ፡ በግብርም ፡ በጥብቅ ፡ ከልክል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ግብጻውያኖቹ ፡ ጳጳሳት ፡ እንዳያስተምሩ ፡ እንዳይሰብኩ ፡ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ ኾነው ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጉዳይ ፡ እንዳይ ናገሩ ፡ በሕግ ፡ ተከልክለው ፡ ነበረ ። በተግባርም ፡ በሚረባ ፡ አኳኋን ፡ አሳባቸውን ፡ ለሕዝብ ፡ እንዳያካፍሉት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ከመነኮሳቱ ፡ ጋራ ፡ እንዳይከራከሩ ፡ ቋንቋቸውን ፡ አያውቁም ፡ ነበረ ። እንዲህ ፡ ባለ ፡ አኳኋን ፡ የግብጺቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የታመነ ፡ መልክተኛ ፡ የኾነው ፡ አቡን ፡ ባህሉን ፡ ለማካፈልና ፡ ለማስፋፋት ፡ ዋና ፡ አስፈላጊ ፡ የኾነውን ፡ የቋንቋ ፡ መግባቢያ ፡ በማጣቱ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ የትምህርቱን ፡ ድምፅ ፡ አሰሚ ፡ ሊኾን ፡ አልቻለም ፡ ሳቡኑ ፡ ማዕርጎችን ከመስጠት ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ ሥልጣን ፡ አልታወቀለትም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ በጠና ፡ አኳኋን፡ የግብጻውያኖቹን ፡ ጳጳሳት ፡ ሥልጣን ፡ መወሰናቸው ፡ የሃይማኖት ፡ ባህላቸውን ፡ የሚጠሉ ፡ ከመኾናቸው ፡ የተነሣ ፡ ይመስለናል ። ብለዋል ።

፩/ የማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ችሎታ ፡ እያለ ፡ በሕግና ፡ በደንብ ፡ መከልከልና፡ በቋንቋ ፡ ባለመተዋወቅ ፡ እንደልብ ፡ በብዛት ፡ ሳይሰብኩ ፡ መቅረት ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ።

ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይላኩ ፡ የነበሩ ፡ ግብጻውያን ፡ ጳጳሳት ፡ ቋንቋ ፡ ካለማወቃቸው ፡ የተነሣ ፡ በአስተርጓሚ ፡ ይሰብኩ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ምናልባት ፡ አስተርጓሚ ፡ ምሥጢር ፡ እያጣው ፡ ነገር ፡ አይከትምና ፡ ቋንቋ ፡ ለቋንቋ ፡ ተስማምቶ ፡ የመነጋገርን ፡ ያህል ፡ እያጠግብም ፡ ተብሎ ፡ ይገመት ፡ ይኾናል ። በዚህ ፡ አስጠግተው ፡ ግብጻውያን ፡ እንዳይሰብኩ ፡ በሕግ ፡ ተከልክለው ፡ ነበረ ፡ ማለትን ፡ ከምን ፡ አግኝተው ፡ ተናገሩት ፤ ይህ ፡ ሕግ ፡ በየትኛው ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ፡ እስኪ ፡ ያስረዱ ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ፡ ብለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ ሊያስረዱ ፡ አይችሉም ፡ ፍጹም ፡ ውሸት ፡ ነው ።

፪/ ኢትዮጵያውያን ፡ እንዲህ ፡ በጠና ፡ አኳኋን ፡ የግብጸውያኖቹን ፡ ጳጳሳት ፡ ሥልጣን ፡ መወሰናቸው ፡ የሃይማኖት ፡ ባህላቸውን ፡ የሚጠሉ ፡ ከመኾናቸው ፡ የተነሣ ፡ ይመስለናል ፡ ብለዋል ።

፫/ ይህን ፡ ያህል ፡ የነገር ፡ አካባቢ ፡ የሚፈጥሩበት ፡ ዘዴ ፡ ለካስ ፡ ይኸ ፡ ኖሯልን ፡ አሁንስ ፡ አገኘሁት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ግብጸውያንን ፡ ራሷ ፡ ፈቅዳ ፡ ለምና ፡ ታመጣቸው ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ በግድ ፡ በጦር ፡ ኃይል ፡ ይመጡባት ፡ ኖሯልን ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ ካቶሊካውያንን ፡ ጠራርጋ ፡ እንዳስወጣቻቸው ፡ እነርሱንም ፡ ጠራርጋ ፡ አታስወጣቸውም ፡ ኖሯልን ፡ ምን ፡ የሚያግዳት ፡ ነበረ ። ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢኾን ፡ በይመስላል ፤ በይኾናል ፡ በያሰኛል ፡ የሚወራ ፡ ወሬ ፡ ኹሉ ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ ከእውነት ፡ የራቀ ፡ መኾኑን ፡ ተገንዝበው ፡ በኢትዮጵያና ፡ በእስክንድርያ ፡ መካከል ፡ የሃይማኖት ፡ ልዩነት ፡ አለ ፡ የሚለውን ፡ ጥርጣሬ ፡ ከልብዎ ፡ ያጥፉ ።

፬/ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ጳጳሶቹ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ የሹመታቸውን ፡ ሥራ ፡ ከመጀመር ፡ በፊት ፡ ስለሃይማኖት ፡ ባህላቸውን ፡ በሚያስጨንቅ ፡ ምርመራ ፡ ይመረመሩ ፡ ነበረ ፡ ይልቁንም ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ በጽኑ ፡ ተመርምረው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ባህል ፡ ተአምኖተ ፡ ሃይማኖት ፡ ሊያደርጉ ፡ ይገደዱ ፡ ነበረ ፡ ይህን ፡ እላደርግም ፡ ያለ ፡ ቢኖር ፡ አይቀበሉትም ፡ ነበረ ፡ ብለዋል ።

፭/ ከዚህ ፡ ላይ ፡ የማስታውሰው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡ ባዬ ፡ ሚናስ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ካቶሊክ ፡ ጳጳስ ፡ መጥቶ ፡ እንጦጦ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበረ ፡ ይባላል ። ያም ፡ ጳጳስ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የ፪ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ የማይቀበሉ ፡ መኾናቸውን ፡ ስላወቀ ፡ ምንምን ፡ ሳይናገር ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ ኖረ ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ቄስ ፡ ዐፄ ፡ ዮሐንስ ፤ ጵራግ ፡ ማሰሬ ፡ ዘመለኮት ፡ የተባሉ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መነኮሳት ፡ ሃይማኖትህ ፡ ምንድነው ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ። ሃይማኖቴ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ ነኝ ፡ አላቸው ። እነርሱም ፡ የእንጦጦ ፡ መምህር ፡ አይናገር ፡ ቢናገር ፡ ባመት ፡ ያውም ፡ ሬት ፡ ብለው ፡ አውግዘውት ፡ ሄዱ ፡ እርሱም ፡ ወዲያው ፡ ተቀሠፈ ፡ ይባላል ።

ምናልባት ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የመጡትን ፡ ጳጳሳት ፡ እንደዚህ ፡ ሳይታወቁ ፡ መስለው ፡ ገብተው ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ እንዳይሰብኩ ፡ ፈርተው ፡ ከየት ፡ መጣህ ፡ ባህልህስ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ በማለት ፡ በርግጥ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ መኾኑን ፡ ለመረዳት ፡ መርምረውት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንጃ ፡ እንጂ ፡ ከቶ ፡ ከእስክንድርያ ፡ መንበር ፡ ተሾሞ ፡ የመጣ ፡ ጳጳስ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ልቀቅ ፡ ተብሎ ፡ ተጠይቆ ፡ አያውቅም ፡ ሊያስረዱት ፡ የማይችሉትን ፡ ነገር ፡ ነው ፡ የሚናገሩ ፡ እስኪ ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ ከኾነ ፡ እገሌ ፡ የሚባል ፡ ግብጻዊ ፡ ጳጳስ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ በማለቱ ፡ ተባረረ ፡ ብለው ፡ ማስረጃ ፡ ያቅርቡ ።

፮/ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የትምህርት ፡ ድርጅት ፡ የካህናቱና ፡ የመነኮሳቱ ፡ ይልቁንም ፡ የነገሥ ፡ ልዩ ፡ ተግባር ፡ ኮነ ። ብለዋል ።

፯/ ኢትዮጵያውያን ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ የሚል ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ባለማቋረጥ ፡ ከልቡናቸው ፡ የሚፈልቅ ፡ ምንጭ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ በርሚል ፡ ውኃ ፡ ከውጭ ፡ ተሞልቶ ፡ ሲፈስ ፡ እንደሚደርቅ ፡ ውኃ ፡ አይደለም ፡ ስለዚህ ፡ ንጉሡም ፡ ካህናቱም ፡ መነኮሳቱም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ትምህርት ፡ ድርጅት ፡ እንደ ፡ ዐይን ፡ ብሌኔ ፡ ይጠባበቁታል ፡ ያውም ፡ ሲኾን ፡ ከግብጻዊ ፡ ጳጳስ ፡ ጋራ ፡ በመስማማት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመለያየት ፡ አይደለም ።

፰/ ስለዚህ ፡ እሲህ ፡ ጳጳሶች ፡ በኢትዮጵያውያኖች ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ እንደማንኛዎችም ፡ የግብጽ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መልክተኞችና ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ሠራተኞች ፡ ተቁጥረው ፡ ይታዩ ፡ ነበረ ፡ ብለው ፡ ለዚሁ ፡ ማዳበሪያ ፡ ዐፄ ፡ ቴዎድሮስ ፡ አቡነ ፡ ሰላማን ፡ ከፍባለ ፡ ዋጋ ፡ ገዝቸዋለሁ ፡ አሏቸው ፤ አሏቸው ፤ መንገም ፡ እንደዚሁ ፡ ተናገርዋቸው ፡ ይባላል ፡ ብለው ፡ ያልተረጋገጠ ፡ አፈ ፡ ታሪክ ፡ ጠቅሰዋል ።

፱/ እኛ ፡ ከከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ ሰላማ ፡ ጀምረው ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ጳጳስ ፡ እስከ ፡ አቡነ ፡ ቄርሎስ ፡ ድረስ ፡ ያሉ ፡ ጳጳሳት ፡ ኹሉ ፡ ክብራቸው ፡ ተጠብቆ ፡ ከመኖር ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ውርደት ፡ የደረሰባቸው ፡ መኾኑን ፡ አናውቅም ፡ በዚያውስ ፡ ላይ ፡ ግብጻውያን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ውርደት ፡ ደረሰብን ፡ ብለው ፡ አቤቱታ ፡ አላቀረቡልም ፡ በእናትና ፡ በልጅ ፡ ወይም ፡ በወንድማማች ፡ መካከል ፡ ገብተው ፡ ይኸን ፡ ሐሰተኛ ፡ ወሬ ፡ ለመፍጠር ፡ ያስገደደዎ ፡ ምንድነው ።

እንግዲህ ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ለመጻፍ ፡ ያሳሰበዎ ፡ በገጽ ፡ ፲፫ ፡ ዛሬ ፡ የወንጌልን ፡ መንፈሳዊ ፡ ሀብት ፡ ለመጠበቅና ፡ እርሱ ፡ ወደሚያመለክተው ፡ ወደ ፡ ጋራ ፡ ከፍተኛ ፡ ዓላማ ፡ ለመድረስ ፡ ክርስቲያኖች ፡ እንዲያብሩና ፡ ኃይላቸውን ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ እንዲያደርጉ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ ያሉት ሐሳብ ፡ መላ ፡ ሐሰት ፡ ማግባቢያ ፡ ኾኖ ፡ እርግጠኛው ፡ ሐሳብዎ ፡ ኢትዮጵያንና ፡ እስክንድርያን ፡ ለማለያየትና ፡ ለማራራቅ ፡ ብቻ ፡ የተመሠረተ ፡ ስብከት ፡ መኾኑን ፡ ተረዳነው ።

ኢትዮጵያ ፡ አሁን ፡ ባለንበት ፡ ዘመን ፡ የግብጽ ፡ ተወላጅ ፡ ብቻ ፡ በልማድ ፡ ሲሾመው ፡ የቆየውን ፡ የጵጵስና ፡ ማዕርግ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ተወላጆች ፡ እንዲሾሙት ፡ ብታደርግም ፡ ኢትዮጵያ ፡



ይህ ሥዕል ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት በአቡነ ዮሳብ እጅ ተቀብተው ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ተብለው ሲሾሙ ግብፃውያንና ኢትዮጵያውያን ጳጳሳት በሥራው ተካፋዮች ሆነው ይታያሉ ይህ የግብፅንና የኢትዮጵያን ጳጳሳት አንድነት ያሳያል ።



ይህ ሥዕል የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ሥዕል ያሳያል ፤ እነርሱም በመካከል ያሉት ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ያሉት ብፁዕ አቡነ [illegible] ዘሐረር ፤ ብፁዕ አቡነ [illegible] ዘሲዳሞ ናቸው ።

በስተግራ ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ዘትግሬ ፤ ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ ዘወለጋ ናቸው ።

እሊህም አቡነ ይስሐቅ [illegible] ቢቀ [illegible] በአቡነ የሐንስ ጅቱ በእስክ የጳጳስ ተቀብተው የተሾሙ ናቸው ።

በኋላ የሚታዩት ደግሞ አቡነ [illegible] ዘ[illegible] ፣ አቡነ ፊልጶስ ዘኢየሩሳሌም ፣ አቡነ ማርቆስ ዘኤርትራ አቡነ ቴዎፍሎስ ዘሐረር ፣ አቡነ ገብርኤል ዘወሎ ናቸው ።

እሊህም በኢትዮጵያዊው ፓትሪያርክ በአቡነ ባስልዮስ ተቀብተው የተሾሙ ናቸው ።

ክርስትናን ከተቀበለችበት ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ በመካከላቸው ፡ ጸንቶ ፡ የኖረው ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ግንኙነት ፡ የተቋረጠ ፡ አይደለም ፡ ወደፊትም ፡ የሚቋረጥ ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ አነጋገርዎ ፡ ርስዎን ፡ ከትዝብት ፡ ላይ ፡ የሚጥል ፡ ስብቅ ፡ ነው ፡ ከመባል ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ መኾኑን ፡ ይረዱት ።

## ፫ኛ ፡ ክፍል ።

### የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ውስጥ ፡ ስላላቸው ፡ ሥልጣን ።

፩/ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ የመንግሥት ፡ ከፍተኛ ፡ ባለሥልጣን ፡ እንደ ነበረ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ሰፊ ፡ ንግግር ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ነገሥታቱ ፡ በሃይማኖት ፡ ጉዳዮችና ፡ ትምህርቶች ፡ ውስጥ ፡ ያላቸው ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ እውነቱ ፡ ምንም ፡ የሕግ ፡ መሠረት ፡ የለውም ፡
ብለው ፡ ነቅፈዋል ።

፪/ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ለመጻፍ ፡ ያተጋዎ ፡ ዋናው ፡ አሳብ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ እንደኾነ ፡ አሳምኖ ፡ የዓለም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ኹሉ ፡ ከሮማው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እግር ፡ በታች ፡ እንዲተዳደሩልዎ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ለዚህም ፡ ጠቃሚ ፡ ኾኖ ፡ የሚገኘው ፡ ነገር ፡ ከብሉይ ፡ ከሐዲስ ፡ ጠቅሶ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ መኾኑን ፡ ማስረዳትና ፡ ማሳመን ፡ ብቻ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ የቃል ፡ ሥጋ ፡ ኩነን ፡ ምሥጢር ፡ ከሚያስረዳ ፡ ግብ ፡ ወጥቶ ፡ ጠቃሚ ፡ ያልኾነውን ፡ ያገር ፡ አስተዳደርን ፡ ነገር መቀባጠር ፡ አስፈላጊ ፡ አልነበረም ።

እርስዎ ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የሚለውን ፡ ባህል ፡ ከብሉይና ፡ ከሐዲስ ፡ ጠቅሶ ፡ ማስረዳት ፡ አስቸጋሪ ፡ ኾኖብዎት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፡ ይህነን ፡ ትተው ፡ በነገር ፡ አካባቢ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ ኖራለችላ ፡ አሰኝቼ ፡ አሁንስ ፡ አባቶቻችን ፡ ወደ ፡ ነበሩበት ፡ ባህል ፡ ብንመለስ ፡ ምን ፡ አለበት ፡ የሚል ፡ አገኛለሁ ፡ መስሎዎ ፡ አስፈላጊዎ ፡ ባልኾነው ፡ በኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አስተዳደር ፡ ገብተው ፡ የጳጳሱ ፡ ሥልጣን ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ የንጉሡ ፡ ሥልጣን፡ ይኸ ፡ ነው ፤ የዕጨጌው ፡ ሥልጣን ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ይደክማሉ ።

ይልቁንም ፡ ይህ ፡ አሁን ፡ የያዙት ፡ እንቀጽ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ዓፄ ፡ ካሌብ ፡ ካቶሊክ ፡ ነበረ ፡ ብለው ፡ ለሚያመጡት ፡ ሐሳብ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሃይማኖት ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚመራ ፡ ከኾነ ፤ ደገኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዓፄ ፡ ካሌብ ፡ ካቶሊክ ፡ ከነበረ ፤ መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በርግጥ ፡ ካቶሊክ ፡ ኖሯል ፡ ለማሰኘት ፡ ይረዳል ፡ ብለው ፡ ያቀዱት ፡ ዘዴ ፡ መኾኑን ፡ ተረድተናል ።

ይህ ፡ ያስተዳደር ፡ ጉዳይ ፤ ኹላችንም ፡ ያልተነጋገርንበት ፡ ስለሆነ ፤ ዋጋ ፡ እንደሌለው ፡ ቈጥሮ ፡ ማለፍ ፡ የሚገባ ፡ ሲኾን ፤ ነገሥታቱ ፡ በሃይማኖት ፡ ጉዳይ ፤ መግባታቸው ፡ የሕግ ፡ መሠረት ፡ የለውም ፡ ብለው ፡ ስለነቀፉ ፡ ለዚህ ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ ግድ ፡ አስፈለገ ፤ ርስዎ ፡ የሕይወት ፡ ታሪክዎን ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ የሀገርዎን ፡ ታሪክና ፡ ወግ ፡ ሕግና ፡ ሥራት ፡ ሳያጠኑ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለተመሩ ፡ ምሥጢሩን ፡ ባያውቁት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ነገሩ ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ፡ የሌላው ፡ ዓለም ፡ ነገሥታትና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ በአምልኮና ፡ በሃይማኖት ፡ ረገድ ፡ አንድ ፡ አይደሉም ።

ቀድሞ ፡ ከዓለም ፡ ነገሥታት ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የማያውቁ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚንቁ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጣዖታትን ፡ የሚያመልኩ ፡ ወይም ፡ ራሳቸው ፡ የሚመለኩ ፡ በጉልበታቸው ፡ የሚመኩ ፡ ነበሩ ። ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ ወንጌልን ፡ አስተምሮ ፡ ሞቶ ፡ ተነሥቶ ፡ ሐዋርያትን ፡ ወንጌልን ፡ ዙራችሁ ፡ አስተምሩ ፡ ብሎ ፡ በላካቸው ፡ ጊዜ ፡ ትምርታቸውን ፡ አንቀበልም ፡ ብለው ፡ በሰይፍ ፡ ይመትሯቸው ፡ የቁልቁሊት ፡ ይሰቅሏቸው ፡ በኩላብ ፡ ያንጠለጥሏቸው ፡ አቍማዳ ፡ ያወጧቸው ፡ በመጋዝ ፡ ይሰነጥቋቸው ፡ ነበረ ።

የሐዋርያትም ፡ መንፈሳዊ ፡ ሥልጣን ፡ ከነገሥታቱ ፡ ሥልጣን ፡ ቢበልጥ ፡ እንጂ ፡ የማያንስ ፡ ስለኾነ ፡ በሌጌዎን ፡ ነጽተው ፡ በነፋስ ፡ ሰቅለው ፡ ገጸ ፡ ከልብ ፡ አሳይተው ፡ በውድም ፡ በግድም ፡ አስጨንቀው ፡ አስጠብበው ፡ በወንጌል ፡ ያሳምኗቸዋል ። ቢያምኑም ፡ አምልኮ ፡ ጣዖትን ፡ ይተዋሉ ፡

ሕገ ፡ ክርስቶስን ፡ ይቀበላሉ ፡ እንጂ ፡ ሕገ ፡ ክርስትናን ፡ እንደ ፡ ሕገ ፡ መንግሥታቸው ፡ አድርገው ፡ ሊጠብቁት ፡ አይችሉም ። ምክንያቱም ፡ የክርስቲያን ፡ መምህራን ፡ በውድም ፡ በግድም ፡ በተአምራት ፡ የወንጌል ፡ ምርኮኞች ፡ ኾነው ፡ ተቀብለውታል ፡ እንጂ ፡ በአእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ ደርሰውበት ፡ ያመኑት ፡ ስላልኾኑ ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ግን ፡ ታሪካቸውን ፡ ቢመለከቱት ፡ ከመጀመሪያ ፡ እንደነዚህ ፡ ኾኖ ፡ አይገኝም ።

(ሀ) ከንግሥተ ፡ አዜብ ፡ አስቀድሞ ፡ እውነትም ፡ ይኹን ፡ ሐሰትም ፡ ይኹን ፡ እርግጠኛው ፡ አይታወቅም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዘንዶ ፡ ታመልክ ፡ ነበረ ፡ እየተባለ ፡ ይተረካል ። ይኹን ፡ እንጂ ፡ የዚህን ፡ ታሪክ ፡ ስንመለከተው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ይህን ፡ ዘንዶ ፡ በኃይለኝነቱ ፡ ሊያሸንፉት ፡ ባለመቻላቸው ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ አድርገው ፡ ገበሩለት ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ አምላክ ፡ አድርገው ፡ ያመለኩት ፡ መኾናቸውን ፡ የሚገልጽ ፡ ጽሑፍ ፡ አናገኝም ።

ይህንም ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ አጋቦስ ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ከወደ ፡ ሐማሴን ፡ መጥቶ ፡ ለዘንዶው ፡ የሚገብሩለትን ፡ ግብር ፡ አይቶ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የምትገብሩለት ፡ ለምንድን ፡ ነው ፤ አትገሉትምን ፡ ቢላቸው ፡ ባንችለው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ወድደን ፡ ነውን ፡ ከቻልክ ፡ አንተ ፡ ግደለውና ፡ እንገዛልሀ ፡ አሉት ።

እርሱም ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ በፍጥነት ፡ የተኛበትን ፡ ሥፍራ ፡ ፯ ፡ ዘር ፡ አጥር ፡ አሳጥሮ ፡ ባራቱ ፡ ማዕዘን ፡ እሳት ፡ ለኩሰበት ፡ ዘንዶው ፡ ከዕንቅልፉ ፡ ተነሥቶ ፡ እወጣለሁ ፡ ቢል ፡ ጭሱና ፡ ወላፈኑ ፡ አፈነው ፡ እንደምንም ፡ ብዬ ፡ እወጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ሲጣጣር ፡ በሰይፍ ፡ ወይም ፡ በምሳር ፡ አናቱን ፡ ብሎ ፡ ገደለው ።

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በዘንዶው ፡ ፈንታ ፡ ገበገቦ ፡ ገዢ ፡ ኾነ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ተመለከ ፡ አይልም ። ይህ ፡ አኳኋን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ አሕዛብ ፡ ጣኦታትን ፡ በማምለክ ፡ ያልተሳሳቱ ፡ ወይም ፡ እኛ ፡ እንመለክ ፡ እስከ ፡ ማለት ፡ ደርሰው ፡ ያልተበቱ ፡ መኾናቸውን ፡ ያስረዳል ።

(ለ) ንግሥተ ፡ አዜብ ፡ የሰሎሞንን ፡ ቤና ፡ መንግሥት ፡ ሰምታ ፡ ጥበቡን ፡ ለመረዳት ፡ በሔደች ፡ ጊዜ ፡ ያስተማራት ፡ ማንም ፡ ሳይኖር ፡ ለይኩን ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ቡሩክ ፡ ዘሠምረ ፡ ያንብርከ ፡ ላዕለ ፡ መንበረ (?) ፡ አትርንስ ፡ እስራኤል ፤ እስመ ፡ አፍቀሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእስራኤል ።

እግዚአብሔር ፡ እስራኤልን ፡ ስለወደደው ፡ በእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ እንድትነግሥ ፡ የፈቀደ ፡ ፈጣሪህ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተባረከ ፡ ይኹን ፡ ብላ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠርታለች ።

ይህም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ የራቁ ፡ ከመኾናቸውም ፡ በላይ ፡ በአእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ ተመራምረው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያወቁ ፡ ለመኾናቸው ፡ በቂ ፡ መረጃ ፡ ሊኾን ፡ ይችላል ።

(ሐ) ቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ በተወለደ ፡ በ፳፪ ፡ ዓመቱ ፡ ካባቱ ፡ ከሰሎሞን ፡ ዘንድ ፡ ሔዶ ፡ እንደ ፡ አሪቱ ፡ ሥራት ፡ ቅብዐ ፡ መንግሥት ፡ ተቀብቶ ፡ በሕግ ፡ ነግሦ ፡ ታቦተ ፡ ጽዮንንና ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ አምጥቶ ፡ ሃይማኖተ ፡ ኦሪትን ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዘርግቷል ። ከዚያ ፡ ጀምሮ ፡ መንግሥተ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከአብራክህ ፡ የተከፈለውን ፡ ልጅህን ፡ በዙፋንህ ፡ አኖርልሃለሁ ።

ልጆችህ ፡ ሕጌን ፡ ቢጠብቁ ፡ ይህን ፡ የማስተምራቸውን ፡ ቢሰሙ ፡ የልጅ ፡ ልጆቻቸው ፡ እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡ በዙፋንህ ፡ ነግሠው ፡ ይኖራሉ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከማለለት ፡ ከዳዊት ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘር ፡ እንዳይወጣ ፤ እነርሱም ፡ ተመርጠው ፡ ሲነግሡ ፡ ከሕግ ፡ ከሥርዓት ፤ እንዳይወጡ ፡ ከአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳይናወጡ ፡ ስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠርተው ፡ እንደአባቶቻቸው ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ሰሎሞን ፤ በካህናት ፡ እጅ ፡ ቅብዐ ፡ መንግሥት ፡ ተቀብተው ፡ ይነግሣሉ ። በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ከነገሡ ፡ በኋላ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከሕገ ፡ መንግሥታቸው ፡ አብልጠው ፡ ይጠብቃሉ ። ሕዝቡንም ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዲጠብቁ ፡ ያስገድዷቸዋል ።

ይኸውም ፡ ሙሴ ፡ ስለጸዓድን ፡ ሰንበትን ፡ ሻርክ ፡ ብሎ ፡ ኢያሱም ፡ አካን ፡ ወልደ ፡ ከርሚን ፡ ለቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲኾን ፡ የተወሰነውን ፡ መባዕ ፡ ደበቅህ ፡ ብሎ ፡ ቅጣት ፡ እንደ ፡ ፈረዱባቸው ፡ ያለ ፡ ነው ።

ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የተማሩ ፡ እንደ ፡ መኾናቸው ፡ መጠን ፡ ካህናቱን ፡ ሕግ ፡ መጠበቃቸውንና ፡ አለመጠበቃቸውን ፡ ይቈጣጠሯቸዋል ። የክህነትን ፡ ሥራ ፡ ግን ፡ እንሥራ ፡ አይሉም ። በዚህም ፡ ላይ ፡ ስለክርስቶስ ፡ መምጣት ፡ የተነገረውን ፡ ትንቢት ፡ የተቈጠረውን ፡ ሱባኤ ፡ ስለሚያውቁ



ይህ ሥዕል ንግሥተ ዐዜብ የሰሎሞንን ዜና መንግሥት ሰምታ ለመጎብኘት በሔደች ጊዜ ማንም ያስተማራት ሳይኖር በሕገ ልቡና እውቀት በእስራኤል ዙፋን ላይ ሲያነግሥህ የወደደ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ብላ እንደ አመሰገነች ያሳያል ነገ ቀዳ፥፲፥፱ ።



ይህ ሥዕል በአብርሃ ወአጽብሐ ዘመነ መንግሥት ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ያመጣውን ፍሬ ምናጦስን ወይም ከሣቴ ብርሃን ሰላማን ያመለክታል ።

እስከ ፡ አብርሀ ፡ ወአጽብሐ ፡ የነበሩ ፡ ነገሥታት ፡ የክርስቶስን ፡ መምጣት ፡ በተስፋ ፡ ይጠባበቁ፡ ነበር ። ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ በኾነበት ፡ ወራት ፡ ሕጽዋ ፡ ለሕንደኬ ፡ በተባለው ፡ ሰው ፡ አማካይነት፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፰ ፡ ፳፮ ።

ከፊልጶስ ፡ እጅ ፡ ጥምቀትን ፡ ተቀብላለች ። ስለኾነም ፡ ይህ ፡ ሕጽዋ፡ ለሕንደኬ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ ያየውን ፡ የሰማውን ፡ ነግሮ ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ሥጋ ፡ እንደ ፡ ለበሰ ፡ ከማሳመን ፡ በቀር ፡ መዓርገ ፡ ክህነት ፡ ስለሌለው ፡ ሳጥምቅ ፡ ሳቍርብ ፡ አላለም ። የሚያጠምቅ ፡ የሚያቈርብ ፡ ሐዋርያ ፡ ስላልተላከ ፡ ሕገ ፡ ክርስትና ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሊስፋፋ ፡ አልቻለም ፤ ከጥቂት ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በአብርሀ ፡ ወአጽብሐ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ በንግድ ፡ ምክንያት ፡ መጥቶ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አስተዳደር ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የተመረኰዘ ፡ መኾኑን፡ከተመለከተ፡በኋላ፡ግዝረተ ፡እሬኢ፡ እምነተ ፡ እሬኢ ፡ ጥምቀትሰ ፡ ወሠሪዐ ፡ ቍርባን ፡ አልቦ ።

በዚህ ፡ ሀገር ፡ ግዝረትና ፡ እምነት ፡ መኖሩን ፡ አያለሁ ፤ ጥምቀትና ፡ ቍርባን ፡ ግን ፡ የለም ፤ ምክንያቱ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ ። ግዝረተ ፡ አምጽኡ ፡ ሌዋውያን ፡ አበዊነ ፡ ወእምነተኒ ፡ አምጽአ ፡ ሕጽዋ፡ ለሕንደኬ ፡ ንግሥተ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለጥምቀትሰ ፡ ወለሠሪዐ ፡ ቍርባን ፡ ኢተፈነወ ፡ሐዋርያ ፡ ኀቤነ ።

ግዝረትን ፡ አባቶቻችን ፡ ሌዋውያን ፡ አመጡልን ፡ እምነትንም ፡ ሕጽዋ ፡ ለሕንደኬ ፡ አመጣልን ፡ ለጥምቀትና ፡ ለቍርባን ፡ ግን ፡ ሐዋርያ ፡ አልተላከልንምና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

አሁንም ፡ አንተ ፡ ሔደህ ፡ ከእስክንድርያ ፡ አምጣልን ፡ ብለው ፡ ስንቅ ፡ ጨምረው ፡ ሰደዱት ። ቢደርስ ፡ ፫፻ ፡ አርዮስን ፡ ረተው ፡ ሃይማኖት ፡ አጽንተው ፡ ሥራት ፡ ሠርተው ፤ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ወስነው ፡ ተለያይተው ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እለእስክንድሮስ ፡ ዐርፎ ፤ አትናቴዎስ ፡ ተሹሞ ፤ አገኘውና ፡ የኢትዮጵያን ፡ እምነት ፡ በሰፊው ፡ አስረድቶ ፡ የተላከውን ፡ ነገረው ፤ ጳጳስ ፡ ሹሞ ፡ እንዲልክላቸው ፡ ለመነው ። አትናቴዎስም ፡ ካንተ ፡ የሚሻል ፡ የለም ፡ አንተ ፡ ፀለመድከው ፡ አስተምራቸው ፡ ሕገ ፡ ወንጌልን ፤ ስበክላቸው ፡ ብሎ ፡ የጵጵስና ፡ ማዕርግ ፡ ሰጥቶ ፡ ሾሞ ፡ ሰደደው ። እርሱም ፡ መጥቶ ፡ በጉባኤ ፡ ኒቅያ ፡ የተወሰነውን ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የምትል ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ሃይማኖትን ፡ አስተማረ ፤ ጥምቀትንና ፡ ቍርባንን ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዘረጋ ። ይህ ፡ ኹሉ ፡ የተደረገ ፡ በነገሥታቱ ፡ በአብርሀና ፡ በአጽብሐ ፡ አማካይነት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሌሎቹ ፡ ሀገሮች ፡ በብዙ ፡ ጻር ፡ ጋር ፡ ያመነች ፡ አይደለችም ። የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ሥራ ፡ በሚሠሩበት ፡ ጊዜ ፡ ሌሎች ፡ የዓለም ፡ ነገሥታት ፡ ይልቁንም ፡ የሮም ፡ ነገሥታት ፡ እነኔሮን ፡ ቄሣር ፡ ሰማዕታተ ፡ ክርስቶስን ፡ ከግሩማን ፡ አራዊት ፡ ጋራ ፡ እያታገሉ ፡ በሰው ፡ ትያትር ፡ ይጫወቱ ፡ ነበረ ።

ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ መንግሥቱ ፤ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘር ፡ ሳይወጣ ፡ የሚነግሡ ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ በጳጳሱ ፡ እጅ ፡ ቅብዐ ፡ መንግሥት ፡ ተቀብተው ፡ ሲነግሡ ፡ ፫፻ ፡ የወሰኗትን ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ ሰላማ ፡ ያስተማራትን ፤ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ የምትል ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖትን ፡ እንዳይለውጡ ፤ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ እንዲጠብቁ ፡ የመሐላ ፡ ቃላቸውን ፡ ሰጥተው ፡ ነው ። ከዚህም ፡ ቢናወጡ ፡ ሕዝቡ ፡ የማይገዛላቸው ፡ መኾኑ ፡ በዐፄ፡ ዘድንግልና ፡ ባጼ ፡ ሱስንዮስ ፡ ታሪክ ፡ ታውቋል ።

ስለዚህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ እንደ ፡ ዖዝያን ፡ በማያገባቸው ፡ ገብተው ፡ የክህነትን ፡ ሥራ፡ እንሥራ ፡ ቅስና ፡ ዲቁና ፡ እንሹም ፡ አይሉም ፡ እንጂ ፡ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዳትለወጥ ፡ ሕገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዳትናወጥ ፡ መጠበቃቸው ፡ የማይካድ ፡ ነገር ፡ ነው ። እንዲያውም ፡ ተላልፈው ፡ ይሞቱላታል ፡ ይኸውም ፡ በዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ታውቋል ።

ዐፄ ፡ ገላውዴዎስ ፡ ግራኝን ፡ አጥፍተው ፡ መንግሥታቸውን ፡ አጽንተው ፡ ተቀምጠው ፡ ሳለ ፡ ድል ፡ ወንበራ ፡ የተባለችቱ ፡ የግራኝ ፡ ሚስት ፡ ኑር ፡ የተባለውን ፡ የግራኝን ፡ የእኅቱን ፡ ልጅ ፡ በጠላትነት ፡ አስነሣችባቸው ፡ ሠራዊቱን ፡ አስከትቶ ፡ መጣባቸው ፡ እርሳቸውም ፡ መኳንንቱን ፡ ሊቃውንቱን ፡ አሰብስበው ፡ እንዋጋን ፡ ወይስ ፡ ምን ፡ እናድርግ ፡ ምከሩ ፡ ቢሏቸው ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ በዚች ፡ ሴት ፡ ፍቅር ፡ ስለተናደደ ፡ የእርስዎን ፡ እራስ ፡ ብቻ ፡ ቆርጦ ፡ ለመሔድ ፡ ይፈልጋል ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ የሚፈልገው ፡ ነገር ፡ የለውም ፤ እርስዎ ፡ የሸሹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግን ፡ ራስዎን ፡ ብቻ ፡ ያድናሉ ፤ ሀገርዎ፡ ትጠፋለች፤ ቤተክርስቲያን፡ ትመዘበራለች፡ አሏቸውም፡ እርሳቸውም፡ ወልድ ፡ ዋሕድ፡ የምትል፡ሃይማኖታችን፡ከምትጠፋ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከምትመዘበር ፡ እኔ ፡ ተለውጬ ፡ ብሞትላት ፡ ይሻለኛል ፡ ብለው ፤ ሔደው ፡ ከኑር ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ተጋጠሙ ። ሠራዊቱ ፡ ጥሏቸው ፡ ሸሸ ፡ ከዚያው ፡ ላይ ፡ ሞተዋል ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ የተባሉት ፡ የደብረ ፡ ሊባኖሱ ፡ መምህርና ፡ ሌሎችም ፡ ብዙዎች ፡ መነኮሳት ፡ አብረው ፡ ሞተዋል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሊቃውንቱ ፡ የሚከተሉትን ፡ ቅኔዎች ፡ ደርሰውላቸዋል ።

## መ ወ ድ ስ ፡

ለገላውዴዎስ ፡ ሰበ ፡ ይቤልዎ ፡ ማእምራን ፡ ዘይመጽእ ፡ ግብር ፡
ባሕቲተከ ፡ ትመውት ፡ እመ ፡ ተጸባዕኮ ፡ ለኑር ።
ወኢይረክባ ፡ ምንሳዌ ፡ ለምድር ።
እመሰ ፡ ኢተጸባዕኮ ፡ ጉንዱየ ፡ ተሐዩ ፡ ወቤቱ ፡ ክርስቲያን ፡ ትትመዘበር ፡ ተሠጥዎሙ ፡ እንዘ ፡
ይብል ፡ ለሰብእ ፡ ውእቱ ፡ ምክር ።
አጥባዕኩ ፡ ለሞቱ ፡ ስደተ ፡ ክርስቲያን ፡ እምእነጽር ።
ወተድባበ ፡ ድንግል ፡ መርዓት ፡ መርዓተ ፡ መርዓዊ ፡ ፍቁር ፡
ውእተ ፡ ጊዜ ፡ በከየት ፡ ወትቤ ፡ እግዚእየ ፡ ወንጉሥየ ፡ ለምኑ ፡ ተኀድገኒ ፡ ወኀበ ፡ አይቴ ፡ ተሐውር ።

## ፪ኛ መ ወ ድ ስ ።

ተድባበ ፡ ማርያም ፡ መርዓት ፤ ዘሊባኖስ ፡ ንእስተ ፡ መጠን ፡ እንዘ ፡ ትብል ፡ ታስቆቁ ፡ በዜማ ኃዘን ።
ወማየ ፡ አንብዕ ፡ ታውኅዝ ፡ እምዓይን ።
ከመ ፡ ንባበ ፡ ኤፍሬም ፡ በድርሳን ።
እስመ ፡ ቅድመ ፡ ገጸ ፡ ነጸረት ፡ ተዘርዎተ ፡ ሕዝባ ፡ ነባብያን ።
ብፅዕት ፡ እምኔየ ፡ ዘኢወለደት ፡ መካን ።
ወአጥባት ፡ እምኔየ ፡ እለ ፡ ኢሐፀና ፡ ደቂቀን ።
ገላውዴዎስሃ ፡ ጼናየ ፡ ቀፀ ፡ ጽጌ ፡ ወይን ።
ቅድመ ፡ ይብጻሕ ፡ ጊዜ ፡ ገሚድ ፡ ዐረረ ፡ ብየ ፡ ዘመን ፡ ወቀሠመ ፡ ብየ ፡ ዘመን ።

እንግዲህ ፡ ከላይ ፡ እንደዘረዘርነው ፡ ልጆችህ ፡ ሕጌን ፡ ቢጠብቁ ፡ የልጅ ፡ ልጆቻቸው ፡ እስከ ፡ ዘለዓለሙ ፡ በዙፋንህ ፡ ይቀመጣሉ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ። ከማለት ፡ ከዳዊት ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ከቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ የተወለዱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ሕገ ፡ ክርስትናን ፡ ራሳቸውን ፡ ከመጠበቅ ፡ አልፈው ሌላውንም ፡ ከማስጠበቃቸው ፡ በላይ ፡ ተላልፈው ፡ የሚሞቱላት ፡ ኾነው ፡ ሲገኙ በመዝሙር ።
ወበህየ ፡ አበቍል ፡ ቀርነ ፡ ለዳዊት ።
ከዚያ ፡ ለዳዊት ፡ ቀንድ ፡ አበቅላለሁ ፡ ማለት ፡ (ህየ ፡ የተባለች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ናት ። )
በኢትዮጵያ ፡ ለዳዊት ፡ መንግሥት ፡ አጸቁማለሁ ።
ወአስተዱሉ ፡ ማኅቶተ ፡ ለመሲሕየ ።
ቀብቼ ፡ ላነገሥኩት ፡ ንጉሥ ፡ መብራትን ፡ አዘጋጃለሁ ፡ ማለት ፡ ሕግ ፡ እሠራለታለሁ ።
ወአለብሶሙ ፡ ኃፍረተ ፡ ለጸላዕቱ ።
ለጠላቶቹም ፡ ኃፍረትን ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ አጐናጽፋቸዋለሁ ።
ወቦቱ ፡ ይፈሪ ፡ ቅድሳትየ ።

በርሱ ፡ ግን ፡ በመመለክ ፡ የጸናሁ ፡ ከፍጡራን ፡ ግብር ፡ የነጻሁ ፡ ከአማልክተ ፡ ሐሰት ፡ ከጣዖታት ፡ የተለየሁ ፡ በሰውና ፡ በመላእክት ፡ እንደበት ፡ መመስገን ፡ የሚገባኝ ፡ የከበርኩ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ መኾኔ ፡ ይገለጸል ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዳዊት ፡ የሰጠው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ተፈጸመ ፡ ያሰኛል ፡ እንጂ ፡ ነውሩ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ እስኪ ፡ ይንገሩኝ ።

ምነው ፡ ሌሎችም ፡ የዓለም ፡ ነገሥታት ፡ እንደነርሱ ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ሲረዱ ፡ ተገኝተው ፤ በተጎዱ ፡ ነበር ። እንግዲህ ፡ የኢትዮጵያ፡ ነገሥታት ፡ ከሃይማኖት ፡ ትምርት ፡ መግባታቸው ፡ ሕጋዊ ፡ ነገር ፡ መኾኑን ፡ ይረዱልኝ ።

፪/ ከኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ንጉሣዊና ፡ ቅዱስ ፡ ከኾነው ፡ ከዳዊት ፡ ዘርዕ ፡ ይወርዳሉ ፡ ተብለው ፡ ስለሚታሰቡ ፡ ወደ ፡ ዙፋናቸው ፡ ወጥተው ፡ ሲቀመጡ ፡ እንደ ፡ ዕብራውያኑ ፡ ጥንታዊ ፡ ልማድ ፡ በተቀደሰ ፡ ቅብዕ ፡ እንደሚቀቡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል ፡ ብለው ፡ እውነተኛውንና ፡ ተገቢውን ፡ ነገር ፡ ባጠራጣሪ ፡ መንገድ ፡ ተናግረውታል።

፪/ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ ከዳዊት ፡ ዘርዕ ፡ የወረዱ ፡ ለመኾናቸው ፡ የያንዳንዳቸውን ፡ ሐረገ ፡ ትውልድ ፡ ቈጥሮ ፡ ለማስረዳት ፡ ይቻላል ። ነገር ፡ ግን ፡ የተነሣንበት ፡ ሥራ ፡ ሌላ ፡ ስለኾነ ፡ ከዚህ ፡ ላይ ፡ መዘርዘር ፡ አላስፈለገም ፡ ቢያስፈልግዎም ፡ ታሪከ ፡ ነገሥት ፡ ይመልከቱ ።

ቅብዐ ፡ መንግሥት ፡ ተቀብቶ ፡ መንገሥንም ፡ ጥንታዊ ፡ ልማድ ፡ በማለት ፡ ነቅፈውታል ።
በዚህም ፡ አነጋገርዎ ፡ ንጉሥ ፡ የሚነግሥ ፡ በራሱ ፡ ኃይልና ፡ ሥልጣን ፡ ነው ፡ ከእግዚአብሔር ፡



ይህ ሥዕል እግዚአብሔር ለዳዊት መንግሥትህን ከዘርኽ አላወጣውም ብሎ በማለለት መሠረት ከቀዳማዊ ምኒልክ ዘርዐ ሳይቋረጥ ወርዶ አሁን ባለንበት በሀያኛው ዘመን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከአባቶቻቸው ከአብ ርሃ ወአጽብሐ ሲያያዝ በወረደው ምርኩት ተቀብተው እንደ ነገሡ ያሳያል ሕገ መን ቍ ፪ ተመልከት ።

መቀበት ፡ እያስፈልግም ፡ ማለት ፡ ስለኾነ ፡ ይሀ ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ንጉሥን ፡ ሊያጣሉበት ፡ ያቀዱት ዘዴ ፡ መስሎ ፡ ታይቷል ።

፪/ በዚሀ ፡ ምክንያት ፡ ኹልጊዜ ፡ እንደ ፡ ተቀደሱ ፡ ሰዎች ፡ ታስበው ፡ ለሕዝብ ፡ ጸዋታና ፡ እርጋታ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ለሃይማኖት ፡ ጥበቃ ፡ እንደተላኩ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ራቢዎች ፡ ስለታዩ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ንጉሥ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እንደራሴ ፡ መኾኑን ክደዋል ።

፫/ የኢትዮጵያ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ መንግሥት ፡ ከዘርህ ፡ አይወጣም ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከማለለት ፡ ከቤተ ፡ ዳዊት ፡ የተወለዱ ፡ ስለኾኑ ፡ በሕግ ፡ በሥርዓት ፡ ሲማሩ ፡ አድገው ፡ በዕውቀታቸው ፡ ተመርጠው ፡ ቅብዐ ፡ መንግሥት ፡ ተቀብተው ፡ ሲነግሡ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከሕገ ፡ መንግሥታቸው ፡ አብልጠው ፡ የሚጠብቁ ፡ መኾናቸው ፡ አይካድም ።

ይህም ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈቀደው ፡ የተቀደሰ ፡ ተግባር ፡ መኾኑ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሐረገ ፡ ትውልዳቸው ፡ ሳይቋረጥ ፡ መንግሥታቸው ፡ ለባዕድ ፡ ሳይሰጥ ፡ በመኖሩ ፡ ይታወቃል ።

፬/ ስለዚሀ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሥርዓት ፡ ሥልጣናቸው ፡ እስከ ፡ ጭራሹም ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ ነው ፡ በኢትዮጵያኖቹም ፡ ዘንድ ከሰሎሞን ፡ ዘር ፡ የሚወለድ ፡ ሊነግሥ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ የማለት ፡ ባህል ፡ በልባቸው ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ የተመሠረተ ፡ ከመኾኑም ፡ የተነሣ ፡ ንጉሥን ፡ መቃወም ፡ ወይም ፡ ከመንግሥቱ ፡ ለማስለቀቅ ፡ መፈተን ፡ የተቀደሰን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ማራከስ ፡ የሚቆጠር ፡ ወንጀል ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ሕዝብንና ፡ ንጉሥን ፡ ለማለያየት ፡ ሞክረዋል ።

፭/ እግዚአብሔር ፡ ቀብቶ ፡ ያነገሠው ፡ ንጉሥ ፡ ከሕግ ፡ ከሥርዓት ፡ ሳይወጣ ፡ እንግዳ ፡ ሃይማኖት ፡ እንግዳ ፡ ባህል ፡ ሳያመጣ ፡ ሃይማኖቱን ፡ ጠብቆ ፡ ፍርዱን ፡ ጠንቅቆ ፡ በሚኖር ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ መሸፈትና ፡ ማመጥ ፡ ሕግ ፡ ያልተሠራላቸው ፡ የአሕዛብ ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የክርስቲያን ፡ ሕግ ፡ አይደለም ። ለንጉሥ ፡ መገዛት ፡ ንጉሥን ፡ ማክበር ፡ እንዲገባ ፡ መጻሕፍት ፡ ተባብረው ፡ ነግረውናል ፡ ወኢታሕስም ፡ ዲበ ፡ መኰንነ ፡ ሕዝብከ ፡ ኢታውርድ ፡ እዴከ ፡ ላዕለ ፡ መሢሐ ፡ እግዚአብሔር ።

ዘሰ ፡ ዐበዮ ፡ ለቄሣር ፡ ዐበዮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሀቡ ፡ ዘነጋሢ ፡ ለነጋሢ ፡ ወዘእግዚአብሔር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፳ ፡ ለኵሉ ፡ ነፍስ ፡ መኰንን ፡ ተኰነኑ ፡ እስመ ፡ ኢይሠየም ፡ መኰንን ዘእንበለ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወእምከመሰ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ኵሉ ፡ ብውሒሎቱ ፡ ወዘሰ ፡ ዐበየ ፡ ተኰንኖ ፡ ለመኰንን ፡ ትእዛዘ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐበየ ። ሮሜ ፡ ፲፫ ፡ ፩ ፡ ፫ ፡ ለእግዚአብሔርኒ ፡ ፍርሀዎ ፡ ወለንጉሥኒ ፡ አክብርዎ ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ፡-፲፯ ፡ እያሉ ፡ መላልሰው ፡ ስለነገሩን ፡ ለንጉሥ ፡ መገዛት ፡ የተቀደሰ ፡ ተግባራችን ፡ ነው ።

ከሰሎሞን ፡ ዘር ፡ የተወለደ ፡ ሊነግሥ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ይሰማቸዋል ፡ ብለው ፡ ስለሚያሽሟጥጡትም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዳዊት ፡ ለዓለም ፡ አስተዴሉ ፡ ዘርዐከ ፡ ወአሐንጽ ለትውልደ ፡ ትውልድ ፡ መንበረከ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ማለለት ። ልጆቹም ፡ ሕጌን ፡ ባይጠብቁ ፡ ትእዛዜን ባይሰሙ ፡ በትንሽ ፡ ተግሣጽ ፡ ይቅር ፡ እላቸዋለሁ ፡ ይቅርታዬን ፡ ግን ፡ ከነርሱ ፡ አላርቅም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ለዳዊት ፡ በቅዱስ ፡ ስሜ ፡ ምየለታለሁና ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ አላፈርስም ፡ ዳዊትን ፡ አልከዳውም ፡ ብሎ መላልሶ ፡ እንደማለለት ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ይነግረናል ፡ መዝ ፡ ፹፱ ፡ ፳ - ፹፰ ።

መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ የሚቀበል ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ይህንን ፡ ቃል ፡ ሊያስተባብል ፡ አይችልም ።

ይህም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለጊዜው ፡ በቤተ ፡ ይሁዳ ፡ ተጠብቆ ፡ መንግሥተ ፡ እሥራኤል ፡ በሮብዓም ፡ ጊዜ ፡ ከኹለት ፡ ቢከፈልም ፡ በ፪ቱ ፡ ነገድ ፡ ያለው ፡ የቤተ ፡ ይሁዳ ፡ መንግሥት ፡ ከቤተ ፡ ዳዊት ከዳዊት ፡ ዘር ፡ ሳይወጣ ፡ ቆይቷል ፡ ተስፋ ፡ በደረሰ ፡ ሥጋ ፡ በለበሰ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ መሲሕ ፡ ክርስቶስን ፡ አልቀበልም ፡ በማለቷ ፡ መንግሥት ፡ ክህነት ፡ ከቤተ ፡ እስራኤል ፡ ጠፍቶ ፡ መኖሩ ፡ የማይካድ ፡ ነው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ግን ፡ የማይታበል ፡ ስለኾነ ፡ ለዳዊት ፡ የማለለት ፡ መሐላ ፡ ከሰሎሞን ፡ በተወለደው ፡ ልጁ ፡ በቀዳማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ዘር ፡ ወርዶ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ በኢትጵዮያ ፡ መንግሥት ፡ ከቤተ ፡ ዳዊት ፡ ሳይወጣ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ።

እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ከሰሎሞን ፡ ዘር ፡ የተወለደ ፡ ሊነግሥ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃዱ ፡ ነው ፡ ቢባል ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ቃል ፡ ተፈጸመ ፡ ያሰኛል ፡ እንጂ ፡ ነውሩ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ስለ ዚህ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዳዊት ፡ የማለለት ፡ መኾኑን ፡ ስለምናውቅ ፡ ከዳዊት ፡ ዘር ፡ ተወልዶ ፡ በሕዝብ ፡ ተመርጦ ፡ በሕግ ፡ ቅብዐ ፡ መንግሥት ፡ ተቀብቶ ፡ የነገሠ ፡ ንጉሥ ፡ ሃይማኖት ፡ ሳይለውጥ ፡ ከሕግ ፡ ከሥርዓት ፡ ሳይናወጥ ፡ አልገዛም ፡ ማለት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አልገዛም ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐውቀን ፡ ከዳዊት ፡ ለተወለደ ፡ ንጉሣችን ፡ እንገዛለን ።

፮/ እነዚህን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ሥልጣን ፡ የሚደግፉ ፡ ኹኔታዎችና ፡ የድሮ ፡ ባህሎች ፡ ለማበረታታትና ፡ የተገቡ ለማስመሰል ፡ የረዳ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለረጅም ፡ ዓመታት ፡ መንፈሳዊ ፡ መሪ ፡ በማጣቷ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ይህም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለረጅም ፡ ዘመናት ፡ ተለይታ ፡ ጳጳሳትና ፡ ካህናት ፡ ባጣችበት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የነገሥታቷ

በሃይማኖት ፡ ጉዳይ ፡ ውስጥ ፡ መግባት ፡ በጣም ፡ በርትቶ ፡ እላይ ፡ ያልነውን ፡ ሥልጣን ፡ እስከማስገኘት ፡ ድረስ ፡ ሥር ፡ ሰዶ ፡ ተመሥረተ ፡ ብለው ፡ ቤተ ፡ መንግሥትንና ፡ ቤተ ፡ ክህነትን ፡ ለማለያየት ፡ ሞክረዋል ።

፰/ የሀገርዎን ፡ ታሪክና ፡ ባህል ፡ ጠንቅቀው ፡ ባለማወቅዎ ፡ ይሆን ፡ የመሰለ ፡ ሕዝብንና መንግሥትን ፡ ቤተ ፡ መንግሥትንና ፡ ቤተ ፡ ክህነትን ፡ የሚያለያይ ፡ ነገር ፡ ይናገራሉ ፡ እንጂ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ እንደሌሎች ፡ የዓለም ፡ ነገሥታት ፡ አይደሉም ፡ ጥንቱንም ፡ ክልደተ ፡ ክርርቶስ ፡ በፊት ፡ ሃይማኖተ ፡ ኦሪትን ፡ ከቤተ ፡ እስራኤል ፡ አምጥታ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የዘረጋች ፡ ንግሥተ ፡ ዓዜብ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ ነቢያት ፡ ካህናት ፡ መጥተው ፡ ሰብከው ፡ ያሳመኗት ፡ ሀገር ፡ አይደለችም ፡ ኋላም ፡ በዘመነ ፡ ሐዲስ ፡ ነገሥታቱ ፡ አብርሃና ፡ አጽብሐ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስን ፡ ልከው ፡ ሕገ ፡ ክርስትናን ፡ አስመጥተው ፡ ወንጌል ፡ እንድትነገር ፡ አድርገዋል ፡ እንጂ ፡ እንደሌሎቹ ፡ አህጉር ፡ ሐዋርያ ፡ ተልኮ ፡ በብዙ ትግል ፡ ያሳመናት ፡ ሀገር ፡ አይደለችም ።

በሀገር ፡ መታወክና ፡ በመንገድ ፡ መራቅ ፡ ምክንያት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መንፈሳዊ መሪ ፡ ያጣችበት ፡ ጊዜ ፡ መኖሩ ፡ የማይካድ ፡ ቢኾንም ፡ ይህ ፡ የጳጳሳቱ ፡ አለመምጣት ፡ የጨመረላቸው ፡ ኃይል ፡ የለም ፡ ቢኖርም ፡ የሚቀነስባቸው ፡ ሥልጣን ፡ አልነበረም ፤ የሚቀነስባቸው ፡ ሥልጣን ኖሮ ፡ የጳጳሳቱን ፡ መምጣት ፡ የማይፈቅዱትስ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ከእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ተላልከው ፡ ተነጋግረው ፡ የሚያስመጥዋቸው ፡ ነገሥታቱ ፡ ስለኾኑ ፡ ሊያስቀሩዋቸውም ፡ በቻሉ ፡ ነበረ ።

እነርሱ፡ግን ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ቀብተው ፡ የሚያነግሡዋቸው ፡ የሚመክሩዋቸው ፡ የሚያስተምሩዋቸው ፡ የሚጸልዩላቸው ፡ ስለኾኑ ፡ አክብረው ፡ ያኖሩዋቸው ፡ እንጂ ፡ የሥልጣን ፡ ተጋፋፊ ፡ አስመስለው ፡ አይመለከቷቸውም ፡ ካህናቱም ፡ እንደዚሁ ፡ አግርር ፡ ፀሮ ፡ ወጸላዕቶ ፡ ዕቀብ ፡ ንግሦ ፡ ወሠራዊቶ ፡ እያሉ ፡ ሲጸልዩላቸው ፡ ይኖራሉ ፡ እንጂ ፡ እርስዎ ፡ እንዳመለከቱት ፡ አመራር ፡ በመገባባት ፡ ዐይን ፡ እየታያዩ ፡ የኖሩ ፡ አይደሉም ። ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ለመጻፍ ፡ ያሳሰበኝ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ አንድነት ፡ ለማደስ ፡ ይረዳል ፡ ብየ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የገለጹትን ፡ ሐሳብ ፡ በመለወጥ ፡ ከመንግሥት ፡ ፖለቲካ ፡ ገብተው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ መዘባረቅዎ ፡ አነሣሥዎን ፡ ከሌላ ፡ ግምት ፡ ላይ ፡ ያዋለው ፡ መኾኑን ፡ ለመግለጽ ፡ ነው ።

፱/ ነገሥታቱ ፡ በጊዜው ፡ ኹኔታዎች ፡ ተገድደው ፡ ከውስጥም ፡ አረማውያን ፡ ከውጭም ፡ እስላሞች ፡ መንግሥታቸውን፡ እንዳይለያዩባቸውና ፡ እንዳይበታትኑባቸው ፡ የሚያስፈራ ፡ ነበረና ፡ አገሪቱን ፡ ከዚህ ፡ አደጋ ፡ ለማዳን ፡ መንግሥቱም ፡ ሕዝቡም፡ በጸጥታ ፡ እንዲኖር ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ በሃይማኖትም ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ ለማድረግ ፡ ሊያስቡበት ፡ ግድ ፡ ኾነባቸው ፤ እንዲህም፡ ባለ ፡ አኳኋን ፡ በነዚያ ፡ ዘመናት ፡ ስለሃይማኖትና ፡ ስለ ፡ ሥርዓተ ፡ አምልኮ ፡ እያሰቡ ፡ መንፈሳውያን ፡ መሪዎች ፡ ሊኾኑ ፡ ግድ ኾነባቸው ፡ ብለዋል ።

፲/ በዚያ ፡ ዘመናት ፡ ብለው ፡ ጊዜ ፡ መወሰንዎ ፡ ብቻ ፡ ተሳስተዋል ፡ እንጂ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታትስ ፡ ለአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀናተኛ ፡ የኾነው ፡ የዳዊት ፡ ዘሮች ፡ እንደ ፡ መኾናቸው ፡ መቸም ፡ መች ፡ ቢኾን ፡ አገሪቱን ፡ ካደጋ ፡ ለማዳን ፡ መንግሥቱም ፡ ሕዝቡም ፡ በሃይማኖት ፡ በምግባር ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ ለማድረግ ፡ መንፈሳውያን ፡ መሪዎች ፡ መሆናቸው ፡ የማይጠረጠር ፡ ነገር ፡ ነው ።

፲፩/ አንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ስንኳ ፡ የተቀደሱና ፡ በጥብቅ ፡ የሃይማኖት ፡ ጉዳይ ፡ የኾነውን ፡ ሥራ ፡ የሚፈጽሙበት ፡ ማዕርግ ፡ ሳይቀር ፡ የነበራቸው ፡ ይመስላል ።

ረ/ ሲፈኸር ፡ አቡ ፡ ሳሊህ ፡ የተባለው ፡ ያረብ ፡ ክርስቲያን ፡ ጸሐፊ ፡ በ፲፫ኛ ፡ ዓ/ም ፡ የነበረው ፡ የዘመኑን ፡ ቅብጦች ፡ አሳብ ፡ ሲገልጥ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ ቄሶች ፡ ናቸው ፡ ሲል ፡ ጽፏል ፡ በመካከለኛ ፡ ዘመን ፡ ያበሻ ፡ ሀገር ፡ በእስላሞች ፡ በተለይም ፡ በግብጽ ፡ እስላሞች ፡ ስበብ ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ለብቻዋ ፡ ስለተለየች ፡ ይህ ፡ መለየትዋ ፡ ምንም ፡ እን ኳን ፡ ከእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ጋራ ፡ በደንብ ፡ መገናኘትዋን ፡ ፈጽሞ ፡ ባያግደው ፡ እያሌ ፡ ችግሮች ፡ እንደደረሱባት ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ጳጳሳቱ ፡ ያለማጸረጥ ፡ እየተሾሙ ፡ እንዳይመጡ ፡ ችግር ፡ እንደተፈጠረባት ፡ ይህም ፡ ችግርና ፡ ማገኛ ፡ ያበሻ ፡ ነገሥታትን ፡ በሃይማኖት ፡ ጉዳይ ፡ ለማሠልጠን ፡ አሳምሮ ፡ እንደረዳና ፡ ምክንያት ፡ ሊኾን ፡ እንደቻለ ፡ አለመዘንጋት ፡ ነው ፡ ይላል፡ ብለዋል ።

፲፪/ ከላይ ፡ እንዳልነው ፡ ይህ ፡ ጸሐፊ ፡ ጊዜ ፡ መወሰኑ ፡ ብቻ ፡ ተሳስቷል ፡ እንጂ ፡ የኢትዮጵያ ነገሥታት ፡ ማናቸውንም ፡ ሥልጣነ ፡ ክህነት ፡ ቢቀበሉ ፡ የሚከለክል ፡ ነውር ፡ የሌለባቸው ፡ በሕገ ፡ እግዚአቤሔር ፡ የጸኑ ፡ መቸም ፡ ቢሆን ፡ በሃይማኖት ፡ በምግባር ፡ ጉዳይ ፡ የሠለጠኑ ፡ በጠቅላላው ፡ መንፈሳውያን ፡ ግብረ ፡ ገቦች ፡ መኾናቸው ፡ አይካድም ፡ ስለዚህ ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ሳሉ ፡ የብሕትውና ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ የነበሩ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ፡ ይኸውም ፡ ሊቃውንቱ ፡ በሚያበረክቱዋቸው ፡ ቅኔዎችና ፡ ራሳቸውም ፡ በሚቀኙዋቸው ፡ ቅኔዎች ፡ ይታወቃል ።

(ሀ) ራስ ፡ ዓሊ ፡ የተባሉት ፡ መስፍን ፡ በውስጥ ፡ የሚሠሩት ፡ ትሩፋት ፡ አንዷቸው ፡ ጨርሶ ለመመነንና ፡ ጥሎ ፡ ለመሔድ ፡ ያስቡ ፡ ነበረ ፡ ይህን ፡ የሚያውቅ ፡ ሊቅ ፡ የሚከተለውን ፡ ቅኔ ፡ አበረከተላቸው ።

ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ዜና ፡ ጽድቅ ፡ ተሰአል ፡ እምላሊበላ ፡
ወዕራቀከ ፡ ኢትቁም ፡ እምንዋየ ፡ ዓለም ፡ ዛቲ ።
ዚአከ ፡ ወዘላሊበላ ፡ እስመ ፡ ምድር ፡ አሐቲ ።
ወልቡናከ ፡ ኢይድከም ፡ ሆለሄ ፡ በእግረ ፡ ልቡና ፡ ሐታቲ ፡
በፍቅር ፡ (መንገለ ፡ ዋልድባ ፡ ወአብረንታንቲ ፡
እመሰ ፡ ተአምር ፡ ባቲ ። ገረገራ ፡ ዋልድባ ፡ ይእቲ ።

(ለ) የጎጃሙ ፡ መስፍን ፡ ደጃዝማች ፡ ጎሹ ፡ ዘውዴ ፡ በዓለም ፡ ተቀምጠው ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ እየሠሩ ፡ የመናኒ ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ ነበረ ፡ ይህን ፡ ያወቀ ፡ ሊቅ ፡ ይህን ፡ መወድስ ፡ አበረከተላቸው ።

ዕጹብ ፡ ውእቱ ፡ ንብረተ ፡ ዚአከ ፡ ደጃዝማች ፡ ጎሹ ፡ ዘሐርከ ፡ ለሰሚዐ ፡ ዕጹብ ፡ ዜና
በፍኖተ ፡ ዓለም ፡ ካልእ ፡ ወበዘክርስቶስ ፡ ፍና ፤
ነሚእ ፡ ጸባሕት ፡ በዘይደሉ ፡ ወውሂብ ፡ ለዘይደልዎ ፡ በስፋሕ ፡ ልቡና ፡
አምጣነ ገበርከ በዋሕድና ከዊነ ነዳይ ትሑት ወከዊነ ንጉሥ በልዕልና
እፎኑመ ፡ ተጋብኡ ፡ በዘዚአከ ፡ ሰብእና ።

ግዕዘ ፡ ወልደ ፡ ዕሜይ ፡ ለተልዕሎ ፡ ወግዕዘ ፡ እንጦንዮስ ፡ ለጽሙና ፡ ወእሮ ፡ ተፈጸመ ፡ ለከ ፡ ዘኢይፈጽሞ ፡ ሕሊና ።
መንኖተ ፡ ዓለም ፡ ምስለ ፡ ዓለም ፡ ወምስለ ፡ ሠራዊት ፡ ብሕትውና ።

(ሐ) አድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ትተው ፡ ስለመነኑ ፡ አለቃ ፡ ናሁዳ ፡ የተባሉት ፡ ሊቅ ፡ የሚከተለውን ፡ መወድስ ፡ ደርሰውላቸዋል ።

ሆሉ ፡ ይትኀደግ ፡ እመ ፡ ኀደግዎ ፡ ምሳሌ ፡ ዝኒ ፡ ነገር ፡ እምሐልዮ ፡ መንበረ ፡ ምጡቅ ።

አምጣነ ፡ ኢያሱ ፡ ኀደገ ፡ ተድላ ፡ መንበሩ ፡ ዘወርቅ ፡
ወከዊኖተ ፡ ንግድ ፡ በበብሔሩ ፡ ኢያስተዐፀበ ፡ ያዕቆብ ፡ ልሒቅ ፡
በእንጸረ ፡ አብርሃም ፡ ወይስሐቅ ፡ ትሩፋነ ፡ እሉሰ ፡ ንሕነ ፡ ሐለፍተ ፡ ፍና
እንበለ ፡ ሰንቅ ።

ለጽድቅ ፡ ኢንዜክራ ፡ ወኢትዜከረነ ፡ ጽድቅ ፡
እስመ ፡ ጊዜ ፡ ብዕልነ ፡ ንትዔበይ ፡ ወጊዜ ፡ ንዴትነ ፡ ንሰርቅ ፡
ትካዝነሂ ፡ ካልእ ፡ እምትካዘ ፡ ጳውሎስ ፡ ሊቅ ።
እስመ ፡ ዘኢየሐልቅ ፡ መሰለነ ፡ ንብረተ ፡ ዓለም ፡ ዘየሐልቅ ።
ይህ ፡ ባለቅኔ ፡ የዐፄ ፡ ኢያሱን ፡ መናኒነትና ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅ ፡ የያዕቆብን ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ፈላሲ ፡ ሆኖ ፡ መኖር ፡ ለራሱና ፡ ድርሰቱን ፡ ለሚሰማ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተግሣጽና ፡ ምክር ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ጠቀሰው ፡ ማስተዋል ፡ ተገቢ ፡ ነገር ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ በርትዕ ፡ ከሚሠራው ፡ ሃይማኖት ፡ ምግባር ፡ አልፈው ፡ ተርፈው ፡ ለትሩፋት ፡ ይህን ያህል ፡ የሚተጉ ፡ ነገሥታት ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ቢገኙ ፡ ነውሩ ፡ ምንድን ነው ፡ በእውነቱ ፡ በማያገባዎ ፡ በመንግሥቱ ፡ አስተዳደር ፡ ገብተው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ መዘባረቅ ፡ ታላቅ ስሕተት ፡ ነው ።

## ፯ኛ ፡ ክፍል ።

## ስለ ፡ ዕጨጌ ፡ አስተዳደርና ፡ ሥልጣን ።

፩/ ግብጻዊ ፡ ጳጳስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ ሊኖረው ፡ ይገባው ፡ ለነበረው ፡ ሥልጣን ፡ የንጉሡ ፡ ሥልጣን ተወዳዳሪ ፡ በመኾኑ ፡ ላይ ፡ የዕጨጌው ፡ ሥልጣን ፡ አሳነሰው ፡ በማለት ፡ ብዙ ፡ ሐተታ ፡ ከጻፉ ፡ በኋላ ፡ ከ፲ ፯፻ ዓ/ም ፡ ጀምሮ ፡ ስለክርስቶስ ፡ ቅብዐት ፡ በሚያስተምሩት ፡ ልዩ ልዩ ፡ ትምህርት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ስምምነትን ፡ የነሣ ፡ ክርክር ፡ አለ ። ስለዕጨጌና ፡ ስለ ፡ አቡኑም ፡ አለመስማማት ፡ በተባለው ፡ ክርክር ፡ የተነሡትን ፡ ኹለቱን ፡ ወገኖች ፡ ማስታወስ ፡ ይበቃል።

ከነዚህ ፡ ወገኖች ፡ አንዱ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ የተዋሕዶዎች ፡ የጸጋ ፡ ልጆች ፡ ወይም ፡ የ፫ ፡ ልደት ፡ እየተባለ ፡ በዕጨጌው ፡ ይመራ ፡ ነበረ ። ኹለተኛው ፡ የጎጃሜዎች ፡ የቅባቶች ፡ ወይም ፡ የካራ ፡ ወይም ፡ የኹለት ፡ ልደት ፡ እየተባለ ፡ በአቡኑ ፡ ይመራ ፡ ነበረ ፡ ኹለቱም ፡ ወገኖች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርት፡ የበላይነትን፡ ለማግኘት፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ጀምረው ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲከራከሩ ፡ ኖረዋል ፡ ብለው ፡ ዝብርቅርቅ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ተናግረዋል ።

፩/ (ሀ) የአቡኑን ፡ ሥልጣን ፡ የንጉሡና ፡ የዕጨጌው ፡ ሥልጣን ፡ አሳነሰው ፡ ለሚሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስተዳደር ፡ ከሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አስተዳደር ፡ የተለየ ፡ ነው ፡ ሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ከመንፈሳዊ ፡ መብታቸው ፡ አልፈው ፡ በሥጋዊ ፡ አስተዳደር ፡ የሚያገባቸው ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸው ፡ አይመስለኝም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ ከነገሥታቶቿ ፡ ደግነት ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ከመንግሥቷ ፡ ሀብት ፡ በሲሶ ፡ ተካፋይ ፡ ናት ። በየጊዜው ፡ የሚሰጧት ፡ ርስት ፡ ጉልት ፡ ሰፊ ፡ ነው ። ይህም ፡ ክርስቷ ፡ ከጉልቷ ፡ የሚገኘው ፡ ግብር ፡ ዐሥራት ፡ የዳኝነት ፡ ገቢ፡የገበያ፡ቀረጥ ፡ ኹሉ ፡ ለራሷ ፡ ገቢ ፡ ነው ፡ መንግሥት ፡ አይነካባትም

ስለዚህ ፡ ለሀብቷ ፡ ሰብሳቢ ፡ መሾም ፡ አስፈለጋት ። ይህን ፡ መብት ፡ ግብጻዊ ፡ ጳጳስ ፡ ይዞ ፡ እንዳይሠራበት ፡ ኹለት ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገሮች ፡ አሉ ።

፩ኛ/ ይህ ፡ ግብጻዊ ፡ ጳጳስ ፡ ይህን ፡ ሥልጣን ፡ ይዞ ፡ እንዳያስተዳድር ፡ የሀገሩን ፡ ቋንቋና ፡ ልማድ ፡ የማያውቅ ፡ እንግዳ ፡ መኾኑ ፡ ያስቸግረዋል ።

ኹለተኛውም ፡ ከሀገሩ ፡ ተመርጦና ፡ ተሾሞ ፡ የመጣበት ፡ ዋናው ፡ ተግባሩ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ የምትል ፡ ሃይማኖትን ፡ ጠብቆ ፡ ቄስ ፡ ዲያቆን ፡ ሊሾም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሥጋዊ፡ አስተዳደር፡ገብቶ ርስት ፡ ጉልት ፡ ሊያካፍል ፡ ግብር ፡ ሊቀበል ፡ ያልመጣ ፡ መኾኑ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ለጳጳሱ ፡ ሃይማኖት ፡ ማስተማር ፡ ቅስና ፡ ዲቁና ፡ መሾሙ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ሌላውም መብቱ ፡ ተጠብቆለት ፡ ሥጋዊ ፡ አስተዳደርን ፡ ለሚመለከት ፡ ሀብቷ ፡ ሰብሳቢ ፡ ዕጨጌው ፡ ኹኖ ሊቀ ፡ ካህናቶችንና ፡ አለቆችን ፡ በያንዳንዱ ፡ ወረዳና ፡ ደብር ፡ መሾም ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

(ለ) ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ቅብዐት ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ስምምነትን ፡ የነሣ ፡ ክርክር ፡ አለ ፡ ስለሚሉት ፡ መጻሕፍት ፡ ነሥአ ፡ ተወክፈ ፡ ያሉትን ፡ ይዘው ፡ ይህ ፡ ንሥኢት ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ አደረገው ፡ ወይም ፡ የጸጋ ፡ ልጅ ፡ አደረገው ፤ ወይም ፡ አልረባውም ፡ አልጠቀመውም ፡ በማለት ፡ መከራከራቸው ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ስለኾነም ፡ ይህ ፡ ንግግራቸው ፡ ያንድ ፡ አባት ፡ ያንድ ፡ እናት ፡ ልጆች ፡ ከእናት ፡ ካባታቸው ፡ ቤት ፡ ሲያድጉ ፡ እንደሚጋጩት ፡ ያለ ፡ የቤት ፡ እንጉርጉሮ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከ፫ቱም ፡ ወገን ፡ ቢኾን ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ የሚደግፍ ፡ አይገኝባቸውም ።

(ሐ) ከነዚህም ፡ ወገን ፡ አንዱ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖሶች ፡ የተዋሕዶዎች ፡ የጸጋ ፡ ልጆች ፡ ወይም ፡ የ፫ ፡ ልደት ፡ እየተባለ ፡ በዕጨጌው ፡ ይመራ ፡ ነበረ ። ኹለተኛውም ፡ የጎጃሜዎች ፡ የቅብዐቶች ፡ የካራ ፡ ወይም ፡ የኹለት ፡ ልደት ፡ እየተባለ ፡ በአቡኑ ይመራ ፡ ነበረ ። ስለሚሉት ።

የኢትዮጵያ ፡ ወግ ፡ ታሪክ ፡ ካልፎ ፡ ሃጅ ፡ መንገደኛ ፡ ጠይቆ ፡ የታሪኩን ፡ አያያዝ ፡ እንዲህ ፡ እግር ፡ በራስ ፡ እያደረጉ ፡ ከማማታት ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንትና ፡ መምህራንን ፡ ጠይቀው ፡ ቢኾን ፤ ሲኾን ፡ ወደ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ከመሳብ ፡ በዳኑ ፡ ነበር ፡ ይህም ፡ ባይኾን ፡ የታሪኩን ፡ አያያዝ ፡ እንዲህ ፡ ጥፍትፍት ፡ አድርገው ፡ አያመጡትም ፡ ነበረ ። የባህሎች ፡ አኳኋን ፤ የታሪኩ ፡ አያያዝ ፡ እንዲህ ፡ እንደሚሉት ፡ አይደለም ። የታሪኩን ፡ አያያዝ ፡ የባህሎችን ፡ አኳኋን ፡ በደንብ ፡ በደንብ ፡ አድርጌ ፡ እንዳላስረዳዎ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ የሚሹት ፡ ለትንኮል ፡ በሰላማዊ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ የርስ በርስ ፡ መለያየትን ፡ ለመፍጠር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሊጠቀሙበት ፡ አይደለም ።

ስለዚህ ፡ ለተንኮል ፡ ረዳት ፡ መኾን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ የማያሰኝ ፡ ሥራ ፡ በመኾኑ ፡ አብራርቼ ፡ ላስረዳዎ ፡ አልፈቀድኩምና ፡ የባህሉን ፡ አያያዝ ፡ የታሪኩን ፡ ኹኔታ ፡ ጠይቀው ፡ ጠንቅቀው ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ መልሱን ፡ በሚገባ ፡ አድርጌ ፡ እጽፍልዎታለሁ ።

(መ) በኢትዮጵያ ፡ የተሾሙ ፡ ዕጨጌዎችና ፡ አቡኖች ፡ ከላይ ፡ እንደዘረዘርኩልዎ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ጸንተው ፡ በየመብታቸው ፡ ተወስነው ፡ ቤተ ፡

ክርስቲያንን ፡ ሲመሩ ፡ ከመኖር ፡ በቀር ፡ በሃይማኖት ፡ የተለያዩበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ፡ ፍጹም ፡ ውሸት ፡ ነው ።

፪/ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከመረመርናቸው ፡ ኹኔታዎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሮማ ፡ መለየት ፡ በትምህርት ፡ ምክንያት ፡ አለመኾኑ ፡ እንዲሁም ፡ ከእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘንድ ፡ ተልከው ፡ ይመጡ ፡ የነበሩት ፡ ከሮማ ፡ ጋራ ፡ ለማጣላትም ፡ ወይም ፡ ትምርታቸውን ፡ ለማስፋፋት ፡ ብለው ፡ የሚያደርጉት ፡ ሥራቸው ፡ ያለፍሬ ፡ ከንቱ ፡ ኾኖ ፡ መቅረቱ ፡ በግልጥ ፡ ይታወቃል ፡ ብለዋል ።

፫ (ሀ) ከእስክንድርያ ፡ እየተላኩ ፡ ይመጡ ፡ የነበሩ ፡ ጳጳሳት ፡ ገና ፡ የሹመታቸውን ፡ ተግባር ፡ ከመጀመራቸው ፡ በፊት ፡ ስለሃይማኖት ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ ያላቸውን ፡ ባህል ፡ በሚያስጨንቅ ፡ ምርመራ ፡ ተመርምረው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ባሕል ፡ እንዳይዙ ፡ የሚገደዱ ፡ ከኾኑ ።

(ለ) ግብጻዊ ፡ ጳጳስ ፡ ሃይማኖትን ፡ በሚያይ ፡ ትምርት ፡ እንዳይገባ ፡ የተከለከለ ፡ ከኾነ ።

(ሐ) ሥልጣኑን ፡ ንጉሡና ፡ ዕጨጊው ፡ ወስደውበት ፡ ስለሃይማኖት ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ እንዳይሰብክ ፡ የተከለከለ ፡ ከኾነ ።

(መ) አሁን ፡ እንደሚሉት ፡ ከእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ተልከው ፡ ይመጡ ፡ የነበሩ ፡ ጳጳሳት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከሮማ ፡ አጣልተው ፡ ትምህርታቸውን ፡ ለማስፋፋት ፡ የሚደክሙት ፡ ድካም ፡ ከንቱ ፡ ኾኖ ፡ ከቀረ ።

(ሠ) ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ የተለየች ፡ በትምህርት ፡ ምክንያት ፡ ካልኾነ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ሮማ ፡ የተለያዩ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ሊሉ ፡ ነው ፡ ይኾን ፡ ይህ ፡ አነጋገርዎ ፡ ወደ ፡ እውነት ፡ ወደብ ፡ የሚጠጋበት ፡ መንገድ ፡ አጥቶ ፡ ቀዛፊ ፡ ሳይኖረው ፡ ማዕበል ፡ ሞገድ ፡ እንደሚያማታው ፡ ጀልባ ፡ ሲንገዋለል ፡ ይታያል ፡ እውነቱን ፡ ሐሰት ፡ ሐሰቱን ፡ እውነት ፡ አደርጋለሁ ፡ ብሎ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ መባዘቅ ፡ እጅግ ፡ ያሳዝናል ።

እነሆ ፡ አሁን ፡ ባለንበት ፡ ዘመን ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ወይም ፡ የግብጽ ፡ እስላሞች ፡ መንገድ ፡ ሊከለክሉ ፡ ባለመቻላቸው ፡ ሮማና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያለችግር ፡ ለመገናኘት ፡ ችለዋል ። ነገሩ ፡ እውነት ፡ ከኾነ ፡ ማንም ፡ አልፎ ፡ ሐጂ ፡ የጻፈውን ፡ ታሪክ ፡ እያጠራቀመ ፡ ከመዘባረቅ ፡ ግራ ፡ ቀኛችንም ፡ ከማንነቅፋቸው ፡ ከብሉያት ፡ ከሐዲሳት ፡ ጠቅሶ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድም ፡ የሚሠርጽ ፡ መኾኑን ፡ ክርስቶስ ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ መኾኑን ፡ ንባብ ፡ አምጥቶ ፡ ማስረዳት ፡ አይሻልም ፡ ነበርን ።

፬/ ኢትዮጵያውያን ፡ እውነተኛውን ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ይውቀውትና ፡ አምነውታልን ፡ ብለን ፡ ለመጠራጠር ፡ እንደፍራለን ፡ ብለዋል ።

(፬) በዚህማ ፡ እንዳይጠራጠሩ ፡ በየጊዜው ፡ የሚመጡ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ላቀረቡት ፡ ጥያቄ ፡ ኹሉ ፡ ተገቢ ፡ መልስ ፡ በመስጠት ፡ እያሳፈሩ ፡ ሲመልሷቸው ፡ እንደኖሩ ፡ ያውቁ ፡ የለምን ፡ እንዲያው ፡ ለጥርጥር ፡ ቢጥፍዎ ፡ እንጂ ፡ ይህስ ፡ አያጠራጥርም ፡ በርግጥ ፡ ይወቁትና ፡ ለመጠራጠር ፡ አይድፈሩ።

፭/ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የዛሬው ፡ የሃይማኖት ፡ አስተያየቷ ፡ ከካቶሊክ ፡ ትምርት ፡ ጋራ ፡ አለመስማማቱ ፡ ካገሩ ፡ ርቀትና ፡ ለረጅም ፡ ዘመናት ፡ ከማይሳሳተው ፡ ከሮማው ፡ አስተማሪነት ፡ ያለውድ ፡ በግድ ፡ ከመለየትዋ ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

፮/ (ሀ) ካገሩ ፡ ርቀት ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ ለሚሉት ፡ የሃይማኖት ፡ ነገር ፡ የሚረዳና ፡ የሚታወቅ ፡ መጻሕፍትን ፡ በመመልከት ፡ መምህራንን ፡ በመጠየቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በቦታ ፡ መቀራረብ ፡ አይደለም ፡ የሀገር ፡ መቀራረብስ ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ መመሰሰል ፡ የሚያደርስ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ሮማ ፡ ባቅራቢያዋ ፡ ከሚገኙ ፡ ከግብጽ ፡ ከሶርያ ፡ ከአርማንያ ፡ ኦርቶዶክሳውያን፡ጋራ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ፡ በማለት ፡ ወይንም፡እነርሱ ፡ ከርስዋ ፡ ጋራ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ወይም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ ሠረጸ ፡ በማለት ፡ በተስማሙ ፡ ነበረ ፡ በእውነቱ ፡ የለያያቸውስ ፡ በሮማም፡በኢትዮጵያም፡የተዘረጋች ፡ አንዲት ፡ ወንጌል ፡ ስትኾን ፡ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትምህርት ፡ በጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ በመለወጥዋ ብቻ ፡ ነው ።

(ለ) ለረጅም ፡ ዘመናት ፡ የማይሳሳት ፡ የሮማ ፡ አስተማሪነት ፡ ስለሚሉትም ፡ ምንም ፡ በርስዎ ፡ ዘንድ ፡ ከስሕተት ፡ ባይቆጥሩት ፡ ፩ኛ ፡ በመጻሕፍት ፡ ያልተገኘውን ፡ በሊቃውንት ፡ ጉባኤ ፡ ያልተወሰነውን ፡ በይመስለኛልና ፡ በያሰኛል ፡ ብቻ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለቷ ፡ በሌላው ፡ ዘንድ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ ተብሏል ።

፪ኛም ፡ መጻሕፍት ፡ ያልተናገሩትን ፡ ሊቃውንት ፡ በጉባኤ ፡ ያልወሰኑትን ፡ ከልብ ፡ ፈጥሮ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ ሠረጸ ፡ ማለት ፡ ታላቅ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

፫ኛ/ ማርቲን ፡ ሉተር ፡ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነፍሳት ፡ ከሲኦል ፡ ወደገነት ፡ የሚተላለፉ በት ፡ የይለፍ ፡ ወረቀት ፡ ካርኒ ፡ ግዙ ፡ እያለች ፡ በገንዘብ ፡ ትሸጥ ፡ ነበረ ፡ ሲል ፡ ጽፏል ፤ ይህም ፡ ተደርጎ ፡ እንደኾነ ፡ ታላቅ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

፬ኛ/ ክርስቶስ ፡ ሥጋዬን ፡ ብሉ ፡ ደሜን ፡ ጠጡ ፡ ብሎ ፡ ላመነበት ፡ ኹሉ ፡ አስተካክሎ ፡ ቢሰጥ ደሙን ፡ ካህናት ፡ ብቻ ፡ ይቀበሉ ፡ ምእመናን ፡ ይከልከሉ ፡ ማለት ፡ ታላቅ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ይህ ፡ ኹሉ ፡ ለሕተት ፡ እያለ ፡ ለረጅም ፡ ዘመናት ፡ የማይሳሳተው ፡ ብሎ ፡ መመካት ፡ አይገባም ፡ ኢትዮ ጵያ ፡ ይህንን ፡ ኹሉ ፡ አመዛዝና ፡ ትምርቱ ፡ ተገቢ ፡ አለመኾኑን ፡ ተመልክታ ፡ የሮማን ፡ ትምህርት ፡ አልቀበልም ፡ ብላለች ፡ እንጂ ፡ ከሮማ ፡ አስተማሪነት ፡ ያለውድ ፡ በግድ ፡ የለያት ፡ የለም ፡ ሐሰት ፡ ነው ።

፭ኛ/ ኢትዮጵያ ፡ ሳትወድ ፡ ወይም ፡ አስፈላጊ ፡ ኾኖባት ፡ ካረመኔዎችና ፡ ከእስላሞች ፡ ወይንም ፡ ከቅብጦችም ፡ ጋራ ፡ ከመቀራረብዋ ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከባህል ፡ የተነሣ ፡ አይደለም ፡ ለማለት ፡ ብንደፍር ፡ ከእውነት ፡ የራቅን ፡ አይመስለንም ፡ ብለዋል ።

፮ኛ ከቅብጥ ፡ መገናኘቷ ፡ ለሚሉት ፡ ከቅብጥ ፡ ጋራ ፡ በሃይማኖትም ፡ በባህልም ፡ መገናኘቷ ፡ የማይካድ ፡ ነው ፡ ኾኖ ፡ ከአረመኔዎችና ፡ ከእስላሞች ፡ መቀራረብዋ ፡ የሚሉት ፡ እንደ አረማውያን፡ ዕንጨት ፡ ጠርባ ፤ ደንጋይ ፡ አለዝባ ፡ ጣዖት ፡ ታመልካለችን ፡ ወይስ ፡ እንደ ፡ እስላሞች ፡ አላሁ፡ አንድ ፡ ነው ፡ አይወርድም ፡ አይወለድም ፡ የምትል ፡ መስለዎ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከአረመኔዎችና ፡ ከእስ ፡ ሞች ፡ ጋራ፡ ግንኙነት ፡ ሳይኖራት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ ትምህርት ፡ የራቀች ፡ ከአረመኔዎችና ፡ ከእስ ላሞች ፡ ጋራ ፡ በመቀራረቧ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ለመናገር ፡ ሲደፍሩ ፡ ከእውነት ፡ የራቅሁ የማይመስልዎ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በከንቱ ፡ ተጠራጥረውታል ፡ እንጂ ፡ ከእ ውነት ፡ መራቅዎ ፡ የማይጠራጥር ፡ ነገር ፡ ነውና ፡ አይጠራጠሩ ፡ በፍጹም ፡ ከእውነት ፡ ርቀዋል ።

፯/ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሮማ ፡ መለየቷ ፡ ሌላም ፡ በጣም ፡ አሳዛኝ ፡ የኾነ ፡ ነገር ፡ አስከትሎባታል ፡ ይኸውም ፡ ያልተካከለ ፡ የምሥጢራት ፡ ጸጋ ፡ አሰጣጥና ፡ ከክርስትናዋ ፡ ጋራ ፡ ተቀላቅሎ ፡ የሚገኘው ፡ የጥንቆላና ፡ የአይሁድ ፡ ልማድ ፡ ነው ብለዋል ።

፯ኛ ያልተካከለ ፡ የምሥጢረ ፡ ጸጋ ፡ አሰጣጥ ፡ ስለሚሉት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዳግመኛ ፡ ከውኃና ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያልተወለደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ሊገባ ፡ አይችልም ፡ ነፋስ ፡ ወደ ፡ ወደደው ፡ ይነፍሳል ፡ ሲነፍስም ፡ ድምፁ ፡ ብቻ ፡ ይሰማል ፡ እንጂ ፡ ከወዴት ፡ እንደተ ነሣና ፡ እንደ ፡ መጣ ፤ ወዴትም ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ አይታወቅም ። ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚወለዱትም ፡ ልደት ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ሲያሰጥ ፡ ተአምራት ፡ ሲያሠራ ፡ ይታወቃል ፡ እንጂ ፡ ባይን ፡ አይታይም ፡ በእጅ ፡ አይዳሰስም ፡ ብሎ ፡ ነግሮናል ። ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፫-፱ ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ አስተምራ ፡ አሳምና ፡ ታጠምቃለች ፡ ታቈር ባለች ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ተጠምቀው ፡ ከብዙ ፡ ጸጋ ፡ ከብር ፡ ደርሰው ፡ ከብራቸው ፡ በሥራ ፡ የተገ ለጸላቸው ፡ ብዙ ፡ ቅዱሳን ፡ መኖራቸው ፡ የማይካድ ፡ ነገር ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በምታጠምቃቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደ ፡ ሸማ ፡ ተጠቅሎ ፡ እንደ ፡ ወርቅ ፡ ተንከብሎ ፡ ሲሰጣቸው ፡ ወይስ ፡ እንደ ፡ አሞራ ፡ በሮ ፡ እንደ ፡ ዘንግ ፡ ተወርውሮ ፡ ሲዋሐዳቸው ፡ ይታያል ፡ ይኾን ፡ እስኪ ፡ ይነገሩኝ ። ሮማ ፡ የምታደርገው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የማታደር ገው ፡ የምሥጢረ ፡ ጸጋ ፡ አሰጣጥ ፡ ሮማ ፡ የክርስቶስን ፡ ደም ፡ ለካህናት ፡ ብቻ ፡ ሰጥታ ፡ ለምእመናን ፡ ስትከለክል ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ጌታ ፡ ትእዛዝ ፡ ለኹሉም ፡ አስተካክላ ፡ መስጠቷ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህን ፡ ከጉድለት ፡ ቈጥረውት ፡ እንደኾነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ የጎደለባት ፡ ነገር ፡ የለም ።

ደግሞስ ፡ ከክርስትናዋ ፡ ጋራ ፡ ተቀላቅሎ ፡ የሚገኘው ፡ ጥንቆላ ፡ ምንድንነው ፡ (የኢትዮ ጵያ ፡ መምህራን ፡ ለክርስትና ፡ የሚያበቃውን ፡ ትምህርት ፡ በሚያስተምሩበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ የጥንቆላ ፡ ትምህርት ፡ ሲያስተምሩ ፡ ወይስ ፡ ጸጋ ፡ ጥምቀትን ፡ በሚሰጡበት ፡ ጊዜ በጥንቆላ ፡ የሚገኝ ፡ ሀብትን ፡ ተስፋ ፡ ሲያስደርጉ ፡ ሰምተዋልን ፡ እስኪ ፡ ይመስክሩ ፡ በኢትዮጵያ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የጥንቆላ ፡ ሥራ ፡ በፍጹም ፡ የተጠላ ፡ ክልክል ፡ ነው ፤ ይህ ፡ አነጋገርዎም ፡ ፍጹም፡ ሐሰት ፡ ነው ።

ደግሞስ ፡ ከክርስትናዋ ፡ ጋራ ፡ የተቀላቀለው ፡ የአይሁድ ፡ ልማድ ፡ ምንድንነው ፡ ኢትዮጵያ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አሪት ፡ ነቢያትን ፡ ልፈጽማቸው ፡ እንጂ ፡ ላሳልፋቸው ፡ አልመጣሁም ሰማይ ፡ ምድር ፡ እስኪያልፉ ፡ ድረስ ፡ ሥራቷ ፡ ጽፈቷ ፡ አንዲት ፡ የኾነች ፡ የውጣ ፡ አታልፍም ፡ ከኒህ ከጥቃቅኑ ፡ ትእዛዛት ፡ አንዲትን ፡ የሻረ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ታናሽ ፡ ይባላል ፡ የፈጸማቸው ፡ ግን ፡ ታላቅ ፡ ይባላል ፡ ብሎ ፡ ካጸናቸው ፡ ትእዛዛት ፡ በቀር ፡ የአይሁድ ፡ ልማድ ፡ በፍጹም ፡ አይታ ወቅም ።



ይህ ሥዕል ከኢትዮጵያ ዕጨጌዎች ፺፱ኛውን ዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስን ያሳያል ።
አሁን ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ።

እንግዲህ ፡ እርስዎ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ለመናገር ፡ የደፈሩበት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ አይሁድ ፡ ልማድ ፡ ደም ፡ ስታፈስ ፡ ስብ ፡ ስታጤስ ፡ ወይም ፡ ላም ፡ በግ ፡ ብትሠዋ ፡ የላም ፡ የፍየል ፡ ደም ፡ በሐር ፡ ጉንጉን ፡ በጽሕም ፡ ጠሊ ፡ ስትረጭ ፡ አይተዋልን ፡ ወይስ ፡ ጠላት ፡ ይቀባል ፡ ጥላት ፡ እንደሚባለው ፡ ስሟን ፡ ላጥፋ ፡ ብለው ፡ ከልብዎ ፡ አንቅተው ፡ ይዋሻሉ ፡ ያዩት ፡ ነገር ፡ ካለ ገልጸው ፡ ይጻፉና ፡ እኔም ፡ የሚገባ ፡ መልሱን ፡ እሰጥዎታለሁ ።

፩/ በዚሁ ፡ በመለየቷ ፡ ዘመናት ፡ ብዙ ፡ ስሕተቶችና ፡ መልካም ፡ ኑሮን ፡ መንፈሳዊ ፡ አስተዳደርን ፡ የሚያበላሹ ፡ ቁሀሎች ፡ ገብተው ፡ ከሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ የለይዋት ፡ እነሆ ፡ ስሕተቶች ፡ ሳይኾኑ ፡ አይቀሩም ፡ ብለዋል ።

፪ኛ ኢትዮጵያን ፡ ከሮማ ፡ የለያት ፡ በሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ የሚታየው ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ። ከሮማ ፡ መለየቷስ ፡ በሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሚነገረው ፡ ስሕተት ፡ ጠበቃት ፡ እንጂ ፡ የጎዳት ፡ ነገር ፡ የለም ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

### ፩/ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሮማ ፡ የተለየችው ፡ መቼ ፡ ነው ።

፩/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና የሮማ ቤተ ክርስቲያን ሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት በሐዋርያት ስብከት ካመኑ ፡ ጀምረው ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ጸንተው ፡ ሲኖሩ ፡ ንስጥሮስ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ብሎ ፡ ቢያስተምር ፡ ኹሉም ፡ አንድ፡ ኾነው፡ ምንም ፡ ንስጥሮስ ፡ ከጉባኤው ፡ ባይገኝ ፡ በቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ አፈጉባኤነት ፡ አውግዘው ፡ ከለዩት ፡ በኋላ ፡ የሮሙ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ልዮን ፡ ከንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ ገሚሱን ፡ ከፍሎ ፡ በአንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ባሕርይ ፡ ብሎ ፡ ሐሳቡን ፡ በገለጠበት፡ ጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ በቆመበት ፡ በ፬፻፶፩ ፡ ዓ/ም ፡ ነው ፡ ሮማና ኢትዮጵያ ፡ የተለያዩበት ፡ እርግጠኛው ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እይጠራጠሩ ።

### ፪ የመለየቷ ፡ የታወቀ ፡ ጊዜ ።

፪/ ባለፈው ፡ ምዕራፍ ፡ መጀመሪያ ፡ እንዳመለከትነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ በግልጽ ፡ አልቀበለውም ፡ ብላ ፡ ጥላ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ መቀበልዋን ፡ የገለጠችበት ፡ ጊዜ ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ መችም ፡ መች ፡ አይገኝም ፡ ብለዋል ።

፪/ ይህን ፡ ማለት ፡ የሚገባ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ከአንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ጋራ ፡ ክጥንት ፡ ጀምሮ ፡ አብሮ ፡ ሲነገር ፡ ኖሮ ፡ ወይ ፡ ክርስትና ፡ የሚገባ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ከኹለቱ ፡ ባህሎች፡ አንዱን ፡ መርጠህ ፡ ያዝ ፡ የሚባል ፡ ቢኾን ፡ ነበረ ። ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ከሐዋርያት ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣ ፡ ተቀዳሚ ፡ ትምህርት ፡ መኾኑ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ግን ፡ ኋላ ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የተደቀለ ፡ ባህል ፡ መኾኑ ፡ የማይታበል ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ።

እርስዎ ፡ ራስዎ ፡ የፊተኞች ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ያስተምራሉ ፡ ኹለተኞች ፡ ግን ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ሲሉ ፡ ያስተምራሉ ብለው ፡ መስክረዋል ፡ (ገጽ ፡ ፲፪ ፡ ተመልከት) ፡ እንዲኸውም ፡ ኢትዮጵያ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ከመፈጠሩ ፡ አስቀድማ ፡ ክርስትናን ፡ ስትቀበል ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ መቀበሏ ፡ እርግጠኛ ፡ ነገር ፡ ነው ። ይህንኑም ፡ እርስዎ ፡ ራስዎ ፡ በገጽ ፡ ፳ ፡ በክርስትናዋ ፡ አዲስ ፡ የነበረችቱ ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በፊት ፡ በድፍን ፡ ይታመን ፡ የነበረውን ፡ መምህራንና ፡ ሊቃውንት ፡ በተራቀቀ ፡ መርምረው ፡ በኋላ ፡ አነጋገር ፡ ያልተወሰነውን ፡ የሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ይዛ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ እንደቆመች ፡ ቀረች ፡ ብለው ፡ መስክረዋል ።

፫/ ነገር ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሮማይቱ ፡ ተለይታ ፡ ራስዋን ፡ ችላ ፡ መገኘቷ ፡ ባይናችን ፊት ፡ ያለ ፡ የማይካድ ፡ እውነት ፡ ነው ' ብለዋል ።

፫/ አሁን ፡ እርስዎ ፡ እንደሚሉት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጥንት ፡ ሐዋርያት ፡ ካስተማሩት ፡ ካንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ሳትናወጥ ፡ በዚያው ፡ ጸንታ ፡ ራሷን ፡ ችላ ፡ ስለምትኖር ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነውን ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ን ፡ ባህል ፡ ፤

(ሀ) በኒቅያ ፡ ጉባኤ ፡ እንደ ፡ ተደረገበት ፡ እንደ ፡ አርዮስ ፡ ባህል ።

(ለ) በቍስጥንጥንያ ፡ ጉባኤ ፡ እንደ ፡ ተደረገበት ፡ እንደ ፡ መቅዶንዮስ ፡ ባህል ።

(ሐ) በኤፌሶን ፡ ጉባኤ ፡ እንደ ፡ ተደረገበት ፡ እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ ባህል ።

ለነርሱ ፡ አራተኛ ፡ ክህደት ፡ ኑፋቄ ፡ አድርጋ ፡ ትቈጥረዋለች ፡ እንጂ ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ አታገባውም ።

ይህንንም ፡ እርስዎ ፡ በግልም ፡ የሚያውቁት ፡ መኾንዎን ፡ በዚሁ ፡ በጽሑፍዎ ፡ መላልሰው ፡ አስረድተዋል ፡ ሮማና ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተለያዩበት ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ተራራ ፡ ጎልቶ ፡ የሚታይ ፡ ሲኾን ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ አልቀበለውም ፡ ብላ ፡ ጥላ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ መቀበሏን ፡ የገለጠችበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ መጻፍ ፡ ለማደናገር ፡ ለማሳሳት ፡ የተፈጠረ ፡ ዘዴ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ሰው ፡ የሚያቀርበው ፡ እውነተኛ ፡ ጥያቄ ፡ አይደለም ።

፬ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ፡ በእርግጥ ፡ አብራ ፡ ትኖርበት ፡ ከነበረችው ፡ መጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እየተከተልን ፡ የዛሬውን ፡ አስተያየቷን ፡ መያዝ ፡ እስከ ፡ ዠመረችበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በመድረክ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ኹናቴ ፡ ለመመርመርና ፡ ስለእርሱ ፡ በቂ ፡ የኾነ ፡ መረጃ ፡ ለማምጣት ፡ እንጣጣራለን ፡ ብለዋል ።

፬/ አሁን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ በግልጥ፡ አልቀበለውም፡ ብላ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን፡ ባህል ፡ የተቀበለችበት ፡ ጊዜ ፡ በታሪክ ፡ አይገኝምና ፡ ከሮማ ፡ አልተለየችም ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ተቀብላለች ፡ በሚል ፡ ሐሳብ ፡ ቆመው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ የተለየችው ፡ መች ፡ ነው ፡ አስረዱኝ ፡ ብለው ፡ የማስተባበያ ፡ ጥያቄ ፡ አቅርበው ፡ ነበር ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ በእርግጥ ፡ ከሮማ ፡ ካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ፡ አብራ ፡ ትገኝበት ፡ የነበረውን ፡ መጨረሻ ፡ ጊዜና ፡ የዛሬውን ፡ አስ

ተያየቷን ፡ መያዝ ፡ የዠመረችበትን ፡ ጊዜ ፡ ተረድተው ፡ ኹኔታውን ፡ ለመመርመርና ፡ በቂ ፡ መረጃ ለማምጣት ፡ የሚጣጣሩ ፡ መኾንዎን ፡ ገልጸዋል ።

ለጠየቁት ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ ሳያገኙ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ለመጻፍ ፡ በቁ ። ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ ጋራ ፡ በኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ የተስማማችበት ፡ ጊዜ ፡ በደቂቃ ፡ ቀርቶ ፡ በሰኮንድም ፡ አያገኙም እንጂ ፡ የሚያገኙ ፡ ከኾነ ፡ የሚያመጡትን ፡ ለመስማት ፡ ዝግጁዎች ፡ ነን ። እኛ ፡ በርግጥ ፡ እንደምናውቀው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ፡ አብራ ፡ የነበረችበት ፡ ጊዜ ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ሳትፈጥር ፡ ገና ፡ ባንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ በነበረች በት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

መጨረሻውም ፡ የሮማው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ልዮን ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ብሎ ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ በከፊል ፡ ያስተማረበት ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ነው ፡ የዛሬውንም ፡ አስተያየቷን መያዝ ፡ የዠመረችው ፡ ክርስትናን ፡ በፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ወይም ፡ በከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ ሰላማ ፡ የተቀበ ለችበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

፳፩/ ከኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ኢትዮጵያ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ክርስቲያን ፡ የተለየችው ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል የያዙ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ተለይተው ፡ የራሳቸውን ፡ ወገን ሊያቋቁሙ በዠመሩበት ፡ በ፭ኛ ፡ ዓለም ፡ ው ስጥ ፡ አይመስልም ፡ ይልቅስ ፡ ያንጊዜ ፡ ገና ፡ አብራ ፡ የነበረች ፡ ይመስላል ፡ ስንል ፡ እናሳስባለን ፡ ብለዋል ።

፳፪/ ኢትዮጵያ ፡ ከላይ ፡ ከዘረዘርኩልዎ ፡ ጊዜ ፡ በቀር ፡ ከሮማ ፡ ጋራ ፡ የተባበረችበት ፡ ጊዜ ፡ እንደሌለ ፡ እኛ ፡ በእርግጥ ፡ እናውቃለን ፡ አሁን ፡ እርስዎ ፡ አንድ ፡ ምስክር ፡ ሳያስመሰክሩ ፡ አንድ ፡ መረጃ ፡ ሳያቀርቡ ፡ አብራ ፡ የነበረች ፡ ይመስላል ፡ እያሉ ፡ ያውሩልናል ።

እንግዲህ ፡ አንድ ፡ መረጃ ፡ ሳንይዝ ፡ እዎን ፡ ብንልዎ ፡ አይታዘቡንም ፡ ይኾን ፡ እርስዎስ ፡ ቃሌን ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ተቀበሉኝ ፡ ብለው ፡ ያምኑት ፡ ይኾን ፡ ከነገሩስ ፡ ሃይማኖትዎ ፡ በያ ሰኛል ፡ የጽሑፍ ፡ ማስረጃዎም ፡ በይመስላል ተወሰነ ፡ ኧረ ፡ ክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ማለ ትን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ጠቅሰው ፡ የሚያስረዱት ፡ መች ፡ ነው ፡ የብሉያት ፡ ትንቢት ፡ በሐዲስ፡ መፈጸሙን ፡ የሚያውቁ ፡ የረቀቀውን ፡ የሐዲሳትንም ፡ ምሥጢር ፡ በሊቃውንት ፡ ትርጓሜ ፡ አጉልተው አበጥረው ፡ አንጠርጥረው ፡ የሚያዩ ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ በይመስላል ፡ ብቻ ፡ አስረዳለሁ ፡ ብለው ፡ መጣጣርዎ ፡ እጅግ ፡ ያሳዝናል ።

## ክፍል ፡ ፪ ።

## ልዩ ፡ ልዩ ፡ አስተያየቶች ።

፩/ አንዳንድ ፡ ጸሐፊዎች ፡ በእናቷ ፡ በእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በፍጹም ፡ ተመርታ ፡ ወይም ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ በፍ ጹም ፡ ተስማምታ ፡ ትኖር ፡ ነበረ ፡ የሚለውን ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ አሳብ ፡ እንደ ፡ እርግጥ ፡ በመከተል ፡ በኹሉም ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ታወቀው ፡ የግብጽ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዲዮስቆሮስ ፡ መሪነት ፡ ከሮማ ፡ የተለየችው ፡ በ፭ኛ ፡ መቶ ፡ ዓ/ም ፡ ነውና ፡ ኢትዮጵያ የተለየችው ፡ ያንጊዜ ፡ ሳይኾን ፡ አይቀርም ፡ ብለው ፡ ደጋግመው ፡ ጽፈዋል ፡ በማለት ፡ እውነተኛውን ፡ ታሪክ ፡ ሊያ ስተባብሉ ፡ ሞክረዋል ።

፪/ መሠረት ፡ የሌለው ፡ ወሬ ፡ እርስዎ ፡ በይመስላል ፡ በይኾናል ፡ የሚጽፉት ፡ አስተያየት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያና ፡ እስክንድርያስ ፡ እርስዎ ፡ ራስዎ ፡ የሚመሰክሩላቸው ፡ እናትና ፡ ልጅ ፡ መኾናቸው ፡ የማይካድ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ የተለየችውም ፡ የግብጽ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ በዲዮስቆሮስ ፡ መሪነት ፡ ከሮማ ፡ በተለየችበት ፡ በ፭ኛው ፡ ፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወሩና ፡ ቀኑ ፡ ሳይቀር፡ ያው ፡ እንደኾነ ፡ በእርግጥ ፡ ይወቁ ፡ አይጠራጠሩ ።

፫/ አንዳንዶችም ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተለየችው ፡ ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ከሶርያ ፡ የመጡበት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ እንዚሁ ፡ ሲሰ ብኩ ፡ የመጡ ፡ የሶርያ ፡ ተወላጆች ፡ ነበሩ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያም ፡ የመጡ ፡ በምስተኛ ፡ መቶ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መጨረሻ ፡ ወይም ፡ በ፮ኛ ፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መዠመሪያ ፡ ነው ።
እንደነዚሁ ፡ አሳብ ፡ ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮችና ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰብከው ፡ ያስፋፉ መኾናቸው ፡ ነው ፡ ብለ ዋል ።

፬/ ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ የመጡ ፡ በአልዓሜዳ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ መኾኑ ፡ የማይካድ ፡ ነው ። ይህነንም ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚገኘው ፡ ታሪክ ፡ ነገሥት ፡ ከ፬፻፸ ፡ እስከ ፡ ፬፻፹፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አልዐሜዳ ፡ ነገሠ ፡ እርሱ ፡ ፱ቱ ፡ ቅዱሳንን ፡ ተላልከ ፡ አስመጣ ፡ ይላል ፡ ስለዚህ ፡ በዘመኑ ፡ አንከራከርም ። በመ ጡም ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አምና ፡ ተጠምቃ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ይዛ ፡ አግኝተዋት ፡ እነርሱም ባንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ጸንተው ፡ ይህነኑ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ክርስትና ፡ ወዳልደረሰበት ፡

ምናልባት ፡ አድርሰው ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ፡ እርግጠኛውስ ፡ ፀሐ ፡ ቅዱሳን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሠሩ ፡ ተብሎ ፡ የሚነገረው ፡ ሕገ ፡ ምንኵስናን ፡ አስተማሩ ፡ ገዳማትን ፡ አቀኑ ፡ ተብሎ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ያስተማሩት ፡ ሕገ ፡ ምንኵስና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ተስፋፍቶ ፡ ይገኛል ፤ ያቀኗቸውም ፡ ገዳማት ፡ እንዳሉ ፡ ይገኛሉ ፡ ስለሃይማኖት ፡ ግን ፡ ከኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ወዳንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ መመለሳቸው ፡ ይቅርና ፡ በጠቅላላው ፡ ይህነን ፡ ክፍለ ፡ ሀገር ፡ መክረው ፡ አስተምረው ፡ ከአረመኔነት ፡ ወደ ፡ ክርስቲያንነት ፡ መለሱ ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ ይገኝ ፡ አይመስለኝም ፡ ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ስብከት ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ለቃ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ተቀበለች ፡ ብለው ፡ የጻፉ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ተሳስተው ፡ አሳስተዋታል ።

## ክ ፍ ል ፫ ።

## በይኾናል ፡ የሚገለጹ ፡ አሳቦች ።

፳/ አንዳንድ የታሪክ ፡ ኹኔታዎችን ፡ ጠንቅቀን ፡ ብንመረምራቸው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተለየችው ፡ ወይም ፡ ከካቶሊክ ፡ ባህል ፡ የማይስማማውን ፡ የያዘችውን ፡ አስተያየቷን ፡ መያዝ ፡ የጀመረችው ፡ እላይ ፡ ከተነገረው ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ ከቆየች ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ የሚያስችሉን ፡ በቂ ፡ ምክንያቶች ፡ ይሰጡናል ። ብለዋል ።

፳ ከላይ ፡ እንደ ፡ ገለጽኩልዎ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አሁን ፡ የያዘችውን ፡ ከካቶሊክ ፡ ባህል ፡ የማይስማማውን ፡ ባህል ፡ የተቀበለች ፡ ሕገ ፡ ክርስትናን ፡ በተቀበለች ፡ ጊዜ ፡ መኾኑ ፡ ከሮማም ፡ የተለየችው ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ በጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ በተፈጠረ ፡ ጊዜ ፡ መኾኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ። ይህ ፡ እርስዎ ፡ የሚሉት ፡ እውነት ፡ ኾኖ ፡ ቢኾን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ በፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ መቀበሏንና ፡ ከእስክንድርያ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ መኾኗን ፡ አረጋግጠው በገጽ ፡ ፵፩ና ፡ ፵፭ ፡ እንደ ፡ ጻፉልን ፤ የኹለት፡ ባሕርይን፡ ባህል ፡ እንደዚሁ ፡ ተቀብላ፡ ቢኾን፡ ከሮማ፡ ጋራም ፡ አንድ ፡ የኾነችበትን ፡ ጊዜ ፡ በዚህን ፡ ያህል ፡ ዓ ፡ ም ፡ በእገሌ ፡ ንጉሥነት ፡ በእገሌ ፡ ሐዋርያነት ፡ ተሰብካ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ተቀበለች ፡ ከሮማ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ኾነች ፡ ከእስክንድርያ ፡ ጋራ ፡ የነበራት ፡ አንድነት ፡ ወደቀ ፡ ብለው ፡ የተረጋገጠ ፡ መረጃ ፡ ያቀርቡ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ምክንያት ፡ ባላስፈለገዎም ፡ ነበር ፡ ብዙ ፡ ምክንያት ፡ የሚፈለግ ፡ ሐሰቱን ፡ እውነት ፤ እውነቱን ፡ ሐሰት ፡ ለማስመሰል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለእውነት ፡ ምክንያት ፡ አይሻላትም ፡ እንግዲህ ፡ እውነቱን ፡ ሐሰት ፡ ለማስመሰል ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የሚደክሙበት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከሮማ ፡ እግር ፡ በታች ፡ ለመጣል ፡ ብቻ ፡ አይደለምን ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ ለማስፋፋትማ ፡ ከኾነ ፡ ሕገ ፡ ክርስትናን ፡ ያልተቀበሉ ፡ በእስልምና ፡ ወይም ፡ በአርምና ፡ ወይም ፡ በልዩ ልዩ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚኖሩ ሕዝቦች ፡ አሉ ፡ እነዚያን ፡ አያስተምሩምን ፡ እኔስ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ከእንዲህ ፡ ያለው ፡ ሐሳብ ፡ እንዲጠብቀኝ ፡ ኢትሚጠ ፡ ልልብየ ፡ ውስተ ፡ ነገር ፡ እኩይ ፡ ለአመክንዮ ፡ ምክንያት ፡ ለኃጢአት ፡ ምስለ ፡ ሰብእ ፡ ገብርተ ፡ ዓመፃ ፡ እያልኩ ፡ በዳዊት ፡ መዝሙር ፡ እጸልያለሁ ።

፱/ እንዲህ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ የታሪክ ፡ ኹኔታዎችን ፡ ብንመረምር ፡ በመላው ፡ ፯ኛ ፡ ፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ገና ፡ በእውነተኛው ፡ በካቶሊክም ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንታ ፡ እንደ ፡ ነበረች ፡ እንረዳለን ። ብለዋል ።

፱/ ይህን ፡ ማለት ፡ የሚችሉ ፡ መጀመሪያ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ የተቀበለችበት ፡ ጊዜ ፡ መኖሩን ፡ ራስዎ ፡ ተረድተው ፡ ለሌላው ፡ ለማስረዳት ፡ ችለው ፡ ቢኾን ፡ ነበረ ፡ ቀድሞ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ የተቀበለችበት ፡ ጊዜ ፡ ሳይኖር ፡ በዚያው ፡ ጸንታ ፡ ነበረ ይላሉን ፡ ይህ ፡ አነጋገርዎና ፡ አረማመድዎ ፡ እርስዎን ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ከማስገመት ፡ በቀር ፡ ማንንም ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ ሊማርከና ፡ ወደ ፡ እሰቡት ፡ ግብ ፡ ሊያደርስልዎ ፡ አይችልም።

፲/ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ይገዛ ፡ የነበረው ፡ ንጉሥ ፡ካሌብ ፡ ተራ ፡ ካቶሊክ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ የበለጠ ፡ ካቶሊክ የካቶሊክ ፡ ነገሥታት ፡ ወዳጅ ፡ ባለኪዳን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ኹሉም ፡ የክርስቲያን ፡ ታሪክየመሰከረለት፡አሁንም፡የሚመሰክርለት ነው ። ይህም ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክስቲያን ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ታከብረዋለች ፡ ብለዋል ።

፲/ ንጉሥ ፡ ካሌብ ፡ ካቶሊክ ፡ ነበረ ፡ ማለትን ፡ ከልብዎ ፡ ፈጥረው ፡ ከመናገር ፡ በቀር ፡ ለሐሳብዎ ፡ መነሻ ፡ የሚኾን ፡ ምክንያት ፡ እንኳን ፡ ያገኙ ፡ አይመስለኝም ፡ እውነት ፡ ከኾነ ፡ ካቶሊክ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የክርስቲያን ፡ ታሪክ ፡ ይመሰክራል ፡ ብሎ ፡ አሲታኮ ፡ ከማለፍ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ታሪክ ፡ ዐዋ ፡ ካሌብ ፡ ካቶሊክ ፡ ነበረ ፡ ይላል ፡ ብሎ ፡ ማቅረብ ፡ አይቀናም ፡ ነበርን ፡ ለዚህ ፡ ይጠቅመኛል ፡ ብለው ፡ የጠቀሱትም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቅዱስ ፡ እለ ፡ አጽብሐ፡ ንጉሥ፡ የክርስቶስን ፡ ጠላቶች ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ በዮስጢኖስ ፡ ንጉሥ ፡ ዘመን ፡ የንጉሥነቱን ፡ ዘውድ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ልኮ ፡ አድርጎት ፡ የነበረውን ፡ ስእለት ፡ ብፅዓት ፡ ለመፈጸም ፡ በምንኩስና ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡ በሰላመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐረፈ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ካቶሊክ ፡ ነበረ ፡ አይልም ።

ደግሞ ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ያከበረችው ፡ ካቶሊክ ፡ ቢኾን ፡ ነው ፡ ብሎ ማሰብ ፡ ተገቢ ፡ ነገር ፡ አይደለም ። ለምሳሌ ፡ ከሉዋርያት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ ድረስ፡ በጉባኤ ፡ ኒቅያ ፡ በጉባኤ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ በጉባኤ ፡ ኤፌሶን ፡ የተሰበሰቡ ፡ አባቶችን ፡ እነአትናቴዎስን ፡ እነቄርሎስን ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅዱሳን ፡ ብላ ፡ እንደምታከብራቸው ፡ የታወቀ እርግጠኛ ፡ ነገር ፡ ነው ።

ከነዚህ ፡ አበው ፡ ክርስቶስ ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ብሎ ፡ ያስተማረ ፡ ወይም ፡ የጻፈ አይገኝም ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ብሎ ፡ ያስተማረ ፡ ኖሮ ፡ ቢኾን ፡ አሁን ፡ በጠቀሱት ነበረ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የማይሉ ፡ አባቶችን ፡ ቅዱሳን ፡ ብላ ፡ የምታከብር ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ንጉሥ ፡ ካሌብንም ፡ ቅዱስ ፡ ብላ ፡ ካከበረችው ፡ የርሱንም ፡ ቅዱስነት ፡ እንደነርሱ ፡ አወቀችለት ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ካቶሊክ ፡ ቢኾን ፡ ነው ፡ ያከበረችው ፡ ብሎ ፡ ማሰብ ፡ በእውነቱ ፡ ያሳቢውን ፡ ግምት ፡ ከመቀነስ ፡ በቀር ፡ እውነት ፡ አሰበት ፡ ተብሎ ፡ ግምት ፡ የሚጣልበት ፡ ንግግር ፡ አይደለም ፡ ይህን ፡ ከማለትስ ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ንጉሥ ፡ ካሌብን ፡ በሃይማኖት ፡ ባይመስላትም ፡ የዮስጢኖስን ፡ ልመና ፡ ተቀብሎ ፡ ሰማዕታተ ፡ ናግራንን ፡ በመታደጉና ፡ ዘውዱን ፡ ለቅድስት ፡ ሀገር ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ገዳም ፡ አበርክቶ ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ተረፈ ፡ ዘመኑን ፡ በምንኩስና ፡ በመጨረሱ ፡ ቅዱስ ፡ ብላ ፡ ታከብረዋለች ፡ ቢሉ ፡ ርስዎም ፡ ባስተያየትዎ ፡ ተመስግነው ፡ የካቶሊክን ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባስመሰገኑ ፡ ነበረ ።

፲፭/ በኢትዮጵያ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የንጉሡ ፡ ሃይማኖት ፡ ያገሩ ፡ ደንበኛ ፡ ሃይማኖት ፡ ከመኾኑም ፡ በላይ ፡ የተባለው ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥት ፡ ካቶሊክ ፡ ነበረ ፡ ከርሱ ፡ የማይስማማ ፡ ሌላ ፡ እምነት ፡ በመንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ሊሠለጥንባት ፡ አይፈቅድም ፡ ነበር ፡ ተብሎ ፡ ቢታሰብ ፡ ያልተገባ ፡ አይደለም ። ብለዋል ።

፲፮/ በኢትዮጵያ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የንጉሡ ፡ ሃይማኖት ፡ ያገሩ ፡ ደንበኛ ሃይማኖት ፡ መኾኑና ፡ ነገሥታቱም ፡ ሌላ ፡ እምነት ፡ በመንግሥታቸው ፡ ውስጥ ፡ እንዲሠለጥን ፡ የማይፈቅዱ ፡ መኾናቸው ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ የነገሥታቱ ፡ ሃይማኖት ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በታሪክ ፡ ይታወቃል ፡ ዛሬም ፡ በዐይን ፡ ይታያል ፡ በሕገ ፡ መንግሥቱም ፡ ተጽፎ ፡ ይገኛል ፡ ይኸውም ፡ ሳይቋረጥ ፡ ከአብርሃ ፡ ወአጽብሐ፡ እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የደረሰ ፡ መኾኑን ፡ አሁን ፡ በጽሑፍዎ ፡ ላይ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የንጉሡ ፡ ሃይማኖት ፡ ያገሩ ፡ ደንበኛ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፡ ብለው አረጋግጠዋል ።

እንግዲህ ፡ የንጉሡና ፡ የሕዝቡ ፡ ሃይማኖት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ ኾኖ ፡ ከአብርሃ ፡ ወአጽብሐ ፡ እስከ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሳይቋረጥ ፡ ተያይዞ ፡ የወረደ ፡ ኾኖ ፡ ሲገኝ በመካከል ፡ ጣልቃ ፡ አግብተው ፡ ንጉሥ ፡ ካሌብ ፡ ካቶሊክ ፡ ነበረ ፡ ማለትን ፡ ምን ፡ መረጃ ፡ ጨብጠው ፡ ተናገሩ ፡ ይኾን ፡ እስኪ ፡ ይንገሩኝ ።

፲፯/ እንግዲህ ፡ በግልጥ ፡ የሚናገሩ ፡ ምስክሮችና ፡ ጽሑፎች ፡ ሲታጡ ፡ በ፮ኛው ፡ ፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገና ፡ የካቶሊክ ፡ ሃይማኖትን ፡ ይዛ ፡ ትኖር ፡ ነበረ ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ። ብለዋል ።

፲፰/ እኛን ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ በጠቅላላው ፡ ይህን ፡ መጽሐፍዎን ፡ የሚመለከተውን ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ቢንቁት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ለመጻፍ ፡ ደፈሩ ፡ ለተናገረው ፡ ነገር ፡ ማስረጃ ፡ ያጣ ፡ ሰው ፡ በተናገረው ፡ ነገር ፡ አፍሮ ፡ ሲመለስ ፡ እንጂ ፡ ምስክር ፡ ባላገኝለትም ፡ ነገሬን ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብላችሁ ፡ ተቀበሉኝ ፡ ብሎ ፡ ዐይኑን ፡ የሚያፈጥ ፡ ሰው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ስለሌለ ፡ ለዚህ ፡ ነገር ፡ አንደኛ ፡ ነዎ ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ፤ ለዚህ ፡ አንደኛነትን ፡ ወስደዋል ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ሲጽፉ ፡ እኛስ ፡ እንቅር ፡ ሕሊናዎ ፡ አይታዘብዎትምን ? ሕሊናዎ ፡ የማይታዘብዎ ፡ ከኾነ ፡ ጽሑፍዎን፡ ያየ ፡ ኹሉ ፡ ይታዘብዎ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ ለዚህ ፡ ነገር ፡ የምሰጠው ፡ መልስ የለኝም ።

## ክፍል፡ ፬፡ ፱፡ ቅዱሳን ፡ ሮማውያን ።

፲፱/ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ ከሰበከ ፡ በኋላ ፡ ፱ ፡ የሮም ፡ ቅዱሳን ፡ መጥተው ፡ በበለጠ፡ አስፋፍትና ፡ አደላደሉት ፡ ይልቁንም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ያገቡ ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ፡ ኢትዮጵያም ፡ ከሮማ ፡ የተለየች ፡ እነርሱ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ የሚገኝ ፡ በለኾነ ፡ ስለርሱ ፡ ልንናገር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ብለዋል ።

፲፫/ አስቀድሞ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰብኮ ፡ ኢትዮጵያም በዚሁ ፡ ባስተማራት ፡ ባንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ሳለች ፡ ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ መጥተው ፡ ይህንኑ ፡ የያዘች ውን ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ተናገርነው ፡ ወዳልደረሰበት ፡ አድርሰው ፡ ይኾናል። በያዙትም ፡ እንዲጸኑ ፡ አድርገው ፡ ይኾናል ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ፡ ባህል፡ በኢትዮጵያ፡ በ፱ቱ፡ ቅዱሳን ጊዜ ፡ ተሰበከ ፡ ሮማና ፡ ኢትዮጵያም ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ተለያዩ ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ ቢገኝ ፡ ማን ፡ ማንም ፡ ሊቀበለው ፡ የማይገባ ፡ ሐሰተኛ ፡ ታሪክ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ማለት ፡ የሚቻል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከ፱ቱ ፡ ቅዱ ሳን ፡ በፊት ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ የተቀበለች ፡ ቢኾን ፡ ነበረ ። ኢትዮጵያ ፡ የተሰበከች ፡ በፍሬ ምናጦስ ፡ ነው ፡ ፍሬምናጦስ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ሰበከላት ፡ እንዳይባል ። የኹለት ፡ ባሕ ርይ ፡ ባህል ፡ በፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ጊዜ ፡ ስንኳን ፡ በሌላው ፡ በሮማም ፡ ቢኾን ፡ ገና ፡ አልተፈጠረም ፡ ነበረ ። እንግዲህ ፡ከፍሬምናጦስ ፡ እስከ ፡ ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ድረስ ፡ ባለው ፡ ዘመን ፡ በምን ፡ ባህል ፡ ቆይታ ፡ ነው ፡ ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ሰበኩላት ፡ ተብሎ ፡ የሚ ታሰበው ፡ ይህ ፡ እኛም ፡ እርስዎም ፡ እውነት ነው ፡ ብለን ፡ የማንቀበለው ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ አሳብ ፡ ስለሆነ ፡ ስለዚህ ፡ ባይደክሙ ፡ የተሻለ ፡ ነበረ ።

፲፬/ የኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ አገራቸውንና ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገቡበትን ፡ ዘመን ፡ የያንዳንዱንም ፡ ስም ፡ ዘርዝረው ፡ ተርከውልን ፡ ስለእምነታቸውና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስለ ሰበኩት ፡ ሃይማኖት ፡ እነርሱ ፡ ካቶሊክ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች መኾናቸውን ፡ የሚነግር ፡ ጽሑፍ ፡ የትም ፡ አልተገኘም ፡ ብለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስለነርሱ ፡ የሚተረከውን ፡ በማእዝም ፡ ባማርኛም ከጠቀሱ ፡ በኋላ ፡ አሁን ፡ ይህ ፡ ታሪክ ፡ የሚለውን ፡ በመመርመር ፡ የመጡበትን ፡ አገርና ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገቡበትን ፡ ዘመን ያምኑት ፡ የነበረውን ፡ ሃይማኖት ፡ ለማወቅ ፡ እንሞክር ። ብለዋል ።

፲፭/ ስለእምነታቸው ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ፡ ባዮች፡ነበሩ ፡ የሚል ፡ በግልጽ ፡ የተጻፈ ፡ ባይገኝም ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ መኾናቸው ፡ በሥራቸውና ፡ በተከታ ዮቻቸው ፡ ታውቋል ።

እነሆ ፡ ኹሉም ፡ ለየራሳቸው ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ገዳም ፡ አቅንተዋል ፡ የኹሉም ፡ ገዳም ፡ ሳይቋረጥ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ከነርሱ ፡ ባገኘው ፡ እምነትና ፡ ሥርዓት ፡ ገዳም ፡ ጸንቶ ፡ ይገኛል ። ከእነዚህ ፡ ገዳማት ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ የያዘ ፡ ወይም ፡ ይዞ ፡ ነበረ ፡ ተብሎ ፡ የሚታማ ፡ አንድ ፡ ገዳም ፡አይገኝም ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዕንጨት ፡ በፍሬው ፡ እንዲታወቅ ፡ መምህርም ፡ በሥ ራው ፡ ይታወቃል ፡ ኮሶ ፡ ኮሶን ፡ ወይን ፡ ወይንን ፡ ያፈራል ፡ እንጂ ፡ ኮሶ ፡ ወይንን ፡ ወይን ፡ ኮሶን ፡ ሊያፈራ ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ነገረን ፡ ማቴ ፡ ፯ ፡ ፲፮-፳ ፡ ካቶሊክ ፡ መምህር ፡ ካቶሊካውያን ፡ ማኅበር ፡ ያቋቁማል ፡ ካቶሊካዊ ፡ ገዳም ፡ ይሠራል ። ኦርቶዶክሳዊ ፡ መምህርም ፡ ኦርቶዶክሳዊ ፡ ገዳም ያቋቁማል ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ገዳም ፡ ይሠራል ፡ እንጂ ፡ ካቶሊካዊ ፡ መምህር ፡ ኦርቶዶክሳዊ ፡ ገዳም ፡ ኦርቶዶክሳዊም ፡ መምህር ፡ ካቶሊካዊ ፡ ገዳም ፡ ሊያቋቁም ፡ አይችልምና ፡ ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ኦርቶዶክ ሳውያን ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ መኾናቸው ፡ በአቋቋሟቸው ፡ ገዳማት ፡ አያያዝ ፡ ይታወቃልና ፡ ስለዚህ ፡ ባይደክሙ ፡ ግድ ፡ አልነበረብዎም ።

፲፮/ የመጡበትን ፡ ዘመን ፡ ለማግኘት ፡ በግልጥ ፡ የተጻፈ ፡ ባለመገኘቱ ፡ አቦልዶባ ፡ ወለዶ ፡ ለአልዓሜዳ ፡ ዘበመዋዕሊሁ ፡ ወፅኡ ፡ ፱ ፡ ቅዱሳን ፡ ይላልና ፡ በማለት ፡ የአልዓሜዳን ፡ ዘመነ ፡ መን ግሥት ፡ መሠረት ፡ ለማድረግ ፡ ሲሞክሩ ፡ እንደኛው ፡ ታሪክ ፡ጸሐፊ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ አልዓሜዳ ፡ በ፫፻፴ና ፡ ፡ በ፫፻፸፭ ፡ መካከል ፡ እንደሞተ ፡ በማሰብ ፡ የቅዱሳኑ ፡ መምጣት ፡ በ፭ኛው ፡ ፻ ፡ ዓ/ም ፡ መጀመሪያ ፡ ሳይኾን ፡ አይቀርም ፡ ብሏል ።

ሳፒት ፡ የተባለው ፡ ታሪክ ፡ጸሐፊ ፡ ደግሞ ፡ አልዓሜዳ ፡ የነገሠ ፡ ከ፬፻፺ ፡ እስከ ፡ ፭፻ ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ የመንግሥቱን ፡ ዘመን ፡ ለመወሰን ፡ አስቧል ። ባሴ ፡ የተባለው ፡ ደግሞ ፡ በ፮ኛ ፡ ፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መጀመሪያ ፡ ነግሧል ፡ ይላል ። ጁባ ፡ ኩልበ ፡ የተባለው ፡ ደግሞ ፡ ከ፬፻፶፭ ፡ እስከ ፭፻፲፭ ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ ይላል ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ የገቡበትን ፡ ዘመን ፡ በመወሰን ፡ ላይ ፡ ጸሐፊዎቹ ፡ አይስማሙም ፡ እንደ ፡ ሳፒቲ ፡ አሳብ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመጡት ፡ በ፭ኛ ፡ ፻ ፡ ዓ ፡ ም፡ መጨረሻ ፡ መኾኑ ፡ ነው ። ባሴ ፡ ደግሞ ፡ በ፭፻፷፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ይላል ። በላንዲሰቲ ፡ በ፬፻፶ ፡ ፓ ፡ ማው ሮዳ ፡ ለዮነሣ ፡ ከ፬፻፹ ፡ ወደ ፡ ፬፻፺ ፡ ግድም ፡ ነው ፡ የመጡት ፡ ይላሉ ፡ ብለው ፡ የታሪክ ፡ ጸሐፊዎችን መለያየት ፡ ካስረዱ ፡ በኋላ ፡ የራስዎን ፡ አስተያየት ፡ ሲገልጹ ፡ ኹሉንም ፡ በማመዛዘን ፡ ለእኛ ፡ እንደሚመስለን ፡ ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ የመጡ ፡ በ፭ኛው ፡ ፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መጨረሻ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

፲፯/ የቅዱሳኑ ፡ መምጣት ፡ በአልዐሜዳ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ መኾኑ ፡ ተረጋግጧል ፡ አሁን የምንሻው ፡ የቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነን ፡ ምሥጢር ፡ ብቻ ፡ ስለኾነ ፡ በዚህ ፡ የሚያከራክረን ፡ ነገር ፡ የለም ፡ በማለት ፡ አልፈነዋል ።

፲፮/ የመጡበትን ፡ አገር ፡ ለማወቅ ፡ ሲሞከሩ ፡ የምንመረምረው ፡ ጽሑፍ ፡ ፬ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ስለመጡበት ፡ አገር ፡ ሲናገሩ ፡ አምሮምያ ፡ (ማለት) ፡ ከሮማ ፡ የመጡ ፡ ናቸው ፡ ይላቸዋል ፡ ብለው ፡ የጽሑፉን ፡ ቃል ፡ ካበረዱ ፡ በኋላ ፡ ከአስተያየትዎን ፡ ሲገልጹ ፡ እንርሱ ፡ የሶርያ ፡ ተወላጆች ፡ መኾናቸው ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊ ፡ አምሮምያ ፡ ሲላቸው ፡ የሮማ ፡ መንግሥት ፡ ሒጋዎች ፡ ወይም ፡ እምነታቸው ፡ የሮማ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ለማስረዳት ፡ የፈለገ ፡ ይመስላል ፡ ብለዋል ፡ ።

፲፯/ በእውነቱ ፡ ይህ ፡ መምሰል ፡ ርስዎን ፡ ብቻ መስሎ ፡ የሚቀር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ የሚተርፍ ፡ አይደለም ፡ ምክንያቱም ፡ እርስዎ ፡ ይህን ፡ ዕባራ ፡ ምኞትዎን ፡ ለመደጋገፍ ፡ ሲሉ ፡ ከማመንጨትዎ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ የተጨበጠ ፡ መረጃ ፡ ስለማይገኝለት ፡ ነው ፡ ግምትስ ፡ ከኾነ ፡ ።

(ሀ) ፬ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ከጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ አስቀድሞ ፡ የዓለም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ኹሉ ፡ ሮማም ፡ ሳትቀር ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ራስዎም ፡ የማይክዱት ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ።

(ለ) የእነሀ ፡ የ፬ ፡ ቅዱሳን ፡ ሃይማኖት ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በኢትዮጵያም የሰበኩት ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ መኾኑ ፡ ያቆዩቸው ፡ ገዳማት ፡ ባለማቋረጥ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ይዘውት ፡ የሚገኙት ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ በመኾኑ ፡ ተረጋግጧል ፡ ።

(ሐ) እነዚህ ፡ ፬ ፡ ቅዱሳን ፡ የመጡ ፡ ጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ ከተደረገበት ፡ ከ፬፻፶፩ኛው ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኋላ ፡ ከ፳ ፡ ዘመን ፡ በማይበልጥ ፡ በ፬፻፸ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እንደኾነ ፡ ተረጋግጧል ፡ ።

(መ) የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ባቋቋመችበት ፡ ዘመን ፡ መርቅያንንና ፡ ብርክልያን ፡ ተደግፋ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡ ስለነበራት ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ባል ተቀበሉ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቅጣትን ፡ ታመጣ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በዲዮስቆሮስ ፡ ላይ ፡ በፈጸመችው ፡ ግፍ ፡ ታውቋል ፡ ።

እንግዲህ ፡ እነዚህን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የዘረዘርኳቸውን ፡ መረጃዎች ፡ ተደግፎ ፡ ፬ ፡ ቅዱሳን ፡ ከሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚደርስባቸውን ፡ ሥቃይ ፡ በመፍራት ፡ ሰማዕትነት ፡ ብቻ ፡ በእሳት ፡ በሰለት ፡ አይደለም ፡ ስደትም ፡ ሰማዕትነት ፡ ነው ፡ ፩ ፡ አካል ፡ ፩ ፡ ባሕርይ ፡ የኾነ ፡ ክርስቶስን ፡ ኹለት ባሕርይ ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ ብንሰደድ ፡ ይሻለናል ፡ ብለው ፡ ከሮምያ ፡ የመጡ ፡ ይመስላል ፡ ብሎ ፡ መገመት ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ይመስላል ፤ ይኾናል ፡ ማለትን ፡ ያተርፋል ፡ እንጂ ፡ የርስዎ ፡ ግምት ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ምንም ፡ ጥግ ፡ አይገኝለትም ፡ ።

፲፰/ ፬ ፡ ቅዱሳን ፡ ርቱዓን ፡ ሃይማኖት ፡ ማለት ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ አንዳንድ ፡ የታሪክ ፡ ኹኔታዎችን ፡ በመመርመር ፡ ይረዳል ፡ ብለዋል ፡ ።

፲፱/ በዚህም ፡ አስተያየትዎ ፡ ካቶሊካውያን ፡ መባልን ፡ ርቱዓን ፡ ሃይማኖት ፡ ወደ ፡ ማለት ፡ ለውጠው ፡ ሊተረጕሙ ፡ ሞክረዋል ፡ ካቶሊክ ፡ ማለት ፡ እንተ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ማለት ፡ እንደኾነ ፡ ኦርቶዶክስም ፡ ማለት ፡ ርትዕት ፡ ሃይማኖት ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የታወቀ ፡ የታመነ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ።

የካቶሊክና ፡ የኦርቶዶክስ ፡ ትርጓሜያቸው ፡ እንዲህ ፡ ሲኾን ፡ ካቶሊካውያን ፡ መባል ፡ ርቱዓን ሃይማኖት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መተርጐም ፡ እንዱን ፡ ልጅ ፡ ከእናቱ ፡ ከንድ ፡ ነጥቆ ፡ ሳልወለደችው እናት ፡ ልጅሽ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እንደማስታቀፍ ፡ የሚቆጠር ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ርቱዓን ፡ ሃይማኖት ፡ ያሰኛቸውስ ፡ ኦርቶዶክሳውያንነታቸው ፡ ነው ፡ ካቶሊካውያን ፡ ኾነው ፡ ተገኝተው ፡ አይደለም ፡ ።

እርስዎም ፡ እንደነርሱ ፡ ርቱዐ ፡ ሃይማኖት ፡ መኾንን ፡ ይፈልጉ ፡ እንደኾነ ፡ በማያገባዎ ፡ ከሰው ፡ ሮም ፡ ሔደው ፡ የተዋሱትን ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ትተው ፡ አባቶችዎ ፡ ወደአቆይዎ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ይመለሱ ፡ ብዬ ፡ የወንድምነቴን ፡ እመክርዎታለሁ ፡ ።

፳/ እጅግ ፡ ጥሩ ፡ ካቶሊክ ፡ የነበረው ፡ ከ፲፱፻፲፰ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፳፮ ፡ የነገሠው ፡ ዮስጢኖስ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ካሌ ፡ ካሌብ ፡ ጋራ ፡ መልካም ፡ ግንኙነት ፡ እንደነበረውና ፡ ሰማዕታተ ፡ ናግራንን ፡ ለመርዳት ፡ እንዲረዳው ፡ በእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በጢሞቴዎስ ፡ አማካይነት ፡ እንደ ፡ ላከበት ፡ ዐፄ ፡ ካሌብም ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ዘመቻ ፡ ከመነሣቱ ፡ በፊት ከ፱ ፡ ቅዱሳን ፡ እንዱን ፡ አባ ፡ ጰንጠሌዎንን ፡ ምክሩንና ፡ ቡራኬውን ፡ እንዲሰጠው ፡ እንደለመነው ፤ አባ ፡ ጰንጠሌዎንም ፡ የቅዱሱ ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የጢሞቴዎስ ፡ እሱትና ፡ የሮምያው ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የዮስጢኖስ ፡ ዕንባዎች ፡ በናግራን ከተማ ፡ ስለክርስቶስ ፡ ስም ፡ የሞቱት ፡ ሰማዕታት ፡ የተቀበሉት ፡ ግፍና ፡ እንደ ፡ መልካም ፡ ሽቱ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ያረገው ፡ የመሥዋዕትነታቸው ፡ መዓዛ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ይኹን፡እግዚአብሔር ፡ ያግዝህ ፡ ጠላቶቻችንን፡የምታሸንፍበትን ፡ ኃይል ፡ ይስጥህ፡ ሲል መረቀው ፡ እያሉ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክና ፡ የቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ታሪክ፡ ጸሐፊዎች፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ይተርካሉ ፡ ብለውካተቱ ፡ በኋላ እንደ ፡ እውነቱም ፡ ያንጊዜ ፡ በዓረብ ፡ አገር ፡ የሚቀመጡ ፡ አይሁድ ፡ ድሁ ፡ ናዋስ ፡ ፊንሐስ ፡ ወይም ፡ ፊንሐስ ፡ በሚባለው ፡ ንጉሣቸው ፡ ተመርተው ፡ የዐረብን ፡ ክርስቲያኖች ፡ በተለይም ፡ የመን ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ የናግራንን ፡ ከተማ ፡ ክርስቲያኖች ፡

ያላድዳቸው ፣ ነበረና ፣ ዮስጢኖስ ፣ በእስክንድርያው ፣ ሊቀ ፣ ጳጳሳት ፣ በጢሞቴዎስ ፣ አማካይነት ፣ ባሳዳጃቸ ፣ ላይ ፣ በሚያደርገው ፣ ጠርነት ፣ እንዲያግዘው ፣ ለንጉሥ ፣ ካሌብ ፣ በላከበት ፣ ጊዜ ፣ ብዙውን ፣ የጦር ፣ ሠራዊቱን ፣ አስከትቶ ፣ ከዚያ ፣ ሔዶ ፣ በመጠኛውን ፣ የአይሁድ ፣ ንጉሥ ፣ ድል ፣ ከነሣ ፣ በኋላ ፣ በእግዚአብሔር ፣ አጋዥነት ፣ ስላገኘው ፣ ድል ፣ ምስጋና ፣ ለማቅረብ ፣ ዘውዱን ፣ ወደ ፣ ተቀደሰው ፣ ወደ ፣ ጌታችን ፣ መቃብር ወደኢየሩሳሌም ፣ ልኮ ፣ መንግሥቱን ፣ ለልጁ ፣ ለገብረ ፣ መስቀል ፣ ትቶ ፣ አንድ ፣ ዋሻ ፣ ውስጥ ፣ ገብቶ ፣ እስከ ፣ ሞቱ ፣ ድረስ ፣ በምናኔ ፣ ኖረ ፡፡ ይህም ፣ የኾነው ፣ በ፭፻፳፭ ፣ ዓ/ም ፣ ነው ፣ ብለው ፣ የኢትዮጵያ ፣ ታሪክና ፣ የቀድሞ ፣ ዘመን ፣ ታሪክ ፣ ጸሐፊዎች ፣ የጻፉት ፣ እርግጠኛ ፣ መኾኑን ፣ እርስዎም ፣ አረጋግጠዋል ፡፡

፲፰/ በዚህ ፣ ነገር ፣ ኹላችንም ፣ እንስማማበታለን ፣ እውነት ፣ ነው ፣ ከማለት ፣ በቀር ፣ ምንም የምቃወመውና ፣ መልስ ፣ የምሰጥበት ፣ የለኝም ፡፡

፲፱/ ከዚህ ፣ ቀጥለው ፣ ከዚህ ፣ በላይ ፣ የተናገሩትን ፣ እኛም ፣ የተስማማንበትን ፣ እውነተኛ ፣ ቃል ፣ ለመለወጥ ፣ እስበው እንነዚህ ፣ ኹኔታዎች ፣ ጠንቅቀው ፣ ቢያስተውሉትቸው ፣ አባ ፣ ጰንጠሌዎንና ፣ ፱ ፣ ባልንጀሮቹ ፣ ካቶሊክ ፣ አልነበሩም ፣ ሊባል ፣ የማይቻል ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ ማሰብ ፣ የማይገባ ፣ አይደለም ፣ ብለዋል ፡፡

፲፱/ በእውነቱ ፣ ይህን ፣ እነጋገርዎን ፣ መላልሼ ፣ ብመለከተው ፣ ስንኳንስ ፣ አሁን ፣ ያልተጠቀሱትን ፣ ቅዱሳን ፣ አባ ፣ ጰንጠሌዎንንም ፣ ቢኾን ፣ ካቶሊክ ፣ ነበሩ ፣ ብሎ ፣ የሚያስጠረጥር ፣ ምክንያት ፣ አላገኘሁበትም ፡፡ ምናልባት ፣ የጢሞቴዎስ ፣ ጸሎትና ፣ የዮስጢኖስ ፣ ዕንባዎች ፣ ይርዱህ ፣ ብሎ የዮስጢኖስ ፣ ዕንባ ፣ ጠቃሚነቱን ፣ መመስከሩ ፣ ካቶሊክ ፣ ቢኾን ፣ ነው ፣ ብለው ፤ እንደ ፣ ኾነ ፣ እግዚአብሔር ፣ ስንኳንስ ፣ በክርስቶስ ፣ ስም ፣ መከራ ፣ ለተቀበሉ ፣ ለናግራን ፣ ሰዎች ፣ በማዘን ፣ የፈሰው ፣ ዕንባና ፣ ማንም ፣ ከሃይማኖተ ፣ ወንጌል ፣ በአፍኣ ፣ ያለው ፣ ሰው ፣ ቢኾን ፣ አልቅሶ ፣ ከለመነው ፣ የሚሰማ ፣ ፍጡሩን ፣ የማይጸየፍ ፣ ቸር ፣ አምላክ ፣ እንደኾነ ፣ የሚያውቁ ፣ ሰው ፣ ናቸው ፡፡ ስለዚህ ፣ ይህ ፣ አነጋገር ፣ ካቶሊክ ፣ ነበሩ ፣ ብሎ ፣ የሚያስጠረጥር ፣ ነገር ፣ አይደለም ፡፡

ምናልባት ፣ ወደፊት ፣ በሚያመጡት ፣ አስተያየት ፣ በቂ ፣ ምክንያት ፣ ይገኝ ፣ እንደኾነ ፣ አጥብቄ እከታተላለሁ ፣ እንጂ ፣ ይህስ ፣ ዋጋ ፣ የሌለው ፣ ግምት ፣ እንደኾነ ፣ እገልጽልዎታለሁ ፡፡

፳/ እንደ ፣ እውነቱም ፣ ዮስጢኖስ ፣ ካቶሊክ ፣ የኬልቄዶንን ፣ ጉባኤ ፣ ደጋፊና ባንድ ፣ ባሕርይ ፣ ባዮች ፣ ዋና ፣ ጠላት ፣ እንደነበረ ፣ በነዚሁም ፣ ዘንድ ፣ እንደ ፣ ክፉ ፣ ሰውና ፣ እንደ ፣ መናፍቅ ፣ ይገመት ፣ እንደ ፣ ነበረ ፣ የተረጋገጠ ፣ ነው ብለዋል ፡፡

፳/ ይህ ፣ እውነት ፣ ሳይኾን ፣ አይቀርም ፣ ይኾን ፣ ይኾናል ፡፡

፳፩/ እንዲሁም ፣ ንጉሠ ፣ ነገሥት ፣ ካሌብ ፣ አላይ ፣ በተገለጠው ፣ ምክንያት ፣ መሠረት ፣ ካቶሊክ ፣ ነበረ ፣ ለማለት ፣ የሚቻል ፣ ነው ፡፡ ብለዋል ፡፡

፳፩/ አላይ ፣ የተገለጠው ፣ መረጃ ፣ ንጉሥ ፣ ካሌብ ፣ ተራ ፣ ካቶሊክ ፣ ብቻ ፣ ሳይኾን ፣ የበለጠ ካቶሊክ ፣ የካቶሊክ ፣ ነገሥታት ፣ ባለኪዳን ፣ የካቶሊክ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ እንደ ፣ ቅዱስ ፣ የምታከብረው ፣ ነበረ ፣ ከማለት ፣ በቀር ፣ ለካቶሊክነቱ ፣ መረጃ ፣ አላቀረቡም ፣ እኔም ፣ ይህ ፣ በቂ ፣ ኾኖ ፣ ካቶሊክ ፣ የማያሰኘው ፣ መኾኑን ፣ በሰፊው ፣ አስረድቸዋለሁ ፣ በቂ ፣ መረጃ ፣ አቅርበው ፣ ካቶሊክነቱን ፣ ያስረዱ ፣ አስመሰለው ፣ ከላይ ፣ በተገለጠው ፣ ምክንያት ፣ ካቶሊክ ፣ ነበረ ፣ ለማለት ፣ ይቻላል ፣ ማለት ፣ ተገቢ ፣ ነገር ፣ አይደለም ፣ የያዝነው ፣ እውነት ፣ ነገር ፣ ለመፈለግ ፣ ሲኾን ፣ ባልተጨበጠ ፣ ነገር ፣ ላጭበርብራችሁ ፣ ማለት ፣ ሐሳብዎን ፣ ዋጋ ፣ እንደ ፣ ማሳጣት ፣ የሚቈጠር ፣ ነው ፡፡

፳፪/ ይህን ፣ መሠረት ፣ በማድረግና ፣ እንደ ፣ ተረጋገጠ ፣ በመቀበል ፣ የምሥራቁ ፣ ንጉሥ ፣ ከንጉሥ ፣ ካሌብ ፣ እገዛን ፣ ለመለመን ፣ ሲፈልግ ፣ ያገናኘው ፣ የእስክንድርያ ፣ ሊቀ ፣ ጳጳሳትና ፣ የኢትዮጵያው ፣ ንጉሠ ፣ ነገሥት ፣ የታመነ ፣ አማካሪ ፣ የኾነው ፣ አባ ፣ ጰንጠሌዎን ፣ ካቶሊክ ፣ ነበረ ፣ ለማለት ፣ የተገባ ፣ ኾኖ ፣ ይታየናል ፣ ካሉ ፣ በኋላ ፣ ተገቢ ፣ ኾኖ ፣ የሚታይበትን ፣ ምክንያት ፣ ሲገልጡ ፣ ዮስጢኖስን ፣ ያህል ፣ ትልቅ ፣ በኾነ ፣ ጉዳይ ፣ ውስጥ በሃይማኖት ፣ በኩል ፣ ከማይስማማውና ፣ ከሚጠላው ፣ ሊቀ ፣ ጳጳሳት ፣ ጋራ ፣ ተስማምቶአል ፣ ማለት ፣ እንዲሁም ፣ ቅዱሱ ፣ ንጉሥ ፣ ካሌብ ፣ ራሱ ፣ ካቶሊክ ፣ ሲኾን ፣ ካቶሊክ ፣ ባልኾነ ፣ ሊቀ ፣ ጳጳሳት ፣ በመታዘዝ ፣ በሃይማኖት ፣ ከርሱ ፣ ጋራ ፣ ከማያብረው ፣ መነኩስ ፣ ምክርና ፣ ቡራኬን ፣ ተቀብሏል ፣ ማለት ፣ ከእውነት ፣ የሚቆጠር ፣ ኾኖ ፣ ስለማይታይ ፣ ነው ፣ ብለዋል ፡፡

፳፪/ ንጉሥ ፣ ካሌብ ፣ ካቶሊክ ፣ ለመኾኑ ፣ የታመነ ፣ መረጃ ፣ ሳይጨብጡ ፣ ካቶሊክ ፣ ነበረ ፣ ብሎ ፣ በማውራት ፣ ብቻ ፣ በርሱ ፣ ጥግ ፣ ከዮስጢኖስ ፣ ጋራ ፣ ያገናኘው ፣ የእስክንድርያው ፣ ሊቀ ፣ ጳጳሳት ፣ አባ ፣ ጢሞቴዎስና ፣ አማካሪው ፣ አባ ፣ ጰንጠሌዎን ፣ ካቶሊካውያን ፣ ኖረዋል ፣ ማለት ፣ ተገቢ ፣ መኾኑ ፣ ሲታየው ፤ ዮስጢኖስ ፣ በሃይማኖት ፣ ከማይስማማው ፣ ሊቀ ፣ ጳጳሳት ፣ ጋራ ፣ ተስማምቷል ማለትና ፣ ንጉሥ ፣ ካሌብ ፣ ካቶሊክ ፣ ላልኾነ ፣ ሊቀ ፣ ጳጳሳት ፣ ታዘዘ ፣ ማለት ፣ እንዲሁም ፣ ከባ ፣ ጰንጠሌዎን ፣ ምክርንና ፣ ቡራኬን ፣ ተቀበለ ፣ ማለት ፣ ከእውነት ፣ የሚቈጠር ፣ መኾኑን ፣ አላይልዎም ፣ ያለውን ፣ ዐይን ፣ ዓይን ፣ አይበሉት ፣ ይህንን ፣ አስተያየት ፣ በማቅረብ ፣ ፈንታ ፣ ዮስጢኖስ ፣ አልወረደም ፣ አልተወለደም ፣ ተስፋ ፣ አልደረሰም ፣ ሥጋ ፣ አልለበሰም ፣ የሚል ፣ ባላጋራ ፣ ቢነግበት ፣

ምንም ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ሁለት ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ብንለያይ ፡ በመሠረቱ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ በማለት ፡ እንተባበራለንና ፡ ብሎ ፡ በባህል ፡ የማይመስለውን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ ጢሞቴዎስን ፡ በባህል ፡ ወደ ፡ ማይመስለው ፡ ወደ ፡ ዐፄ ፡ ካሌብ ፡ ላከ ፡ እነርሱም ፡ እንደዚሁ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ብንለያይም ፡ በመሠረቱ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ በማለት ፡ እንገናኛለን ፡ ሲሉ ፡ ርዳታ ፡ አደረጉለት ፡ ብለው ፡ ቢኾን ፡ አስተዋይ ፡ አርቆ ፡ ተመልካች ፡ ባሰኘዎ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ይህስ ፡ አሁን ፡ ያቀረቡት ፡ አስተያየት ፡ ምንም ፡ ሳይነካው ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ የሚፈርስ ፡ የእንቧይ ፡ ካብ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ በሚከተለው ፡ መሥመር ፡ ርስዎ ፡ እራስዎ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እያሉ ፡ ሲያፈራርሱት ፡ ይገኛሉ ።

፳፫/ የ፱ ፡ ቅዱሳን ፡ በሃይማኖት ፡ ከንጉሡና ፡ ከጳጳሱ ፡ ሃይማኖት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እንደነበሩም ፡ በገድለ ፡ ያሬድ ፡ ወኀበረ ሃይማኖቶሙ ፡ ምስለ ፡ ንጉሥ ፡ ወጳጳስ ፡ ባለው ፡ ይረዳል ፡ ብለዋል ።

፳፫/ ፱ ፡ ቅዱሳን ፡ በሃይማኖት ፡ ከንጉሡና ፡ ከጳጳሱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ መኾናቸው ፡ የማይካድ ፡ ነው ፡ የኸውም ፡ አንድ ፡ የኾኑበት ፡ ሃይማኖት ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ አይደለም ፡ (መረጃ) ።

(ሀ) ኢትዮጵያ ፡ በፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ የተቀበለች ፡ መኾኗን ፡ እርስዎ ራስዎ ፡ ያረጋገጡት ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ገጽ ፡ ፵፱ ፡ ፹ ፡ ፹፩ ፡ ፹፪ ።

(ለ) ከፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ጀምሮ ፡ አሁን ፡ በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ብርታትና ፡ ትጋት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጳጳሳት ፡ እስኪሾሙ ፡ ድረስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚሾሙ ፡ ጳጳሳት ፡ ግብጸውያን ፡ ጳጳሳት ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ የማይካድ ፡ ነው ።

(ሐ) በኢትዮጵያ ፡ የሚሾሙ ፡ ግብጸውያን ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ አጽንተው ፡ የያዙ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ አጥብቀው ፡ የሚቃወሙ ፡ መኾናቸው ፡ የማይካድ ፡ ነው ።

(መ) ኢትዮጵያ ፡ በዚህ ፡ ባንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ጸንታ ፡ ከመኖሯ ፡ በቀር ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ እገሌ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ አስተምሯት ፡ ተቀበለች ፡ የሚባልበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ፡ እርስዎ እንኳን ፡ ያልኾነውን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በማስመሰል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሮማ ፡ የተለየችው ፡ መቼ ፡ ነው ፤ የተለየችበትስ ፡ ምክንያት ፡ ምንድርን ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ከመጠየቅ ፡ በቀር ፡ ያንድ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ መቀበሏን ፡ አረጋግጠው ፡ እንደመሰከሩ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይንም ፡ ባህል ፡ በዚህ ጊዜ ፡ ተቀበለች ፡ ብለው ፡ ለማስረዳት ፡ አልሞከሩም ፡ እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ ኹሉ ፡ መረጃ ፡ ኢትዮጵያ ከፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ጀምራ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ብቻ ፡ ይዛ ፡ የኖረች ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ያልተቀበለች ፡ መኾንዋ ፡ ስለተረጋገጠ ፡ ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ከንጉሡና ፡ ከጳጳሱ ፡ ጋራ ፡ የተባበሩበት ፡ ሃይማኖት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ እንደኾነ ፡ ተረጋገጠ ፡ ማለት ፡ ነው ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ንጉሥ ፡ ካሌብ ፡ ካቶሊክ ነበረ ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ካቶሊክ ፡ ነበረ ፡ አባ ፡ ጰንጠሌዎንም ፡ ካቶሊክ ፡ ነበረ ፡ ያሉትን ፡ አስተያየት ፡ ርስዎ ፡ ራስዎ ፡ መልሰው ፡ እንዳፈራረሡት ፡ ይረዱት ።

፳፬/ ኹለቱን ፡ ካቶሊኮች ፡ ዮስጢኖስንና ፡ ካሌብን ፡ ያገናኘው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ካቶሊክ ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባይ አይደለም ፡ የሚለውን ፡ እኛ ፡ የምናቀርበውን ፡ አሳብ ፡ የሚቃወሙ ፡ ስንክሳርና ፡ የአኩስምን ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ያባ ፡ ጰንጠሌዎንን ፡ ገድል ፡ የመሰሉ ፡ በጣም ፡ የተከበሩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መጻሕፍቶች ፡ አሉ ።

እነርሱም ፡ የተባለው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በርግጥ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ እንጂ ፡ ካቶሊክ ፡ ያልነበረው ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ፫ኛ ፡ ከ፭፻፷፰ ፡ እስከ ፡ ፭፻፺፮ ፡ የእስክንድርያው ፡ ፴፪ኛው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ ብለው ፡ ሐሳብዎን ፡ የሚቃወሙ ፡ መጻሕፍት ፡ መኖራቸውን ፡ ካስረዱ ፡ በኋላ ፡ ምስክርነታቸውን ፡ በራስዎ ፡ ሐሳብ ፡ ብቻ ፡ ሊያፈርሱ ፡ ፈልገው ፡ ይህን ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ከማይስማሙ ፡ ምስክሮች ፡ የተነሣውን ፡ ችግር ፡ ለመፍታት ፡ ዮስጢኖስ ፡ ጥሩ ፡ ካቶሊክ ፡ እንደ ፡ ነበርና ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትን ፡ በተለየም ፡ ጢሞቴዎስን ፡ በመልካም ፡ ዓይን ፡ ያያቸው ፡ እንዳልነበረ ፡ ማሰብ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

፳፬/ ባሁኑ ፡ ንግግርዎስ፡ላይ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ በእርግጥ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ መኾኑን ፡ የሚመሰክሩ ፡ መጻሕፍት ፡ መኖራቸውን ፡ መጻሕፍቱም ፡ የተከበሩ ፡ መኾናቸውን ፡ አረጋግጠው ፡ ከመሰከሩ ፡ በኋላ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ የማይስማሙ ፡ ምስክሮች ፡ ብለው ፡ ምስክርነታቸውን ፡ ሊነቅፉ ፡ ሞክረዋል ። ነገሩ ፡ እውነት ፡ ኹኖ ፡ ቢኾን ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ መጽሐፍ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ መጽሐፍ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አፈረሰው ፡ እያሉ ፡ ዘርዝረው ፡ ባስረዱ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ የማይስማሙ ፡ ምስክሮች ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ ባልዘለሉትም ፡ ነበረ ። እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ ንግግርዎ ፡ ዮስጢኖስንና ፡ ካሌብን ፡ ያገናኘው ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ጢሞቴዎስ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ እንዳልነበረ ፡ የሚያረጋግጡ ፡ መጻሕፍት ፡ በኢትዮጵያ ፡ መኖ

ራቸውን ፡ ካረጋገጡ፡ ምስክርነታቸው፡ የማይስማማ ፡ መኾኑንም ፡ በቃል ከማውራት ፡ በቀር ፡ ዘርዝሮ ፡ ማስረዳት ፡ ካልቻሉ ፡ ዮስጢኖስንና ፡ ካሌብን ፡ ያገናኘው ፡ አባ ፡ ጢሞቴዎስና ፡ አባ ፡ ጳንጠሌዎን ፡ ካቶሊክ ፡ ኖረዋል ፡ ለማለት ፡ የተገባ ፡ ኾኖ ፡ ይታየናል ፡ ያሉት ፡ ትክክለኛ ፡ አስተያየት ፡ አለመኾ ኑን ፡ ይገንዘቡት ፡ የተናገሩትንም ፡ መልሰው ፡ እንዳፈረሱ ፡ ይረዱ ።

፳፮/ የዲዮስቆሮስ ፡ ወገን ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ለሊቀ ፡ ጳጳስነት ፡ በተመረጠ ፡ ጊዜ ፡ ዮስጢኖስ ፡ አልቀበለውም ፡ ብሎ ፡ ካቶሊኮቹ ፡ ሌላ ፡ እንዲመርጡ ፡ አዘዘ ፡ አስጡርዮስን ፡ አስመርጦ ፡ ኹለቱ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ በእስክንድርያ ፡ ተገኝተው ፡ ነበረ ። ይህ ፡ እውነት ፡ ከኾነ ፡ ዮስጢኖስ ፡ የዐረብ ፡ ክርስቲያኖችን ፡ መርዳት ፡ ን ፡ ያህል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለው ፡ ጉዳይ ፡ ሲቀበለው ፡ ባልፈለገ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አድርጎ ፡ ሲያከናውነው ፡ ፈቀደ ፡ ብሎ ፡ ማሰብ ፡ እውነት ፡ አይመስልምና ፡ ስለዚህ ፡ ዮስጢኖስ ፡ ከንጉሥ ፡ ካሌብ ፡ ጋራ ፡ የተስማማው ፡ በካቶሊኩ ፡ በእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በአስጡርዮስ ፡ አማካይነት ፡ ሳይኾን ፡ አይቀርም ፡ ብለዋል ።

፳፯/ መላልሼ ፡ እንደአስገነዘብኩዎ ፡ ከላይ ፡ የሰጡት ፡ አስተያየት ፡ የተካከለ ፡ ካለመኾኑ ፡ የተነሣ ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ካቶሊክ ፡ ነበረ ፡ ያሉት ፡ አስተያየት ፡ ዋጋ ፡ እንዳላወጣ፡ ተረድተውት ፡ ዮስጢኖስንና ፡ ካሌብን ፡ ያገናኘ ፡ አስጡርዮስ ፡ የተባለው ፡ ካቶሊክ ፡ ነው ፡ ወደ ፡ ማ ለት ፡ አዘንብለዋል ። ይህም ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ አስጡርዮስ ፡ ያለውድ ፡ በግድ ፡ በእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስነት ፡ ቢሾም ፡ በጢሞቴዎስ ፡ ላይ ፡ እንደጠፍ ፡ ታቦት ፡ ተደርቦ ፡ ብጽብጽንና ፡ ሁከትን ፡ ፈጠረ ፡ እንጂ ፡ ስንኳንስ ፡ ስብከቱ ፡ እስከ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ደርሶ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የሚሠራ ተሰሚነት ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ ሊኖረው ፡ በእስክንድርያ ፡ ያሉምእመናንም ፡ ወደው ፡ አልተቀበሉ ትም ፡ ሥልጣኑንም ፡ አላወቁለትም ። ታሪኩም ፡ ኢጣልያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በግፍ ፡ ወረረች ፡ ተብሎ ፡ እንደሚነገረው ፡ በወራሪነትና ፡ በግፈኝነት ፡ ተጽፎበታል ፡ እንጂ ፡ ሕጋዊ ፡ ኾኖ ፡ አልተጻፈለትም ፡ ስለዚህ ፡ በዓመፅ ፡ ተጋፍቶ ፡ በሰው ፡ ወንበር ፡ ልቀመጥ ፡ ባለ ፡ በአስጡርዮስ ፡ አማካይነት ፡ ሳይኾን አይቀርም ፡ ብሎ ፡ ማሰብ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

፳፰/ በገድል ፡ አራታ ፡ ስማዕት ፡ በጢሞቴዎስ ፡ ፈንታ ፡ አስተርዮስ ፡ የሚለውን ፡ እናገኛለን ፡ በዚሁ ፡ ገድል ፡ ውስጥ ፡ ድሁንዋስ ፡ በክርስቲያኖች ፡ ላይ ፡ ይፈጽመው ፡ የነበረውን ፡ ግፍ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ንጉሥ ፡ በሕምያሮች ፡ ላይ ፡ እንዲያነሣሣው ፡ ወደ ፡ አስጡርዮስ ፡ ላከ ፡ የእስክንድርያውም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ንዋሮንና ፡ አስቆጥስ ፡ ካሉ ፡ ርቱዓን ፡ ሃይማኖት ፡ መነኮሳት ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ምህላ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ካሳረገ ፡ በኋላ ፡ የዮስጢኖስን ፡ አሳብ ፡ ለንጉሡ ፡ አስታወቀው ፡ የሚል ፡ ደግሞ ፡ እናገኛለን ፡ ስለዚህ ፡ ካቶሊኩ ፡ ንጉሥ ፡ ካሌብ ፡ የታዘዘለት ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቅዱሱም ፡ መነኮስ ፡ አባ ፡ ጰንጠሌዎን ፡ ጸሎቱና ፡ ቡራኬው ፡ ካንተ ፡ አይለይ ፡ ሲል ፡ የተመኘለት ፡ ካቶሊኩ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አስጡርዮስ ፡ ሊኾን ፡ ግድ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

፳፱/ ለዚህ ፡ ተግባር ፡ መደበኛ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ መኾኑን ፡ በገጽ ፡ ፳፫ ፡ አረጋግጠው ፡ ጽፈው ፡ ነበረ ፡ ሌሎችም ፡ መጻሕፍት ፡ ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ መደበኛው ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ጢሞ ቴዎስ ፡ መኾኑን ፡ እያረጋገጡ ፡ ጽፈዋል ። ይህም ፡ ከኾነ ፡ ፬፻፶ ፡ ዘመን ፡ በላይ ፡ ኾኗል ፡ እንግዲህ ፡ በርስዎ ፡ አሳብ ፡ ይህን ፡ ያስደረገ ፡ አስጡርዮስ ፡ መኾኑ ፡ ግድ ፡ የማይቀር፡ ከኾነ ፡ መልእክ ፡ ዕዝራን ጸውዓ ፡ ለዕለት ፡ እንተ ፡ ትማልም ፡ ሐለፈት ።

ትላንት ፡ ያለፈችቱን ፡ ቀን ፡ መልስህ ፡ የዛሬ ፡ ቀን ፡ አድርገህ ፡ አሳየኝ ፡ እንዳለው ፡ እርስዎም ፡ ያችን ፡ ጢሞቴዎስና ፡ ካሌብ ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ የሠሩባትን ፡ ዕለት ፡ ጠርተው ፡ የዛሬን ፡ ቀን ፡ አድር ገው ፡ ሥራውንም ፡ እንደገና ፡ በአስጡርዮስ ፡ አሠርተው ፡ ያሳዩን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በቃል ብቻ ፡ ግድ ፡ ነው ፡ ቢሉን ፡ አንቀበልዎትም ።

፴/ የስሞች ፡ መለዋወጥ ፡ ባህላቸውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ በማድረግ ፡ የታሪኩን ፡ መጻሕፍት ፡ ለማበላሸት ፡ ያልኾነውንና ፡ ያልዋለውን ፡ አስመስለው ፡ የመጻፍ ፡ ልማድ ፡ ካንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ ግብጻውያን ፡ ተንኮል ፡ የመጣ ፡ መኾኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

፴፩/ በልዩ ልዩ መጻሕፍት ፡ ተጽፎ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የቆየውን ፡ ታሪክ ፡ እርስዎ ፡ በሐሳብዎ ፡ ሊለውጡ ፡ ከጅለው ፡ ከሐሳብዎ ፡ እያመነጩ ፡ ይህ ፡ ሳይኾን ፡ አይቀርም ፡ ይህ ፡ ሊኾን ፡ ግድ ፡ ነው፤ እንዲህ ፡ ማለት ፡ የተገባ ፡ ይመስለናል ፡ እያሉ ፡ ሲጣጣሩ ፡ አየን ፡ እንጂ ፡ ግብጻውያን ፡ ይህን ፡ ሲያደርጉ ፡ ባለማየታችን ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ልንቀበልዎ ፡ አልቻልንም ።

፴፪/ እንግዲህ ፡ እላይ ፡ በተባለው ፡ መሠረት ፡ ቅዱሱ ፡ ንጉሥ ፡ ካሌብ ፡ ምክርንና ፡ ቡራኬን ፡ ለመቀበል ፡ እንደመናፍቅ ፡ የሚቆጥረውን ፡ ሰው ፡ መረጠ ፡ ማለት ፡ ከእውነት ፡ ሊቆጠር ፡ ስለማይቻል ፡ የንጉሡ ፡ መንፈሳዊ ፡ አባት ፡ የነበረው ፡ አባ ፡ ጰንጠሌዎን ፡ ከነባልንጀሮቹ ፡ ካቶሊክ ፡ እንደነበሩ ፡ እርግጥን ፡ በሚያህል ፡ ሊታመን ፡ የማቻል ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

፴፫/ መጀመሪያ ፡ የንጉሥ ፡ ካሌብን ፡ ካቶሊክነት ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ሳያቀርቡ ፡ እርግጥን ፡ በሚያህል ፡ ሊታመን ፡ የሚቻል ፡ ነው ፡ በማለትዎ ፡ እርግጥ ፡ የሚባለውን ፡ አማርኛ ፡ ፍጹም ፡

መተማመኛ ፡ ከመኾን ፡ አውጥተው ፡ ሐሰትን ፡ የሚያመለክት ፡ አድርገውታል ፡ በይኾናልና ፡ በይመስላል፡ ብቻ፡ የተጠጋጋ፡ ምኞትዎን ፡ እንደቁም ፡ ነገር ፡ ቆጥረውት ፡ እንዲህ ፡ ማለትዎ ፡ እጅግ ያሳዝናል ፡ በእውነቱ ፡ ሊታመን ፡ የማይቻልስ ፡ አንድ ፡ መረጃ ፡ ሳይዙ ፡ ካቶሊካዊው ፡ ዮስጢኖስ ፡ ከ፬ ፡ ካሌብ ፡ ርዳታ ፡ ከጠየቀ ፡ ፬ ፡ ካሌብ ፡ ካቶሊክ ፡ ይኾናል ፡ ፬ ፡ ካሌብም ፡ ምናልባት ፡ ካቶሊክ ፡ ኾኖ ፡ እንደኾን ፡ አባ ፡ ጰንጠሌዎን ም ፡ ካቶሊክ ፡ ይኾናል ፡ እያሉ ፡ መተቸት ፡ ነው ።

መቼም ፡ የተጨበጠ ፡ እውነት ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ለግምት ፡ ግምት ፡ ምነው ፡ ዮስጢኖስ ፡ በእስክ ንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በአባ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ አማካይነት ፡ ወደ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ፬ ፡ ካሌብ ፡ ርዳታ ፡ መጠየቁ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ቢኾን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መገመት ፡ አይሻልም ፡ ነበርን ። ለዚህ ፡ ምኞት ፡ አሳቢውም ፡ ተናጋሪውም ፡ ሰሚውም ፡ ተቀባዩም ፡ እርስዎ ፡ ብቻ ፡ ነዎ ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ተቀባይ ፡ አያገኙም ።

፴/ ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ካቶሊኮች ፡ እንደነበሩ ፡ ከተረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተለይታ ፡ ወዳንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ያለፈችው ፡ በነርሱ ፡ ሰብኮት ፡ ነው ፤ የሚባለው ፡ አሳብ ፡ ሊቀበሉት ፡ የማይቻል ፡ ኾኖ ፡ ይቀራል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

፴/ ኢትዮጵያ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ በ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ተቀበለች ፡ ይላሉ ፡ ማለትን ፡ እርስዎ ፡ ለማደናገር ፡ የፈጠሩት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ከመፈጠሩ ፡ አስቀድማ ፡ በፍሬምናጦስ ፡ ተቀበለችው ፤ ከዚያም ፡ እስ ከዚህ ፡ ድረስ ፡ በዚያው ፡ ጸንታ ፡ ትኖራለች ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ የተቀበለችበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ በ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ጊዜ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ተቀበለች ፡ አንልም ፡ አንድ ፡ መረጃ ፡ ሳያቀርቡ ፡ ፱ቱ ፡ ቅዱሳን ፡ ካቶሊኮች ፡ እንደነበሩ ፡ ከተረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ ብሎ ፡ መና ገርም ፡ ፍጹም ፡ ማጭበርበር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ንግግር ፡ አይደለም ።

፴፭/ እንግዲህ ፡ በ፮ኛ ፡ ፻ ፡ ዘመን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገና ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ፡ አብራ ፡ ትኖር ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ ማሰብ ፡ የተገባ ፡ ነው ። ብለዋል ።

፴፭/ ኢትዮጵያ ፡ ገና ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ፡ አብራ ፡ ትኖር ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ ማሰብ አስቀድሞ ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ፡ የተገናኘችበት ና ፡ በኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ የተ ስማማችበት ፡ ጊዜ ፡ መኖሩን ፡ አረጋግጦ ፡ አስረድቶ ፡ ነበረ ።

ኢትዮጵያ ፡ የአንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ከተቀበለችበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ከዚህ ፡ ባህል ፡ ያልተና ወጠች ፡ መኾኗ ፡ ሲታወቅ ፡ ገና ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ፡ ነበረች ፡ እያሉ ፡ ማውራት ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ አሳብ ፡ ቀላል ፡ አድርጎ ፡ እንደሚያስገምት ፡ ባለመገንዘብዎ ፡ አዝናለሁ ።

፴፯/ አንዳንዶቹ ፡ ስንኳን ፡ ለምሳሌ ፡ ሶስርዮ ፡ አላይ ፡ ከተባለው ፡ ዘመን ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ከቆየች ፡ በኋላ ፡ ነው ይላሉ ። እንደ ፡ እውነቱም ፡ ለዚህ ፡ አሳብ ፡ የሚኾኑት ፡ ምስክሮችና ፡ ኹኔታዎች ፡ አይታጡም ፡ ብለዋል ።

፴፯/ ካልታጡ ፡ እያመጧቸውም ፡ ኖሯልን ፡ ለመቼ ፡ ይቆጥቧቸዋል ? እርስዎ ፡ ራስዎ ፡ ብቻ፡ ይመስላል ፤ ያሰኛል ፤ እያሉ ፡ ምኞትዎን ፡ ይቀባጥራሉ ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ደጋፊ ፡ እያገኙም ። በዚህ ፡ በ፪ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ያቀዱት ፡ ዐቅድ ፡ ጠቅላላ ፡ አስተያየቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከጥንት ፡ ጀምራ ፡ ካቶሊክ ፡ ነበረች ፡ ማለትን ፡ መላልሼ ፡ በመናገር ፡ የሰማዕያኑን ፡ ጆሮ ፡ ከመላሁት ፡ በኋላ ፡ ምናልባት ፡ እው ነት ፡ ይኾን ፡ የሚል ፡ ስሜት ፡ በልቡናቸው ፡ ሲፈጠር ፡ እንግዲህ ፡ ቀድሞ ፡ ወደ ፡ ነበራችሁበት ፡ ወደ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ብትመለሱ ፡ ምን ፡ አለበት ፡ ለማለት ፡ ይመቸኛል ፡ ብለው ፡ ያቀዱት ፡ መኾኑን ፡ ተገንዝበናል ።

ይህንም ፡ እቅድ ፡ እውነት ፡ ለማስመሰል ፡ ይረዳዎ ፡ ዘንድ ፡ የቍስጥንጥንያው ፡ ንጉሥ ፡ ዮስ ጢኖስ፡በእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በጢሞቴዎስ ፡ አማካይነት ፡ የኢትዮጵያው ፡ ንጉሥ ፡ ፬ ካሌብ፡ የመን ፡ ከተማ ፡ በናግራን ፡ ባሉ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ላይ ፡ በግፍ ፡ የተነሣባቸውን ፡ አይሁዳዊ ፡ ጠላት ፡ እንዲበቀልና ፡ እንዲያጠፋው ፡ የለመነው ፡ መኾኑንና ፡ ንጉሥ ፡ ካሌብም ፡ ልመናውን ፡ ሰምቶ ፡ ከአባ ፡ ጰንጠሌዎን ፡ በረከትን ፡ ተቀብሎ ፡ ሒዶ ፡ ግፈኛውን ፡ ጠላት ፡ ተበቅሎ ፡ ማጥ ፋቱን ፡ ጠቅሰዋል ። ይህ ፡ ዓለም ፡ በሙሉ ፡ ተካክሎ ፡ የሚያውቀው ፡ እውነተኛ ፡ ታሪክ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ በሙሉ ፡ ያወቀውን ፡ እውነተኛ ፡ ታሪክ ፡ በይኾናል ፡ ሊለውጡ ፡ አሰበው ።

ሀ/ ዮስጢኖስ ፡ በካቶሊክነት ፡ የታወቀ ፡ ስለኾነ ፡ የእስክንድርያውን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ጢሞ ቴዎስን ፡ መላኩ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ካቶሊክ ፡ ቢኾን ፡ ይኾናል ።

ለ/ ንጉሥ ፡ ካሌብ ፡ የዮስጢኖስን ፡ ልመና ፡ በጢሞቴዎስ ፡ አማካይነት ፡ መቀበሉ ፡ ካቶሊክ ፡ ቢኾን ፡ ይኾናል ።

ሐ/ አባ ፡ ጰንጠሌዎን ፡ የጢሞቴዎስ ፡ ጸሎት ፡ የዮስጢኖስ ፡ ዕንባ ፡ የስማዕታተ ፡ ናግራን ፡ የመሥዋዕትነታቸው ፡ መዓዛ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፡ ብሎ ፡ ቡራኬውን ፡ መስጠቱ ፡ ካቶሊክ ፡ ቢኾን ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ፡ ዮ ስ ጢ ኖ ስ ን ፡ ያህል ፡ ካቶሊክ ፡ ንጉሥ ፡ በሃይማኖት ፡ ከማይመስሉት ሰዎች ፡ ርዳታን ፡ ጠየቀ ፡ ማለት ፡ እውነት ፡ አይመስልም ፡ እያሉ ፡ ምኞትዎን ፡ በይኾናልና፡ በይመስላል ፡ ሊያጸድቁ ፡ ይጣጣራሉ ።

ምነው ፡ ነገሩን ፡ በእውነት ፡ የሚያመዛዝኑ ፡ ከኾነ ፡ ዮስጢኖስ ፡ አርቶዶክስ ፡ ኖሯል ፡ የተባለ፡ እንደሆነ ፡ ክብሩ ፡ ይቀንሳል ፡ ብለው ፡ ያሰቡትን ፡ ያህል ፡ እንደዚኹውም ፡ ካሌብን ፡ ያህል ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት ፡ ጢሞቴዎስን ፡ ያህል ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ጰንጠሌዎንን ፡ ያህል ፡ ጻድቅ ፡ አንድ ፡ መረጃ ፡ ሳል ይዝ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ነበሩ ፡ ብዬ ፡ ባወራ ፡ ክብራቸው ፡ ይቀንሳል ፡ አይሉም ፡ ነበረን ፡ ሐሳብዎን ፡ ያጋፌ ፡ ለወገንዎ ፡ አድላዊ ፡ መኾንዎ ፡ በዚህ ፡ ይታወቃል ።

በዚህ ፡ ፈንታስ ፡ ኹሉንም ፡ በየባህላቸው ፡ አጽንተው ፡ ዮስጢኖስ ፡ አይሁዳዊው ፡ ግፈኛ ፡ ጠላት ፡ ናግራን ፡ ባሉ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ላይ ፡ ያደረሰውን ፡ ግፍ ፡ በማየቱ ፡ ከጢሞቴዎስና ፡ ከዐፄ ፡ ካሌብ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ብንለያይም ፡ የናግራን ፡ ሰዎች ፡ በሃይማኖት ፡ ወንድሞቻችን ፡ ናቸው ፡ አይጨክኑባቸውም ፡ ይረዷቸዋል ፡ ብሎ ፡ ላከባቸው ።

አባ ፡ ጢሞቴዎስም ፡ ዮስጢኖስ ፡ ባይወደኝ ፡ ባላጋራየም ፡ ቢኾን ፡ ርዳታ ፡ የሚደረግላቸው ፡ የናግራን ፡ ሰዎች ፡ የሃይማኖት ፡ ወንድሞቼ ፡ አይደሉምን ፡ ብሎ ፡ የዮስጢኖስን ፡ ሐሳብ ፡ ለዐፄ ፡ ካሌብ ፡ አስተላለፈለት ።

ዐፄ ፡ ካሌብም ፡ ነገሩን ፡ ያስታወሰኝ ፡ ዮስጢኖስ ፡ በባህል ፡ ባይመስለኝስ ፡ ርዳታ ፡ የሚደረግላቸው ፡ የናግራን ፡ ሰዎች ፡ የሃይማኖት ፡ ወገኖቼ ፡ ወንድሞቼ ፡ አይደሉምን ፡ በዚያውስ ፡ ላይ ፡ ይህነን ፡ ተግባር ፡ ብፈጽም ፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ራሱን ፡ ለወንድሙ ፡ ቤዛ ፡ አድርጎ ፡ ከመስጠት ፡ የበለጠ ፡ ፍቅር ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ የሰጠውን ፡ ትእዛዝ ፡ መፈጸሜ ፡ አይደለምን ፡ ብሎ ፡ የዮስጢኖስን ፡ ልመና ፡ ተቀበለው ።

አባ ፡ ጰንጠሌዎንም ፡ ዮስጢኖስ ፡ ለናግራን ፡ ሰዎች ፡ አዝኖ ፡ አባ ፡ ጢሞቴዎስን ፡ ወደ ፡ ዐፄ ካሌብ ፡ መላኩን ፡ አባ ፡ ጢሞቴዎስም ፡ የዮስጢኖስን ፡ ጥላቻ ፡ ሳያስታውስ ፡ አሳቡን ፡ ለዐፄ ፡ ካሌብ ማካፈሉን ፡ ዐፄ ፡ ካሌብም ፡ የዮስጢኖስን ፡ ሃይማኖት ፡ ልዩነት ፡ ሳይመለከት ፡ ለሃይማኖት ፡ ወንድሞቹ ፡ አዝኖ ፡ ለርዳታ ፡ መነሣቱን ፡ አይቶ ፡ ኹሉቸንም ፡ በማመስገን ፡ ቡራኬውን ፡ ለዐፄ ፡ ካሌብ ሰጠ ፡ የሚል ፡ አስተያየት ፡ አቅርበው ፡ ቢኾን ፡ ምንያህል ፡ በተመሰገኑ ፡ ነበረ ፡ በዕውነቱ ፡ ይህ ፡ ዮስጢኖስ ፡ ዐፄ ፡ ካሌብን ፡ መለመኑ ፡ እርስዎ ፡ ራስዎ ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ሲያሳትሙ ፡ በሃይማኖት ፡ ከማይመስሉዎ ፡ ከግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የገንዘብ ፡ ርዳታ ፡ አገኘሁ ፡ እንደሚሉት ፡ ያለ ፡ ነው ። በገጽ ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ ተመልከት ።

## ክ ፍ ል ፫ ።

በኢትዮጵያ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ለመያዝ ፡ የመቻልና ፡ ለኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የመቃወም ፡ መጀመሪያ ፡ ምልክቶች ።

፴፪/ የመጀመሪያው ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ ጳጳስ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገባው ፡ ፯ኛ ፡ ፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወደ ፡ መጨረሻው ፡ ሲቃረብ ፡ ነው ፡ ስሙም ፡ ቴርሎስ ፡ ይባል ፡ ነበረ ፡ የላከውም ፡ ብንያም ፡ የእስክንድርያው ፡ ፴፰ኛ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ከ፮፻፳፭-፮፻፷፰ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

፴፫/ ይህ ፡ ንግግር ፡ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ታህል ፡ እውነት ፡ ያልተደባለቀችበት ፡ ፍጹም ፡ ውሸት ፡ ነው ። ፍጹም ፡ ውሸት ፡ መኾኑንም ፡ በብዙ ፡ ዓይነት ፡ መረጃ ፡ አስረዳዎታለሁና ፡ ልብ ፡ ብለው ፡ ይስሙ ።

ሀ/ ከፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ዠምሮ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚመጡ ፡ ጳጳጳሳት ፡ ኹሉ ፡ ከእስክንድርያ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ እየተሾሙ ፡ የሚመጡ ፡ መኾናቸው ፡ እርግጠኛ ፡ ነገር ፡ ነው ። እርስዎም ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍዎ ፡ ውስጥ ፡ በ፵፪ ፡ ገጽ ፡ በ፫ኛው ፡ ክፍል ፡ በሰፊው ፡ አትተው ፡ ጽፈውታል ።

የእስክንድርያ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያንም ፣ የኹለት ፣ ባሕርይ ፣ ባህል ፣ ከተጀመረ ፣ ጀምሮ ፣ ሰ፪ ፣ ባሕርይ ፣ ባህል ፣ ተ ቀዋሚነቷ ፣ እስከ ፣ ዛሬ ፣ ያላቋረጠ ፣ ነው ፣ በዚሁ ፣ መሠረት ፣ ከእስክንድርያ ፣ ተሾመው ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ የሚመጡ ፣ ግብጻውያን ፣ ጳጳሳት ፣ ኹሉ ፣ ወልድ ፣ ዋሕድ ፣ አንድ ፣ አካል ፣ አንድ ፣ ባሕርይ ፣ ማለትን ፣ አስተማሩ ፣ እንጂ ፣ በ፪ ፣ ባሕርይ ፣ አንድ ፣ አካል ፣ ብሎ ፣ ያስተማረ ፣ አንድም ፣ የለ ። ይህ ፣ አሁን ፣ በ፳ኛ ፣ ፻ ፣ ዓ/ም ፣ መጨረሻ ፣ ግድም ፣ መጣ ፣ የሚሉት ፣ ቄርሎስ ፣ የተባለው ፣ ጳጳስ ፣ ከፍሬ ፣ ምናጦስ ፣ ጀምሮ ፣ ቢቈጠር ፣ ፻፭ኛ ፣ ነው ። ከርሱ ፣ በፊት ፣ የነበሩት ፻፬ቱ ፣ ጳጳሳት ፣ የኹለት ፣ ባሕርይን ፣ ባህል ፣ ሲያስተምሩ ፣ የኖሩ ፣ አስመስሎ ፣ የ፩ ፣ ባሕርይን ፣ ባህል የሰበከ ፣ ፻፭ኛው ፣ ጳጳስ ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ መናገር ፣ ተናጋሪውን ፣ የሚያሳፍር ፣ ሰሚውን ፣ የሚያስቅቅ ፣ ፍጹም ፣ ውሸት ፣ ነው ።

ለ/ አንድ ፣ ባሕርይ ፣ ባዮች ፣ ኢትዮጵያውያንና ፣ ኹለት ፣ ባሕርይ ፣ ባዮች ፣ ካቶሊካውያን ፣ በ፲፮፻ ፣ ዓ ፣ም ፣ በዐፄ ፣ ዘድንግል ፣ ዘመን ፣ ሰፊ ፣ ክርክር ፣ ማድረጋቸውን ፣ በገጽ ፣ ፻፲፭-፻፳ ፣ ባሉት መሥመሮች ፣ ጽፈዋል ፣ ዐፄ ፣ ዘድንግልም ፣ በዚሁ ፣ ምክንያት ፣ ጦር ፣ ተነሥቶ ፣ በጦነርቱ ፣ ላይ ፣ እንደ ፣ ሞቱ ፣ ታሪክ ፣ ይነግረናል ።

፪ኛም ፣ በዐፄ ፣ ሱስንዮስ ፣ ዘመን ፣ ካቶሊካውያን ፣ በብዙ ፣ ሺህ ፣ የሚቈጠሩ ፣ ኢትዮጵያውያንን ፣ በዚሁ ፣ ምክንያት ፣ እንዳሳረዷቸው ፣ በታሪክ ፣ የታወቀ ፣ ነው ፣ ዘመኑም ፣ ከሺ፳፻፭፳—ሺ፮፻፳፫ ዓ ፣ ም ፣ ነው ፣ እንግዲህ፣ ኢትዮጵያ፣ ያንድ ፣ ባሕርይን ፣ ባህል ፣ ከመጀመሪያው ፣ ዠምራ ፣ የያዘች ፣ መኾኗ ፣ ሲታወቅ ፣ መዠመሪያው ፣ አንድ ፣ ባሕርይ ፣ ባይ ፣ ጳጳስ ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ የገባ ፣ በ፳ኛው ፣ ፻ ፣ ዓ ፣ ም ፣ መጨረሻ ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ መጻፍ ፣ ታላቅ ፣ ስሕተት ፣ መኾኑን ፣ ይገንዘቡልኝ ።

ሐ/ ወደኢትዮጵያ ፣ ከተላኩት ፣ ጳጳሳት ፣ ፳፬ኛው ፣ ጳጳስ ፣ ቄርሎስ ፣ ይባላል ፣ ይኸውም በላሊበላና ፣ በነአኩቶ ፣ ለአብ ፣ ዘመን ፣ ነው ፣ የእነርሱም ፣ ዘመን ፣ ከ፲፩፻፺፪ ፣—ሽ፪፻፴፮ ፣ ዓ፣ም ፣ ድረስ ፣ ነው ።

፪ኛም ፣ ፷፩ኛው ፣ ጳጳስ ፣ ቄርሎስ ፣ ይባላል ፣ እርሱ ፣ የመጣበት ፣ ዘመን ፣ ተለይቶ ፣ ባይታወቅም ፣ ከዐፄ ፣ ዘርዐ ፣ ያዕቆብ ፣ ዘመነ ፣ መንግሥት ፣ በፊት ፣ መኾኑ ፣ ታውቋል ፣ የዐፄ ፣ ዘርዓ ያዕቆብም፣ ዘመነ ፣ መንግሥት ፣ ከሽ፬፻፳፯—ሽ፬፻፷ ነው ፣ ይህ ፣ ፷፩ኛው ፣ ቄርሎስ ፣ የተባለው ፣ ጳጳስ ፣ በ፲፯ኛው ፣ ፻ ፣ ዘመን ፣ እንዳልደረሰ ፣ ልብ ፣ ይበሉ ።

፫ኛም ፣ በዘመነ ፣ መሳፍንት ፣ በትግሬ ፣ ራስ ፣ ወልደ ፣ ሥላሴ ፣ በበጌምድር ፣ ራስ ፣ ጉግሳ ፣ በሸዋ ፣ ወሰን ፣ ሰገድ ፣ በጎጃም ፣ ደጃች ፣ ኀሹ ፣ ይገዙ ፣ በነበረበት ፣ ጊዜ ፣ ቄርሎስ ፣ የተባለ ፣ ጳጳስ ፣ መጥቷል ፣ እኒህ ፣ መሳፍንት ፣ የግዛታቸው ፣ ዘመን ፣ ከሽ፯፻፺፯ ፬— ሽ፰፻፲፰ ፣ ዓ ፣ ም ፣ ድረስ ፣ ነው ፣ እንግዲህ ፣ ከነ ፣ ፬ ፣ ቄርሎስ ፣ እየተባሉ ፣ ከሚጠሩት ፣ ጳጳሳት ፣ ኹሉ ፣ የ፲፯ኛው ፣ ፻ ፣ ዘመን ፣ መጨረሻ ፣ የብንያሚን ፣ ዘመን ፣ የያዘ ፣ አልተገኘም ፣ በ፲፱ኛው ፣ ፻ ዘመን ፣ መጨረሻ ፣ ቄርሎስ ፣ የሚባል ፣ ጳጳስ ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ ያልተላከ ፣ ከኾነ ፣ ቄርሎስ ፣ የሚባለው ፣ አንድ ፣ ባሕርይ ፣ ባይ ፣ ጳጳስ ፣ ፳ኛው ፣ ፻ ፣ ዓ/ም ፣ ወደ ፣ መጨረሻው ፣ ሲቃረብ ፣ በኢትዮጵያ ፣ ገባ ፣ የሚሉት ፣ ትችት ፣ መሠረት ፣ የሌለው ፣ ፍጹም ፣ ውሸት ፣ መኾኑ ፣ በጉልህ ፣ ታወቀ ፣ ሊባል ፣ ይቻላል ፣ የብላቴን ፣ ጌታ ፣ ኅሩይ ፣ ወልደ ፣ ሥላሴን ፣ መጽሐፍ ፣ ዋዜማ ፣ ተመልከት ።

ምናልባት ፣ ደግሞ ፣ ክቡር ፣ ብላቴን ፣ ጌታ ፣ ኅሩይ ፣ በዚሁ ፣ ዋዜማ ፣ በተባለው ፣ መጽሐፍ ፣ በዘመነ ፣ መሳፍንት ፣ የመጣው ፣ ቄርሎስ ፣ የተባለው ፣ ጳጳስ ፣ የጐንደር ፣ ሊቃውንት ፣ በቅብዐተ ፣ መንፈስ ፣ ቅዱስ ፣ የባሕርይ ፣ ልጅ ፣ የጸጋ ፣ ልጅ ፣ በመባባል ፣ ሲከራከሩ ፣ ቢያገኛቸው ፣ ወልድ ፣ ቅብዕ፣ ለሊሁ ፣ ቀባዒ ፣ ወለሊሁ ፣ ተቀባዒ ፣ ብሎ ፣ ለጐንደር ፣ ሊቃውንት ፣ የማይስማማ ፣ ትምርት ፣ አስተማረ ፣ ብለው ፣ ጽፈዋል ።

ምናልባት ፣ ይህን ፣ ሰምተው ፣ ይጠቅመኛል ፣ መስሎዎ ፣ ጠቅሰውት ፣ እንደ ፣ ኾነ ፣ እነዚህ ፣ ኹለቱም ፣ ወገኖች ፣ ወልድ ፣ ቅብዕ ፣ መንፈስ ፣ ቅዱስ ፣ ቅብዕ ፣ በመባባል ፣ የሚከራከሩ ፣ ኹለት ፣ ባሕርይ ፣ ከማለት ፣ እንጠበቃለን ፣ እያሉ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ማንኛቸውም ፣ ቢኾኑ ፣ የኹለት ፣ ባሕርይን ባህል ፣ አይደግፉም ፣ ለጊዜው ፣ እንደየአስተያየታቸው ፣ ወልድ ፣ ቅብ ፣ መንፈስ ፣ ቅዱስ ፣ ቅብዕ ፣ በመባባል ፣ ቢከራከሩም ፣ ኹለት ፣ ባሕርይ ፣ ባይ ፣ በመጣ ፣ ጊዜ ፣ ኹለቱም ፣ ወገኖች ፣ ይህን ፣ ክርክር ወደ ፣ ጐን ፣ ጥለው ፣ ልዩን ፣ ተኩላ መሳጤ ፣ በማለት ፣ ተባብረው ፣ ኹለት ፣ ባሕርይ ፣ ባዩን ፣ ለመቃወም ታጥቀው ፣ ይነሣሉ ፣ እንጂ ፣ የኹለት ፣ ባሕርይን ፣ ባህል ፣ ልቀበል ፣ ልደግፍ፣ የሚል አይገኝባቸውም ። ይህ ፣ የኹለቱ ፣ ወገኖች ፣ ክርክርም ፣ ኹለት ፣ ወንድማማቾች ፣ ከእናት ፣ ካባታቸው ፣ ቤት ፣ ሲያድጉ ለጊዜው ፣ በምኑም ፣ በምኑም ፣ ቢጋጩ ፣ መልሰው ፣ ወንድሜ ፣ ወንድሜ ፣ ተባብለው ፣ እንደሚሳሳሙት ፣ ጳውሎስንና ፣ በርናባስንም ፣ ተምሁ ፣ ወተፋለጡ ፣ ተጣልተው ፣ ተለያዩ ፣ እንደሚላቸው ፣ ያለ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ከእያት ፣ ከቅድመ ፣ እያት ፣ የወረደ ፣ ጥንተ ፣ ባላጋራ ፣ ምክንያት ፣ አድርጎ ፣ ሊገ

ባበትና ፡ ሊጠቀምበት ፡ የሚችል ፡ የበረታ ፡ ጠብ ፡ አይደለም ። የበረታና ፡ የሚያለያይ ፡ ጠብ ፡ ካለመ ኾኑም ፡ የተነጣ ፡ ኹለቱም ፡ ወገኖች ፡ በእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ሥር ፡ ይኖራሉ ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ አፈንግጠ ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የተጠጋ ፡ የለም ። ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ የተቀበለች ፡ መጀመሪያ ፡ ክርስትናን ፡ ስትቀበል ፡ በፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኖራ ፡ ኖራ ፡ በ፷ኛው ፡ ፻ ፡ ዓ/ም ፡ መጨረሻ ፡ ግድም ፡ አለመኾኑ ፡ በግልጽ ፡ የታወቀ ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ፡ ንግግርዎ ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ ፍጹም ፡ ውሸት ፡ ነው ።

፴፬/ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዩ ፡ ጳጳስ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ወዲያው ፡ ኢትዮጵያ ፡ በመላዋ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ አን ዳለፈች ፡ ማመን ፡ አይገባም ፡ ብለዋል ።

፴፭/ እንዲህ ፡ ማለት ፡ የሚገባ ፡ አንደኛ ፡ ከአባ ፡ ቄርሎስ ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ ጳጳሳት ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ መኾናቸውን ፡ ኹለተኛም ፡ ኢትዮጵያ ፡ አስቀድማ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ተቀብላ ፡ የኖረች ፡ መኾኗን ፡ አስረድቶ ፡ ይህ ፡ ሲታመን ፡ ነበረ ።

በጠቅላላው ፡ መቸም ፡ መች ፡ ቢኾን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ የተቀበለችበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ፡ ብለን ፡ ብናስተባብልዎ ፡ የተቀበለችበትን ፡ ጊዜ ፡ ማማረጥ ፡ ማጭበርበር ፡ ማደናገር ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሊቀበለው ፡ አይችልም ።

፴፮/ ኢትዮጵያ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮችን ፡ መቀበል ፡ የቀጠለች ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በኋላ ፡ በሮማና ፡ በእስክንድርያ ፡ መካከል ፡ የኾነውን ፡ ሳታውቅ ፡ የቅዱስ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ የተገቡ ፡ ወራሾች ፡ የትምህርቱና ፡ የስብከቱ ፡ ቀጣዮች ፡ መስለዋት በልበ ፡ ገርነት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በኬልቄዶን ፡ ላይ ፡ ከግብጽ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ለማመጥ ፡ አይደለም ፡ ብለዋል ።

፴፯/ ቅዱስ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ የአንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያስተማረ ፡ የኬልቄ ዶን ፡ ጉባኤ ፡ የወሰነው ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ከመፈጠሩ ፡ አስቀድሞ ፡ በ፫፻፳፭ ፡ ወይም ፡ ፴ ፡ ዘመን ፡ ነው ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዲዮስቆሮስም ፡ በፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ጊዜ ፡ የነበረ ውን ፡ ትምህርት ፡ በመለወጥ ፡ በኬልቄዶን ፡ የተወሰነውን ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ አልቀበ ልም ፡ ብሎ ፡ የተለየ ፡ በ፬፻፶፩ ፡ ዓ፡ም፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ከሰበከላት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሃ፭ ፡ ወይም ፡ ሃ፮ ፡ ዘመን ፡ ይገኛል ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ በእስክንድርያ ፡ ያሉ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ በኢትዮጵያም ፡ የተላኩ ፡ ጳጳሳት ፡ ካንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ያልወጡ ፡ መኾናቸው ፡ ሲታወቅ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ የኹ ለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ አስተምሮ ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ የተነሡ ፡ ጳጳሳት ፡ ለውጠው ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ባህል ፡ ያስተማሩ ፡ በማስመሰል ፡ የቅዱስ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ የተገቡ ፡ ወራሾች ፡ የትምህርቱና ፡ የስብ ከቱ ፡ ቀጣዮች ፡ መስለዋቸው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መናገር ፡ ያው ፡ የተለመደው ፡ ማስመሰል ፡ ማጭበርበር ፡ ማደናገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ንግግር ፡ አይደለም ፡ ከጉባኤ ፡ ከቄልቄዶን ፡ በፊት ፡ ፍሬ ፡ ምና ጦስ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ማስተማሩ ፡ ይቅርና ፡ በሮማም ፡ ቢኾን ፡ በአንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የሚል ፡ ባህል ፡ ለመኖሩ ፡ መረጃ ፡ አያገኙም ፡ እውነት ፡ ከኾነ ፡ ቀድሞ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ለማስተማሩ ፡ ተከታዮቹ ፡ የርሱን ፡ ባህል ፡ ሠርዘው ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ለመከተላቸው ፡ መረጃ ፡ አያቀርቡምን ? ኢትዮጵያስ ፡ በየጊዜው ፡ የሚ መጡ ፡ የሮም ፡ ካቶሊኮችን ፡ በመጡበት ፡ እኳኋን ፡ እያሳፈረች ፡ የምትመልሳቸው ፡ በሮማና ፡ በእስ ክንድርያ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ መለያየት ፡ ከማወቅ ፡ አልፋ ፡ የተለያዩበትን ፡ ምሥጢሩንም ፡ ዐውቃ ጠንቅቃ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በልበ ፡ ገርነት ፡ አይደለም ።

ኢትዮጵያ ፡ ገርነትን ፡ የዋህነትን ፡ የምትይዘው ፡ የዋህ ፡ ብእሲ ፡ ኵሉ ፡ ዘነገርዎ ፡ የአምን ፡ በተባለው ፡ መንገድ ፡ ሳይኾን ፡ ኩኑ ፡ ጠቢባነ ፡ ከመ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ ወየዋሃነ ፡ ከመ ፡ ርግብ ፡ ባለው መንገድ ፡ እውነቱን ፡ ከሐሰት ፡ ጽድቁን ፡ ከኃጢአት ፡ ለይታ ፡ አውቃ ፡ ነው ። ደግሞም ፡ ምናልባት አማርኛውን ፡ ጠንቅቀው ፡ አላወቁት ፡ እንደኾነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እገሌ ፡ ዐመጠ ፡ ተብሎ ፡ የሚነገር ፡ በገዢና ፡ በተገዢ ፡ መካከል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ትክክለኛነት ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ በልበ ፡ ገርነት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከግብጽ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ ለማመጥ ፡ አይደለም ፡ ያሉትን ፡ እንጋገርዎን ያርሙ ።

፴፰/ ኢትዮጵያውያን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በቅዱስ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ለተሰበከው ፡ ሃማኖት ፡ ተከታዮች ፡ ነን ፡ ብለው ፡ ያምናሉ ፡ ብለው ፡ ባጠራጣሪ ፡ አነጋገር ፡ ተናግረዋል ።

፴፱/ በቅዱስ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ጊዜ ፡ የ፪ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ በፍጹም ፡ አልተሰበከም ፡ ነበረ ስለዚህ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሰበከላት ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ መኾኑ ፡ የማያ ጠራጥር ፡ እውነተኛ

ነገር ፡ ነውና ፡ እርስዎም ፡ ያለጥርጥር ፡ ይመኑት ።

፴፯/ ኋላም ፡ ግብጽ ፡ በመላዋ ፡ ወዳንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ እስከ ፡ ወደቀችበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በመላዋ ፡ ባይኾን ፡ በሚበልጠው ፡ ክፍል ፡ ከካቶሊክ ፡ ጋራ ፡ መገናኘትዋን ፡ በመቀጠል ፡ በእውነተኛው ፡ በካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ጸንታ ፡ የነበረች ፡ ይመስላል ፡ ብለዋል ።

፴፰/ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ በተፈጠረበት ፡ በጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ ጊዜ ፡ የእስክንድርያው ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ይህ ፡ ባህል ፡ የንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ ነው ፡ ጉባኤውም ፡ ጉባኤ ፡ አብዳን ፡ ነው ፡ አልቀበለውም ፡ ብሎ ፡ ነቅፎ ፡ በዚኽው ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ያደረሰ ፡ ታላቅ ፡ ፈተና ፡ የደረሰበት ፡ መኾኑ ፡ ሲታወቅ ፡ ከዚያም ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ግብጽ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ የተቀበለችበት ፡ በሴኮንድ ፡ የሚቆጠር ፡ ጊዜ ፡ አለመኖሩ ፡ ሲታወቅ ፡ ግብጽ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ተቀብላ ፡ ቆይታ ፡ ኋላ ፡ ወዳንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ያለፈች ፡ አስመስሎ ፡ ግብጽ ፡ ወዳንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ እስከ ፡ ወደቀችበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ብሎ ፡ መናገር ፡ ለዚኽውም ፡ መረጃው ፡ ይመስላል ፡ ኾኖ ፡ ሲገኝ ያው ፡ የተለመደው ፡ ማጭበርበር ፡ ማደናገር ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ መልስ ፡ ሊሰጠው ይቻላል ።

ኢትዮጵያ ፡ በ፫፻፴ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ተቀብላው ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ተረድታው ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፈተናዎችን ፡ እየተቀበለች ፡ ከሸህ፮፻ ፡ በላይ ፡ የሚቆጠሩ ፡ ዘመናት ፡ ያሳለፈችበትን ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ የሚል ፡ ሃይማኖቷን ፡ በመጻሕፍት ፡ አስረጅነት ፡ ሳይኾን ፡ በይመስላልና ፡ በይኾናል ፡ ሳይኾን ፡ አይቀርም ፡ አስለቅቃታለሁ ፡ ብለው ፡ ማሰብዎ ፡ ምኞት ፡ የቱን ፡ ያኽል ፡ ቢሠለጥንብዎ ፡ ነው ፡ በእውነቱ ፡ ያሳዝናል ።

፴፱/ በ፱ነኛው ፡ ፱ ፡ ዘመን ፡ ከእስክንድርያ ፡ የሚመጡትን ፡ ጳጳሳት ፡ የመቃወም ፡ መንፈስ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ተገልጦ ይታይ ፡ ነበረ ፡ በአባ ፡ ዮሴፍም ፡ ጊዜ ፡ የተላከላትን ፡ አባ ፡ ዮሐንስን ፡ አልቀበለውም ፡ ብላ ፡ አበራ ፡ ሌላ ፡ መርጣለች ፡ ስለዚሁ ፲ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ካንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ ጳጳስ ፡ ሳይቀበሉ ፡ ተቀመጡ ፡ በ፲ ፪ኛው ፡ ፲ ፡ ዘመን ፡ መጨረሻ ፡ ለእስክንድርያ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ የሚቃወሙ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳትና ፡ ቀሳውስት ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከካቶሊክና ፡ ከሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ጋራ ፡ እንዳትገናኝ ፡ በእስላሞችና ፡ በግብጻውያን ፡ መንገድ ፡ ስለተዘጋባት ፡ ወደ ፡ እረመኔነት ፡ እንዳትወድቅ ፡ ብላ ፡ ከእስክንድርያ ፡ መታረቅና ፡ የምትልካቸውን ጳጳሳት ፡ መቀበል ፡ ሳትወድ ፡ እሺ ፡ ማለት ፡ ግድ ፡ ኾነባት ፡ ስለዚህ ፡ ፊሎቴዎስ ፡ የተባለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ከእስክንድርያ ፡ ጋራ ፡ አስታርቀህ ፡ እኔና ፡ ሕዝቤን ፡ ከግዞት ፡ አስፈታን ፡ የሚመራንም ፡ ጳጳስ ፡ እንዲሰጠን ፡ ለምንልን ፡ አገራችን ፡ ፮ ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ምንም ፡ ሳያስቡላት ፡ ስላለፋና ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሶቻችን ፡ ቀሳውስቶቻችን ፡ ኹሉ ፡ ስለሞቱ ፡ ያለጠባቂ ፡ ተጥላ ፡ ቀርታለች ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፎ ፡ ለሞባው ፡ ንጉሥ ፡ ለጊዮርጊስ ፡ ላከ ። በኖባው ፡ ንጉሥ ፡ አስታራቂነት ፡ ዳንኤል ፡ የሚባለው ፡ ጳጳስ ፡ መጣ ፡ ከዚህም ፡ መታረቅ በኋላ ፡ በኢትዮጵያውያኖችና ፡ ባንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ ጳጳሳት ፡ መካከል ፡ ግጭት ፡ አልታጣም ። በሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ገብርኤል ፡ ዳግማዊ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጳጳሳት ፡ ይሾሙልኝ ፡ ብላ ፡ ጥያቄ ፡ አቅርባ ፡ ነበረ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ መለያየትን ፡ ያስከትላል ፡ በሚል ፡ ምክንያት ፡ ሳትሰማ ፡ ቀረች ፡ ይህም ፡ እስከ ፡ ፲፱ተኛው ፡ ፲ ፡ ዘመን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ይኑስ ፡ ይብዛ ፡ በቅብጥ ፡ ቤተክርስቲያን ፡ ላይ ፡ የመቃወም ፡ መንፈስ ፡ መኖሩን ፡ ያስረዳል ፡ ብለው ፡ በሰፊው ፡ ካተቱ ፡ በኋላ ፡ የዚህ ፡ ምርምር ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተለይታ ፡ የኬልቄዶንን ፡ ጉባኤ ፡ የሚቃወም ፡ ባህል ፡ ይዛ ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ ለመደገፍ ፡ የተሰለፈችበት ፡ ጊዜ ፡ መቼ ፡ እንደኾነ ፡ በእርግጥ ፡ አይታወቅም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ እውነቱን ፡ በሐሰት ፡ ሊለውጡ ሞክረዋል ።

፵/ ኢትዮጵያ ፡ ከጥንት ፡ ጀምራ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ጳጳስ ፡ ይሾምልኝ ፡ ብላ ፡ ስትጠይቅ ፡ የቅብጥ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የራሷን ፡ ጥቅም ፡ ብቻ ፡ በመፈለግ ፡ መከልከሏን ፡ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ግጭት ፡ መነሣቱና ፡ መልሳ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከግብጽ ፡ ዕርቅ ፡ መጠየቋ ፡ የማይካድ ፡ ነገር ፡ ነው ።

ርስዎም ፡ ራስዎ ፡ በአባ ፡ ገብርኤል ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ጳጳስ ፡ ይሾምልኝ ፡ ብላ ፡ ጠይቃ ነበረ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሳትሰማና ፡ መብቷን ፡ ሳታገኝ ፡ ቀረች ፡ ብለው ፡ ጥሉ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ መኾኑን ፡ አስረድተዋል ፡ ይህም ፡ ግብጽ ፡ የሚገባትን ፡ መብቷን ፡ ስትከለክላት ፡ ከሮማ ፡ ወይም ፡ ከሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ልገናኝ ፡ ሳትል ፡ መልሳ ፡ እርቅ ፡ መጠየቋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ ከግብጽ ፡ ያገኘችውን ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ወዳድ ፡ መኾኗን ፡ ለመረዳት ፡ በቂ ፡ ምስክር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ ስላላት ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮችን ጳጳሳት ፡ አልቀበልም ፡ ብላ ፡ ፲ ፡ ዘመን ፡ አሳለፈች ፡ የሚል ፡ መሠረተቢስ ፡ ሐሳብዎን ፡ የሚደግፍ ፡ አይደለም ፡ እውነት ፡ ከኾነ ፡ ፲ ፡ ዘመን ፡ ያለጳጳስ ፡ ብቻዋን ፡ ስትቀመጥ ፡ ከሮም ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ ጳጳስ ፡ አታስመጣም ፡ ኖሯልን ። ይልቁንም ፡ እንደነ ፡ አባ ፡ ማትያስ ፡ ያሉት ፡ የካቶሊክ ፡ ሰባኪዎች ፡ ፭ ፡ ፭ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሊቃውንት ፡ ጸጋ ፡ ቅብዓት ፡ በሚለው ፡ የርስ በርስ ፡ ግጭት ፡ ምክንያት ፡ ብስጭት ፡ ባገኛቸው ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ መግቢያ ፡ አገኘን ፡ መስሏቸው ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ተቀበሉን ፡ ከሮሙ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ተላልከን ፡ የጵጵስና ፡ መዓርግ ፡ እናሰጣችሁ ፡ እያሉ ፡ እንዳባበልዋቸውና ፡ እነርሱም ፡ በሹመት ፡ ተደልለን ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ የምትል ፡ ሃይማኖታችንን ፡ የምን ለውጥ ፡ አይደለንም ፡ እያሉ ፡ እያሳፈሩ ፡ እንደ ፡ መለሰዋቸው ፡ ታሪክ ፡ ይነግረናል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሃይማኖቷ ፡ ክብሯን ፡ የምትወድ ፡ ኾና ፡ ቢኾን ፡ ግብጽ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ጳጳስ ፡ አልሾምም ፡ ባለቻት ጊዜ ፡ ከሮማ ፡ ወይም ፡ ከማንም ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሔዳ ፡ ሹመቱን ፡ ለማ

ምጣት ፡ ሥልጣን ፡ ነበራት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ባህሉን ፡ ጠንቅቃ ፡ የተረዳችው ፡ ዐውቃ ፡ የያዘችው ፡ ስለ ኾነች ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ መሔድን ፡ አልፈቀደችም ፡ ኹሙቱንም ፡ በራሷ ፡ ሥልጣን ፡ መርጣ ፡ እንዳትሾም፤ አልቦ ፡ ዘይነሥእ ፡ ክብረ ፡ ለርእሱ ፡ ዕብ ፡ ፭ ፡ ቍ ፡ ፬ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ የምታውቅ ፡ ስለኾነች ፡ ምንም ፡ ብትበደል ፡ መልሳ ፡ ዕርቅን ፡ ከግብጽ ፡ ብትጠይቅ ፡ ከእስክንድርያ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የምትኾንበትን ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ለውጣ ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ከእስክንድርያ ፡ ልትለይ ፡ የማትፈቅድ ፡ መኾኗን ፡ በግልጽ ፡ ስለሚያስረዳ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተለይታ የኬልቄዶንን ፡ ጉባኤ ፡ የሚቃወም ፡ ባህል ፡ ይዛ ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ ለመደገፍ ፡ የተሰለፈችበት ፡ ጊዜ፡ መቼ ፡ እንደኾነ ፡ በርግጥ ፡ አይታወቅም ፡ ብለው ፡ የጻፉት ፡ ጽሑፍ ፡ ማንም ፡ ሊቀበለው ፡ የማይችል ፍሬቢስ ፡ ትችት ፡ መኾኑን ፡ ይረዱልኝ ።

፴፰/ እኛ ፡ ከምናውቃቸው ፡ ጽሑፎች ፡ ጥንታዊ ፡ የኾነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነውን ፡ ትምህርት ፡ እንደማትቀበለው ፡ የሚያስረዳን ፡ በ፲፬ኛ ፡ ፻ ፡ ዘመን ፡ መጨረሻ ፡ ከዐረብኛ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ የተተረጐመው የስንክሳር ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

፴፱/ በዚህ ፡ እንጋገርዎ ፡ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከእስክንድርያ ፡ የመጡትን ፡ ጳጳሳት ፡ መቀበሏ ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በኋላ ፡ በሮማና ፡ በእስክንድርያ ፡ መካከል ፡ የኾነውን ፡ ሳታውቅ ፡ በልበ ፡ ገርነት፡ ነው ፡ እንጂ፡ከግብጽ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ በማመጥ ፡ አይደለም ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሚበልጠው ፡ ክፍሏ ፡ ከካቶሊክ ፡ ጋራ ፡ መገናኘቷን ፡ በመቀጠል ፡ በእውነተኛው ፡ በካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ ጸንታ ፡ የነበረች ፡ ይመስላል ፡ እያሉ ፡ የተቹት ፡ ትችት ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ ፍሬ ፡ ቢስ መኾኑን ፡ አረጋግጠው ፡ መስክረዋል ።

ስንክሣርም ፡ ጥንታዊ ፡ መጽሐፍ ፡ መኾኑን ፡ አረጋግጠዋል ። በዚህም ፡ ላይ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከጥንት ፡ ጀምራ ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ መስላ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ይዛ ስትገኝ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ምን መረጃ ፡ ይገኛል ፡ ብለው ፡ ነው ፡ ከግብጽ ፡ የተላኩ ፡ ጳጳሳትን ፡ አልቀበልም ፡ ብላ ፡ ነበረ ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ ለመደገፍ ፡ የተሰለፈችበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ፡ እያሉ ፡ ሰውን ፡ ለማሳሳት ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የሚጣጣሩ ፡ ስለምንድን ፡ ነው ፡ ወይኩን ፡ ነገርክሙ ፡ ፩ ፡ እሙኒ ፡ እወ ፡ እወ ፡ ወእሙኒ ፡ አልቦ ፡ አልቦ ፡ ወፈድፋደሰ እምእሉ ፡ እምእኩይ ፡ ውእቱ ፡ ማቴ ፡ ፭ ፡ ፴፯ ፡ እውነቱን ፡ እውነት ፡ ሐሰቱን ፡ ሐሰት ፡ በማለት ፡ ንግግራችሁ፡አንድ ፡ ይኹን ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ አልፎ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እውነት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሐሰት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አዎን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አሌ ፡ ማለትስ ፡ ከሰይጣን ፡ የተገኘ ፡ ነው ። ያለ፡ እግዚአብሔርን ይሀ ፡ አነጋገር ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘው ፡ መሰለዎን ።

፵/ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ በነሐሴ ፡ ፯ ፡ ቀን ፡ ላይ ፡ ለዲዮስቆሮስ ፡ መስተጋድልና ፡ ቅዱስ ፡ የሮሙ ፡ ጳጳስ ፡ ልዮን በግፍ ፡ ያሳደደው ፡ ተብሎ ፡ ተጽፎለታል ፡ በማለት ፡ የሽሙጥ ፡ አነጋገር ፡ ተናግረዋል ።

፵/ በስንክሣርም ፡ ኾነ ፡ በሌሎችም ፡ የታሪክ ፡ መጻሕፍት ፡ ኹሉ ፡ የሮሙ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ልዮን ፡ በአንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ ጠባይዕ ፡ ኹለት ፡ ፈቃድ ፡ ኹለት ፡ ሥምረት ፡ መለኮት ፡ የመለኮትን ፡ ሥራ ፡ ትስብእት ፡ የትስብእትን ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፎ ፡ ቢልክ ፡ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ይህን ፡ ባህል ፡ በመቃወም ፡ ጠማሩን ፡ ቀደደው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ጥርሶቹ ፡ እስኪሰበሩ ፡ ድረስ ፡ በጥፊ ፡ ተመታ ፡ በደሴተ ፡ ጋግራ ፡ ታስሮ ፡ ተግዞ ፡ ሞተ ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ እናገኛለን ፡ ይህንንም ፡ ታሪክ ፡ እርስዎ ፡ ራስዎ ፡ ኢትዮጵያውያን እንዲህ ፡ ይላሉ ፡ ብለው ፡ በማስተባበል ፡ መልክ ፡ ከ፹፩—፹፬ ፡ ገጽ ፡ ባሉት ፡ መሥመሮች ፡ ዘርዝረው ፡ ከጻፉት ፡ በኋላ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ አልፈውታል ፡ እንጂ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ይህ ፡ ግፍ ፡ አልደረሰበትም ፡ በደሴተ ፡ ጋግራ ፡ ታስሮ ፡ አልሞተም ፡ ወይም ይህ ፡ ግፍዕ ፡ የደረሰበት ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ብለው፡ በዚህ ፡ ምትክ ፡ ማፍረሻ ፡ የጻፉት ፡ ታሪክ ፡ የለም ። በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ሳይተኩ ፡ ሊነቅፉት ፡ የቃጡ ፡ በነሐሴ ፡ ፯ ፡ የተጻፈው ፡ ስንክሣር ፡ እርግጠኛ ፡ መኾኑን ፡ ይወቁት ። ይህነንም ፡ አካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ የሚለውን ፡ አነጋገር ፡ አካል ፡ ለመለኮት ፡ እንጂ ፡ ለትስብእት ፡ የለውም ፡ ለትስብእት ፡ ያለው ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በማለቱ ፡ አፍርሶታል ።

፵፩/ በዚሁ ፡ ወር ፡ በ፳፩ ፡ ም ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ያስተማረው ፡ ትምህርት ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስና ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ትምህርት ፡ ኦርቶዶክሳዊ ፡ ማለት ፡ የቀና ፡ ነው ፡ ተብሏል ፡ በማለት ፡ ሹሙጥምን ፡ ቀጥለዋል ።

፵፪/ የዚህን ፡ እርግጠኛ ፡ ነገር ፡ ለማወቅ ፡ ብንፈልግ ፡ አስቀድመን ፡ የዲዮስቆሮስ ፡ ባህል ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ የተወሰነው ፡ የልዮን ፡ ባህል ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ መርምረን በየራሳቸው ፡ ከመደብን ፡ በኋላ ፡ የነሀ ፡ የፎቱ ፡ ሊቃውንት ፡ ባህል ፡ ከማናቸው ፡ ወገን ፡ ተስማሚ ፡

እንደ ፡ ኾነ ፡ ማመዛዘን ፡ አለብን ። የዲዮስቆሮስ ፡ ባህል ፡ መሠረቱ ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ ሥጋ ፡ ቢለብስ ፡ ምንታዌ ፡ የሌለበት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በምንም ፡ በምን ፡ ኹለት ፡ አይባልም ፡ ማለት ፡ ነው ።

በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነው ፡ የልዮን ፡ ባህልም ፡ መሠረቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ቃል ፡ ሰው ፡ ቢኾን ሥጋ ፡ ቢለብስ ፡ አካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ ተዋሐደ ፡ እንጂ ፡ ባሕርይ ፡ ትስብእትን ፡ አልተዋሐደም ፡ ስለ ዚህ ፡ ክርስቶስ ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ ፈቃድ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ የሊ ቃውንቱን ፡ ቃል ፡ እናመዛዝን ።

፩ኛ/ ከኒህ ፡ ከተጠቀሱት ፡ ሊቃውንት ፡ አንዱ ፡ ባስልዮስ ፡ በሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ወኢንሬ ስዮ ፡ ለዝንቱ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ክልኤተ ፡ ወኢንቤ ፡ ከመ ፡ መለኮት ፡ በህላዌሁ ፡ ወትስብእትሂ ፡ በህላዌሁ ፡ አላ ፡ ንብል ፡ ፩ ፡ ህላዌ ፡ ወ፩ ፡ አካል ።

አንድ ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንናገራለን ፡ እንጂ ፡ መለኮት ፡ በባሕርዩ ፡ ለብቻ ፡ ትስብእትም ፡ በባሕርዩ ፡ ለብቻ ፡ እንዳለ ፡ አድርገን ፡ ኹለት ፡ የምንለው አይደለም ።

ወጴጥሮስሂ ፡ ሐዋርያ ፡ ኢዘከረ ፡ ክልኤተ ፡ ህላዌ ፡ ወባሕቱ ፡ አምነ ፡ ወይቤ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ሐመ ፡ በእንቲአነ ፡ በሥጋ ።

ሐዋርያ ፡ ጴጥሮስም ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንደ ኾነ ፡ አምኖ ፡ ክርስቶስ ስለእኛ ፡ በሥጋ ፡ መከራ ፡ ተቀበለ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ እንደ፡ ኾነ አልተና ገረም ፡ ብሏል ።

፪ኛውም ፡ ሊቅ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ እኅው ፡ ባስልዮስ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢፍጡር ፡ ወፍጡር ፡ ኅቡሩ በ፩ ፡ ህላዌ ፡ ወ፩ ፡ አካል ፡ ኅቡረ ። ንብል ፡ በእንቲአሁ ፡ ኢፍጡር ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ እም ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ወእስከ ፡ ለዓለም ፡ ውእቱ ፡ ፈጣሬ ፡ ኵሉ ፡ ዘሀሎ ፡ ወዘሰ ፡ ንቤ ፡ ፍጡር ፡ ውእቱ ፡ በእንተ ፡ ዘተሳተፈ ፡ ሥጋ ፡ ድካምነ ፡ በሥርዓት ፡ ዘገብሮ ፡ በእንቲአነ ።

ፈጣሪ ፡ መለኮትና ፡ ፍጡር ፡ ትስብእት ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ስለኾኑ ፡ ክርስቶስ ፡ ተባለ ። ያለውን ፡ ኹሉ ፡ የፈጠረ ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነበረ ፡ ቀዳማዊ ፡ ስለኾነ ፡ ፈጣሪ ፡ እንለዋለን ።

ስለእኛ ፡ ብሎ ፡ ባደረገው ፡ በተዋሕዶ ፡ ደካማ ፡ ሥጋችንን ፡ ስለተዋሐደ ፡ ፍጡር ፡ እንለዋለን ፡ ብሏል ። በ፩ዱ ፡ ህላዌ ፡ ወአካል ፡ ብሎ ፡ በአካልም ፡ በባሕርይም ፡ አንድ ፡ መኾኑን ፡ እንዳስረዳ ፡ ማስተዋል ፡ ነው ።

በሌላም ፡ አንቀጽ ፡ ኢተሐልዩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘኮነ ፡ ብእሴ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ክፉል እመለኮቱ ፡ አላ ፡ እመኑ ፡ ከመ ፡ ፩ ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ አምላክ ፡ ወውእቱ ፡ ብእሲ ፡ ኅቡረ ።

በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ የኾነ ፡ አምላክና ፡ ሰው ፡ እንደኾነ ፡ እመኑ ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ የኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመለኮቱ ፡ የተለየ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ እንደኾነ ፡ አታስቡ ፡ ብሏል ።

በዚህም ፡ አንቀጽ ፡ አምላክ ፡ ወሰብእ ፡ ለሚለው ፡ ለክርስቶስ ፡ ፩ ፡ የሚባል ፡ አንድነቱን ፡ የሚ ያመለክት ፡ ቅጽል ፡ እንጂ ፡ ኹለትነትን ፡ የሚያመለክት ፡ ክልኤቱ ፡ የሚል ፡ አኀዝ ፡ እንዳልተቀ ጸለለት ፡ ማስተዋል ፡ ነው ።

ከዚህም ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ በሚገኘው ፡ ወሶበ ፡ ርኢክ ፡ ለዝንቱ ፡ ወልድየ ፡ እንዘ ፡ ይፌውስ ፡ ድውያነ ፡ ወያነጽሕ ፡ እለ ፡ ለምጽ ፡ በቃሉ ፡ ወይገብር ፡ አዕይንተ ፡ እምጽቡር ፡ ወያጸግብ ፡ ለ፶፻ ፡ ብእሲ ፡ እም፭ ፡ ኅብስት ፡ ወያኀድፆ ፡ በተግሣጹ ፡ ለቀላየ ፡ ባሕር ፡ ወየሐውር ፡ በእገሪሁ ፡ ዲበ ፡ ልኅት ከመ ፡ ዘየሐውር ፡ ዲበ ፡ ባሕር ፡ ወይኤዝዞሙ ፡ ለአጋንንት ፡ ወይትኤዘዙ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ እግብርት ፡ ኢትሐሊ ፡ ዘንተ ፡ ለመለኮት ፡ ባሕቲቱ ፡ ወኢተሐሊ ፡ ምግባራተ ፡ ልዑላተ ፡ ለ፩ ፡ ወዘይቴሐት ፡ ለካልኡ ፡ አላ ፡ ዝንቱ ፡ ወዝክቱ ፡ ኵሉ ፡ ለ፩ ፡ ባሕቲቱ ፡ ቦቱ ፡ ኵሉ ፡ ዘመለኮት ፡ ወዓዲ ፡ ቦቱ ፡ ኵሉ ፡ ዘትስብእት ፡ ቦቱ ፡ ተአምራት ፡ ወዓዲ ፡ ቦቱ ፡ ሕማማት ።

ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ክርስቶስ ፡ ድውያንን ፡ ሲፈውስ ፤ ለምጽ ፡ ሲያነጻ ፡ ጋኔን ፡ ሲያወጣ ፡ ፭ ፡ እንጀራ አበርክቶ ፡ ለ፭ሺህ ፡ ሰው ፡ ሲያበላ ፡ አጋንንትን ፡ ሲያዝዛቸው ፡ እነርሱም ፡ እንደ ፡ ባሪያ ፡ ሲታ ዘዙለት ፡ ብታይ ፡ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ሥራ ፡ ለመለኮት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ አታስብ ። የመለኮት ሥራ ፡ ተአምራት ፡ ማድረግ ፡ የትስብእት ፡ ሥራ ፡ መከራ ፡ መቀበል ፡ ኹሉም ፡ ለአንድ ፡ ለእርሱ

ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የአምላክነት ፡ ሥራ ፡ ለመለኮት ፡ የሰውነት ፡ ሥራ ፡ ለትስብእት ፡ ነው ፡ ብለህ አታስብ ፡ ብሏል ።

ይህም ፡ አነጋገር ፡ መለኮት ፡ የመለኮትን ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ ትስብእትም ፡ የትስብእትን ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ የሚለውን ፡ አነጋገር ፡ የሚቃወም ፡ መኾኑን ፡ መገንዘብ ፡ ነው ።

## ፪ኛ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ነባቤ ፡ መለኮትም ።

ወኢፈለሰ ፡ ሀላዌ ፡ መለኮቱ ፡ ኀበ ፡ ሀላዌ ፡ ትስብእቱ ፡ ወኢሀላዌ ፡ ትስብእቱ ፡ ኀበ ፡ ሀላዌ ፡ መለኮቱ ፡ አላ ፡ በ፩ ፡ አካል ፡ ወለደቶ ፡ ማርያም ፡ ድንግል ፡ ወበ፩ ፡ ሀላዌ ፡ ሰገዱ ፡ ሎቱ ፡ ሰብእ ፡ ሰገል አኮ ፡ ዘይትበሀል ፡ ተዋሕዶተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ፪ሀላዌ ፡ ወ፪ ፡ አካል ፡ መለኮት ፡ ምስለ ፡ ትስብእት ፡ በከመ ፡ ይቤሉ ፡ ሰብእ ፡ ንሡራን ፡ ወርኩሳን ፡ እለ ፡ ይሬስይዎ ፡ ለመለኮት ፡ ነኪረ ፡ እምልደተ ፡ ሥጋ ።

ድንግል ፡ ማርያም ፡ በአንድ ፡ አካል ፡ ወለደችው ፡ ሰብአ ፡ ሰገልም ፡ ባንድ ፡ ባሕርይ ፡ ሰገዱ ለት ፡ እንጂ ፡ ባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ወደመኾን ፤ ባሕርየ ፡ ትስብእቱ ፡ ባሕርየ ፡ መለ ኮት ፡ ወደመኾን ፡ አልተለወጠም ። መለኮትን ፡ ከልደተ ፡ ሥጋ ፡ ልዩ ፡ የሚያደርጉት ፡ ወራዶችና ፡ ርኩሳን ፡ የኾኑ ፡ ሰዎች ፡ እንደሚናገሩት ፡ መለኮት ፡ ከትስብእት ፡ ጋራ ፡ ፪ ፡ አካል ፡ ፪ ፡ ባሕርይ ፡ የሚባል ፡ አይደለም ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ብሏል ። -

፫ኛ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስም ፡ ወቦ ፡ በኢያእምሮቶሙ ፡ ይሬስይዎ ፡ ለክርስቶስ ፡ ፪ ፡ ሀላዌ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ እስመ ፡ መለኮት ፡ ተፈልጠ ፡ እምትስብእት ፡ ጊዜ ፡ ይርኅብ ፡ ወይጸምዕ ፡ ጊዜ ፡ የሐምም ፡ ወይደክም ፡ ሶበሰ ፡ ሀልው ፡ መለኮቱ ፡ ምስሌሁ ፡ እምገብረ ፡ ኃይላተ ። ወእለ ፡ ይብሉ ፡ ከመዝ ፡ ፍሉ ጣን ፡ እሙንቱ ፡ እምሃይማኖተ ፡ ክርስቲያን ፡ ርትዕት ። ንሕነሰ ፡ ንትአመን ፡ በ፩ ፡ ሀላዌ ፡ እንበለ፣ ፍልጠት ።

በተራበ ፡ በተጠማ ፡ በታመመ ፡ በደከመ ፡ ጊዜ ፡ መለኮት ፡ ከትስብእት ፡ ተለይቷል ። ሲራብ ፡ ሲጠማ ፡ መለኮት ፡ ከትስብእት ፡ ባይለይስ ፡ ኖሮ ፡ ተአምራት ፡ ባደረገ ፡ ነበረ ፡ እያሉ ፡ ባለማወቃ ቸው ፡ ክርስቶስን ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ የሚሉት ፡ አሉ ፡ እንዲህ ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ከቀናችቱ ፡ ከክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ የወጡ ፡ ናቸው ፡ እኛስ ፡ መለኮትንና ፡ ትስብእትን ፡ ሳንለያይ ፡ ፩ ፡ ባሕ ርይ ፡ ብለን ፡ እናምናለን ።

እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክ ፡ ፍጹም ፡ ኢሐማሚ ፡ ወለሊሁ ፡ ብእሲ ፡ ፍጹም ፡ ሐማሚ ፡ ወ፩ ፡ ሀላዌ ፡ ውእቱ ፡ እንበለ ፡ ፍልጠት ።

ክርስቶስ ፡ ሕማም ፡ ሞት ፡ የሌለበት ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ሲኾን ፡ ሕማም ፡ ሞት ፡ ያለበት ፡ ፍጹም ሰው ፡ ቢኾንም ፡ ያለመለየት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ።

ወበእንተዝ ፡ ናበውእ ፡ ልቡናነ ፡ ኀበ ፡ ፩ ፡ ተዋሕዶ ፡ ዘቦቱ ፡ ወልድ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክር ስቶስ ፡ ወንብል ፡ እስመ ፡ ፪ቱ ፡ ሀላዌያት ፡ ኮኑ ፡ እሐደ ።

ስለዚህ ፡ ልቡናችንን ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ወደኾነበት ፡ ተዋሕዶ ፡ መልሰን ፡ ኹለቱ ፡ ባሕርየ ፡ መለኮትና ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት፡አንድ፡ ኾኑ ፡ እንላለን ፡ ብሏል ።

ወደንስጥሮስ ፡ በጸፈውም ፡ መልእክቱ ፡ ኢኮነ ፡ ዝንቱ ፡ ፩ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ክልኤተ ፡ ወለእመኒ ፡ ይትዐወቅ ፡ እምኔቱ ፡ በኢቱሳሔ ፡ አብእ ፡ ተዋሕዶተ ፡ ሀላዌ ፡ እንበለ ፡ ፍልጠት ፡ በአም ጣነ ፡ ይትዐወቅ ፡ ሰብእ ፡ በከመ ፡ ውእቱ ፡ እምነ ፡ ሥጋ ፡ ወነፍስ ፡ ወአኮ ፡ ውእቱ ፡፡ አላ ፡ ፩ ፡ እም፪ ፡

ሰው ፡ ከነፍስና ፡ ከሥጋ ፡ ተገኝቶ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ ሰው ፡ እንዳይባል ፡ ክርስቶስም ፡ ከኹለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ከኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አይ ባልም ።

ነአምን ፡ በኵሉ ፡ ዘተብህለ ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘኮነ ፡ ሰብአ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ፩ ፡ አካል ፡ ወ፩ ፡ ሀላዌ ።

ሰው ፡ ስለኾነው ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በተናገረው ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕ ርይ ፡ እንደኾነ ፡ እናምናለን ።

ወዝንቱ ፡ ኅሱም ፡ ወዓመፃ ፡ ዓቢይ ፡ ከመ ፡ ይትበሀል ፡ ፪ቱ ፡ ሀላዌያት ፡ ለ፩ ፡ ክርስቶስ፡ ወአበዊነ ፡ ቅዱሳን ፡ ኢመሀሩነ ፡ ንእመን ፡ በክርስቶስ ፡ ዋሕድ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ፪ቱ ፡ ሀላዌ ፡ ወባሕቱ ፡ ለሊከሙ ፡ ትፈልጥዎ ፡ እንዘ ፡ ትብሉ ፡ ከመ ፡ እሙንቱ ፡ ይቤሉ ፡ እስመ ፡ ለክርስቶስ፡ ቦቱ ፡ ፪ ፡ ሀላዌያት ፡ እምቅድመ ፡ ይትዋሐድ ፡ ወእምድኅረ ፡ ተዋሕዶ ፡ ገብሩ ፡ ተዋሕዶተ ፡ ወእሙንቱሰ ፡ መሀሩነ ፡ በሆሉ ፡ ጊዜ ፡ ወአጠየቁ ፡ ከመ ፡ ፩ ፡ ሀላዌ ፡ ውእቱ ።

አንድ ፡ ክርስቶስን ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ እጅግ ፡ የከፋ ፡ ታላቅ ፡ በደል ፡ ነው ፡ ቅዱሳን ፡ አባቶቻችንም ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ እንደኾነ ፡ እንድናምን ፡ አላስተማሩንም ። እናንተ ፡ ለክርስቶስ ፡ ከተዋሕዶ ፡ በፊት ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ከተዋሕዶም ፡ በኋላ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ እንደሚሉ ፡ አድርጋችሁ ፡ እንዲህ ፡ ይላሉ ፡ እያላችሁ ፡ ትለያዩታላችሁ ፡ እንጂ ፡ እነርሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኹልጊዜ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስረዱ ።

ወለእመኒ ፡ ንቤ ፡ እስመ ፡ ፪ቱ ፡ ሀላዌያት ፡ ኀብሩ ፡ በከዊነ ፡ ፩ ፡ ሀላዌ ፡ እምድኅረ ፡ ተዋሕዶሰ ፡ ኢንፈልጦሙ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወኢንከፍሎ ፡ ለዋሕድ ፡ ዘኢይትከፈል ፡ ከመ ። ንሬስዮ ፡ ክልኤተ ፡ አላ ፡ ንብል ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ፩ ወልድ ፡ ዋሕድ ።

ባሕርየ ፡ መለኮትና ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ኹለቱ ፡ በክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ኾኑ ፡ ተዋሐዱ ፡ ብንልም ፡ ማለት ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ የኾኑ ፡ ኹለቱ ፡ ባሕርያት ፡ ከተዋሕዶ ፡ በፊት ፡ ኹለት ፡ ነበሩ ፡ ብንልም ፡ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ አንለያያቸውም ።

እርሱ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ወልድ ፡ እንደኾነ ፡ እንናገራለን ፡ እንጂ ፡ የማይከፈል ፡ አንድ ፡ ክርስቶስን ፡ ኹለት ፡ እናደርገው ፡ ዘንድ ፡ የምንከፍለው ፡ አይደለንም ። እስመ ፡ ንሕነ ፡ ፍጡራን ፡ እምነፍስ ወሥጋ ፡ ወኢንሬኢ ፡ ክልኤተ ፡ ሀላዌያተ ፡ ፩ ፡ ዘሥጋ ፡ ወ፩ ፡ ዘነፍስ ፡ አላ ፡ ፩ ፡ ውእቱ ፡ ብእሲ ፡ በተዋሕዶ ፡ እምክልኤቱ ፡ ወኢይትበሀል ፡ ፪ቱ ፡ እደው ፡ በከዊኖቱ ፡ እም፪ቱ ፡ ሀላዌያት ፡ አላ ፡ ፩ ፡ ብእሲ ፡ ውእቱ ፡ዘኮነ ፡ እምነፍስ ፡ ወሥጋ ።

እኛ ፡ ከነፍስ ፡ ከሥጋ ፡ የተፈጠርን ፡ ነን ፡ ሰው ፡ ከኹለቱ ፡ ባሕርያት ፡ የተዋሐደ ፡ አንድ ፡ ነው፡ እንጂ ፡ ከኹለቱ ፡ ባሕርያት ፡ ስለተገኘ ፡ አንዱ ፡ የነፍስ ፡ አንዱ ፡ የሥጋ ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ ኾነው ፡ አናይም ፡ ከነሀ ፡ ከኹለቱ ፡ ባሕርያት ፡ የተገኘ ፡ ሰውም ፡ ከነፍስ ፡ ከሥጋ ፡ የተገኘ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ከኹለቱ ፡ ባሕርያት ፡ በመገኘቱ ፡ ኹለት ፡ ሰው ፡ አይባልም ።

ወእመ ፡ ንሬኢ ፡ ዘንተ ፡ ነአምር ፡ ከመ ፡ እግዚእነ ፡ ክርስቶስ ፡ ፩ ውእቱ ፡ ዘኮነ ፡ እም፪ቱ ፡ ሀላዌያት ፡ እለ ፡ ኢየኀብሩ ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወእምድኅረ ፡ ተዋሕዶሰ ፡ ኢይትፈለጡ ።

ሰው ፡ ከነፍስና ፡ ከሥጋ ፡ ከኹለቱ ፡ ተፈጥሮ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዲባል ፡ ካወቅን ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ከማይገናኙ ፡ ከተዋሕዶም ፡ በኋላ ፡ ከማይለያዩ ፡ ባሕርየ ፡ መለኮትና ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእትን ፡ የተዋሐደ ፡ ክርስቶስም ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እናውቃለን ፡ እናምናለን ፡ ብሏል ።

የነሀ ፡ የተጠቀሱት ፡ ሊቃውንት ፡ ባህል ፡ እንደ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ባህል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ፈቃድ ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በተጠቀሱት ፡ ጥቅሶች ፡ በሰፊው ፡ ተረድተናል ። ከዚህ አልፈው ፡ እንደ ፡ ኬልቄዶን ፡ ውሳኔ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ በ፪ኤ ፡ ባሕርያት ፡ ሲሉ፡ አይገኙም ፡ እንግዲህ ፡ እንዲህ ፡ ከኾነ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ትምህርት ያስተማረው ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ባስልዮስ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ነው ፡ ቢባል ፡ ምን ፡ ቅር ፡ የሚያሰኝ ፡ ነገር ፡ ተገኝቶበት ፡ ያሽሚጥጣሉ ።

፺፩/ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ ያስተማረውና ፡ የዲዮስቆሮስ ፡ ባህል ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ሲባል ፡ የቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ትምህርት ና ፡ የኬልቄዶኑ ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ እንደሚቃረኑ ፡ በማስመሰል ፡ ተጽፏል ። ብሰዋል ።

፺፪/ ቄርሎስና ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ስለክርስቶስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ያስተማሩት፡ አንድ፡ መኾኑን፡ በላይኛው፡ መሥመር ፡ ከቄርሎስ ፡ መጽሐፍ ፡ እየጠቀስኩ ፡ አስረድቻለሁ ፡ እርስዎ ፡ የሚናገሩት ፡ እውነት ፡ ከኾነ ፡ እንደሚቃረኑ ፡ በማስመሰል ፡ ተጽፏል፡ብሎ ፡ ከማለፍ ፡ ከቄርሎስ ፡ መጽሐፍ ፡ በ፩ ፡ አካል ፡ ፪ ፡ ባሕርይ ፡ የሚል ፡ ንባብ ፡ ጠቅሰው ፡ የቄርሎስ ፡ ትምህርት ፡ ከኬልቄዶን ፡ ውሳኔ ፡ ጋራ ፡ ተስማሚ ፡ መኾኑን ፡ አያስረዱ ፡ ነበርን ፡ ማስመሰል ፡ የሚባል ፡ እንዲህ ፡ እንደርስዎ ፡ ለነገሩ ፡ ማስረጃ ፡ ሳይሰጡ ፡ ሳይኾን ፡ አይቀርም ፡ ይኾን ፡ ይኾናል ፡ እያሉ ፡ መላ ፡ እየጣሉ ፡ መናገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለነገሩ፡መረጃ ሰጥቶ ፡ መናገር ፡ ማስመሰል ፡ አይባልም ።

፺፫/ ነገር ፡ ግን ፡ ይሀን ፡ የመሰለ ፡ አስተያየት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ውስጥ ፡ ወዲያውኑ ፡ ተዘርግቶ ፡ ሥር ፡ ሰዶ የታመነ ፡ አይመስልም ፡ ስለኢትዮጵያ ፡ ክርስቲያኖች ፡ መጀመሪያ ፡ የተገኙ ፡ ወሬዎች ፡ የኾኑትን ፡ የጺጋ ፡ ዘአብና ፡ የንጉሥ ፡

ገላውዴዎስ ፡ ደንበኞች ፡ ምስክሮች ፡ ለኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ተቃራኒ ፡ ከኾነው ፡ ከስንክሣር ፡ አስተያየት ፡ በጣም ፡ የተራራቁና ፈጽመው ፡ የተለያዩ ፡ ናቸው ፡ ብለዋል ።

፺፫/ ስንክሣር ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በደንብ ፡ የተቀበለችው ፡ መጽሐፍ ፡ መኾኑ የማይካድ ፡ ነው ። ለስንክሣር ፡ ተቃራኒ ፡ አድርገው ፡ የጠቀሷቸው ፡ ወሬዎች ፡ ግን ፡ ፩ኛ ፡ የጸጋ ፡ ዘአብን ፡ ወሬ ፡ አሁን ፡ እርስዎ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍዎ ፡ ውስጥ ፡ ሲያውሩት ፡ ከመስማት ፡ በቀር ፡ በፍጹም፡ አታውቀውም ፡ ስለርሱም ፡ የሚሰጠው ፡ መልስ ፡ ርሱ ፡ በተጠቀሰበት ፡ አንቀጽ ፡ በሰፊው ፡ የተጻፈ፡ ስለኾነ ፡ አሁን ፡ ኹለተኛ ፡ መድገም ፡ አላስፈለገም ፡ ገጽ ፡ ፶፬ ።

ስለንጉሥ ፡ ገላዎዴዎስም ፡ የታሪክ ፡ መጽሐፋቸው ፡ እንደሚነግረን ፡ በግራኝ ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ተልኮ ፡ ፖርቱጊዞችን ፡ ለርዳታ ፡ ያመጣቸው ፡ ቤርሙዲዝ ፡ የተባለው ፡ ካቶሊክ ፡ ግራኝ ፡ ገና ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ገሚሱ ፡ ለፖርቱጊዝ ፡ መንግሥት ፡ ይሰጥ ፡ አቡንም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ከእስክንድርያ ፡ መምጣቱ ፡ ቀርቶ ፡ ከሮማ ፡ ይምጣ ፡ እኔም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መጀመሪያ፡ አቡን ፡ ልኾን ፡ ብሎ ቢጠይቃቸው ፡ ወዳጅ ፡ ለወዳጁ ፡ እንደሚረዳ ፡ ክርስቲያኑ ፡ የፖርቱጊዝ ፡ መንግሥት፡ለክርስቲያኗ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ርዳታ ፡ ባደረገበት ፡ ምክንያት ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ሃይማኖትን ወደ ፡ ካቶሊክነት ፡ ሊለውጥ ፡ አይችልም ፡ ብለው ፡ የመጨረሻ ፡ ቃላቸውን ፡ ሰጥተውታል ፡ ከሊቃውንቱም ፡ ዝክሪና ፡ ጳውሊ ፡ የተባሉ ፡ የጎጃም ፡ ሊቃውንት ፡ ስለተዋሕዶ ፡ ሃይማኖትና ፡ ወደ ፡ ካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መደባለቅ ፡ አይቻልም ፡ ብለው ፡ አጥብቀው ፡ እንደተቃወሙት ፡ ይነግረናል ፡ እንጂ ፡ የካቶሊክን ፡ ባህል ፡ ለመቀበል ፡ ከስንክሣር ፡ አስተያየት ፡ የራቀ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አይነግረንም ፡ የዝክሪና ፡ የጳውሊንም ፡ ታሪክ ፡ በመቅድሙ ፡ ላይ ፡ በሰፊው ፡ ገልጸነዋል ።

ስለዚህ ፡ የጸጋ ፡ ዘአብንና ፡ የንጉሥ ፡ ገላውዴዎስን ፡ ወሬ ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ወዲያውኑ፡ ተዘርግቶ ፡ ሥር ፡ ሰዶ ፡ የታመነ ፡ አይመስልም ፡ ብለው ፡ የተኹት ፡ ትችት ፡ ከእውነት ፡ የራቀ ፡ ፍሬቢስ ፡ አስተያየት ፡ ነው ።

፺፬/ እስከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያሁኑ ፡ አስተያየት ፡ ተፈጥሮ ፡ አልነበረም ፡ የኢትዮጵያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ ዛሬ ፡ በእውነት ፡ ተለይታ ፡ እንደምትገኘው ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እርቃ ፡ ትገኝ ፡ አልነበረችም ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

፺፭/ ኢትዮጵያ ፡ ከመሠረቷ ፡ ጀምራ ፡ ፩ ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ጸንታ ፡ የዲዮስቆሮስን ፡ ባህል ተቀባይ ፡ ለመኾኗና ፡ የልዮንን ፡ ባህል ፡ የማትቀበል ፡ ለመኾኗ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ጸንታ ፡ ከመገኘቷም ፡ በላይ ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ እንደነባስልዮስ ፡ እንደነጎርጎርዮስ ፡ እንደነቄርሎስ ፡ ንጹሕ ፡ ክቡር ፡ ብፁዕ ፡ ቅዱስ ፡ እያለች ፡ ስትጽፍለት ፡ ስለ ፡ ልዮን ፡ ተከፋ ፡ መሣጢ ፡ የሚለውን ፡ ንባብ ፡ በመቀበሏና ፡ ከንስጥሮስ ፡ ጋራ ፡ ልዮንን ፡ እያጫፈረች ፡ የምትደርሳቸው ፡ ቅኔዎች ፡ በቂ ፡ መረጃ ፡ ለመኾን ፡ ይችላሉ ።

እንዲህ ፡ ጎልቶ ፡ የታወቀውን ፡ ነገር ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ርቃ ፡ ትገኝ ፡ አልነበረችም ፡ የሚያሰኝ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ የሰውን ፡ ልቡና ፡ እለውጠዋለሁ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ይቀበለኛል ፡ ብሎ ፡ ማሰብ ፡ እንዱን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወይም ፡ ዘሬን ፡ ትውልድኽ ፡ ተወልጄ ፡ ያደግሁበትን፡ ሀገርና ፡ ዛሬም ፡ ያለሁበትን ፡ ሀገር ፡ እጣርቼ ፡ የማውቀውን ፡ ዘርህ ፡ ትውልድህ ፡ ኢጣልያ ፡ ነው ፡ ተወልደህም ፡ ያደግህ ፡ ሮማ ፡ ነው ፡ ዛሬም ፡ ያለህ ፡ ሮማ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አዎን ፡ ብሎ ፡ ይቀበለኛል ብሎ ፡ እንደ ፡ ማሰብ ፡ የሚቈጠር ፡ ነገር ፡ ነው ።

፺፮/ እንደኛ ፡ አሳብ ፡ ይህን ፡ አለመስማማት ፡ የፈጠረ ፡ የካቶሊክ ፡ ሰባኪዎች ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያልተለመደውን ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ አነጋገር ፡ ለሳገቡና ፡ በማያምር ፡ አደራረግ ፡ የማያስፈልገውን ፡ ሥርዓተ ፡ አምልኮ ፡ ለማግባት ፡ ሞከሩ ። ኢትዮጵያውያኖችን ፡ ብዙ ፡ አበሳጨዋቸው ፡ ይህን ፡ የመጣላት ፡ መንፈስ ፡ ለማንሣት ፡ ምክንያት ፡ ኾነባቸው ፡ ከዚህም ፡ በላይ ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትና ፡ እስላሞች ፡ በሚጥሏቸው ፡ አደጋዎች ፡ ምክንያት ፡ እንዲሁም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ መጥተው ፡ ነፃነታችንን ፡ ይነጥቁብናል ፡ ብለው ፡ ከመፍራት ፡ የተነሣ ፡ ይልቁንም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ በኩል ፡ በጣም ፡ የቀዘቀዘ ፡ ኾኖ ፡ ከመገኘቱ ፡ የተነሣ ፡ ይህ ፡ አሳዛኝ ፡ መለያየትና ፡ መራራቅ ፡ እያደር ፡ እንዲብስና ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ ኾነ ፡ ብለዋል ።

፺፯/ ሀ/ የማያስፈልገውን ፡ ሥርዓተ ፡ አምልኮ ፡ ለማግባት፡ ሞከሩ ፡ ስለሚሉት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የኹለት ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ተቀብለው ፡ በሌላው ፡ ሥርዓተ ፡ አምልኮ ፡ የተበሳጩ ፡ አስመስለው ፡ ተናግረዋል ፡ እርስዎ ፡ እንደሚሉት ፡ በሥርዓተ ፡ አምልኮ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ በጠቅላላው ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ከሚለው ፡ ውሳኔ ፡ ጀምሮ ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የወሰነውን ፡ ሁሉ ፡ የማይቀበሉ ፡ መኾናቸው ፡ የተረጋገጠ ፡ ነገር ፡ ነው ።

(ለ) የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትና ፡ እስላሞች ፡ በሚጥሉት ፡ አደጋ ፡ ነው ፡ ያሉት ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ኢትዮጵያውያንና ፡ ካቶሊካውያን ፡ በሃይማኖት ፡ ስምምነት ፡ እግኝተው ፡ የመገናኘት ፡ ፈቃድ ፡ ኖሯቸው ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትና ፡ እስላሞች ፡ የከለከሉበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ፡ እን ከልክልም ፡ ቢሉ ፡ የሚከለክሉበት ፡ ሥልጣን ፡ የላቸውም ፡ ምክንያቱም ፡ ኢትዮጵያም ፡ ሮማም ፡ ራሳቸውን ፡ የቻሉ ፡ ማንም ፡ የማያዝዛቸው ፡ ነፃ ፡ መንግሥቶች ፡ ስለኾኑ ፡ ነው ፡

ሐ/ ነፃነታችንን ፡ ይነጥቁብናል ፡ ብለው ፡ ነው ፡ ስለሚሉት ፡ ከጥንት ፡ ጀምራ ፡ ሮማ ፡ ሰባኪያ ኗን ፡ እየላከች ፡ ኢትዮጵያን ፡ የምትጕበኝት ፡ ነፃነቷን ፡ ለመንጠቅ ፡ ለምታደርገው ፡ ዝግጅት ፡ የሚላኩት ፡ ሰላዮች ፡ ያለችግር ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሊመግባት ፡ ለመውጣት ፡ እንዲመቻቸው ፡ የታቀደ ፡ ዘዴ ፡ መኾኑ ፡ ግልጥ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ በ፲፰፻፷፰ ፡ ዓ ፡ ምና ፡ በ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ፡ም በሥራ ፡ ተገልጧል ። ሮማውያን ፡ ለሃይማኖት ፡ ቅናት ፡ አድሮባቸውስ ፡ ቢኾን ፡ አስቀድመው ፡ ባጠ ገባቸው ፡ ከሃይማኖተ ፡ ወንጌል ፡ በእፍኅየሚገኙትን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ አምልኮ ፡ ጸንተው ፡ ያሉትን ፡ ወገኖች ፡ ለማስተማር ፡ በተጉ ፡ ነበረ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ የሀገር ፡ ነፃነት ፡ አስፈላጊ ፡ እንደመኾኑ ፡ የሃይማኖት ፡ ነፃነትም ፡ አስፈላጊ ፡ መኾኑን ፡ ስለምታውቅ ፡ የመንግሥቷን ፡ ነፃነት ፡ ሊያጠፉ ፡ የሚ መጣውን ፡ ጠላት ፡ በአርበኞቿ ፡ ቀስት ፡ ግንባር ፡ ግንባሩን ፡ ብላ ፡ እንደምትመልሰው ፡ የሃይማኖ ቷንም ፡ ነፃነት ፡ የሚያጠፉ ፡ መናፍቅ ፡ ሲመጣ ፡ ከሊቃውንቶቿ ፡ አንደበት ፡ በሚወረወር ፡ ልብን ፡ እንደ ፡ ፍላጻ ፡ በሚሰነጥቅ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ትመለስዋለች ፡ እንጂ ፡ ነፃነቴን ፡ እነጠቃለሁ ፡ ብላ ፡ አትሰጋም ።

መ/ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ የቀዘቀዘች ፡ ስለኾነ ፡ ነው ፡ ስለሚሉት ፡ በየጊዜው ፡ የመጡ ፡ ካቶሊካውያንን ፡ በመጡበት ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ግንባር ፡ ግንባራቸውን ፡ እያለች ፡ ስትመልሳቸው ፡ የኖረች ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ብትቀዘቅዝ ፡ ነውን ። ይህ ፡ ያልታረመ ፡ ንግግር ፡ ነው ። ከልደተ ፡ ክርስቶስ ፡ አስቀድሟ ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ ተመራምራ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይዛ ፡ የተገኘች ፡ ኢትዮጵያን ፡ በንቅዱስ ፡ ጴጥሮስና ፡ በንቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በሌሎችም ፡ ሰማዕታተ ፡ ክርስቶስ ፡ ደም ፡ ስትታጠብ ፡ የነበረች ፡ ሮማን ፡ ለማጕልመስ ፡ ብለው ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ የቀዘቀዘች ፡ ነበረች ፡ ቢሏት ፡ የርስዎን ፡ ግብዝነት ፡ ያስገም ታሉ ፡ እንጂ ፡ ይህነን ፡ ዕውነት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሚቀበል ፡ አይገኝም ።

፶፯/ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሮማ ፡ በደንብ ፡ የተለየችበት ፡ ዘመን ፡ ምንም ፡ አይገኝም ፡ እያሉ ፡ እየመሳሰሉ ፡ ይናገራሉ ።

፶፰/ እኔም ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ መላልሼ ፡ እንዳስረዳኹዎ ፡ ከኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ጋራ ፡ የተ ገናኘችበት ፡ ጊዜ ፡ ሳይኖር ፡ የተለየችበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ፡ እያሉ ፡ መወትወት ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ የማይ ሰጠው ፡ መሠረተ ፡ ቢስ ፡ ንግግር ፡ ነው ።

፶፱/ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሮማ ፡ ርቃ ፡ መገኘቷ ፡ ከእምቢተኝነት ፡ ወይም ፡ ከባህልና ፡ ከትምህርት ፡ ልዩነት ፡ የተነሣ ፡ ከመኾኑ ፡ ይልቅ ፡ የጥንቱን ፡ ሃይማኖት ፡ ይዞ ፡ በመመራመር ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ካለመግፋት ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

፷/ ሀ/ ለመጻሕፍት ፡ ቃል ፡ አልታዘዘም ፡ ያለው ፡ እንቢተኛ ፡ መጻሕፍት ፡ በአኃዝ ፡ ወሰ ነው ፡ ፩ ፡ አካል ፡ ወ፩ ፡ ህላዌ ፡ ያሉትን ፡ ወሰን ፡ አልፎ ፡ ፩ ፡ አካል ፡ በ፪ ፡ ባሕርያት ፡ የሚል ፡ ነው ። መጻሕፍት ፡ በደነገጉት ፡ አበው ፡ በወሰኑት ፡ ጸንቶ ፡ የተገኘ ፡ እንቢተኛ ፡ አይባልም ።

ለ/ ከባህልና ፡ ከትምህርት ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ ስለሚሉት ፡ ትምህርቱ ፡ በመሠረቱ ፡ አንድ ፡ ቢኾን ፡ እንዲህ ፡ ማለት ፡ ይኾናል ፡ እንዲህ ፡ ማለት ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ፡ እንዲህ ፡ ያሰኛል ፡ የሚል ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ፈጠራ ፡ ብያኔ ፡ ስለተጨመረበት ፡ ትምህርቱና ፡ ባህሉ ፡ እየተለያየ ፡ መሔዱ ፡ እርግጠኛ ፡ ነገር ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ይኾናል ፤ ያሰኛል ፤ ይመስላል ፡ የሚለውን፡ ፈጠራ ፡ ብያኔ ፡ ያመጣች ፡ ሮማ ፡ ነች ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወይም ፡ እስክንድርያ ፡ አይደለችም ።

ሐ/ ለመመራመር ፡ ወደፊት ፡ [illegible] ፡ ነው ። ስለሚሉትም ፡ መጻሕፍት ፡ ከተናገሩት ፡ መም ህራን ፡ ካስተማሩት ፡ አልፎ ፡ [illegible] ፡ ይመስላል ፡ ይኾናል ፡ ሳይኾን፡ አይቀርም ፡ ብሎ ፡ ከመጻሕፍት ፡ ቃል ፡ መውጣት ፡ [illegible] ፡ ስለኾነ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ከዚህም ፡ ቀደም ፡ አላደረገችውም ፡ ወደፊትም ፡ አታደርገውም ።

፷፩/ ይህም ፡ ማለት ፡ በክርስትናዋ ፡ አዲስ ፡ የነበረችው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክር ስቲያናት ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በፊት ፡ በድፍን ፡ ይታመን ፡ የነበረውን ፡ መምህራንና ፡ ሊቃውንት ፡ በተራቀቀ ፡ መርምረውት ፡ በኋላ ፡ አነጋገር ፡ ያልተወሰነውን ፡ የሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ይዛ ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ እንደቆመች ፡ ቀረች ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ዛሬም ፡ ቢኾን ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነውን ፡ ትምህርት ፡ ከጉባኤው ፡ በፊት ፡ ከዛሬው ፡ ልዩ ፡ በኾነና ፡ ባረጀው ፡ አነጋገር ፡ ይታመንበት ፡ እንደነበረው ፡ ታምናለች ፡ እንጂ ፡ አነጋገሯን ፡ በተራቀቀ ፡ አኳኋን ፡ ከቀድሞው ፡ ዘመን ፡ ምንም ፡ አልለወጠችም ፡ ብለዋል ።

፵፰/ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ባለፉት ፡ መሥመሮች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በፊት ፡ ይታመን ፡ የነበረውን ፡ ሃይማኖት ና ፡ ባህል ፡ ትታ ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነውን ፡ የኹለት ባሕርይን ፡ ባህል ፡ የተቀበለች ፡ በማስመሰል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሮማ ፡ የተለየችው መቼ ፡ ነው ፡ እስከ ፡ ፳ኛው ፡ ፻ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ፡ አብራ ፡ የቆየች ፡ ይመስላል ፡ እያሉ ፡ በመመላለስ ፡ ሲናገሩ ፡ ነበረ ። እኔም ፡ መጀመሪያ ፡ የኬልቄዶንን ፡ ውሳኔ ፡ የተቀበለችበት ፡ ጊዜ ፡ ሳይኖር ፡ መቼ ፡ ተለየች ፡ ብሎ ፡ መጠየቅ ፡ ማጭበርበርና ፡ ማደናገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ጥያቄ ፡ አይደለም ፡ እያልኩ ፡ መላልሼ ፡ መልስ ፡ ስጥቸዎ ፡ ነበረ ። አሁን ፡ ግን፡ የማታ ፡ ማታ ፡ እውነት ፡ ይረታ ፡ እንደሚባለው ፡ ኹሉ ፡ ሐሰትም ፡ ቢኾን ፡ ቃሌን ፡ አልለውጥም ፡ ብለው ፡ ሳይገደረደሩ ፡ እመሰኬ ዝኩ ፡ ዘነሥትኩ ፡ ኪያሁ ፡ ክመ ፡ አሐንጽ ፡ ዐላዌ ፡ ረሰይኩ ፡ ርእስየ ፡ ገላ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ።

ያንን ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ የነቀፍኩትን ፡ መልሼ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ ሳመሰግን ፡ ብገኝ ፡ ራሴን ፡ ሐሰተኛ ፡ ማድረጌ ፡ ነው ፡ ሳይሉ ፡ እውነተኛው ፡ ነገር ፡ በግድ ፡ አስገድዶዎ፡ኢትዮጵያ፡ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በፊት ፡ ይታመን ፡ የነበረውን ፡ የሃይማኖተ ፡ ትምህርት ፡ ይዛ ፡ ቀረች ፡ ብለው ፡ እውነቱን ፡ ስለመሰከሩ ፡ አመሰግንዎታለሁ ።

እውነት ፡ ነው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሃይማኖቷን ፡ አላሻሻለችም ። ያላሻሻለችበትም ፡ ምክንያት ፡ ቅዱስ ጳውሎስ ፡ አነክረክሙ ፡ እፎ ፡ ከመዝ ፡ ፍጡነ ፡ ትፈልሱ ፡ እምሃይማኖተ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘጸውዐክሙ ፡ በጸጋሁ ፡ ውስተ ፡ ካልእ ፡ ትምህርት ፡ ዘኢኮነ ፡ ሀልወ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘየሐውኩክሙ ፡ ወይፈቅዱ ፡ ይዕልዉ ፡ ትምህርቶ ፡ ለክርስቶስ ፡ አንትሙሰ ፡ ዐሠረ ፡ ዚአነ ፡ ትልዉ ፡ አንትሙሰ ፡ መልአክ ፡ እምሰማይ ፡ ለእመ ፡ መሀረክሙ ፡ ካልአ ፡ እምዘመሀርናክሙ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ፡ ገላ ፡ ፩ ፡ ፯-፲ ።

በቸርነቱ ፡ የጠራችሁ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ካስተማራት ፡ ሃይማኖት ፡ ወጥታችሁ ፡ የክርስቶስን ፡ ትምህርት ፡ ሊለውጡ ፡ ወደው ፡ ልዩ ልዩ ፡ እንግዳ ፡ ባህል ፡ እያመጡ ፡ የሚያውኳችሁ ፡ ሰዎች፡ ፈጥረውታል ፡ እንጂ ፡ ከመጻሕፍት ፡ ወዳልተገኘ ፡ ቀዋሚ ፡ ወዳይደለ ፡ ሃይማኖትና ፡ ባህል ፡ እንዴት፡ ተጨልጣችሁ ፡ ትሔዳላችሁ ፡ ብዬ ፡ አደንቅባችኋለሁ ፡ እናንተስ ፡ እኛ ፡ ያስተማርነውን ፡ ትምህርት፡ ያዙ ፡ እኛን ፡ ምሰሉ ፡ እኛ ፡ ካስተማርናችሁ ፡ ትምህርት ፡ ወጥቶ ፡ ሌላ ፡ ትምህርት ፡ ያስተማራችሁ ቢኖር ፡ መልአክ ፡ እንኳን ፡ ቢኾን ፡ ልዩ ፡ ይኹን ፡ ይለይ ፡ ብሎ ፡ አስጠንቅቋል ። በዚሁ ፡ መሠረት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያስተማረው ፡ ትምህርት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ቢመረመር ፡ አንሰ ፡ እብለክሙ ፡ አነ ፡ ውእቱ ።

እኔ ፡ እንዲህ ፡ እላችኋለሁ ። እኔ ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡ ራሱን ፡ ባንድ ፡ ጾታ ፡ እየጠራ ፡ አንድነቱን ፡ ከመግለጥ ፡ በቀር ፡ በምንም ፡ አይነት ፡ ምንታዌ ፡ ያለበት ፡ መኾኑን ፡ ያሳየበት ፡ አንቀጽ ፡ አይገኝም።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ እንደዚሁ ፡ ፩ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እያለ ፡ ፩ ፡ የሚባል ፡ አኀዝ ፡ ብቻ ፡ ይቀጽልለታል ፡ እንጂ ፡ በማናቸውም ፡ አኳኋን ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፪ቱ ፡ የሚል ፡ አኀዝ ፡ የቀጸለለት ፡ ጽሑፍ ፡ አይገኝም ።

ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ አልፎ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፪ቱ ፡ የሚለውን ፡ አኀዝ ፡ እየቀጸሉ ፡ ፪ ፡ ባሕርያት ፡ ፪ ፈቃድ ፡ ፪ ሥምረት ፡ ሲሉ ፡ መገኘት ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘረውን ፡ የቅዱስ ፡ ጳውሎስን ፡ ዐዋጅ ፡ መጣስ ፡ መኾኑን ፡ በግልጥ ፡ ስለተረዳች ፡ ነው ።

ወዲያውም ፡ በተራቀቀና ፡ በመመራመር ፡ የሚደረስበት ፡ ሥነ ፡ ፍጥረትን ፡ እንመረምራለን ፡ የሚሉ ፡ ሳይንቲስቶች ፡ በምርመራ ፡ ደርሰውበት ፡ ፍሬው ፡ እንደ ፡ ታየለት ፡ በሰማይ ፡ እንደ ፡ መብረር ፡ በምድር ፡ እንደ ፡ መሽከርከር ፡ ያሉ ፡ ቴክኒካውያን ፡ ተግባሮች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ የሃይማኖት ነገር ፡ አይደለም ።

እንዲህም ፡ ማለት ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ተመርምሮ ፡ ይደረስበታል ፡ ባሕርዩ ፡ ግን ፡ በምርመራ ፡ አይገኝም ፡ ማለት ፡ ነው ።

የሃይማኖትስ ፡ ነገር ፡ የሚወሰን ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ አብዳነሁ ፡ ለዝ፡ዓለም ፡ ኀረየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ያስተኀፍሮሙ ፡ ለጠቢባን ። ወዘይሔሊ ፡ እምውስቴትክሙ ፡ ከመ ፡ ጠቢብ ፡ ውእቱ ፡ በዝ ዓለም ፡ አብደ ፡ ለይረሲ ፡ ርእሶ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ጠቢበ ፡ እስመ ፡ እበድ ፡ ውእቱ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥበቡ ፡ ለዝ ፡ ዓለም ፡ ፩ ቆር ፡ ፩ ፡ ፳፯ ፤ ፫ ፡ ፲፰ ።

እግዚአብሔር ፡ ዐዋቆች ፡ ነን ፡ የሚሉትን ፡ ሰዎች ፡ ያሳፍራቸው ፡ ዘንድ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ዐላዋቆች ፡ መረጠ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ዕውቀት ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ጥበብ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ስንፍና ፡ ድንቁርና ፡ ነውና ፡ ከናንተ ፡ ወገን ፡ ብልህ ፡ ዐዋቂ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የሚያስብ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ በእግዚአብ



ይህ ሥዕል ክርስቶስ በሥጋ እንደ ተነሣ ያሳያል ማቴ ፳፰ ፩—፯ ።

ሔር ፡ ዘንድ ፡ ብልህ ፡ ዐዋቂ ፡ ኾኖ ፡ ይገኝ ፡ ዘንድ ፡ ራሱን ፡ ዐላዋቂ ፡ ሰነፍ ፡ ያድርግ ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ ራሳቸውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ለመመረጥ ፡ የበቃ ፡ አድርገው ፡ ተገኝተው ፡ ወኢይከውን ተነብዮ ፡ ግሙራ ፡ እምፈቃደ ፡ ሰብእ ፡ ወእምሥምረተ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ አላ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነበቡ ፡ ቅዱሳን ፡ ሰብእ ፡ ተፈኒዎሙ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፳፩ ።

ቅዱሳን ፡ ሰዎች ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተልከው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተገልጾላቸው ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩ ፡ የሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ አስተማሩ ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ በፈቃዱ ፡ ትንቢት ፡ ሊናገር ፡ የሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ ላስተምር ፡ ቢል ፡ አይቻለውም ፡ ብሎ ፡ ቅ ፡ ጴጥ ፡ እንዳስረዳን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተልከው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተገልጾላቸው ፡ ሐዋርያት ፡ ከጻፉት ፡ መጽሐፍ ፡ ከተናገሩት ፡ ቃል ፡ ሳይወጡ ፡ በፍጹም ፡ ልቡና ፡ ከማመን ፡ በቀር ፡ ዐጠረ ፡ ብሎ ፡ የማይቀጥሉበት ፡ ረዘመ ፡ ብሎ ፡ የማይቀንሱበት ፡ መኾኑን ፡ እንዲገነዘቡት ፡ አሳስብዎታለሁ ።

፺፱/ የማይታመን ፡ ይመስላል ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምትቃወመውስ ፡ በ፬፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተሰበሰበውን ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ አይደለም ፤ ያኑ ፡ የመሰለ ፡ ስም ፡ ያለው ፡ የንስጥሮስንና ፡ የአውጣኪን ፡ ባህል ፡ ተቀብሰው ፡ አጸደቀት ፡ የሚባለውን ፡ ሌላ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ጉባኤ ፡ ነው ። ብለዋል ።

፺፱/ ምንም ፡ ርስዎ ፡ እንዳሉት ፡ የንስጥሮስንና ፡ የአውጣኪን ፡ ባህል ፡ አለመቀበሏ ፡ መቃወሟ ፡ እርግጠኛ ፡ ነገር ፡ ቢኾን ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ አልተቃወመችም ፡ ብለው ፡ ደፍረው ፡ የጻፉትን ፡ ስመለከት ፡ የኾነውን ፡ አልኾነም ፡ ያልኾነውን ፡ ኾነ ፡ የሚያሰኝ ፡ ምን ፡ መንፈስ ፡ አድሮባቸዋል ፡ ይኾን ፡ ብዬ ፡ በጣም ፡ ተገረምኩ ። የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንስ ፡ በጣም ፡ አጥብቃ ፡ የምትቃወመው ፡ የአውጣኪንና ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ በ፬፻፶፩ ፡ ዓ/ም ፡ የተደረገውን ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ የተፈጠረበትን ፡ መልኩን ፡ አጠይሞ ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ ይዞ ፡ ብቅ ፡ ያለውን ፡ የልዮን ፡ ውሳኔ ፡ የተገለጠበትን ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤንም ፡ መኾኑን ፡ እኛ ፡ ባለቤቶቹ ፡ እናረጋግጥልዎታለንና ፡ አይጠራጠሩ ።

፺/ ይህ ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ለወደፊት ፡ በሰፊው ፡ ልናየው ፡ እንወዳለን ፡ ብለዋል ።

፺/ ያው ፡ እንደለመዱት ፡ እንዲህ ፡ ሳይኾን ፡ አይቀርም ፡ እንዲህ ፡ ይኾን ፡ ይኾናል ፡ እያሉ ምኞትዎ ፡ የሚቃናበትን ፡ መንገድ ፡ ለማግኘት ፡ ከሚፈጥሩት ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ንግግር ፡ በቀር ይህን ፡ የሚያስረዳ ፡ የተጨበጠ ፡ ነገር ፡ አያገኙም ፡ እንጂ ፡ የሚያገኙ ፡ ከኾነስ ፡ ዐይንዎን ፡ አፍጠው ይመልከቱ ፡ እኛም ፡ ነቅተን ፡ ተግተን ፡ እንጠባበቅዎታለን ።

፺፩/ ኢትዮጵያውያን ፡ የኬልቄዶኑን ፡ አነጋገር ፡ አገላለጥ ፡ በቃል ፡ አንቀበለውም ፡ ሲሉ ፡ በተግባርና ፡ በእውነት ፡ በእርሱ ፡ የሚነገረውንና ፡ የሚገለጠውን ፡ ትምርት ፡ በማመናቸው ፡ ይታወቃል ። ይኸውም ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ አነጋገርና ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ አነጋገር ፡ ቢያነጻጥሩት ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ ይታወቃል ፡ የኬልቄዶኑንም ፡ አነጋገር ፡ በ፻ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ እናመጣዋለን ፡ ብለዋል ።

፺፩/ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመላዋ ፡ ከጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ በፊት ፡ በምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ በኩል ፡ አብ ፡ ወልድን ፡ ወለደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አሠረጸ ፡ የወልድና ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መሠረት ፡ መገኛ ፡ አብ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ስለምሥጢረ ፡ ሥጋዌም ፡ ክርስቶስ ፡ ቱሳሔ ፡ ውላጤ ፡ ቡዐዴ ፡ ምንታዌ ፡ የሌለበት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ጸንታ ፡ በሥርዓተ ፡ ቍርባንም ፡ በኩል ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥጋዬን ፡ ብሉ ፡ ደሜን ፡ ጠጡ ፡ ብሎ ፡ ባዘዘው ፡ መሠረት ፡ ለካህናትም ፡ ለምእመናንም ፡ አስተካክላ ፡ ሥጋውንም ፡ ደሙንም ፡ በማቀበል ፡ ጸንታ ፡ ከዚህ ፡ ባህል ፡ የሚናወጡ ፡ እነመቅዶንዮስን ፡ እነንስጥሮስን ፡ እያወገዘች ፡ እየለየች ፡ ትኖር ፡ ነበረ ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ ሮም ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በ፬፻፶፩ ፡ ዓ/ም ፡ በ፩ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የሚል ፡ ምንታዌን ፡ የተመረኰዘ ፡ እንግዳ ፡ ባህል ፡ ፈጠረች ። እንዲሁም ፡ በየጊዜው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ ሠረጸ ፡ ካህናት ፡ ሥጋውንም ፡ ደሙንም ፡ ይቀበሉ ፡ ምእመናን ፡ ግን ፡ ሥጋውን ብቻ ፡ ይቀበሉ ፡ እንጂ ፡ ደሙን ፡ አይቀበሉ ፡ እያለች ፡ ከመጽሐፍ ፡ ያልተገኘ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ትምህርት ፡ አስተምራለች ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ሥራት ፡ ሠርታለች ።

ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ትምህርትና ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ሥራት ፡ አልቀበልም ፡ ብላ ፡ ከተመሠረተችበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምራ ፡ ተለይታ ፡ ትኖራለች ።

እንግዲህ ፡ እንደእውነቱ ፡ አነጋገርዎ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክስቲያን ፡ በየጊዜው ፡ የፈጠረችውን ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ባህል ፡ የደገፈችበት ፡ መንገድ ፡ ካለ ፡ መረጃ ፡ ያቅርቡ ፡ እንቀበልም ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ አልተለወጠም ፡ አልተቀላቀለም ፡ አልተጠፋፋም ፡ በማለት ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አልተለየችም ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ትምህርት ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዋንተ ፡ ትምህርቷ ፡ ስለኾነ ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሌላውን ፡ ስትለውጥ ፡ ይህንን ፡ አልለወጠችውም ፡ ያሰኛታል ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያስ ፡ በጥንታዊው ፡ ትምህርት ፡ ጸንታለች ፡ ምንም ፡ አልለወጠችም ፡ ከማሰኘት ፡ በቀር ፡ የካቶሊክን ፡ ባህል ፡ ተቀበለች ፡ አያሰኛትም ።

፶፪/ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለክርስቶስ ፡ አዋሕዶ ፡ ሲናገሩ ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በፊት ፡ የነበሩትን ፡ አበው ፡ በተለይም ፡ የቅዱስ ፡ ቄርሎስን ፡ አነጋገር ፡ ስለሚይዙ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ እውነት ፡ ነገር ፡ ተናግረዋል ።

፶፫/ ኢትዮጵያ ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በፊት ፡ የነበሩት ፡ አበውን ፡ ቃል ፡ አክብራ ፡ መያዟ እርግጥ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ የአበውን ፡ ቃል ፡ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ብትኾን፡ በጉባኤ ፡ኬልቄዶን፡ ባህሏን ፡ እስክትለውጥ ፡ ድረስ ፡ ትቀበለው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የታመነ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ምክንያቱም ፡ ይህ ፡ የአበው ፡ ቃል ፡ ከቅዱስ ፡ ወንጌልና ፡ ከሌሎችም ፡ የሐዋርያት ፡ መጻሕፍት ፡ ግብ ፡ ያልወጣ ፡ ፡ ኾኖ ፡ ስለተገኘ ፡ ነው ፤ የኬልቄዶን ፡ ውሳኔ ፡ ግን ፡ ከመጻሕፍት ፡ ቃል ፡ የወጣ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ውሳኔ ፡ ስለኾነ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አትቀበለውም ።

፶፬/ የቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ አነጋገር ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በራሱ ፡ የቀና ፡ ቢኾን ፡ ለዩቶ ፡ ለማያውቅ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ስሕተት ፡ የሚመራ ፡ አተረጓጐም ፡ ሲሰጠው ፡ የሚቻል ፡ ነው ። ብለው ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስንም ፡ ለመንቀፍ ፡ ሞከር ፡ አድርገዋል ።

፶፭/ አለስ ፡ አልቦሙ ፡ ትምህርት ፡ እለ ፡ ኢለበዉ ፡ ይመይጥዎ ፡ ለቃለ ፡ መጽሐፍ ፡ ከመ ፡ ሜጥዎን ፡ ለብዙኃት ፡ መጻሕፍት ፡ በግእዞሙ ፡ ወያማስኑ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፤ ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ትምህርት ፡ የጐደላቸውና ፡ ያላስተዋሉ ፡ ሰዎች ፡ ለባህላቸው ፡ እንዲስማማ ፡ ሲሉ ፡ በድፍረት ፡ ይለውጡት ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያስ ፡ ወእንትሙሰ ፡ አኀዊነ ፡ አቅድሙ ፡ አእምሮ ፡ ወተዐቀቡ ፡ ከመ ፡ ኢትስሐቱ ፡ በዘኢይበቍዕ ፡ ትምህርት ፡ ከመ ፡ ኢትደቁ ፡ እምነ ፡ ምጽናዕክሙ ፡ ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ።

ወንድሞቻችን ፡ እናንተስ ፡ አስቀድማችሁ ፡ የመጻሕፍትን ፡ ምሥጢር ፡ ዕወቁና ፡ በማይረባ ፡ በማይጠቅም ፡ ትምርት ፡ ተሳስታችሁ ፡ ከጽኑ ፡ እምነታችሁ ፡ እንዳትወድቁ ፡ ተጠንቀቁ ፡ ያለውን ፡ ስለምታውቅ ፡ የቅዱስ ፡ ቄርሎስን ፡ ቃል ፡ ጠንቅቃ ፡ ትተረጕመዋለች ፡ እንጂ ፡ የኾኑ ፡ ቢኾን ፡ ፩ ፡ አካል ፡ ወ፩ ፡ ህላዌ ፡ ብሎ ፡ ያነበበውን ፡ ንባብ ፡ አሐዱን ፡ በክልኤቱ ፡ ለውጣ ፡ ኹለት ፡ ብላ ፡ አትተረጕመውም ።

፶፮ ኢትዮጵያ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ እንደ ፡ ተቀበለች ፡ በግልጥ ፡ የሚናገሩ ፡ እርግጠኞች ፡ ምስክሮች ፡ አላገኘንም ፡ እውነተኛውን ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ በደንብ ፡ አላመነችውም ። ብለዋል ።

፶፯/ ምነው ፡ አሁን ፡ ከዚህ ፡ ከፍ ፡ ብለው ፡ በሚገኙት ፡ መሥመሮች ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንደሌሎቹ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ከኬልቄዶኑ ፡ ጉባኤ ፡ በፊት ፡ በድፍን ፡ ይታመን ፡ የነበረውን ፡ ሃይማኖት ትምርት ፡ ይዛ ፡ ቀረች ፡ ዛሬም ፡ ቢኾን ፡ ከዛሬው ፡ ልዩ ፡ በኾነና ፡ ባረጀ ፡ አነጋገር ፡ ይታመንበት ፡ እንደነበረው ፡ ታምናለች ፡ እንጂ ፡ አነጋገሯን ፡ በተራቀቀ ፡ አሻሽላ ፡ ምንም ፡ አልለወጠችም ፡ የዚህም ፡ ምክንያት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ሲናገሩ ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በፊት ፡ የነበሩትን ፡ አበው ፡ በተለይም ፡ የቅዱስ ፡ ቄርሎስም ፡ አነጋገር ፡ ስለሚይዙ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ ከነበሩ ፡ አበው ፡ የሃይማኖት ፡ ባህል ፡ ልዩ ፡ መኾኑንና ፡ ኢትዮጵያም ፡ በንቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ባህል ፡ ጸንታ ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ውሳኔ ፡ ያልተቀበለች ፡ መኾኗን ፡ እያረጋገጡ ፡ መላልሰው ፡ ተናግረው ፡ አልነበረምን ፡ የኬልቄዶኑስ ፡ ጉባኤ ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ ከነበሩ ፡ አበው ፡ የተለየበት ፡ እነርሱ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ሲሉ ፡ እርሱ ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ባሕርይ በማለቱ ፡ አይደለምን ፡ ከመቼው ፡ ረሱትና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢኾን ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ አልተቀበለችም ፡ ይላሉ ፡ አሁን ፡ ተናግረው ፡ አሁን ፡ ለምን ፡ ይረሳሉ ፡ ያየ ፡ የሰማ ፡ ሰው ባንድራብ ፡ ኹለት ፡ ምላስ ፡ ይለኛል ፡ አይሉምን ፡ ይተው ፡ ቃልምን ፡ ያክብሩት ፡ ይጠብቁት ።

፶፰/ ይሁንም ፡ በንል ፡ ለኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ አልታዘዘም ፡ ብላ ፡ የተቃወመችበት ፡ ጊዜና ፡ በግልጥ ፡ ለመለየት ፡ የፈለገ ፡ በት ፡ ጊዜ ፡ እንዳለ ፡ የሚገልጥ ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ስለማይገኝ ፡ ነው ። ብለዋል ።

፶፱/ ኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ ክርስትናን ፡ ከተቀበለች ፡ ጀምሮ ፡ እስክንድርያን ፡ መስላ ፡ ከእስክንድርያ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ኾና ፡ ትኖራለች ፡ እንጂ ፡ ከማናቸውም ፡ ሌላ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ፡ ግንኙነት ፡ የላትም ፡ የኬልቄዶኑንም ፡ ውሳኔ ፡ በታሪክ ፡ ብቻ ፡ አጥንታው ፡ ጉባኤውን ፡ ማኅበረ ፡ አብዳን ፡ ሊቀ ፡ ጉባኤውን ፡ ተኩላ ፡ መሠሪ ፡ እያለች ፡ በመንቀፍ ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ መስላ ፡ መኖሯ ፡ መጻሕፍቶቿና ፡ ድርሰቶቿ ፡ ይመሰክራሉ ፡ በጊዜው ም ፡ ጊዜ ፡ ሮማውያን ፡ መጥተው ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ እንስበክ ፡ ቢሉ ፡ ደም ፡ እስከመፋሰስ ፡ ደርሳ ፡ ጠራርጋ ፡ እንዳስወጣቻቸው ፡ ብዙ ፡ የታሪክ ፡ መጻሕፍቶች ፡ ይመሰክራሉ ፡ እንግዲህ ፡ ለኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ አልታዘዝም ፡ ብሎ ። መቃወም ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ሊደረግ ፡ ኖሯል ፡ ኢትዮጵያ ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ውሳኔ ፡ አልቀበልም ፡ ብላ ፡ በግልጥ ፡ መቃወሟ ፡ እንዲህ ፡ ግልጥ ፡ ነውና ፡ ይተው ፡ እያጭበርበሩን ፡ አያደናግሩን ።

፺፮/ ከግብጽ ፡ ተልከው ፡ የሚመጡ ፡ ጳጳሶች ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በፊት ፡ ያምኑት ፡ ከነበረ ፡ ልዩ ፡ የኾነ ፡ አዲስ ፡ ትምርት ፡ ሊሰብኩና ፡ ሊያስፋፉት ፡ አልቻሉም ፡ የአውጣኪንም ፡ ትምርት ፡ ለመስበክና ፡ ለማስፋፋት ፡ ብሎ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገባ ፡ ሳይባረር ፡ የቀረ ፡ ማንም ፡ አይታወቅም ፡ ብለዋል ።

፺፯/ ኢትዮጵያ ፡ በእውነት ፡ በአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኩል ፡ ከቤተ ፡ እስራኤል ፡ በቀር ፡ ተቀዳሚ ፡ የሌላት ፡ ሮማም ፡ ግብጽም ፡ ሌሎችም ፡ ሀገሮች ፡ የማይተካከሏት ፡ ተመራምራ ፡ ያመነች ፡ ሀገር ፡ ናት ፡ አስቀድማ ፡ መጻሕፍተ ፡ ብሉያትን ፡ የተቀበለች ፡ በመኾኗ ፡ ስለክርስቶስ ፡ ሰው ፡ መኾን ፡ የተነገረውን ፡ ትንቢት ፡ የተቈጠረውን ፡ ሱባኤ ፡ ታውቅ ፡ ስለነበረ ፡ ሥጋዌ ፡ መቼ ፡ ይደርስ ፡ ይኾን ፡ እያለች ፡ ስታወጣ ፡ ስታወርድ ፡ ፊትም ፡ ሕጽዋ ፡ ለሕንደኬ ፡ ኋላም ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ተስፋ ፡ ደረሰ ፡ ሥጋ ፡ ለበሰ ፡ ብለው ፡ ቢነግሯት ፡ የሚያጠምቅ ፡ የሚያቈርብ ፡ መምህር ፡ ላኩልን ፡ ብላ ፡ ስንቅ ፡ ጨምራ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስን ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ልካለች ፡ እንጂ ፡ ግብጽ ፡ መጥታ ፡ አስተምራ ፡ ያሳመነቻት ፡ ሀገር ፡ አይደለችም ።

ከፍሬ ፡ ምናጦስም ፡ በኋላ ፡ አልቦ ፡ ዘይነሥእ ፡ ክብረ ፡ ለርእሱ ፡ ሥልጣነ ፡ ክህነት ን ፡ ሀብተ ፡ ክህነትን ፡ በገዛ ፡ ሥልጣኑ ፡ ገንዘብ ፡ ማድረግ ፡ የሚቻለው ፡ የለም ፡ የሚለውን ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ስለምታውቅ ፡ ጳጳስ ፡ ሲሞት ፡ በገዛ ፡ ሥልጣኔ ፡ ሾሜ ፡ ልተካ ፡ ሳትል ፡ ጳጳስ ፡ ላኩልኝ ፡ እያለች ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ከመላክ ፡ በቀር ፡ ሃይማኖቷን ፡ ረስታና ፡ ዘንግታ ፡ መምህር ፡ የምትፈልግ ፡ አይደለችም ።

ስለዚህ ፡ አሁንም ፡ ቢኾን ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ የሚል ፡ ሃይማኖቷን ፡ ጾም ፡ ጸሎት ፡ ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ሥነ ፡ ምግባሯን ፡ የሚለውጥ ፡ ከኾነ ፡ ግብጻዊ ፡ ሮማዊ ፡ ሳትል ፡ ማንንም ፡ የማትቀበል ፡ መኾኗ ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ሊሰብክ ፡ መጥቶ ፡ ሳይባረር ፡ የቀረ ፡ እንደሌለ ፡ በእርግጥ ፡ ሲያውቁ ፡ የአውጣኪን ፡ ባህል ፡ ሊሰብክ ፡ መጥቶ ፡ ሳይባረር ፡ የቀረ ፡ የለም ፡ እንዳሉት ፡ የኹለት ፡ ባሕርይንም ፡ ባህል ፡ ሊሰብክ ፡ መጥቶ ፡ ሳይባረር ፡ የቀረ ፡ የለም ፡ ባለማለትዎ ፡ ከእውነት ፡ የራቀ ፡ ሐሳባቸውን ፡ ብቻ ፡ ደጋፊ ፡ ናቸው ፡ ብዬ ፡ ታዘብኩዎ ።

፺፰/ ኢትዮጵያንና ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ለያይቶ ፡ ያለው ፡ መጋረጃ ፡ በጣም ፡ የረቀቀ ፡ ነው ፡ አሁን ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ ምርመራ ፡ ክፍል ፡ ይህን ፡ መጋረጃ ፡ ገልጠን ፡ ከባለቤቶቹ ፡ በቀጥታ ፡ የተገኙና ፡ የተረጋገጡ ፡ ማስረጃዎች ፡ እያመጣን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ የምታምነው ፡ ትምርት ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ መኾኑን ፡ መርምረን ፡ እንወስናለን ፡ ብለዋል ።

፺፱/ ኢትዮጵያውያንና ፡ ካቶሊካውያን ፡ የተለያዩበት ፡ መጋረጃ ፡ ምንም ፡ የረቀቀ ፡ አይደለም ፡ በጣም ፡ የጎላ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመምህራን ፡ ከመጻሕፍት ፡ ያልተገኘ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ትምህርት ፡ አምጥታ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ ሠረጸ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ክርስቶስ ፡ ሁለት ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ብላ ፡ ስታስተምር ፡ ምእመናን ፡ ሥጋውን ፡ ይቀበሉ ፡ እንጂ ፡ ደሙን ፡ አይቀበሉ ፡ ብላ ፡ ስትበይን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይህ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ነው ፡ አልቀበልም ፡ በማለቷ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ይህንንም ፡ መጋረጃ ፡ ገልጦ ፡ ማሳየት ፡ የሚቻል ፡ ይህ ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የወሰነችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ አልቀበልም ፡ ያለችው ፡ ውሳኔ ፡ ከመጻሕፍት ፡ የተገኘ ፡ መኾኑን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ እየጠቀሱ ፡ በማስማማት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ አይደለም ።

ደግሞ ፡ ከባለቤቶቹ ፡ የተገኙትን ፡ ማስረጃዎች ፡ መርምሬ ፡ እወስናለሁ ፡ ስለሚሉት ፡ በሕይወት ፡ ታሪክዎ ፡ እንደ ፡ ገለጹልን ፡ ስንኳንስ ፡ በተማሪ ፡ ቤት ፡ የቆዩበት ፡ የተወለዱበትም ፡ ቢኾን ፡ ጊዜው ፡ በጣም ፡ አጭር ፡ ነው ፡ ያነኑም ፡ በካቶሊክ ፡ ሚሲዮን ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ አሳልፈውታል ፡ እንጂ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መምህራን ፡ ስንኳን ፡ የተማሩበት ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ የተጨዋወቱበት ፡ ጊዜ ፡ እንኳ ፡ የለምትም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መምህራን ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ ጠይቀው ፡ ምሥጢር ፡ መረዳት ፡ ይቅርና ፡ ከፊታቸው ፡ ደርሰው ፡ ፊታቸውን ፡ አይተው ፡ በማያውቁበት ፡ በዚህ ፡ ባጭሩ ፡ ዘመንዎና ፡ በጠባቡ ፡ ምርመራዎ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መምህራን ፡ መላ ፡ ዘመናቸውን ፡ አንገታቸውን ፡ አቀርቅረው ፡ መጻሕፍት ፡ በመመልከት ፡ ሲያጣሩት ፡ የኖሩትን ፡ ባህል ፡ አንዳንድ ፡ የተቆራረጡ ፡ የመጻሕፍት ፡ ቁርጥራጮችና ፡ መውጫ ፡ መግቢያቸውን ፡ የማያውቋቸውን ፡ ቅኔዎች ፡ አጠራቅሜ ፡ እወስናለሁ ፡ ማለትዎ ፡ ፍጹም ፡ የውሸት ፡ ውሸት ፡ ነው ፡ አይችሉም ፡ አቅምዎም ፡ አይደለም ። ይህንን ፡ ለመወሰን ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ በመጽሐፍ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ መቆየትና ፡ የሊቃውንትን ፡ መምህራን ፡ አስተያየት ፡ ጠይቆ ፡ መረዳት ፡ ያስፈልጋል ፡ ይህም ፡ በምርመራ ፡ ደረስኩበት ፡ የሚሉት ፡ አስተያየት ፡ ኹሉ ፡ ስሕተት ፡ መኾኑን ፡ በያንቀጹ ፡ እገልጽልዎታለሁና ፡ ልብ ፡ ብለው ፡ ይመልከቱ ።

## ለአንባቢዎች ፡ ልዩ ፡ ማስገንዘቢያ ።

ያጻጻፉን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መግቢያ ፡ በሚለው ፡ አርእስት ፡ ላይ ፡ ገልጸናል ፤ በ፫ኛው ፡ ቍ ፡ የዶክተር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ ንግግርና ፡ መልሱ ፡ ባንድ ፡ መልክ ፡ የታተመ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ንባቡ ፡ ተሰባጥሮ ፡ ተመልካችን ፡ እንዳያስቸግር ፡ በማለት ፡ የአባ አየለን ፡ ንግግር ፡ በረቂቅ ፡ የኔን ፡ መልስ ፡ በጉልህ ፡ እንዲታተም ፡ ያደረግሁ ፡ መኾኔን ፡ አስታውሳለሁ ።

ይህ ፡ አሠራር ፡ ለሥራው ፡ መቀልጠፍ ፡ ዙሪያ ፡ ጥምጥም ፡ ኾኖ ፡ ሥራውን ፡ ከመንተቱም ፡ በላይ ፡ ብዙ ፡ ተመልካቾች ፡ ይህ ፡ በረቂቅና ፡ በጉልህ ፡ እየተቀላቀለ ፡ የሚሠራው ፡ አሠራር ፡ የመጽሐፉን ፡ መልክ ፡ ከማጥፋቱም ፡ ሌላ ፡ ረቂቁ ፡ ፊደል ፡ ለንባብ ፡ አይመችምና ፡ ባንድ ፡ መልክ ፡ ቢሔድ ፡ ይሻላል ፡ ብለው ፡ ሐሳባቸውን ፡ ስለ ፡ ገለጹልኝ ፡ ከምዕራፍ ፡ ፫ ፡ ጀምሮ ፡ በአንድ ፡ መልክ ፡ ፊደል ፡ እንዲታተም ፡ የደራሲውና ፡ የመላሹ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ተለይቶ ፡ እንዲታወቅም ፡ ከአባ ፡ አየለ ፡ ለተገኘው ፡ ንግግር ፡ ደራሲው ፡ የሚል ፡ ብቻውን ፡ አንድ ፡ መሥመር ፡ የያዘ ፡ አርእስት ፡ እንዲሰጠው ።

ለመልሱም ፡ እንደዚሁ ፡ መላሽ ፡ የሚል ፡ ብቻውን ፡ አንድ ፡ መሥመር ፡ የያዘ ፡ አርእስት ፡ እንዲሰጠው ፡ አድርገናል ።

በዚያም ፡ ኾነ ፡ በዚህ ፡ ድካማችን ፡ ተመልካችን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘት ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡ እየገለጽን ፡ ይቅርታ ፡ እንለምናለን ።

## ምዕራፍ ፫ ።

ከካቶሊክ ፡ የተለዩት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ያሏቸው አስተያየቶች ።

### ደራሲው ።

፩/ ኢትዮጵያ ፡ በሃይማኖት ፡ ታሪኳ ፡ ውስጥ ፡ ለካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በግልጥ ፡ ለመቃወም ፡ የተነሣችበት ፡ እርግጠኛና ፡ የማያከራክር ፡ ዘመን ፡ እንደማይገኝ ፡ አስረድተናል ፡ ብለዋል።

### መላሽ ።

፩/ እርስዎ ፡ በኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ፍቅር ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ስለነደዱ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ እንደርስዎ ፡ አዎን ፡ አዎን ፡ የሚለኝ ፡ መስሎዎ ፡ እንዲህ ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡ ርስዎም ፡ ለዚህ ፡ ነገር ፡ የሚበቃ ፡ መረጃ ፡ አላቀረቡ ፡ አዎን ፡ ብሎ ፡ የተቀበለዎም ፡ ሰው ፡ የለ ።

ኢትዮጵያ ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ተገኝታ ፡ ይህን ፡ ተናገረች ፡ ባትባልም ፡ ከዚያ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ መስላ ፡ መኖሯ ፡ የታወቀ ፡ እርግጠኛ ፡ ነገር ፡ የኾነውን ፡ ያህል ፡ ካቶሊካውያን ፡ መጥተው ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ እንስበክ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ ላቀረቡላት ፡ ጥያቄ ፡ በቂ ፡ መልስ ፡ ሰጥታ ፡ ከማሳፈርዋም ፡ በላይ ፡ ደም ፡ እስከ ፡ መፋሰስ ፡ ደርሳ ፡ ያስወጣቻቸው ፡ መኾኗ ፡ ሲታወቅ ፡ የተቃወመችበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ ማውራት ፡ እንደ ፡ ሥራ ፡ ፈትነት ፡ የሚያስቆጥር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ማንም ፡ ሊሰማው ፡ አይችልም ።

### ደራሲው ።

፪/ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢኾን ፡ ሊስፋፋ ፡ አልቻለም ፡ እውነተኛው ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አለመገኘቱን ፡ ገልጠናል ፡ ምክንያቱም ፡



ይህ ሥዕል እመቤታችን እንደ ቃልህ ይደረግልኝ ብላ የቅዱስ ገብርኤልን ብሥራት በተቀበለች ጊዜ ከአብ ከመ ንፈስ ቅዱስ ጋራ አንድ የምትኾን በዘዊን የምትለይ ባሕርይ ያለችው አካለ ቃል ሰብአዊ ባሕርይ ያለው ሰብአዊ አካልን እንስለ ዘርዕ ነሥቶ ሰው እንደ ኾነ ያሳያል ። ሉቃ ፩፣ ፳፮—፴፱ ።



ዮሐንስ ወንጌሉን ቃል ሥጋ ኾነ እያለ ሲጽፍ ያሳያል ዮሐ ፩ ፲፬ ።



ይህ ሥዕል ፀጎል ተጥሎ በሬጨርቅ ተጠቅሎ አህያና በሬ ትንፋሻቸውን እያሟሟቁት የእናቱን ጡት ሽቶ ሲያለቅስ ያሳያል ። ሉቃ ም፪፡ ቍ ፯ ።



ይህ ሥዕል መለኮት በሥጋ እንደ ተጠመቀ አብም ይህ ልጄ ነው ብሎ እንደ መሰከረ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል እንደ ወረደ ያሳያል ማቴ ፫—፲፯ ።

ኢትዮጵያውያን ፡ ለዚህ ፡ ባህል ፡ ደጋፊዎች ፡ ብቻ ፡ ሳይኾኑ ፡ ከእስክንድርያ ፡ የሚመጡትን ፡ ጳጳሳት ፡ ጠንክረው ፡ ይቃወሟቸው ፡ ስለነበረ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፪/ ኢትዮጵያውያን ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ደግፈው ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትን ፡ መስለው ፡ ካቶሊካውያንን ፡ በማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ተቃውመው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጠራርገው ፡ እንዳ ስወጧቸው ፡ በነዐፄ ፡ ዘድንግል ፡ በነዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ በነዐፄ ፡ ፋሲል ፡ በነዐፄ ፡ ዮሐንስ ፡ ታሪክ ተጽፎ ፡ ይገኛል ።

ኢትዮጵያውያን ፡ የ፪ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ደግፈው ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ እስክንድራው ያንን ፡ የተቃወሙ ፡ በማን ፡ ዘመን ፡ በየት ፡ ቦታ ፡ ነው ፡ ይህንስ ፡ ያደረጉ ፡ እነማን ፡ ናቸው ፡ እስኪያ ምጡት ፡ ምነው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ውሸት ፡ ይገባልን ፡ አይገባም ።

ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሊስፋፋ ፡ አልቻለም ፡ ስለሚሉትም ፡ ጎድረት ፡ ውላጤ ፡ ቱሳሔ ፡ ቡዐዴ ፡ የሌለበት ፡ ተዐቅቦ ፡ ያልጠፋበት ፡ ከሐዋርያትና ፡ ከ፫ቱ ፡ ዐበይት ፡ ጉባኤያት ፡ ተያ ይዞ ፡ የወረደው ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምንጊዜም ፡ ቢኾን ፡ ተስፋፍቶ ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፡ የተጣበበበት፡ጊዜ ፡ የለም ፡ ሊስፋፋ ፡ አልቻለም ፡ ማለትን ፡ ርስዎ ፡ ብቻ ፡ ያወራሉ ፡ እንጂ ፡ አንድም ፡ እውነት ፡ የሚልዎ ፡ አይገኝም ።

## ደ ራ ሲ ው

፫/ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ በሮማ ፡ መካከል ፡ ላለው ፡ አለመስማማት ፡ ምክንያቶቹ፣ ለኢትዮጵያውያን ፡ ስለኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ያልዋቸው ፡ ያልተካከሉ ፡ አስተያየቶች ፡ እንዲሁም ፡ ስለተዋሕዶተ ፡ ባሕርያት ፡ ሲናገሩ ፡ የሚያገቡት ፡ ልዩ ፡ አነጋገርና ፡ አገላለጥ ፡ ናቸው ፡ በዚህ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ የምንለውን ፡ በተረጋገጡ ፡ ምስክሮች ፡ እያስረዳን ፡ በየምዕራፉ ፡ ለይተን ፡ በ፤ፊው ፡ እን ናገርበታለን ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፫/ በኔ ፡ አስተያየት ፡ ኢትዮጵያና ፡ ሮማን ፡ ለያይቷቸው ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ በምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ በኩል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ ሠረጸ ፡ ማለት ፡ በምሥጢረ ፡ ሥጋዌም ፡ በኩል ፡ መጻ ሕፍት ፡ ክርስቶስ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ብለው ፡ ቢያስተምሩ ፡ ከዚህ ፡ ወጥቶ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ በ፪ቱ ፡ ባሕርያት ፡ ብሎ ፡ መጨመር ፡ በሥርዓት ፡ ቍርባንም ፡ በኩል ፡ ምእመናን ፡ ሥጋውን ፡ እንጂ ፡ ደሙን አይቀበሉ ፡ ብሎ ፡ መበየንና ፡ ሌሎችም ፡ ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ናቸው ።

ከነዚህ ፡ ሌላ ፡ የሚያመጧቸው ምክንያቶች ፡ ካሉ ፡ በየምዕራፉ ፡ እየጠበቅሁ ፡ ዋጋቸውን ፡ ለመስጠት ዝግጁ ነኝ ።

## ደ ራ ሲ ው ።

፬/ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባሁኑ ፡ ዘመን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ የም ታምነው ፡ ትምህርት ፡ ባሳቡና ፡ ባገላለጡ ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በፊት ፡ ልክ ፡ ክርስቲያኖቹ ፡ ኹሉ ፡ ያምኑት ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ነው ። ይህም ፡ ትምህርት ፡ ለንስጥሮስ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ለአውጣ ኪም ፡ ባህል ፡ ፈጽሞ ፡ ተቃራኒ ፡ በመኾኑ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ካስተማረውና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በደንብ ፡ ባትወስነው ፡ በኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ይታ መን ፡ ከነበረው ፡ ትምህርት ፡ ፈጽሞ ፡ የተስማማ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፬/ ሮማንና ፡ ኢትዮጵያን ፡ የለያያቸው ፡ ምክንያት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመሠረቷ ፡ አንድ ፡ ኾና ፡ ተስማምታ ፡ ስትኖር ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ አበው ፡ የወሰኑትን ፡ ውሳኔ ፡ አፍርሶ ፡ ስላበላሸውና ፡ ኢትዮጵያም ፡ ይህን ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ውሳኔ ፡ አልቀበልም ፡ ብላ ፡ የቀደሙ ፡ አበው ፡ ከወሰኑት ፡ ውሳኔ ፡ አለመናወጧ ፡ ነው ፡ እርስዎም ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ከርሱ በፊት ፡ የነበሩ ፡ ሐዋርያት ፡ ፫ቱ ፡ ፻ ፡ የሌሎችም ፡ ጉባኤያት ፡ የወሰኑትን ፡ ውሳኔ ፡ አፍርሶ ፡ ሌላ ፡ ባህል ፡ ማቋቋሙን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ውሳኔ ፡ አልቀበልም ፡ ብላ ፡ በዚያው ፡ በቀድሞው ፡ ውሳኔ ፡ መጽናቷን ፡ ካረጋገጡልኝ ፡ ሌላ ፡ የምፈልገው ፡ የለኝም ፡ ይኸው ፡ በቂየ ፡ ነው።

ይህ ፡ ትምህርት ፡ ለንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለአውጣኪም ፡ ባህል ፡ ተቃራኒ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ለኬልቄዶኑም ፡ ባህል ፡ ፈጽሞ ፡ ተቃራኒ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ባለመጨመርዎ ፡ ብቻ ፡ ቅር ፡ ይለኛል ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ በመናገርዎ ፡ አመሰግንዎታለሁ ። ፊትዎን ፡ ጸፍቶ ፡ አፍዎን ፡ ከፍቶ ፡ እውነት ላናገረዎ ፡ አምላክም ፡ ጥልቅ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ። በእውነት ፡ ይህን ፡ ያናገረዎ ፡ በልዓም ፡ ቤተ ፡ እስራኤልን ፡ ሊረግም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ያለፈቃዱ ፡ በግድ ፡ ፊቱን ፡ ጸፍቶ ፡ አፉን ፡ ከፍቶ ፡ ኮከብ ፡ ይሠርቅ ፡ እምያዕቆብ ፡ ወያዓትት ፡ ኃጢአተ ፡ እምእስራኤል ፡ አሰኝቶ ፡ ያናገረው ፡ ኃይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደኾነ ፡ አምናለሁ ።

ደ ራ ሲ ው ።

፭/ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ በተደረገው ፡ ማመጥ ፡ ማበርዋንና ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ በተነሣው ፡ ክርክር ፡ ውስጥ ፡ መግባቷ ን ፡ የሚያስረዳ ፡ ምስክር ፡ ምንም ፡ አይገኝም ። ኢትዮጵያውያኖቹ ፡ በኬልቄዶን ፡ ስለተደረገው ፡ ነገር ፡ ወሬውን ፡ የሰሙ ፡ ከብዙ ፡ ዘመናት ፡ በኋላ ፡ ነው ፡ በመጻሕፍታቸውም ፡ ውስጥ ፡ ከ፲፬ኛ ፡ ፲ ፡ ዘመን ፡ ምሕረት ፡ በፊት ፡ አይናገሩበትም ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፭/ አሁን ፡ የዚህ ፡ አነጋገርዎ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በኬልቄዶኑ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ የዲዮስቆሮስ ፡ ተባባሪ ፡ በመኾን ፡ ተቃውሟ ፡ ሐሳቧን ፡ ያልገለጸችበት ፡ ምክንያት ፡ ከጉባኤው ፡ ላይ ፡ ባለመገኘቷና ፡ ነገሩን ፡ ባለመስማቷ ፡ መኾኑን ፡ ነገሩንም ፡ የሰማችው ፡ ከ፲፬ኛው ፡ ፲ ፡ ዓ/ም ፡ በኋላ ፡ መኾኑን ፡ አረጋግጠዋል ።

ደ ራ ሲ ው ።

፮/ ኢትዮጵያውያኖቹ ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ ይቀበሉታልን ? ፡ እነርሱ ፡ ክርስቶስ ፡ ያምላክንና ፡ የሰውን ፡ ሥራዎች ፡ የሚሠራ ፡ ፍጹም ፡ አምላክና ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ መኾኑን ፡ በግልጥ ፡ ያምናሉ ነገር ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ አለመቀበል ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ጠንክረው ፡ ይቃወሙታል ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፮/ ኢትዮጵያ ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ጊዜ ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ መስላ ፡ ያልተቃወመችና ፡ ያልተከራከረች ፡ ባለ ፡ መኖሯና ፡ ባለመሰማቱ ፡ መኾኑን ፡ በሰማችም ፡ ጊዜ ፡ ጠንክራ ፡ የተቃወመች ፡ መኾኗን ፡ ካወቁ ፡ የኬልቄዶንን ፡ ጉባኤ ፡ መኖሩን ፡ መፈጠሩን ፡ ሳታውቀው ፡ ለምን ፡ አልተቃወመችውም ፡ ማለትዎ ፡ ነውን ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ የተቀበለችበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ፡ ገና ፡ በኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ነበረች ፡ ይሉና ፡ደግሞ ፡ መልሰው ፡ ኢትዮጵያ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በፊት ፡ በነበረው ፡ እምነት ፡ ታምናለች ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ ጠንክራ ፡ ትቃወማለች ፡ እያሉ ፡ ነገሩን ፡ በማማታት ፡ ለምን ፡ መጨበጫ ፡ ያሳጡታል ፤ እወና ፡ አልቦ ፡ ባንድ ፡ አፍ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሊነገሩ ፡ ይቻላልን ፡ አይቻልም ።

ደግሞ ፡ በዚሁ ፡ አነጋገርዎ ፡ ላይ ፡ ክርስቶስ ፡ ያምላክንና ፡ የሰውን ፡ ሥራዎች ፡ የሚሠራ ፡ ፍጹም አምላክ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ማለትን፡የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የመሠረተው ፡ ኹኖ ፡ ኢትዮጵያም ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ ይህን ፡ ብቻ ፡ ለይታ ፡ ተቀብላ ፡ የቀረውን ፡ በከፊል ፡ አልቀበልም ፡ ያለች በማስመሰል ፡ ተናግረዋል ።

ይህም ፡ አንድ ፡ ማደናገሪያ ፡ መንገድ ፡ ነው ። ክርስቶስ ፡ የአምላክነትንም ፡ የሰውነትንም ፡ ሥራ ፡ ባንድ ፡ ፈቃድ ፡ ባንድ ፡ ሥምረት ፡ የሚሠራ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ማለትን ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ አበው ፡ ቅዱሳን ፡ ያስተማሩት ፡ ትምርት ፡ ኢትዮጵያም፡ አስቀድማ ፡ የተቀበለችው ፡ ትምህርት ፡ ነው ።

የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የወሰነው ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ትምህርት ፡ በአካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ የኾነ፡ ክርስቶስ ፡ ያልተዋሐዱ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ አሉት ፡ እኒህ ፡ ኹለቱ ፡ ባሕርያትም ፡ ገዢና ፡ ተገዢናቸው ፡ እነርሱም ፡ በፈቃድ ፡ የማይገናኙ ፡ ስለኾነ ፡ መለኮትም ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ የመለኮትን ፡ ሥራ ይሠራል ፡ ትስብእትም ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ የትስብእትን ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ ብሎ ፡ የወሰነው ፡ ውሳኔ ፡ ነው ። ኢትዮጵያም ፡ የማትቀበለው ፡ ይህን ፡ ውሳኔ ፡ ነው ፡ በዚሁ ፡ መጽሐፍዎ ፡ በገጽ ፡ ፲፲፯ና ፡ ፲፲፰ ፡ የጻፉትን ፡ ይመልከቱ ።

## ደ ራ ሲ ው ።

፯/ የጉባኤው ን ፡ እውነተኛውን ፡ ታሪክ ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ እንደማያውቁት ፡ በእርሱም ፡ ያወገዙትና ፡ የወሰኑት ፡ ትምህርት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በትክክል ፡ እንዳልተረዱት ፡ ግልጥ ፡ ኾኖ ይታያል ፡ ያልኾነና ፡ ያልዋለውን ፡ በማውራት ፡ ትምህርቱን ፡ በፍጹም ፡ ያበላሹታል ። ይህም ፡ መኾኑ ፡ የግብጽ ፡ ጳጳሳት ፡ ከዐረብ ፡ ወደግእዝ ፡ አያበላሹ ፡ ስለተረጐሙት ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፯/ ታሪኩ ፡ ቢለወጥም ፡ ባይለወጥም ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የለውም ፡ መለያየትን ፡ ያመጣው ፡ ፍሬው ፡ ነገር ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ከሐዋርያት ፡ሲያያዝ ፡ የመጣውን ፡ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሳትቀር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመላዋ ፡ ታምነው ፡ የነበረውን ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ማለትን ፡ ለውጦ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ ፈቃድ ፡ ማለትን ፡ ፈጠረ ፡ በመባሉ ፡ ነው ። ይህ ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ መኾኑንም ፡ ርስዎ ፡ ራስዎ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ አረጋግጠዋል ።

አሁንም ፡ ቢኾን ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የሚል ፡ አንግዳ ፡ ትምህርትን ፡ ሳያመጣ ፡ በሐሰት ፡ ተወርቶበታል ፡ የሚሉን ፡ እንደኾነ ፡ የሰማነውን ፡ ያጠናነውን ፡ ታሪክ ፡ ኹሉ ፡ ሠርዘን ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ እንስማማና ፡ አንድ ፡ እንኾን ። ይህ ፡ ካልኾነ ፡ ግን ፡ ሌላውን ፡ ወሬ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ በመባባል ፡ መጨቃጨቅ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነገር ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ው ።

፰/ የግብጽ ፡ ጳጳሳት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከሮማ ፡ አርቀው ፡ በራሳቸው ፡ ቀንበር ፡ ለመቆራኘት ፡ ሲሉ ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤና ፡ የሮማውን ፡ ጳጳስ ፡ የልዮንን ፡ በጠቅላላው ፡ የካቶሊኮችን ፡ ስም ፡ በማጥፋት ፡ ላንድ ፡ በሕርይ ፡ ባዩ ፡ ለዲዮስቆሮስ ፡ እየተከላከሉለት ፡ የሃይማኖቱን ፡ ኦርቶዶክስነት ፡ የሕይወቱን ፡ ቅድስና ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ለማውራት ፡ ተጣጣሩ ፡ ጥረታቸውም ፡ በከንቱ ፡ አልቀረም ።

ስለኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚነገረው፡ወግ ፡ ከያዕቆብያውያን ፡ ወይም ፡ ከምስር ፡ ቅብጦች ፡ የወረደ ፡ በመኾኑ ፡ በጠቅላላው ፡ ያም ፡ ኾነ ፡ ያ ፡ ኹሉም ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ስለቅብጦች ፡ ወጎች ፡ በአብዛኞቹ ፡ ሰዎች ፡ አፍ ፡ የሚነገረው ፡ ለኢትዮጵያውያኖቹ ፡ የሚስማማ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፰/ በዚህ ፡ አነጋገርዎ ፡ የግብጽ ፡ ጳጳሳት ፡ ኢትዮጵያን ፡ እንደ ፡ መኪና ፡ እየቃኙ ፡ እነርሱ ፡ በወደዱት ፡ መንገድ ፡ የሚነዷት ፡ እንጂ ፡ ርሷ ፡ ራሷ ፡ ምንም ፡ እንደማታውቅ ፡ አድርገው ፡ ተናግረዋል ።

ነገሩ ፡ እንዲህ ፡ እርስዎ ፡ እንደሚመስልዎና ፡ እንደሚያወሩት ፡ አይደለም ፡ ኢትዮጵያ ፡ የኬልቄዶንን ፡ ውሳኔ ፡ የልዮንን ፡ ባህል ፡ ዝቅ ፡ አድርጋ ፡ የምትመለከትበት ፡ የዲዮስቆሮስን ፡ ባህል ፡ ከፍ ፡ አድርጋ ፡ የምታይበት ፡ ምክንያት ፡ የኹለቱንም ፡ ባህል ፡ አመዛዝና ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ አነጻጽራ ፡ የልዮን ፡ ባህል ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የወጣ ፡ የራቀ ፡ ሲኾን ፡ የዲዮስቆሮስ ፡ ባህል ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ቃል ፡ ያልወጣ ፡ ኾኖ ፡ ተባብሮ ፡ ተስማምቶ ፡ ስላገኘችው ፡ ነው ።

ከግብጽ ፡ ጳጳሳትም ፡ ጋራ ፡ ተስማምታ ፡ ተባብራ ፡ መኖሯ ፡ በሃይማኖት ፡ ባህል ፡ ስለተስማሙ በፈቃዷ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በግዴታ ፡ አይደለም ።

በግድ ፡ የተያዘች ፡ አስመስሎ ፡ በራሳቸው ፡ ቀንበር ፡ ለመቆራኘት ፡ ብሎ ፡ መናገር ፡ ተገቢ ፡ ንግግር ፡ አይደለም ።

## ደ ራ ሲ ው ።

፱/ ለኢትዮጵያውያን ፡ ስለኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ያላቸው ፡ አስተያየት ፡ ለብቻው ፡ ተጠንቶ ፡ መመርመር ፡ የሚገባው ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ልዩ ልዩ ፡ ምክንያት ፡ አይታጣም ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፱/ የግብጽ ፡ ጳጳሳት ፡ በራሳቸው ፡ ቀንበር ፡ ለመቆራኘት ፡ ብለው ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ ውስጡን፡ገብቶ ፡ መመርመር ፡ ተገቢ ፡ ነገር ፡ ነው ። ቢመረምሩትም ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተከተለችው ፡ ያንድ፡

ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ተስማሚነቱ ፡ ከእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ የሌሎችም ፡ አህጉር ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትና ፡ ከጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ የሮም ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ጸንተው ፡ የኖሩበት ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የተገኘ ፡ መኾኑን ፡ እንደሚረዱት ፡ እምናለሁ ።

## ደ ራ ሲ ው ።

፲/ ግብጻውያን ፡ የኬልቄዶንን ፡ ጉባኤ ፡ ሲቃወሙት ፡ ትምህርቱንም ፡ አንቀበለውም ፡ ሲሉት ፡ ጥፋታቸውን ፡ የሚያቃልል ፡ ያለማወቅ ፡ ምክንያት ፡ አይገኝላቸውም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ቢያደርጉት ፡ ግን ፡ ያለማወቅ ፡ ሙሉ ፡ ምክንያት ፡ አላቸው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲/ እንዲህ ፡ ማለት ፡ የሚገባ ፡ ባለማወቅ ፡ አጥፍቻለሁ ፡ የሚል ፡ ሲኖር ፡ ነበረ ፡ ጥፋተኛው ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቢቃወሙት ፡ ጥፋቱን ፡ ዐውቆ ፡ ይቅርታ ፡ የለመነ ፡ ያለ ፡ አስመስሎ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መጻፍ ፡ ማጭበርበር ፡ ነው ፡ ማጭበርበር ፡ አይገባም ።

## ደ ራ ሲ ው ።

፲፩/ ግብጻውያን ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ የሚቃወሙት ፡ ከኬልቄዶን ፡ ሊቃውንት ፡ ጋራ ፡ በተደረገው ፡ ቀጥተኛ ፡ ግጭት ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ግን ፡ የሚቃወሙት ፡ በሚበቃ ፡ እኳኋን ፡ ካለማወቃቸው ፡ የተነሣ ፡ በመኾኑ ፡ አንቀበለውም ፡ ቢሉ ፡ በውነት ፡ ተቃወሙት ፡ ሊባል ፡ አይገባውም ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፩/ ግብጻውያን ፡ የኬልቄዶንን ፡ ውሳኔ ፡ በጊዜው ፡ ጊዜ ፡ ከጉባኤው ፡ ላይ ፡ ተገኝተው ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ ቢሰሙት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ኖረው ፡ ኖረው ፡ ቢሰሙት ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ያው ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ ነው ። ከዚያም ፡ ወዲህ ፡ በየጊዜው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚመጡ ካቶሊካውያን ፡ ኹሉ ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የወሰነው ፡ ያነኑ ፡ ቀድሞ ፡ የሰማነውን ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከማረጋገጥ ፡ በቀር ፡ አሻሽሎ ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ተብሎ ፡ አልተወሰነም ፡ ብሎ ፡ ያወራ ፡ የለም ። እንግዲህ ፡ አነጋገሩ ፡ ካልተለወጠ ፡ በግብጻውያን ፡ ቃል ፡ ሲሰማ ፡ ያለዕውቀት ፡ ነው ፤ በሮማውያን ፡ ቃል ፡ ሲሰማ ፡ በእውቀት ፡ ነው ፡ የሚባልበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድን ፡ ነው ።

ኢትዮጵያስ ፡ የሮማን ፡ ካቶሊክ ፡ የምትቃወማት ፡ ባህሏን ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ዐውቃ ፡ ጠንቅቃ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባለማወቅ ፡ አይደለም ።

እንዲህ ፡ ታውቆ ፡ ተጠንቶ ፡ የተደረገውን ፡ ነገር ፡ ሳታውቀው ፡ ነው ፡ አይፈረድባትም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ በአፍም ፡ በጽሑፍም ፡ ሲነቅፉትና ፡ ሲቃወሙት ፡ ቢገኙ ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ በተንኰል ፡ በሀገራቸው ፡ ውስጥ ፡ የዘሩባቸውን ፡ ያልኾነ ፡ ወሬ ፡ ሳያበጥሩት ፡ በመታለል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ አይደለም ፡ እያሉ ፡ መጻፍ ፡ ማሽቧቧት ፡ ማባበል ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ አይደለም ።

ይህም ፡ በአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኵል ፡ ከቤተ ፡ እስራኤል ፡ በቀር ፡ ተቀዳሚ ፡ የሌላት ፡ ኢትዮጵያን ፡ የሚያሳዝናት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛት ፡ አይደለም ። ወዲያውስ ፡ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ያልተጻፈ ፡ እንግዳ ፡ ትምህርት ፡ አምጥታ ፡ በሐዋርያት ፡ እምነት ፡ ላይ ፡ ያመጠች ፡ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መኾኗ ፡ ሲታወቅ ፡ እስክንድርያና ፡ ኢትዮጵያ፡ሌሎችም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ይህን ፡ ውሳኔ ፡ አንቀበለውም ፡ ቢሉ ፡ በዐመፁ ፡ ከሮም ፡ ጋራ ፡ አንተባበርም ፡ አሉ ፡ ያሰኛቸዋል ፡ እንጂ ፡ ዐመፁ ፡ ያሰኛቸዋልን ፡ አያሰኛቸውም ።

## ክ ፍ ል ፩ ።

## ደ ራ ሲ ው ።

በጉባኤው ፡ ውስጥ ፡ ስለተደረገው ፡ ያላቸው ፡ ታሪካዊ ፡ ስሕተት ፡

፲፪/ ኢትዮጵያውያኖቹ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ በኬልቄዶኑ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ የተነሣው ፡ ከጥንት ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የነበረውን ፡ ትምህርት ፡ ጉባኤዎች ፡ ስላበላሹትና ፡ ስለለወጡት ፡ ለመከላከል ፡ ጥሩውንም ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ያምናሉ ፡ ብለው ፡ በሚያጠራጥር ፡ እኳኋን ፡ ተናግረዋል።

## መ ላ ሽ ።

፲፪/ እርስዎ ፡ ራስዎ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍዎ ፡ በገጽ ፡ ፲፪ ፡ ፊተኞቹ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ያስተምራሉ ። ፪ኞቹ ፡ ግን ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ባንድ፡ አካል ፡ ሲሉ ፡ ያስተምራሉ ፡ ብለው ፡ መጻፍዎን ፡ አይዘነጉትም ።

ፊተኞች ፡ የተባሉ ፡ ከሐዋርያት ፡ እስከ ፡ ጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ ያሉ ፡ አበው ፡ መኾናቸውን ፡ ኋለኞች ፡ የተባሉትም ፡ በጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ የተሰበሰቡ ፡ መኾናቸውን ፡ አይክዱም ። ዲዮስቆሮስም ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ብሎ ፡ የወሰነውን ፡ ውሳኔ ፡ አልቀበልም ፡ በማለት ፡ መለየቱ ፡ ግልጽ ፡ ነገር ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ከጥንት ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ ከሐዋርያት ፡ ተያይዞ ፡ የመጣውን ፡ ባህል ፡ ስለለወጠው ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ይህንን ፡ ባህል ፡ አልቀበልም ፡ ብሎ ፡ ተለየ ፡ ቢባል ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የሚያስተባብሉብት ፡ ምክንያት ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ የኬልቄዶን ጉባኤ ፡ የወሰነው ፡ ሌላ ፡ ባህል ፡ ነው ፡ ይላሉን ፡ ወይስ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ተቀብሎታል ፡ አልተለየም ፡ ይላሉ ።

## ደ ራ ሲ ው ።

፲፫/ በጉባኤው ፡ የተሰበሰቡ ፡ አባቶች ፡ ያወገዙት ፡ ያባረሩትና ፡ ያሳደዱት ፡ እርሱ ፡ ላቀረበላቸው ፡ ሐተታዎች ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ እስከ ፡ ማጣት ፡ ድረስ ፡ ስላሳፈራቸው ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ ብለው ይህንም ፡ በማስተባበል ፡ ዐይነት ፡ ተናግረዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፫/ የዚህን ፡ እንጋገር ፡ እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ ለማግኘት ፡ ርስዎ ፡ የጻፉልንን ፡ ይህን ፡ መጻፍ፡ በሰፊው ፡ መመርመር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። እነሆ ፡ እርስዎ ፡ ከጉንጻጉንጺ ፡ አገኘሁት ፡ ብለው ፡ በ፫ኛ ፡ ምዕራፍ ፡ በ፹፩ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ የጻፉት ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ መርቅያን ፡ በነገሠበት ፡ ልዮን ፡ በሮም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትነት ፡ በተሾመ ፡ ጊዜ ፡ አውጣኪ ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋው ፡ ረቂቅ ፡ ነው ፡ እንደኛ ፡ ሕማም ፡ አይሰማውም ፡ ስላለ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ፮፻፴፮ ፡ መምህራን ፡ ተሰበሰቡ ፤ እነሱም ፡ በ፫ኛው ፡ ጉባኤ ፡ የተሰበሰቡ ፡ አበው ፡ በቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ አፈ ፡ ጉባኤነት ፡ ንስጥሮስን ፡ ያወገዙትን ፡ ውግዘት ፡ ፈርተው ፡ ንስጥሮስ ፡ የክርስቶስ ፡ አካሉ ፡ አንዱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተወለደው ፡ አንዱ ፡ ከማርያም ፡ የተወለደው ፡ ኾኖ ፡ ኹለት ፡ ነው ።

እኒህ ፡ ኹለቱ ፡ በተዋሕዶ ፡ ሳይኾን ፡ በመቃረብ ፡ አንድ ፡ ኾኑ ፡ ያለውን ፡ ብቻ ፡ አስቀርተው ፡ ከቄርሎስ ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ማለትን ፡ ጨምረው ፡ የንስጥሮስ ፡ ትምህርት ፡ ኹለት ፡ ጠባይዕ ፡ ኹለት ፡ ፈቃድ ፤ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ ሥምረት ፡ አንዱ ፡ የመለኮት ፡ አንዱ ፡ የትስብእት ፡ በኹለት ፡ ስልት ፡ አንዱ ፡ የመለኮትን ፡ አንዱ ፡ የትስብእትን፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ አንዱ ፡ ተአምራት ፡ ያደርጋል ፡ አንዱ ፡ መከራ ፡ ይቀበላል ፡ ስለዚህ ፡ ትስብእት ፡ ከመለኮት ፡ ያንሳል ፡ ብለው ፡ ወሰኑ ፡ የልዮንም ፡ ጦማር ፡ እንደዚሁ ፡ ትላለች ፡ ብሎ ፡ ይተርካል ።

ይህም ፡ ውሳኔ ፡ ርግጠኛ ፡ የኬልቄዶን ፡ ውሳኔ ፡ መኾኑን ፡ በ፹፯ኛ ፡ ገጽ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ በ፪ ፡ ባሕርያት ፡ ብለው ፡ በ፶፲፰ኛው ፡ ገጽ ፡ ኹለቱ ፡ ፈቃዶች ፡ አልተጣሉም ፡ መቸውንም ፡ አይጣሉም ፡ የትስብእቱ ፡ ባሕርይ ፡ ለመለኮቱ ፡ ባሕርይ ፡ መቸውንም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተገዛ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አረጋግጠዋል ።

እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ውሳኔ ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ መኾኑን ፡ በርስዎ ፡ ጽሑፍ ፡ ካረጋገጥን ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ምርመራ ፡ እንራመድ ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ይኸው ፡ እርስዎ ፡ የጠቀሱት ፡ መጽሐፍ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ የንጉሡን ፡ ቁጣ ፡ የማኅበሩን ፡ ብዛት ፡ ሳይፈራ ፡ ተነሥቶ ፡ ይህ ፡ እንግዳ ፡ ልማድና ፡ ባህል ፡ ምንድን ፡ ነው ። እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ ሃይማኖታችንን ፡ የሚክድ ፡ አለ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ በቄርሎስ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተደረገው ፡ ጉባኤ ፡ ይከፈትና ፡ እንከራከር ። አባቶቻችን ፡ ያቆዩንን ፡ ሃይማኖት ፡ ለመለወጥ ፡ ኹላችሁም ፡ መክራችሁ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እኔ ፡ ይችን ፡ ጉባኤ ፡ አወግዛታለሁ ፡ አለ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡም ፡ ኤጲስቆጶሳቱም ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ይህ ፡ የምትሰማው ፡ ቃል ፡ ልዮን፡ የላከው ፡ የሃይማኖት ፡ ጦማር ፡ ነው ፡ ልዮንም ፡ በጴጥሮስ ፡ ወንበር ፡ የተቀመጠ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ነው ፤ የጴጥሮስም ፡ ወንበር ፡ ካንተ ፡ ወንበር ፡ ይበልጣል ፡ ለምን ፡ አትቀበልም ፡ አሉት ።

ዲዮስቆሮስም ፡ ሲመልስ ፡ ቀድሞ ፡ ሳጥናኤል ፡ ከመላእክት ፡ ኹሉ ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ነበረ ፡ ሃይማኖቱን ፡ ቢክድ ፡ ግን ፡ ከመዓርጉ ፡ ተዋርዶ ፡ በመንጸፈ ፡ ደይን ፡ ወደቀ ፡ እንደ ዚኹውም ፡ ሐዋርያት ፡ ባስተማሩን ፡ ትምህርት ፡ ጸንቶ ፡ ከተገኘ ፡ በሊቀ ፡ ሐዋርያቱ ፡ በጴጥሮስ ፡ ወንበር ፡ የተቀመጠው ፡ አለቃየ ፡ ነው ፡ የሐዋርያትን ፡ ቃል ፡ ለውጦ ፡ ከሃይማኖት ፡ ከወጣ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሳጥናኤል ፡ ከመዓርጉ ፡ ይዋረዳል ፡ እንጂ ፡ የኔ ፡ አለቃ ፡ ሊኾን ፡ አይችልም ፡ አለ ።

ከዚህ ፡ አያይዞ ፡ ባንድ ፡ በክርስቶስ ፡ ፪፡ ፍና፡ማለት ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ እስኪ ፡ ንገሩኝ ፡ ክርስቶስን በቃና ፡ ዘገሊላ ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ ቤት ፡ የጠሩት ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ነውን ፡ እንደ ፡ አምላክ ፡ አላቸው ።

እነርሱም ፡ እንደሰው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አምላክስ ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ አይጠራም ፡ አሉት ። እርሱም ፡ መልሶ ፡ ወኀውንሳ ፡ ወይን ፡ ያደረገው ፡ እንደ ፡ አምላክ ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ።

እነርሱም ፡ እንደ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰውስ ፡ ውኃውን ፡ ወይን ፡ ሊያደርግ ፡ አይችልም ፡ አሉት ፡ ዲዮስቆሮስም ፡ ሲመልስ ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ ቤት ፡ የተጠራው ፡ ውኃውንም ፡ ወይን ፡ ያደረገው፡ አንድ ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሌላ ፡ የለምና ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ ቤት ፡ የተጠራው ፡ እርሱ፡ ውኃውንም ፡ ወይን ፡ እንዳደረገው ፡ እነሆ ፡ ታወቀ ፡ ተረዳ ። የተጠራው ፡ እርሱ ፡ ውኃውን ፡ ወይን ፡ አደረገ ፡ ካላችሁ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ ፈቃድ ፡ ብላችሁ ፡ ከኹለት ፡ ልትከፍሉት ፡ አይቻልም ።

ትንሽ ፡ ቆይታችሁ ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ የተጠራው ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ ውኃውን ፡ ወይን ፡ ያደረገ ፡ መለኮት ፡ ነው ፡ አትበሉ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ ቤት ፡ የተጠራው ፡ ውኃውን ፡ ወይን ፡ አደረገ ፡ የምትሉ፡ ከኾነ ፡ መልካም ፡ ነው ። ከዚህ ፡ አልፋችሁ ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ ቤት ፡ የተጠራ ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ ውኃውን፡ ወይን ፡ ያደረገ ፡ መለኮት ፡ ነው ፡ የምትሉ ፡ ከኾነ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ንግግር ፡ ንስጥሮስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተወለደው ፡ ተአምራት ፡ ያደርጋል ፡ ከማርያም ፡ የተወለደው ፡ ግን ፡ መከራ ፡ ይቀበላል ፡ ብሎ ፡ ያስተማረውን ፡ ትምህርት ፡ የመሰለ ፡ ነው ።

እናንተም ፡ እንዲህ ፡ የምትሉ ፡ ከኾነ ፡ መለኮት ፡ የሚገባውን ፡ የመለኮትን ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ፤ የማይገባውን ፡ የትስብእትን ፡ ሥራ ፡ የማይሠራ ፡ ከኾነ ፡ ትስብእትም ፡ እንደዚሁ ፡ የሚገባውን ፡ የትስብእትን ፡ ሥራ ፡ የሚሠራ ፡ የማይገባውን ፡ የመለኮትን ፡ ሥራ ፡ የማይሠራ ፡ ከኾነ ፡ መለኮትም ፡ ትስብእትም ፡ በየራሳቸው ፡ ተለያይተው ፡ በኹለት ፡ መንገድ ፡ መሔዳቸው ፡ ነው ።

እንዲህ ፡ ከኾነ ፡ ተዋሕዶ ፡ ወዴት ፡ አለ ፡ እስኪ ፡ ንገሩኝ ፡ ለትስብእትስ ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ ቤት ፡ መጠራት ፡ ልማዱ ፡ ነውና ፡ ይገባዋል ፡ ኸረ ፡ መለኮት ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ ቤት ፡ መግባት ፡ የማይገባው ፡ ሲኾን ፡ ለምን ፡ ተጠራ ። ትስብእት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መለኮት ፡ አልተጠራም ፡ አልሔደም ፡ እንዳትሉም ፡ ትስብእት ፡ ብቻውን ፡ ውኃውን ፡ ወይን ፡ ሊያደርግ ፡ አይችልም ፡ መለኮት ፡ ካልሔደ ፡ ውኃውን ፡ ወይን ፡ ማን ፡ አደረገው ፡ ትስብእት ፡ ሲሔድ ፡ መለኮት ፡ ሔደ ፡ ብትሉ ፡ ግን ፡ እነሆ ፡ መለኮት ፡ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ አገኘነው ፡ ማለታችሁ ፡ ነውና ፡ መለኮት ፡ ከትስብእት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ ቤት ፡ ሲሔድ ፡ ትስብእትም ፡ ከመለኮት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ኾኖ ፡ ውኃውን ፡ ወይን ፡ ሲያደርግ ፡ አግኝተነዋልና ፡ ከዛሬ ፡ ጀምራችሁ ፡ ይህን ፡ ባህላችሁን ፡ ተው ።

ደግሞ ፡ በዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በምራቁ ፡ ጭቃ ፡ ለውሶ ፡ ዕውር ፡ ኾኖ ፡ የተወለደውን ፡ ሰው ፡ ግንባሩን ፡ ቀብቶ ፡ ዐይን ፡ እንደ ፡ ፈጠረለት ፡ ተጽፏል ። ትስብእት ፡ በደረቅ ፡ ግንባር ፡ ዐይን ፡ አልፈጠረም ፡ የምንል ፡ ከኾነ ፡ መለኮት ፡ ጭቃ ፡ የሚለውስበት ፡ ምራቅ ፡ አለውን፡ የለውም ፡ የሌለውም ፡ ከኾነ ፡ እነሆ ፡ ትስብእት ፡ በምራቁ ፡ ዐይን ፡ እንደፈጠረ ፡ ዐወቅን ፡ ተረዳን ። ትስብእት ፡ በምራቁ ፡ ዐይን ፡ ሲፈጥር ፡ ከቻለ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ ፈቃድ ፡ የምትሉት ፡ ወዴት ፡ አለ ፡ በዚህ ፡ ተዋሕዶ ፡ አንድነት ፡ መካከል ፡ ይህ ፡ ምራቁን ፡ እንትፍ ፡ ያለ ፡ (የተፋ) ፡ ነው፡ ይህ ፡ ያዳነው ፡ ነው ፡ (ማለት) ፡ ምራቁን ፡ የተፋ ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ ያዳነው ፡ ግን ፡ ይኸኛው ፡ ነው ፡ ብሎ መለያየት ፡ የለም ። የፈጣሪያችን ፡ የአማኑኤል ፡ የተዋሕዶው ፡ ምሥጢር ፡ ከንቱ ፡ ሐሰት ፡ እንዳይኾን ፡ ይህ ፡ የመለኮት ፡ ነው ፡ ይህ ፡ የትስብእት ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ልንለያይ ፡ አይገባንም ።

ወደ ፡ ሠርግ ፡ ቤት ፡ የተጠራው ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ ውኃውን ፡ ወይን ፡ ያደረገው ፡ እርሱ ፡ ሰው ፡ እንደመኾኑ ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ ቤት ፡ ተጠራ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ ተአምራት ፡ አደረገ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ ሲወለድ ፡ በቡትት ፡ ተጠቀለለ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ ከሰብአ ፡ ሰገል ፡ እጅ፡

መንሻ ፡ ተቀበለ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ ተርቦ ፡ የበለስን ፡ ፍሬ ፡ ሊበላ ፡ ፈለገ ፡ አምላክ ፡ እንደ መኾኑ ፡ ፳ ፡ እንጀራ ፡ ለ፭ሺ ፡ ሰው ፡ አበላ ፡ እንደ ፡ ሰውነቱ ፡ መንገድ ፡ በመሔድ ፡ ደከመ ፡ እንደ፡ አምላክነቱ ፡ ባሕሩን ፡ በእግሩ ፡ እየጠቀጠቀው ፡ ሔደ ።

ይህን ፡ ኹሉ ፡ ያደረገ ፡ አንዱ ፡ እርሱ ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ከአብ፡ያለ፡እናት፡ የተወለደው ፡ አንድ ፡ ልደት ፡ ኹለተኛው ፡ ድኅረ ፡ ዓለም ፡ ከእመቤታችን ፡ ያለአባት ፡ የተወለደው ፡ አንድ ፡ ኾኖ ፡ ኹለት ፡ ልደት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በፈቃድ ፤ በባሕርይ ፡ በጠባይዕ ፡ ኹለት ፡ አይደለም ፡ ኹለት ፡ አይባልም ና ፡ እናንተ ፡ የኬልቄዶን ፡ ሰዎች ፡ ስሕተታችሁን ፡ ከእናንተ ፡ አርቁ ፡ አላቸውና ፡ ልዮን ፡ የላከትን ፡ ጦማር ፡ ቀደዳት ፡ ጉባኤውንም ፡ አወገዘ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ በጥፊ ፡ መቱት ፡ ጽሕሙንም ፡ ነጩት ጥርሱን ፡ ሰበሩት ፡ ደሴተ ፡ ጋግራ ፡ አጋዙት ፡ በዚያው ፡ ዐረፈ ፡ ይላል ።

እንግዲህ ፡ ይህን ፡ እኳኋን ፡ ስንመለከተው ፡ እርስዎ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ለመሰከሩለት፡ ፪ ፡ ባሕርይ ፡ ፪ ፡ ፈቃድ ፡ ለሚለው ፡ ለኬልቄዶኑ ፡ ውሳኔ ፡ ይህ ፡ የዲዮስቆሮስ ፡ መልስ ፡ ነው ፡ ተብሎ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የሰማነው ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ ትክክለኛ ፡ መልሱ ፡ መኾኑን ፡ ተረድተናል ። በዚሁም ፡ ላይ ፡ ጉባኤዎቹ ፡ ለዲዮስቆሮስ ፡ የመለሱለት ፡ ኀይለ ፡ ቃል ፡ እንደሌለ ፡ ተመልክተናል ።

ርስዎም ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍዎ ፡ ውስጥ ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ኢትዮጵያውያኖቹን ፡ የዲዮስቆሮስን ፡ ስም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ በኬልቄዶኑ ፡ ጉባኤና ፡ በልዮን ፡ ጳጳስ ፡ ላይ ፡ ያልኾነ ውን ፡ የሐሰት ፡ ሐሜት ፡ እየፈጠሩ ፡ አወሩባቸው ፡ ደግሞም ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ የሚያስነቅፉ ፡ ኑፋቄያቸውንም ፡ የሚያስመሰግኑ ፡ ብዙ ፡ ተአምራቶች ፡ ተፈጽመዋል ፡ ሲሉ ፡ ራሳቸው ፡ ፈጥ ረው ፡ በማውራት ፡ አታለልዋቸው ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ ቢላቸው ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ መለ ሱለት ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ተናግረው ፡ መልስ ፡ አሳጡት ፡ ብለው ፡ ወይንም ፡ በጠቅላላው ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ እነጋገር ፡ በጉባኤው ፡ ላይ ፡ አልተነገረም ።

ዲዮስቆሮስም ፡ የተናገረው ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ ጉባኤውም ፡ የመለሰ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ መቃወሚያ ፡ አልጻፉም ፡ ማናቸውም ፡ የተነገረ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ መቃወሚያ ፡ ቀርቦ በት ፡ ካልተለወጠ ፡ በቀር ፡ ቀዋሚ ፡ እውነት ፡ ኾኖ ፡ መቅረት ፡ አለበት ፡ በዚህ ፡ መሠረት ፡ እኛም ፡ በዚህ ፡ነገር ፡ ተቃዋሚ ፡ ስላልቀረበበት ፡ ቅዱስ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የተሰበሰቡ ፡ አባቶችን ፡ መልስ ፡ እስከ ፡ ማሳጣት ፡ ድረስ ፡ ደርሶ ፡ አሳፍሯቸዋል ፡ ለማለት ፡ ችለናል ።

## ደ ራ ሲ ው ።

፲፬/ ኋላም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የኬልቄዶኑ ፡ ጉባኤ ፡ በኤፌሶን ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነውን ፡ እፍርሶ ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ አስተምሯል ፡ ብለው ፡ ያምናሉ ፡ ሲሉ ፡ በማጠራጠር ፡ ተናግረዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፭/ አሁን ፡ ይህ ፡ የሚናገሩት ፡ ነገር ፡ በላይኛው ፡ አንቀጽ ፡ ቅዱስ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ወደ ፡ ሥርዓ ቤት ፡ የተጠራ ፡ ትስብእት ፡ ነው ፤ ወኃውን ፡ ወይን ፡ ያደረገ ፡ መለኮት ፡ ነው ፡ የምትሉ ፡ ከኾነ ፡ ንስ ጥሮስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ስለኾነ ፡ ከማርያም ፡ የተወለደው ፡ መከራ ፡ ይቀበላል ፡ ከአብ ፡ የተወለደው ፡ ተአምራት ፡ ያደርጋል ፡ ብሎ ፡ ካስተማረው ፡ ትምህርት ፡ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ ነው ። ለዚህ ፡ መልሱ ፡ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ ስለተሰጠ ፡ አሁን ፡ ኹለተኛ ፡ አላስፈለገም ።

## ደ ራ ሲ ው ።

፲፮/ ከዚህም ፡ በስተቀር ፡ ልዮን ፡ የሮማው ፡ ጳጳስ ፡ የአውጣኪ ፡ ወገን ፡ ኾኗል ፡ ስለዚህም ፡ አይዞህ ፡ ባህልህን ፡ በመያዝ ፡ በርታ ፡ ሲል ፡ የማጽናናት ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፎ ፡ ልኮለታል ፡ ይላሉ ፡ ብለዋል

## መ ላ ሽ ።

፲፯/ ኢትዮጵያ ፡ የአውጣኪን ፡ ባህል ፡ ተቀባይ ፡ አለመኾኗን ፡ ርስዎ ፡ ራስዎ ፡ በ፸፩ ፡ ገጽ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የአውጣኪን ፡ ባህል ፡ ልስበክ ፡ ብሎ ፡ ገብቶ ፡ ሳይባረር ፡ የቀረ ፡ የለም ፡ ብለው ፡ እን ዲሁም ፡ በ፸፰ ፡ ገጽ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ትምህርት ፡ ለንስጥሮስ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ለአውጣኪም ፡ ባህል ፡ ፈጽሞ ፡ ተቃራኒ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አረጋግጠው ፡ መስክረውልናል ።

ስለዚህ ፡ የአውጣኪን ፡ ነገር ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ አግብተን ፡ የምንመለከተው ፡ ስለኾነ ፡ ቢጽፍለትም ባይጽፍለትም ፡ የኹለቱ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ፡ እኛን ፡ የማያገባን ፡ ስለኾነ ፡ ለዚህ ፡ መልስ ፡ ልሰጥበት ፡ አልፈለግሁም ።

## ድ ራ ሲ ው ።

፲፯/ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ታሪክ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አስተያየት ፡ ትልቅ ፡ ግምት ፡ ባላቸው በኹለት ፡ መጻሕፍቶቻቸው ፡ ተተርኮ ፡ እናገኘዋለን ፡ እኒህም ፡ መጻሕፍቶች ፡ አንደኛው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሃይማኖት ፡ ትምርት ፡ የሚገለጥበት ፡ ምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ የተባለው ፤ ኹለተኛ ፡ ከጉንዳጉንዲ የተገኘው ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የመጻሕፍቱን ፡ መገኛ ፡ ካስረዱ ፡ በኋላ ፡ ምሥጢረ ፡ ሥላሴ የተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ስለ ፡ ንስጥሮስና ፡ ስለ ፡ አውጣኪ ፡ ይናገራል ።

ሀ/ስለ ፡ ንስጥሮስ ፡ ሲናገር ፡ ንስጥሮስ ፡ የቍስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ነው ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እምነቱን ፡ ሲገልጽ ፡ ክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ ፈቃድ ፡ ኹለት ፡ ግብር ፡ ነው ፡ ተዋሕዶውም ፡ የፈቃድና ፡ የፍቅር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የባሕርይ ፡ አልኾነም ፡ እመቤታችን ፡ የወለደችው ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አምላክ ፡ አይደለም ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ በክርስቶስ ፡ ያደረበት ፡ እንደኾነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የጸጋ ፡ ልጅ ፡ ይኾናል ፡ እያለ ፡ ያስተምር ፡ ነበረ ።

የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ይህነን ፡ ሰምቶ ፡ ለታላቁ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ነግሮ ፡ በኤፌሶን ፡ ጉባኤ ፡ ተደረገ ፡ ፪፻ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ተሰበሰቡ ፡ የሮሙ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቅልስጢንም ፡ ስለ ፡ ሽምግልናው ፡ መምጣት ፡ ባይችለው ፡ ፪ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ፪ ፡ ቀሳውስት ፡ ልኮ ነበረ ።

የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ ከቃሉ ፡ ለመረዳት ፡ ና ፡ ብለው ፡ ቢልኩበት ፡ አልመጣም ፡ እለ ፡ በደብዳቤ ፡ ቢከራከሩትም ፡ አሻፈረኝ ፡ አልሰማም ፡ ብሎ ፡ ቢመልስ ፡ እርሱንም ፡ ሃይማኖቱንም ፡ ገዝተው፡ ከሹመቱም ፡ ሽረው ፡ ስደት ፡ ፈረዱበት ፡ በግብጽ ፡ ውስጥ ፡ አክሚም ፡ ከምትባል ፡ ከተማ ፡ ተሰዶ ፡ ሞተ ፡ ይላል ፡ ብለው ፡ ጠቅሰው ፡ ተርከዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፯/ ይህን ፡ ታሪክ ፡ ስንኳንስ ፡ ሌላ ፡ ተቀዋሚ ፡ ሊኖረው ፡ እርስዎም ፡ ቢኾኑ ፡ ይህ ፡ ታሪክ ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ንስጥሮስም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አልካደ ፡ በኤፌሶንም ፡ ጉባኤ፡አልተደረገ ፡ ብለው ፡ በጭራሽ ፡ አልካዱም ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ የንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ፡ ብለው ፡ የጻፉት ፡ ማስተባበያ ፡ ቃል ፡ የለም ፡ ስለዚህ ፡ ማስተባበያ ፡ ያልቀረበበት ፡ ነገር ኹሉ ፡ በእውነትነት ፡ ጸንቶ ፡ ይቀራል ፡ ብዬ ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ገለጽኩልዎ ፡ ይህም ፡ ታሪክ ፡ ተቃራኒ ፡ የሌለው ፡ ስለኾነ ፡ እውነተኛ ፡ ታሪክ ፡ አድርገን ፡ ተቀብለነዋል ።

በዚሁ ፡ መሠረት ፡ የኬልቄዶንን ፡ ውሳኔ ፡ ጠንክረን ፡ የምንቃወመው ፡ ይህ ፡ የኤፌሶን ፡ ጉባኤ አውግዞ ፡ ከለየው ፡ ከንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ማለትን ፡ ብቻ ፡ አስቀርቶ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ፪ ፡ ፈቃድ ፡ ፪ ፡ ግብር ፡ የሚለውን ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ ተቀባይ ፡ ኾኖ ፡ ስላገኘነው ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ንስጥሮስ ፡ ተዋሕዶው ፡ የፈቃድ ፡ የፍቅር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የባሕርየ ፡ አይደለም ፡ እመቤታችን ፡ የወለደችው ፡ ሰው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አምላክ ፡ አይደለም ፡ የሚለውን ፡ ባህል ፡ ይህ ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ተቀባይ ፡ መኾኑን ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍዎ ፡ ለባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእቱ ፡ መቻም ፡ ቢኾን ፡ እንደ ፡ ተገዛ ፡ ነው ፡ ኹለቱ ፡ ፈቃዶች ፡ አይጣሉም ፡ ብለው ፡ በ፺፲፰ ገጽ ፡ ገልጠውታል ፡ ስለዚህ ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ ከንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ በምንም ፡ ያልተለየ ፡ መኾኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

## ድ ራ ሲ ው ።

፲፰/ ስለ ፡ አውጣኪ ፡ ሲናገር ፡ አውጣኪ ፡ የቍስጥንጥንያ ፡ ባለገዳም ፡ ነው ፡ እርሱ ፡ የጌታችን ፡ ሥጋ ፡ ረቂቅ ፡ ነው ፡ ሕማም ፡ መከራ ፡ አያገኘውም ፡ አይሰማውም ፡ እያለ፡ ያስተምር፡ ነበረ ። አውሳብዮስ ፡ የተባለ ፡ የንስጥሮስ ፡ ጠበቃ ፡ የነበረ ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ በፍላብያኖስ ፡ ላይ ፡ ከሰሰው ፡ የቍስጥንጥንያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ፍላብያኖስ ፡ ይህነን ፡ የአውጣኪን ፡ ክህደት ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ፴ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሰብስቦ ፡ አውጣኪን ፡ አውግዞ ፡ ለየው ። ነገር ፡ ግን ፡ እኒህ ፡ የተሰበሰቡት ፡ ፴ው ፡ ኤጲስቆጶሳትና ፡ ፍላብያኖስ ፡ የአውጣኪን ፡ ቱሳሔ ፡ አጠፉን ፡ ሲሉ ፡ የንስጥሮስን ፡ ክህደት ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ አደሱት ፡ አውጣኪም ፡ ወደ ፡ ሮሙ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወደ ፡ ልዮን ፡ ዘንድ ፡ አለአገባብ ፡ ተገዘትኩ ፡ ብሎ ፡ ላከ ።

ልዮንም ፡ ይድረስ ፡ ከከበረ ፡ ልጄ ፡ ከአውጣኪ ፡ የላክህልኝን ፡ ቃል ፡ አወቅሁት ፡ እነዚያ ፡ ደፋሮች ፡ የንስጥሮስን ፡ ኑፋቄ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ማሳደሳቸውን ፡ አገኘሁት ፡ አንተ ፡ ግን ፡ አይዞህ ፡ ባለህበት

ጥና ፡ በቀናች ፡ ሃይማኖት ፡ አምላክ ፡ ይጠብቅህ ፡ ነገርክን ፡ እስክጨርስልህ ፡ ድረስ ፡ በርታ ፡ ተጸፈ በየዚራን ፡ ወር ፡ በ፬፻፶ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈለት ።

አውጣኪ ፡ ወደ ፡ ልዮን ፡ እንደ ፡ ላከ ፡ እንዲሁም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ያለ ፡ ኃጢአት ፡ ተገዝትኩ ፡ ፍርድ ፡ ይታይልኝ ፡ ሲል ፡ አቤቱታውን ፡ አቀረበ ። ንጉሥ ፡ ቴዎዶስዮስም ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከእስክንድርያ ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ ዮልያኖስ ፡ ዘኢየሩሳሌምን ፡ ድምኑስ ፡ ዘአንጾኪያን ፡ እስጢፋኖስ ፡ ዘኤፌሶንን ፡ አስጠራቸው ፡ እነርሱም ፡ እንደ ፡ መጡ ፡ ፻፷ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሰብስበው ፡ አውጣኪን ፡ የገዘትክበትን ፡ ምክንያት ፡ መጥተህ ፡ ንገረን ፡ ብለው ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ከፍላብያኖስ ፡ ዘንድ ፡ ላኩበት ። ፍላብያኖስም ፡ ወደ ፡ ልዮን ፡ ዘሮም ፡ ዘንድ ፡ ተማጽኘብሃለሁ ፡ እድነኝ ፡ ሲል ፡ ላከና ፡ ጉባኤው ፡ ለላከበት ፡ አልመጣም ፡ እንቢኝ ፡ ብሎ ፡ ቀረ ።

ልዮንም ፡ ለአውጣኪ ፡ አይዞህ ፡ ብሎ ፡ እንደላከበት ፡ ለፍልብያኖስም ፡ አይዞህ ፡ ብሎ ፡ ላከበት ፡ ፍላብያኖስም ፡ የልዮንን ፡ ቃል ፡ ተስፋ ፡ በማድረግ ፡ ጉባኤውን ፡ አልመጣም ፡ ብሎ ፡ ቀረ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከዲዮስቆሮስ ፡ ጋራ ፡ የተሰበሰቡ ፡ ፻፷ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ፍላብያኖስ ፡ መጥቼ ፡ የገዘትኩበትን ፡ ምክንያት ፡ አላስረዳም ፡ ስላላቸው ፡ አውጣኪን ፡ አስጠርተው ፡ ሃይማኖቱን ፡ ጠየቁት ፡ እሱም ፡ ክህደቱን ፡ በልቡ ፡ አስቀምጦ ፡ ሃይማኖቴ ፡ የ፫፻፲፰ ፡ ሊቃውንት ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ነአምን ፡ በ፩ ፡ አምላክ ፡ ካለው ፡ ዠምሮ ፡ ሐመ ፡ ወሞተ ፡ ወተቀብረ ፡ ወተንሥአ ፡ እሙታን ፡ እስከሚለው ፡ ድረስ ፡ እያነበበ ፡ ሃይማኖቴ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ገለጸ ፡ ቱሳሔ ፡ ብዬ ፡ መናገሬን ፡ አላውቅም ፡ አለ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ የተሰበሰቡትን ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ምን ፡ ትላላችሁ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቃቸው ፡ ዮልያኖስ ፡ ዘኢየሩሳሌም ፡ አውጣኪ ፤ ከፊታችን ፡ የታመነበት ፡ ሃይማኖት ፡ የ፫፻፲፰ ፡ ሃይማኖት ፡ ነውና ፡ ከግዝቱ ፡ ይፈታ ፡ ከሹመቱ ፡ ይግባ ፡ አለ ፡ ድምኑስ ፡ ዘአንጾኪያም ፡ እኔ ፡ አስቀድሜ ፡ አውጣኪን ፡ መገዘቴ ፡ ፍላብያኖስ ፡ ቢልክብኝ ፡ ነው ፡ አሁን ፡ ግን ፡ በወረቀት ፡ ጽፎ ፡ ለእናንተ ፡ ያቀረበውን ፡ ሃይማኖት ፡ ብመለከተው ፡ በኒቅያ ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነው ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፡ አለ ።

እንዲሁም ፡ እስጢፋኖስ ፡ ዘኤፌሶን ፡ ከምእመናን ፡ ይቀላቀል ፡ አለ ፡ ከርሱም ፡ ቀጥሎ ፡ ጳላስዩስ ፡ ዘቂሳርያ ፡ ይግባ ፡ ሲል ፤ ፈረደ ፡ ከያገሩ ፡ የተሰበሰቡትም ፡ አበው ፡ ኹሉ ፡ እንደዚሁ ፡ ፈረዱ ፡ ከዚህ ፡ ኹሉ ፡ በኋላ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ተነሥቶ ፡ እናንተ ፡ እንዲህ ፡ ከፈረዳችሁ ፡ እኔም ፡ ይህን ፡ የተቀደሰው ፡ ጉባኤ ፡ የሰጠውን ፡ ፍርድ ፡ እቀበላለሁ ፡ አውጣኪም ፡ ከሹመቱ ፡ ይመለስ ፡ ከግዝቱ ፡ ይፈታ ስል ፡ ፈርጃለሁ ፡ አለ ።

ደግሞ ፡ የአውጣኪ ፡ መነኮሳት ፡ ጥፋታችንን ፡ ሳናውቅ ፡ ፍላብያኖስ ፡ ገዘተን ፡ ብለው ፡ ለጉባኤው ፡ አቤት ፡ አሉ ። ዲዮስቆሮስ ፡ ከጉባኤው ፡ ጋራ ፡ ኾኖ ፡ እናንተን ፡ እንጠረጥራችኋለን ፡ የምታምኑትን ፡ ሃይማኖት ፡ ግለጹልን ፡ አላቸው ፡ መነኮሳቱም ፡ ፫፻ ፡ በኒቅያ ፡ በወሰኑትና ፡ ፪ቱ ፡ ፺ ፡ ሊቃውንት ፡ በዚች ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ ከተማ ፡ በወሰኑት ፡ ሃይማኖት ፡ እናምናለን ፡ አሉ ።

ዲዮስቆሮስም ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ እንደ ፡ ቀሩት ፡ ቅዱሳን ፡ አበው ፡ እምነት ፡ ታምናላችሁን ፡ [illegible]ቸው ። መነኮሳቱም ፡ አዎን ፡ እናምናለን ፡ አሉ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዮልያኖስ ፡ ዘኢየሩሳሌም ፡ በእው[illegible] ፡ ሃይማኖት ፡ ካመኑ ፡ ከምእመናን ፡ ጋራ ፡ ይቀላቀሉ ፡ ሲል ፡ ፈረደ ።

[illegible] ፡ በኋላ ፡ የቀረው ፡ ጉባኤ ፡ ይህነን ፡ ፍርድ ፡ ተቀብለናል ፡ አሉ ። በመጨረሻም ፡ ቅዱስ [illegible]ኪንና ፡ የመነኮሳቱን ፡ ሃይማኖት ፡ መርምረን ፡ ከምእመናን ፡ ጋራ ፡ ይቀላቀሉ ፡ ካልን ፡ [illegible] ፡ በክርስቶስ ፡ እንዴት ፡ እንደሚያምን ፡ ሃይማኖቱን ፡ እንጠይቀው ፡ ብሎ ፡ [illegible] ፡ ፊት ፡ ቢጠይቀው ፡ በንስጥሮስ ፡ ሃይማኖት ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለቱን ፡ ገለጸ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የተሰበሰቡት ፡ [illegible] ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ፍላብያኖስን ፡ ገዝተው ፡ ከክህነቱ ፡ [illegible] ፡ እንደቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ እንደቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፡ ሥጋው ፡ ቃል ፡ ክርስቶስ ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የማይል ፡ ግዙተናል ፡ ሲሉ ፡ ወሰኑ ፡ ይላል ፡ ብለው ፡ ከመጽሐፉ ፡ ያገኙትን ፡ ታሪክ ፡ ከተረኩ ፡ በኋላ ፡ እንደሚታየው ፡ በተጠቀሰው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ስለኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ምንም ፡ አይነገርበትም ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ ስለኾነው ፡ ግርግርና ፡ ከጉባኤው ፡ ተካፋይ ፡ ስለኾኑት ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ እነጋገሩን ፡ ምንም ፡ ሳያጎላ ፡ ይናገራል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፮/ በዚህ ፡ እነጋገርዎ ፡ አሁን ፡ ከዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የጠቀሱትን ፡ ታሪክ ፡ ግርግር ፡ ነው ፡ እን ጋገሩ ፡ የኃላ ፡ አይደለም ፡ የሚል ፡ ስም ፡ ከመስጠትዎ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ የተጠቀሰው ፡ ጉባኤ ፡ መሰብ ሰቡና ፡ ይህን ፡ ውሳኔ ፡ መወሰኑ ፡ እርግጠኛ ፡ መኾኑን ፡ አረጋግጠውልናል ፡ ማለት ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ ጉባኤወና ፡ ውሳኔው ፡ እውነት ፡ መኾኑን ፡ ካረጋገጡልን ፡ የታሪኩን ፡ ኹናቴ ፡ ወደ መመርመር ፡ እንመለስ ።

የንስጥሮስ ፡ ክህደቱ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ፈቃድ ፡ ማለት ፡ እንደ ኾነ ፤ በኤፌሶንም ፡ የተሰበሰቡ ፡ ፪፻ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ በቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ አፈ ፡ ጉባኤነት ፡ አውግ ዘው ፡ የለዩት ፡ ይህንኑ ፡ ባህል ፡ መኾኑን ፡ ባለፈው ፡ አንቀጽ ፡ ተረድተናል ። እርስዎም ፡ በዚሁ ፡ በመ ጽሐፍዎ ፡ በ፲፪ኛ ፡ ገጽ ፡ ፊተኞች ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ያስተምራሉ ፡ ኹለተኞቹ ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ሲሉ ፡ ያስተምራሉ ፡ ብለው ፡ አረጋግጠውልናል ።

እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ታሪክ ፡ አውጣኪ ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋው ፡ ረቂቅ ፡ ነው ፡ ሕማም ፡ ሞት ፡ አይ ሰማውም ፡ ተዋሕዶውም ፡ ቱሳሔ ፡ ነው ፡ ቢል ፡ ፍላብያኖስ ፡ ፴ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ይዞ ፡ አወገዘው ፤ የን ስለኾነም ፡ አውጣኪ ፡ ቱሳሔ ፡ ያለውን ፡ ክህደት ፡ ለማጥፋት ፡ ሲል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ የን ስጥሮስን ፡ ክህደት ፡ አደሰው ፡ ብሎ ፡ እንዳስረዳን ፡ ይህ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሥር ፡ የሰደደና ፡ ያቆጠቆጠ ፡ በፍላብያኖስ ፡ ጊዜ ፡ መኾኑ ፡ ነው ። ቱሳሔም ፡ ማለት ፡ መቀላቀል ፡ መደባለቅ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ለምሳሌ ፡ ቡንና ፡ ወተት ፡ በቀላቀልዋቸው ፡ ጊዜ ፡ ቡን ፡ ጥቁረቱን ፡ ለቆ ፡ ወደነጭነት ፡ ይሳባል ፡ ወተትም ፡ ነጭነቱን ፡ ለቆ ፡ ወደ ፡ ጥቁረት ፡ ይሳባል ፤ በመካከላቸው ፡ ሌላ ፡ መልክ ፡ ይፈ ጠራል ፡ ሌላ ፡ ጣዕም ፡ ይወለዳል ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ እንደአውጣኪ ፡ ባህል ፡ የክርስቶስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቱሳሔ ፡ ነው ፡ የተባለ ፡ እንደኾነ ፡ መለኮት ፡ መለኮትነቱን ፡ ለቆ ፤ ትስብእትም ፡ ትስብእትነቱን ፡ ለቆ ፡ በመካከላቸው ፡ ሌላ ፡ ሕማም ፡ ሞት ፡ የማይስማማው ፡ ረቂቅ ፡ ሥጋ ፡ ኾነ ፡ ከማለት ፡ ያደርሳል ።

እንዲህም ፡ ከኾነ ፡ መጻሕፍት ፡ ኹሉ ፡ ናጽንዕ ፡ አሚነ ፡ ቦቱ ፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቲነ ዘኢይክል ፡ ሐሚመ ፡ ለድካምነ ፡ ዳዕሙ ፡ ምኩር ፡ በኵሉ ፡ አምሳሊነ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ባሕ ቲታ ፡ ዕብ ፡ ፬ ፡ ፲፬—፲፭ ።

ሊቀ ፡ ካህናታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከኃጢአት ፡ በቀር ፡ እንደኛ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ እኛን ፡ መስሎ ፡ በእኛ ፡ በደረሰብን ፡ ጸዋትወ ፡ መከራ ፡ ኹሉ ፡ የተፈተነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የኛን ፡ ድካም ፡ ለማጥፋት ፡ እኛን ፡ ለማበርታት ፡ መከራ ፡ መቀበል ፡ የማይቻለው ፡ አይደለም ፡ እያሉ ፡ የተናገሩት ኹሉ ፡ ከንቱ ፡ ሐሰት ፡ ኾኖ ፡ መቅረቱ ፡ ነው ።

ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ ፈቃድ ፡ ማለትም ፡ የክርስቶስን ፡ ተዋሕዶ ፡ ኅድረት ፡ ወይም ፡ ተላጽቆ ፡ ተቃርቦ ፡ ያደርገዋል ፡ እንጂ ፡ ፍጹም ፡ ተዋሕዶ ፡ ሊያደርገው ፡ አይችልም ።

ተላጽቆ ፡ ተቃርቦ ፡ ማለትም ፡ የዕንጨትና ፡ የብረት ፡ ሠራተኛ ፡ ዕንጨቱን ፡ ጠርቦ ፡ አለዝቦ ፡ ብረቱን ፤ ሞርዶ ፡ አስማምቶ ፡ በምስማር ፡ ቢያያይዛቸው ፡ ለጊዜው ፡ አንድ ፡ ይኾናሉ ፡ ምስማሩ ቢነቀል ፡ ይለያያሉ ፤ እነዚህ ፡ ተዋሐዱ ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ፡ የክርስቶስንም ፡ ተዋሕዶ ፡ እንደ ዚህ ፡ ነው ፡ ያልን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወንጌላዊ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ያለው ፡ ታበለ ፡ ውሸት ፡ ኾነ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ከነርሱ ፡ በፊት ፡ በሮምም ፡ በእስክንድርያም ፡ የነበሩ ፡ አባቶቻችን ፡ ግን ፡ የክርስቶስ ፡ ተዋሕዶ ፡ እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ ኅድረት ፡ ወይም ፡ ተላጽቆ ፡ ተቃርቦ ፡ እንደ ፡ አውጣኪ ፡ ቱሳሔ ፡ ሳይኾን ፡ እንደ ነፍስና ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ የከዊን ፡ በተፀቅቦ ፡ መኾኑን ፡ ጠንቅቀው ፡ አስረድተውናል ።

የሮምያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡሊድስ ፡ (ሐፖሊቶስ) በሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ወዘተወልደ ፡ እግ ርያም ፡ ድንግል ፡ እምድኅረ ፡ ተሰምየ ፡ ፩ ፡ ዋሕደ ፡ ውእቱሙ ፡ ዘቦቱ ፡ ኮነ ፡ ኵሉ ፡ ፩ ፡ ህላዌ ፡ ወ፩ ፡ አካል ፡ ውእቱ ፡ ወአልቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ዘይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፪ ፡ አልቦ ፡ ለሥጋሁ ፡ ህላዌ ፡ ፍሉጥ ፡ እመ ለኮቱ ፡ ኀበ ፡ ገጸ ፡ ፍና ፡ ወኢለመለኮቱ ፡ አልቦቱ ፡ ህላዌ ፡ ፍሉጥ ፡ እምትስብእቱ ፡ ኀበ ፡ ገጸ ፡ ፍና ፡ አላ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ዘ፩ ፡ ህላዌሁ ፡ ከማሁ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘኮነ ፡ በአርዓያ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።

ሶበሰ ፡ ኢያእመርዎ ፡ በተዋሕዶ ፡ ናሁ ፡ ይደልዎሙ ፡ ዓዲ ፡ ይክፍልዎ ፡ ለብእሲ ፡ ኀበ ፡ ብዙኅ ፡ ወይበልዎ ፡ ከመ ፡ ቦቱ ፡ ህላዌያት ፡ ብዙኃን ፡ እስመ ፡ ሥጋ ፡ እስትጉቡእ ፡ ውእቱ ፡ እምብዙኅ ፡ እም

ሳላት ፡ እምነ ፡ አዕፅምት ፣ ወአምትንት ፡ ወአሥራው ፡ ወሥጋ ፡ ወማዕስ ፡ ወአጽፋር ፡ ወፀጉር ፣ ወደም ፡ ወመንፈስ ፡ ወእሉ ፡ ኵሉ ፡ ፍሉጣን ፡ በበይናቲሆሙ ፡ ወዳዕሙ ፡ በአማን ፡ ፩ ፡ ህላዌ ፡ ውእቱ ፡ ወከማሁ ፡ መለኮትሂ ፡ ወትስብእት ፡ ፩ውእቱ ፡ ወኢይትከፈል ፡ ኀበ ፡ ፪ ፡ ህላዌ ።

ከማርያም ፡ የተወለደ ፡ እርሱ ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ ከኾነ ፡ በኋላ ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ የተፈጠረበት፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ኹለትነት ፡ መከፈል ፡ የለበትም ። በሰው ፡ አምሳል ፡ ሰው ፡ የኾነ ፡ ክርስቶስ ፡ ባሕርዩ ፡ አካሉ ፡ አንድ ፡ እንደኾነ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለትስብእቱ ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ ከመለኮቱ ፡ የሚለይበት ፡ አካል ፡ ባሕርይ ፡ ለመለኮቱም ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ ከትስብእቱ ፡ የሚለይበት ፡ አካል ፡ ባሕርይ ፡ የለውም ።

በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ የኾነ ፡ ክርስቶስን ፡ ባንድነት ፡ የማያውቁት ፡ ከኾነስ ፡ ሰውም ፡ ሥጋው ፡ ከአጥንት ፡ ከጅማት ፡ ከሥጋ ፡ ከደም ፡ ከጥፍር ፣ ከጠጕር ፣ ከቁርበት ፡ ከብዙ ፡ ነገር ፡ የተጠራቀመ ፡ ነውና ፡ ብዙ ፡ አካል ፡ ከሥጋ ፡ ከነፍስ ፡ የተዋሐደ ፡ ነውና ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ከብዙ ሊከፋፍሉት ፡ ይገባቸዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የተለያዩ ፡ ሲኾኑ ፡ በእውነት ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ልዩዎች ፡ አይደሉም ፡ እንደዚኸውም ፡ መለኮትና ፡ ትስብእትም ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ኹለትነት ፡ ተከፍሎ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አይደለም ።

ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ዘወረደ ፡ እምሰማያት ፡ ወወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘተወልደ ፡ እምብእሲት ፡ ኢይትዌከፍ ፡ ክፍለተ ፡ ኀበ ፡ ፪ ፡ ህላዌ ። ከሰማይ ፡ የወረደው ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ከማርያም ፡ የተወለደው ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ኹለትነት ፡ አይከፈልም ፡ ማለት ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አይደለም ።

ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ዘወረደ ፡ እምሰማይ ፡ ይሰመይ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአኮ ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ፡ እመሕያው ፡ ወዘሂ ፡ ተወልደ ፡ እምብእሲት ፡ ይሰመይ ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ወአኮ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ።

እንዲህ ፡ ካልኾነስ ፡ ከሰማይ ፡ የወረደው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንጂ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ባልተባለም ፡ ነበር ፣ ከማርያም ፡ የተወለደውም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በተባለ ፡ እንጂ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ባልተባለም ፡ ነበረ ።

ወዝንቱ ፡ ንባብ ፡ ይተሉ ፡ ስሕተቶሙ ፡ ወዕልወቶሙ ፡ ለጳውሎሳውያን ፡ እንዲህ ፡ ማለት ፡ ዕሩቅ ብእሲ ፡ የሚሉ ፡ የጳውሎስ ፡ ሳምሳጢ ፡ ወገኖችን ፡ መከተል ፡ መያዝ ፡ ማጽደቅ ፡ ማመን ፡ ነው ።

ወለነሰ ፡ እስመ ፡ መጻሕፍተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሜህሩነ ፡ ከመ ፡ ንእመን ፡ በ፩ ፡ እግዚእ ፡ ዘወረደ ፡ እምሰማያት ፡ ወተወልደ ፡ እምብእሲት ፡ ወእለሰ ፡ የአምኑ ፡ ዘንተ ፡ ኢይወድቁ ፡ ወኢየኀብሩ ፡ ምስለ ፡ እለ ፡ ይሔልዩ ፡ ዘሎ ፡ ዘበቱ ፡ ተቃርኖት ፡ ከመ ፡ ኢይጽርፉ ፡ በንባብ ፡ እለ ፡ ይባርኩ ፡ በልቦሙ ።

ለእኛስ ፡ ከሰማይ ፡ የወረደው ፡ ከማርያም ፡ የተወለደው ፡ ጌታ ፡ <u>አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ</u> ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያጻፋቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ይነግሩናል ፡ ያስተምሩናልና ፡ <u>አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ</u> ፡ ብለው ፡ የሚያምኑ ፡ ሰዎች ፡ አይስቱም ፡ አይበድሉም ። በልቡናቸው ፡ አመን ፡ አከበርን ፡ ሲመስላቸው ፡ በአነጋገር ፡ እንዳይበድሉ ፡ ባንድነቱ ፡ ምንታዌን ፡ በሦትነቱ ፡ ርባዔን ፡ ከሚያስቡ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ አይተባበሩም ።

ወእለሰ ፡ የአምኑ ፡ በ፪ ፡ ህላዌ ፡ ያጌብርሙ ፡ ይስግዱ ፡ ለ፩ ፡ ወለካልኡ ፡ ኢይስግዱ ፡ ይጠመቁ ፡ በዘመለኮት ፡ ወኢይጠመቁ ፡ በዘትስብእት ።

ኹለት ፡ <u>አካል</u> ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ብለው ፡ ለሚያምኑ ፡ ሰዎች ፡ ለአንዱ ፡ <u>አካል</u> ፡ ለአንዱ ፡ ባሕርይ ፡ እንዲሰግዱ ፡ ለአንዱ ፡ <u>አካል</u> ፡ ላንዱ ፡ ባሕርይ ፡ እንዳይሰግዱ ፡ በመለኮት ፡ <u>አካል</u> ፡ በመለኮት ፡ ባሕርይ ፡ ስም ፡ እንዲጠመቁ ፡ በትስብእት ፡ አካል ፡ በትስብእት ፡ ባሕርይ ፡ ስም ፡ እንዳይጠመቁ ፡ ግድ ፡ ይኾንባቸዋል ፡ ብሏል ።

ለ/ የእስክንድርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስም ፡ የመለኮትንና ፡ የትስብእትን ፡ ተዋሕዶ፡ በነፍስና ፡ በሥጋ ፡ ተዋሕዶ ፡ መስሎ ፡ ያስረዳ ፡ መኾኑን ፡ በ፪ኛ ፡ ምዕራፍ ፡ በቍ ፡ ፵፩ ፡ ዘርዝረን ፡ ያስረዳን ፡ ስለኾነ ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ መድገም ፡ አላስፈለገም ፡ ያንኑ ፡ መመልከት ፡ በቂ ነው ፡ የቀደሙ ፡ አባቶቻችንም ፡ እኛም ፡ ክርስቶስ ፡ ከኹለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ከኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ብለን ፡ ማመናችን ፡ ስለዚህ ፡ ነው ።

ፍላብያኖስ ፡ ግን ፡ ከአውጣኪ ፡ ቱሳሔ ፡ ሲሸሽ ፡ ከንስጥሮስ ፡ ጉድጓድ ፡ ምንታዌ ፡ የወደቀ ፡ መኾኑ ፡ በዚህ ፡ ታወቀ ፡ ተረዳ ፡ ኢሳ ፡ ፳፬ ፡ ፲፰ ።

ሐ/ የሮሙ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ልዮን ፡ ግን ፡ አውጣኪ ፡ ለጻፈለት ፡ መልስ ፡ ፍላብያኖስ ፡ አላገባብ አወገዘኝ ፡ ብሎ ፡ ቢልክበት ፡ የላከኽልኝን ፡ ቃል ፡ አወቅሁት ፡ እኒያ ፡ ደፋሮች ፡ የንስጥሮስን ፡ ኑፋቄ እንደገና ፡ ማሳደሳቸውን ፡ አገኘሁት ፡ ብሎ ፡ መጻፉ ፡ የንስጥሮስ ፡ ኑፋቄ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ ስለኾነ ፡ ይህንኑም ፡ ያደሰ ፡ ፍላብያኖስ ፡ ስለኾነ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ልዮን ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል፡ አልተቀበለም ።

አንድ ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ገና ፡ ከዲዮስቆሮስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነበረ ፡ ማለት ፡ ነው ።

መ/ ልዮን ፡ ለአውጣኪ ፡ አይዞህ ፡ ብሎ ፡ እንደላከበት ፡ ለፍላብያኖስም ፡ አይዞህ ፡ ብሎ ፡ ላከበት ፡ ይላል ። በጽሕፈት ፡ ተላልከው ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ እንደኾነ ፡ አልተገለጠም ፡ እንጂ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ የተቀበለ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ይመስላል ።

ሠ/ ከዲዮስቆሮስ ፡ ጋራ ፡ የተሰበሰቡ ፡ ፻፶ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ፍላብያኖስን ፡ ያወገዝክበትን ፡ ምክንያት ፡ መጥተህ ፡ አስረዳን ፡ ቢሉት ፡ እንቢ ፡ ስላላቸው ፡ የተወገዘውን ፡ አውጣኪን ፡ አስጠርተው ፡ ሃይማኖትህን ፡ ግለጽልን ፡ አሉት ፡ እርሱም ፡ ሃይማኖቴ ፡ በኒቅያ ፡ የተሰበሰቡ ፡ ፫፻፲፰ ፡ ሊቃውንት ፡ በወሰኑት ፡ ጸንቻለሁ ፡ ብሎ ፡ ነአምን ፡ በ፩ ፡ አምላክ ፡ ካለው ፡ ጀምሮ ፡ ሐመ ፡ ወሞተ ወተቀብረ ፡ እያለ ፡ በፊታቸው ፡ ሃይማኖቱን ፡ ገለጸ ፡ ቱሳሔ ፡ ብለሃል ፡ ቢሉትም ፡ ቱሳሔ ፡ ብዬ ፡ መናገሬ ፡ አይታወቀኝም ፡ አለ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከግዝቱ ፡ ፈቱት ። ከአውጣኪ ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ መነኮሳትም ፡ እንዲሁ ፡ ሃይማኖታችን ፡ በ፫፻፲፰ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፤ ፍላብያኖስ ፡ ያወገዘን ፡ በከንቱ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በ፫፻፲፰ ፡ ሃይማኖት ፡ ስለታመኑ ፡ ከግዝቱ ፡ ፈቷቸው ፡ ይላል ።

እንግዲህ ፡ ወይም ፡ ፍላብያኖስ ፡ ቀርቦ ፡ ስሕተታቸውን ፡ ካላስረዳቸው ፡ ወይንም ፡ እነርሱ ፡ በቃላቸው ፡ ካላመኑ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ተወግዘው ፡ ይቅሩ ፡ ይላሉ ። ከፍላብያኖስ ፡ ጋራ ፡ ኾኖ ፡ አውግዞት ፡ የነበረው ፡ ድሙኑስ ፡ ዘአንጾኪያ ፡ እኔ ፡ ያወገዝኩት ፡ ፍላብያኖስ ፡ ቢልክብኝ ፡ ነው ፡ አሁን ፡ ጽፎ ፡ ያቀረበው ፡ በ፫፻፲፰ ፡ ቃል ፡ የተወሰነውን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሲመሰክርለት ፡ ጊዜ ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ላዕለ ፡ ልሒቅ ፡ ኢትስማዕ ፡ ውዴተ ፡ ዘእንበለ ፡ ይዝልፍዎ ፡ ፪ቱ ፡ ወ፫ ፡ ሰማዕት ፡ ፩ ፡ ጢሞ ፡ ፭ ፡ ፲፱ ።

ኹለት ፡ ሦስት ፡ ምስክሮች ፡ ካልመሰከሩበት ፡ በቄሱ ፡ ላይ ፡ ነገረ ፡ ሠሪ ፡ አትስማ ፡ ያለውን ፡ ተመልክቶ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ አውጣኪንና ፡ ተከታዮቹን ፡ የፈታቸው ፡ ከኾነ ፡ የሚያስነቅፈው ፡ ምንድን ፡ ነው ፤ ሰው ፡ ካነጋገር ፡ ይፈረዳል ፡ ካያያዝ ፡ ይቀደዳል ፡ እንደሚባለው ፡ የነገሩትን ፡ ሰምቶ ፡ ይፈርዳል ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ምን ፡ መብት ፡ አለው ፤ ኩላሊት ፡ ያጢሰውን ፡ ልቡና ፡ ያመላለሰውን ፡ መርምሮ ፡ መፍረድማ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ አይደለምን ።

ረ/ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ፍላብያኖስን ፡ ጠርተው ፡ ቢጠይቁት ፡ በንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ እላለሁ ፡ ቢላቸው ፡ ገዝተው ፡ ከክህነቱ ፡ ሻሩት ፡ ከዚሁ ፡ አያይዘው ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ፡እንደ ቅዱስ ፡ አትናቴዎስ ፤ ሥግው ፡ ቃል ፡ ክርስቶስ ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የማይል ፡ ገዝተናል ሲሉ ፡ ወሰኑ ፡ ይላል ፡ ይህ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ። ባህል ፡ በጉባኤ ፡ ኤፌሶን ፡ የተወገዘ ፡ መኾኑ ፡ የታወቀ ፡ ነው ፤ ይህን ፡ አፍርሶ ፡ ሲገኝ ፡ ቢያወግዙት ፡ ምን ፡ ቅር ፡ ያሰኛል ፡ አያሰኝም ።

ሰ/ በተጠቀሰው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ስለኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ምንም ፡ አይነገርበትም ፡ ስሰሚሉት ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በኬልቄዶን ፡ የተሰበሰቡ ፡ ሊቃውንት ፡ ኹሉ ፡ ንስጥሮስ ፡ ያመነጨውን ፡ ፍላብያኖስ ፡ የተቀበለውን ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ሳይሰሙ ፡ ገና ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ ስለነበሩ ፡ በነገሩ ፡ ሳይኖሩበት ፡ ምን ፡ ብሎ ፡ ያነሣቸው ፡ ይላሉ ፡ ያላነሣቸው ፡ ባይኖሩ ፡ ነገሩ ፡ ገና ፡ ቢኾን ፡ ነው ።

ቀ/ ለጉባኤው ፡ ተካፋይ ፡ ስለነበሩት ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ አነጋገሩን ፡ ሳያኳላ ፡ ይናገራል ፡ ስለሚሉትም ፡ የነበሩትን ፡ ስማቸውን ፡ ጠርቶ ፡ ንግግራቸውን ፡ ለይቶ ፡ እገሌ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እገሌም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ እያለ ፡ ተናግሯል ፡ ማጕላትና ፡ መናገር ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ በእኛ ፡ አስተያየት ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ የጎላ ፡ አነጋገር ፡ ምንም ፡ አይገኝም ፡

## ደ ራ ሲ ።

፲፰/ እላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ መጻሕፍቶች ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የኬልቄዶንን ፡ ጉባኤ ፡ እውነተኛውን ፡ ታሪኩንና ፡ በእርሱ ፡ ውስጥ ፡ የተወሰነውን ፡ ትምርት ፡ መልካም ፡ አድርገው ፡ አያውቁቱም

ስንል ፡ ያቀረብነውን ፡ አሳብ ፡ የሚደግፍ ፡ ነው ። በነዚሁ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ የኾኑትን ፡ ነገሮች ፡ ያፋልሳቸዋል ፡ የተወሰነውንም ፡ ትምህርት ፡ በፍጹም ፡ ሳይረዱት ፡ ቀርተዋል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፰/ ሀ/ የተወሰነው ፡ ትምርት ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ መኾኑን ፡ ዐውቀን ፡ ተረድተን ፡ ይህ ፡ የንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ ነው ፡ እንቀበልም ፡ ብለናል ። ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የሚል ፡ ውሳኔ ፡ የለም ፡ የሚሉን ፡ ከኾነ ፡ ልንስማማ ፡ እንችላለን ።

ለ/ ስለታሪኩ ፡ እውነተኛውን ፡ ታሪክ ፡ አያውቁትም ፡ የኾኑትን ፡ ነገሮች ፡ ያፋልሷቸዋል ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ እውነተኛው ፡ ታሪክ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ የተባለው ፡ ቃል ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ያቀረቡት ፡ መቃወሚያ ፡ የለም ። ማስተባበያ ፡ ተቃዋሚ ፡ ያልቀረበበት ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ኹልጊዜ ፡ እውነተኛነትን ፡ ይዞ ፡ የሚገኝ ፡ ስለኾነ ፡ ይህ ፡ ታሪክ ፡ እውነተኛነትን ፡ ይዞ ፡ ይኖራል ። በዚሁ ፡ ምዕራፍ ፡ ከ፲፱ ፡ /ቍ-፲፰ ፡ ቍ ፡ በተጻፈው ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ዘርዝሬ ፡ እንዳስረዳኹዎ ዲዮስቆሮስ ፡ በጉባኤው ፡ ላይ ፡ የተነሣ ፡ ሲወርድ ፡ ሲዋረድ ፡ የነበረውን ፡ ትምርት ፡ ጉባኤው ፡ ስላበላሸው ፡ ነው ፤ ጉባኤውም ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ ያወገዘውና ፡ ያሰደደው ፡ መልስ ፡ እስከማሳጣት ፡ ደርሶ ጉባኤውን ፡ ስላሳፈረው ፡ ነው ፡ የምንል ፡ በዚህ ፡ ታሪክ ፡ መሠረት ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ው ።

፲፱/ አሁንም ፡ በተጠቀሱት ፡ መጻሕፍት ፡ እንደሚታየው ፡ ኢትዮጵያውያኖቹ፡ስዲዮስቆሮስ፡ ባህሉን ፡ ሳይከተሉ ፡ ይከላከሉለትና ፡ ያከብሩታል ፡ ምክንያቱም ፡ ፊት ፡ እንዳወሳነው ፡ ለወደፊትም እንደምናየው ፡ የኃላ ፡ ኋላ ፡ ያውጣኪ ፡ ባለሴራ ፡ ከኾነው ፡ ከዲዮስቆሮስ ፡ ባህል ፡ ፈጽሞ ፡ ልዩ ፡ የኾነ ትምህርት ፡ ስለሚያምኑ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፱/ ባለፈው ፡ አውጣኪ ፡ ከዲዮስቆሮስ ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ የተነገረበትን ፡ ክህደት ፡ ቢጠየቅ ፡ ይህን ፡ ክህደት ፡ አልተናገርኩም ፡ ሃይማኖቴ ፡ ፫፻፲በኒቅያ ፡ የወሰኑት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከመታመኑም፡ በላይ ፡ የተወራበትን ፡ ክህደት ፡ ቀርቦ ፡ የመሰከረበትና ፡ ያስረዳበት ፡ ስላልኖረ ፡ ከግዝቱ ፡ እንደ ፡ ፈታው ፡ አንብበናል ፡ እንጂ ፡ አውጣኪ ፡ የክርስቶስ ፡ ተዋሕዶው ፡ ቱሳሔ ፡ ነው ፡ ሥጋውም ፡ ረቂቅ ፡ ኢሐማሚ ፡ ኢመዋቲ ፡ ነው ፡ አለ ፡ የተባለውን ፡ ባህል ፡ ተቀብሎ ፡ ከግዝቱ ፡ ፈታው ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ አላገኘንም ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ አናገኝም ።

እርስዎ ፡ በጥል ፡ በቃ ፡ የአውጣኪ ፡ ባለሴራ ፡ እያሉ ፡ በዲዮስቆርስ ፡ ላይ ፡ የሚናገሩት ፡ ፍጹም ውሸት ፡ ነው ፤ እኛም ፡ ለአውጣኪ ፡ ተቃዋሚ ዎች ፡ መኾናችንን ፡ ርስዎ ፡ ራስዎ ፡ መስክረውልናል። ስለዚህ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ የንስጥሮስንና ፡ የልዮንን ፡ እንዲሁም ፡ የአውጣኪን ፡ ባህል ፡ ተቃዋሚ ፡ መኾኑን ፡ ዐውቀን ፡ ተከትለነዋል ፡ አክብረነዋል ፡ እንጂ ፡ ከዲዮስቆሮስ ፡ ባህል ፡ ፈጽሞ ፡ ልዩ ፡ የኾነ ፡ ትምርት ፡ የምናምን ፡ አይደለንም ።

## ደ ራ ሲ ።

፳/ ኢትዮጵያውያኖች ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ የሚያከብሩትና ፡ የርሱ ፡ ተከታዮች ፡ ነን ፡ ብለው ፡ የሚመኩበት ፡ ምክንያት ፡ እነርሱ ፡ አንዳንዶቹን ፡ የቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ቃሎች ፡ በማይስማማ ፡ አኳኋን ፡ እንደ ፡ ፈቀዳቸው ፡ በመተርጐም ፡ የእውነተኛው ፡ ሃይማኖት ፡ ጠባቂና ፡ ያገር ፡ ናት ፡ የሚሏት ፡ የእናት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸው ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ የነበረ ፡ በመኾኑ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳/ ዲዮስቆሮስን ፡ የተከተልነውንና ፡ ያከበርነው ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ውሳኔ ፡ ሲቃወም ፡ የሰጠው ፡ መግለጫ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ግብ ፡ ያልወጣ ፡ ከ፫ቱ ፡ ዐበይት ፡ ጉባኤያት ፡ ባህል ፡ ጋራ ፡ የተስማማ ፡ ኾኖ ፡ ብናገኘው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በመኾኑ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

አንዳንዶቹን ፡ የቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ቃሎች ፡ በማይስማማ ፡ አኳኋን ፡ እንደ ፡ ፈቃዳቸው፡ ተረጐሚቸው ፡ የሚሏቸውንም ፡ እንዲህ ፡ የሚለው ፡ ንባብ ፡ እንዲህ ፡ ተብሎ ፡ መተርጐም ፡ ሲገባው ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ለውጠው ፡ ተርጕመውታል ፡ እያሉ ፡ ዘርዝረው ፡ ቢያስረዱን ፡ ኖሮ ፡ ተገቢ

ውን ፡ መልስ ፡ በሰጠንዎ ፡ ነበረ ፡ ገልጸው ፡ ካላስረዱን ፡ ግን ፡ የሚናገሩት ፡ ነገር ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ጉንጭ ፡ አልፋ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ከማለፍ ፡ በቀር ፡ የማይጨበጥ ፡ ነገር ፡ ስለኾነ ፡ ዋጋ ፡ ሊሰጠው ፡ አልተቻለም ።

## ደራሲው ።

፳፩/ ከእስክንድርያ ፡ የሚመጣው ፡ ትምርት ፡ ከኹሉ ፡ የሚበልጥና ፡ እውነተኛ ፡ መኾኑን ፡ ሲያስረዱ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የሚጠቅሷቸው ፡ ቃሎች ።

ሀ/ ውእተ ፡ አሚረ ፡ ይከውን ፡ ምሥዋዑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በብሔረ ፡ ግብጽ ፡ ወቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ ደወለ ፡ ዚአሆሙ ፡ ኢሳ ፡ ፲፱ ፡ ፲፱—፳ ።

በዚያ ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ መካከል ፡ ይኾናል ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ዓምድ ፡ በዳርቻው ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ የእግዚአብሔር ፡ የሠራዊት ፡ አምላክ ፡ ምልክት ምስክር ፡ ይኾናል ።

ለ/ ወየአምርዎ ፡ ግብጽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ውእተ ፡ አሚረ ፡ ወይሠውዑ ፡ መሥዋዕተ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወይበፅዑ ፡ ብፅዐተ ፡ ወያበውዑ ፡ መባዓ ፡ ኢሳ ፡ ፲፱ ፡ ፳፩ ።

በዚያን ፡ ቀን ፡ ግብጻውያን ፡ ጌታን ፡ ያውቁታል ፡ እንስሳትን ፡ በመሠዋትና ፡ እኽልን ፡ በማበርከት ፡ ይሰግዱለታል ፡ ለጌታም ፡ ስለት ፡ ይሳሉለታል ፡ ስእለቱንም ፡ ይፈጽሙለታል ።

ሐ/ አንተ ፡ ባረከ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸባኦት ፡ ወይብል ፡ ቡሩክ ፡ ሕዝብየ ፡ ዘውስተ ፡ ግብጽ ። ኢሳ ፡ ፲፱ ፡ ፳፭ ።

እነርሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ የባረካቸው ፡ ናቸው ፡ ግብጻውያን ፡ የተባረኩ ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው ፡ ይላል ፡ ማለት ፡ ነው ። በዚህ ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ ተርጓሚ ፡ እዚህ ፡ የተባረከ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ሃይማኖታቸው ፡ የቀናና ፡ የጠና ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ምን ፡ ሊያሰማ ፡ ነው ፡ ይላል ፡ ብለው ፡ ሽሙጥ ፡ ያዘለ ፡ አነጋገር ፡ ተናግረዋል ።

## መላሽ ።

፳፩/ እነዚህ ፡ ቃላት ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ጠቀሷቸው ፡ ኢሳይያስ ፡ የተናገራቸው ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ የጻፍናቸው ፡ አይደሉም ፡ ኢሳይያስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አልተናገረም ፡ ወይም ፡ ትርጓሜ ፡ ተለውጧል ፡ ይሉ ፡ እንደኾነ ፡ ዘርዝረው ፡ ያስረዱ ። ሰውስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ቡሩክ ፡ ሕዝብየ ፡ ተብሎ ፡ ለመመስገን ፡ የሚበቃ ፡ ሃይማኖቱ ፡ የቀና ፡ ምግባሩ ፡ የጸና ፡ ኾኖ ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ እስኪ ፡ ያስረዱ ፡ ለሚያስተባብሉት ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እውነተኛው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ማስተባበያ ፡ ካልተከበት ፡ በቀር ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ ሐሰት ፡ ሊያደርገው ፡ አይችልም ፡ የሚያስተባብሉበትም ፡ ምክንያት ፡ ከሌለዎ ፡ ኢሳይያስን ፡ ስለግብጽ ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ ለምን ፡ ተናገርክ ፡ ብለው ፡ ይወቅሱት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እኛን ፡ ምን ፡ በሉ ፡ ይሉናል ።

## ደራሲ ።

፳፪/ ከኢትዮጵያውያን ፡ ጋራ ፡ ተከራክሬ ፡ የነዚህ ፡ ቃሎች ፡ ትርጕማቸው ፡ ሌላ ፡ መኾኑን ፡ አስረዳቸዋለሁ ፡ ብለህ ፡ መጣጣር ፡ ከንቱ ፡ ድካም ፡ ነው ። እነርሱ ፡ ይህነኑ ፡ ጥቅስ ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ እየተረጐሙት ፡ እንደማይፈርስ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ ምስክር ፡ አድርገው ፡ ብቻ ፡ ይከራከሩበታል ፡ ብለዋል ።

## መላሽ ።

፳፪/ ይህን ፡ የተናገረ ፡ ኢሳይያስ ፡ ነው ፡ መጽሐፈ ፡ ኢሳይያስም ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ አንዱ ፡ መኾኑ ፡ ሲታወቅ ፡ እንደማይፈርስ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ አድርገው ፡ ይከራከሩበታል ፡ በማለትም ፡ እናዝናለን ፡ እንጂ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ መጽሐፈ ፡ ኢሳይያስ ፡ መኾኑን ፡ እናምናለን ። ስለትርጓሜውም ፡ ይህን ፡ የሚያስለውጥ ፡ ሌላ ፡ ትርጓሜ ፡ ካለው ፡ አሁን ፡ አይናገሩትም ፡ ነበርን ፡ ለመቼ ፡ ሊኾንዎ ፡ ቆጠቡት ፡ እኛስ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ፡ ትምህርት፡ የሌላቸው፡ የማያስተውሉ ፡ ሰዎች ፡ የመጽሐፍን ፡ ቃል ፡ ይለውጡታል ፡ ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ። ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ ስለምናውቅ ፡ ልንለውጠው ፡ አንፈቅድም ።

ደግሞም ፡ እስክንድርያ ፡ የምንከተላት ፡ ከሐዋርያት ፡ ከ፫፻ ፡ ቃል ፡ ሳትናወጽ ፡ በዚያው ፡ ጸንታ ፡ ብናገኛት ፡ እንጂ ፡ ኢሳይያስ ፡ ስለግብጽ ፡ ይህን ፡ ተናገረ ፡ በማለት ፡ እንዳይደለ ፡ ይወቁልን ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፫/ የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ በኢትዮጵያውያኖቹ ፡ ዘንድ ፡ የዲዮስቆሮስን ፡ ስም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ በኬልቄዶኑ ፡ ጉባኤና ፡ በተቀባዮቹ ፡ በተለይም ፡ በልዮን ፡ ላይ ፡ ያልኾነውን ፡ የሐሰት ፡ ሐሜት ፡ እየፈጠሩ ፡ አወሩባቸው ፡ ደግሞም ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ የሚያስነቅፉ ፡ ኑፋቄ ያቸውንም ፡ የሚያስመስግኑ ፡ ብዙ ፡ ተአምራቶች ፡ ተፈጽመዋል ፡ ሲሉ ፡ ራሳቸው ፡ ፈጥረው ፡ በማ ውራት ፡ አታለሏቸው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፫/ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ነገር ፡ መላልሰው ፡ ይናገሩታል ፡ መልስ ፡ እንዳይሰጥበት ፡ እውነ ተኛው ፡ ነገር ፡ የኸ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ያቀረቡት ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ዋጋ ፡ በሌለው ፡ ነገር ፡ ሥራ ፡ በማስፈታትዎ ፡ እያዘንኩ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነገር ፡ ነው ፡ በማለት ፡ አልፌዋለሁ ።

## ክ ፍ ል ፡ ፪ ፡ ደ ራ ሲ ።

### ስለ ፡ ተወሰነው ፡ ትምህርት ፡ ያላቸው ፡ ስሕተት ።

## መ ላ ሽ ።

ለርስዎ ፡ ስለመሰለዎ ፡ ስሕተት ፡ ይሉታል ፡ እንጂ ፡ እኛስ ፡ ስለኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ የምንናገረው ፡ ኹሉ ፡ ርትዕ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስሕተት ፡ አይደለም ።

## ደ ራ ሲ ።

፩/ ኢትዮጵያውያን ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ የሚቃወሙትና ፡ የጉባኤውንም ፡ ሰብሳቢ ፡ ልዮን ፡ ጳጳስን ፡ የሚሰድቡት ፡ በጉባኤው ፡ የተወሰነውን ፡ ትምህርት ፡ ቅንነት ፡ በጣም ፡ የሚነኩ ፡ በሐሰተኝነት ፡ የተፈጠሩ ፡ ሐሜቶች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ በዲዮስቆሮስ ፡ ላይ ፡ ግፍ ፡ ተሠራበት ፡ ብለው ፡ አይደለም ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፩/ ይህ ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ የኬልቄዶንን ፡ ጉባኤ ፡ የምንቃወመውና ፡ ልዮንንም ፡ የማ ንቀበልበት ፡ ምክንያት ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ቃልና ፡ ከ፫ ፡ ዐበይት ፡ ጉባኤያት ፡ ውሳኔ፡ወጥ ተው ፡ ብናገኘቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለዲዮስቆሮስ ፡ ረዳቶች ፡ ኾነን ፡ አይደለም ።

ዲዮስቆሮስንም ፡ የምናከብረውና ፡ የምንወደው ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ቃል ፡ ሳይወጣ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ አባቶች ፡ በወሰኑት ፡ ውሳኔ ፡ ጸንቶ ፡ ብናገኘው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የአድልዎ ፡ አይደለም ።

## ደ ራ ሲ ።

፪/ በእውነትም ፡ ስለኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የሚናገሩትን ፡ የኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍቶች ፡ ኹሉ ፡ ብንመለከት ፡ የተባለው ፡ ጉባኤ ፡ ንስጥሮስና ፡ አውጣኪ ፡ በተነቀፉበትና ፡ በተገዘቱበት ፡ ምክንያት ፡ እንደሚነቀፍና ፡ እንደሚገዘት ፡ እንረዳለን ፡ የቀድሞዎቹን ፡ ጉባኤዎች ፡ ትምህርት ፡ አበላሽቷል ፡ ብለው ፡ በማመን ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ የመናፍቃን ፡ ስብሰባ ፡ ብለው ፡ ይጠሩታል ፡ የተባለው ፡ ጉባኤ ፡ እንደነርሱ ፡ አሳብ ፡ ምንም ፡ ችሎታና ፡ ሥልጣን ፡ የሌለው ፡ መኾኑ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፪/ እውነት ፡ ነው ፡ እርስዎም ፡ እንደተረዱት ፡ ይህን ፡ ጉባኤ ፡ የምንቃወመው ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የሚለውን ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ አድሶታል ፡ በማለት ፡ ነው ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለትም ፡ ቀድሞ ፡ ንስጥሮስ ፡ የወጠነው ፡ ኋላም ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ያጸናው ፡ መኾኑን ፡ እርስዎም ፡ አይ ክዱትም ።

አሁንም ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ የሚተው ፡ ከተገኘ ፡ ልንስማማ ፡ እንችላለን ፡ ይህን ፡ ካልተወ ፡ ግን ፡ የቀድሞዎችን ፡ ጉባኤያት ፡ ትምህርት ፡ ማበላሸቱ ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ እኛም ፡ የመና ፍቃን ፡ ስብሰባ ፡ ብለን ፡ መጥራታችንና ፡ ጉባኤውም ፡ በኛ ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ምን ፡ ሥልጣን ፡ የሌለው ፡ መኾኑ ፡ እርግጥ ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፫/ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ሲናገሩ ፡ ምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ በሚባለው ፡ መጽሐፋቸው ፡ የኬልቄዶንን ፡ ጉባኤ ፡ አለመቀበላችን ፡ የሰው ፡ ፈቃድ ፡ መፈጸሚያ ፡ ስለኾነ ፡ ነው ፡ በኒቅያ ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነውን ፡ የቍስጥንጥንያ ፡ ጉባኤ ፡ ተቀብለው ፤ የቍስጥንጥንያ ፡ ጉባኤ ፡ የወሰነውንም ፡ የኤፌሶን ፡ ጉባኤ ፡ ተቀብሎ ፡ በግዝት ፡ አጸናው ። የኤፌሶንም ፡ ሊቃውንት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከተዋሐደ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፈቃድ ፡ ወስነው ፡ ሲጨርሱ ፡ ይህን ፡ አንድ ፡ ኾነን ፡ የወሰነውን ፡ ሃይማኖት ፡ የሚለውጥ ፡ ቢኖር ፡ አውግዘን ፡ እንለየዋለን ፡ ብለው ፡ ከወሰኑ ፡ በኋላ ፡ በመርቅያንና ፡ በብርክልያ ፡ በልዮን ፡ የተወሰነው ፡ ሃይማኖት ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ያልተገኘ ፡ ነውና ፡ እንቀበለውም ። ደግሞ ፡ የቅዱስ ፡ ቄርሎስንና ፡ የቅዱስ ፡ አትናቴዎስን ፡ ልጅ ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ አስመጥተው ፡ በኤፌሶን ፡ የተገዘቱትን ፡ መናፍቃን ፡ ተቀብለው ፡ የንስጥሮስን ፡ ክህደት ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ አድሰዋልና ፡ ስለዚህ ፡ አንቀበላቸውም ፡ ይላል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፫/ የኬልቄዶንን ፡ ውሳኔ ፡ የማንቀበልበት ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የጠቀሱት ፡ ምክንያት ፡ መኾኑ ፡ እውነት ፡ ነው ። ይህም ፡ ምክንያት ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ እንዳይሉ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ከንስጥሮስ ፡ መንጭቶ ፡ በኤፌሶን ፡ ጉባኤ ፡ የተወገዘው ፡ መኾኑን ፡ አይክዱትም ። የኬልቄዶን ፡ ጉባኤም ፡ ከንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ተስማሚ ፡ መኾኑ ፡ ግልጥ ፡ ነገር ፡ ነው ። ይህም ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ይመስላል ፡ ያሰኛል ። ይኸን ፡ ይኸናል ፡ በሚል ፡ በልብ ፡ ወለድ ፡ አሳብ ፡ የተመሠረተ ፡ ከመሆኑ ፡ በቀር ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ወይም ፡ ከጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ በፊት ፡ ከነበሩ ፡ ሊቃውንት ፡ መጻሕፍት ፡ ፪ ፡ ባሕርይ ፡ ፪ ፡ ፈቃድ ፡ ፪ ፡ ጠባይዕ ፡ የሚል ፡ ተገኝቶ ፡ በዚያ ፡ የተመሠረተ ፡ አይደለም ፡ ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ጉባኤ ፡ አንቀበልም ፡ ማለታችን ፡ በሚገባ ፡ መኾኑን ፡ ይገንዘቡልኝ ።

ከዚህ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዲገልጹልኝ ፡ አሳስብዎታለሁ ፤ ኢትዮጵያ ፡ የኬልቄዶንን ፡ ጉባኤ ፡ አለመቀበሏን ፡ አረጋግጣ ፡ ጽፋ ፡ ከፍፋ ፡ የኖረች ፡ መኾኗን ፡ እንዲህ ፡ በእርግጥ ፡ ያወቁ ፡ ሲኾኑ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የኬልቄዶንን ፡ ጉባኤ ፡ በግልጥ ፡ የተቃወመችበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ፡ እያሉ ፡ መላልሰው ፡ የጻፉ ፡ ለማደናገርና ፡ ለማጭበርበር ፡ ነውን ፡ ምክንያቱ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ቢገልጹልኝ ፡ ደስ ፡ ይለኝ ፡ ነበር ።

## ደ ራ ሲ ።

፬/ ኢትዮጵያውያን ፡ የባሕርይንና ፡ የአካልን ፡ አሳቦች ፡ በግልጥ ፡ ከማደባለቃቸው ፡ የተነሣ ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የክርስቶስን ፡ አንድነት ፡ የሚያጠፋውን ፡ በኤፌሶን ፡ ጉባኤ ፡ የተገዘተውን፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ አጽንተው ፡ አስተምረዋል ፡ እያሉ ፡ ዛሬም ፡ ቢኾን ፡ ያምናሉ ፡ ብለው ፡ ያልኾነ ፡ ነገር ፡ የምናምን ፡ አስመስለው ፡ ተናግረዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፬/ የባሕርይንና ፡ የአካልን ፡ አሳቦች ፡ ከማደባለቃቸው ፡ የተነሣ ፡ ብለው ፡ ድፍን ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ተናግረዋል ፡ እንጂ ፡ የአካል ፡ ስልቱ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የባሕርይ ፡ ስልቱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ገልጸው ፡ የጻፉት ፡ ነገር ፡ የለም ፤ የባሕርይ ፡ ስልቱ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ የአካል ፡ ስልቱ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ገልጸው ፡ የጻፉት ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ ግልጥ ፡ ያለ ፡ መልስ ፡ ይሰጥበት ፡ ነበረ ። ስለዚህ ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የክርስቶስን ፡ አንድነት ፡ የሚያጠፋውን ፡ በኤፌሶን ፡ የተገዘተውን ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ አጽንቶዋል ፡ ብለን ፡ ማመናችን ፡ በሚገባ ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ለዚህ ፡ ቃል ፡ የምንሰጠው ፡ ሌላ ፡ መልስ ፡ የለንም ።

## ደ ራ ሲ ።

፭/ ይህም ፡ እውነት ፡ አለመሆኑ ፡ ጉባኤው ፡ ባደረገው ፡ ውሳኔ ፡ በግልጥ ፡ ይረዳል ፡ ብለው ፡ የጉባኤውን ፡ ውሳኔ ፡ ጽፈዋል ። ቃሉም ፡ የሚከተለው ፡ ነው ።

ተሊወነ ፡ እንከ ፡ አበዊነ ፡ ቅዱሳን ፡ ንሜህር ፡ ኵልነ ፡ ኅቡረ ፡ ከመ ፡ ይደሉ ፡ ይትአመኑ ፡ በ፩ ፡ ከመ ፡ ወልድ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወውእቱ ፡ ፍጹም ፡ በመለኮት ፡ ወፍጹም ፡ በትስብእት ፡ አምላክ ፡ ዘበአማን ፡ ወሰብእ ፡ ዘበአማን ፡ ዘውእቱ ፡ እምነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወእምሥጋ ፡ ኅቡረ ፡ ህላዌ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ በመለኮቱ ፡ ወውእቱ ፡ ኅቡረ ፡ ህላዌ ፡ ምስሌነ ፡ በትስብእቱ ፡ ዘተመሰለ ፡

ኪያን ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ባሕቲታ ፡ ዘተወልደ ፡ እምአብ ፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ በመለኮቱ ፡ ወበትስብእቱሰ ፡ ተወልደ ፡ በደኃሪ ፡ መዋዕል ፡ በእንቲአነ ፡ ወበእንተ ፡ መድኃኒትነ ፡ እማርያም ፡ ድንግል ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ።

ወይደሉ ፡ ይትአመኑ ፡ ከመ ፡ ፩ ፡ ወውእቱመ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ በ፪ኤ ፡ ባሕርያት ፡ ዘእንበለ ፡ ቱሳሔ ፡ ወኢውላጤ ፡ ዘእንበለ ፡ ፍልጠት ፡ ወኢቡዐዴ ፡ እንዘ ፡ ኢይጠፍዕ ፡ ፍልጠተ ፡ ባሕርየት ፡ በእንተ ፡ ተዋሕዶቶሙ ፡ ወባሕቱ ፡ እንዘ ፡ ይትዐቀብ ፡ ዘዘኢአሆሙ ፡ ለክልኤ ፡ ባሕርያት ፡ ወእንዘ ፡ ይከውኑ ፡ ፩ ፡ አካለ ፡ ወ፩ ፡ ህላዌ ፡ ኢንፉቅ ፡ ወኢክፉል ፡ ለኀበ ፡ ፪ኤ ፡ አካላት ፡ አላ ፡ ፩ ፡ ከመ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እግዚእ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በከመ ፡ ቀዲሙ መሐሩነ ፡ ነቢያት ፡ በእንቲአሁ ፡ ወለሊሁ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእ ፡ መሀረነ ፡ ወተወፈይናሁ ፡ እምተአምኖተ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘአበዊነ ።

## መላሽ ፡

፳/ ነቢያት ፡ አስቀድመው ፡ ስለርሱ ፡ እንዳስተማሩን ፡ እርሱ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ እንዳስተማረን ፡ ከአባቶቻችን ፡ እምነት ፡ እንዳገኘነው ፡ አባቶቻችን ፡ ቅዱሳንን ፡ ተከትለን ፡ ይህን ፡ ውሳኔ ፡ ወስነናል ፡ ብለዋል ።

እንግዲህ ፡ በነቢያት ፡ ስብከት ፡ በክርስቶስ ፡ ትምህርት ፡ በሐዋርያት ፡ ስብከት ፡ በሊቃውንት ፡ አስተያየት ፡ የተመሠረቱት ፡ ቃላት ፡ የትኞቹ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ በይመስላል ፡ በይኾናል ፡ የተመሠረቱት ፡ ቃላት ፡ የትኞቹ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ጋራ ፡ እያመሳከርን ፡ እንመርምር ።

፩/ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ይትአመኑ ፡ በ፩ ፡ ከመ ፡ ወልድ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ሊታመን ፡ ይገባል ፡ ለሚለት ፡ ቃል ፡ መሠረቱ ፡ ወልድ ፡ ዋሕዶ ፡ ዘሀሎ ፡ ውስተ ፡ ሕፅነ ፡ አቡሁ ፡ ውእቱ ፡ ነገረነ ፡ እስከ ፡ ወልዶ ፡ ዋሕደ ፡ ወሀበ ፡ ወመጠወ ፡ ቤዛ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ነው ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፰ ። ፫ ፡ ፲፮ ።

ይህን ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ሐዋርያት ፡ በጸሎተ ፡ አመክንዮ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ዘፅሩይ ፡ ምስሌሁ ፡ ብለዋል ፡ ሃይ ፡ አበ ።

፫፻፲ም ፡ በጸሎተ ፡ ሃይማኖት ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ ዋሕድ ፡ ዘፅሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ በመለኮቱ ፡ ብለዋል ፡ ሃይ ፡ አበ ።

ይህን ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ፩ ፡ አካል ፡ ወ፩፡ ህላዌ ፡ እያሉ ፡ የጻፉ ፡ ሊቃውንት ፡ ብዙ ፡ ናቸው ።

፪/ ወውእቱ ፡ ፍጹም ፡ በመለኮት ፡ ወውእቱ ፡ አምላክ ፡ ዘበአማን ፡ ላሉትም ፡ ቃል ፡ መሠረቱ ፡ ወፃእኩ ፡ እምአብ ፡ ወመጻእኩ ። አነ ፡ ወአብ፡ ፩ ንሕነ ። ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፴፪ ። ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ያለው ፡ ነው ፡ ማቴ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ።

ይህን ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ሐዋርያት ፡ ነገረነ ፡ በወልዱ ፡ ጸዳለ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ወአምሳለ ፡ አርአያሁ ፡ ዘባሕርይሁ ፡ ዕብ ፡ ፪ ፡ ፫ ። እግዚእየ ፡ ወአምላኪየ ። ዮሐ ፡ ፳ ፡ ፳፰ ። ብለዋል ።
፫፻ቱ ፡ ፪ ፡ አምላክ ፡ ዘእምአምላክ ፡ ዘበአማን ፡ ብለዋል ።

፫/ ወፍጹም ፡ በትስብእት ፡ ወሰብእ ፡ ዘበአማን ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ ሲኾን ፡ አነጋገሩ ፡ ሊታረምና ፡ ሊተካከል ፡ ይገባዋል ። ምክንያቱም ፡ መጻሕፍቱ ፡ አምላክ ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ ይሉናል ፡ እንጂ ፡ አምላክ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ስለማይሉን ፡ ነው ።

ሀ/ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ቃል ፡ በቅድምና ፡ ነበረ ፡ ያም ፡ ቃል ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ዓለም ፡ በርሱ ፡ ተፈጠረ ፡ እያለ ፡ መጥቶ ፡ ያ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኾነ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ያ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ አላለም ። መጻሕፍት ፡ ኹሉ ፡ ይህንን ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ቀዳማዊ ፡ አምላክነቱን ፡ ሲናገሩ፡ መጥተው ፡ በፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ ይሉናል ፡ እንጂ ፡ ቀድሞ ፡ አምላክ ፡ ነበረ ፡ ዛሬም ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ እንደሚሉን ፤ ቀድሞ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ዛሬም ፡ ሰው ፡ ነው ፡ አይሉንም ። ነውና ፡ ኾነ ፡ ልዩነት ፡ አላቸው ፡ አምላክነት ፡ ጥንተ ፡ ገንዘቡ ፡ ስለኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ አይባልም ።

ትስብእት ፡ ግን ፡ ኖሮ ፡ ኖሮ ፡ ያገኘው ፡ ስለኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ አይባልም ፡ ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ክርስቶስን ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ነው ፡

ስንል ፡ ምንታዌን ፡ እንዳያስከትልብን ፡ በመፍራት ፡ ክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ የኾነ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ በማለት ፡ እነጋገሩን ፡ ከመጠንቀቅ ፡ በቀር ፡ የምንርቀው ፡ ንባብና ፡ ባህል ፡ አይደለም ።

፬/ ዘውእቱ ፡ እምነፍስ ፡ ነባቢት ፡ ወእምሥጋ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ሥጋን ፡ ለመንሣቱ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ብሏል ፤ ነፍስንም ፡ ለመንሣቱ ፡ እባ ፡ አመሐፅን ፡ ነፍስየ ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፡ ብሏልና ፡ ከመጻሕፍት ፡ የተመሠረተ ፡ ስለኾነ ፡ የምንስማማበት ፡ ነው ።

፭/ ኅቡረ ፡ ህላዌ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ በመለኮቱ ፡ ለሚለውም ፡ ቃል ፡ መሠረቱ ፡ እነ ፡ በአብ ፡ ወአብ ፡ ብየ ፡ ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፲ - ፲፪ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ነው ። ይህን ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ሊቃውንት ፡ በየአንቀጹ ፡ ዘዕሩይ ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ በመለኮቱ ፡ እያሉ ፡ ነግረውናል ።

፮/ ወውእቱ ፡ ኅቡረ ፡ ህላዌ ፡ ምስሌነ ፡ በትስብእቱ ፡ ለሚለውም ፡ ቃል ፡ መሠረቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ በነቢይ ፡ አድሮ ፡ ነየ ፡ እነ ፡ ወደቂቅ ፡ ዘወሀበኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ኢሳ ፡ ፰ ፡ ፲፰ ።

ይህንንም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እስመ ፡ ደቂቅ ፡ ተሳተፉ ፡ በሥጋ ፡ ወደም ፡ ወከመ ፡ ቢጸሙ ፡ ኮነ ፡ ሎሙ ፡ ብሎ ፡ አስፋፍቶ ፡ ተርጕሞታል ፡ ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲፬ ።

፯/ ዘተመሰለ ፡ ኪያነ ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ ባሕቲታ ፡ ለሚለውም ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ መሠረቱ ፡ ወተመሰለ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ወኮነ ፡ ከመ ፡ ሰብእ ፡ ሰምዐ ፡ ወተአዘዘ ፡ እስከ ፡ በጽሐ ፡ ለሞት ፡ ፊልጵ ፡ ፪ ፡ ፰ ።

ይመጽእ ፡ መልአኩ ፡ ለዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ወኢይረክብ ፡ በላዕሌየ ፡ ወኢምንተኒ ። የሚለው ፡ ቃል ፡ ነው ። ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፴ ።

፰/ ዘተወልደ ፡ እምአብ ፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ፡ በመለኮቱ ፡ ለሚለው ፡ ቃል ፡ መሠረቱ ፡ በብሉይ ፤ ሰሎሞን ፡ እምቅድመ ፡ አድባር ፡ ወአውግር ፡ ወለደኒ ።

ዳዊትም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቤለኒ ፡ ወልድየ ፡ አንተ ፡ ወእነ ፡ ዮም ፡ ወለድኩከ ፡ ያለው ፡ ነው ። በሐዲስም ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ። ወፃእኩ ፡ እምአብ ፡ ወመጻእኩ ፡ ያለው ፡ ነው ።

፱/ ወበትስብእቱሰ ፡ ተወልደ ፡ በደኃሪ ፡ መዋዕል ፡ በእንቲአነ ፡ ወበእንተ ፡ መድኃኒትነ ፡ እማርያም ፡ ድንግል ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ለሚለውም ፡ ቃል ፡ መሠረቱ ፡ ወአመ ፡ በጽሐ ፡ ዕድሜሁ ፡ ፈነወ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልዶ ፡ ወተወልደ ፡ እምብእሲት ፡ ያለው ፡ ነው ፡ ገላ ፡ ፬ ፡ ፬ ፡ ማቴ ፡ ፳፩-፳፭ ። ሉቃ ፡ ፩ ፡ ፳፮-፴፱ ፡ ፪ ፡ ፩-፰ ፡ ተመልከት ።

ዘእንበለ ፡ ቱሳሔ ፤ ወኢውላጤ ፡ ዘእንበለ ፡ ፍልጠት ፡ ወኢቡዐዴ ፡ ስለሚለው ፡ ቃል ፡ ቱሳሔ ፤ ውላጤ ፤ ፍልጠት ፡ ቡዐዴ ፤ በየጊዜው ፡ የተነሡ ፡ መናፍቃን ፡ ያመነጭዋቸው ፡ ስሕተቶች ፡ ናቸው ፤ ካነሥዋቸውም ፡ ዘንድ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ በያይነታቸው ፡ ስልት ፡ ስልታቸውን ፡ ብንገላልጠው ፤ አይከፋም ።

ውላጤ ፡ ማለት ፡ ወንጌላዊ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ውኅደረ ፡ ላዕሌነ ፡ ብሎ ፡ ጻፈ ፡ ኃደረ ፡ ላዕሌነን ፡ ያልተመለከቱ ፡ ሰዎች ፡ ሥጋ ፡ ኮነን ፡ ብቻ ፡ ተመልክተው ፡ ብእሲተ ፡ ሎጥ ፡ ተለውጣ ፡ ሐውልተ ፡ ጨው ፡ እንደኾነች ።

ማየ ፡ ቃና ፡ ተለውጦ ፤ ወይን ፡ እንደኾነ ፡ ቃልም ፡ ተለውጦ ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ ብለዋል ።

ኅደረን ፡ ብቻ ፡ የተመለከቱ ፡ ኮነን ፡ ያልተመለከቱ ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ እንደማድጋ ፡ ውኅ ፡ ትስብእት ፡ ማኅደር ፡ መለኮት ፡ ኀዳሪ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አልተዋሐደም ፡ ብለዋል ።

ወንጌላዊ ፡ ግን ፡ ኮነን ፡ ይዘው ፡ ተለወጠ ፡ እንዳይሉበት ፡ ኀደረ ፡ ብሏል ፤ ኀደረን ፡ ይዘው ፡ ኀደረት ፡ እንዳይሉበት ፡ ኮነ ፡ ብሎ ፡ ኹለቱንም ፡ ተናገረ ፡ ስለዚህ ፡ ኮነን ፡ ይዞ ፡ ተለወጠ ፡ የሚል ፡ ሲነሣ ፡ ኀደረ ፡ ብሎብሃል ፤ ኀደረን ፡ ይዞ ፡ ኀድረት ፡ የሚል ፡ ሲነሣ ፡ ኮነ ፡ ብሎብሃል ፡ ሲሏቸው ፡ ይረታሉ ።

ቱሳሔ ፡ ማለት ፡ ከላይ ፡ በ፲፯ኛ ፡ ቍ ፡ እንዳስረዳነው ፡ መቀላቀል ፡ መደባለቅ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ኅብረ ፡ መልክእ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጣዕም ፡ ያላቸው ፡ ኹለት ፡ ነገሮች ፡ ቢያደባልቋቸው ፡ ከኹለቱም ፡ ወገን ፡ የተውጣጣ ፡ ልዩ ፡ ኅብረ ፡ መልክእ ፤ ያሳያሉ ፡ ልዩ ፡ ጣዕም ፡ ይሰጣሉ ፡ ለምሳሌ ፡ ወተትና ፡ ቡና ፡ ቢቀላቅሏቸው ፡ ወተት ፡ ነጭነቱን ፡ ለቆ ፡ ወደጥቁረት ፡ ይሳባል ፤ ቡንም ፡ ጥቁርነቱን ፡ ለቆ ፡ ወደነጭነት ፡ ይሳባል ፡ ከኹለቱም ፡ የተውጣጣ ፡ ልዩ ፡ መልክእ ፡ ይታያል ፡ ልዩ ፡ ጣዕም ፡ ይገኛል ።

መለኮት ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ውላጤ ፡ ሳይኖርበት ፡ ከእመቤታችን ፡ የነሣውን ፡ ሥጋ ፡ ባለው፡ እጽ ንቶ ፡ የፍጡር ፡ ልቡና ፡ መርምሮ ፡ በማይደረስበት ፡ በግብር ፡ አምላካዊ ፡ ጥልቅ ፡ በኾነ ፡ ምሥጢር ፡ በከዊን ፡ ተዋሐደው ፡ እንጂ ፡ እላይ ፡ በመሰልነው ፡ ምሳሌ ፡ እኳኋን ፡ መለኮትና ፡ ትስብእት ፡ ተቀ ላቅለው ፡ በመካከላቸው ፡ ሌላ ፡ ነገርን ፡ ያስገኙ ፡ ወይም ፡ የተጠፋፉ ፡ አይደሉም ፡ ስለዚህ ፡ ቱሳሔ ፡ ማለት ፡ ታላቅ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

ቡዐዴ ፡ ማለት ፡ ተዋሕዶው ፡ ተላጽቆ ፡ ተቃርቦ ፡ ነው ፤ ማለት ፡ ነው ፡ ተላጽቆ ፡ ተቃርቦ ፡ ማለ ትም ፡ እላይ ፡ በቍ ፡ ፲፯ ፡ እንደገለጽነው ፡ የዕንጨትና ፡ የብረት ፡ ሠራተኛ ፡ ዕንጨቱን ፡ ጠርቦ ፡ አለ ዝቦ ፡ ብረቱን ፡ ሞርዶ ፡ አስማምቶ ፡ በማሰሪያ ፡ ወይም ፡ በቡሎን ፡ በምስማር ፡ አንድ ፡ ቢያደርጋ ቸው ፡ አንድ ፡ ይኾናሉ ፡ ማሠሪያውን ፡ ወይንም ፡ ቡሎኑን ፡ ቢፈታው ፡ ይለያያሉ ። ቡዐዴ ፡ ተላጽቆ ፡ ተቃርቦ ፡ ማለት ፡ እንዲህ ፡ የተለያየ ፡ ነገር ፡ ስለሆነ ፡ የክርስቶስ ፡ ተዋሕዶም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፤ ማለት ፡ ታላቅ ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ፍልጠት ፡ ማለት ፡ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ የሚመጣ ፡ መለየት ፡ ማለት ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ነፍስና ፡ ሥጋ ፡ ተዋሕደዋል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ተፈልጦ ፡ አለባቸው ። የመለኮትና ፡ የት ስብእት ፡ ተዋሕዶ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ በነፍስና ፡ በሥጋ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቢመስል ፡ እንደ ፡ ነፍስና ፡ እንደ ሥጋ ፡ ተፈልጦ ፡ የለበትም ፤ ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ በመልዕልተ ፡ መስቀል ፡ አባ ፡ አማሕፅን ፡ ነፍ ስየ ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፡ ብሎ ፡ ክብርት ፡ ነፍሱን ፡ ከክብርት ፡ ሥጋው ፡ በገዛ ፡ ሥልጣኑ ፡ በለየ ፡ ጊዜ ፡ መለኮት ፡ ከነፍስም ፡ ከሥጋም ፡ ተፈልጦ ፡ ሳይኖርበት ፡ በአካለ ፡ ሥጋ ፡ ወደመቃብር ፡ ወርዶ ፡ሙስና፡ መቃብርን ፡ አጥፍቶልናል ፡ ሙስና ፡ መቃብርም ፡ ማለት ፡ በመቃብር ፡ ፈርሶ ፡ በስብሶ ፡ መቅረት ፡ ነው ፡ ይኸንን ፡ ፫ ፡ መዓልት ፡ ፫ ፡ ሌሊት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሮ ፡ በመነሣቱ ፡ አጥፍቶልናል ። እኛም ፡ እርሱን ፡ በኩር ፡ አድርገን ፡ የምንነሣ ፡ ኾነናል ።

በአካለ ፡ ነፍስም ፡ መለኮት ፡ ወደሲዖል፡ ወርዶ ፡ ግዕዛንን፡ ለነፍሳት ፡ ሰብኮ ፡ ከቁራኝነት፡ አስለ ቅቆናል ። በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ አኳኋን ፡ መለኮት ፡ ከትስብእት ፡ የማይለይ ፡ ስለኾነ ፡ ፍልጠት ፡ ማለት ፡ ታላቅ ፡ ስሕተት ፡ ነው ።

፩ ፡ አካል ፡ ወ፪ ፡ ህላዌ ፡ ኢንፋቅ ፡ ወኢክፉል ፡ ለኀቡ፡ ፪ቱ፡አካላት ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ፩ ፡ አካል ፡ ወ፩ ፡ ህላዌ ፡ እንዳለው ፡ ኹሉ ፡ ኢንፋቅ ፡ ወኢክፉል ፡ ለኀበ ፡ ፪ኤ ፡ አካላት ፡ ሲልም ፡ ወኢለኀበ ፡ ፪ኤ ፡ ህላዌያት ፡ ብሎ ፡ ማስተካከል ፡ ነበረበት ፤ ይሆን ፡ ማስተካከል ፡ ብቻ ፡ ጎሎበታል ፡ እንጂ ፡ ሌላው ፡ አነጋገር ፡ ከመጻሕፍት ፡ ያልወጣ ፡ ነው ።

እንዘ ፡ ይትዐቀብ ፡ ዘዘዚአሆሙ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ተዓቅቦን ፡ የሚመለከት ፡ ነው ፡ ተዐቅቦም ፡ ማለት ፡ በጠቅላላው ፡ ትስብእትና ፡ መለኮትን ፡ ከቱሳሔ ፡ ከውላጤ ፡ የሚጠብቅ ፡ አነጋገር ፡ ነው ፤ ምሥጢሩም ፡ ሙሴ ፡ በደብረ ፡ ሲና ፡ ሐመልማል ፡ ከነበልባል ፡ ተዋሕዶ ፡ ነበልባሉ ፡ ሐመልማሉን ፡ ሳያቃጥለው ፡ ሐመልማሉም ፡ ነበልባሉን ፡ ሳያጠፋው ፡ እንዳየ ፤ መለኮትም ፡ ትስብእትን ፡ በተዋ ሐደ ፡ ጊዜ ፡ መለኮቱ ፡ ትስብእቱን ፡ አላጠፋውም ፡ ትስብእቱም ፡ መለኮቱን ፡ አልለወ ጠውም ፡ ማለት ፡ ነው ።

ትስብእቱም ፡ ማለት ፡ አካልንም ፡ ባሕርይንም ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ የሚያሳይ ፡ አነጋገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አካልን ፡ ወይም ፡ ባሕርይን ፡ ብቻ ፡ የሚያሳይ ፡ አነጋገር ፡ አይደለም ።

ይህም ፡ ተዐቅቦ ፡ የባሕርይንም ፡ የአካልንም ፡ ተዐቅቦ ፡ ያሳያል ፡ እንጂ ፡ የአካልን ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ የባሕርይን ፡ ብቻ ፡ የሚያሳይ ፡ አይደለም ።

ተሊወነ ፡ እንከ ፡ አበዊነ ፡ ቅዱሳነ ፡ ከመ ፡ ቀዲሙ ፡ መሐሩነ ፡ ነቢያት ፡ በእንቲአሁ ፡ ወለሊሁ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚእ ፡ መሐረነ ፡ ወተወፈይናሁ ፡ እምተአምኖተ ፡ ሃይማኖት ፡ ዘአበዊነ ፡ ያሉት ፡ ቃል ፤ እውነት ፡ ወይም ፡ ሐሰት ፡ መኾኑን ፡ ለመረዳት ፡ የጉባኤው ፡ ውሳኔ ፡ ናቸው ፡ ያሏቸውን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ብንመረምር ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ቃላት ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የተገኙ ፡ መኾና ቸውን ፡ ተረድተናል ። እኛም ፡ የምንቀበላቸው ፡ ነን ።

በ፪ ፡ ባሕርያት ፡ እንዘ ፡ ኢይጠፍዕ ፡ ፍልጠተ ፡ ባሕርያት ፡ ዘዘዚአሆሙ ፡ ለ፪ኤ ፡ ባሕርያት ፤ የሚሉአቸውን ፡ ቃላት ፡ ግን ፡ ከንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ እንጂ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ኾነው ፡ አላገኘ ናቸውም ፤ ለማስመሰል ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ከተገኙት ፡ ቃላት ፡ ጋራ ፡ አቀላቅለው ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ከተገኙት ፡ ቃላት ፡ ጋራ ፡ አቀላቅለው ፡ ተናግረዋቸዋል ፡ እንጂ ፡ ነቢያት ፡ ሐዋርያት ፡ ከጻፉዋቸው ፡ መጻሕፍት ፡ ጌታ ፡ ባስተማራት ፡ በወንጌል ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ንባብ ፡ አይገኝም ፡ ፍጹም ፡ ውሸት ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ይህንን ፡ ባሕል ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ወለእመኒ ፡ መልአክ ፡ መሀረክሙ ፡ ካልአ ፡ እም ዘመሀርናክሙ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ፡ ብሎ ፡ ካስጠነቀቀን ፡ ትምህርት ፡ ቆጥረነው ፡ አንቀበለውም ። እርስዎም ፡ ባሕርይን ፡ ከአካል ፡ ለይቶ ፡ ኹለት ፡ የሚል ፡ ንባብ ፡ መኖሩን ፡ ሊያስረዱ ፡ አይችሉም ።

## ድ ራ ሲ ።

፮/ ወሶበ ፡ አቀምነ ፡ ዘንተ ፡ በኵሉ ፡ ጻሕቀ ፡ ወትጋሀ ፡ ወሰነ ፡ ጉባኤ ፡ ቅዱስ ፡ ወዘእምኵለሄ ፡ ከመ ፡ ኢብውህ ፡ ወኢለመኑሂ ፡ ይንግር ፡ አው ፡ ይጽሐፍ ፡ አው ፡ ይድርስ ፡ አው ፡ ይምሐር ፡ ለካልአን ፡ ሃይማኖተ ፤ ካልአ ።

ይህንን ፡ በፍጹም ፡ ትጋት ፡ ከወሰን ፡ በኋላ ፡ ማንም ፡ ማን ፡ ቢኾን ፡ ሌላ ፡ ሃይማኖት ፡ ሊደርስ ፡ ሊጽፍ ፡ ሊነግር ፡ ሊያስተምር ፡ የማይገባው ፡ መኾኑን ፡ ይህን ፡ ጉባኤ ፡ ወሰን ፡ ስለሚለው ።

## መ ላ ሽ ።

፮/ ይህን ፡ ማለት ፡ የሚገባ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ግብ ፡ ሳይወጡ ፡ በዚያው ፡ ጸንቶ ፡ ተገኝቶ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ከግቡ ፡ ወጥቶ ፡ ልብ ፡ እንዳፈራው ፡ ተናግሮ ፡ እንዲህ ፡ ቢሉት ፡ ማን ፡ በጅ ፡ ይላል ፡ አስቀድመው ፡ የነበሩ ፡ አባቶች ፡ የወሰኑትን ፡ አፍርሶ ፡ የኔን ፡ ውሳኔ ፡ አክብሩልኝ ፡ ማለት ፡ ማንም ፡ የማይቀበለው ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ነው ።

## ድ ራ ሲ ።

፯/ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ያስተማረው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ማናቸውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ከሚለው ፡ በስተቀር ፡ ሌላ ፡ የሚነቀፍ ፡ እንደማይገኝበት ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ። አንድ ፡ ባሕርይ ፡ በሚለው ፡ አነጋገር ፡ አለመስማማታቸው ፡ ግን ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ ካለመግባባትና ፡ ኹለቱ ፡ ወገኖች ፡ የሚሰጡት ፡ ትርጉም ፡ ልዩ ፡ ከመኾኑ ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

፯/ እንግዲህ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ከሚለው ፡ በስተቀር ፡ የሚነቀፍ ፡ አይገኝበትም ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ከለቃሚና ፡ ካቃሚ ፡ ያመለጠ ፡ ስሕተት ፡ ይመስለኛል ፡ እንጂ ፡ የርስዎ ፡ ቃል ፡ አይመስለኝም ። ምክንያቱም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የሚቃወሙ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ ስላልኾነ ፡ ነው ።

ስሕተት ፡ አይደለም ፡ ቃሌ ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ የሚያስማማን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚያጣላን ፡ አይደለም ። ያቃሚ ፡ ስሕተት ፡ መኾኑን ፡ ተገንዝበው ፡ ፪ ፡ ባሕርይ ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ የሚነቀፍ ፡ የለበትም ፡ ብለው ፡ የሚያርሙት ፡ ቢኾን ፡ ግን ፡ ከትርጉም ፡ ልዩነት ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ የሚገባ ፡ ንባብ ፡ አንድ ፡ ኾኖ ፡ ትርጓሜ ፡ ብቻ ፡ ሲለያይ ፡ ነበረ ፡ መጻሕፍት ፡ በየአንቀጹ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ እያሉ ፡ አንድነትን ፡ መሳልሰው ፡ ለተናገሩለት ፡ ላንድ ፡ ለክርስቶስ ፡ ፪ቱ ፡ የሚል ፡ ቅጽል ፡ በመስጠቱ ፡ በንባብ ፡ እንደተለያየን ፡ አያስታውሱምን ፡ በ፩ና ፡ በ፪ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነትስ ፡ ቀላል ፡ መሰለዎትን ፡ ከሰማይና ፡ ከምድር ፡ የተራራቀ ፡ ነው ።

## ድ ራ ሲ ።

፰/ እንደ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አስተያየት ፡ ባሕርይ ፡ ሲሉ ፡ አንድ ፡ በራሱ ፡ የቆመና ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ህልው ፡ ያሰማሉ ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፰/ የአንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ኪራኮስ ፡ ኢይደሉ ፡ ይኩን ፡ ህላዌ ፡ ዘእንበለ ፡ አካል ፡ ወኢይደሉ ፡ ይትረከብ ፡ አካል ፡ ዘእንበለ ፡ አምሳሉ ፡ ለአካል ፡ ዘውእቱ ፡ አርአያሁ ።

ባሕርይ ፡ ያለአካል ፡ ሊኖር ፡ አይችልም ፡ አካልም ፡ ከሚመስለው ፡ ከባሕርይ ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ብቻውን ፡ ሊገኝ ፡ አይቻልም ፡ ይኸውም ፡ መታወቂያው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እንዳስረዳን ፡ ባሕርይ ፡ የሌለው ፡ አካል ፡ እንደ ፡ ሌለ ፡ ባሕርይም ፡ ያለአካል ፡ ብቻውን ፡ ሊገኝ ፡ የማይቻል ፡ መኾኑን ፡ እናውቃለን ። አካል ፡ የሌለው ፡ ባሕርይ ፡ አለመኖሩንና ፡ ባሕርይ ፡ ያለአካል ፡ ሊኖር ፡ አለመቻሉን ፡ ምክንያት ፡ ፍጥረት ፡ የኾኑ ፡ ፬ቱን ፡ ባሕርያት ፡ ብንመረምር ፡ ልንረዳ ፡ እንችላለን ።

ለምሳሌ ፡ ወኃ ፡ አካልም ፡ ባሕርይም ፡ አለው ፡ አካሉ ፡ በእጅ ፡ ባይጨበጥም ፡ በጥርስ ፡ ባይላመጥም ፡ ሲፈስ ፡ ወይም ፡ በቀላይ ፡ ተዘርግቶ ፡ በማድጋ ፡ ተቀድቶ ፡ ይታያል ፡ ባሕርዩም ፡ እርጥበት ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ባሕርዩ ፡ የኾነ ፡ እርጥበት ፡ አካሉ ፡ በደረሰበት ፡ ኹሉ ፡ ይገኛል ፡ እንጂ ፡ አካሉ ፡ በሌለበት ፡ ቦታ ፡ ብቻውን ፡ ሊገኝ ፡ አይችልም ፡ አካሉም ፡ ከባሕርዩ ፡ ከርጥበት ፡ ተለይቶ ፡ ብቻውን ፡ ሊገኝ ፡ አይችልም ።

እሳትም ፡ እንደዚሁ ፡ አካል ፡ ባሕርይ ፡ አለው ፡ ባሕርዩም ፡ ዋዕይ ፡ ነው ፡ አካሉ ፡ በዕንጨት ፡ ወይም ፡ በመብራት ፡ ላይ ፡ ይታያል ፤ ባሕርዩ ፡ የሆነ ፡ ዋዕይ ፡ ግን ፡ አካሉ ፡ ሲገለጥ ፡ ከአካሉ ፡ ላይ ፡

ሲፋጅ ፡ ሲያቃጥል ፡ ይገለጻል ፡ እንጂ ፡ አካሉ ፡ በሌለበት ፡ ብቻውን ፡ ሊገኝ ፡ አይችልም ፡ ስለዚህ ፡ የወኃ ፡ ባሕርይ ፡ ርጥበትን ፡ የፈለገ ፡ የወኃን ፡ አካል ፡ የእሳት ፡ ባሕርይ ፡ ሙቀትን ፡ የፈለገ ፡ የእሳትን ፡ አካል ፡ መፈለግ ፡ ግድ ፡ ይኾንበታል ፡ አካል ፡ የሌለው ፡ ባሕርይ ፡ ላለመኖሩና ፡ ባሕርይም ፡ ያለአካል ፡ ብቻውን ፡ ሊገኝ ፡ ላለመቻሉ ፡ ይህ ፡ በቂ ፡ መረጃ ፡ ነው እንዲህ ፡ አድርገን ፡ ባሕርይ ፡ የሌለው ፡ አካል ፤ አካል ፡ የሌለው ፡ ባሕርይ ፡ የለም ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ ባሕርይን ፡ ከአካል ፡ ለይተን ፡ አንድ ፡ በራስ ፡ የቆመ ፡ ህልው ፡ ነው ፡ አንልም ።

## ደ ራ ሲ ።

፱/ ባጭሩ ፡ እነርሱ ፡ አካልና ፡ ባሕርይ ፡ የሚሉትን ፡ ቃሎች ፡ ትርጕማቸውን ፡ አንድ ፡ በማድረግ ፡ ያደባልቋቸዋል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፱/ ይህም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ አካል ፡ በእጅ ፡ የሚዳሰሰው ፡ በዐይን ፡ የሚታየው ፡ ነው ፡ ባሕርይ ፡ ግን ፡ በአካል ፡ ህልው ፡ ኾኖ ፡ ከአካል ፡ ሳይለይ ፡ አካል ፡ የሚሰጠውን ፡ ስሜት ፡ የሚገልጽ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ትርጕማቸውን ፡ ለይተን ፡ እንናገራለን ፡ እንጂ ፡ ትርጕማቸውን ፡ አንድ ፡ በማድረግ ፡ የምናደባልቅ ፡ አይደለንም ።

## ደ ራ ሲ ።

፲/ ስለዚህ ፡ ክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ አሉት ፡ ሲባል ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ኹለት ፡ አካላት ፡ አሉት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ኾኖ ፡ ይሰማቸዋል ። የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤና ፡ ልዮን ፡ ጳጳስን ፡ በንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ ያምናሉ ፡ ብለው ፡ የሚያሟቸው፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲/ ኢትዮጵያውያን ፡ አካልንና ፡ ባሕርይን ፡ ለይተው ፡ አያውቁም ፡ ብለው ፡ እንደሚገምቱን ፡ አይደለንም ፤ የአካልንና ፡ የባሕርይን ፡ አንድነታቸውንም ፡ ባለፉት ፡ መስመሮች ፡ ዘርዝሬ ፡ አስረድቼዎታለሁ ፡ ንስጥሮስም ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ብሎ ፡ አስተማረ ፡ እንጂ ፡ ሁለት ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ ብሎ ፡ አልቀረም ።

ጉባኤ ፡ ኤፌሶንም ፡ በቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ አፈ ፡ ጉባኤነት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ብሎ ፡ ወሰነ ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ ብሎ ፡ አልቀረም ፡ ስለዚህ ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ማለትን ፡ በቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ ከንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ አምጥቶ ፡ ዝንጕርጕር ፡ የሆነ ፡ ውሳኔ ፡ ወሰነ ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በማለቱ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ይላል ፡ ብለን ፡ አናውቅም ፡ ነበረ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ባሕርይ ፡ ያለአካል ፡ ብቻውን ፡ የማይገኝ ፡ ስለኾነ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ካላችሁ ፡ አካል ፡ የሌለው ፡ ባሕርይ ፡ የለምና ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ያሰኝባችኋል ፡ ብንል ፡ የሚያሳፍረን ፡ አይደለም ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፩/ ኢትዮጵያውያን ፡ ባሕርይና ፡ አካል ፡ የሚሉትን ፡ ቃሎች ፡ አንድ ፡ አድርገው ፡ እንደሚያስቧቸው ፡ የሚገልጥ ፡ ሌላም ፡ ማስረጃ ፡ አለ ። እርሱም ፡ ካቶሊኮች ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ሲሉ ፡ በቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ፪ ፡ አካላት ፡ አሉ ፡ ማለታቸው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ማመናቸው ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፩/ በላይኛው ፡ መስመር ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ባሕርይ ፡ ሲሉ ፡ አንድ ፡ በራሱ ፡ የቆመና ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ ህልው ፡ ያሰማሉ ፡ ብለው ፡ አካልንና ፡ ባሕርይን ፡ እንደምንለያይ ፡ አድርገው ፡ ተናግረው ፡ ነበረ ፤ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ባሕርይና ፡ አካል ፡ የሚሉትን ፡ ቃሎች ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ አድርገው ፡ ያስቧቸዋል ፡ በማለት ፡ ቃልዎን ፡ በመለዋወጥ ፡ ይናገራሉ ፡ ኧረ ፡ ምናልባት ፡ ይህን ፡ የርስዎን ፡ ጽሑፍ ፡ ይቼ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ባህል ፡ ልመርምር ፡ የሚል ፡ ቢገኝ ፡ የትኛውን ፡ ይጨብጥ ፡ ብለው ፡ ነው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አንዱን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አንዱን ፡ የሚናገሩ ፤ እኛስ ፡ ስለአካልና ፡ ስለባሕርይ ፡ በያንቀጹ ፡ መላልሰን ፡ ተናግረናል ፡ አሁንም ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ሰብእስ ፡ ይትበሀል ፡ በእንተ ፡ ፍጥረተ ፡ ጠባይዑ ።

ሰው ፡ በባሕርዩ ፡ አካል ፡ ገዝቶ ፡ ስለመገኘቱ ፡ ሰው ፡ ይባላል ፡ ብሎ ፡ ሊቁ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ እንዳስረዳን ፡ (ሃይ ፡ አበ) ፡ ሰው ፡ ባልን ፡ ጊዜ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ አካል ፡ ወይም ፡ አካል ፡ ያለው ፡ ባሕ

ርይ ፣ በማለት ፣ አካልንና ፣ ባሕርይን ፣ አንድ ፣ አድርገን ፣ እንናገራለን ፣ እንጂ ፣ አካልን ፣ ከባሕርይ ፣ ባሕርይን ፣ ከአካል ፣ ለይተን ፣ አንናገርም ።

ስለዚህ ፣ ቃል ፣ ሰው ፣ ኾነ ፣ ስንል ፣ አካልንም ፣ ባሕርይንም ፣ አንድ ፣ ተዋሐደ ፣ እናምናለን ፣ እንጂ ፣ አካል ፣ ተዋሐደ ፤ ባሕርይ ፣ አልተዋሐደም ፣ አንልም ። ይህም ፣ ቃል ፣ ከእመቤታችን ፣ የነሣው ፣ ትስብእት ፣ የባሕርይ ፣ አምላክነትን ፣ በተዋሕዶ ፣ ገንዘብ ፣ አድርጎ ፣ በየማን ፣ አብ ፣ በዘባን ፣ ኪሩብ ፣ እንደ ፣ ተቀመጠ ፣ መጻሕፍት ፣ በያንቀጹ ፣ ነግረውናል ፣ ማር ፣ ፲፮ ፣ ፲፱ ። ኤፌ ፣ ፯ ፣ ፳ ። ዕብ ፣ ፩ ፣ ፫ ። ፩ ፣ ጴጥ ፣ ፫ ፣ ፳፪ ።

በየማን ፣ አብ ፣ በዘባን ፣ ኪሩብ ፣ ተቀመጠ ፣ ስንልም ፣ ለሥላሴ ፣ ፬ኛ ፣ ኾነ ፣ አንልም ፤ ምክን ያቱም ፣ ምንታዌ ፣ በተዋሕዶ ፣ ስለጠፋ ፣ ነው ።

እንደ ፣ ካቶሊካውያን ፣ አነጋገር ፣ ግን ፣ አካላዊ ፣ ተዋሕዶ ፣ መኖሩን ፣ አምነው ፣ የባሕርይን ፣ ተዋሕዶ ፣ ክደው ፣ ኹለት ፣ ባሕርይ ፣ ይላሉ ።

አካላዊ ፣ ተዋሕዶን ፣ ቢክዱም ፣ ቃል ፣ ሥጋ ፣ ኮነ ፣ በጠቅላላው ፣ መቅረቱ ፣ ነው ። በየማን ፣ አብ ፣ በዘባን ፣ ኪሩብ ፣ አልተቀመጠም ፣ እንዳይሉም ፣ ከላይ ፣ የጠቀስናቸው ፣ መጻሕፍት ፣ ይመሰክ ሩባቸዋል ።

ተቀመጠ ፣ የሚሉም ፣ ሲኾን ፣ ተዋሕዶን ፣ ነሥተው ፣ በምንታዌ ፣ አጽንተውታልና ፣ ይህ ፣ ሰብአዊ ፣ ባሕርይ ፣ ለሥላሴ ፣ ፬ኛ ፣ ኾነ ፣ ማለት ፣ ግድ ፣ ይኾንባቸዋል ፣ ብንል ፣ እውነት ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ሐሰት ፣ አይደለም ።

## ድ ራ ሲ ።

፲፪ / ኢትዮጵያውያን ፣ በአካላዊ ፣ ተዋሕዶ ፣ ምሥጢርም ፣ ቢኾን ፣ ባሕርይ ፣ ያለአካልነቱ ፣ ሊገኝ ፣ መቻሉን ፣ አያምኑም ። ስለዚህ ፣ በአካለ ፣ ቃል ፣ የሚገኘውንም ፣ ሰብአዊ ፣ ባሕርይ ፣ አካል ፣ ብለው ፤ ይሰይሙታል ፣ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፪ / እውነት ፣ ነው ፣ አካል ፣ ካልተገኘ ፣ ባሕርይ ፣ ብቻውን ፣ ይገኛል ፣ ብለን ፣ አናምንም ፣ ይኸውም ፣ የባሕርይንና ፣ የአካልን ፣ ኹኔታ ፣ አስቀድመን ፣ በውኃ ፣ በእሳት ፣ መስለን ፣ በተናገር ነው ፣ መሠረት ፣ እሳት ፣ ካልተገኘ ፣ ዋዕይ ፤ ውኃ ፣ ካልተገኘ ፣ ርጥበት ፣ ባለመገኘቱ ፣ ይታወቃል ።

ስለዚህ ፣ ቃል ፣ በማኅፀነ ፣ ማርያም ፣ የተዋሐደውንና ፣ በየጥቂቱ ፣ ያደገውንም ፣ አካል ፣ ሰብ አዊ ፣ ባሕርይ፣ ያለው ፣ ሰብአዊ ፣ አካል ፣ እንለዋለን ፣ እንጂ ፣ አካል ፣ የሌለው ፣ ባሕርይ ፣ እንለውም ። የማንልበትም ፣ ምክንያት ፣ ወንጌላዊ ፣ ቃል ፣ ሥጋ ፣ ኮነ ፣ ከማለት ፣ በቀር ፣ ቃል ፣ ኮነ ፣ ባሕርየ ፣ ባለማለቱ ፣ ነው ። ኮነ ፣ ሥጋ ፣ ያለውም ፣ ሰው ፣ መኾኑን ፣ እንደኾነ ፣ ቅዱስ ፣ ጳውሎስ ፣ መጽአ ፣ እም ዘርዐ ፣ ዳዊት ፣ በሥጋ ፣ ሰብእ ፣ ብሎ ፣ አጉልቶታል ፣ ሮሜ ፣ ፩ ፣ ፬ ።

ይህም ፣ ሥጋ ፣ ሰብእ ፣ የሚባለው ፣ ከራስ ፣ ጠጉር ፣ እስከ ፣ እግር ፣ ጥፍር ፣ ያለው ፣ ሕዋስ ፣ ወይም፣ ቅርጽ ፣ ነው ። ይህም ፣ ቅርጽ ፣ ሥጋ ፣ አካል ፣ ተብሎ ፣ መጠራቱን ፣ ቅዱስ ፣ ዳዊት ፣ ወኢይትኀባእ ፣ እምኔከ ፣ አዕፅምትየ ፣ ዘገበርከ ፣ በኅቡእ ፣ ወኢአካልየ ፤ በመትሕተ ፣ ምድር ። ወአካልየኒ ፣ ወኢ ከመ ፣ ምንት ፣ በቅድሜከ ፣ ብሏል ።

ባሕርይ ፣ ግን ፣ ርጥበት ፣ በውኀ ፣ ህልው ፣ ኾኖ ፣ የውኀን ፣ ጠባይዕ ፤ ውዕየት ፣ በእሳት ፣ ህልው ፣ ኾኖ ፣ የእሳትን ፣ ጠባይዕ ፣ እንዲገልጽ ፤ ባሕርየ ፣ ሰብእም ፣ በአካለ ፣ ሰብእ ፣ ህልው ፣ ኾኖ ፣ የአካልን፣ ጠባይዕ ፣ የአካልን ፣ ስሜት ፣ የሚገልጽ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ከአካል ፣ ተለይቶ ፣ ብቻውን ፣ የሚገኝ ፣ ቀዋሚ ነገር ፣ አይደለም ።

ስለዚህ ፣ ቃል ፣ ባሕርየ ፣ ሰብእ ፣ ያለውን ፣ አካለ ፣ ሰብእ ፣ ተዋሕዶ ፣ በሕፃናት ፣ መጠን ፣ በየ ጥቂቱ ፣ አደገ ፣ እንላለን ፣ እንጂ ፣ ቃል ፣ የነሣውን ፣ ሰብአዊ ፣ አካል ፣ ባሕርይ ፣ ብለን ፣ አንጠራውም ። ባሕርይስ ፣ በነሣው ፣ አካል ፣ ህልው ፣ ኾኖ ፣ ክርስቶስ ፣ ያሳየውን ፣ ሰብአዊ ፣ ስሜት ፣ የሚገልጽ ፣ ጠባይዕ ፣ ነው ።

አሁን ፣ በዚህ ፣ አንቀጽ ፣ በአካለ ፣ ቃል ፣ የሚገኝ ፣ ሰብአዊ ፣ ባሕርይ ፣ ያሉት ፣ እኛ ፣ አካል ፣ ብለን ፣ የጠራነውን ፣ ከራስ ፣ ጠጉር ፣ እስከ ፣ እግር ፣ ጥፍር ፣ ያለውን ፣ ሕዋስ ፤ ወይም ፣ ባጥንት ፣ በጅማት ፣ ጸንቶ ፣ ያለውን ፣ ሥጋ ፣ ነው ። ይህንኑም ፣ ቃል ፣ በተዋሕዶ ፣ ምንታዌን ፣ አጥ ፍቶ ፣ ገንዘብ ፣ አደረገው ፣ በማለት ፣ የተስማማን ፣ እንደ ፣ ኾነ ፣ እኛ ፣ አካል ፣ ብንለው ፣ እርስዎ ፣

ባሕርይ ፡ ቢሉት ፡ የስሙ ፡ መዛወር ፡ ምንም ፡ የሚጎዳን ፡ አይደለምና ፡ በዚህ ፡ ተስማምተን ፡ በ፪ኤ ፡ ባሕርይ ፡ የሚሉትን ፡ የኹለተኛውን ፤ ባሕርይ ፡ አነጋገር ፡ ወደ ፡ መመርመር ፡ እንራመድ ።

በ፪ኤ ፡ ባሕርይ ፡ የምንለው ፡ እናንተ ፡ አካል ፡ ብላችሁ ፡ የምትጠሩትን ፡ በአካለ ፡ ቃል ፡ የሚገኘውን ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ። ይህ ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ከተዋሕዶ ፡ በእፍአ ፡ ነው ፡ የሚሉን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግን ፤ ካቶሊካውያን ፡ እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ይላሉ ፡ ብሎ ፡ ለመናገር ፡ ጥርጊያ ፡ መንገድ ፡ መኾኑን ፡ ይገንዘቡት ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፫ / ኢትዮጵያውያን ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ ትምህርት ፡ በቀጥታ ፡ ይክዱታል ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ፡ ካቶሊኮችንና ፡ ልዮን ፡ ጳጳስን ፡ የሚገዘቷቸው ፡ የቀድሞዎቹን ፡ የሮቱን ፡ ጉባኤ ፡ ትምርት ፡ አበላሽተው ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ ይከተላሉ ፡ ብለው ፡ ስለሚገምቷቸው ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፫ / የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ከሚገኘው ፡ ትምህርት ፡ ጋራ ፡ ቀላቅሎ ፡ ከመጻሕፍት ፡ ያልተገኘ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ትምህርት ፡ በይመስላል ፡ ብቻ ፡ የወሰነ ፡ መኾኑን ፡ በላይኛው ፡ አንቀጽ ፡ ዘርዝሬ ፡ አሳይቻለሁ ።

እኒህም ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ጋራ ፡ እያመሳከርኩ ፡ የተቀበልኳቸው ፡ ቃላት ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የተጠቀሱ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ የጉባኤው ፡ ውሳኔዎች ፡ አይደሉም ።

የጉባኤው ፡ ውሳኔ ፡ የሚባሉት ፡ በ፪ኤ ፡ ባሕርያት ፡ እንዘ ፡ ኢይጠፍዕ ፡ ፍልጠተ ፡ ባሕርያት ፡ ዘዚአሆሙ ፡ ለክልኤ ፡ ባሕርያት ፡ የሚሉት ፡ ቃላት ፡ ብቻ ፡ ናቸው ።

እነዚህን ፡ ቃላት ፡ ተቀብለናቸው ፡ ቢኾን ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ ትምህርት ፡ በቀጥታ ፡ ይክዱታል ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ፡ ቢሉ ፡ ከእውነት ፡ ገብቶ ፡ በተቈጠረልዎ ፡ ነበረ ።

ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የተጠቀሱትን ፡ ቃላት ፡ ተቀብለን ፡ ብንገኝ ፡ አስቀድመው ፡ ተቀብለዋቸው ፡ የነበሩትን ፡ አጸኑ ፡ ያሰኛል ፡ እንጂ ፡ የጉባኤውን ፡ ውሳኔ ፡ ተቀበሉ ፡ አያሰኝም ። ጉባኤውም ፡ በ፪ኤ ፡ ባሕርይ ፡ ብሎ ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ መከተሉ ፡ ግልጥ ፡ ነገር ፡ ሲኾን ፡ ገምተው ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ተገቢ ፡ ነገር ፡ አይደለም ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፬ / ኢትዮጵያውያን ፡ የኬልቄዶኑ ፡ ጉባኤ ፡ ሃይማኖት ፡ ባነጋገሩ ፡ የቀና ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጉባኤውና ፡ ልዮን ፡ ጳጳስ ፡ ምንም ፡ በአንድ ፡ አካል ፡ ማለትን ፡ ቢጨምሩ ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ ለመሸፈን ፡ ሲሉ ፡ በልባቸው ፡ ሳያምኑት ፡ ባፋቸው ፡ ይናገሩታል ፡ ብለው ፡ እንደሚያስቡ ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፬ / የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ በማለቱ ፡ የቀና ፡ ቢኾን ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በማለቱ ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ ተከትሏል ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ በልባቸው ፡ ሳያምኑ ፡ በአፋቸው ፡ ይናገራሉ ፡ አላልንም ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ በ፲፪ኛው ፡ ቍጥር ፡ በአካለ ፡ ቃል ፡ የሚገኘውን ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ አካል ፡ ይሉታል ፡ ብለው ፡ እንደተናገሩት ፡ ክልኤ ፡ ባሕርይ ፡ የምትሉት ፡ ይህንኑ ፡ እኛ ፡ አካል ፡ የምንለውን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ማለታችሁ ፡ የማያጠራጥር ፡ ነገር ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፭ / እውነተኛውን ፡ የታሪክ ፡ ኹኔታ ፡ ትቶ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የማይስማሙ ፡ ኹለት ፡ ጉባኤያት ፡ አንዱ ፡ በ፬፻፶፩ ፡ ዓ/ም ፡ የተደረገውና ፡ እውጣኪን ፡ ያወገዘው ፡ ኹለተኛው ፡ የቀደሙትን ፡ የምስቱን ፡ ጉባኤያት ፡ ትምርት ፡ አፍርሶ ፡ የንስጥሮስንና ፡ የእውጣኪን ፡ ባህል ፡ ተቀብሎ ፡ አፀተምሯል ፡ የሚሉት ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ታሪክ ፡ እንዳለ ፡ አድርጎ ፡ ቢታሰብ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ/ም የተደረገውን ፡ እውነተኛውን ፡ ጉባኤ ፡ ተቀብለው ፡ ኹለተኛውን ፡ ያወግዙታል ፡ ይህም ፡ ማለት ፡ በ፬፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተደረገውን ፡ እውነተኛውን ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ ይቀበሉታል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፭ / እንደ ፡ አሁኑ ፡ አነጋገርዎ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ነገር ፡ አመዛዝኖ ፡ አበጥሮ ፡ ከእውነተኛው ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ አይችሉም ፡ እንደ ፡ መስከ ፡ ወኃ ፡ በመኖራቸው ፡ ይሐዳሉ ፡ ማለትዎ ፡ ነው ። ኢትዮጵያውያን ፡ የሚፈልጉት ፡ ጉባኤው ፡ የሰጠው ፡ ውጤት ፡ ጠቃሚ ፡ መኾኑንና ፡ አለመኾኑን ፡ ብቻ ፡ ስለኾነ ፡ አንደኛም ፡ ኾነ ፡ ኹለተኛም ፡ ኾነ ፡ የሚቃወሙት ፡ ያንኑ ፡ በክልኤ ፡ ባሕርያት ፡ ብሎ ፡ የወሰነውን ፡ በ፬፻፶፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የተደረገውን ፡ ጉባኤ ፡ ነው ።

## ዶ ራ ሲ ።

፲፮ / ኢትዮጵያውያንንና ፡ ካቶሊካውያንን ፡ ለማቀራረብ ፡ ሲደከም ፡ በካቶሊክ ፡ ላይ ፡ ያላቸውን ፡ የተሳሳተ ፡ ግምት ፡ አስወግዶ ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ እውነተኛ ፡ ታሪኩንና ፡ ግብጻውያን ፡ በቀልም ፡ ቀብተው ፡ ያሳይዋቸውን ፡ ትተው ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እውነተኛውን ፡ ፊቷን ፡ እንዳለ ፡ እንዲያውቁት ፡ ማድረግ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፮ / የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ እውነተኛ ፡ ታሪኩና ፡ እውነተኛ ፡ ፊቱ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ ኢትዮጵያ ፡ አይታ ፡ የነቀፈችው ፡ ነው ። አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የሚል ፡ ሌላ ፡ መልክ ፡ አላት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ልትቀበል ፡ ትችላለች ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለትንስ ፡ በፍጹም ፡ የማትቀበለው ፡ ናት ።

ግብጻውያን ፡ በቀለም ፡ ቀብተው ፡ ያሳይዋቸውን ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ግብጽ ፡ እጅዋን ፡ ይዛ ፡ የምትጎትታት ፡ ዕውር ፡ ማለትዎ ፡ ነው ። በእውነቱ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትንና ፡ ሌሎችንም ፡ የታሪክ ፡ መጻሕፍት ፡ ቢመለከቱ ፡ ኖሮ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከግብጽና ፡ ከሮማ ፡ በጠቅላላው ፡ ከመላው ፡ ዓለም ፡ አስቀድማ ፡ ሃይማኖተ ፡ አሪትን ፡ ከቤተ ፡ እስራኤል ፡ እንደተቀበለች ፡ ኋላም ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ሥጋ ፡ እንደ ፡ ለበሰ ፡ አውቃ ፡ ግብጽን ፡ የሚያጠምቅ ፡ የሚያቈርብ ፡ መዐርገ ፡ ክህነት ፡ ያለው ፡ መምህር ፡ ላኪልኝ ፡ ብላ ፡ ከመጠየቅ ፡ በቀር ፡ ግብጽ ፡ አስባ ፡ መጥታ ፡ ያላስተማረቻትና ፡ ያላጠመቀቻት ፡ መኾኗን ፡ በተረዱ ፡ ነበረ ።

ይህንንም ፡ ተረድተውት ፡ ቢኾን ፡ ሀገርዎ ፡ ቃለመኪም ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ሊባዕድ ፡ ጥገኛ ፡ ኾነው ፡ አይሰድቧትም ፡ ነበረ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ እርስዎ ፡ አይደሉም ፡ እናትና ፡ አባትዎ ፡ አስቀድመው ፡ የሀገርዎን ፡ ታሪክና ፡ ባህል ፡ ሳያስጠኑ ፡ ለባዕድ ፡ አሳልፈው ፡ ስለሰጡዎ ፡ ነው ።

እኛስ ፡ በማንም ፡ ሐሳብ ፡ የማንመራ ፡ የቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ከላይ ፡ እርእስታቸውን ፡ ከታች ፡ ኅዳጋቸውን ፡ ተመልክተን ፡ አውጥተን ፡ አውርደን ፡ እውነተኛውን ፡ ምሥጢር ፡ ተረድተን ፡ የምንናገር ፡ ነን ። ይህንንም ፡ በጻፍንልው ፡ መልስ ፡ ሊረዱት ፡ ይችላሉና ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ በደንብ ፡ የተዋወቅን ፡ መኾናችንን ፡ ተረድተው ፡ ንግግርዎን ፡ ያርሙ ።

## ዶ ራ ሲ ።

፲፯ / የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ ተቀባይ ፡ አድርገው ፡ የሚገምቱት ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ፡የንስጥሮስንና ፡ የአውጣኪን ፡ ባህል ፡ ያወገዘ ፡ መኾኑን ፡ የቄርሎስ ፡ ትምህርትና ፡ የኬልቄዶን ፡ ውሳኔ ፡ በመሠረቱ ፡ ያው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዲዮስቆሮስም ፡ የአውጣኪ ፡ ባለቤራ ፡ መኾኑን ፡ ሊያስረዱዋቸው ፡ ቢችሉ፡ ኖሮ ፡ ከካቶሊክ ፡ ትምህርት ፡ የሚለዩበት ፡ ምክንያት ፡ አይኖራቸውም ፡ ነበረ ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፯ / ሀ/ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ አወገዘ ፡ ለሚሉት ፡ በጉባኤ ፡ ኤፌሶን ፡ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ኾና ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ብላ ፡ ንስጥሮስን ፡ ማውገዟ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጉባኤ ፡ ኬልቄዶንስ ፡ በክልኤ ፡ ባሕርይ ፡ ብሎ ፡ በፈሊጥ ፡ አደሰው ፡ እንጂ ፡ አላወገዘውም ።

ለ/ የኬልቄዶን ፡ ውሳኔ ፡ በመሠረቱ ፡ ከቄርሎስ ፡ ትምህርት ፡ ጋራ ፡ ፩ ፡ ነው ፡ ስለሚሉት ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ኋላ ፡ በኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ብሎ ፡ እስኪለውጠው ፡ ድረስ ፡ በቄርሎስ ፡ ጊዜ ፡ መሠረቱ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እርግጥ ፡ ነው ።

ሐ/ ዲዮስቆሮስ ፡ ቃል ፡ ሕማም ፡ ሞት ፡ የሚስማማውን ፡ ግዙፍ ፡ ሥጋን ፡ ተዋሐደ ፡ ብሎ ፡ አስተማረ ፡ እንጂ ፡ የአውጣኪ ፡ ሴረኛ ፡ ኾኖ ፡ እንደ ፡ አውጣ ኪ ፡ ረቂቅ ፡ ሥጋን ፡ ተዋሐደ ፡

ሕማም ፡ ሞት ፡ አልተሰማውም ፡ ብሎ ፡ አላስተማረም ፡ በመጽሐፉም ፡ ተጽፎ ፡ አይገኝ ፡ እናንተ ፡ ጠላቶቹ ፡ አወራችሁ ፡ ብለን ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ልንል ፡ አንችልም ።

መ/ ይህንን ፡ ቢያስረዱዋቸው ፡ ኖሮ ፡ ለሚሉትም ፡ ይህንን ፡ የሚሉትን ፡ ኹሉ ፡ እውነት ፡ አስመስላ ፡ ለማሳመን ፡ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በየጊዜው ፡ ብዙ ፡ ደክማ ፡ ነበረ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ቢኾን ፡ ሐሰት ፡ እውነት ፡ ሊኾን ፡ ባለመቻሉ ፡ ልታስረዳ ፡ አልተቻላትም ።

የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በይመስላልና ፡ በይኾናል ፡ የበየነችውን ፡ ለትስብእት ፡ አካል ፡ የለውም ፡ መለኮት ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእትን ፡ እንጂ ፡ አካለ ፡ ትስብእትን ፡ አልተዋሐደም ፡ ካለች ፡ በኋላ ፡ መልሳ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ባሕርይ ፡ አልተዋሐደም ፡ ማለቷን ።

መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብም ፡ ከወልድም ፡ ሠረጸ ፡ ማለቷን ፡ ስርዛ ፡ እንደአባቶቻችን ፡ እንደ ፡ ሐዋርያት ፡ እንደ ፡ ፫፻ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብ ፡ ብቻ ፡ ሠረጸ ፡ እንጂ ፡ ከወልድ ፡ አልሠረጸም ፡ ቃልም ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለውን ፡ ሰብአዊ ፡ አካል ፡ በሕፃናት ፡ መጠን ፡ ነሥቶ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኾነ ፡ የምትል ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ የሮማና ፡ የኢትዮጵያ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሚገናኙበት ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ የማይገኝ ፡ መኾኑን ፡ ይወቁ ።

ደ ራ ሲ ።

፲፰ / ይህ ፡ ቢገኝ ፡ የሚታረመውና ፡ የሚተካከለው ፡ የቃሎች ፡ ትርጉም ፡ ብቻ ፡ ነበረ ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፲፰ / ሮማውያን ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ሊያስረዱዋቸው ፡ የሚመኙዋቸው ፡ ነገሮች ፡ ኹሉ ፡ መሠረት ፡ የሌላቸው ፡ መኾናቸውን ፡ ዐውቀው ፡ ሕሊናዎን ፡ በዚህ ፡ ሐሳብ ፡ ከመባከን ፡ ያሳርፉት ።

ምዕራፍ ፱ ።

ደ ራ ሲ ው ።

ኢትዮጵያውያን ፡ የክርስቶስን ፡ አካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ ሲተረጉሙ ፡ ስለሚያገቧቸው ።

ቃ ሎ ች ።

ደ ራ ሲ ው ።

፩ / ኢትዮጵያውያኖቹ ፡ በቀድሞውም ፡ ኾነ ፡ ባኹኑም ፡ ዘመን ፡ በመጻሕፍቶቻቸው ፡ ውስጥ ፡ በክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ ይገኛል ፡ ብለው ፡ በግልጥ ፡ ያምናሉ ፤ በብዙዎች ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ ናቸው ፡ የሚባሉበት ፡ ምክንያት ፡ በዚህ ፡ የተመሠረተ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፩ / በቀድሞው ፡ ኾነ ፡ ባኹኑ ፡ ዘመን ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ማለታችን ፡ የማይካድ ፡ ነው ። አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ስንልም ፡ ቅድመ ፡ ተዋሕዶ ፡ መለኮታዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ አካለ ፡ መለኮት ፡ በቃልነት ፡ ካዊን ፡ ለብቻ ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ አካለ ፡ ትስብእት ፡ በአዳማዊነት ፡ ለብቻ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እናውቃለን ።

የመለኮት ፡ አካሉ ፡ ምሉእ ፡ ስፉሕ ፡ ረቂቅ ፡ ነው ። ባሕርዩም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ዘውእቱ ፡ ብርሃነ ፡ ስብሓቲሁ ፡ ወአምሳለ ፡ አርአያሁ ፡ ወነበረ ፡ በየማነ ፡ ዕበዩ ፡ በሰማያት ፡ ያለውን ፡ ዮሐንስ ፡ አፈወርቅ ፡ ሲተረጉም ፡ እስመ ፡ ሶበ ፡ ኢረከበ ፡ ስመ ፡ ዘይኤምር ፡ ኀበ ፡ ባሕርይሁ ፡ ብህለ ፡ በዝንቱ ፡ ስም ፡ እስመ ፡ ዕበይ ፡ ወኢስብሐት ፡ ኢይኤምሩ ፡ ኀበ ፡ ውእቱ ፡ ስም ፡ ዘፈቀደ ፡ ይዝክር ።

ዕበይ ፡ ስብሐት ፡ ማለት ፤ ሊናገረው ፡ የወደደውን ፡ የባሕርይ ፡ ስሙን ፡ ሊያስረዱ ፡ አይችሉምና ፡ የባሕርይ ፡ ስሙን ፡ የሚያስረዳ ፡ ስም ፡ ባያገኝ ፡ የባሕርይ ፡ ስሙን ፡ ዕበይ ፡ ስብሐት ፡ በማለት ፡ ተናገረ ፡ ብሎ ፡ የባሕርዩን ፡ አለመመርመር ፡ ምንም ፡ ቢያስረዳን ፡ ዐቅማችን ፡ የፈቀደልንን ፡ ያኽል ፡ ባሕርዩ ፡ ከሂል ፡ ከሃሊነት ፡ ነው ፡ እንላለን ።

የትስብእትም ፡ አካሉ ፡ ግዙፍ ፡ የሚታይ ፡ የሚጨበጥ ፡ የሚዳሰስ ፡ ነው ። ባሕርዩም ፡ ለተፈጥሮው ፡ ምክንያት ፡ የኾኑ ፡ የወኃ ፡ የመሬት ፡ የነፋስ ፤ የእሳት ፡ የነፍስ ፡ ባሕርያት ፡ ናቸው ። ይህ ፡

አካሉ ፡ ምሉእ ፡ ስፉሕ ፡ ረቂቅ ፤ ባሕርዩ ፡ ከሂል ፡ የኾነ ፡ መለኮት ፤ ይህን ፡ አካሉ ፡ ግዙፍ ፡ ውሱን ፡ ባሕርዩ ፡ የወኀ ፡ የመሬት ፡ የነፋስ ፡ የእሳት ፡ የነፋስ ፡ ባሕርይ ፡ የኾነ ፡ ትስብእትን ፡ ሲዋሐድ ፡ መለኮት ፡ ምልአቱን ፡ ስፋቱን ፡ ርቀቱን ፡ ለቆ ፡ ሳይገዝፍ ፡ ሳይለወጥ ፡ ትስብእትም ፡ ውሱንነቱን ፡ ግዙፍነቱን ፡ ለቆ ፡ ሳይረቅ ፡ ሳይለወጥ ፡ በተዐቅቦ ፡ ነው ።

ተዐቅቦውም ፡ እንደ ፡ ነፍስና ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ ትዐቅቦ ፡ ነው ። ሥጋ ፡ አካሉ ፡ ግዙፍ ፡ ባሕርዩ ፡ በውኀ ፡ በመሬት ፡ በነፋስ ፡ በእሳት ፡ ያሉ ፡ ባሕርያት ፡ ርጥበት ፡ ይብሰት ፡ ውዕየት ፡ ቊረት ፡ ነው ። የነፍስ ፡ አካሏ ፡ ረቂቅ ፡ ባሕርይዋ ፡ ለባዊትነት ፡ ነባቢትነት ፡ ሕያዊትነት ፡ ነው ።

እነሆ ፡ ኹለቱ ፡ ነፍስና ፡ ሥጋ ፡ ሲዋሐዱ ፡ ሥጋ ፡ ግዙፉን ፡ ለቆ ፡ ሳይረቅ ፡ ሳይለወጥ ፡ ነፍስ ፡ ርቀቷን ፡ ለቃ ፡ ሳትገዝፍ ፡ ሳትለወጥ ፡ ነው ። የነሀም ፡ አካላቸው ፡ ሲዋሐድ ፡ ባሕርያቸውም ፡ እንደዚሁ ፡ ተዋሕዷል ፡ እንጂ ፡ ተለይቶ ፡ የቀረ ፡ አይደለም ።

ነፍስና ፡ ሥጋ ፡ በተዐቅቦ ፡ ተዋሕደው ፡ የተገኘው ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ እንዳይባል ፡ ረቂቅ ፡ መለኮትም ፡ ግዙፍ ፡ ሥጋን ፡ በተዐቅቦ ፡ ቢዋሐድ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ።

የነፍስና ፡ የሥጋ ፡ አካላቸው ፡ ሲዋሐድ ፡ ባሕርያቸው ፡ ከተዋሕዶ ፡ በአፍአ ፡ እንዳልቀረ ፡ መለኮትና ፡ ትስብእትም ፡ አካላቸው ፡ ሲዋሐድ ፡ ባሕርያቸው ፡ አልተዋሐደም ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ።

ይህንም ፡ ምንም ፡ ዛሬ ፡ ስለመሰከረባቸው ፡ የሮም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አይደለም ፡ አናውቀውም ብለው ፡ ሊክዱት ፡ ቢሞክሩ ፡ ከጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ በፊት ፡ የነበረው ፡ የሮም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡሊድስ ፡ በሃይማኖተ ፡ አበው ፡ አምልቶ ፡ አስፍቶ ፡ አጉልቶ ፡ ነግሮናል ። ቃሉም ፡ በም ፡ ፫ ፡ በቍ ፡ ፲፯ ። የጠቀስነው ፡ ነው ፡ አሁን ፡ ኹለተኛ ፡ ከዚህ ፡ ልንጠቅሰው ፡ አላስፈለገም ፡ ያንኑ ፡ መመልከት ፡ በቂ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ መሠረት ፡ አድርገን ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለታችን ፡ አይካድም ።

## ደ ራ ሲ ።

፩ / ፊት ፡ በተጠቀሱትና ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ መገኘታቸውን ፡ በግልጥ ፡ በሚክዱባቸው ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ የቃሎችን ፡ መደባለቅና ፡ አለመወሰን ፡ እናገኛለን ፡ የባሕርይና ፡ የአካልም ፡ አሳቦች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በጽሑፎች ፡ እየተወራረሱ ፡ ተነግረዋል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፩ / በእኛ ፡ ዘንድ ፡ የአካልና ፡ የባሕርይ ፡ አሳቦች ፡ በየበኩላቸው ፡ ደንባቸውን ፡ ይዘው ፡ ይገኛሉ ፡ እንጂ ፡ የተደባለቁና ፡ ያልተወሰኑ ፡ አላገባብ ፡ የተወራረሱ ፡ አይደሉም ። የአካልን ፤ የባሕርይን ፡ የቱሳሔን ፡ የውላጤን ፡ የቡዐዴን ፡ የፍልጠትን ፡ ስልት ፡ ስልታቸውን ፡ ለይተን ፡ ባለፉት ፡ መሥመሮች ፡ ወይም ፡ አንቀጾች ፡ ጽፈናል ፡ ወደፊትም ፡ በሚመጣው ፡ አስፈላጊ ፡ ኾኖ ፡ ስናገኘው ፡ ዘርዝረን ፡ መጻፋችንን ፡ አንተውምና ፡ ጠንቅቀው ፡ ሲመለከቱት ፡ ስለአካልና ፡ ስለባሕርይ ፡ ያለን ፡ አስተያየት ፡ የማይለወጥ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ መኾኑን ፡ ሊረዱ ፡ ይችላሉ ።

## ደ ራ ሲ ።

፪ / የምሥራቅንና ፡ የምዕራብን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ለያይተዋቸው ፡ ካሉ ፡ ምክንያቶች ፡ አንዱ ፡ የአሳብ ፡ ወይም ፡ የትምህርት ፡ ልዩነት ፡ ከመኾኑ ፡ ይልቅ ፡ የሃይማኖትን ፡ ትምርት ፡ የሚገልጡበት ፡ ያነጋገር ፡ ልዩነትና ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ አለመተዋወቅ ፡ ነው ። በሃይማኖት ፡ መለያየታቸው ፡ በቋንቋ ፡ መለያየታቸውን ፡ ያህል ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ክርስቲያኖችን ፡ ለያይቶ ፡ ያለውን ፡ ምሽግ ፡ ለማረስ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አብሮ ፡ አስፈላጊ ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ ለመግለጥ ፡ የሚያገለግል ፡ ስለቋንቋው ፡ ጉዳይ ፡ መመካከርና ፡ በቂ ፡ የጎብረት ፡ አነጋገር ፡ መወሰን ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፪ / ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለሐዋርያት ፡ አስቀድሞ ፡ የኹሉን ፡ ቋንቋ ፡ ባይገልጽላቸው ፡ ወንጌልን ፡ ከኹሉ ፡ ሊያዳርሱ ፡ ባልቻሉም ፡ ነበር ፤ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ ቢኾን ፡ በቋንቋ ፡ መተባበርን ፡ ያህል ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ አይገኝም ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ሐሳብ ፡ ማንም ፡ ሊቃወመው ፡ የማይገባ ፡ መልካም ፡ አሳብ ፡ ስለኾነ ፡ የምንቀበለውና ፡ የምንስማማበት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የምንቃወመው ፡ አይደለም ።

ደ ራ ሲ ።

፩/ /ከሮማ ፡ የተለዩ ፡ ምሥራቃውያን ፡ የሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ የሚገልጡበት ፡ ያነጋገራቸው ፡ ልዩነት ፡ የፍልስፍናና ፡ የሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ እጅግ ፡ የሠለጠኑ ፡ ታላላቅ ፡ ሊቃውንት ፡ ከኾኑ ፡ ካገራቸው ፡ ልጆች ፡ የወረሱት ፡ ስለሆነ ፡ እንዳኗኗር ፡ የፍልስፍና ፡ አስተያየት ፡ አይታጣውም ።

የኢትዮጵያውያን ፡ ከሮማ ፡ አለመስማማት ፡ ግን ፡ የፍልስፍና ፡ ሳይኾን ፡ ባነጋገሩ ፡ ልዩነት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፩/ በዚህ ፡ አነጋገርዎ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከልጆቿ ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ የሠለጠኑ ፡ ሊቃውንት ፡ እንደ ፡ ሌሏት ፡ አድርገው ፡ ተናግረዋል ። ኢትዮጵያ ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ከኹሉ ፡ አስቀድማ ፡ የሠለጠነች ፡ መኾኗን ፡ ለመረዳት ፡ በምዕራፍ ፡ በ፫ ቍ ፡ ፲፮ ፡ የጻፍኩልዎን ፡ ቢመለከቱ ፡ ይረዱታል ።

እንዲሁም ፡ ማለትዎ ፡ የምሥጢረ ፡ ሥላሴና ፡ የምሥጢረ ፡ ሥጋዌ ፡ ትምህርት ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ቴክኒካዊ ፡ ሥራ ፡ በሳይንስ ፡ መርማሪዎች ፡ የሚገኝ ፡ መስሎዎ ፡ ነው ። እኛስ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እሴብሐከ ፡ እግዚኦ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ፡ እስመ ፡ ኅባእኮ ፡ ለዝንቱ ፡ እምጠቢባን ፡ ወእማእምራን ፡ ወከሠትኮ ፡ ለሕፃናት ።

የሰማይ ፡ የምድር ፡ ጌታ ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡ ምሥጢር ፡ ከዋዐቆች ፡ ከፈላስፎች ፡ ሰውረህ ፡ ለሕፃናት ፡ አእምሮ ፡ ገልጸኸዋልና ፡ አመሰግንሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ማቴ ፡ ፲፩ ፡ ፳፭ ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ እስመ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ፡ እነ ፡ አኅጕል ፡ ጥበቢሆሙ ፡ ለጠቢባን ፡ ወእሜንን ፡ ምክሮሙ ፡ ለመካርያን ። አኮኑ ፡ አዕበዳ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለጥበበ ፡ ዝ ፡ ዓለም ፡ እስመ ፡ በጥበቡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘኢየአምርዎ ፡ ዓለም ፡ በጥበቢሆሙ ፡ መከረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ያድኅኖሙ ፡ ለእለ ፡ የአምኑ ፡ በእበደ ፡ ሥጋ ። አብዳኒሁ ፡ ለዝ ፡ ዓለም ፡ ኀረየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ያስተኃፍሮሙ ፡ ለጠቢባን ፡ ብሎ ፡ ይህ ፡ የሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ከፈላስፎች ፡ ዕውቀት ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ፈላስፎች ፡ ሊደርሱበት ፡ የማይችሉ ፡ መኾኑን ፡ ስለነገረን ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲፱ - ፳፭ ፡ ከጌታ ፡ ከሐዋርያት ፡ ያገኘነውን ፡ ትምህርት ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ተግባረ ፡ እድ ፡ ትምህርት ፡ በፍልስፍና ፡ ልንለውጠውና ፡ ልንገለባብጠው ፡ አንፈቅድም ፡ በዚኽውም ፡ ላይ ፡ እመቦ ፡ መልአክ ፡ እምሰማይ ፡ ዘመሀረክሙ ፡ ካልአ ፡ እምዘመሀርናክሙ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ፡ ብሎ ፡ አስጠንቅቆናል ።

## ክፍል ፡ ፩ ፡ የቃሎች ፡ ምርመራ ።

ደ ራ ሲ ።

፩/ ብዙዎች ፡ ጸሐፊዎች ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አካልና ፡ ባሕርይ ፡ ለሚሉት ፡ ቃሎች ፡ እንደ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ሊቃውንት ፡ አሳብ ፡ በፍልስፍና ፡ ምርመራ ፡ የተደነገገ ፡ ትርጕም ፡ ያላቸው ፡ ይመስላቸዋል ኢትዮጵያውያን ፡ ለነዚህ ፡ ቃሎች ፡ የሚሰጡት ፡ ትርጕም ፡ ተራቅቆ ፡ የሌለበት ፡ ግዙፍና ፡ የተራ ፡ ሕዝብ ፡ ትርጕም ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፩/ ሮማውያን ፡ በፍልስፍና ፡ ያራቀቁትን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በግዙፍ ፡ የተናገሩትን ፡ ከዚሁ ፡ ላይ ፡ በመለየት ፡ ሮማውያን ፡ አራቀው ፡ እንዲህ ፡ የሚሉትን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ባልተጣራ ፡ አነጋገር ፡ እንዲህ ፡ ይሉታል ፡ ብለው ፡ ጽፈው ፡ ቢኾን ፡ የኹለቱንም ፡ ንግግር ፡ አመዛዝኖ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ይመች ፡ ነበረ ። ይኽ ፡ ካልኾነ ፡ ግን ፡ ለዚህ ፡ አነጋገር ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ ሊሰጠው ፡ አይቻልም ፡ (ስለኾነም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በግዙፍ ፡ ቢናገሩ ፡ ሮማውያን ፡ በተራቅቆ ፡ ቢናገሩ ፡ ስም ፡ ከመለዋወጥ ፡ በቀር ፡ የአካልንም ፡ ኾነ ፡ የባሕርይን ፡ ክፍፍላቸውንና ፡ የሥራ ፡ ውጤታቸውን ፡ መለወጥና ፡ ለአሳቡ ፡ ዶጋፊ ፡ ማድረግ ፡ የሚቻለው ፡ የለም ። ስለዚሁ ፡ ስም ፡ አጠራራቸውን ፡ በማራቀቅ ፡ የተደከመውን ፡ ድካም ፡ ዋጋ ፡ እንዳለው ፡ አድርገን ፡ አንቆጥረውም ። ምክንያቱም ፡ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ በ፩ኛው ፡ ቍጥር ፡ ጠቅሼ ፡ እንዳስረዳሁት ፡ እግዚአብሔር ፡ የሃይማኖትን ፡ ምሥጢር ፡ ዐዋቆች ፡ ነን ፡ ከሚሉ ፡ ሰውሮ ፡ ዐላዋቆች ፡ ነን ፡ ለሚሉት ፡ እንደ ፡ ገለጸው ፡ ስለምናውቅ ፡ ነው ።

ደ ራ ሲ ።

፪/ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ሲያስተምሩ ፡ የሚናገሩባቸው ፡ ቃሎች ፡ ከዚህ ፡ አምጥተን ፡ ትርጕማቸውን ፡ ብንመረምረው ፡ የምንለው ፡ በፍጹም ፡ እውነት ፡ መኾኑን ፡ እን

ረዳለን ፡ ብለው ፡ እስከዚህ ፡ ክፍል ፡ መጨረሻ ፡ እስከ ፡ ኹለተኛው ፡ ክፍል ፡ ድረስ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለ ፡ አካልና ፡ ስለ ፡ ባሕርይ ፡ ሲናገሩ ፡ እንዲህ ፡ ይላሉ ፡ እንዲህም ፡ ይላሉ ፡ እንዲህም ፡ ይላሉ ፡ እያሉ ፡ ብዙ ፡ የተማታ ፡ ነገር ፡ ጽፈዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፮/ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የጸፉትን ፡ ስንመለከተው ፡ የኢትዮጵያን ፡ የሃይማኖት ፡ ባህል ፤ ያገኙትን ፡ መጽሐፍ ፡ ኹሉ ፡ በመመልከት ፡ ሊረዱ ፡ ያሰቡ ፡ መኾንዎን ፡ ተረድተናል ፡ መጽሐፍ ፡ የሰጡትን ፡ ቃል ፡ ይዞ ፡ ከመገኘቱ ፡ በቀር ፡ የጠመመ ፡ መስሎ ፡ የሚታየውን ፡ አቃንቶ ፡ የረቀቀውን ፡ አጉልቶ ፡ ሊያስረዳ ፡ ስለማይችል ፡ እንዲሁም ፡ ይላሉ ፡ እንዲህም ፡ ይላሉ ፡ በማለት ፡ ሐሳብዎ ፡ ባክኖ ፡ ቀርቷል ። በዚህስ ፡ ፈንታ ፡ የተጣሉ ፡ መሰለው ፡ የታይዎን፡መጻሕፍት፡ ከኢትዮጵያ ፡ መምህራን ፡ ዘንድ ፡ ይዘው ፡ ቀርበው ፡ ይህ ፡ እንደምንድን ፡ ነው ፡ ይህስ ፡ እንደምንድን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ጠይቀው ፡ ቢኾን ፡ ድርሱን ፡ በተረዱት ፡ ነበር ። እኛ ፡ የምንለውን ፡ እኛ ፡ ስናውቀው ፡ እኛ ፡ የምንለውን ፡ ለእኛ ፡ ለማስረዳት ፡ አንዱን ፡ ከአንዱ ፡ ከማማታት ፡ ካቶሊካውያን ፡ ስለአካልም ፡ ሆነ ፡ ስለባሕርይ ፡ እንዲህ ፡ ይላሉ ፡ ብለው ፡ ጽፈውልን ፡ ቢኾን ፡ የሚያስማማ ፡ መንገድ ፡ ቢገኝለት ፡ የስምምነቱን ፤ ባይገኝለት ፡ መልሱን ፡ ለመጻፍ ፡ ምቹ ፡ መንገድ ፡ በተገኘለት ፡ ነበረ ። በእኛ ፡ በኩል ፡ ስለአካልና ፡ ስለባሕርይ ፡ ያለንን ፡ አስተያየት ፡ ባለፈው ፡ አንቀጽ ፡ በም ፡ ፫ ፡ በቍ ፡ ከ፷—፲፫ ፡ በስፈው ፡ ጽፈናል ። ነገር ፡ ግን ፡ ብንጽፍም ፡ ያለፈው ፡ ይበቃል ፡ ብለን ፡ ዝም ፡ የምንል ፡ አይደለንም፡ በያንቀጹ ፡ መልሳችንን ፡ እንቀጥላለን ።

## ደ ራ ሲ ።

፯/ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ሲያስተምሩ ፡ የሚናገሩባቸውን ፡ ቃሎች ፡ ከዚህ ፡ አምጥተን ፡ ትርጕማቸውን ፡ ብንመረምረው ፡ የምንለው ፡ በፍጹም ፡ እውነት፡ መኾኑ፡ ይረዳል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፯/ ይህን ፡ ማለት ፡ አስቀድሞ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ተዋሕዶ ፡ የሚናገሩትን ፡ ባህል ፡ ከመምህራን ፡ ጠይቆ ፡ ተረድቶ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ አንዳንድ ፡ የተቆራረጡ ፡ ታሪኮችን ፡ በማንበብ ፡ አልነበረም ፡ ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ሐሳብ ፡ የሚፈጸም ፡ አይመስለኝም ፡ ከኾነም ፡ ትርጕማቸውን ፡ በሚገባ ፡ መርምረው ፡ ሲያስረዱ ፡ ለመስማት ፡ እንጠባበቃለን ።

## ደ ራ ሲ ።

፰/ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ኾነ ፡ ብለው ፡ በሚያደርጓቸው ፡ የሐሳብ ፡ ውሳኔዎች ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አካል ፡ ሲሉ ፡ ግዙፍ ፡ ሥጋ ፡ ገላ ፡ ወይም ፡ ቊመት ፡ ማለትን ፡ ያሰማሉ ። ባሕርይም ፡ ሲሉ ፡ ስሜት ፡ ያለው ፡ ሥጋ ፡ ማለት ፡ ያንድ ፡ ሕያው ፡ ኑሮ ፡ የቆመው ፡ ግዙፍ ፡ ሥጋ ፡ ጠባዕያት ፡ ማለትን ፡ ያሰማሉ ። ለምሳሌ ፡ የጴጥሮስ ፡ አካል ፡ ሲባል ፡ ገላው ፡ ወይም ፡ ግዙፍ ፡ ሰውነቱ ፡ በመላው ፡ መኾኑ ፡ ነው ፡ ባሕርዩ ፡ ሲባል ፡ ግን ፡ ገላው ፡ ወይም ፡ ግዙፍ ፡ ሰውነቱ ፡ የስሜት ፡ ጠባይዕ ፡ ያለው ፡ መኾኑ ፡ ነው ።

ባጭሩ ፡ ባሕርዩ ፡ የሚባለው ፡ ግዙፍ ፡ ሰውነቱ ፡ ስሜት ፡ ሲኖረውና ፡ መታመም ፡ የሚችል ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ከኢትዮጵያውያን ፡ ባህል ፡ የተለየ ፡ አነጋገር ፡ ተናግረዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፰/ ስለአካል ፡ አካል ፡ ስለግዙፍ ፡ ሥጋ ፡ ገላ ፡ ወይም ፡ ቊመት ፡ ማለትን ፡ ያሰማሉ ። ለምሳሌ ፡ የጴጥሮስ ፡ አካል ፡ ሲባል ፡ ገላው ፡ ወይም ፡ ግዙፍ ፡ ሰውነቱ ፡ በመላው ፡ መኾኑ ፡ ነው ፡ ያሉት ፡ ትክክለኛ ፡ ንግግር ፡ ነው ። ስለባሕርይ ፡ ግን ፡ ስሜት ፡ ያለው ፡ ሥጋ ፡ ማለት ፡ ገላው ፡ ወይም ፡ ግዙፍ ፡ ሰውነቱ ፡ የስሜት ፡ ጠባይዕ ፡ ያለው ፡ መኾኑ ፡ ነው ፡ ያሉት ፡ አነጋገር ፡ ያንኑ ፡ የአካል ፡ ኹናቴ ፡ የሚገልጽ ፡ አነጋገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የባሕርይን ፡ ኹናቴ ፡ የሚገልጥ ፡ አይደለም ። ምክንያቱም ፡ አካል ፡ ባሕርይ ፡ ስንል ፡ ኹለቱንም ፡ ለየራሳቸው ፡ አንቀጽ ፡ ተቀባዮች ፡ የነገር ፡ ባለቤቶች ፡ አድርገን ፡ እንመለከታቸዋለን ፤ ይህ ፡ ስለባሕርይ ፡ የተናገሩት ፡ አነጋገር ፡ ግን ፡ እንደዚያው ፡ ስለአካል ፡ እንደተናገሩት ፡ አነጋገር ፡ ባሕርይን ፡ የቅጽል ፡ ባለቤት ፡ የነገር ፡ ተሳቢ ፡ አድርጎ ፡ የአካልን ፡ ባለቤትነት ፡ ከመግለጽ ፡ በቀር ፡ የባሕርይን ፡ ባለቤትነት፡ የማያሳይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ። በእኛ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ ስለአካልና ፡ ስለባሕርይ ፡ በም ፡ ፫ ፡ በቍ ፡ ፲፱ ፡ በሰፈው ፡ ስለጻፍን ፡ ያንኑ ፡ መመልከት ፡ በቂ ፡ ነው ።

## ድ ራ ሲ ።

፱/ መዝገበ ፡ ሃይማኖት ፡ ስለሚለው ፡ መጽሐፍ ፡ አካል ፡ ማለት ፡ እጅ ፡ እግር ፡ ዐይን ፡ ጆሮ ፡ ጥርስ ፡ አፍ ፡ ፊት ፡ ከእግር ፡ ጥፍር ፡ እስከራስ ፡ ጠጕር ፡ ማለት ፡ ነው ። የሥላሴ ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ የማይራበው ፡ የማይጠማው ፡ የማይታመም ፡ የማይደክም ፡ የማይሞት ፡ ማለት ፡ ነው!! የሰው ፡ ባሕርይ ፡ ማለትም ፡ የሚርበው ፡ የሚጠማው ፡ የሚታመም ፡ የሚሞት ፡ የሚደክም ፡ ማለት ፡ ነው፣ ይላል ፡ ብለዋል ።

፲/ አሁን ፡ በዚህ ፡ አስተያየትዎ ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ መራብ ፡ መጠማት ፡ መታመም ፡ መሞት ፡ ያለው ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፤ አለመራብ ፡ አለመጠማት ፡ አለ ፡ መድከም ፡ አለመሞት ፡ የሥላሴ ፡ ባሕርይ ፡ ያለ ፡ በማስመሰል ፡ ገምተው ፡ ተናግረዋል ።

ባሕርይ ፡ ማለት ፡ በእሳት ፡ ውዕየትና ፡ በወኃ ፡ ርጥበት ፡ እንደተናገርነው ፡ በሴኮንድ ፡ በሚቆጠር ፡ ጊዜም ፡ ቢኾን ፡ ተፈልጦ ፡ ሳይኖርበት ፡ በአካል ፡ ህልው ፡ ኾኖ ፡ የሚኖር ፡ ነገር ፡ ነው ። መራብ መጠማት ፡ መታመም ፡ መሞት ፡ ግን ፡ በእኽል ፡ በውኃ ፡ በመድኃኒት ፡ የሚርቅ ፡ እኽል ፡ ውኃ ፡ ወይም ፡ መድኃኒት ፡ ሲታጣ ፡ የሚመጣ ፡ ነው ። መራብ ፡ መጠማት ፡ መታመም ፡ መሞት ፤ የባሕርይ ፡ ተስማሚ ፡ ግብር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባሕርይ ፡ አይደለም ። ይህም ፡ መጽሐፍ ፡ በዚህ ፡ አነጋገሩ ፡ መራብ ፡ መጠማት ፡ መታመም ፡ መሞት ፡ ለሰው ፡ የባሕርይ ፡ ተስማሚ ፡ ግብር ፡ መኾኑን ፤ አለመራብ ፡ አለመጠማትም ፡ ለሥላሴ ፡ ባሕርይ ፡ ተስማሚ ፡ ግብር ፡ መኾኑን ፡ የሚያስረዳ ፡ አነጋገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መራብ ፡ መጠማት ፡ ራሱ ፡ የሰው ፡ ባሕርይ ፡ ነው ። አለመራብ ፡ አለመጠማትም ፡ የሥላሴ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ አለመኾኑን ፡ በቅጥነተ ፡ ልብ ፡ ይመልከቱልኝ ። እኛስ ፡ የባሕርይን ፡ ነገር ፤ ጠንቅቆ ፡ ለማስረዳት ፡ ምንም ፡ ዐቅማችን ፡ ባይፈቅድልን ፡ የተቻለንን ፡ ያኽል ፡ በ፩ኛ ፡ ም ፡ በቍ ፡ ፩ ፡ እንደገለጽነው ፡ ነው ፡ የምንለውጠው ፡ የለም ።

## ድ ራ ሲ ።

፲/ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ባሕርይ ፡ ሲሉ ፡ የሰው ፡ መንፈሳዊና ፡ ግዙፍ ፡ ክፍሎች ፡ ለየብቻቸው ፡ ተለይተው ፡ ማለትን ፡ ያስማሉ ፤ አካል ፡ ሲሉም ፡ ኹለቱ ፡ የሰው ፡ ክፍሎች ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ተሰብስበው ፡ ሰው ፡ በሙሉ ፡ ማለትን ፡ ያስማሉ ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲/ ይህ ፡ አነጋገር ፡ የሰው ፡ መንፈሳዊ ፡ ክፍሉ ፡ ሲል ፡ ነፍስን ፤ ግዙፍ ፡ ክፍሉ ፡ ሲል ፡ ሥጋን ፡ ይመለከታል ። ሥጋ ፡ ነፍስ ፡ ተለይታው ፡ ብቻውን ፡ ሲኾን ፡ ነፍስም ፡ ከሥጋ ፡ ተለይታ ፡ ብቻዋን ፡ ስትሆን ፡ ባሕርይ ፡ ይባላሉ ፡ ሲዋሐዱና ፡ አንድ ፡ ሲኾኑ ፡ ግን ፡ አካል ፡ ይባላሉ ፡ ብሎ ፡ የሚያስተምር፡ የለም ።

ስለኾነም ፡ ሰው ፡ ከመፈጠሩ ፡ አስቀድሞ ፡ ምን ፡ እንደነበረ ፡ ከምን ፡ ተፈጥሮ ፡ ከዚህ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ብንመረምር ፡ ለዚህ ፡ አነጋገር ፡ አንድ ፡ ስሜት ፡ እናገኝለት ፡ ይኾናል ። የሰው ፡ ተፈጥሮው ፡ ከውኃ ፡ ከመሬት ፡ ከነፋስ ፡ ከእሳት ፡ ነው ፡ እኒኽውም ፡ በየራሳቸው ፡ ሲጠሩ ፡ ባሕርያት ፡ ይባላሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ንግበር ፡ ሰብአ ፡ ባለጊዜ ፡ ካራቱ ፡ ባሕርያት ፡ ተጠራቅሞ ፡ ባምስተኛ ፡ ባሕርየ ፡ ነፍስ ፡ ሕያው ፡ የኾነ ፡ በሦስት ፡ ክንድ ፡ ከስንዝር ፡ ቁመት ፡ የተወሰነ ፡ ሰብአዊ ፡ አካል ፡ ተገኝቷል ። ስለዚህ ፡ ለተፈጥሮው ፡ ጥንት ፡ መሠረት ፡ የኾኑት ፡ ወኀ ፡ መሬት ፤ ነፋስ ፡ እሳት ፡ ነፍስ ፡ ባሕርያት ፡ ይባላሉ ። ከነዚህ ፡ ካምስቱ ፡ ባሕርያት ፡ ተጠራቅሞ ፡ የተገኘው ፡ ቅርጽ ፡ ሰብአዊ ፡ አካል ፡ ይባላል ፡ ቢባል ፡ እውነተኛ ፡ ነገር ፡ ነው ።

## ድ ራ ሲ ።

፲፩/ ስለዚህ ፡ ለክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ አሉት ፡ ሲባል ፡ ለነርሱ ፡ ሦስት ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ኾኖ ፡ ይሰማቸዋል ፡ ማለት ፡ ኹለቱ ፡ የሰው ፡ ባሕርዮች ፡ መንፈሳዊና ፡ ግዙፉ ፡ ሦስተኛው ፡ የመለኮት ፡ ባሕርይ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ኾኖ ፡ ይሰማቸዋል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፩/ ሰው ፡ ካራቱ ፡ ባሕርያት ፡ ተፈጥሮ ፡ ፭ኛ ፡ ነፍስ ፡ ተዋሕደው ፡ ስለተገኘ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ አራት ፡ ወይም ፡ አምስት ፡ አይባልም ። እንደዚኽውም ፡ መለኮታዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ አካለ ፡ ቃል ፤ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ ትስብእትን ፡ በሕፃናት ፡ መጠን ፡ ነሥቶ ፡ አካል ፡ ዘየአክልን ፡ ገንዘብ ፡ ቢያደርግ ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኾነ ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡

ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የምንል ፡ አይደለንም ። ስለዚህም ፡ የሮሙ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡሊዮስ ፡ በሃይማኖተ ፡ አበው ፡ አስፋፍቶ ፡ የጻፈውን ፡ በም ፡ ፫ ፡ በክፍል ፡ ፭ ፡ በቍ ፡ ፲፯ ፡ በሀ ፡ ፊደል ፡ ስለ ጠቀስነው ፡ ያነን ፡ ቢመለከቱ ፡ ይጠቅማል ።

እናንተን ፡ ካቶሊካውያንንም ፡ ያነኑ ፡ የምትሉትን ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ይላሉ ፡ እንላችኋለን ፡ እንጂ ፡ ሦስት ፡ ባሕርይ ፡ ይላሉ ፡ ብለናችሁ ፡ አናውቅም ።

ደ ራ ሲ ።

፲፪/ በእውነትም ፡ ባሕርይ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ለሚሰማው ፡ እን በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ይገኛሉ ፡ ማለት ፡ የማይሰማ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግልጥ ፡ ነው ፡ እን ርሱም ፡ ባሕርይ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ተራቅቆ ፡ በሌለው ፡ በግዙፉ ፡ ትርጕሙ ፡ ስለሚሰሙት ፡ በክር ስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ አሉ ፡ ማለት ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ ፬ ፡ እግሮች ፡ ፬ ፡ ዓይኖች ፡ ይገኛሉ ፡ ማለ ትን ፡ ያኽል ፡ ገሮርን ፡ የሚቀድ ፡ የኾነ ፡ የማይሰማ ፡ ባህል ፡ መስሎ ፡ ይታያቸዋል ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፲፪/ ይህ ፡ አነጋገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ የተለየች ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ውሳኔ ፡ ሳታውቀው ፡ ነው ፡ የሚሉትን ፡ መሠረተ ፡ ቢስ ፡ አሳብ ፡ እውነት ፡ ለማስመሰል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ንግግር ፡ አይ ደለም ፡ እኛስ ፡ ካቶሊካውያንን ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ይላሉ ፡ የምንላቸው ፡ ንስጥሮስ ፡ መለኮትንና ፡ ትስብእትን ፡ ለያይቶ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ያስተማረውን ፡ ተከትለው ፡ ክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፤ ባሕርየ ፡ ትስብእቱ ፡ ለባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ይገዛል ፡ ይላሉ ፡ ብለን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ እርሲዎ ፡ እንደሚሉት ፡ ዐራቱን ፡ ባሕርያት ፡ ለብቻ ፡ ነፍስን ፡ ለብቻ ፤ መለ ኮትን ፡ ለብቻ ፡ ቆጥረን ፡ አይደለም ። ደግሞ ፡ በያንቀጹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ባሕርይ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ተራቅቆ ፡ በሌለው ፡ በግዙፍ ፡ ትርጕሙ ፡ ይናገሩታል ፡ እያሉ ፡ መላልሰው ፡ ይናገራሉ ፡ እንጂ ፡ የተራቅቆ ፡ ትርጕም ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አልገለጹልንም ፡ ለባሕርይ ፡ እኛ ፡ ከምንሰጠው ፡ የተለየ ፡ የተራቀቀ ፡ ትርጕም ፡ ካለው ፡ አይናገሩትምን ፡ ለመቸ ፡ ይቆጥቡታል ።

ደ ራ ሲ ።

፲፫/ ደግሞ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ባንዱ ፡ ክርስቶስ ፡ መለኮትና ፡ ትስብእት ፡ መገኘታቸውን ፡ በተግባር ፡ ሲያምኑና ፡ ሲታመኑ ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ መኖራቸውን ፡ በአፍ ፡ ብቻ ፡ መካ ዳቸው ፤ ባሕርይ ፡ ለሚለው ፡ ቃል ፡ የካቶሊክ ፡ ሊቃውንት ፡ ከሚሰጡት ፡ ትርጕም ፡ በጣም ፡ ልዩ ፡ የኾነ ፡ ትርጕምን ፡ እንደሚሰጡት ፡ ያስረዳናል ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፲፫/ ከላይ ፡ እንደ ፡ ገለጽኩት ፡ ካቶሊካውያን ፡ ባሕርይ ፡ ለሚለው ፡ ቃል ፡ የፍልስፍናና ፡ የተ ራቀቀ ፡ ትርጕም ፡ ይሰጡታል ፡ እያሉ ፡ ሽፍንፍን ፡ ያለ ፡ ያልተገለጠ ፡ ነገር ፡ ከመናገር ፡ በቀር ፡ እን ዲህ ፡ ብለው ፡ ይተረጕሙታል ፡ ብለው ፡ የገለጹበት፡ አንቀጽ፡ የለም፡ እንግዲህ፡ ለዚህ፡ ላልተገለጠው፡ አነጋገር ፡ እውነት ፡ ነው፡ ወይም፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ እንደምን ፡ ይቻላል ፡ ምንም ፡ አይቻልም ።

ስለኾነም ፡ መለኮትና ፡ ትስብእት ፡ በማኅፀነ ፡ ማርያም ፡ ምንታዌን ፡ አጥፍተው ፡ ተዋሕዱ ፡ አንድ ፡ ኾኑ ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ በኹለትነት ፡ ይገኛሉ ፡ ብለን ፡ አናምንም ።

ደ ራ ሲ ።

፲፬/ ፕሮስፖንና ፡ አፖስታሲስ ፡ የሚሉትን ፡ የጽርእ ፡ ቃሎች ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አካል ፤ ብለው ፡ ይተረጕሟቸዋል ፡ ኡሲያና ፡ ፋሲስ ፡ የሚሉትንም ፡ ባሕርይ ፡ ወይም ፡ ህላዌ ፡ ብለው ፡ ይተረጕሟቸዋል ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፲፬/ የጽርእ ፡ ቋንቋ ፡ ስለማላውቅ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ መልስ ፡ ልሰጥበት ፡ አልችልም ።

ደ ራ ሲ ።

፲፭/ ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ቃሎች ፡ በምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ትምህርት ፡ ሲነገሩባቸው ፡ የተገባ ውን ፡ የፍልስፍናን ፡ ትርጕም ፡ ሲሰጣቸው ፡ በክርስቶስ ፡ አዋሐድ ፡ ትምህርት ፡ ሲገቡ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ከባዩ ፡ ወደ ፡ ባዩ ፡ የሚለዋወጥና ፡ በጣም ፡ ያልተወሰነ ፡ ትርጕም ፡ ስለሚሰጣቸው ፡ አንዳንድ ፡

ጊዜ ፡ ፈጽመው ፡ ሲወራረሱና ፡ አንድ ፡ አሳብ ፡ ብቻ ፡ ሲገልጡ ፡ ይገኛሉ ፡ ብለው ፡ እፍን ፤ ጭፍን ፡ ያለ ፡ አነጋገር ፡ ተናግረዋል ።

መ ላ ሽ ።

፲፭/ እፍን ፡ ጭፍን ፡ ያለ ፡ አነጋገር ፡ ያልኩት ፡ እኛ ፡ በማናውቃቸው ፡ ፕሮሶፖን ፡ እፖስታሲስ ፡ ሁሲያ ፡ ፋሲስ ፡ በሚባሉ ፡ በጽርእ ፡ ቃላት ፡ የተመሠረተ ፡ ከመኾኑም ፡ በላይ ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ከባዩ ፡ ወደ ፡ ባዩ ፡ ይለዋወጣሉ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ፈጽመው ፡ ይወራረሳሉ ፡ አንድ ፡ አሳብ ፡ ብቻ ፡ ይገልጣሉ ፡ ያሉትን ፡ አነጋገር ፡ ነው ።

እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከኾነ ፡ ለነዚህ ፡ አነጋገሮች ፡ ላያንዳንዳቸው ፡ የሚጠቅም ፡ ከባዩ ፡ ወደ ፡ ባዩ ፡ ያሉት ፡ ምን ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አንድ ፡ አሳብ ፡ ብቻ ፡ ይገልጣሉ ፡ ያሉትም ፡ ምን ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግልጥ ፡ አድርጎ ፡ ማስረጃ ፡ ሰጥቶ ፡ መጻፍ ፡ ነበረብዎ ፡ ስለዚህ ፡ ነገሩን ፡ በእርግጥ ፡ ሳይረዱ ፡ መልስ ፡ ልስጥበት ፡ ማለት ፡ ታላቅ ፡ ስሕተት ፡ ስለኾነ ፡ መልስ ፡ ልሰጥበት ፡ አልፈቀድኩም ።

ደ ራ ሲ ።

፲፮/ ስለዚህ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ እነዚህ ፡ ቃሎች ፡ በምሥጢረ ፡ ሥላሴና ፡ በክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ትምህርት ፡ ሲገቡ ፡ ትርጕማቸው ፡ አንድ ፡ አለመኾኑን ፡ አለመዘንጋት ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፲፮/ እንዲህ ፡ ማለት ፡ የሚገባ ፡ አስቀድሞ ፡ ቃላቶቹን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ጠቅሶ ፡ የትኞቹ ፡ መኾናቸውን ፡ ካስረዱ ፡ በኋላ ፡ እንደዚሁም ፡ በምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ሲገቡ ፡ የሚሰጡትን ፡ በክርስቶስ ፤ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ትምህርት ፡ ሲገቡ ፡ የሚሰጡትን ፡ አስተያየት ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ጠቅሶ ፡ በማስረዳት ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ አነጋገር ፡ አልነበረም ።

ደ ራ ሲ ።

፲፯/ ምክንያቱም ፡ በካቶሊክ ፡ መምህራን ፡ ዘንድ ፡ እንደሚደረገው ፡ በሚሥጢረ ፡ ሥላሴና ፡ በክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ትምህርት ፡ አንድ ፡ የኾነ ፡ ትርጕም ፡ ስለማይሰጣቸው ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፲፯/ ይህም ፡ እንደዚያው ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ ማለት ፡ የሚገባ ፡ በካቶሊክ ፡ መምህራን ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ የሚል ፡ ትርጕም ፡ እንደሚሰጣቸው ፡ ካስረዱ ፡ በኋላ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ የኾነ ፡ ትርጕም ፡ የማይሰጣቸው ፡ ቃላት ፡ የትኞች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ገልጦ ፡ በማስረዳት ፡ ነበረ ።

ደ ራ ሲ ።

፲፰/ በተለይም ፡ ከላይ ፡ እንዳየነው ፡ ለወደፊትም ፡ በሰፊው ፡ እንደምናየው ፡ በኹለቱ ፡ የትምህርት ፡ ቅርንጫፎች ፡ ይኸውም ፡ ልዩ ፡ የኾነው ፡ ትርጕም ፡ የሚሰጠው ፡ ባሕርይ ፡ ለሚለው ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፲፰/ ባሕርይ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ልዩ ፤ ልዩ ፡ ትርጕም ፡ የሚሰጠው ፡ መኾኑ ፡ አይካድም ። ባሕርይ ፡ ለሚለው ፡ ንባብ ፡ በያንቀጹ ፡ ተገቢውን ፡ ትርጕም ፡ ለመስጠት ፡ የሚቻለው ፡ የግእዝን፡ጠባይዕ ፡ በሚገባ ፡ አጥንቶ ፡ የመጻሕፍትን ፡ ከላይ ፡ መነሻቸውን ፡ ከታች ፡ መድረሻቸውን ፡ ተመልክቶ ፡ ቀጥተኛ ፡ ትርጓሜ ፡ ለመስጠት ፡ እስቲቻል ፡ ድረስ ፡ ጠንክሮ ፡ በመማር ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ደ ራ ሲ ።

፲፱/ ይህ ፡ ቃል ፡ በአካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ ምሥጢር ፡ የሚወራረሱት ፡ ሌሎችም ፡ ቃሎች ፡ እሉት ፡ አብዛኛውም ፡ ጊዜ ፡ የሚያመለክተው ፡ እንዱን ፡ ኳኝ ፡ ለማቆም ፡ የሚገባውን ፡ መሠረታዊ ፡ ክፍል ፡ ሳይኾን ፡ የራሱ ፡ ህላዌ ፡ ያገኘውንና ፡ ራሱን ፡ ችሎ ፡ ለብቻው ፡ የኾነውን ፡ ኳኙን ፡ ራሱን ፡ ነው ። ይህም ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ እውነተኛው ፡ አነጋገር ፡ አካል ፡ ወይም ፡ ቅንም ፡ ሲባል ፡ የሚገባውን ፡ ያመለክታል ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብለዋ ።

## መ ላ ሽ ።

፲፱/ በአካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ ምሥጢር ፡ የሚወራረሱት ፡ ሌሎችም ፡ ቃላት ፡ እሉ ፡ ያልዋቸውን ፡ ቃላት ፡ እነማን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ገልጸውልን ፡ ቢኾን ፡ ለእኛም ፡ ተገቢውን ፡ መልስ፡ ለመስጠት ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ በተጠመን ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እርስዎ ፡ ሳይገልጹልን ፡ በመቅረትዎ ፡ እኛንም ፡ ተገቢውን ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ዕድል ፡ አልገጠመንም ። እንደ ፡ እውነተኛው ፡ አነጋገር ፡ አካል ፡ ወይም ፡ ቅንም ፡ ሊባል ፡ የሚገባውን ፡ ያመለክታል ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ገለጹት ፡ የኾነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይህ ፡ አነጋገር ፡ ባሕርይን ፡ አካል ፡ እንደምንለው ፡ አስመስሎ ፡ የሚያሳይ ፡ አነጋገር ፡ ነው ። በዚህ ፡ መልሱ ፡ ባጭሩ ፡ አካልን ፡ አካል ፤ ባሕርይን ፡ ባሕርይ ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ ባሕርይን ፡ አካል ፡ እንለውም ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መልስ ፡ የለውም ።

## ደ ራ ሲ ።

፳/ በምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ትምህርት ፡ ባሕርይን ፡ ለማመልከት ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ የሚነገረው ፡ ቃል ፡ መለኮት ፡ የሚለው ፡ የተራቀቀ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ፩ አምላክ ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ ይመለከታል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳/ ባሕርይ ፡ ለፈጣሪም ፡ ለፍጡራንም ፡ እንዳላቸው ፡ ይነገራል ፡ ምክንያቱም ፡ አካል ፡ ያለ ፡ ባሕርይ ፡ ባሕርይም ፡ ያለአካል ፡ ብቻ ፡ ብቻቸውን ፡ ሊገኙ ፡ የማይቻል ፡ ስለ ኾነ ፡ ነው ።

መለኮት ፡ አምላክ ፡ ማለት ፡ ግን ፡ ለፈጣሪ ፤ እንጂ ፡ ለፍጡራን ፡ አይነገርም ፡ ስለዚህ ፡ መለኮታዊ ፡ ባሕርይ ፤ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ እንናገራለን ፡ እንጂ ፡ በምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ትምህርት ፡ መለኮትን ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ አንናገረውም ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፩/ የአካልነት ፡ አሳብ ፡ ደግሞ ፡ በምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ትምህርት ፡ ኹልጊዜ ፡ አካል ፡ በሚለው ፡ ቃል ፡ ይገለጻል ። ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ገጽ ፡ ወይም ፡ ግጻዌ ፡ የሚሉት ፡ ወይም ፡ ቅንም ፡ መልክእ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ስም ፤ ወይም ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ነፍስ ፡ የሚሉት ፡ ቃሎች ፡ ይወራረሱታል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፩/ የአካልነት ፡ አሳብ ፡ አካል ፡ በሚለው ፡ ቃል ፡ ይገለጻል ፡ ያሉት ፡ ቃል ፡ እውነት ፡ ነው ። ይወራረሱታል ፡ የሚሏቸው ፡ ቃላት ፡ ግን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ያሏቸው ፡ ናቸው ።

ሀ/ ገጽ ፡ ሲል ፡ ልብስ ፡ የማይሸፍነውን ፡ ከአንገት ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ መገለጫን ፡ መታወቂያን ፡ ግንባርን ፡ ያመለክታል ።

ስለዚህ ፡ የሰው ፡ መታወቂያው ፡ መገለጫው ፡ ካንገቱ ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ፊቱና ፡ ግንባሩ ፡ ስለ ኾነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ፊቱን ፡ ቢሸፈን ፡ ወይም ፡ ካንገቱ ፡ ላይ ፡ ተቆርጦ ፡ ካንገቱ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ አካል ፡ ቢጠፋና ፡ ካንገቱ ፡ በታች ፡ ያለው ፡ አካል ፡ በምሉ ፡ ቢታይ ፡ ግን ፡ እንደኾነ ፡ ሊታወቅ ፡ አይቻልም ፤ የገጽ ፡ ትርጓሜ ፡ መገለጫ ፡ መታወቂያ ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይህ ፡ በቂ ፡ መረጃ ፡ ነው ።

ለ/ ግጻዌ ፡ ሲልም ፡ ግንባር ፡ ያለው ፡ አካል ፡ ማለትን ፡ ወይም ፡ መታየት ፡ መገለጥ ፡ መታወቅ ፡ ማለትን ፡ ያመለክታል ። ገጽ ፡ ካለው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ኹሉም ፡ ገጸወ ፡ ታየ ፡ ተገለጠ ፡ ከሚለው ፡ ግሥ ፡ የተገኙ ፡ ናቸው ።

ሐ/ አቃኒም ፡ ሲልም ፡ ፍጹም ፡ ገጽ ፡ ፍጹም ፡ መልክእ ፡ ያለው ፡ አካል ፡ ማለትን ፡ ያሰማል ። ከአካል ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

መ/መልክእ ፡ ባለ ፡ ጊዜም ፡ ቀይ ፡ ጥቁር ፡ ማለት ፡ ሲከተለው ፡ ኅብርን ፤ መልካም ፡ ክፉ ፡ ማለት ፡ ሲከተለው ፡ ደግሞ ፡ ቅርጽን፡ ደም ፡ ግባትን ፡ ያመለክታል። ይኸውም ፡ ቀይ ፡ መልክ ፤ ጥቁር ፡ መልክ ፡ ወይም ፡ መልክ ፡ መልካም ፤ መልክ ፡ ክፉ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ።

እነዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተዘረዘሩት ፡ ኹሉ ፡ የአካልን ፡ ስልት ፡ ስልቱን ፡ የሚያሳዩ ፡ አነጋገሮች ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደሉም ፡ ያው ፡ ተለይተው ፡ አካል ፡ በመባል ፡ ይጠቀለላሉ ።

ሠ/ ስም ፡ የሚለው ፡ ግን ፡ ከራስ ፡ ጠጉር ፡ እስከ ፡ እግር ፡ ጥፍር ፡ ያለው ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ አካል ፡ ከሌላው ፡ ሰው ፡ አካል ፡ ተለይቶ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ታውቆ ፡ የሚጠራበት ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ አካል ፡ አይደለም ።

ይኸውም ፡ አዳም ፡ ሴት ፡ ኖኅ ፡ አብርሃም ፡ እንደማለት ፡ ነው ፡ ይህ ፡ የተጸውዖ ፡ ስም ፡ ይባላል ፤ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ የአካል ፤ የግብር ፡ ስም ፡ አለ ፡ የአካል ፤ ስም ፡ ሰው ፡ ላም ፡ በግ ፡ ፈረስ ፤ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሰውም ፤ ላምም ፤ በግም ፤ ፈረስም ፤ ቢኾኑ ፡ ይህነን ፡ ስም ፡ የሚያገኙት ፡ አካል ፡ ሲገኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኖረው ፡ ኖረው ፡ የሚያገኙት ፡ አይደለምና ፡ ስለዚህ ፡ ይህን ፡ የመሳሰለው ፡ የአካል ፡ ስም ፡ ይባላል ።

የግብር ፡ ስም ፡ ደግሞ ፡ ሠዓሊ ፡ ጸሐፊ ፤ ነጋዴ ፤ ገበሬ ፤ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ኹሉ ፡ ነው ፡ ቢሥል ፤ ሠዓሊ ፤ ቢጽፍ ፤ ጸሐፊ ፤ ቢነግድ ፤ ነጋዴ ፤ ቢያርስ ፡ ገበሬ ፡ ይባላል ። ሥራውን ፡ ቢተው ፡ ግን ፡ ነበረ ፡ ከመባል ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ ስም ፡ ሊጠራበት ፡ አይችልም ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ የመሳሰለው ፡ ስም ፡ የግብር ፡ ስም ፡ ይባላልና ፡ እንደዚኸው ፡ ለሥላሴም ፡ የአካል ፡ ስም ፤ የአካል ፡ ግብር ፡ ስም ፤ አካላት ፡ በህልውና ፡ የሚገናዘቡበት ፡ የባሕርይ ፡ ካዊን ፡ ስም ፡ አላቸው ። አሁን ፡ ለያዝነው ፡ ነገር ፡ የሚረዱንን ፡ እኒህን ፡ ብቻ ፡ ጠቀስን ፡ እንጂ ፡ ሌሎችም ፡ የሚጠሩባቸው ፡ ስሞች ፡ አሉ ። የአካል ፡ ስም ፡ ማለት ፡ አብ ፡ ወልድ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ። ሰው ፤ ሰው ፡ መባልን ፡ የሚያገኘው ፡ አካሉ ፡ ሲገኝ ፡ እንደኾነ ፡ ይህም ፡ አብ ፤ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚባለው ፡ ስም ፤ ምንም ፡ ሥላሴ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ተገኙ ፡ የሚባልበት ፡ ጊዜ ፡ ባይኖር ፡ ጥንት ፡ መሠረት ፡ ሳይኖረው ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ሲኖር ፡ የኖረ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ተጸውዖ ፡ ስም ፡ ኖሮ ፡ ኖሮ ፡ የወጣ ፡ ስም ፡ አይደለም ።

ወይም ፡ ሰው ፡ ኖሮ ፡ ኖሮ ፡ ልጅ ፡ ሲወልድ ፡ አባት ፡ እንዲባል ፡ አብም ፡ ከወልድ ፡ ቀድሞ ፡ ኖሮ ፡ ኖሮ ፡ ወልድን ፡ ወልዶ ፡ አብ ፡ የተባለ ፡ አይደለም ። ወልድም ፡ ልጅ ፡ ካባቱ ፡ በዘመን ፡ ወደ ኋላ ፡ ኾኖ ፡ ኖሮ ፡ ኖሮ ፡ በእናቱ ፡ ማኅፀን ፡ ተጥሎ ፡ ፅንስ ፡ ሽል ፡ ሲባል ፡ ኖሮ ፡ ከ፱ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ አካል ፡ ዘየአካል ፡ ተፈጽሞለት ፡ ሲወለድ ፡ ልጅ ፡ እንዲባል ፡ ከአብ ፡ በዘመን ፡ ወደኋላ ፡ ኾኖ ፡ ኖሮ ፡ ኖሮ ፡ ተወልዶ ፡ ወልድ ፡ የተባለ ፡ አይደለም ።

፪ኛ ፡ ወላዲ ፤ ተወላዲ ፤ ሠራጺ ፡ ማለት ፡ የአካል ፡ ግብር ፡ ስም ፡ ነው ፡ የአካል ፡ ግብር ፡ ስም ፡ ማለትም ፡ አብ ፡ ወልድን ፡ ቢወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ቢያሠርጽ ፡ ወላዲ ፡ አሥራጺ ፡ ተባለ ፡ ወልድም ፡ ከአብ፡ቢወለድ፡ተወላዲ ፡ ተባለ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ከአብ ፡ ቢሠርጽ ፡ ሠራጺ ፡ ተባለ ፡ ማለት ፡ ነው ። አብ ፡ ተለውጦ ፤ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንዳይኾን ፡ እንዳይባል ፤ ወልድም ፡ ተለውጦ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንዳይሆን ፡ እንዳይባል ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ተለውጦ ። አብ ፡ ወልድ ፡ እንዳይኾን ፡ እንዳይባል ፡ ወላዲነት ፤ አሥራጺነትም ፡ ከአብ ፡ ወጥቶ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተወላዲነትም ፤ ከወልድ ፤ ወጥቶ ፡ በአብ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ ሠራጺነትም ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፤ ወጥቶ ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ የሚሠራ ፡ ግብር ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ስም ፡ ፫ቱ ፡ አካላት ፡ የሚለያዩበት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚገናዘቡበት ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ የሚኾኑበት ፡ ስም ፡ አይደለም ።

አካላት ፡ በህልውና ፡ የሚገናዘቡበት ፡ የባሕርይ ፡ ከዊን ፡ ስም ፡ አላቸው ፡ ያልነውም ፡ ልብ ፤ ቃል ፤ እስትንፋስ ፡ መባል ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ተከፍሎ ፡ ተፈልጦ ፡ በሌለባት ፡ ባንዲት ፡ ባሕርይ ፡ ያለ ፡ የከዊን ፡ ስም ፡ ነው ። እርሱም ፡ ልዩነት ፡ ሳለበት ፡ አንድነት ፤ አንድነት ፡ ሳለበት ፡ ልዩነት ፡ አለበት ። ልዩነቱ ፡ በከዊን ፤ አንድነቱ ፡ በህልውና ፡ መገናዘብ ፡ ነው ። ይህነንም ፡ በነፍስ ፡ ከዊን ፡ ልንረዳው ፡ እንችላለን ፡ ነፍስ ፡ በአካሏ ፡ አንድ ፡ ስትኾን ፡ ፫ ፡ ከዊን ፡ አላት ። ይኸውም ፤ ልብ ፤ ቃል ፤ እስትንፋስ ፡ መኾን ፡ ነው ። የልብነቷ ፡ ከዊን ፡ ቃል ፡ እስትንፋስን ፡ አስገኝቶ ፡ ዕውቀት ፡ ይኾናል ፤ የቃልነቷ ፤ ከዊን ፡ ከልብነቷ ፡ ከዊን ፡ ተገኝቶ ፡ ከሥጋ ፡ ምላስ ፡ ጋር ፡ ተዋሕዶ ፡ ንባብን ፡ ይሰጣል ፤ የእስትንፋስነቷ ፡ ከዊን ፡ ከልብ ፡ መንጭቶ ፡ አየርን ፡ በማውጣት ፡ በማግባት ፡ ሕይወት ፡ ይኾናል ።

የሥላሴም ፡ ከዊን ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ። አንዲት ፡ የምትኾን ፡ ባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ፫ ፡ ከዊን ፡ ስላላት ፡ የልብነቷ ፡ ከዊን ፡ አብ ፡ ነው ። አብ ፡ በልብነቱ ፡ ቃል ፡ የተባለ ፡ ወልድን ፤ እስትንፋስ ፡ የተባለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አስገኝቶ ፡ ለራሱና ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዕውቀት ፡ ይኾናል ። የቃልነቷ ፡ ከዊንም ፡ ወልድ ፡ ነው ፡ ወልድ ፡ በቃልነቱ ፡ ከዊን ፡ ልብ ፡ በተባለ ፡ ከአብ ፡ ተወልዶ ፡ ለራሱና ፡ ለአብ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ንባብ ፡ ይኾናል ።

የእስትንፋስነቷ ፡ ከዊንም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በእስትንፋስነቱ ፡ ከዊን ፡ ልብ ፡ ከተባለ ፡ ከአብ ፡ ሠርጾ ፡ ለራሱና ፡ ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ሕይወት ፡ መኾን ፡ ነው ። የነፍስ ፡ የልብነቷ ፡ ከዊን ፡ በልብነቱ ፡ የቃልነቷም ፡ ከዊን ፡ በቃልነቱ ፡ የእስትንፋስነቷ ፡ ከዊን ፡ በእስትንፋስነቱ ፡ ጸንቶ ፡ ከመኖር ፡ በቀር ፡ የልብነቷ ፡ ከዊን ፡ ወደ ፡ እስትንፋስነት ፡ ወደ ፡ ቃልነት ፤ የቃልነቷም ፡ ከዊን ፡ ወደ ፡ ልብነት ፡ ወደ ፡ እስትንፋስነት ፤ የእስትንፋስነቷም ፡ ከዊን ፡ ወደ ፡ ልብነት ፡ ወደ ፡ ቃልነት ፡ እንደማይለወጥ ፡ እንደማይቀላቀል ፡ ያንዲት ፡ ባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ከዊንም ፡ እንደዚሁ ፡ የልብነቷ ፡ ከዊን ፡ በአብ ፤ የቃልነቷ ፡ ከዊን ፡ በወልድ ፡ የእስትንፋስነቷ ፡ ከዊን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፡ አይለወጥም ፡ አይቀላቀልም ።

የከዊን ፡ ሦስትነት ፡ አንድነት ፡ ሳለበት ፡ ልዩነት ፡ አለበት ፡ ያልነው ፡ ይሀ ፡ ነው ።
የከዊን ፡ ሦስትነት ፡ አንድነት ፡ ሳለበት ፡ ልዩነት ፡ አለበት ፡ ሳይኖርባቸው ፡ ከልብ ፡
፪ኛም ፡ ቃል ፤ እስትንፋስ ፤ ከልብ ፡ ቢገኙም ፡ ተከፍሎ ፡ ተፈልጦ ፡ ሳይኖርባቸው ፡ ከልብ ፡ በቃልነትና ፡ በእስትንፋስ
ሳይለዩ ፡ ሀልዋን ፡ ኹነው ፡ እንዲኖሩ ፡ ወልድና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በቃልነትና ፡ በእስትንፋስ
ነት ፡ ከዊን ፤ በልብነት ፡ ከዊን ፡ ካለ ፡ ከአብ ፡ ቢገኙ ፡ ተከፍሎ ፡ ተፈልጦ ፡ ሳይኖርባቸው ፡ በአብ ፡
ሀልዋን ፡ ኹነው ፡ ይኖራሉ ፡ እንጂ ፡ ተከፍሎ ፡ ተፈልጦ ፡ የለባቸውም ። ሥላሴ ፡ በሀልውና ፡ አንድ ፡
ናቸው ፡ የሚያሰኘው ፡ ምሥጢር ፡ ይሀ ፡ ነው ። አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የተባሉ ፡ ፫ቱ ፡ አካ
ላት ፡ በከዊን ፡ ሀልውና ፡ እንዲገናዘቡ ፡ አንዲት ፡ ባሕርየ ፡ መለኮትም ፡ በከዊን ፡ ከሦስት ፡ እንደ ፡ ተከ
ፈለች ፡ በሚበቃ ፡ ምሳሌ ፡ ተረድተናል ። እነሆ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነን ፡ ምሥጢር ፡
ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ በተመሠረተ ፡ የተራቀቀና ፡ የፍልስፍና ፡ አነጋገር ፡ አጣርታ ፡ የምታውቅ ፡
መኾኗን ፡ አሁን ፡ ከዚሀ ፡ ላይ ፡ በጻፍኩልዎ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ተረድተው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ለነዚሀ ፡
ቃሎች ፡ የሚሰጡት ፡ ትርጉም ፡ ተራቅቆ ፡ የሌለበት ፡ ግዙፍና ፡ የተራ ፡ ሕዝብ ፡ ትርጉም ፡ ነው ፡ የሚ
ሉትን ፡ አነጋገርዎን ፡ እንዲያርሙት ፡ አሳስብዎታለሁ ።

እንግዲሀ ፡ ወደ ፡ ሥር ፡ ነገራችን ፡ እንመለስ ፡ ካቶሊካውያንንና ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ለያይቶ
ያለው ፡ ምሥጢር ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አካል ፡ ያለባሕርይ ፡ ባሕርይም ፡ ያለአካል ፡ ሊገኝ ፡ አይቻል
ምና ፡ አካልም ፡ ባሕርይም ፡ ተዋሐደ ፡ ብለው ፡ ሲያስተምሩ ፡ የሮም ፡ ካቶሊካውያን ፡ አካል ፡ እንጂ ፡
ባሕርይ ፡ አልተዋሐደም ፤ ባሕርይ ፡ ተዋሐደ ፡ ያልን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የሥላሴ ፡ ባሕርይ ፡ አንዲት ፡
ናትና ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ሰው ፡ ኾኑ ፤ ያሰኝብናል ፡ ስለሚሉ ፡ ነው ።

ወንጌላዊ ፡ ግን ፡ አካል ፡ እንጂ ፡ ባሕርይ ፡ አልተዋሐደም ፡ እንዳይሉበት ፡ አካል ፡ በሚጠራበት ፡
ስም ፡ ወልድ ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ሳይል ፡ ጠንቅቆ ፡ አካል ፡ በባሕርይ ፡ ከዊን ፡ በሚጠራበት ፡ ስም ፡ ቃል
ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ብሏል ። ባሕርይ ፡ ከተዋሐደ ፡ ፫ቱም ፡ ሰው ፡ ኾኑ ፡ ያሰኛል ፡ እንዳይባልም ፡ አብ ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከሚጠሩበት ፡ ከልብ ፡ ከእስትንፋስ ፡ ለይቶ ፡ ወልድ ፡ ብቻ ፡ በሚጠራበት ፡ ስም ፡ ቃል ፡
ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ብሏል ፤ ቃልም ፡ ከአካለ ፡ አብና ፡ ከአካለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በከዊን ፡ የምትለይ ፡ በሀ
ልውና ፡ የምትገናዘብ ፡ መኾኗን ፡ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ አስረድተናል ።

ነፍስ ፡ በቃልነቷ ፡ ከዊን ፡ ከሥጋ ፡ ምላስ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዳ ፡ ንባብን ፡ ስትሰጥ ፡ በልብነቷ ፡ ከዊ
ንና ፡ በእስትንፋስነቷ ፡ ከዊን ፡ ከምላስ ፡ ጋራ ፡ እንደማትዋሐድ ፡ ግልጥ ፡ ነገር ፡ ነው ።

ይሀም ፡ በልብነቷ ፡ በእስትንፋስነቷ ፡ ከዊን ፡ ሳይኾን ፡ በቃልነቷ ፡ ከዊን ፡ ብቻ ፡ ከምላስ ፡ ጋራ ፡
መዋሐዷ ፡ ነፍስን ፡ ከሦስት ፡ የሚከፍላት ፡ አንድነቷን ፡ የሚያጠፋ ፡ አይደለም ።

እንደዚኹውም ፡ አንዲት ፡ ባሕርየ ፡ መለኮት ፡ በልብነቷ ፡ በእስትንፋስነቷ ፡ ከዊን ፡ ሳይኾን ፡
በቃልነቷ ፡ ከዊን ፡ ሥጋን ፡ ተዋሐደች ፡ ቢባል ፡ በልብነቷ ፡ በእስትንፋስነቷ ፡ ሥጋን ፡ ተዋሐደች ፡
አያሰኝም ፡ ማለት ፡ በቃልነት ፡ ከዊን ፡ ያለ ፡ ወልድ ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ በልብነት ፡ በእስትንፋስነት ፡
ከዊን ፡ ያሉ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ ኾኑ ፡ አያሰኝም ። አንዲት ፡ ባሕርየ ፡ ሥላሴንም ፡ ከሦ
ስት ፡ የሚከፋፍላት ፡ አይደለም

እኛ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አካልም ፡ ባሕርይም ፡ ተዋሐደ ፡ የምንልበትን ፡ ምሥጢር ፡ እነኾ ፡ በተ
ቻለ ፡ መጠን ፡ አብራርቼና ፡ ግልጥልጥ ፡ አድርጌ ፡ አስረድቻለሁ ። እርስዎ ፡ ግን ፡ ካቶሊካውያን ፡
በፍልስፍና ፡ በተራቀቀ ፡ የሚናገሩት ፡ እያሉ ፡ ባነጋገር ፡ ከማጎባጎብና ፡ ከማጋነን ፡ በቀር ፡ ገላልጠው ፡
አብራርተው ፡ የጻፉት ፡ ሳይኖር ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የሚናገሩት ፡ ያልተማረ ፡ ሰው ፡ የሚናገረው
ግዙፍ ፡ አነጋገር ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ በመንቀፍዎ ፡ አዝናለሁ ።

ረ/ ነፍስ ፡ ማለት ፡ የሥጋ ፡ ሕይወት ፡ ተብላ ፡ ለፍጡራን ፡ ከመነገሯ ፡ በቀር ፡ ለሥላሴ ፡ አካል ፡
ተብላ ፡ የምትነገርበት ፡ አንቀጽ ፡ ያለ ፡ አይመስለኝም ፡ እኔ ፡ አላውቅም ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፪/ በዚሀ ፡ ልናመለክተውና ፡ ልናስረዳው ፡ የምንፈልገው ፡ ባሕርይና ፡ አካል ፡ የሚሉት ፡
ቃሎች ፡ በምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ትምህርት ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የአካልነትን ፡ አሳብ ፡ ለመግለጥ ፡ ብዙ
ዎች ፡ ቃሎች ፡ ቢገኙ ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ መቻወንም ፡ አለመወራረሳቸውን ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፪/ ይሀ ፡ አነጋገር ፡ እውነተኛ ፡ አነጋገር ፡ ነው ፡ ባሕርይ ፤ ባሕርይ ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፡ አካል ፡
አይባልም ፤ አካልም ፡ አካል ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፡ ባሕርይ ፡ አይባልምና ፡ በስም ፡ አይወራረሱም ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፫/ በግምትም ፡ አካል ፡ የሚለው ፡ አንድ ፡ የተለየ ፡ ለብቻው ፡ የኾነና ፡ በራሱ ፡ የቆመ ፡ ኋኝን ፡ ያመለክታል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፫/ እውነት ፡ ነው ፡ ከራስ ፡ ጠጕር ፡ እስከ ፡ እግር ፡ ጥፍር ፡ ባጥንት ፡ በጅማት ፡ በሥጋ ፡ በቁርበት ፡ ተያይዞና ፡ ተሸፍኖ ፡ የሚታየው ፡ ቅርጽ ፣ አካል ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ባሕርይ ፡ አይባልም ፣ ይኸውም ፡ የባሕርይ ፣ የግብር ፣ የስም ፡ ባለቤት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አካል ፡ ያለባሕርይ ፡ ብቻውን ፡ አይቆምም ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፬/ ባሕርይ ፡ የሚለው ፡ ግን ፡ ያንድ ፡ ወገን ፡ መለያ ፡ የኾነ ፡ ኹኔታ ፣ ወይም ፡ አንድ ፡ ለብቻው ፡ የኾነና ፡ ያንድ ፡ ወገን ፡ የኾኑ ፡ ብዙዎች ፡ ኋኞች ፡ የሚያብሩበትን ፡ ነገር ፡ ያመልክታል፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፬/ ይኸም ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ባሕርይ ፡ ባሕርይ ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፡ አካል ፡ አይባልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ባሕርይና ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ሲኾኑ ፡ ልዩዎች ፡ ልዩዎች ፡ ሲኾኑ ፡ አንድ ፡ ስለኾኑ ፡ አካል ፡ ያለ ባሕርይ ፡ ብቻውን ፡ እንደማይቆም ፡ ባሕርይም ፡ ያለ ፡ አካል ፡ ሊገለጽና ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ። አንድነታቸው ፡ ይህ ፡ ነው ።

ያንድ ፡ ወገን ፡ መለያ ፡ ያሉትም ፡ አነጋገር ፡ ወኃ ፡ በርጥበቱ ፡ እሳት ፡ በውዕየቱ ፡ ይታወቃል ፡ እንጂ ፡ ወኃ ፡ ርጥበት ፡ ከሌለው ፡ ወኃነቱ ፡ እሳትም ፡ ውዕየት ፡ ከሌለው ፡ እሳትነቱ ፡ አይታወቅም ፡ እንደማለት ፡ ያለ ፡ አነጋገር ፡ ነው ፡ ልዩነታቸው ፡ በዚህ ፡ ይታወቃል ፡ ማለት ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፭/ በክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ትምህርት ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ኹለቱ ፡ ቃሎች ፡ የተወሰነ ፡ ትርጕም ፡ ስለሌላቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይወራረሱና ፡ ይለዋወጣሉ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ከላይ ፡ የአካል ፡ ተወራራሾች ፡ ብለን ፡ የጠቀስናቸው ፡ ቃሎች ፡ ኹሉ ፡ በምሥጢረ ፡ ሥላሴም ፡ ኾነ ፡ ወይም ፡ በተዋሕዶተ ፡ ባሕርያት ፡ ትምህርት ፡ አብዛኛው ፡ ጊዜ ፡ የአካልነትን ፡ አሳብ ፡ ይገልጣሉ ፡ ማደናገርን ፡ የሚያመጣው ፡ ባሕርይ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፭/ ይህ ፡ አነጋገር ፡ አካል ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ በአካልነቱ ፡ ስናጸና ፡ ባሕርይ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ባሕርይ ፡ እያልን ፡ እንደምንተረጕመው ፡ አስመስሎ ፡ የሚያሳይ ፡ አነጋገር ፡ ነው ፡ ይሆን ፡ ካሉ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ባሕርይን ፡ አካል ፡ ብለው ፡ ተርጕመውታል ፡ ብሎ ፡ ጠቅሶ ፡ ማስረዳት ፡ ነበረብዎ ፡ እንጂ ፡ ፩ ፡ መረጃ ፡ ሳይሰጡ ፡ ባሕርይን ፡ አካል ፡ ብለው ፡ ይተረጕሙታል ፡ ብሎ ፡ መናገር ፡ አይገባም ። እኛስ ፡ ባሕርይን ፡ ባሕርይ ፡ ብለን ፡ ከመተርጐም፡ በቀር ፡ አካል ፡ ብለን ፡ የምንተረጕምበት ፡ አንቀጽ ፡ የለም ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፮/ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ሲናገሩ ፡ የባሕርይነትን ፡ ወይም ፡ በጽርእ ፡ ቋንቋ ፡ ፉሲስ ፡ የሚሉትን ፡ አሳብ ፡ ለመግለጥ ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉትን ፡ ቃሎች ፡ ያገባሉ ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የሚነገረው ፡ ቃል ፡ ባሕርይ ፡ የሚለው ፡ ነው ። ይህ ፡ ቃል ፡ በጥንቱ ፡ ከባሕር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ክቡር ፡ ዕንቍን ፡ ያመለክት ፡ ነበረ ። ስለክርስቶስ ፡ ሲነገር ፡ ግን ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ተባለው ፡ የባሕርይነትን ፡ አሳብ ፡ ለማመልከት ፡ ይገባል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፮/ ባሕርይ ፡ የሚለው ፡ አነጋገር ፡ በጥንቱ ፡ ከባሕር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘውን ፡ ዕንቍ ፡ ያመለክት ፡ ነበረ ፡ ያሉት ፡ አነጋገር ፡ የተሳሳተ ፡ አስተያየት ፡ ነው ፡ ይህ ፡ አሁን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ልንገልጸው ፡ የምንፈልገው ፡ ባሕርይ ፡ ለፍጥረቱ ፡ ኹሉ ፡ ጥንት ፡ መሠረት ፡ የኾኑ ፡ ውኀ ፣ መሬት ፡ ነፋስ ፡ እሳት ፡ አካላቸው ፡ ሲገኝ ፡ ተገኝቶ ፡ በአካላቸው ፡ ህልው ፡ ኾኖ ፡ የሚኖር ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ እኒህ ፡ ምክንያተ ፡ ፍጥረት ፡ የኾኑ ፡ ወኀ ፡ መሬት ፤ ነፋስ ፤ እሳት ፡ አራቱ ፡ ባሕርያት ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ። ይህ ፡ ከባሕር ፡ የሚገኘው ፡ ዕንቍ ፡ ግን ፡ ግብር ፡ እምግብር ፡ ከሚገኙ ፡ ፍጥረታት ፡ አንዱ ፡ ነው ። ከኒህ ፡ ባሕርያት ፡ ተብለው ፡ ከሚጠሩት ፡ ከወኀ ፤ ከመሬት ፡ ዋዕየ ፡ እሳት ፡ካለው ፡ ብርሃን ፡ ፀሐይ ፡ ስለተፈጠረ ፤ ስሙን ፡ ከነርሱ ፡ ወርሶ ፡ ባሕርይ ፡ ተብሏል ፡ እንጂ ፡ ለርሱ ፡ ተረክቦ ፡ ምክንያት ፡ የኾኑ ፡ ወኀ ፤ መሬት ፤ ከርሱ ፡ ወስደው ፡ ባሕርያት ፡ የተባሉ ፡ አይደለም ።

ወይም ፡ ከየብስ ፡ የሚገኙ ፡ ብዙ ፡ አዕናቍ ፡ አሉና ፡ ከነዚያ ፡ ለይቶ ፡ ከባሕር ፡ የተገኘ ፡ መኾኑን ፡ ለመግለጽ ፡ ባሕርይ ፡ ተብሏል ። ባሕራይ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ። የኸውም ፡ ተባዕታይ ፡ አንስታይ ፡ እንዳለው ፡ ያለ ፡ ወገን ፡ ቅጽልነትን ፡ የሚያሳይ ፡ አነጋገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ ስለክርስቶስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ልንገልጸው ፡ የምንወደውን ፡ ባሕርይ ፡ የሚለውን ፡ አነጋገር ፡ የሚገልጽ ፡ አይደለም ።

ደ ራ ሲ ።

፳፪/ ነገር ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ባሕርይ ፡ ሲሉ ፡ የሚያመለክቱት ፡ አንድ ፡ ቅውም ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ለብቻው ፡ ተወስኖ ፡ በራሱ ፡ የቆመ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከአካልነቱ ፡ ተለይቶ ፡ በተራቅቆ ፡ የሚገኘው ፡ ወይም ፡ ሳንድ ፡ ኋኝ ፡ መለያ ፡ የሚኾነው ፡ እውነተኛው ፡ የፍልስፍና ፡ አሳብ ፤ አለመኾኑን ፡ ማስተዋል ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፳፪/ በእኛ ፡ አስተያየት ፡ ባሕርይ ፡ ስንል ፡ በአካል ፡ ህልው ፡ ኾኖ ፡ ከአካል ፡ ሳይለይ ፡ የአካልን ፡ ጠባይዕ ፡ ወይም ፡ ስሜት ፡ ይገልጻል ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ ለብቻው ፡ ተወስኖ ፡ ከአካል ፡ ተለይቶ ፡ በራሱ ፡ የቆመ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ አንልም ። ለብቻው ፡ ተወስኖ ፡ በራሱ ፡ የቆመ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ማለትንስ ፡ አሁን ፡ እርስዎ ፡ ከአካልነቱ ፡ ተለይቶ ፡ በተራቅቆ ፡ የሚገኝ ፡ ላንድ ፡ ኋኝ ፡ መለያ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ሲናገሩ ፡ ሰማን ።

ተራቅቆ ፡ ፍልስፍና ፡ እያሉ ፡ በያንቀጹ ፡ ከመናገር ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ ተራቅቆና ፡ ፍልስፍና ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የገለጹበት ፡ አንቀጽ ፡ የለም ። ስለዚህ ፡ ተራቅቆ ፡ ፍልስፍና ፡ ለሚሏቸው ፡ ንግግሮች ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ አላገኘንላቸውም ።

ደ ራ ሲ ።

፳፫/ ስለዚህ፡በክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ አለ ፡ ሲሉ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድነቱ ፡ ያልተነካ ፡ ኋኝ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ አድራጊ ፡ ማለትን ፡ ያሰማሉ ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፳፫/ ሰው ፡ ካራቱ ፡ ባሕርያተ ፡ ሥጋና ፡ ፫ ፡ ግብራተ ፡ ባሕርይ ፡ ለባዊትነት ፡ ነባቢትነት ፡ ሕያዊትነት ፡ ካላት ፡ ከነፍስ ፡ የተፈጠረ ፡ መኾኑ ፡ ሳይዘነጋ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዲባል ፤ ክርስቶስም ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ የኾነ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ መኾኑ ፡ ሳይዘነጋ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለታችን ፡ የማይካድ ፡ ነው ። ይሆንም ፡ የምንልበት ፡ ምክንያት ፡ መጻሕፍት ፡ በያንቀጹ ፡ የመለኮትንና ፡ የትስብእትን ፡ ተዋሕዶ ፡ በነፍስና ፡ በሥጋ ፡ ተዋሕዶ ፡ ከመሰሉ ፡ በኋላ ፡ ፩ዱ ፡ የሚል ፡ ቅጽል፡ እንጂ ፡ ክልኤቱ ፡ የሚል ፡ ቅጽል ፡ የሚቀጽልለት ፡ ባለማግኘታችን ፡ ነው ።

ደ ራ ሲ ።

፳፬/ የባሕርይነትን ፡ አሳብ ፡ ለመግለጽ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ሌላ ፡ ቃል ፡ ሀለወ ፡ ኖረ ፡ ኮነ ፡ ኾነ ፡ ከሚለው ፡ አንቀጽ ፡ የወጣ ፡ ህላዌ ፡ ወይም ፡ ህሉና ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ነው ። ህላዌ ፤ ህሉና ፤ ሀልዎ ፤ ሀልዎት ፡ ሲል ፡ የመኖርንና ፡ የመኾንን ፡ አሳብ ፡ ያሰማል ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፳፬/ እውነት ፡ ነው ፡ ህላዌ ፡ ማለት ፡ መኾን ፤ መገኘት ፤ መኖር ፤ ማለት ፡ ነው ፡ ለመኾን ፡ ለመገኘት ፡ ለመኖር ፡ መሠረቱ ፡ አራቱ ፡ ባሕርያት ፡ ናቸውና ፡ ህላዌ ፡ ማለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ ያመለክታል ፤ ስለዚህ ፡ የባሕርይነትን ፡ አሳብ ፡ ለመግለጽ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ቃል ፡ ህላዌ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ያሉት ፡ እውነት ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፴/ ነገር ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ከሚናገሩባቸው ፡ ቃሎች ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ትርጕሙ ፡ የሚያደናግርና ፡ ያልተወሰነ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፴/ ይህ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ፩ኛ ፡ የሰዋስውን ፡ ጠባይዕ ፡ ፪ኛ ፡ የቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነን ፡ ምሥጢር ፡ መርምሮ ፡ ጠንቅቆ ፡ ከተረዱ ፡ በኋላ ፡ የመጻሕፍትን ፡ ከላይ ፡ መነሻቸውን ፡ ከታች ፡ መድረሻቸውን ፡ ተመልክቶ ፡ የሚገባውን ፡ ትርጕም ፡ ካልሰጡት ፡ በመላ ፡ በድፍረት ፡ ልተርጕምህ ፡ ቢሉት ፡ ማስ ቸገሩና ፡ ማደናገሩ ፡ አይቀርም ። ለምሳሌ ፡ አብርሃም ፡ አብርሃም ፡ እየተባሉ ፡ የሚጠሩ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ይገኛሉ ። ከነዚህም ፡ ፩ኛ ፡ አበ ፡ ብዙኃን ፡ ዐርከ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተባለውን ፡ አብርሃምን ። ፪ኛ ፡ በተአምራት ፡ ተራራ ፡ ያፈለሰውን አብርሃም ፡ ሶርያዊን ። ፫ኛ ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥትን ፡ ጻፈ ፡ የሚባለ ውን ፡ ግብጻዊ ፡ አብርሃም ፡ ቀሲስን ፡ እንጥቀስ ። መጽሐፍ ፡ ሦስቱንም ፡ ባስፈለገው ፡ ጊዜ ፡ ይጠቅ ሳቸዋል ፡ ስማቸው ፡ አይለወጥም ፡ ያው ፡ አብርሃም ፡ ነው ፡ የሚጠቀሱበት ፡ ምሥጢር ፡ ግን ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ቢኾን ፡ ያንዱ ፡ ካንዱ ፡ የማይገናኝ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ አንባቢ ፡ ወይም ፡ ተርጓሚ ፡ መጽሐፉ ፡ ከላይ ፡ የተነሣበትን፡ ከታች ፡ የሚደርስ በትን ፡ አውቆ ፡ ተረድቶ ፡ በሚገባው ፡ ላይ ፡ ሳያውል ፡ ንባቡ ፡ አብርሃም ፡ ካለ ፡ ብሎ ፡ የአብርሃም ፡ አበ ፡ ብዙኃንን ፡ ለአብርሃም ፡ ሶርያዊ ፡ የአብርሃም ፡ ሶርያዊን ፡ ለአብርሃም ፡ ቀሲስ ፡ ሰጥቼ ፡ ልተር ጕምህ ፡ ልተርክህ ፡ ቢሉት ፡ ታሪኩም ፡ አሳቡም ፡ ፈራሽ ፡ ኾኖ ፡ ይቀራል ። በዚህ፡ ጊዜ ፡ ተርጓ ሚው ፡ አላዋቂ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ መጽሐፉ ፡ ተሳሳተ ፡ አጠፋ ፡ አይባልም ። የህላዌንም ፡ ነገር ፡ ለይቶ ፡ አለማወቅና ፡ የሚገባውን ፡ ትርጕም ፡ አለመስጠት ፡ እንደዚህ ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፴፩/ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የመኖርን ፡ የመኾንንና ፡ የባሕርይን ፡ አሳብ ፡ ለመግለጽ ፡ ያገቡታል ፡ ሌላ ጊዜም ፡ አካል ፡ ወይም ፡ ቅኑም ፡ የሚባሉትን ፡ ቃላት ፡ የሚገልጡትን ፡ አሳብ ፡ ያሰማል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፴፩/ የመኾንን ፤ የመኖርን ፤ የባሕርይን ፡ አሳብ ፡ ለመግለጥ ፡ ያገቡታል ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ እንዳሉት ፡ ኾኖ ፡ የሚገባበትን ፡ ከመጻሕፍት ፡ ንባብ ፡ ጠቅሰው ፡ እንዲህ ፡ ይላሉ ፡ ብለው ፤ የአካል ንም ፡ አሳብ ፡ ያሰማሉ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ እንደዚሁ ፡ ጠቅሰው ፡ አቅርበው ፡ ቢኾን ፡ ትክክለኛውን ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ በተቻለ ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እርስዎ ፡ የሚናገሩት ፡ ነገር ፡ የዳበሳ ፡ ኾኖ ፡ የተብራራ ፡ ነገር ፡ ባይኖርበት ፡ በመሰለን ፡ መንገድ ፡ የተቻለንን ፡ ያኽል ፡ ነገሩን ፡ ለማብራ ራት አንሞክራለን ፡ የመኾንን ፡ የመኖርን ፡ አሳብ ፡ ለመግለጥ ፡ ያገቡታል ፡ ለሚሉት በቍ ፡ ፳፱ የጻፍነው ፡ በቂ ፡ ነው ፡ ያንን ፡ ይመልከቱ ። አካል ፡ ወይም ፡ ቅኑም ፡ የሚባሉትን ፡ ቃላት ፡ የሚገል ጡትን ፡ አሳብ ፡ ያሰማሉ ፡ ስለሚሉትም ፡ ምናልባት ፡ ከላይ ፡ ለመኾን ፡ ለመኖር ፡ ለመገኘት ፡ መሠ ረቶች ፡ አራቱ ፡ ባሕርያት ፡ ናቸው ፡ ብለን ፡ እንደ ፡ ገለጽነው ፡ ኗሪ ፡ ኗኝ ፡ የሚባለው ፡ አካል ፡ ወይም ፡ ቅኑም ፡ ከነዚህ ፡ ካራቱ ፡ ባሕርያት ፡ የሚገኝ ፡ ስለሆነ ፡ በመገኛው ፡ አካልን ፡ ህላዌ ፡ የሚል ፡ ንባብ ፡ ይገኝ ፡ ይኾናል ። እርስዎ ፡ ህላዌን ፡ አካል ፡ የሚል ፡ ንባብ ፡ ጠቅሰው ፡ አቅርበውልኝ ፡ ቢኾን ፡ በማ ያጠራጥር ፡ መንገድ ፡ ቀጥተኛውን ፡ መልስ ፡ በሰጠሁዎ ፡ ነበረ ፡ ስለዚህ ፡ ጉድለቱ ፡ ከእኔ ፡ አለመኾ ኑን ፡ እንዲገነዘቡልኝ ።

## ደ ራ ሲ ።

፴፪/ ጠባይዕ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ አካልን ፡ ወይም ፡ ቅኑምን ፡ ለማሰማት ፤ ገብቶ ፡ መቸውንም ፡ ስለ ማይገኝ ፡ ትርጕሙ ፡ የሚያደናግር ፡ አይደለም ። ርሱ ፡ የሚያሰማው ፡ ፍጡራን ፡ ወይም ፡ የተፈጠሩ ፡ ነገሮች ፡ ተፈጥሮ ፡ ጠባይዕ ፡ የተፈጥሮ ፡ ስጦታ ፡ ማለትን ፡ ነው ፤ በሃይማኖት ፡ ትምህርትም ፡ የተፈ ጠረውን ፡ የክርስቶስን ፡ ባሕርይ ፡ ያሰማል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፴፪/ ባሕርይና ፡ ጠባይዕ ፡ የሚሉት ፡ ቃላት ፡ እጅግም ፡ ልዩነት ፡ የላቸውም ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ እርስዎ ፡ ግን ፡ ጠባይዕ ፡ ለፍጡራን ፡ እንጂ ፡ ለፈጣሪ ፡ አይነገርም ፡ የሚል ፡ አስተያየት ፡ አቅርበዋል ፡ አይደለም ። ጠባይዓቲሁስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ንጹሐት ፡ እማንቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ነውር ፡ ሲል ፡ ይገኛ

ልና ፤ ባሕርይ ፡ ለፈጣሪም ፡ ለፍጡራንም ፡ እንደሚነገር ፡ ጠባይዕም ፡ ለፈጣሪም ፣ ለፍጡራንም ፡ ይነ ገራል ፡ እንጂ ፡ እርስዎ ፡ እንደሚሉት ፡ አይደለም ።

ደ ራ ሲ ።

፴፫/ ሌላም ፡ የባሕርይነትን ፡ አሳብ ፡ ለመግለጽ ፡ የሚነገር ፡ ክዋኔ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ አለ ። ርሱም ፡ ኮነ ፡ ኾነ ፡ ከሚለው ፡ አንቀጽ ፡ የወጣ ፡ ነው ። ይህም ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ኹኔታን ፡ ወይም ፡ ባሕርይን ፡ ለማስማት ፡ ይገባል ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፴፫/ የክዋኔን ፡ መልስ ፡ የህላዌን ፡ መልስ ፡ በሰጠንበት ፡ በቍ ፡ ፳፱ ፡ መኾን ፡ ኋኝ ፡ በሚለው ፡ አነጋገር ፡ የተሰጠ ፡ ስለኾነ ፡ ከዚህ ፡ መድገም ፡ አላስፈለገም ።

ደ ራ ሲ ።

፴፬/ በመጨረሻ ፡ የባሕርይን ፡ አሳብ ፡ ለመግለጽ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ፈጠረ ፡ ከሚለው ፡ አን ቀጽ ፡ የወጣውን ፡ ፍጥረት ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ያመጣሉ ። ይህ ፡ ቃል ፡ የመፈጠርንና ፡ የተፈጠሩትን ፡ ነገሮች ፡ ኹሉ ፡ ከማሰማት ፡ በላይ ፡ በጽርእ ፡ ቋንቋ ፡ ፉሲስ ፡ የሚሉትንም ፡ የባሕርይን ፡ አሳብ ፡ ለመ ግለጽ ፡ ይገባል ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፴፬/ እኛ ፡ ፍጥረት ፡ ለሚለው ፡ ቃል ፡ የምንሰጠውን ፡ እውነተኛውን ፡ ትርጕም ፡ እርስዎ ፡- ራስዎ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ የመፈጠርንና ፡ የተፈጠሩትን ፡ ነገሮች ፡ ኹሉ ፡ ያሰማል ፡ ብለው ፡ በዚሁ ፡ ቍጥር ፡ በሚገኘው ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ገልጸውታል ። እኛም ፡ የምንለው ፡ ይኸው ፡ ነው ። ምናልባት ፡ መጽሐፍ ፡ ጠባይዐ ፡ ፍጥረቱ ፡ ለአዳም ፡ ይላል ።

ባለቅኔዎችም ፡ እምአዳምኑ ፡ ይእቲ ፡ ባሕቱ ፡ ወእምአርዌ ፡ ምድር ፡ ፍጥረታ ፡ እያሉ ፡ ያገቡታል ። ይህ ፡ አነጋገር ፡ ፍጥረትን ፡ ባሕርይ ፡ ለማለት ፡ መስሎዎ ፡ እንደኾነ ፡ አይደለም ።

ጠባይዐ ፡ ፍጥረቱ ፡ ለአዳም ። የአዳም ፡ የተፈጥሮ ፡ ጠባይዕ ፡ ሲል ፡ በተፈጥሮው ፡ ያገኘውን ፡ ጠባይዕ ፡ ያሰማል ።

እምአዳምኑ ፡ ይእቲ ፡ ወእምአርዌ ፡ ምድር ፡ ፍጥረታ ። ተፈጥሮዋ ፡ ከአዳም ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ ከምድር ፡ አውሬ ፤ ሲልም ፡ የተፈጥሮዋን ፡ ትውልድ ፤ ወገን ፤ ነገድ ፡ ያመለክታል ፡ እንጂ ፡ ፍጥረት ፡ ማለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ እንደኾነ ፡ አያስረዳም ።

በጽርእ ፡ ቋንቋ ፡ ፉሲስ ፡ የሚሉትም ፡ የባሕርይን ፡ አሳብ ፡ ለመግለጽ ፡ ይገባል ፡ ስለሚሉት ፡ ግን ፡ ይህን ፡ አነጋገር ፡ ከመጽሐፍ ፡ አገኘሁ ፡ ብለው ፡ እንጂ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ የተናገሩት ፡ አይመስ ለኝም ። ከመጽሐፍ ፡ አገኘሁት ፡ የሚሉ ፡ ከኾነ ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በጽርእም ፡ በግእዝም ፡ የተጻፈ ፡ መኾን ፡ አለበት ። ይህን ፡ ለመናገር ፡ ሲሹ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በዚህን ፡ ያኸል ፡ ምዕራፍ ፤ በዚህን ፡ ያኸል ፡ ቍጥር ፡ በጽርዕ ፡ እንዲህ ፡ የሚለው ፡ ንባብ ፡ በግእዝ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ ብለው ፡ ጽርእ ፤ ፉሲስ ፡ የሚለውን ፤ ግእዝ ፡ ፍጥረት ፡ ብሎ ፡ ያነበበበትን ፡ ወይም ፡ የተረጐመበትን ፡ ማስረዳት ፡ ነበረብዎ ፡ እንዲያው ፡ በቃል ፡ እንዲህ ፡ ይሉታል ፡ ብሎ ፡ አውርቶ ፡ መሔድ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ የለውም ።

እነሆ ፡ አሁን ፡ በያዝነው ፡ በዚሁ ፤ ክፍል ፡ በ፯ኛው ፡ ቍ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ሲያስተምሩ ፡ የሚናገሩባቸውን ፡ ቃሎች ፡ ከዚህ ፡ አምጥተን ፡ ትርጕማቸውን ፡ ብንመረምር ፡ የምንለው ፡ በፍጹም ፡ እውነት ፡ መኾኑን ፡ እንረዳለን ፣ ስላሉን ፡ በሚገባ ፡ ተከታ ትለነው ፡ ነበረ ፤ እርስዎ ፡ ስለመሰለዎ ፡ እንዲህ ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡ በእኛ ፡ አስተያየት ፡ እውነት ፡ ብለን፡የተረዳነው ፡ እንድም ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ እንደሌለ ፡ በዚህ ፡ በሰጠኹዎ ፡ መልስ ፡ እንዲረዱልኝ ፡ አሳስብዎታለሁ ።

## ክ ፍ ል ፬ ።

ኢትዮጵያውያን ፣ የኬልቄዶን ፣ ጉባኤ ፣ የወሰነውን ፣ ይቀበላሉ ፣ ስለሚሉት ፡፡

### ዶ ራ ሲ ።

፴፭/ኢትዮጵያውያን ፣ ከኬልቄዶን ፣ ጉባኤ ፣ የማይቀበሉት ፣ አነጋገሩን ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ የወሰነውንስ ፣ ሃይማኖት ፣ አይክዱትም ።

### መ ላ ሽ ።

፴፮/ ይህ ፣ ሃይማኖት ፣ የተወሰነው ፣ ባነጋገር ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ በቴክኒካዊ ፣ ተግባር ፣ በእጅ ፣ ሥራ ፣ አይደለም ፣ ሃይማኖትም ፣ በቃል ፣ ተነግሮ ፣ በጆሮ ፣ ተሰምቶ ፣ በልብ ፣ የሚታመን ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ በዐይን ፣ የሚታይ ፣ በእጅ ፣ የሚጨበጥ ፣ አይደለም ፣ አነጋገሩን ፣ የማይቀበሉት ፣ ከኾነ ፣ ሃይማኖቱን ፣ አይክዱትም ፣ ማለት ፣ ያልተካከለ ፣ ንግግር ፣ ነው ፣ ንግግርምን ፣ ያስተካክሉ ።

### ዶ ራ ሲ ።

፴፯/ አሁን ፣ በመረመርናቸው ፣ ቃሎች ፣ የሚገለጠው ፣ የባሕርይ ፣ አሳብ ፣ የጠቀስናቸውን ፣ ጽሑፎች ፣ በጥንቃቄ ፣ ቢያስተውሉባቸው ፣ እንደ ፣ ካቶሊክ ፣ ትምህርት ፣ ያንድ ፣ ወገን ፣ መለያ ፣ የማለትን ፣ የተራቀቀና ፣ ጠቅላይ ፣ የኾነ ፣ ትርጉም ፣ አያሰማም ፣ ነገር ፣ ግን ፣ ባንድ ፣ ጓኝ ፣ ውስጥ ፣ የሚገኘውን ፣ ነገር ፣ ወይም ፣ አንድ ፣ የራሱ ፣ ህላዌ ፣ ያለው ፣ ልዩና ፣ የተወሰነ ፣ ጓኝን ፣ ያሰማል ፣ ብለዋል ።

### መ ላ ሽ ።

፴፰/ አነጋገሩ ፣ ባይተካከል ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ አስተያየቱ ፣ ከእውነት ፣ የተቃረበ ፣ ሳይኾን ፣ አይቀርም ። አንድ ፣ የራሱ ፣ ህላዌ ፣ ያለው ፣ ልዩና ፣ የተወሰነ ፣ ጓኝ ፣ ባሉ ፣ ጊዜ ፣ አካልን ፣ ባንድ ፣ ጓኝ ፣ ውስጥ ፣ የሚገኝ ፣ ነገር ፣ ባሉ ፣ ጊዜ ፣ ባሕርይን ፣ ያሰማል ፣ ቢሉ ፣ አነጋገርዎ ፣ በተቃና ፣ ነበር ። ምክንያቱም ፣ አካል ፣ አንድ ፣ የተወሰነ ፣ ነገር ፣ ሲኾን ፣ ባሕርይ ፣ በዚህ ፣ በተወሰነው ፣ አካል ፣ ህልው ፣ ኾኖ ፣ የአካልን ፣ ጠባይዕ ፣ የሚገልጽ ፣ እንጂ ፣ ከአካል ፣ በአፍኣ ፣ የሚገኝ ፣ ሌላ ፣ ህላዌ ፣ ስላልኾነ፣ነው።

### ዶ ራ ሲ ።

፴፱/ ይህም ፣ ማለት ፣ ቅዱስ ፣ ቄርሎስ ፣ ስለክርስቶስ ፣ ሲናገር ፣ በጽርእ ፣ ፉሲስ ፣ በሚለው ፣ ቃል ፣ ይገልጠው ፣ የነበረውን ፣ አሳብ ፣ ልክ ፣ ማለት ፣ አካል ፣ ወይም ፣ ቅኑም ፣ ማለትን ፣ ያሰማል ፣ ማለት ፣ ነው ፣ ብለዋል ።

### መ ላ ሽ ።

፵/ በዚህ ፣ አነጋገርዎ ፣ ቄርሎስ ፣ ስለ ፣ ክርስቶስ ፣ ሲናገር ፣ ፉሲስ ፣ የሚለው ፣ ቃል፣ አካልን ፣ እንጂ ፣ ባሕርይን ፣ አያሰማም ፣ በማለትዎ ፣ ቄርሎስ ፣ ስለክርስቶስ ፣ ሲናገር ፣ ፩ ፣ ማለትን፣ ስለ አካል ፣ እንጂ ፣ ስለባሕርይ ፣ አልተናገረም ፣ ለማለት ፣ የከጀሉ ፣ ይመስላል ። ቅዱስ ፣ ቄርሎስ ፣ ክርስቶስን ፣ በአካልም ፣ በባሕርይም ፣ አንድ ፣ ለማለቱ ፣ ፩ ፣ አካል ፣ ወ፩ ፣ ህላዌ ፣ የሚል ፣ ግልጥ ፣ ያለ ፣ ንባብ ፣ እናገኛለን ፣ ይህ ፣ የሚሉት ፣ እውነት ፣ ከኾነ ፣ እንደ ፣ ካቶሊካውያን፣አነጋገር፣፩ዱን፣ለአካል ፣ ክልኤቱን ፣ ለባሕርይ ፣ ቅጽል ፣ አድርጎ ፣ የተናገረበት ፣ ፩ ፣ አካል ፣ በ፪ ፣ ባሕርያት ፣ የሚል ፣ ንባብ ፣ ማምጣት ፣ ያስፈልጋል ።

### ዶ ራ ሲ ።

፵፩/ ህላዌና ፣ ባሕርይ ፣ የሚሉቱ ፣ ቃላት ፣ የክርስቶስን ፣ አንድነት ፣ ለማጽደቅ ፣ ወይም ፣ ማናቸውንም ፣ ብዙነት ፣ መገኘቱን ፣ ለመካድ ፣ ብዙ ፣ ጊዜ ፣ አንድ ፣ ላይ ፣ ተቆጥረው ፣ ይገኛሉ ፣ ብለዋል ።

### መ ላ ሽ ።

፵፪/ ይህ ፣ እውነት ፣ ነው ፣ መጻሕፍት ፣ በየአንቀጹ ፣ ለክርስቶስ ፣ አሐዱ ፣ የሚለውን ፣ ቍጥር ፣ ብቻ ፣ በመቀጸል ፣ ፩ ፣ አካል ፣ ፩ ፣ ህላዌ ፣ እያሉ ፣ ጽፈው ፣ ይገኛሉ ።

### ዶ ራ ሲ ።

፵፫/ ስለዚህ ፣ ኢትዮጵያውያን ፣ በክርስቶስ ፣ ኹለት ፣ ባሕርያት ፣ የሉም ፣ ሲሉ ፣ በኤፌሶን ፣ ጉባኤ ፣ የተወገዘውን ፣ ኹለት ፣ አካላት ፣ የማለትን ፣ የንስጥሮስን ፣ ኑፋቄ ፣ ለመካድ ፣ ነው ፣ የኬልቄዶንን ፣ ጉባኤና ፣ ካቶሊኮቹን ፣ ልዮን ፣ ጳጳስንም ፣ የንስጥሮስን ፣ ባህል ፣ ይዘዋል ፣ የሚሏቸው ፣ በዚህ፣ ምክንያት ፣ ነው ፣ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፴፱/ ይህ ፡ አነጋገር ፡ እንደማደናገርና ፡ እንደማጭበርበር ፡ የሚቆጠር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ንግግር ፡ አይደለም ። የንስጥሮስ ፡ ኑፋቄ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ ጭምር ፡ ነው ። የኤፌሶን ፡ ጉባኤም ፡ የወሰነ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ማለትን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ ጨምሮ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ለኤፌሶን ፡ ጉባኤ ፡ መደበኛ ፡ የኾነው ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ በየአንቀጹ ፡ ፩ ፡ አካል ፡ ወ፩ ፡ ህላዌ ፡ በማለቱ ፡ ይታወቃል ።

በዚህም ፡ ባሕል ፡ በኤፌሶን ፡ ጉባኤ ፡ ጊዜ ፡ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተባባሪ ፡ እንደ ፡ ነበረች ፡ የማይካድ ፡ ነው ። ኋላ ፡ ግን ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የተሰበሰቡ ፡ ሰዎች ፡ ከንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ አደሱት ፡ ከኤፌሶን ፡ ጉባኤ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ አፈረሱት ፡ ብለን ፡ ለይተን ፡ እንናገራለን ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የሚሉትን ፡ አነጋገር ፡ ለውጠን ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ይላሉ ፡ ብለን ፡ አንናገርም ።

## ደ ራ ሲ ።

፵/ በተለይም ፡ ልዮንን ፡ በክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ አለ ፡ ማለቱ ፡ የተሳሳተውን ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ መያዙ ፡ እንዳይታወቅብኝ ፡ ብሎ ፡ በማስመሰል ፡ የተናገረው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ባልኾነ ፡ ይከሱታል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፵/ ይህንን ፡ የምንልበትን ፡ ምክንያት ፡ በም ፡ ፫ ፡ በቍ ፡ ፲፪ ፡ ፲፬ ፡ ስለገለጽን ፡ ያንኑ ፡ መመልከት ፡ በቂ ፡ ነው ፤ ኹለተኛ ፡ ከዚህ ፡ መዘርዘር ፡ አላስፈለገም ።

## ደ ራ ሲ ።

፵፩/ ኢትዮጵያውያኖቹ ፡ በምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ እንደሚያስማው ፡ የባሕርይነትን ፡ ወይም ፡ (የፋሲስ) ፡ ማለት ፡ የተራቀቀውን ፡ ያንድ ፡ ወገን ፡ የመለያ ፡ ህላዌ ፡ የሚያመለክት ፡ አሳብ ፡ ለመግለጥ ፡ የፈለጉ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የክርስቶስን ፡ አምላክነት ፡ ለማመልከት ፡ ህላዌ ፡ መለኮት ፡ ባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ይላሉ ፤ ሰውነቱንም ፡ ለማመልከት ፡ ባሕርየ ፡ ሥጋ ፤ ህላዌ ፡ ሥጋ ፡ ይላሉ ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፵፩/ ምናልባት ፡ ከተዋሕዶ ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ አኳኋን ፡ ለመግለጽ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ምክንያት ፡ ቢገጥመን ፡ ባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፤ ህላዌ ፡ መለኮት ፡ ህላዌ ፡ ትስብእት ፡ እንላለን ። ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ የኾነውን ፡ ለመግለጽ ፡ ብንፈልግ ፡ ግን ፡ ክርስቶስ ፡ በሰውነቱ ፡ ተሰቀለ ፡ ሞተ ፡ በመለኮቱ ፡ ሕያው ፡ ነው ፡ ብለን ፡ በተዋሕዶ ፡ ስሙ ፡ ጠርተን ፡ እንናገራለን ፡ እንጂ ፡ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ ተፈልጦ ፡ ያለበት ፡ አስመስለን ፡ ባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ይህን ፡ ሠራ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ይህን ፡ አደረገ ፡ የምንል ፡ አይደለንም ።

ይህስ ፡ አነጋገር ፡ ተፈልጦ ፡ ባላቸው ፡ በነፍስና ፡ በሥጋ ፡ ላይ ፡ ያውም ፡ በተወሰነ ፡ ሰዓት ፡ ነፍሱን ፡ ከሥጋው ፡ ከለየበት ፡ ጊዜ ፡ አንሥቶ ፡ ነፍሱና ፡ ሥጋው ፡ ተዋሕደው ፡ እስከ ፡ ተነሡበት ፡ ድረስ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የሚነገር ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ሥጋው ፡ በዮሴፍ ፤ በኒቆዲሞስ ፡ እጅ ፡ ተገንዞ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ወረደ ፡ ነፍሱ ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ወረደች ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ።

መለኮት ፡ ግን ፡ የተዋሐደ ፡ ነፍስንም ፡ ሥጋንም ፡ ስለኾነ ፡ መለኮት ፡ በአካለ ፡ ሥጋ ፡ ወደመቃብር ፡ ወርዶ ፡ ሙስና ፡ መቃብርን ፡ አጠፋ ። መለኮት ፡ በአካለ ፡ ነፍስ ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ወርዶ ፡ ቍራኝነትን ፡ አጠፋ ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ መለኮትንና ፡ ትስብእትን ፡ ለያይተን ፡ የምንናገርበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ።

## ደ ራ ሲ ።

፵፪/ በኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ በክርስቶስ ፡ ትስብእት ፡ ወይም ፡ ህላዌ ፡ ትስብእት ፡ አይገኝም ፡ በርሱ ፡ የሚገኘው ፡ መለኮት ፡ ወይም ፡ ባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚገኝ ፡ የሚል ፡ የትም ፡ አይገኝም ፤ የአውጣኪንም ፡ ባህል ፡ የሚገልጹ ፡ እኒህ ፡ ቃሎች ፡ ናቸው ፤ ይህን ፡ ባህል ፡ የሚደግፍ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አንድም ፡ አይገኝም ። ይህም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ትምህርት ፡ በመሠረቱ ፡ አይክዱትም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፻፪/ የዚህ ፡ እነጋገር ፡ ጠቅላላ ፡ ትርጓሜው ፡ ክርስቶስን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወይም ፡ ዕሩቅ፡ ቃል ፡ አይሉትም ፡ ማለት ፡ ነው ። እውነት ፡ ነው ፡ ክርስቶስ ፡ ማለት ፡ ከኹለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ከኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ቢኾን ፡ የወጣለት ፡ ስም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መለኮት ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ ትስብእት ፡ ብቻ ፡ የሚጠራበት ፡ ስም ፡ አይደለም ። ስለዚህ ፡ ክርስቶስ ፡ ባልን ፡ ጊዜ ፡ ቃል ፡ ምንታዌን ፡ አጥፍቶ ፡ ትስብእትን ፡ እንደተዋሐደ ፡ በሚያስረዳ ፡ አነጋገር ፡ እንናገራለን ፡ እንጂ ፡ክርስቶስን ፡ ዕሩቅ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ አንለውም ።

በመሠረቱ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ትምህርት ፡ አይክዱትም ፡ ስለሚሉት ፡ ግን ፡ እኛ ፡ ቱሳሔ ፡ ውላጤ ፡ በተፀቅቦ ፡ እንደጠፉ ፡ ምንታዌም ፡ በተዋሕዶ ፡ ጠፉ ፡ ስንል ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ምንታዌ ፡ አልጠፉም ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ አልተዋሐዱም ፡ በኹለትነት ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ፡ ስትል ፡ ምን ፡ አገናኝቶን ፡ የኹለት ፡ ባሕርያትን ፡ ትምርት ፡ አይክዱትም ፡ ይላሉ ፡ ይህ ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፻፫/ ኢትዮጵያውያን ፡ ከካቶሊኮቹ ፡ ጋራ ፡ ሲከራከሩ ፡ እናንተ ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ ተከታዮች ፡ ናችሁ ፡ እያሉ ፡ ሲከሷቸው ፡ በክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ ስለመገኘቱ ፡ ይናገራሉ ፡እንጂ፡ ስለኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አንሥተው ፡ ተናግረው ፡ አያውቁም ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፻፬/ ይህ ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ። ከካቶሊካውያን ፡ ጋራ ፡ በምንከራከርበት ፡ ጊዜ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በማለታችሁ ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ በከፊል ፡ የተከተላችሁ ፡ መኾናችሁን ፡ በመግለጥ ፡ ነው ። ይህም ፡ በኋኛ ፡ ምዕራፍ ፡ በቍ ፡ ፭፮ ፡ በጠቀስነው ፡ በአለቃ ፡ ውድነህ ፡ እሸቴ ፡ መወድስ ፡ ቅኔ ፡ ይታወቃል ። አንድ ፡ አካል ፡ በማለትማ ፡ ኹላችንስ ፡ አንድ ፡ አይደለምን ፡ ምን ፡ ያጣላናል ።

## ደ ራ ሲ ።

፻፭/ ይህም ፡ እነርሱ ፡ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ በክርስቶስ ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ አይገኝም ፡ ብለው ፡ የሚክዱት ፡ ንስጥሮስ ፡ ያስተማረውን ፡ የኹለት ፡ አካል ፡ ባህልን ፡ ለመካድ ፡ መኾኑን ፡ በግልጥ ፡ ያስረዳል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፻፮/ ይህም ፡ ውሸት ፡ ነው ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ በምንቃወምበት ፡ ጊዜ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ እንመልሳለን ፤ የኬልቄዶንንም ፡ ጉባኤ ፡ በምንቃወምበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ በማለት ፡ የምንተባበር ፡ መኾናችንን ፡ ዐውቀን ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በማለታቸው ፡ ብቻ ፤ ለይተን ፡ እንከራከራለን ፡ እንጂ ፡ የንስጥሮስንና ፡ የልዮንን ፡ ባህል ፡ ለይተን ፡ ያላወቅን ፡ ኾነን ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ ለልዮን ፡ ሰጥተን ፡ የምንናገር ፡ አይደለንም ።

## ደ ራ ሲ ።

፻፯/ ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ትምርት ፡ ያላቸው ፡ አስተያየት ፡ ኹሉ ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ የሚቃወም ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፻፰/ ይህም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ነገሩ ፡ ንስጥሮስን ፡ የሚያገባው ፡ በመኾኑ ፡ በግድ ፡ ነገሩ ፡ አግብቶት ፡ ከመገኘቱ ፡ በስተቀር ፡ በጉባኤ ፡ ኤፌሶን ፡ የንስጥሮስ ፡ መለየት ፡ በኹላችንም ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ስለኾነ ፡ የርሱን ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ትተን ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ በምንቃወምበት ፤ ጊዜ ፡ አስተያየታችንን ፡ የምንጥለው ፡ በኬልቄዶኑ ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ ላይ ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፻፱/ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ከካቶሊኮቹ ፡ ጋራ ሲከራከሩ ፡ ለንስጥሮሳውያን ፡ የሚቃወሙ ፡ እየመሰላቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የአካላዊስ ፡ ተዋሕዶ ትምርታቸው ፡ ከካቶሊክ ፡ ትምህርት ፡ ለብቻው ፡ ከኾነ ፡ አነጋገር ፡ ወይም ፡ አገላለጥ ፡ በስተቀር የሚለይበት ፡ የለም ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፵፮/ ለንስጥሮሳውያን ፡ የሚቃወሙ ፡ እየመሰላቸው ፡ ነው ፡ ለሚሉት ፡ መልሱን ፡ በቍ ፡ ፲፮ ፡ ስለጻፍኩ ፡ ከዚህ ፡ መድገም ፡ አላስፈለገም ። ስለአካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ የሚለዩበት ፡ የለም ፡ ስለሚሉት ፡ በመሠረቱ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ በማለት ፡ እንለያይም ፡ እውነት ፡ ነው ።

በከዊኑ ፡ ምሥጢር ፡ አገላለጽ ፡ ግን ፡ መሊያየታችን ፡ የታወቀ ፡ ሲሆን ፡ ከካቶሊክ ፡ ትምህርት የሚለዩበት ፡ የለም ፡ ማለት ፡ ማግባባት ፡ ይመስላል ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ንግግር ፡ አይደለም ።

## ደ ራ ሲ ።

፵፯/ ካቶሊካውያንና ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ኾነው ፡ ተስማምተው ፡ ያነጋገሩን ፡ ጉዳይ ፡ ቢጨርሱትማ ፡ ኖሮ ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ ያላንዳች ፡ ችግር ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ ይቀበሉት ፡ ነበር ፡ ኹለቱም ፡ ወገኖች ፡ ፍጹም ፡ ስምምነትን ፡ ያገኙ ፡ ነበረ ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፵፯/ የርስዎ ፡ ሐሳብዎ ፡ ኹሉ ፡ በኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ፍቅር ፡ የተነደፈ ፡ ስለኾነ ፡ በኹለቱ ፡ ባህሎች ፡ መካከል ፡ ቆሞ ፡ ግራ ፡ ቀኙንም ፡ ባህሎች ፡ በሚዛናዊ ፡ አስተያየት ፡ በማመዛዘን ፡ ፈንታ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ በእውነተኝነት ፤ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ በስሕተት ፡ መደብ ፡ አቁመው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የኬልቄዶኑን ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ ያለችግር ፡ ይቀበሉት ፡ ነበረ ፡ እንደሚሉት ፡ ኹሉ ፤ በኢትዮጵያውያንም ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ስሜት ፡ በርስዎ ፡ ዘንድ ፡ ካለው ፡ ስሜት ፡ የማያንስ ፡ በመኾኑ ፡ ተስማምተው ፡ ያነጋገሩን ፡ ጉዳይ ፡ ቢጨርሱት ፡ ኖሮ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የሚል ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ባህላቸውን ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ ጥንተ ፡ ባህላቸው ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ወደ ፡ ማለት፡ ይመለሱ ፡ ነበረ ፡ የሚል ፡ ሕሊና ፡ በዚህም ፡ በኩል ፡ እንዳለ ፡ ይወቁ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ኹለታችንም ፡ ወገኖች ፡ የእኔ ፡ ይበልጣል ፡ የሌላው ፡ ያንሳል ፤ የኔ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ የሌላው ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ መንፈስ ፡ አርቀን ፡ በወንድማማችነት ፡ መንፈስ ፡ ተቀራርበን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ባንድነት ፡ ብንለምነው ፡ ኀበ ፡ ሀለው ፡ ፪ ፡ ወ፫ ፡ ጉቡአን ፡ በስምየ ፡ ሀየ ፡ እሄሉ ፡ ማእከሌሆሙ ፡ ያለ ፡ እርሱ ፡ በመካከላችን ፡ ተገኝቶ ፡ ስምምነትን ፡ የሚሰጠን ፡ መኾኑ ፡ የታመነ ፡ የማይከድ ፡ ነገር ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፵፰/ ሉዶልፍ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከኢየሱሳውያን ፡ መላክተኞች ፡ ጋር ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ሲከራከሩ ፡ አለመስማማታቸው ፡ አሳባቸውን ፡ ለሚገልጡባቸው ፡ ቃሎች ፡ ለየብቻው ፡ የኾነ ፡ ትርጒም ፡ ከመስጠታቸው ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ የጻፈው ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፵፰/ ኢትዮጵያውያንና ፡ ካቶሊካውያን ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኾነ ፡ በማለት ፡ አንድ ፡ ሲኾኑ ፡ የማይስማሙበት ፡ ምክንያት ፡ አሳባቸውን ፡ የሚገልጡባቸው ፡ ቃሎች ፡ ካለመስማማታቸው ፡ የተነሣ ፡ መኾኑ ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ የሚያከራክር ፡ አይደለም ።

## ደ ራ ሲ ።

፵፱/ የካቶሊክ ፡ ሰባኪዎች ፡ ከኬልቄዶኑ ፡ እነጋገር ፡ ይልቅ ፡ ትምህርቱን ፡ ይዘው ፡ በትርጒሙ አንድ ፡ የኾነ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የሚቀበሉት ፡ አነጋገር ፡ ለምሳሌ ፡ ክርስቶስ ፡ በመለኮትና ፡ በትስብእት የቆመ ፡ ፍጹም ፡ አምላክና ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ተወስነው ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ያለ ጥርጥር ፡ በትምህርት ፡ ያልበሰለ ፡ ማይምን ፡ ሊሰማው ፡ ወደማይችል ፡ ብዙ ፡ ረቂቅ ፡ ክርክሮች ፡ ከመውደቅ ፡ ድነው ፡ ፍሬ ፡ ካለው ፡ ፍጻሜ ፡ ላይ ፡ ይደርሱ ፡ ነበረ ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፵፱/ እውነት ፡ ነው ፡ ባሕርየ ፡ መለኮትና ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ በተዋሐዶ ፡ አንድ ፡ አልሆኑም ፡ መለኮትም ፡ ከትስብእት ፡ ተለይቶ ፡ የመለኮትን ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፤ ትስብእትም ፡ ከመለኮት ፡ ተለይቶ ፡ የትስብእትን ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ ከሚለው ፡ ከትምህርት ፡ ውጭ ፡ ከኾነው ፡ ከኬልቄዶኑ ፡ አነጋገር ፡ ይልቅ ፡ በመሠረተ ፡ ትምህርቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ከኹለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ከኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የኾነ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ተወስነው ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ ካለው ፡ ፍጻሜ ፡ በደረሱ ፡ ነበረ ።

## ደ ራ ሲ ።

፶/ ሉዶልፍ ፡ በክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ትምህርት ፡ በኩል ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ፍጹም ፡ ስምምነትን ፡ ለማግኘት ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ የሚለውን ፡ የኬልቄዶንን ፡ አነጋገር ፡ መለኮትና ፡ ትስብእት ፡ በሚል ፡ ቢተኩት ፡ ህላዌ ፡ የሚለውንም ፡ ቃል ፡ ባሕርይ ፡ ወይም ፡ አካል ፡ በሚል ፡ ቢተኩት ፤ የአካልነትንም ፡ አሳብ ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ በሚል ፡ አነጋገር ፡ ቢገልጡት ፡ በጣም ፡ የተሻለ ፡ ነበረ ፡ ሲል ፡ ጽፎ ፡ የተወልን ፡ ምክር ፡ ከወርቅና ፡ ካልማዝ ፡ የከበረ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፶/ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ መለኮትና ፡ ትስብእት ፡ ቢሉት ፡ በኢትዮጵያውያንና ፡ በካቶሊካውያን ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ አይገኝም ፤ ምክንያቱም ፡ የሚያጣላን ፡ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ በክርስቶስ ፡ ምንታዌ ፡ የለበትም ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ በማለትና ፡ በክርስቶስ ፡ የባሕርይ ፡ ምንታዌ ፡ አልጠፋም ፡ በማለት ፡ እንጂ ፡ መለኮትና ፡ ትስብእት ፡ ወይም ፡ ባሕርያት ፡ በማለት ፡ ስላልኾነ ፡ ነው ።

ህላዌ ፡ የሚለውንም ፡ ባሕርይ ፡ ወይም ፡ አካል ፤ በማለት ፡ ቢተኩት ፡ ምንታዌ ፡ ጠፋ ፡ የማይባል ፡ ከኾነ ፡ ምንም ፡ ስምምነት ፡ አይገኝም ።

የአካልነትንም ፡ አሳብ ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ በሚል ፡ አነጋገር ፡ ቢገልጡት ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የሚል ፡ አነጋገር ፡ ካልተጨመረበት ፡ ምንም ፡ የቀሻለ ፡ አይኾንም ።

## ደ ራ ሲ ።

፶፩/ እንዲሁም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ የሚያምኑትን ፡ ትምህርት ፡ ጠንቀቀው ፡ ያጠኑት ፡ ሌሎች ፡ ደራሲዎች ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለምሥጢረ ፡ ሥጋዌም ፡ ኾነ ፡ የሚናገሩትን ፡ አነጋገር ፡ ከኬልቄዶን ፡ ትምህርት ፡ ጋራ ፡ ለማስማማት ፡ ሲናገሩ ፡ ያንኑ ፡ አሳብ ፡ ይደግማሉ ፤ በጠቅላላው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የሚያምኑት ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ የቃል ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ባሕርይ ፡ ለሚለው ፡ ቃል ፡ የአካል ፡ ትርጉም ፡ ከመስጠትና ፡ ምሥጢረ ፡ ሥጋዌን ፡ ለመግለጥ ፡ ከሚያገቡት ፡ ለብቻው ፡ ከኾነ ፡ አሮጌ ፡ አነጋገር ፡ የተነሣ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ኹሉም ፡ ይስማማሉ ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፶፩/ ስለምሥጢረ ፡ ሥጋዌም ፡ ኾነ ፡ ስለሌላውም ፡ የሃይማኖት ፡ ጉዳይ ፡ ኹሉ ፡ የምንናገረው ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መንጭቶ ፡ ባሕርያት ፡ ልቡና ፡ ተቀድቶ ፡ ለዓለም ፡ ኹሉ ፡ የደረሰውን ፡ አሮጌውን ፡ አነጋገር ፤ እንደ ፡ ልብስ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ የዓለማዊ ፡ አኗኗር ፡ ያልቀያየርነው ፡ መኾናችን ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ወደፊትም ፡ ልንለዋውጠው ፡ አንወድም ። ምክንያቱም ፡ ለክርስቶስ ፡ ትምህርት ፡ ሌላ ፡ ትክ ፡ ምትክ ፡ የሚኾን ፡ ትምህርት ፡ ስለማይገኝለት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ እነዚህ ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ሊቃውንት ፡ በጥንታዊው ፡ ሃይማኖት ፡ የጸናን ፡ መኾናችንን ፡ ከመመስከር ፡ በቀር ፡ የማንንም ፡ ክህደትና ፡ ኑፋቄ ፡ ያልተከተልን ፡ መኾናችንን ፡ ስለመሰከሩልን ፡ በጣም ፡ እንደሰታለን ።

## ደ ራ ሲ ።

፶፪/ ካፑቺኑ ፡ መልእክተኛ ፡ አቡነ ፡ ማትያስ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለታቸው ፡ ባሕርይና ፡ አካል ፡ የሚሉትን ፡ ቃሎች ፡ ትርጉማቸውን ፡ በትክክል ፡ ለይተው ፡ ካላማወቃቸውና ፡ ከማወራረሳቸው ፡ የተነሣ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የነርሱ ፡ አነጋገር ፡ በቃል ፡ ብቻ ፡ ከኛው ፡ የተለየ ፡ ሲኾን ፡ በምሥጢሩ ፡ ከኛው ፡ ጋራ ፡ ፈጽሞ ፡ እንደሚስማማ ፡ አያጠራጥርምና ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ይገኛሉ ፡ ብለው ፡ በግልጥ ፡ ካልታመኑ ፡ አይኾንም ፡ ብሎ ፡ መጠንከር ፡ አስፈላጊ ፡ ኾኖ ፡ አይታየኝም ፡ ይላሉ ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፶፪/ እኛ ፡ በበኩላችን ፡ የአካልንና ፡ የባሕርይን ፡ ጠባይዕ ፡ ለይተን ፡ እንናገራለን ፡ እንጂ ፡ አደባልቀንና ፡ አቀላቅለን ፡ አንናገርም ። ያሁኑ ፡ አነጋገር ፡ የባሕርይንና ፡ የአካልን ፡ ትርጉም ፡ ለይተው ፡ አያውቁም ፡ ያወራርሳሉ ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ የባሕርይ ፡ ጠባይዕ ፡ ወይም ፡ ስሜት ፡ እንዲህ ፡ ነበረ ፡ የአካልም ፡ ጠባይዕ ፡ እንዲህ ፡ ነበረ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ያወራርሱታል ፡ እንዲህ ፡ አድርገው ፡ ያደባልቁታል ፡ ብለው ፡ የገለጡት ፡ ነገር ፡ የለም ። የተገለጠ ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፡ መልስ ፡ ይሰጥበት ፡ ነበረ ፡ ያልተገለጠ ፡ ነገር ፡ ስለኾነ ፡ መልስ ፡ ሊሰጥበት ፡ አልተቻለም ።

ደግሞ ፡ እኛ ፡ መለየታችን ፡ በተዋሕዶ ፡ ምንታዌ ፡ ስለጠፋ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ማለትና ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ምንታዌ ፡ አልጠፋም ፡ ማለት ፡ የተለያዩ ፡ ነገሮች ፡ መስለው ፡ ስለሚታዩን ፡ ነው ፤ ካቶሊካውያን ፡ ይህ ፡ አነጋገር ፡ በምሥጢር ፡ አንድ ፡ መኾኑን ፡ ከተረዱት ፡ ባነጋገሩ ፡ ብቻ ፡ ምን ፡ እንጎዳ ፡ ብለው ፡ ነው ፤ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ምንታዌ ፡ በተዋሕዶ ፡ ጠፍቷል ፡ አይሉና ፡ አንስማማምን ።

## ደ ራ ሲ ።

፶፫/ መታመን ፡ የሚገባው ፡ የተወሰነው ፡ ትምህርትና ፡ እርሱን ፡ የሚገልጡባቸው ፡ ቃሎች ፡ ለየብቻው ፡ ነው ። ትምርቱም ፡ ከጥንት ፡ የነበረና ፡ መቸውንም ፡ የማይለወጥ ፡ ነው ፡ የማያምነውም ፡ እንደ ፡ መናፍቅ ፡ መቆጠር ፡ አለበት ፤ ቃሉ ፡ ግን ፡ ባነጋገሩና ፡ ባጣጣሉ ፡ እንደየቦታውና ፡ እንደየጊዜው ፡ እንደ.የገባቡ ፡ ትርጕሙ ፡ የሚለዋወጥ ፡ ነው ፡ ብለዋል ፡ ስለሚሉት ።

## መ ላ ሽ ።

፶፫/ የሚታመነው ፡ ትምህርትና ፡ የሚገለጥበት ፡ ቃል ፡ ለየብቻው ፡ ነው ፡ ያሉበትን ፡ ምክንያት ፡ ገልጠውልን ፡ ቢኾን ፡ መልስ ፡ እንሰጥበት ፡ ነበረ ፡ ካልተገለጸ ፡ ግን ፡ ምን ፡ ሊደረግ ፡ ይቻላል ።

ትምርቱ ፡ ከጥንት ፡ የነበረ ፡ ነው ፡ መቸውንም ፡ አይለውጥም ፡ ማለታቸው ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ ትምርቱም ፡ ጥንታዊ ፡ ነው ፡ እርሱም ፡ ወአናቅጽ ፡ ሲኦልኒ ፡ ኢይኄይልዋ ፡ ተብሎ ፡ የተነገረለት ፡ እንደ መኾኑም ፡ ማንም ፡ ሊለውጠው ፡ አይችልም ፤ የማይቀበለውም ፡ እንደመናፍቅ ፡ መቆጠሩ ፡ አይካድም ፤ ቃሉ ፡ እንደ ፡ ጊዜውና ፡ እንደ ፡ አገባቡ ፡ ትርጕሙ ፡ ይለዋወጣል ፡ ያሉትም ፡ እውነት ፡ነው ።

ለምሳሌ ፡ ጌታ ፤ አነ ፡ ውእቱ ፡ አምላከ ፡ አብርሃም ፡ ወአምላከ ፡ ይስሐቅ ፡ ወአምላከ ፡ ያዕቆብ ብሏል ። ማቴ ፡ ፳፪ ፡ ፴፪ ።

ሙሴንም ፡ ረሰይኩከ ፡ አምላኮ ፡ ለፈርኦን ፡ ብሎታል ። አነ ፡ ውእቱ ፡ አምላከ ፡ አብርሃም ፡ ያለውና ፡ አምላኮ ፡ ለፈርዖን ፡ ያለው ንባብ ፡ አንድ ፡ ከኾነ ፡ ብለን ፡ አንድ ፡ ትርጕም ፡ አንስጠውም ፡ አምላከ ፡ አብርሃም ፡ ያለውን ፡ የአብርሃም፡ፈጣሪ፡አምላኩ፡ለፈርኦን፡ያለውን፡በፈርኦን፡ላይ፡ተአምራት ፡ ማድረግ ፡ የሚቻለው ፡ ነቢይ ፡ ብለን ፡ እንተረጕመዋለን ፤ ሌላውም ፡ ኹሉ ፡ እንደዚሁ ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ አኳኋን ፡ እንደ ፡ ጊዜውና ፡ እንዳመጣጡ ፡ መለዋወጡ ፡ አይቀርም ።

## ደ ራ ሲ ።

፶፬/ የቃል ፡ ቁም ፡ ነገሩ ፡ ሰው ፡ በልቡናው ፡ ያለውን ፡ አሳብ ፡ የሚገልጥበት ፡ መኾኑ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ካደማመጡ ፡ አይደለም ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ሊታመን ፡ የሚገባው ፡ ትምህርት ፡ ባንዳንድ ፡ ያልተለመዱ ቃሎች ፡ ተነግሮ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ሊረዱት ፡ የማይችሉ ፡ ከኾነ ፡ የሚፈለገው ፡ አሳቡን ፡ መረዳት ፡ ነውና ፡ ለቃሎቹ ፡ ግድ ፡ ማድረግ ፡ የሚያሻ ፡ አይመስልም ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በግልጥ ፡ እመኑበት ፡ ብላ ፡ ሳታዝዝ ፡ ሊቀበሉትና ፡ ሊያምኑበት ፡ የምትፈልገው ፡ ትምርቱን ፡ ነው ፡ የተወሰነ ፡ ድምፅ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ አይደለም ። ምክንያቱም ፡ ቃሉ ፡ ባንዳንዶች ፡ ዘንድ ፡ ስሕተትን ፡ ሊያሰማ ፡ ስለሚችል ፡ ነው ፡ ይላሉ ፤ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፶፬/ እኛ ፡ ከመጻሕፍት ፡ ተመልክተን ፡ ከመምህራን ፡ ሰምተን ፡ የተረዳነው ፡ ትምርት ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡ ሳይለወጥ ፡ ሳይቀላቀል ፡ በተፀቅቦ ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ አካለ ፡ ሥጋን ፡ ተዋሐደ ፡ በተዋሕዶ ፡ ምንታዌ ፡ ጠፋ ፡ ማለት ፡ ነው ። ሰብአዊ ፡ አካልን ፡ ሲዋሐድ ፡ ባሕርዩን ፡ ለይቶ ፡ ከተዋሕዶ ፡ በአፍዓ ፡ እንደተወው ፡ አይነግሩንም ። ስለዚህ ፡ ለትስብእት ፡ አካል ፡ የለውም ፡ ቃል ፡ የተዋሐደ ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይን ፡ ነው ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፡ ባሕርየ ፤ ሰብእን ፡ አልተዋሐደም ፡ የባሕርይ ፡ ምንታዌ ፡ አልጠፋም ፡ ማለት ፡ በመጻሕፍትም ፡ ተጽፎ ፡ ስለማይገኝ ፡ መምህሮቻችንም ፡ ስለማይነግሩን ፡ ስሕተት ፡ መስሎ ፡ ታይቶናል ። በናንተ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ የናንተ ፡ ባህልና ፡ የእኛ ፡ ባህል ፡ አንድ ፡ መኾኑን ፡ ከተረዳችሁት ፤ ስሕተት ፡ መስሎ ፡ ካልታያችሁ ፤ ሰውም ፡ የሚፈልገው ፡ አሳቡን ፡ መረዳት ፡ እንጂ ፡ አሳብ ፡ የሚገለጥበትን ፡ አነጋገር ፡ አለመኾኑን ፡ ከተረዳችሁት ፡ እንደኛው ፡ አነጋገር ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ብላችሁ ፡ ለእኛ ፡ በሚሰማን ፡ አነጋገር ፡ ንግግራችሁን ፡ አርማችሁት ፡ እንስማማምን ፡ ምን ፡ ያጣላናል ።

እንዲህ ፡ ብለው ፡ ከኾነስ ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የአባ ፡ ማሲያስን ፡ ምክር ፡ ተቀብላ ፡ ንግግሯን ፡ አርማ ፡ ቢኾን ፡ በመካከላችን ፡ስምምነት ፡ ይገኝ ፡ ኖሯል ።

## ደ ራ ሲ ፡፡

፺፩/ ፩ኛ ፡ ዮሲፍ ፡ ሳፔቶ ፤ ፪ኛ ፡ አንቶኒና ፡ ዲባዲ ፤ ፫ኛ ፡ ጀባ ፡ ኩልቦ ፤ ፬ኛ ፡ ማ ፡ ዩገር ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከሮማ ፡ ጋራ ፡ አለመስማማታቸው ፡ ባፍ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ምክንያቱም ፡ ምሥጢሩን ፡ ለመግለጥ ፡ ከሚያገቡት ፡ ቃል ፡ ልዩነትና ፡ ባሕርይንና ፡ አካልን ፡ ስለሚያወራርዷቸው ፡ ነው ፡ እሉ ፡ ብለዋል ፡፡

## መ ላ ሽ ፡፡

፺፪/ የኒህም ፡ ያራቱ ፡ መርማሪዎች ፡ አነጋገር ፡ ከላይ ፡ ከተጻፉት ፡ ከነሉዶልፍ ፡ ከነ ፡ አባ ፡ ማስያስ ፡ አነጋገር ፡ ልዩነት ፡ ስለሌለው ፡ መልሱ ፡ ከላይ ፡ የተጻፈው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከማሰብ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የምሰጠው ፡ መልስ ፡ የለኝም ፡፡ የኾነ ፡ ኾኖ ፡ እኒህን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ኢትዮጵያ ፡ የንስጥሮስን ፡ ወይም ፡ የአውጣኪን ፡ ወይም ፡ የማናቸውንም ፡ መናፍቅ ፡ ስሕተት ፡ ተቀብላለች ፡ ብለው ፡ ባለመጻፋቸው ፡ እውነተኞች ፡ ናቸው ፡ ብዬ ፡ አመሰግናቸዋለሁ ፡፡

## ደ ራ ሲ ፡፡

፺፫/ ኢትዮጵያውያን ፡ ባሕርይ ፡ ሲሉ ፡ የራሱ ፡ ፍጹም ፡ ህላዌ ፡ ያለው ፡ ኋኝ ፡ (ማለት) ፡ አካል ፡ ወይም ፡ ቅኑም ፡ ማለትን ፡ እንደሚያሰሙ ፡ ኹሉም ፡ የሚታመኑበት ፡ ነው ፡ ብለዋል ፡፡

## መ ላ ሽ ፡፡

፺፬/ ይህ ፡ አነጋገር ፡ ባሕርይና ፡ አካል ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ እንደ ፡ ሌላቸው ፡ የሚያመለክት ፡ ንግግር ፡ ነው ፡፡ ይህን ፡ የሚያምኑ ፡ ሰዎች ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ አነጋገር ፡ ገና ፡ አልደረሱበትም ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ፡፡

አካል ፡ ማለት ፡ የሚታየው ፡ የሚጨበጠው ፡ ነው ፤ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ ግን ፡ በአካል ፡ ህልው ፡ ኾኖ ፡ አካል ፡ ሲገኝ ፡ ተገኝቶ ፡ የአካልን ፡ ኹኔታ ፡ የሚገልጽ ፡ ጠባይዕ ፡ ነው ፡፡

እንዲህ ፡ ማለት ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ገለጽነው ፡ እሳት ፡ አካሉ ፡ በዕንጨት ፡ ወይም ፡ በመብራት ፡ ላይ ፡ ሲገለጽ ፡ ዋዕይ ፡ ከአካሉ ፡ ተገኝቶ ፡ በአካሉ ፡ ህልው ፡ ኾኖ ፡ የእሳትን ፡ ጠባይዕ ፡ ይገልጻል ፡፡

ወኃም ፡ አካሉ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ ርጥበት ፡ ከአካሉ ፡ ተገኝቶ ፡ በአካሉ ፡ ህልው ፡ ኾኖ ፡ የውኃን ፡ ጠባይዕ ፡ ይገልጻል ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡

ስለዚህ ፡ ባሕርይ ፡ ከአካል ፡ ተገኝቶ ፡ በአካል ፡ ህልው ፡ ኾኖ ፡ ከአካል ፡ ሳይለይ ፡ የአካልን ፡ ጠባይዕ ፡ ይገልጻል ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ አካል ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ባሕርይ ፡ አካል ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ቀላቅለን ፡ አንናገርም ፡፡

## ደ ራ ሲ ፡፡

፺፭/ ኢትዮጵያውያን ፡ የአካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ ምሥጢርን ፡ የሚገልጡበት ፡ አነጋገር ፡ ምንም ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ በጠቅላላ ፡ ሲሰሙት ፡ በኬልቄዶን ፡ የተወሰነውን ፡ ትምህርት ፡ የሚቃወም ፡ ቢኾን ፡ በንግግሩ ፡ ውስጥ ፡ የሚቀድመውንና ፡ የሚከተለውን ፡ ቢያስተውሉበት ፡ በአሳቡ ፡ ከኬልቄዶኑ ፡ ውሳኔ ፡ ጋራ ፡ መስማማቱን ፡ ኹሉም ፡ ያከብሩበታል ፡ ብለዋል ፡፡

## መ ላ ሽ ፡፡

፺፮/ ኢትዮጵያውያን ፡ ቃል ፡ ከእመቤታችን ፡ በሕፃናት ፡ መጠን ፡ ሥጋን ፡ ነሥቶ ፡ ሲዋሐድ ፡ በተዋሕዶ ፡ ምንታዌ ፡ ጠፋ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኾነ ፡ ሲሉ ፡ ባሕርይም ፡ የአካል ፡ መገኛ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ በአካል ፡ ህልው ፡ ኾኖ ፡ የአካልን ፡ ጠባይዕ ፡ የሚገልጽ ፡ ከመኾኑ ፡ በቀር ፡ ከአካል ፡ በአፍኣ ፡ ስላልኾነ ፡ አካል ፡ ሲዋሐድ ፡ ባሕርይም ፡ ተዋሐደ ፡ በተዋሕዶ ፡ ምንታዌ ፡ ጠፋ ፡ ይላሉ ፡፡ ካቶሊካውያን ፡ ግን ፡ ቃል ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይን ፡ ተዋሐደ ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡ ሰብአዊ ፡ አካልን ፡ ተዋሐደ ፡ አይሉም ፡፡

መልሰው ፡ ደግሞ ፡ ባሕርይ ፡ አልተዋሐደም ፡ ምንታዌ ፡ አልጠፋም ፡ ይላሉ ፡፡ ከዚህም ፡ ኢያይዘው ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኾነ ፡ ምንታዌ ፡ ጠፋ ፡ ካላችሁ ፡ አንዱ ፡ ባሕርይ ፡ ጠፋ ፡ ማለት ፡ ግድ ፡ ነውና ፡ ከመለኮት ፡ ባሕርይና ፡ ከትስብእት ፡ ባሕርይ ፡ የጠፋ ፡ የትኛው ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ያቀርባሉ ፡ ለዚህም ፡ ጥያቄ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሰብአዊ ፡ አካል ፡ የሚሉትን ፡ ካቶሊካውያን ፡ ሰብአዊ ፡

ባሕርይ ፡ ቢሉትም ፡ ስም ፡ መለዋወጥ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ወንጌላዊ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፤ ኮነ ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ ቃል ፡ ባዕድ ፡ ሥጋን ፡ እንደ ፡ ተዋሐደ ፡ ቢዋሐድም ፡ መለኮቱ ፡ ትስብእቱን ፡ ሳያጠፋው ፡ ትስብእቱ ፡ መለኮቱን ፡ ሳይለውጠው ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኾነ ፡ በግልጽ ፡ ይናገራሉ ። ቃል ፡ ባዕድ ፡ ሥጋን ፡ ከተዋሐደ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ የሚባል ፡ ከመለኮትና ፡ ከትስብእት ፡ የትኛው ፡ ጠፍቶ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ የጥያቄ ፡ መልስ ፡ ማቅረብ ፡ ግድ ፡ ይኾንብናል ። እንዲህም ፡ ማለት ፡ ቃል ፡ በሕፃናት ፡ መጠን ፡ ሥጋን ፡ ነሥቶ ፡ ሰብአዊ ፡ አካልን ፡ ገንዘብ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ እንደኾነ ፡ የባሕርይም ፡ ተዋሕዶ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ በኢትዮጵያውያንና ፡ በካቶሊካውያን ፡ መካከል ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ መለያየት ፡ ሳለ ፡ ይስማማሉ ፡ ማለት ፡ እንደምን ፡ ይቻላል አይቻልም ።

ደ ራ ሲ ።

፶፰/ ይህም ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ካቶሊክ ፡ ቄስ ፡ ጽፈው ፡ ትተውልናል ፡ ብለው ፡ በግእዝ ቋንቋ ፡ አካልና ፡ ባሕርይ ፡ አይወራረሱም ፡ የሚወራረሱ ፡ ባሕርይና ፡ ህላዌ ፡ ናቸው ፡ አሉ ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፶፰/ ይህ ፡ እውነተኛ ፡ ንግግር ፡ ነው ፡ ባሕርይን ፡ አካላዊ ፡ ፍጹመ ፡ አካል ፡ በማለት ፤ አካልንም ፡ ባሕርያዊ ፡ ሕያው ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ እናገናዝባቸዋለን ፡ እንጂ ፡ አካልን ፡ ባሕርይ ፤ ባሕርይን ፤ አካል ፡ ብለን ፡ አንጠራቸውም ። ባሕርይና ፡ ህላዌ ፡ ይወራረሳሉ ፡ የሚሉት ፡ ግን ፡ ህላዌ ፡ ግእዝ ፡ ስለኾነ ፡ ባሕርይ ፡ ተብሎ ፡ የሚተረጐምበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፤ አኗኗር ፡ ተብሎ ፡ የሚተረጐምበትም ፡ ጊዜ ፡ አለ ፤ እንደ ፡ ነገሩ ፡ አመጣጥ ፡ በብዙ ፡ ዐይነት ፡ ይፈታል ። ባሕርይ ፡ ግን ፡ በግእዝም ፡ ባማርኛም ፡ ሞልቶ ፡ የሚገኝ ፡ ቋንቋ ፡ ስለኾነ ፡ ያው ፡ ባሕርይ ፡ ተብሎ ፡ ይፈታል ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ትርጓሜ ፡ የለውም ፡ ስለዚህ ፡ ባሕርይና ፡ ህላዌ ፡ ይወራረሳሉ ፡ ያሉት ፡ የሚያጠግብ ፡ ንግግር ፡ አይደለም ።

ደ ራ ሲ ።

፶፱/ አንዱን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሊቅ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ አምላክና ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ እንደኾነ ፡ ማለት ፡ የመለኮትና ፡ የሥጋ ፡ ባሕርያት ፡ ያሉት ፡ መኾኑን ፡ ታምናላችሁን ፡ ስል ፡ ብጠይቀው ፡ እንዴታ ፡ በደንብ ፡ እንጂ ፡ ሲል ፡ መለሰልኝ ። እኔም ፡ ቀጥዬ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ አምላክና ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ይሠራ ፡ ነበርን ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አነጋገር ፡ አምላካዊና ፡ ሰብአዊ ፡ የኾኑ ፡ ኹለት ፡ ሥራዎች ፡ በክርስቶስ ፡ ይገኛሉን ፡ ብለው ፡ ምንም ፡ ሳይሰጋ ፡ መለሰልኝ ፡ እንዲህማ ፡ ከኾነ ፡ እናንተም ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ መኖራቸውን ፡ ታምናላችኋ ፡ ብለው ፡ የለም ፡ አናምንም ፡ ሲል ፡ ካደኝ ፡ አሉ ፡ ስለሚሉት ።

መ ላ ሽ ።

፶፱/ ያ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሊቅ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክ ፡ ወሰብእ ፡ ነዎይ ፡ ቢሉት ፡ አዎን ፡ ማለቱ ፡ አካለ ፡ ቃል ፡ ባሕርየ ፡ ቃል ፡ አካለ ፡ ሰብእን ፡ ባሕርየ ፡ ሰብእን ፡ በተዐቅቦ ፡ ስለተዋሐደ ፡ ነው ። የመለኮትና ፡ የትስብእት ፡ ሥራዎች ፡ በርሱ ፡ መገኘታቸውን ፡ ቢጠይቁት ፡ ይገኛሉ ፡ ብሎ ፡ ማመኑ ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ ቤት ፡ መጠራት ፤ በምራቅ ፡ ጭቃ ፡ መለወስ ፡ በመርከብ ፡ ላይ ፡ መተኛት ፡ አልዓዛርን ፡ ወዴት ፡ ቀብራችሁ ፡ ብሎ ፡ መጠየቅ ፡ ይህን ፡ የመሳሰለው ፡ የሰውነት ፡ ሥራ ፤ ውኃውን ፡ ወይን ፡ ማድረግ ፤ በደረቅ ፡ ግንባር ፡ ዓይን ፡ መፍጠር ፤ ነፋሳትንና ፡ ማዕበላትን ፡ መገሠጽ ፤ አልዓዛር ፡ አልዓዛር ፡ ብሎ ፡ ጠርቶ ፡ ከመቃብር ፡ ማስነሣት ፡ የአምላክነት ፡ ሥራዎች ፡ ስለኾኑ ፡ ነው ።

እንግዲያማ ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ አሉ ፡ ትላላችኋ ፡ ቢሉት ፡ መካዱ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በተዋሕዶ ፡ ምንታዌን ፡ አጥፍቶ ፤ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የኾነ ፡ ክርስቶስ ፡ ኹለቱን ፡ የአምላክነትንና ፡ የሰውነትን ፡ ሥራዎች ፡ ባንድ ፡ ፈቃድ ፡ ባንድ ፡ ሥምረት ፡ ባንድ ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ሠራቸው ፡ ያምናሉ ፡ እንጂ ፡ እንደካቶሊካውያን ፡ መለኮትንና ፡ ትስብእትን ፡ ለያይተው ፡ የመለኮትን ፡ ሥራ ፡ መለኮት ፡ ሠራ ፡ የትስብእትን ፡ ሥራ ፡ ትስብእት ፡ ሠራ ፡ የማይሉ ፡ ስለኾነ ፡ ይህ ፡ መልስ ፡ የባሕርይ ፡ ምንታዌን ፡ የሚከላከል ፡ ትክክለኛ ፡ መልስ ፡ ነው ።

የመለኮትና ፡ የሥጋ ፡ ባሕርያት ፡ ያሉት ፡ መኾኑን ፡ ታምናላችሁ ፡ ወይ ፡ ብለው ፡ አዎን ፡ አለ ፡ የሚሉት ፡ ግን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ በክርስቶስ ፡ ላይ ፡ ምንታዌን ፡ የሚያመለክት ፡ ባሕርያት ፡ የሚል ፡ ንግግር ፡ በፍጹም ፡ ስለሌለ ፡ ያ ፡ ሊቅ ፡ ይህን ፡ መልስ ፡ ይሰጣል ፡ ብየ ፡ አላምንም ።

ደ ራ ሲ ።

፳/ እኔም ፡ ፆ ፡ ሲቅ ፡ በፊት ፡ በሃልቀ ፡ የታመነበት ፡ ኋላ ፡ የከዳኝ ፡ ባሕርይ ፡ ለሚለው ፡ ቃል ፡ ምንድ ፡ ጓኝ ፡ ወይም ፡ ፀልው ፡ ትርጉም ፡ ከመስጠቱ ፡ የተገኘ ፡ ነው ፤ ባሕርይ ፡ ለሚለውም ፡ ቃል ፡ ፊት ፡ እንዳልኩት ፡ የሀላዌ ፡ ወይም ፡ የጓኝ ፡ ትርጉም ፡ አለው ፡ ብለዋል ፡ ስለሚሉት ።

መ ላ ሽ ።

፳/ በኢትዮጵያውያን ፡ ባሀል ፡ በብዙ ፡ ስፍራ ፡ መላልሰን ፡ እንዳስረዳነው ፡ ባሕርይ ፡ አካልን ፡ አስገኝቶ ፡ በአካል ፡ ሀልው ፡ ኾኖ ፡ የአካልን ፡ ጠባይዕ ፡ የሚገኝ ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ ጓኝ ፡ አይደለም ፡ ይህ ንንስ ፡ ስሜት ፡ የሚሰጥ ፡ አካል ፡ ተዋሐደ ፡ ባሕርይ ፡ ግን ፡ አልተዋሐደም ፡ የሚለው ፡ የካቶሊክ ፡ ባሀል ፡ ነው ።

ደ ራ ሲ ።

፳፩/ ከኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ አካል ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በመሠረታዊ ፡ ትርጉሙ ፡ እንደማያደና ግርና ፡ ለመስማቱ ፡ እንደማያስቸግር ፡ እናሳስባለን ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፳፩/ እንደ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አነጋገር ፡ አካል ፡ ሲባል ፡ ከራስ ፡ ጠጉር ፡ እስከ ፡ እግር ፡ ጥፍር ያሉትን ፡ ሕዋሳት ፡ ያመለክታል ። ይህንንም ፡ አካል ፡ ቃል ፡ በተዋሕዶ ፡ ገንዘብ ፡ አድርጎታል ፡ ገንዘብ ፡ አደረገውም ፡ ስንል ፡ በማኅፀነ ፡ ማርያም ፡ በሕፃናት ፡ መጠን ፡ የዕለት ፡ ፅንስ ፡ ኾኖ ፡ እስከ፡ ፵ ቀን ፡ ተሥዕሎተ፡ መልክእ ፡ ተፈጽሞለት ፡ በየጥቂቱ ፡ አደገ ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ ከተዋሕዶ ፡ በፊት ፡ ሙሉ ፡ ቅርጽ ፡ አካል ፡ ተገኝቶ ፡ ያንን ፡ ተዋሐደ ፡ የምንል ፡ አይደለንም ፤ በዚኸውም ፡ አካል ፡ ተገልጾ ፡ የአምላክነትንም ፡ የሰውነትንም ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሠራ ፡ እናምናለን ፤ ስለዚህ ፡ በኛ ፡ አነጋ ገር ፡ የአካል ፡ ትርጓሜ ፡ ምንም ፡ አስቸጋሪነት ፡ የለበትም ።

በካቶሊክ ፡ አነጋገር ፡ ግን ፡ ቃል ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይን ፡ ተዋሐደ ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡ ሰብአዊ ፡ አካልን ፡ ተዋሐደ ፡ አይሉም ፤ ወንጌላዊ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ ቃል ፡ በከዊን ፡ የተ ገለጸበትን ፡ ሥጋ ፡ ባሕርይ ፡ እንጂ ፡ አካል ፡ አንለውም ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ ነው ፡ ሲሉን ፡ በእውነቱ ፡ ቃል ፡ የተዋሐደ ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይን ፡ ከኾነ ፡ አልተዋሐደም ፡ በምንታዌ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ የሚሉትም ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይን ፡ ከኾነ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ የሚሉት ፡ ዕሩቅ ፡ ቃልን ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ ሌላን ፡ አካል ፡ አለ ፡ በማለት ፡ እንቸገራለን ። ሰብአዊ ፡ ባሕርይን ፡ ተዋሐደ ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፡ ባሕርይ ፡ አልተዋሐደም ፡ ሲሉን ፡ ለነገሩ ፡ መጨበጫ ፡ ልናገኝለት ፡ አልቻ ልንም ።

ደ ራ ሲ ።

፳፪/ ይህ ፡ ኹሉ ፡ ችግርና ፡ ያሳብ ፡ ድንግርግር ፡ የሚነግው ፡ ባሕርይና ፡ ሀላዌ ፡ የሚሉት ፡ ቃላት ፡ ትርጉማቸው ፡ ያልተወሰነ ፡ በመኾኑ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፳፪/ እንደኛ ፡ ባሀል ፡ የባሕርይ ፡ ትርጓሜ ፡ እንደ ፡ አካል ፡ የተወሰነ ፡ ስለኾነ ፡ ምንም ፡ ችግር ፡ የለበትም ፡ ሀላዌ ፡ ግን ፡ በብዙ ፡ ዐይነት ፡ የሚተረጐም ፡ ስለሆነ ፡ መጻሕፍትን ፡ ከላይ ፡ እርእስታ ቸውን ፡ ከታች ፡ ኅዳጋቸውን ፡ አይቶ ፡ መምህራንን ፡ ጠይቆ ፡ ካልተረዱት ፡ በመላ ፡ በድፍረት ፡ ልተ ርጉምህ ፡ ቢሉት ፡ ማስቸገሩ ፡ አይቀርም ፡ ከስሕተት ፡ ላይ ፡ ይጥላል ።

ደ ራ ሲ ።

፳፫/ ከኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ሲከራከሩ ፡ ስለኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ያላቸው ፡ ያልተካከለ ፡ አስተያየትና ፡ አሳብ ፡ ከልባቸው ፡ ለማራቅ ፡ ጠቃሚ ፡ የኾነው ፡ መንገድ ፡ ፪ቱ ፡ ባሕርያት ፡ ፪ቱ ፡ ህላዌያት ፡ የሚሉትን ፡ በፍልስፍና ፡ በጣም ፡ የተራቀቁትን ፡ ቃሎች ፡ ትቶ ፡ የባሕርይነትን ፡ አሳብ ፡ በኹሉ ፡ ዘንድ ፡ በታወቁ ፡ ቃሎችና፡ የጋራ፡ በኾነ ፡ አነጋገር ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ጓኝ ፡ አንድ ፡ ቀውም፡ ኗሪ ፡ አንድ ፡ ህልው ፡ የግብሮችና ፡ የኹኔታዎች ፡ ባለቤት ፡ ነው ፡ በማለት ፤ ወይም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስ ቶስ ፡ ፍጹምና ፡ እውነተኛ ፡ ሰው ፤ ፍጹምና ፡ እውነተኛ ፤ አምላክ ፡ ነው ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ አምላክና ፡ ሰው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ሲገልጡት ፡ መኾኑን ፡ እናሳስባለን ። እንዲህ ፡ ያለውን ፡ አነጋገር ፡ የሚቃ ወም ፡ አንድም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ባልተገኘም ፡ ነበረ ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፬/ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ኋኝ ፡ አንድ ፡ ቅውም ፡ ኗሪ ፡ አንድ ፡ ሀልው ፡ የግብሮችና ፡ የኹኔታዎች ፡ ባለቤት ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ከአሥራው ፡ መጻሕፍት ፡ የተመሠረተ ፡ አነጋገር ፡ ነው ። ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ኹለት ፡ ህላዌያት ፡ ማለት ፡ ግን ፡ ከአሥራው ፡ መጻሕፍት ፡ ያልተመሠረተ ፡ በፍልስፍና ፡ የተመሠረተ ፡ አነጋገር ፡ ነው ፡ በልብ ፡ ወለድ ፡ የተመሠረተውን ፡ ትክክለኛ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተቀብሎ ፡ በአሥራው ፡ መጻሕፍት ፡ የተመሠረተውን ፡ ትክክለኛ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ መንቀፍ ፡ ያሳዝነናል ፡ እንጂ ፡ ከክርስቶስ ፡ ምንታዌን ፡ አርቆ ፡ አንድ ፡ ሀልው ፡ የግብሮችና ፡ የኹኔታዎች ፡ ባለቤት ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ከተገኘ ፡ መስማማታችን ፡ አይቀርም ።

ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ የሚለው ፡ አነጋገር ፡ ግን ፡ ጠማማ ፡ ልቡና ፡ ሲይዘው ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ባለጊዜ ፡ ዕሩቅ ፡ አምላክ ፡ ማለትን ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ባለጊዜ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ማለትን ፡ አሰምቶ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ የሚያስከትል ፡ መስሎ ፡ ስለሚታይ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ የኾነ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ንግግሩ ፡ እንዲሻሻል ፡ አሳስብዎታለሁ ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፭/ ይህ ፡ አገላለጥ ፡ እንደ ፡ ቀናውም ፡ ትምህርት ፡ የባሕርይን ፡ ፈላስፋዊ ፡ አሳብ ፡ በውስጡ የያዘ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፮/ በዚህ ፡ አነጋገርዎ ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክ ፡ ወሰብእ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ያልደረሱበት ፡ ካቶሊካውያን ፡ በፍልስፍናና ፡ በተራቅቆ ፡ ያገኙት ፡ ጥልቅ ፡ እውቀት ፡ አስመስለው ፡ ይናገራሉ ። መጻሕፍት ፡ የአምላክነቱን ፡ ወይም ፡ የሰውነቱን ፡ ነገር ፡ በ ፡ በሚል ፡ አገባብ ፡ መማሪያነት ፡ ሞተ ፡ በሥጋ ፡ ወሐይወ ፡ በመንፈስ ፡ እያሉ ፡ ይነግሩናል ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ ባለቤት ፡ አድርገው ፡ ሥጋ ፡ ሞተ ፡ መለኮት ፡ ሕያው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አይነግሩንም ።

ሥጋ ፡ ሞተ ፡ መለኮት ፡ አልሞተም ፡ ብሎ ፡ ለያይቶ ፡ መናገር ፡ ከተዋሕዶ ፡ የሚያወጣ ፡ ምንታዌን ፡ የሚያስከትል ፡ መኾኑን ፡ በሥጋ ፡ ሞተ ፡ በመለኮት ፡ ሕያው ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ግን ፡ ካንድነት ፡ የማያወጣ ፡ ምንታዌን ፡ የማያስከትል ፡ ያንድነት ፡ አነጋገር ፡ መኾኑን ፡ ይመልከቱልኝ ።

ስለዚህ ፡ የክርስቶስን ፡ ተዋሕዶ ፡ እጥፍተው ፡ ኅድረት ፡ ወይም ፡ ምንትው ፡ አካል ፡ ምንትው ፡ ባሕርይ ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ የወደቁበት ፡ የስሕተት ፡ ጉድጓድ ፡ መኾኑን ፡ በመገንዘብ ፡ እንቀበለውም ፡ እንጂ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ክርስቶስ ፡ ያምላክነትንም ፡ የሰውነትንም ፡ ሥራ ፡ ከሠራ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ያስኘዋል ፡ ብለው ፡ የሚናገሩት ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ንግግር ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ ፍልስፍናና ፡ ተራቅቆ ፡ የሌለበት ፡ እንደ ፡ ተራራ ፡ ገዘፎ ፡ የሚታይ ፡ መኾኑን ፡ ይወቁ ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፯/ ኢትዮጵያውያን ፡ የክርስቶስን ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ሲተረጕሙ ፡ የሚያገቧቸው ፡ ቃሎችና ፡ የባህል ፡ መግለጫዎች ፡ ሠንጠረዥ ፡ የላቲንና ፡ የጽርእ ፡ ቃሎች ፡ ትርጕማቸው ፡ በግእዝ ፡ ብለው ፡ በሠንጠረዥ ፡ ጽፈዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፰/ ይህነን ፡ አመዛዝኖ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ እኒህን ፡ ቋንቋዎች ፡ ጽርእን ፤ ላቲንን ፤ ግእዝን ፤ አማርኛን ፡ አጣርቶ ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል ። እኔ ፡ በበኩሌ ፡ ግእዝና ፡ አማርኛ ፡ ባውቅ ፡ ጽርእና ፡ ላቲን ፡ ባለማወቄ ፡ ልክ ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ልክ ፤ አይደለም ፡ ብሎ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ አልደፍርም ። ርስዎም ፡ በበኩልዎ ፡ ምናልባት ፡ ጽርእና ፡ ላቲን ፡ አጣርተው ፡ ያውቁ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግእዝና ፡ አማርኛን ፡ አጣርተው ፡ ያውቁ ፡ ስለማይመስለኝ ፡ ሚዛኑ ፡ ተካክሎ ፡ ይገኝ ፡ አይመስለኝም ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፱/ ኹለተኛ ፡ ሠንጠረዥ ፡ የኢትዮጵያውያንና ፡ የካቶሊካውያን ፡ የባህል ፡ መግለጫዎች ፡ አነጣጠር ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ተነሥተው ፡ ኢትዮጵያውያንና ፡ ካቶሊካውያን ፡ የሚያብሩባቸው ፡ ትምህርቶች ፡ ክርስቶስ ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ የቆመ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ይተባበራሉ ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፰፯/ ለመለኮትም ፡ ለትስብእትም ፡ አካል ፡ አለው ፡ ለመለኮት ፡ አካል ፡ መኖሩ ፡ አብኒ ፡ ፍጹም ፡ በአካሉ ፡ ወልድኒ ፡ ፍጹም ፡ በአካሉ ፡ ባለው ፡ ታውቋል ፡ ለትስብእትም ፡ አካል ፡ መኖሩ ፡ ወአካልየኒ ፡ ወኢከመ ፡ ምንት ፡ በቅድሜክ ፡ ባለው ፡ ይታወቃል ። ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ይህን ፡ ጠንቅቀው ፡ ክርስቶስ ፡ በተዋሕዶ ፡ ከኹለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኾነ ፡ ይላሉ ። ካቶሊካውያን ፡ ግን ፡ አካል ፡ የመለኮትም ፡ የትስብእትም ፡ መኖሩ ፡ ሲታወቅ ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ ኾነ ፡ ሳይሉ ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ ሲሉ ፡ ይህ ፡ አካል ፡ የቃል ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ የትስብእት ፡ ብቻ ፡ ሊኾን ፡ የሚችል ፡ ስለኾነ ፡ ይልቁንም ፡ ለትስብእት ፡ አካል ፡ የለውም ፡ የሚሉ ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ የሚሉት ፡ የዕሩቅ ፡ ቃልን ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ የሚያመለክት ፡ ስለኾነ ፡ ይኸውም ፡ የሚያስተባብራቸው ፡ መስሎ ፡ አይታይም ።

## ደ ራ ሲ ።

፰፰/ ይህንንም ፡ በካቶሊካውያን ፡ አፈታት ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ባሕርየ ፡ መለኮትና ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ማለት ፡ ክርስቶስ ፡ በአካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ የተዋሐዱ ፡ የአምላክነት ፡ ባሕርይና ፡ የሰውነት ፡ ባሕርይ ፡ አሉት ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፰፱/ አንድ ፡ አካል ፡ የሚሉት ፡ ይህ ፡ አካል ፡ የቃል ፡ ብቻ ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ የትስብእት ፡ የቃል ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንዳይሉ ፡ ወንጌላዊ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ያለው ፡ ቀርቶ ፡ ዕሩቅ ፡ ቃል ፡ ያሰኛል ። የትስብእት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ቢሉም ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ያሰኛል ፡ እንጂ ፡ ሥግው ፡ ቃል ፡ አያሰኝም ። ኹለተኛም ፡ ተዋሕዶ ፡ ማለት ፡ ኹለቱ ፡ አንድ ፡ መኾናቸውን ፡ ያመለክታል ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ ተዋሐደ ፡ ሊባል ፡ አይቻልምና ፡ በተዋሕዶ ፡ ከኹለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኾነ ፡ ማለት ፡ ግድ ፡ በግድ ፡ ነው ። ይህም ፡ ተዋሕዶ ፡ ቱሳሔ ፡ ምንታዌ ፡ ቡዓዴ ፡ ውላጤ ፡ ፍልጠት ፡ የሌለበት ፡ በተዐቅቦ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ መኾኑ ፡ በኹላችንም ፡ ዘንድ ፡ የሚካድ ፡ አይመስለኝም ።

ባሕርያትም ፡ እንደዚሁ ፡ በአካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ የተዋሐዱ ፡ ናቸው ፡ ካሉ ፡ ባሕርያት ፡ ከአካላት ፡ የተለዩ ፡ ነገሮች ፡ አይደሉምና ፡ አካላት ፡ ሲዋሐዱ ፡ ባሕርያትም ፡ መዋሐዳቸው ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ይህም ፡ ተዋሕዶ ፡ ያው ፡ ከላይ ፡ የጠቀስነው ፡ የአካላዊው ፡ ተዋሕዶ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ ተዋሕዶ ፡ ስላልኾነ ፡ ባሕርያትንም ፡ እንደ ፡ አካላት ፡ ከምንታዌ ፡ ከቱሳሔ ፡ ከቡዓዴ ፡ ከፍልጠት ፡ በተዐቅቦ ፡ ተጠብቆ ፡ የሚኖር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ ተዋሕዶ ፡ አይደለም ።

እንግዲህ ፡ አካልና ፡ ባሕርይ ፡ በስም ፡ ቢለያዩ ፡ በከዊን ፡ የሚለያዩ ፡ ስለላልኾኑ ፡ አካላት ፡ ተዋሕዱ ፡ ባልን ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ተዋሕዶ ፡ ምንታዌን ፡ አጥፍቶ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ማስገኘቱን ፡ አምነው ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ካሉ ፡ ባሕርያትም ፡ በአካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ ተዋሐዱ ፡ በሚሉበት ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ተዋሕዶ ፡ ምንታዌን ፡ አጥፍቶ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የሚያሰኝ ፡ መኾኑን ፡ ተገንዝበው ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስን ፡ መስለው ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ይበሉ ።

ወይም ፡ ይህ ፡ ተዋሕዶ ፡ ምንታዌን ፡ አያጠፋም ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ እላለሁ ፡ የሚሉ ፡ ከኾነ ፡ በአካልና ፡ በባሕርይ ፡ ተዋሕዶ ፡ ልዩነት ፡ ስለሌለ ፡ ያው ፡ አንድ ፡ ተዋሕዶ ፡ ስለኾነ ፡ ምንታዌ ፡ ከአካልም ፡ አልጠፋ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ንስጥሮስን ፡ ጨርሰው ፡ ይምሰሉት ፡ እንጂ ፡ በቄርሎስና ፡ በንስጥሮስ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ልዩነት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዓለም ፡ ያወቀው ፡ ሲኾን ፡ ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ እንደ ፡ ቄርሎስ ፡ ነኝ ፡ ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ ነኝ ፡ እያሉ ፡ ማደናገርና ፡ የሰማዕያንን ፡ ልቡና ፡ ማባከን ፡ ተገቢ ፡ ነገር ፡ አይደለም ፡ መንተው ፡ መንቃ ፡ አደረገ ፡ ማለትና ፡ ተዋሐደ ፡ አንድ ፡ ኾነ ፡ ማለትም ፡ ተቃራንያን ፡ መኾናቸውን ፡ አይዘንጉ ።

## ደ ራ ሲ ።

፺/ የኢትዮጵያውያኖቹ ፡ አፈታት ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ሲሉ ፡ በመለኮቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ የአምላክነት ፡ ባሕርይ ፡ አለው ፡ ማለት ፡ ነው ። በትስብእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ማለት ፡ የሰውነት ፡ ባሕርይ ፡ አለው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ የቆመ ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፷፰/ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ሲናገሩ ፡ መለኮት ፡ በተዋሕዶ ፡ የሥጋን ፡ ርስት ፡ ገንዘብ ፡ አድርጎ ፡ ነደየ ፡ ርኅበ ፡ ጸምአ ፡ ተጸነሰ ።

ደኀየ ፡ ተራበ ፡ ተጠማ ፡ ተቸገረ ፡ እንዲ ፡ ተባለ ፡ ትስብእትም ፡ በተዋሕዶ ፡ የቃልን ፡ ርስት ገንዘብ ፡ አድርጎ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ዘአፈቅር ፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተባለ ፡ ብለው ፡ ይናገራሉ ፡ እንጂ ፡ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ክርስቶስን ፡ ለያይተው ፡ በመለኮቱ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ በሰውነቱ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ነው ፡ አይሉም ። እንዲሀማ ፡ ከኾነ ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ ወዴት ፡ ይገኛል ። ምናልባት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ባባቱ ፡ ከንጉሥ ፤ በናቱ ፡ ከደሃ ፡ ቢወለድ ፡ ያው ፡ በጅ ክንድ ፡ ከስንዝር ፡ ቁመቱ ፡ የተወሰነው ፡ አካሉ ፡ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ ንግሥ ፡ ያስገብራል ፡ የደሃ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ ርስቱን ፡ ይዞ ፡ ይገብራል ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ በመለስ ፡ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ይገበርለት ፡ ከዚህ ፡ በመለስ ፡ የደሃ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ይገብር ፡ አይባልም ፡ ከንገሠም ፡ በኋላ ፡ ቢኾን ፡ በናቱ ፡ በኩል ፡ የወረደ ፡ ድኅነቱ ፡ መነገሩ ፡ ሳይቀር ፡ ንጉሥ ፡ እገሌ ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፡ ደኀ ፡ እገሌ ፡ አይባልም ። ክርስቶስም ፡ በመለኮቱ ፡ ከአብ ፡ በሰውነቱ ፡ ከእመቤታችን ፡ በመወለዱ ፡ አምላክ ፡ ወሰብእ ፡ ቢባልም ፡ ትስብእትንም ፡ መለኮትንም ፡ በሚያዋሕድ ፡ ስም ፡ አማኑኤል ፡ ክርስቶስ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ አምላክነቱ ፡ ባሕርን ፡ አስገበረ ፡ እንደ ፡ ሰውነቱ ፡ ገበረ ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡ መለኮትን ፡ ለብቻ ፡ ትስብእትን ፡ ለብቻ ፡ ያልተዋሐዱ ፡ አስመስሎ ፡ በሚያሳይ ፡ አነጋገር ፡ በመለኮቱ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ በሰውነቱ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አይናገሩም ። ማቴ ፡ ፲፬ ፡ ፳፪ ።

## ድ ራ ሲ ።

፷፱/ ይህም ፡ ማለት ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፤ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፷፱/ አምላክ ፡ ወሰብእ ፡ የሚባልበትን ፡ ምክንያት ፡ ለመግለጽ ፡ ያው ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የኾነ ፡ ክርስቶስ ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ከአብ ፡ እንደ ፡ መወለዱ ፡ አምላክ ፡ ድኅረ ፡ ዓለም ፡ ከእመቤታችን ፡ እንደ ፡ መወለዱ ፡ ሰብእ ፡ ይባላል ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ መለኮቱን ፡ ከትስብእቱ ፡ ለይተን ፡ አምላክ ፤ ትስብእቱን ፡ ከመለኮቱ ፡ ለይተን ፡ ሰብእ ፡ የምንል ፡ አይደለንም ።

## ምዕራፍ ፡ ፳ ።

ኢትዮጵያውያን ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ሊቃውንት ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሲከራከሩ ፡ የሚሰጡት ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ የሚያምኑት ፡ ትምህርት ።

## ድ ራ ሲ ።

፩/ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሌላ ፡ ቋንቋ ፡ የተተረጐመ ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ የሃይማኖቷን ፡ ትምህርቷ ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ ጠቅልሎና ፡ አደራጅቶ ፡ የሚናገር ፡ ከልጆቿ ፡ በገዛ ፡ ቋንቋ ፡ የተደረሰ ፡ መጽሐፍ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አላየንም ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፩/ የሃይማኖታችን ፡ መሠረት ፡ የኾኑት ፡ ወንጌልና ፡ ሌሎችም ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የቀደሙት ፡ በዕብራይስጥ ፡ በሮማይስጥ ፡ በጽርእ ፡ በሱርስጥ ፡ በሌሎችም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋዎች ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በግእዝ ፡ ወይም ፡ ባማርኛ ፡ አይደለምና ፡ ከሌላ ፡ ቋንቋ ፡ የተተረጐሙትን ፡ መጻሕፍት ፡ መፈለግ ፡ ግድ ፡ ይኾንብናል ፡ ስለዚህ ፡ የሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ጋዜጣ ፡ ጸሐፊ ፡ በቋንቋችን ፡ ከልባችን ፡ አንቅተን ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፈን ፡ አናውቅምና ፡ ይህ ፡ እውነተኛ ፡ ንግግር ፡ ነው ።

## ድ ራ ሲ ።

፪/ ስለዚህ ፡ እውነተኛውን ፡ እምነቷን ፡ ለመወሰንና ፡ ስለማናቸውም ፡ ትምርት ፡ ያላት ፡ አስተያየት ፡ በእርግጥ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ በጣም ፡ ያስቸግራል ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፱/ የኢትዮጵያን ፡ እውነተኛውን ፡ እምነቷንና ፡ ያላትን ፡ አስተያየት ፡ ለመረዳት ፡ ባህሎቿን ፡ ኹሉ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ማመዛዘንና ፡ መምህራኖቿን ፡ መጠየቅ ፡ በጣም ፡ ይጠቅማል ፡ ይህ ፡ ካልኾነ ፡ በልብ ፡ ምኞት ፡ ብቻ ፡ ሊደረስበት ፡ አይቻልም ።

ደ ራ ሲ ።

፲/ ስለኢትዮጵያውያን ፡ የሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ዛሬ ፡ የሚታወቀው ፡ ኹሉ ፡ አብዛኛው ፡ በየክፍሉ ፡ ከተተረጐሙ ፡ ከቅዱሳን ፡ አበው ፡ መጻሕፍት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰባኪዎችና ፡ ጐብኚዎች ፡ ከጻፍዋቸው ፡ የወሬ ፡ ጽሑፎች ፡ ግማሹም ፡ ከኢትዮጵያውያኖች ፡ የሥርዓተ ፡ አምልኮ ፡ መጻሕፍት ፡ ተወጣጥቶ ፡ የተገኘ ፡ ጥርቅም ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፲፩/ የኢትዮጵያ ፡ የሃይማኖት ፡ ባህል ፡ በየክፍሉ ፡ ከተተረጐሙ ፡ ከቅዱሳን ፡ አበው ፡ መጻሕፍት ፡ የተሰበሰበ ፡ መኾኑ ፡ የማይካድ ፡ ነው ። እነሆም ፡ ቅዱሳን ፡ አበው ፡ ከጌታ ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መንጭቶ ፡ በሐዋርያት ፡ ላይ ፡ የጐረፈውን ፡ የሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ሳይቋረጥ ፡ እንደ ፡ ቦይ ፡ እንደ ፡ መሽረብ ፡ ኾነው ፡ እስከ ፡ እኛ ፡ ያደረሱልን ፡ ፫፻፲፰ ፡ ሊቃውንትና ፡ እነዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ እነቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ሌሎችም ፡ በሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ያሉ ፡ ሊቃውንት ፡ ናቸው ።

ይህም ፡ የነርሱ ፡ ትምህርት ፡ ያው ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያስተማረውን ፡ ሐዋርያት ፡ ተከትለው ፡ ያስፋፉት ፡ ትምህርት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ልዩ ፡ አይደለም ።

ስለዚህ ፡ ከጌታ ፡ መንጭቶ ፡ በሐዋርያት ፡ ላይ ፡ መልቶ ፡ በኒህ ፡ በተጠቀሱት ፡ አባቶች ፡ ላይ ፡ እየጐረፈ ፡ እስከ ፡ እኛ ፡ የደረሰው ፡ ጥሩ ፡ ምንጭ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ጥርቅም ፡ አይባልም ።

የውጭ ፡ አገር ፡ ሰባኪዎችና ፡ ጐብኚዎች ፡ ከጻፍዋቸው ፡ የወሬ ፡ ጽሑፎች ፡ ያሉትን ፡ ግን ፡ አሁን ፡ እርስዎ ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍዎ ፡ ላይ ፡ አጠራቅመዋቸው ፡ አየን ፡ እንጂ ፡ እኛስ ፡ ስንኳን ፡ ለሃይማኖት ፡ ምስክር ፡ ልናደርጋቸው ፡ በፍጹም ፡ አናውቃቸውም ። ጥርቅም ፡ የሚባልም ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ እንጂ ፡ ከቅዱሳን ፡ አበው ፡ የተተረጐመው ፡ አይደለም ።

ደ ራ ሲ ።

፲፪/ እነህ ፡ ኹሉ ፡ ለውጥናችን ፡ የሚረዱ ፡ ናቸው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ሲጽፉም ፡ ሲከራከሩም ፡ የሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ መግለጫዎችን ፡ ከነዚሁ ፡ ትርጓሜዎችና ፡ ጽሑፎች ፡ አውጥተው ፡ ይወስዳሉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እነህ ፡ መግለጫዎች ፡ የሚሰጡት ፡ ፍችና ፡ ትክክለኛ ፡ ትርጉም ፡ እንዴት ፡ እድርጎ ፡ ይታወቃል ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፲፫/ ለዚህ ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ገለጽኩልዎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ግለጽልኝ ፡ ብሎ ፡ ከመለመን ፡ ጋራ ፡ መምህሮቻችንን ፡ ጠንክሮ ፡ ከመጠየቅ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መድኃኒት ፡ የለውም ።

ደ ራ ሲ ።

፲፬/ ከዚህም ፡ በላይ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሥርዓተ ፡ አምልኮ ፡ መጻሕፍቶቿ ፡ ውስጥ ፡ እንዳች ፡ የሃይማኖት ፡ ስሕተት ፡ እንደማይገኝባቸው ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ፡ እንግዲያ ፡ ከሮማ ፡ ጋራ ፡ አለመስማማቷ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ ብለዋል

መ ላ ሽ ።

፲፭/ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሃይማኖቷ ፡ ስሕተት ፡ የሌለባት ፡ መኾኗን ፡ እንኳን ፡ ተረዱልኝ ፡ እንጂ ፡ ከሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ፡ የማትስማማበትስ ፡ ምክንያት ፡ መልሱ ፡ ቅርብ ፡ ነው ። የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ከተጻፈው ፡ አልወጣም ፤ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በይመስለል ፡ በያስኛል ፡ በይኾናል ፡ ያመጣችውን ፡ ባህል ፡ አልቀበልም ፡ በማለቷ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ደ ራ ሲ ።

፲፮/ ደግሞ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰባኪዎችና ፡ ጐብኚዎች ፡ የጻፍዋቸው ፡ የወሬ ፡ ጽሑፎች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መሠረታዊ ፡ በኾኑ ፡ ነገሮች ፡ ላይ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ የማይስማሙትን ፡ አሳቦች ፡ ያቀርባሉ ፡

እንግዲያስ ፡ ዛሬ ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ የሃይማኖት ፡ እውነተኛውን ፡ ባህላቸውን ፡ ወደማወቅ ፡ የሚመራና ፡ ከተረጋገጠው ፡ ፍጻሜ ፡ ላይ ፡ የሚያደርስ ፡ መንገድ ፡ የትኛው ፡ መኾኑ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፩/ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰባኪዎችና ፡ ጐብኝዎች ፡ ከዕንጨት ፡ ለታሚ ፡ ከወነ ፡ ቀጂ ፡ ከማናቸውም ፡ ካገኙት ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ጠይቀው ፡ የሰሙትን ፡ ማናቸውንም ፡ ያልተጣራ ፡ ነገር ፡ ከመጻፍ ፡ በቀር ፡ መጻሕፍትን ፡ መርምረው ፡ መምህራንን ፡ ጠይቀው ፡ የጻፉ ፡ ስላልኾኑ ፡ ጽሑፋቸው ፡ ስምምነት ፡ ሊያገኝ ፡ አይችልም ። የኢትዮጵያውያንን ፡ እውነተኛ ፡ ባህል ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡ የሚመራ ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ገለጽኩልዎ ፡ ትምህርት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፪/ እነዚህን ፡ ሐተታዎች ፡ ለመፍታት ፡ ከውጭ ፡ ሀገር ፡ ከመጡ ፡ ከካቶሊክ ፡ ሰባክያን ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ባህሎች ፡ ያሏቸው ፡ ያገሩ ፡ ሊቃውንትና ፡ አድባራት ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲከራከሩ ፡ ወይም ፡ በጽሑፍ ፡ ሲመላለሱ ፡ የሚሉትን ፡ ጠንቅቆ ፡ በመከታተል ፡ ማጥናት ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፪/ ይህንን ፡ ተከታትሎ ፡ ቢያጠኑት ፡ እገሌ ፡ እገሌን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ እርሱም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፡ እያሉ ፡ ወሬ ፡ ለማጋጨት ፡ ብቻ ፡ ይጠቅም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ ለመረዳት ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ በቂ ፡ አይኾንም ፤ ለዚህ ፡ የሚረዳ ፡ ከላይ ፡ እንደገለጽኩት ፡ ጠንክሮ ፡ መማር ፡ ብቻ ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፫/ እነዚህን ፡ ክርክሮቻቸውን ፡ በጥንቃቄ ፡ በመመርመር ፡ ለቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ጥቅሶች ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ትርጉም ፡ እንደሚሰጥዋቸው ፡ በገር ፡ ለማወቅ ፡ እንችላለን ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፫/ ይኽ ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ በትምህርት ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ ሊደርሱበት ፡ አይችሉም ።

## ደ ራ ሲ ።

፬/ እላይ ፡ ባወሳንባቸው ፡ ተተርጉመው ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ በገቡት ፡ በቅዱሳን ፡ አበው ፡ መጻሕፍት ፡ ወይም ፡ በክፍላቸው ፡ ውስጥ ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ የሃይማኖት ፡ እውነተኛውን ፡ አሳብ ፡ አገኛለሁ ፡ ማለት ፡ ዘበት ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፬/ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ ባገር ፡ ለማወቅ ፡ ይቻላል ፡ ያሉትን ፡ ቃልዎን ፡ በመለወጥዎ ፡ ከመገረም ፡ በቀር ፡ ያሁኑ ፡ ንግግር ፡ እውነተኛ ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ ሌላ ፡ መልስ ፡ የለውም ።

## ደ ራ ሲ ።

፭/ ኋላም ፡ መጻሕፍቶቹን ፡ ያስተረጐሟቸው ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ናቸው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከላይ ፡ እንዳስረዳነው ፡ በትምህርት ፡ በኵል ፡ ማናቸውም ፡ ሥልጣን ፡ ስላልነበራቸው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አሳባቸውን ፤ በመከተል ፡ ይታዘዙላቸው ፡ አልነበሩም ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፭/ ያሁኑ ፡ አነጋገርዎ ፡ ከንቱ ፡ ውዳሴን ፡ በማቀማመስ ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍትና ፡ ከእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ሊያለያዩ ፡ የከጀሉ ፡ መኾንዎን ፡ በግልጽ ፡ ያሳያል ። ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ በከማቴ ፡ ብርሃን ፡ ሰላማ ፡ መተርጐማቸው ፡ እርግጥ ፡ ነው ፤ በሌሎችም ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ጊዜ ፡ የተተረጐሙ ፡ ሌሎች ፡ መጻሕፍትም ፡ አይታጡም ።

በትምህርት ፡ በኵል ፡ ሥልጣን ፡ አልነበራቸውም ፡ አይታዘዙላቸውም ፡ ነበረ ፡ ለሚሉት ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የእስክንድርያን ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ አባቶቻችን ፡ ብለው ፡ አክብረው ፡ ትምህርታቸውንም ፡ ተቀብለው ፡ ከመኖር ፡ በቀር ፡ እንቀበላችሁም ፡ ማለታቸውን ፡ አላውቅም ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፩/ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በእስክንድርያ ፡ እየተመራች ፡ መኖሯ ፡ ምንም ፡ ቢታመን ፡ እምነቷንና ፡ ትምህርቷን ፡ ትከታተል ፡ ነበረ ፡ ወይም ፡ አሁን ፡ ትከተለዋለች ፡ ማለት ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ በፍጹም ፡ አያስደፍርም ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

እስክንድርያና ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሺ፮፻ ፡ ዘመን ፡ በላይ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ተባብረው ፡ እናትና ፡ ልጅ ፡ ኾነው ፡ መኖራቸው ፡ አይካድም ። እንደዚኹሙም ፡ አሁን ፡ ባለንበት ፡ ዘመን ፡ በሃይማኖት ፡ በኩል ፡ ሳይኾን ፡ ባስተዳደር ፡ ረገድ፡ኢትዮጵያ፡ከልጆቿ ጳጳስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ልሹም ፡ ብትል ፡ እስክንድርያ ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ ግብጻዊ ፡ ጳጳስ ፡ ልላክ ፡ በመባባል ፡ መነጋገራቸው ፡ አልቀረም ፡ ነበረ ። ይህም ፡ በስምምነት ፡ ተፈጽሞ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከልጆቿ ፡ ጳጳሳት ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ፓትርያርክ ፡ አሹማ ፡ ኹለቱም ፡ አገሮች ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ በሃይማኖታቸው ፡ ጸንተው ፡ በሰላም ፡ ተቀምጠው ፡ ሳለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የእስክንድርያን ፡ ትምርቷንና ፡ እምነቷን ፡ ትከተለዋለች ፡ ለማለት ፤ አያስደፍርም ፡ ብሎ ፡ ሰብቅ ፡ ቀመስ ፡ ነገር ፡ መጻፍ ፡ (ለእመ ፡ ረከበ ፡ ንሰቲተ ፡ ሙባእ ፡ ውእቱ ፡ ያርህቦ ፡ ለመካን ፡ ወይሬስዮ ፡ አንቀጸ ፡ ገመል ፡ ስፉሕ ) ።

ትንሽ ፡ መግቢያ ፡ ያገኘ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስፋፍቶ ፡ ገመል ፡ የሚያስገባ ፡ ያደርገዋል ፡ እንደተባለው ፡ ባስተዳደር ፡ ጉዳይ ፡ የተነጋገሩትን ፡ ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ በመካከላቸው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መለያየትን ፡ ለመፍጠር ፡ የታቀደ ፡ ዘዴ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ንግግር ፡ አይደለም ።

በመቸውም ፡ ጊዜ ፡ ቢኾን ፡ እስክንድርያና ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሃይማኖት ፡ ረገድ ፡ የሚለያዩበት ፡ ምክንያት ፡ የለም ። በዚህ ፡ ተነሥቶ ፡ በነበረው ፡ ባስተዳደር ፡ ምክንያት ፡ መለያየት ፡ ቢፈጠር ፡ እንኳን ፡ ኖሮ ፡ ኹሉም ፡ በያሉበት ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ በማለት ፡ ጸንተው ፡ ይኖሩ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚያፈገፍግ ፡ አልነበረም ።

## ፩ኛ ፡ ክፍል ።

### ፩/ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመጡ ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ የካቶሊክ ፡ ምዕራባውያን ፡ ሰባኪዎች

## ደ ራ ሲ ።

፲፪/ ከ፲፮ኛው ፡ ፻ ፡ ዘመን ፡ በፊት ፡ ያለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክርስትና ፡ ታሪክ ፡ በጨለማ ፡ ጉም ፡ እንደ ፡ ተሸፈነ ፡ ነው ፡ ኢትዮጵያ ፡ በእስላሞች ፡ ተከባ ፡ ከሌሎች ፡ ክርስቲያኖች ፡ ተለይታ ፡ ከቀረችበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እላይ ፡ እስካልነው ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ስለክርስትናዋ ፡ ኹኔታ ፡ በግልጥ ፡ የሚናገር ፡ ጽሑፍ ፡ በሀገሩ ፡ ውስጥ ፡ ምንም ፡ አይገኝም ። ስለዚህ ፡ የዚሁ ፡ ዘመናት ፡ ታሪክ ፡ ቀጥተኞች ፡ ባልኾኑ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ጽሑፎች ፡ መሠረት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በይኾናል ፡ የሚታመነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፪/ ኢትዮጵያ ፡ በ፲፭፻፳፯ ፡ ወይም ፡ ፴ ፡ ዓ/ም ፡ ጀምራ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰባኪዎች ፡ መጥተው ፡ እስከበጠበጧት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ወንጌልን ፡ በከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ ሰላማ ፡ ተቀብላ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ በማለት ፡ ጸንታ ፡ የኖረች ፡ መኾኗ ፡ ርስዎም ፡ የማይክዱት ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ በትክክል ፡ ያወቀው ፡ እውነተኛው ፡ ታሪክ ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ በእስላሞች ፡ ተከባ ፡ ከሌሎች ፡ ክርስቲያኖች ፡ ተለይታ ፡ በቆየችበትም ፡ ጊዜ ፡ በክርስትናዋ ፡ ጸንታ ፡ የኖረች ፡ ሃይማኖቷን ፡ በማናቸውም ፡ ምክንያት ፡ ያለወጠች ፡ መኾኗ ፡ በእርግጥ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

እንዳሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የሃይማኖት ፡ ብጥብጥ ፡ ቢኖር ፡ ኖሮ ፡ ይጻፍ ፡ ነበረ ። አለመጻፉ ፡ በኒህ ፡ ዘመኖች ፡ ውስጥ ፡ የሃይማኖት ፡ ብጥብጥ ፡ ሳይኖር ፡ በሰላም ፡ የኖረች ፡ አገር ፡ መኾኗን ፡ ያስረዳል ። እንግዲህ ፡ የነገሩ ፡ ኹኔታ ፡ እንዲህ ፡ ኾኖ ፡ ሲገኝ ፡ ቀጥተኞች ፡ ባልኾኑ ፡ በይኾናል ፡ ብቻ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የጻፍዋቸውን ፡ ጽሑፎች ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ በጨለማ ፡ ጉም ፡ እንደተሸፈነ ፡ ነው ፤ ብሎ ፡ መጻፍ ፡ አግባብ ፡ አይደለም ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፬/ የሃይማኖቱን ፡ ታሪክ ፡ ለማወቅ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ከተደረገው ፡ ምርምር ፡ ኹሉ ፡ ከ፲፬ ፻ኛ ፡ ዘመን ፡ በፊት ፡ ለእስላሞችና ፡ ለግብጽ ፡ መናፍቃኖች ፡ ከመቃወማቸውና ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ከመታገላቸው ፡ በቀር ፡ ኢትዮጵያውያኖቹ ፡ በሃይማኖት ፡ ነገር ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ወይም ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ስምምነትን ፡ አጥተዋል ፡ ወይም ፡ ተጣልተዋል ፡ የሚል ፡ ምስክር ፡ ምንም ፡ አይታወቅም ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፬/ ከግብጽ ፡ መናፍቃኖች ፡ ጋራ ፡ ሲታገሉ ፡ ያሉት ፡ በግብጽ ፡ ጳጳሳትና ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ መካከል ፡ ስምምነት ፡ አልነበረም ፡ እያሉ ፡ የሚያወሩትን ፡ መሠረተ ፡ ቢስ ፡ ወሬ ፡ እውነት ፡ ለማስመሰል ፡ የተናገሩት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ።

በሌላው ፡ አነጋገርዎ ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያ ፡ በሃይማኖት ፡ ጸንታ ፡ በስምምነት ፡ የኖረች ፡ መኾኗን ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የተረዱት ፡ሲኾኑ ፡ በጨለማ ፡ ጉም ፡ እንደተሸፈነ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መጻፍዎ ፡ በጭቅጭቅ ፡ መኖር ፡ ብርሃን ፡ በስምምነት ፡ በሰላም ፡ መኖር ፡ ጨለማ ፡ መስሎ ፡ ታየዎ ፡ ይኾን ፡ በእውነቱ ፡ ይገርማል ። የኾነ ፡ ኾኖ ፡ አሁን ፡ እርስዎ ፡ እንደ ፡ ተናገሩት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰባኪዎች ፡ ካቶሊካውያን ፡ መጥተው ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ በሚል ፡ ንጹሕ ፡ ዘርዕ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ላይ ፡ ክልኤ ፡ ባሕርይ ፡ የሚል ፡ እንክርዳድ ፡ ዘርተው ፡ የእርስ ፡ በርስ ፡ መጠላላትን ፡ አብቅለው ፡ ደም ፡ እስኪያፋስሷቸው ፡ ድረስ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በስምምነት ፡ ኗሪዎች ፡ እንደነበሩ ፡ እኔም ፡ አረጋግጥልዎታለሁ ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፭/ ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ የጻፉት ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ መጀመሪያ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የመጡ ፡ የካቶሊክ ፡ ሰባኪዎች ፡ ፍራንቸስካውያን ፡ ናቸው ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ተነሥተው ፡ የነርሱን ፡ አኳኋን ፡ የሚዘረዝር ፡ ብቻ ፡ ነው ።

## መ ላ ሽ ።

፲፭/ እኛ ፡ በጠቅላላው ፡ የካቶሊክን ፡ ሰባኪዎች ፡ ኢትዮጵያ ፡ አልተቀበለቻቸውም ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አልመጡም ፡ አንልም ። እገሌ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ተልኳል ፡ እገሌ ፤ ተከትሏል ፡ እገሌ ፡ የብዙ ፡ ሰው ፡ ደም ፡ አፋሰሰ ፤ እገሌ ፡ ምንም ፡ ሳይሠራ ፡ ተመለሰ ፡ እያሉ ፡ ከመላክተኞቹ ፡ የተላከበትን ፡ ተግባር ፡ በሚገባ ፡ የፈጸመ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወይም ፡ ምንም ፡ ሳይሠራ ፡ የተመለሰ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ መቈጣጠር ፡ የላኪቻቸው ፡ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የግል ፡ ተግባሯ ፡ ነው ።

ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ዋናው ፡ ዓላማዋ ፡ ማንኛውንም ፡ የካቶሊክ ፡ ሰባኪ ፡ ጠንክራ ፡ ከመከላከል በቀር ፡ ያልተቀበለቻቸው ፡ መኾኑን ፡ ማስረዳት ፡ ብቻ ፡ ስለኾነ ፡ ይህን ፡ ጽሑፍ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ምንም ፡ ዋጋ ፡ እንደሌለው ፡ አድርገን ፡ አልፈነዋል ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፮/ ወደ ፡ መጨረሻው ፡ በሚገኘው ፡ መሥመር ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክርስትና ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ቤተ ፡ ክህነቱና ፡ ሕዝቡ ፡ ሃይማኖቱን ፡ በጥሩ ፡ ለመጠበቅ ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ ጠንክሮ ፡ ቢታገል ፡ የድንቁርናና ፡ የጥንቆላ ፡ ጭማሪ ፡ ተቀላቀለበት ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፮/ ባለፈው ፡ ንግግርዎ ፡ በገጽ ፡ ፵፬ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ ከጥንት ፡ጀምሮ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ የመንግሥት ፡ ከፍተኛ ፡ ባለሥልጣን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ ለቤተ ፡ ክህነቱ ፡ ባለሥልጣን ፡ መኾኑን ፡ አረጋግጠው ፡ ጽፈዋል ።

ባሁኑ ፡ አነጋገርዎም ፡ ቤተ ፡ ክህነቱና ፡ ሕዝቡ ፡ ሃይማኖቱን ፡ ለመጠበቅ ፡ ጠንክሮ ፡ ይታገል፡ ነበረ ፡ ሲሉ ፡ ንጉሡም ፡ ከነሠራዊቱ ፡ በዚህ ፡ ትግል ፡ ውስጥ ፡ መግባቱ ፡ ግድ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ ቤተ ፡ ክህነቱም ፡ ሕዝቡም ፡ ሃይማኖቱን ፡ በጥሩ ፡ ለመጠበቅ ፡ መታገሉን ፡ ካመኑበት ፡ ድንቁርናና ፡ ጥንቆላ ፡ ተጨማሪ ፡ ኾኖ ፡ የተቀላቀለ ፡ በማን ፡ ላይ ፡

ነው ፡ ከኒህ ፡ ከፓቱ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከቤተ ፡ ክህነት ፡ ከሕዝቡ ፡ የተለየ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ወገን ፡ አለና ፡ ተቀላቀለ ፡ ይላሉ ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፯/ አሁንም ፡ ቢኾን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለይቶ ፡ ይዘዋት ፡ ያለ ፡ ከሌሎች ፡ ይልቅ ፡ ይኸው ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ የገባው ፡ አበላሽ ፡ የኾነው ፡ ጭማሪ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፯/ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገቡ ፡ የሮማ ፡ ካቶሊክ ፡ ሰባኪዎች ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ የገባ ፡ እንደሌለ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ እኒያው ፡ የሮማ ፡ ሰባኪዎች ፡ ጨመሩት ፡ ይሉ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ማን ፡ ጨመረው ፡ ይላሉ ።

ይህነንም ፡ እርስዎ ፡ በተናገሩት ፡ መለስኩልዎ ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ አበላሽ ፡ የኾነ ፡ ጭማሪ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አይገባኝም ።

በውነቱ ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ሮማንስ ፡ ለያይቶ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ዘሠረጸ ፡ እምወልድ ፤ ክርስቶስን ፡ ክልኤ ፡ ባሕርይ ፡ ብላ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ስብከት ፡ ከመሰበኳም ፡ በላይ ፡ ለሮማ ፡ መንግሥት ፡ የፖለቲካ ፡ መሣሪያ ፡ ኾና ፡ በየጊዜው ፡ የምታስፈስሰው ፡ ደም ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፰/ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ክርስትና ፡ ተቀላቅሎ ፡ የሚታየው ፡ የአይሁድነት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ የአረመኔነትና ፡ የእስልምና ፡ ባህልና ፡ ልማድ ፡ የዚሁ ፡ የምንናገርበት ፡ ዘመን ፡ ገቢ ፡ ነው ፡ እኒኸውም ፡ ከአረመኔዎችና ፡ ከእስላሞች ፡ ጋራ ፡ መገናኘት ፡ ካፈራቸው ፡ መጥፎ ፡ ፍሬዎች ፡ ብዙ ፡ ሴቶችን ፡ ማግባት ፡ መፍታት ፡ እንዲሁም ፡ በኢትዮጵያውያኖቹ ፡ መካከል ፡ ሥልጥነው ፡ የሚገኙት ፡ ሌሎች ፡ ብዙ ፡ የጥንቆላ ፡ ልምዶች ፡ ናቸው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፰/ የአይሁድነት ፡ ሥራ ፡ ለሚሉት ፤ ኢትዮጵያ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢመጻእኩ ፡ እሥዐሮሙ ፡ ለኦሪት ፡ ወለነቢያት ፡ ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ ከመ ፡ እፈጽሞሙ ፡ ብሎ ፡ ካጸናቸው ፡ ትእዛዛት ፡ በቀር ፡ ሕግ ፡ አድርጋ ፡ የያዘችው ፡ የአይሁድ ፡ ልማድ ፡ የለም ፡ ሐሰት ፡ ነው ።

የአረመኔነት ፡ ሥራ ፡ ለሚሉት ፡ ለአረመኔነት ፡ ምንጩ ፡ መሠረቱ ፡ ዞሮ ፡ መግቢያው ፡ ምዕላዱ ፡ ሮማ ፡ ናት ። ይህነንም ፡ ለመረዳት ፡ የቀድሞዎችን ፡ የኔሮንን ፤ የቅርቦችን ፡ የነሙሶሊንን ፤ የነግራዝያኒን ፤ ሰውን ፡ ካውሬ ፡ ጋራ ፡ እያታገሉ ፡ ትያትር ፡ የሚጫወቱትን ፤ በሰው ፡ ላይ ፡ መርዝ ፡ እየረጩ፡እሳት ፡ የሚያዘንሙትን ፡ የሚገዙትን ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ዕንጨት ፡ በፋስ ፡ የሚፈልጡትን ፡ የነርሱን ፡ ታሪክ ፡ ይመልከቱ ።

ለዚህም ፡ የአረመኔነት ፡ ሥራ ፡ ፈጻሚዎች ፡ የሮማ ፡ ነገሥታት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾኑ ፡ ጳጳሳቱም ፡ ጭምር ፡ ለመኾናቸው ፡ ከሮማ ፡ ጳጳሳት ፡ አንዱ ፡ በአረመኔነት ፡ ጠባይ ፡ የክርስቲያኖችን ፡ ደም ፡ ለማፍሰስ ፡ የሚወጣውን ፡ የጦር ፡ ሠራዊትና ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ባርከው ፡ መርቀው ፡ በማስናበታቸው ፡ ታውቋል ።

ይህ ፡ ግፍ ፡ የሚሠራበት ፡ ወገን ፡ ተቆርቋሪ ፡ ኾኖ ፡ ኢትዮጵያን ፡ አረመኔ ፡ ብሎ ፡ መስደብ ፡ አዙሮ ፡ አለማየት ፡ ይሉኝ ፡ አለማለት ፡ ነው ።

የእስልምና ፡ ባህል ፡ ስለሚሉት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ልምድ ፡ አድርገው ፡ የያዙት ፡ የእስልምና ፡ ባህል ፡ ምንድን ፡ ነው ፤ ገልጸው ፡ ጽፈውልኝ ፡ ቢኾን ፡ መልሱን ፡ እጽፍልዎ ፡ ነበረ ። ስላልጻፉልኝ፡የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የእስልምናን ፡ ባህል ፡ አልያዘችም ፡ ውሸት ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የምጽፍልዎ ፡ የለኝም ።

ብዙ ፡ ሴቶችን ፡ ማግባት ፡ መፍታት ፡ ስለሚሉትም ፡ አንዳንድ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የኾኑ ፡ ሰዎች ፡ ሕግ ፡ መተላለፍ ፡ ይሠሩት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግ ፡ ኾኖ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አውቃው ፡ የሚሠራበት ፡ ሕግ ፡ አይደለም ። ይህነንም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በሌሎችም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሚኖሩ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ የኾኑ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ እንደሚያደርጉት ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ለምሳሌ ፡ ብዙ ፡ የሮማ ፡ ሰዎች ፡ ሌሎችም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የኾኑ ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ሀገራችን ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሴቶች ፡ ይልቁንም ፡ ከእስላም ፡ ሴቶች ፡ የጋብቻን ፡ ሕግ ፡ በመተላለፍ ፡ ደቅለው ፡ ይገኛሉ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የየክፍላቸው ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የጋብቻ ፡ ሕግ ፡ የላቸውም ፡ ተብለው ፡ ይወቀሳሉን ፤ አይወቀሱም ። እንግዲያስ ፡ በኢትዮጵያም ፡ በዚህ ፡ ሥራ ፡ ያው ፡ ሕግ ፡ ተላላፊው ፡ ራሱ ፡ ይቀጣበታል ፡ ይወቀስበታል ፡ እንጂ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግ ። የላትም ፡ ተብላ ፡ ልትወቀስበት ፡ አይገባም ።

የጥንቆላ ፡ ልምዶች ፡ ስለሚሉትም ፡ የጥንቆላ ፡ ሥራ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕግ ፡ የተነቀፈ ፡ የተጠላ ፡ ነው ፡ እንዲያውም ፡ የጥንቆላ ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ የተገኘ ፡ በወንጀል ፡ ተከሶ ፡ ሲረታ ፡ ግርፋትና ፡ እስራት ፡ ወይም ፡ ስደት ፡ ይፈረድበት ፡ ነበረ ። እስከ ፡ ሞትም ፡ ድረስ ፡ የተፈረደባቸው ፡ ይገኛሉ ። ዛሬም ፡ አዲሱ ፡ የተሻሻለው ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ በሚያዝዘው ፡ መሠረት ፡ በጽኑ ፡ እስራት ፡ ይቀጣሉ ፡ እንጂ ፡ ጥንቆላ ፡ ሕግ ፡ ኹኖ ፡ አይሠራበትም ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፬/ ስለዚህ ፡ ሰባክያኖቹ ፡ የጊዜውን ፡ ግድነት ፡ በመመልከት ፡ ስለሃይማኖት ፡ የመራቀቅና ፡ የመከራከርን ፡ መንገድ ፡ ትተው ፡ ደክሞ ፡ የነበረውን ፡ የክርስትና ፡ መንፈስ ፡ ለማነቃቃት ፡ ተጣጥረው ፡ ይኾናሉ ፡ ብለው ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ትችት ፡ አሳይተዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፬/ የክርስትና ፡ መንፈስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ማንም ፡ የዘራው ፡ ሳይኖር ፡ በሕገ ፡ ልቡና ፡ በቅሎ ፡ በየለቱ ፡ ሲያብብ ፡ ሲያፈራ ፡ የሚኖር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሙቸም ፡ ቢኾን ፡ የደከመበትና ፡ የቀዘቀዘበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ። ስንኳን ፡ ሮማውያን ፡ ግብጻውያንም ፡ ቢኾኑ ፡ እርሷው ፡ አውቃ ፡ የማያጠምቅ ፡ የማያቈርብ ፡ መምህር ፡ ሹሙልኝ ፡ ብትለን ፡ ሾመን ፡ ላክንላት ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ እኛ ፡ መክረን ፡ አስተምረን ፡ ከእርምና ፡ ወደ ፡ ክርስትና ፡ ወይም ፡ ከሕገ ፡ ኦሪት ፡ ወደ ፡ ሕገ ፡ ጥምቀት ፡ መለስናት ፡ ብለው ፡ ሊመኩባት ፡ አይችሉም ። የካቶሊክ ፡ ሰባኪዎችም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በመጡበት ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፡ ከቤተ ፡ ክህነቱ ፡ አያያዝ ፡ አልፈው ፡ በመንግሥቱ ፡ ፖለቲካ ፡ እየገቡ ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ እያለያዩ ፡ ደም ፡ ሲያፋስሱ ፡ ከመኖር ፡ በቀር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ያደረጉላት ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ አንድም ፡ አይገኝም ። ሮማ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ በጎ ፡ ትውልላታለች ፡ መልካም ፡ ትሠራላታለች ፡ ብሎ ፡ ከማሰብ ፡ ቀበሮ ፡ ወይም ፡ ተኵላ ፡ ለበግ ፡ መልካም ፡ ትሠራለች ፡ ብሎ ፡ ማሰብ ፡ ይቀላል ። ይህን ፡ በመተቸትስ ፡ ፈንታ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱም ፡ ቤተ ፡ ክህነቱም ፡ ሕዝቡም ፡ አንድ ፡ ኾኖባቸው ፡ መግቢያ ፡ ቢያጡ ፡ ሕዝቡን ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ አለያይተው ፡ አሁን ፡ በኛ ፡ ዘመን ፡ የፈጸሙትን ፡ ያጥቂነት ፡ ተግባር ፡ ለመፈጸም ፡ መግቢያ ፡ የሚያገኙበትን ፡ ዘዴ ፡ ሲያጠኑ ፡ የቆዩ ፡ ይመስላል ፡ ብለው ፡ ተችተው ፡ ቢኾን ፡ ትችትዎ ፡ እውነትን ፡ የተመረኰዘ ፡ ኾኖ ፡ በተገኘ ፡ ነበር ።

## ክ ፍ ል ፪ ።

## ከውጭ ፡ አገር ፡ ሰባኪዎች ፡ ጋራ ፡ የተደረጉ ፡ የመጀመሪያ ፡ ክርክሮች ።

## ደ ራ ሲ ።

፩/ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የባህል ፡ መለያየትና ፡ የሃይማኖት ፡ ክርክር ፡ የተነሣ ፡ በ፲፬፻ ፡ ዘርዐ ፡ ያዕቆብ ፡ መንግሥት ፡ ነው ፡ የተከራከሩ ፡ ከማን ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ምክንያቱም ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አይታወቅም ።

ነገር ፡ ግን ፡ አባ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የደረሰው ፡ መጽሐፍ ፡ ስለምሥጢረ ፡ ሥላሴና ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ የሚናገር ፡ ስለኾነ ፡ ስለርሱ ፡ ሳይኾን ፡ አይቀርም ።

መላክተኞቹ ፡ የሰበኩትን ፡ ትምርት ፡ ለመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ጠንክረው ፡ የተቃወሙት ፡ አይመስልም ። መላክተኞች ፡ ይሰብኩት ፡ የነበረውና ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ያምኑት ፡ የነበረው ፡ ትምርት ፡ ብዙ ፡ ይመሳሰል ፡ ኖሯል ፡ ለማለት ፡ እንችላለን ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፩/ ይህን ፡ ማለት ፡ የሚገባ ፡ ይመሳሰሉ ፡ ኖሯል ፡ ለማለት ፡ የበቁባቸውን ፡ ንግግሮች ፡ ጠቅሰ ፡ እርስዎ ፡ ተረዳሁ ፡ የሚሉትን ፡ ያህል ፡ ሰሚና ፡ ተመልካችም ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ይመስላል ፡ እስኪል ፡

ድረስ ፣ አስረድቶ ፣ ነበረ ፣ እንጂ ፣ እንዲያው ፣ ዝም ፣ ብሎ ፣ ይኽናል ፣ ይመስላል ፣ ብሎ ፣ መናገር ፣ ባስተዋይ ፣ ዘንድ ፣ ቁም ፣ ነገር ፣ ኾኖ ፣ አይገኝም ፣ ስለዚህ ፣ ዋጋ ፣ እንደሌለው ፣ ቈጥረን ፣ አልፈነዋል ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፩/ ኢትዮጵያውያን ፣ ከካቶሊክ ፣ ሰባኪዎች ፣ ጋራ ፣ በተገናኙ ፣ ጊዜ ፣ የእምነታቸውን ፣ ብዙ ፣ እናቅጽ ፣ እንደ ፣ ገና ፣ መመርመርና ፣ በበለጠ ፣ አጥንተው ፣ መወሰን ፣ ግድ ፣ ኾነባቸው ፣ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፩/ ኢትዮጵያውያን ፣ ከካቶሊካውያን ፣ ጋራ ፣ በተገናኙ ፣ ጊዜ፣ትምህርታቸው ፣ ተመሳሳይ ፣ ኾኖ ፣ ካገኙት ፣ እንደ ፣ ገና ፣ ወደ ፣ መመርመርና ፣ ወደ ፣ መወሰን ፣ ምን ፣ ወሰዳቸው ፣ ዝም ፣ ብለው ፣ አይቀበሉትም ፣ ኖሯልን ። በላይኛው ፣ መሥመር ፣ የተቈጸት ፣ ትችት ፣ ዋጋ ፣ የሌለው ፣ መኾኑ ፣ በዚህ ፣ ይታወቃል ።

እውነተኛውስ ፣ ነገር ፣ ይህ ፣ አሁን ፣ የተናገሩት ፣ ነው ። አርበኛ ፣ ሰላም ፣ በኾነበት ፣ ጊዜ ፣ ጋሻ ፣ ጦሩን ፣ ሰቅሎ ፣ ወደ ፣ ዕለት ፣ ተግባሩ ፣ ይሠማራል ፤ ጠላት ፣ በተነሣበት ፣ ጊዜ ፣ ከተሰቀለበት ፣ አውርዶ ፣ ጦሩን ፣ ይወለውላል ፣ ጋሻውን ፣ ይሰነግላል ፣ ይህ ፣ የአርበኞች ፣ ሕግ ፣ ነውና ፣ ኢትዮጵያውያንም ፣ ጠላት ፣ በጠፋበት ፣ ጊዜ ፣ በዕረፍት ፣ ኖረው ፣ የሃይማኖት ፣ ክርክር ፣ በተነሣባቸው ፣ ጊዜ ፣ መልስ ፣ ለመስጠት ፣ መጽሐፍ ፣ ለመመልከት ፣ ታጥቀው ፣ ቢነሡ ፣ የሚያስነቅፋቸው ፣ አይደለም ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፪/ በዚህ ፣ ሥጋት ፣ ምክንያት ፣ የእስክንድርያ ፣ ሊቃነ ፣ ጳጳሳት ፣ የካቶሊክ ፣ መልእክተኞች ፣ ከሚሰብኩት ፣ ትምህርት ፣ ለኢትዮጵያውያን ፣ መጠበቂያ ፣ ይኾናቸው ፣ ዘንድ ፣ በኬልቄዶን ፣ ጉባኤ ፣ በልዮን ፣ ጳጳስና ፣ በካቶሊክ ፣ ትምርት ፣ ላይ ፣ ያልዋለውንና ፣ ያልተባለውን ፣ ውሸት ፣ ፈጥረው ፣ የመሉባቸው ፣ ያንድ ፣ ባሕርይን ፣ ባህል ፣ የሚያስተምሩ ፣ መጻሕፍት ፣ በፍጥነት ፣ ወደ ፣ ግእዝ ፣ አስተርጕመው ፣ በኹሉ ፣ ዘንድ ፣ እንዲስፋፉ ፣ አደረጉ ፣ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፪/ ያንድ ፣ ባሕርይ ፣ ባህል ፣ የሚናገሩ ፣ መላው ፣ ቅዱሳት ፣ መጻሕፍት ፣ ናቸው ፣ እንጂ ፣ በከፊል ፣ አይደለም ። እኒኽውም ፣ እያንዳንዳቸው ፣ ወደ ፣ ኢትዮጵያ ፣ የገቡበት ፣ ጊዜ ፣ የታወቀ ፣ ነው ። ይህ ፣ የሚናገሩት ፣ እውነት ፣ ከኾነ ፣ በዚያን ፣ ጊዜ ፣ በፍጥነት ፣ ወደ ፣ ግእዝ ፣ ተተርጕመው ፣ የተላኩት ፣ መጻሕፍት ፣ የትኞዎቹ ፣ ናቸው ፣ እስኪ ፣ ያስረዱን ።

ደግሞስ ፣ በኬልቄዶን ፣ ጉባኤ ፣ ያልዋለውን ፣ በሐሰት ፣ ጽፈው ፣ እንዲስፋፉ ፣ ያደረጉት ፣ የትኛውን ፣ ነው ።

የእስክንድርያ ፣ ሊቃነ ፣ ጳጳሳት ፣ ስለ ፣ ኬልቄዶን ፣ ጉባኤ ፣ ውሳኔ ፣ የነገሩን ፣ መለካውያን ፣ በሮቱ ፣ ዐበይት ፣ ጉባኤያት ፣ የተወሰነውን ፣ ለውጠው ፣ አንድ ፣ አካል ፣ ኹለት ፣ ባሕርይ ፣ በማለት ፣ የንስጥሮስን ፣ ግማሽ ፣ ክህደት ፣ አጸደቁ ፣ ማለትን ፣ ነው ። ይህንም ፣ የሮማ ፣ ቤተ ፣ ክርስቲያን ፣ የምትክደው ፣ አይመስለኝም ። ይህ ፣ ሐሰት ፣ ነው ፣ ጉባኤው ፣ እንዲህ ፣ ብሎ ፣ አልወሰነም ፣ የሚሉ ፣ ከኾነ ፣ ዛሬም ፣ ቢኾን ፣ ልንስማማ ፣ እንችላለን ። ኹላችንም ፣ በየበኩላችን ፣ ልዮን ፣ የንስጥሮስ ፣ ተከታይ ፣ ነው ፣ ዲዮስቆሮስ ፣ የአውጣኪ ፣ ሌረኛ ፣ ነው ፣ የምንለው ፣ ወሬ ፣ ዋጋ ፣ የለውም ።

# ክፍል ፣ ፫ ።

## በ፲፮ኛና ፣ በ፲፯ኛ ፻ ፣ ዘመን ፣ የተደረጉ ፣ ክርክሮች ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፫/ በዚህ ፣ ዘመን ፣ ቅዱስ ፣ ፍራንቸስኮስንና ፣ ቅዱስ ፣ ዶመኒኮስ ፣ በ፲፭፻፶፬ ፣ ዓ/ም ፣ ግድም ፣ ኢየሱሳውያን ፣ መልክተኞች ፣ ተከተሏቸው ፣ የዚህም ፣ ታሪክ ፣ ቤካሪ ፣ በተባለ ፣ መጽሐፍ ፣ ይገኛል ፣ ካሉ ፣ በኋላ ፣ ወደ ፣ ፍሬ ፣ ነገሩ ፣ ገባ ፣ ሲሉ ፣ ያለመስማማታቸው ፣ ዋና ፣ ምክንያት ፣ ኢትዮጵያውያኖቹ ፣ በኬልቄዶን ፣ የዋለውን ፣ እስከዚያ ፣ ጊዜ ፣ ድረስ ፣ ደኅና ፣ አድርገው ፣ ሳያውቁ ፣ ቆይተው ፣ ከኬልቄዶን ፣ ጉባኤ ፣ በፊት ፣ ይነገርበት ፣ የነበረውን ፣ የቅዱስ ፣ ቄርሎስን ፣ አነጋገር ፣ ገና ፣ ይዘው ፣ ስለ ነበረ ፣ ነው ። ስለዚህም ፣ ከካቶሊካውያን ፣ ሰባኪዎች ፣ ጋራ ፣ መጀመሪያ ፣ በተገናኙና ፣ የኬልቄዶኑን ፣ አዲስ ፣ አነጋገር ፣ ሲያገቡ ፣ በሰሟቸው ፣ ጊዜ ፣ ያሰናከሉባቸው ፣ ነበረ ፣ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፫/ በዚህ ፡ አነጋገርዎ ፡ የቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ አነጋገር ፡ ከጥንት ፡ ከሐዋርያት ፡ ከ፫፻ ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣ ፡ መኾኑን ፡ የኬልቄዶኑ ፡ አነጋገር ፡ አዲስ ፡ ውሳኔ ፡ መኾኑን ፤ ኢትዮጵያም ፡ በቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ባህል ፡ የጸናች ፡ መኾኗን ፡ አረጋግጠው ፡ ተናግረዋል ።

ኢትዮጵያ ፡ በምንም ፡ ዐይነት ፡ እንዳልተሳሳተች ፡ ይህ ፡ በቂ ፡ መረጃ ፡ ነውና ፡ በዚህ ፡ አነጋገርዎ ፡ በጣም ፡ ትደሰትበታለች ።

የኬልቄዶኑን ፡ አነጋገርም ፡ ያሰናከሉባቸው ፡ የነበረ ፡ ይህ ፡ ኪሐዋርያት፡ከ፫፻፡፪፡ትምህርት፡ ውጭ ፡ በመኾኑ ፡ ነው ። አሁንም ፡ ቢኾን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሐዋርያት ፡ ውሳኔ ፡ መውጣትን ፡ የማትፈቅድ ፡ ስለኾነች ፡ የኬልቄዶንን ፡ ውሳኔ ፡ በመቃወም ፡ ላይ ፡ ናት ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፬/ በንጉሥ ፡ ዘደንግል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ ከፓድሬ ፡ ፓየዝ ፡ ጋራ ፡ የተደረገ ፡ ንግግር ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ሲናገሩ ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ መነኩሴ ፡ ለፓድሬ ፡ ፓየዝ ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ አሉ ፤ ባሕርየ ፡ ሥጋም ፡ ከባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ጋራ ፡ እኩል ፡ አይደለም ፡ በምትሉት ፡ አንስማማም ፡ ሲል ፡ ጉባኤውን ፡ ከፈተ ።

ፓድሬ ፡ ፓየዝም ፡ ሲመልስ ፡ እውነተኛው ፡ ሃይማኖት ፡ ይህ ፡ ነው ። ጌታችን ፡ ስለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደሙን ፡ አፍሷል ፡ እኛም ፡ በክቡር ፡ ደሙ ፡ ድነናል ።

ይህም ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ መኖራቸውን ፡ በግልጥ ፡ ያስተምረናል ፡ ምክንያቱም ፡ እምላክ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፡ ደም ፡ የለውምና ፡ የተባሉት ፡ ምስክሮች ፡ የሚሰማ ፡ ትርጉም ፡ የማይገኝላቸው ፡ ስለኾነ ፡ ነው ፡ አለ ።

በዚያ ፡ ከነበሩት ፡ ጨዋዎች ፡ አንዱ ፡ ከትንሣኤ ፡ በኋላ ፡ በክርስቶስ ፡ የሚገኘው ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ አለ ።

ፓድሬ ፡ ፓየዝም ፡ ሲመልስ ፡ ከ፪ቱ ፡ ባሕርያት ፡ የትኛው ፡ ጠፋ ፡ የሚጠፋ ፡ ቢኖር ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ሊኾን ፡ ግድ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ክርስቶስ ፡ ለቶማስ ፡ ቁስሎቹን ፡ አሳይቶ ፡ አማኝ ፡ እንጅ ፡ ተጠራጣሪ ፡ አትኹን ፡ አለው ። በዚህም ፡ ቶማስ ፤ ጌታዬ ፡ አምላኬ ፡ ብሎ ፡ አመነበት ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ሊፈርስ ፡ አይችልም ።

መለኮትም ፡ የማይታይና ፡ የማይነካ ፡ ስለኾነ ፡ ያሳየውና ፡ ያስነካው ፡ ሥጋውን ፡ እንጂ ፡ መለኮቱን ፡ አይደለም ። ከትንሣኤ ፡ በኋላ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ እንደ ፡ ነበሩት ፡ ይህ ፡ ያስረዳል ፡ አለ ። ሰውየው ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ መልስ ፡ አጣ ።

ፓድሬ ፡ ፓየዝ ፡ ግን ፡ ጥያቄውን ፡ ቀጥሎ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ አይደለምን ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ ።

ሊቁ ፡ ከክርክሩ ፡ ሊያመልጥ ፡ እንደ ፡ ፈለገ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ለምን ፡ አትመልስም ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ መኾኑን ፡ ልትክደው ፡ ነውን ፡ አለውና ፡ ሊቁ ፡ በክርስቶስ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ መኖሩን ፡ አንክድም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ሊባል ፡ እንጂ ፡ ሁለት ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ፡ አለ ።

ፓድሬ ፡ ፓየዝም ፡ በክርስቶስ ፡ የተዋሐዱ ፡ እንጂ ፡ ያልተደባለቁ ፡ ባሕርየ ፡ መለኮትና ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ የሚገኙ ፡ ከኾነ ፡ ስለምን ፡ ኹለት ፡ ሊባሉ ፡ አይቻልም ። ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ፡ ልትሉ ፡ ከፈለጋችሁ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ አለውና ፡ ስለዚህ ፡ በፍጹም ፡ እውነት ፡ ነው ፡ አለ ።

የፓድሬ ፡ ፓየዝ ፡ ንግግር ፡ ከዚያ ፡ ለነበሩ ፡ ሰዎች ፡ እስከማመን ፡ ድረስ ፡ ተረዳቸው ። አብዛኛዎቹ ፡ ግን ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮችን ፡ አነጋገር ፡ በመደገፍ ፡ ጸኑ ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳/ በየጊዜው ፡ የመጡ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ኹሉ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ጋራ ፡ ክርክር፡ ማድረጋቸው ፡ አይካድም ። የክርክሩን ፡ አመራር ፡ ግን ፡ እንደዚሁ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ለማመን ፡ አንችልም ። ምክንያቱም ፡ ስለክርክሩ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የተጻፈው ፡ ታሪክ ፡ ከዚህ ፡ ልዩ ፡ ስለኾነ ፡ ነው ።

ነገር ፡ ግን ፡ ያለፈውን ፡ ክርክር ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ እንደዚህ ፡ አይደለም ፡ እያሉ ፡ የሥራ ፡ ኪዜን ፡ ከማባከን ፡ መልሱን ፡ መስጠት ፡ የተሻለ ፡ መስሎ ፡ ስለታየኝ ፡ መልሱን ፡ አጽፋለሁ ። መልስ ፡ ከመ ሰጠቱም ፡ አስቀድመን ፡ ኹላችንም ፡ የአካልንና ፡ የባሕርይን ፡ ነገር ፡ እንመርምር ።

## ፩ኛ ፡ አካል ።

አካል ፡ ማለት ፡ ከራስ ፡ ጠጕር ፡ እስከ ፡ እግር ፡ ጥፍር ፤ ባጥንት ፡ በጅማት ፤ በሥጋ ፡ በቁርበት ፡ የተየያዘ ፡ ፍጹም ፡ ገጽ ፤ ፍጹም ፡ መልክእ ፡ ያለው ፡ ነፍስ ፡ የተዋሐደችው ፡ የባሕርይ ፤ የስም ፤ የግ ብር ፤ ባለቤት ፡ ነው ። ይህም ፡ አካል ፡ መባል ፡ ለአምላክም ፡ ለሰውም ፡ ይነገራል ።

ለአምላክ ፡ ሲነገር ፡ አብኒ ፡ ፍጹም ፡ በአካሉ ፡ ወበመልክኡ ፡ ወበገጹ ፤ ወልድኒ ፡ ፍጹም ፡ በአ ካሉ ፤ ወበመልክኡ ፡ ወበገጹ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስኒ ፡ ፍጹም ፡ በአካሉ ፡ ወበመልክኡ ፡ ወበገጹ ፡ ይላል ።

ለሰውም ፡ ሲነገር ፡ ወኢአካልየ ፡ በመትሕተ ፡ ምድር ። ወአካልየኒ ፡ ወኢከመ ፡ ምንት ፡ በቅ ድሜከ ፡ ይላል ። መዝ ፴፰ ፡ ፭ ፤ ፻፴፰ ፡ ፲፭ ።

## ፪ኛ ፡ ባሕርይ ።

ባሕርይ ፡ ማለት ፡ የአካል ፡ መገኛ ፡ ሥር ፤ አካል ፡ ሥራውን ፡ የሚሠራበት ፡ መሣሪያ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አካል ፡ ያለባሕርይ ፡ ብቻውን ፡ አይቆምም ፡ ባሕርይም ፡ ያለአካል ፡ አይፈጸምም ። አካ ልና ፡ ባሕርይ ፡ እንደ ፡ ሥርና ፡ እንደ ፡ ዐፅቅ ፡ እንደ ፡ ቅንጣትና ፡ እንዳገዳ ፡ የተየያዙ ፡ የማይለያዩ ፡ ናቸው ።

እንዲህም ፡ ስለኾኑ ፡ ባሕርይ ፡ አካላዊ ፡ ፍጹመ ፡ አካል ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፡ አካል ፡ አይባልም ። አካልም ፡ ባሕርያዊ ፡ ሕያው ፡ ባሕርይ ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፡ ባሕርይ ፡ አይባልም ።

ባሕርይ ፡ አካል ፡ ሥራውን ፡ የሚሠራበት ፡ የአካል ፡ መሣሪያ ፡ ነው ፡ (ማለት) ፡ ለምሳሌ ፤ ለወኀ ፡ አካልም ፡ ባሕርይም ፡ አለው ፤ አካሉ ፡ በጽዋዕ ፡ በማድጋ ፡ የሚቀዳው ፤ ባሕርዩ ፡ ርጥበቱ ፡ ነው ። ሥራውም ፡ የደረቀውን ፡ ማራስ ፡ የራሰውን ፡ ማበስበስ ፡ ነው ። ወኀ ፡ ማናቸውንም ፡ የደረቀ ፡ ነገር ፡ ሲነከሩበት ፡ ማራሱ ፡ ርጥበት ፡ ባሕርዩ ፡ ቢኾን ፡ ነው ፤ ርጥበት ፡ ባይኖረው ፡ ሊያርስ ፡ አይችልም ፡ ነበረ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ባሕርይ ፡ የአካል ፡ መገኛ ፡ ነው ፡ ባልን ፡ ጊዜም ፡ ወኃን ፡ መሬትን ፡ ነፋስን ፡ እሳትን ፡ ባሕር ያት ፡ ብለን ፡ የአዳም ፡ ምሉ ፡ አካሉ ፡ ከነዚህ ፡ ካራቱ ፡ ከወኀ ፡ ከመሬት ፡ ከነፋስ ፡ ከእሳት ፡ መገኘ ቱን ፡ መናገራችን ፡ ነው ።

እንዲህም ፡ ባልን ፡ ጊዜ ፡ ለአራቱ ፡ ኹሉ ፡ አካልም ፡ ባሕርይም ፡ እንዳላቸው ፡ እንዘንጋ ። የእሳት ፡ አካሉ ፡ በዕንጨት ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ ነበልባሉ ፡ ቦግ ፡ ቦግ ፡ ሲል ፡ ይታያል ፤ ባሕርዩ ፡ ውዕየት ፡ ይብሰት ፡ ብሩህነት ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ባሕርያት ፡ መኖራቸውን ፡ ለማወቅ ፡ የምንችል ፡ እሳቱ ፡ በመፋጀቱ ፡ በማቃጠሉ ፡ ብርሃን ፡ በማሳየቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባሕርያትን ፡ እንደ ፡ አካል ፡ ተገል ጸው ፡ ወይም ፡ ከአካል ፡ ተለይተው ፡ አይተናቸው ፡ አይደለም ።

ወኀም ፡ አካሉ ፡ ሲፈስ ፡ ይታያል ፡ በዋንጫ ፡ በብርጭቆ ፡ ይያዛል ፤ ባሕርዩ ፡ ግን ፡ ርጡብ ፡ ቈሪር፤ ብሩህ ፤ ወይም ፡ ንጹሕ ነው ። እነዚህ ፡ ባሕርያት ፡ መኖራቸው ፡ የሚታወቅ ፡ ያነን ፡ ሲፈስ ፡ የምናየ ውን ፡ አካሉን ፡ የርጥበት ፡ የቍረት ፡ የጽሩይነት ፡ ሥራ ፡ ሲያሠሩት ፡ በማየታችን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ አካሉ ፡ ገዝፈው ፡ ታይተው ፡ ተዳሰው ፡ ከአካል ፡ ተለይተው ፡ ሥራ ፡ ሠርተው ፡ አይደለም ።
መሬት ፡ አካሉ ፡ ገዝፎ ፡ ይታያል ፡ ለመሬት ፡ ግዙፍነት ፡ ብዙ ፡ ሐተታ ፡ አያስፈልገውም ።

ባሕርዩ ፡ ጽሉም ፡ ውዑይ ፡ ይቡስ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ባሕርያት ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ መኖራቸውን ፡ የምናውቀው ፡ ግዙፉን ፡ አካሉን ፡ የጽሉምነት ፡ የውዑይነት ፡ የይቡስነት ፡ ሥራ ፡ ሲያሠሩት ፡ በማ የታችን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከአካሉ ፡ ተለይተው ፡ ሥራ ፡ ሲሠሩ ፡ አይተናቸው ፡ አይደለም ።

ነፋስ ፡ አካሉ ፡ ረቂቅ ፡ ነው ፡ ዛፍ ፡ ሲያናውጽ ፡ ባሕር ፡ ሲገሥጽ ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ ባይን ፡ አይ ታይም ። ባሕርዩ ፡ ግን ፡ ጽሉም ፡ ይቡስ ፡ ቈሪር ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ባሕርያት ፡ ነፋስን ፡ የጽሉምነት ፡ የይቡስነት ፡ የቈሪርነት ፡ ሥራ ፡ ሲያሠሩት ፡ አይተን ፡ መኖራቸውን ፡ ከማወቅ ፡ በቀር ፡ ከአካሉ ፡ ተለይተው ፡ ሲታዩ ፡ ወይም ፡ ሥራ ፡ ሊሠሩ ፡ አይችሉም ።

እነሆ ፡ አሁን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በዘረዘርናቸው ፡ ነገሮች ፡ አካልና ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ሲኾኑ ፡ ልዩነት ፡ እንዳላቸው ፤ ልዩነት ፡ ሲኖራቸውም ፡ ተፈልጠ ፡ የሌለባቸው ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፤ አካል ፡

ሠሪ ፤ ባሕርይ ፡ አሠሪ ፡ መኾናቸውን ፤ ባሕርይም ፡ አካላዊ ፡ ፍጹም ፡ አካል ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፡ አካል ፡ አለመባሉን ፡ አካልም ፡ ባሕርያዊ ፡ ሕያው ፡ ባሕርይ ፡ ቢባል ፡ እንጂ ፡ ባሕርይ ፡ አለመባሉን ፡ በስፊው ፡ አስረድተናል ።

ሰውም ፡ ከነርሱ ፡ የተፈጠረ ፡ ስለኾነ ፡ አካሉም ፡ የነርሱ ፡ አካል ፤ ባሕርዩም ፡ የነርሱ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ።

እንዲሁም ፡ ለቃል ፡ ከአብ ፤ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የተለየ ፡ ፍጹም ፡ አካል ፡ አለው ፡ ባሕርዩ ፡ ግን ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የምታደርገው ፡ በከዊን ፡ የምትለይ ፡ አሐቲ ፡ ባሕርይ ፡ ናት ። ይቺ ፡ በሦስቱ፡ አካላት ፡ ያለች ፡ አሐቲ ፡ ባሕርይም ፡ በከዊን ፡ ከሦስት ፡ ትከፈላለች ።

መከፈሏም ፡ ፩ኛ ፡ ልብ ፡ በመኾን ፤ ፪ኛ ፡ ቃል ፡ በመኾን ፤ ፫ኛ ፡ እስትንፋስ ፡ በመኾን ፡ ነው ። በከዊን ፡ ሦስት ፡ ስንልም ፡ እንደ ፡ አካላት ፡ ያለ ፡ ሦትነት ፡ ሦስት ፡ የምንል ፡ አይደለንም ።

አካላት ፡ መጠቅለልና ፡ መቀላቀል ፡ ሳይኖርባቸው ፡ በተከፍሎ ፡ በተፈልጦ ፡ በፍጹም ፡ ገጽ ፡ በፍጹም ፡ መልክእ ፡ በየራሳቸው ፡ የቆሙ ፡ ናቸው ።

ኩነታት ፡ ግን ፡ ተፈልጦ ፡ ተከፍሎ ፡ ሳይኖርባቸው ፡ በተዋሕዶና ፡ በተጋብአ ፡ ባንድነት ፡ አካላትን ፡ በህልውና ፡ እያገናዘቡ ፡ ባንድ ፡ መለኮት ፡ ባንድ ፤ ባሕርይ ፡ ያሉ ፡ የሚኖሩ ፡ ናቸው ።

እሊህም ፡ ከዊነ ፡ ልብ ፤ ከዊነ ፡ ቃል ፤ ከዊነ ፡ እስትንፋስ ፡ ናቸው ። ከዊነ ፡ ልብ ፡ በአብ ፡ መሠረትነት ፡ ለራሱ ፡ ለባዊ ፡ ኾኖ ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዕውቀት ፡ መኾን ፡ ነው ፤ ከዊነ ፡ ቃል ፡ በአብ ፡ መሠረትነት ፡ ለራሱ ፡ ነባቢ ፡ ኾኖ ፡ ለአብ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ንባብ ፡ መኾን ፡ ነው ፤ ከዊነ ፡ እስትንፋስ ፡ በአብ ፡ መሠረትነት ፡ ለራሱ ፡ ሕያው ፡ ኾኖ ፡ ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ሕይወት ፡ መኾን ፡ ነው ። ሦስት ፡ ኩነታት ፡ የተባሉ ፡ እኒህ ፡ ናቸው ።

የኸውም ፡ የከዊን ፡ ምሥጢር ፡ ሥላሴ ፡ ንግበር ፡ሰብአ ፡ በአርዓያነ ፡ ወበአምሳሊነ ፡ ብለው ፡ ላንድነታቸው ፡ ለሦስትነታቸውም ፡ ምሳሌ ፡ ባደረጉት ፡ በነፍስ ፡ ከዊን ።

ሊቃውንትም ፡ ላንድነት ፡ ለሦስትነት ፡ ምሳሌ ፡ ባደረጓቸው ፡ በፀሐይ ፡ በእሳት ፡ በቀላይ ፡ ከዊን ፡ ቢመረምሩት ፡ ይገኛል ።

ሲመሰልም ፡ የሥላሴን ፡ አካል ፡ በምሳሌዎች ፡ ባሕርይ ፡ የሥላሴን ፡ ባሕርይ ፡ በምሳሌዎች ፡ አካል ፡ አዛውሮ ፡ መመሰል ፡ ነው ።

## ፩ኛ ፡ ነ ፍ ስ ።

ነፍስ ፡ በአካሏ ፡ ከሦስት ፡ የማትከፈል ፡ አንዲት ፡ ስትኾን ፡ በባሕርይዋ፡ እንደ ፡ ሥላሴ ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ አላት ፤ ይኸውም ፡ ከዊነ ፡ ልብ ፤ ከዊነ ፡ ቃል ፤ ከዊን ፡ እስትንፋስ ፡ ነው ፡ በባሕርይዋ ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ ያላት ፡ መኾንዋ ፡ አካሏን ፡ ከሦስት ፡ አይከፍለውም ።

እንደዚኸውም ፡ የሥላሴ ፡ ከዊን ፡ መለኮትን ፡ ወይም ፡ ባሕርይን ፡ ከሦስት ፡ አይከፍለወ ም ። እንዲሁ ፡ ሳትከፈል ፡ የልብነትዋ ፡ ከዊን ፡ ከቃሏና ፡ ከእስትንፋስዋ ፡ ከዊን ፡ ሳይለይ ፡ በራሱ ፡ ከዊን ፡ ከሥጋዊ ፡ ልብ ፡ ጋራ ፡ ይዋሐዳል ።

የቃልዋም ፡ ከዊን ፡ ከልብነትዋና ፡ ከእስትንፋስነትዋ ፡ ከዊን ፡ ሳይለይ ፡ በራሱ ፡ ከዊን ፡ ከሥጋ ፡ አንደበት ፡ ወይም ፡ ምላስ ፡ ጋራ ፡ ይዋሐዳል ።

የእስትንፋስዋም ፡ ከዊን ፡ ከልብነትዋና ፡ ከቃልነትዋ ፡ ከዊን ፡ ሳይለይ ፡ በራሱ ፡ ከዊን ፡ ከሥጋዊ ፡ እስትንፋስ ፡ ጋራ ፡ ይዋሐዳል ፡ (ሳምባ) ።

## ፪ ኛ ም ፡ እ ሳ ት ።

እሳት ፡ በአካሉ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ በባሕርዩ ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ አለው ፡ ይኸውም ፡ ነበልባል ፡ ብርሃን ፡ ዋዕይ ፡ ነው ። በነበልባሉ ፡ አብ ፤ በብርሃኑ ፡ ወልድ ፤ በዋዕዩ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመሰላሉ ። ይኸውም ፡ ተፈልጦ ፡ ተከፍሎ ፡ ሳይኖርበት ፡ ባንድ ፡ ህላዌ ፡ የሚኖር ፡ ነው ።

ይህ ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ የእሳትን ፡ አንድ ፡ ህላዌ ፡ ከሦስት ፡ እንዳይከፋፍለው ፤ የሥላሴም ፡ ከዊን ፡ መለኮትን ፡ ወይም ፡ ባሕርይን ፡ ከሦስት ፡ አይከፍለውም ።

## ፫ኛ ፡ ፀሐይ ።

ፀሐይ ፡ በባሕርዩ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ አለው ፤ ክበብ ፡ ብርሃን ፤ ዋዕይ ፤ በክበቡ ፡

አብ ፡ በብርሃኑ ፡ ወልድ ፡ በዋዕዩ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመሰላሉ ። ፀሐይ ፡ በከዊን ፡ ሦስት ፡ ሲኾን ፡ በአካል ፡ አንድ ፡ እንደኾነ ፡ መለኮትም ፡ ወይም ፡ ባሕርይ ፡ በከዊን ፡ ሦስት ፡ ቢኾን ፡ በህልውና ፡ አንድ ፡ ነው ።

## ፬ኛ ፡ ባሕር ።

ባሕር ፡ ባሕርዩ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ አለው ፡ ስፍሐት ፤ ርጥበት ፤ ሑከት ፡ ናቸው ። በስፍሐቱ ፡ አብ ፤ በርጥበቱ ፡ ወልድ ፤ በሑከቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመሰላሉ ።

ይህ ፡ ከዊን ፡ ባሕርን ፡ ከሦስት ፡ እንዳይከፋፍለው ፡ የሥላሴም ፡ ከዊን ፡ መለኮትን ፡ ወይም ፡ ባሕርየ ፡ እግዚአብሐርን ፡ ከሦስት ፡ የሚከፋፍል ፡ አይደለም ።

ሥላሴን ፡ በህልውና ፡ አንድ ፡ የሚያሰኛቸው ፡ ምሥጢር ፡ ይህ ፡ ነው ።

ይህንም ፡ ምሳሌ ፡ ልብ ፡ ወሰድ ፡ አምጥተን ፡ የተናገርነው ፡ አይደለንም ፡ ስለእሳት ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቀሌምንጦስ ፡ በተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ አቡየ ፡ እሳት ፡ ወአነ ፡ ብርሃኑ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዋዕዩ ፡ ብሏል ። ፫፻ም ፡ በቅዳሴ ፡ አቡየ ፡ ወአነ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እሳት ፡ ወነበልባል ፡ ወፍሕም ፡ ብለዋል ። አባ ፡ ሕርያቆስም ፡ አብ ፡ እሳት ፡ ወልድ ፡ እሳት ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እሳት ፡ ፩ ፡ ውእቱ ፡ እሳተ ፡ ሕይወት ፡ ዘእምእርያም ። ብሏል ።

ስለፀሐይም ፡ በቀሌምንጦስ ፡ አቡየ ፡ ፀሐይ ፡ ወአነ ፡ ብርሃኑ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዋዕዩ ፡ ብሏል። ፫፻ም ፡ በቅዳሴ ፡ አቡየ ፡ ወአነ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፀሐይ ፡ ወብርሃን ፡ ወዋዕይ ፡ ብለዋል ። አባ ፡ ሕርያቆስም ፡ አብ ፡ ፀሐይ ፡ ወልድ ፡ ፀሐይ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፀሐይ ፡ ፩ ፡ ውእቱ ፡ ፀሐየ ፡ ጽድቅ ፡ ዘላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ብሏል ።

ስለባሕርም ፡ ምሳሌነት ፡ አረጋዊ ፡ መንፈሳዊ ፡ በ፳፪ኛው ፡ ድርሳን ፡ ነጽርኬ ፡ ዘተብህለ ፡ በእንተ ፡ አበ ፡ ኵሉ ፡ ከመ ፡ መሰልዋ ፡ ለዛቲ ፡ ባሕር ፡ እንተ ፡ ትትገሠሥ ፡ ለወልድኒ ፡ ዘይሰገድ ፡ በኀበ ፡ ኵሉ ፡ መሰልዎ ፡ በርጥበተ ፡ ማይ ፤ ለመንፈስ ፡ ቅዱስኒ ፡ ዘይሴባሕ ፡ በሑከተ ፡ ማይ ፡ ዘውስተ ፡ ባሕር ። ለመኑ ፡ ይትከሀሎ ፡ ከመ ፡ ይክፍል ፡ ኃይለ ፡ ባሕር ፡ እምነ ፡ ጠባይዒሁ ፡ ይትከሀሎኑ ፡ ለባሕር ፡ ከመ ፡ የሀሉ ፡ እንበለ ፡ ርጥበት ፡ ወእንበለ ፡ ተሐውኮ ፡ ወለመኑ ፡ ይትከሀሎ ፡ ይፍልጥ ፡ ሁከተ ፡ እምነ ፡ ማይ ፡ ወባሕር ፡ ወያቅማ ፡ በባሕቲታ ፡ ለማይኒ ፡ ወለርጥበት ፡ በበባሕቲቶሙ ፡ አውመኑ ፡ ዘርእየ፡፩፡እምኔሆሙ ፡ እንዘ ፡ ይቀውም ፡ በባሕቲቱ ፡ ዘእንበለ ፡ በትሥልስቱ ፡ እስመ ፡ ፩ ፡ እሙንቱ ፡ እንዘ ፡ ፫ ፡ ወእንዘ ፡ ፫ቱ ፡ ፩ደ ፡ ይትበሀሉ ፡ ወሰበሂ ፡ ይትሐለይ ፡ ወይትኔጸር ፡ ምስለ ፡ ኃይላቲሁ ፡ ወኢይትሌለዮ ፡ ኃይላቲሁ ፡ እምጠባይዑ ፡ ወጠባይዑ ፡ እምኃይላቲሁ ፡ ወከመዝ ፡ እሑሊ ፡ በእንተ ፡ ጠባይዓት ፡ ስቡሓት ።

የኹሉ ፡ መገኛ ፡ አብን ፡ ነፋስ ፡ በሚያማታት ፡ ባሕር ፡ ባለች ፤ በውኀ ፡ ስፍሐት ፡ እንደመሰሉት ፡ በኹሉ ፡ ዘንድ ፡ የሚሰገድ ፡ ወልድንም ፡ በወኀ ፡ ርጥበት ፡ እንደመሰሉት ፡ በኹሉ ፡ ዘንድ ፡ የሚመሰገን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ በባሕር ፡ ባለ ፡ በወኀ ፡ ሑከት ፡ እንደመሰሉት ፡ እወቅ ። የባሕርን ፡ ኃይል ፡ ከጠባይው ፡ መለየት ፡ ለማን ፡ ይቻለዋል ፤ ባሕር ፡ ያለርጥበትና ፡ ያለመታወክ ፡ ሊኖር ፡ ይችላልን ፤ ሑከትን ፡ ከስፍሐትና ፡ ከርጥበት ፡ ለይቶ ፡ ለብቻዋ ፡ ማቆም ፡ ለማን ፡ ይቻለዋል ፤ ስፍሐትንና ፡ ርጥበትንስ ፡ ከሑከት ፡ ለይቶ ፡ ለብቻቸው ፡ ማቆም ፡ ለማን ፡ ይቻለዋል ፤ በ፫ትነቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከነዚህ ፡ አንዱን ፡ ብቻውን ፡ ቆሞ ፡ ያየው ፡ ማነው ። ሦስት ፡ ሲኾኑ ፡ አንድ ፡ ናቸውና ፡ ሦስት ፡ ሲኾኑም ፡ አንድ ፡ ይባላሉና ። በሦስት ፡ ኩነት ፡ እንዳለ ፡ ቢታይ ፡ ቢታሰብም ፡ ስፍሐት ፡ ኃይሉን ፡ ከሚገልጽባቸው ፡ ከርጥበትና ፡ ከሑከት ፡ ጋራ ፡ ይታሰባል ። ኃይሉን ፡ የሚገልጥባቸው ፡ ርጥበትና ፡ ሑከትም ፡ ከስፍሐት ፡ አይለዩም ፡ ስፍሐትም ፡ ከርጥበቱና ፡ ከሑከቱ ፡ አይለይም ።

ስለተመሰገኑ ፡ ጠባይዓትም ፡ እንዲህ ፡ እናገራለሁ ፡ ብሏል ።

እነሆ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከዘረዘርናቸው ፡ መምሪያዎች ፡ ለትስብእት ፡ ከአራቱ ፡ ባሕርይ ፡ ባሕርያት ፡ የተገኘ ፡ ነፍስ ፡ የተዋሐደችው ፡ ፍጹም ፡ አካልና ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ መኾኑን ፡ እንደ ፡ ገለጽን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወልድም ፡ ቃል ፡ በመኾን ፡ የሚለይ ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የሚኾንበት ፡ አንድ ፡ መለኮት ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንዳለው ፡ አስረድተናል ።

እንግዲህ ፡ የመለኮትንና ፡ የትስብእትን ፡ ተዋሕዶ ፡ ወደ ፡ መመርመር ፡ እንመለስ ።

ስለኾነም ፡ ላንባቢዎች ፡ የማስታውሰው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ቀርቶኛል ። ይኸውም ፡ አብ ፤ ወልድ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማለት ፡ የአካል ፡ ስም ። ልብ ፤ ቃል ፤ እስትንፋስ ፡ ማለት ፡ የከዊን ፡ ስም ፡ መኾኑን ፡ እንዳትዘነጉብኝ ፡ ነው ። የአካል ፡ ስም ፡ ማለት ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ከተወለደ ፡ በኋላ ፡ ሊጠራ

በት ፡ እንደሚወጣለት ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅ ፡ ዳዊት ፡ ሰሎሞን ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ያይደለ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ያለ ፡ አካል ፡ ሲገኝ ፡ የሚገኝ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ገጽ ፡ ፪፻፬ ።

ልብ ፡ ቃል ፡ እስትንፋስ ፡ ማለት ፡ ግን ፡ ተፈልጦ ፡ ተከፍሎ ፡ በሌለባት ፡ ባንዲት ፡ ባሕርይ ፡ ያለ ፡ የከዊን ፡ ስም ፡ ነው ። ይኸውም ፡ አንድነት ፡ ሳለበት ፡ ልዩነት ፤ ልዩነት ፡ ሳለበት ፡ አንድነት ፡ ያለበት ፡ ነው ። ልዩነቱ ፡ በከዊን ፡ ነው ። አንድነቱ ፡ ግን ፡ በህልውና ፡ መገናዘብ ፡ ነውና ፡ ወደ ፡ ተዋሕዶ ፡ ምሥጢር ፡ ስንገባ ፤ እንዳንቸገር ፡ እነዚህን ፡ ኹለቱን ፡ ዓይነት ፡ ስሞች ፡ ጠንቅቀን ፡ እንድንረዳ ፡ ደጋግሜ ፡ አሳስባለሁ ።

የተነገረው ፡ ትንቢት ፡ የተቈጠረው ፡ ሱባኤ ፡ ሲፈጸም ፡ እመቤታችን ፡ መልአኩ ፡ ቅዱስ ፡ ገብ ርኤል ፡ የነገራትን ፡ ብሥራት ፡ ሰምታ ፡ ይኩነኒ ፡ በከመ ፡ ትቤለኒ ።

እንደቃልህ ፡ ይደረግልኝ ፡ ብላ ፡ ቃሉን ፡ባመነችው ፡ ጊዜ ፡ ቃሏን ፡ ምክንያት ፡ አድርጎ ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የምትሆን ፡ በከዊን ፡ የምትለይ ፡ ባሕርይ ፡ ያለችው ፡ አካለ ፡ ቃል ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ ሰብአዊ ፤ አካልን ፡ እንበለ ፡ ዘርዕ ፡ በሕፃናት ፡ መጠን ፡ ነሥቶ ፡ ተዋሐደ ። በተዋሕዶ ፡ ምንታዌ ፡ ጠፋ ። የቃል ፡ ገንዘብ ፡ ለሥጋ ፤ የሥጋ ፡ ገንዘብ ፡ ለቃል ፡ ኾነ ።

ይህም ፡ ተዋሕዶ ፡ የአካል ፡ ተዋሕዶ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ የባሕርይም ፡ መኾኑን ፡ የሚያስረዳ ፡ ወንጌላዊ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ በሚጠራበት ፡ ስም ፡ ወልድ ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ሳይል ፡ አካልን ፡ በህልውና ፡ እያገናዘበ ፡ ሥላሴን ፡ በህልውና ፡ አንድ ፡ በሚያሰኝ ፡ በባሕርይ ፡ ከዊን ፡ ስሙ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ብሏል ።

የትስብእትንም ፤ አካልን ፡ እንጂ ፡ ባሕርይን ፡ አልተዋሐደም ፡ እንዳይባል ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ወኀደረ ፡ ላዕሌነ ፡ ብሏል ። ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ብቻ ፡ ብሎ ፡ ቢኾን ፡ የእንስሳትም ፡ የአራዊ ትም ፡ ሥጋ ፡ ሥጋ ፡ የሚባል ፡ ስለሆነ ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ ሰብአዊ ፡ አካልን ፡ እንደነሣ ፡ ባላስረዳም ፡ ነበረና ፤ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ ሰብአዊ ፡ አካልን ፡ እንደነሣ ፡ በሚያስረዳ ፡ አነጋ ገር ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ወኀደረ ፡ ላዕሌነ ፡ ብሏል ።

፪ኛም ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ብቻ ፡ ብሎ ፡ ቢኾን ፡ ብእሲተ ፡ ሎጥ ፡ ተለውጣ ፡ ሐውልተ ፡ ጼው ፡ እንደኾነች ፤ ማየ ፡ ቃና ፡ ተለውጦ ፡ ወይን ፡ እንደሆነ ፤ ቃልም ፡ ተለውጦ ፡ ሥጋ ፡ ኾነ ፡ ማለትን ፡ ባሳየ ፡ ነበረና ፡ ወኀደረ ፡ ላዕሌነ ፡ ብሏል ።

ኀደረ ፡ ላዕሌነ ፡ ብቻ ፡ ብሎም ፡ ቢኾን ፡ በማድጋ ፡ እንደ ፡ ተቀዳ ፡ ወኀ ፡ በብርሌ ፡ እንደ ፡ ተቀዳ ፡ ጠጅ ፡ ቃል ፡ በትስብእት ፡ አድሮ ፡ ሔዶ ፡ ገብቶ ፡ ወጣ ፡ ማለትን ፡ ባሳየ ፡ ነበረና ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ብሏል ።

በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ተሳሔ ፡ ውላጤ ፡ ፍልጠት ፡ ቡዐዴ ፡ ምንታዌ ፡ ሳይኖርበት ፡ ቃል ፡ ርቀቱን ፡ ምልአቱን ፡ ስፋቱን ፡ ሳይለቅ ፡ ትስብእትም ፡ ግዘፉን ፡ ውሱንነቱን ፡ ሳይለቅ ፡ በተዐቅቦ ፡ እንደ ፡ ተዋ ሐደ ፡ እናምናለን ።

ይኸውም ፡ እንደ ፡ ነፍስና ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ ተዋሕዶ ፡ ነው ፤ ነፍስና ፡ ሥጋ ፡ ምንም ፡ በሞት ፡ ተፈልጦ ፡ ቢኖርባቸው ፡ እስከ ፡ ጊዜው ፡ ጽንዐ ፡ ተዋሕዶ ፡ አላቸው ፡ ሥጋ ፡ ግዘፉን ፡ ሳይለቅ ፡ ነፍ ስም ፡ ርቀቷን ፡ ሳትለቅ ፡ ተዋሕደው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዲባል ፡ መለኮትም ፡ ትስብእትን ፡ ቢዋሐድ ፡ አንድ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ አይባልም ።

በዚህን ፡ አኳኋን ፡ ተዋሕዶ ፡ አካላትንም ፡ ባሕርያትንም ፡ ከምንታዌ ፡ ከፍልጠት ፡ ከቡዐዴ ፡ እንዲጠብቅ ፤ ተዐቅቦም ፡ አካላትንም ፤ ባሕርያትንም ፡ ከውላጤ ፡ ከቱሳሔ ፡ ከመጠፋፋት ፡ የሚጠ ብቅ ፡ መኾኑን ፡ እንገንዘብ ።

ለኢትዮጵያ ስለአካላትና ስለባሕርያት ፡ ያላትን ፡ አስተያየት ፡ በሰፊው ፡ ከገለጽን ፡ ክርክሩን ፡ ወደ ማመዛዘን ፡ እንመለስ ።

## ደ ራ ሲ ።

### ፩ ፡ ስለክርክሩ ፡ አነሣሥ ።

፳፰/ አሁን ፡ እርስዎ ፡ ስለክርክሩ ፡ አነሣሥ ፡ ሲናገሩ ፡ የጠቀሱት ፡ ያ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ መነኩሴ ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ አሉ ፤ ባሕርየ ፡ ሥጋ ፡ ከባሕርየ ፡ መለኮት ፡ እኩል ፡ አይደለም ፡ በማለታችሁ ፡ አንስማማም ፡ ማለቱ ፡ የመለኮት ፡ ክብር ፡ በተዋሕዶ ፡ ለትስብእት ፡ እንደ ፡ ተሳለፈና ፡

ባሕርይም ፡ እንደ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ መኾኑን ፡ ስለሚያውቅ ፡ ነው ። የፓድሪ ፡ ፓየዝን ፡ መልስ ፡ ስን መረምር ፡ ከሌላው ፡ ንግግሩ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ አይደለም ፡ ልትሉ ፡ ከፈለ ጋችሁ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ አለውና ፡ ይህ ፡ በፍጹም ፡ እውነት ፡ ነው ፡ አለ ፡ ያሉትን ፡ አስቀድመን ፡ ልንመረምር ፡ አስፈላጊያችን ፡ ኾነዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፩/ የመለኮት ፡ አካልና ፡ የሰው ፡ አካል ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መኾናቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ። አንድ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ አለው ፡ የምንለው ፡ ይህ ፡ አካል ፡ የቃል ፡ ብቻ ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ የትስብእት ፡ ? የቃል ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንዳይሉ ፡ የቃል ፡ አካል ፡ ምሉእ ፡ ስፉሕ ፡ ረቂቅ ፡ ባይሆን ፡ የማይታይ ፡ በእጅ ፡ የማይዳ ሰስ ፡ የሚቀረስ ፡ ሥጋ ፡ የሚፈስ ፡ ደም ፡ የሌለው ፡ ስለኾነ ፡ በሥጋው ፡ በደሙ ፡ ዓለምን ፡ አዳነ ፡ ማለት፡አይቻልም ። ወንጌላዊም ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ያለው ፡ መቅረቱ ፡ ነው ።

የትስብእት ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንዳይሉም ፡ የዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ሥጋ ፡ የዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ደም ፡ ስንኳ ፡ ዓለምን ፡ ሊያድን ፡ ራሱም ፡ ሊድን ፡ አይችልም ። ስለዚህ ፡ ርስዎ ፡ ራስዎ ፡ በዚሁ ፡ መጽ ሐፍ ፡ በመግለጫው ፡ ላይ ፡ አካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ ብለው ፡ እንደገለጹት ፡ ተዋሕዶ ፡ ማለት ፡ ኹለት ፡ ነገሮች ፡ አንድ ፡ መኾናቸውን ፡ የሚገልጽ ፡ ንግግር ፡ እንጂ ፡ ለአንድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ የማይነገር ፡ ስለኾነ ፡ ክርስቶስ ፡ ከኹለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኾነ ፡ ማለት ፡ ግድ ፡ ነው ።

አንድ ፡ አካል ፡ ስንልም ፡ በተዋሕዶ ፡ ፍልጠት ፡ ምንታዌ ፡ ቡዐዴ ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ ማመን ፡ አለብን ፡ ይህ ፡ ካልኾነ ፡ ግን ፡ እንደንስጥሮስ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ያሰኛል ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አያሰኝም ። ተዋሐደ ፡ ስንልም ፡ እንደ ፡ ነፍስና ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ መለኮት ፡ ርቀቱን ፡ ለቆ ፡ ሳይገዝፍ ፡ ምልእት ፡ ስፋቱን ፡ ለቆ ፡ ሳይወሰን ። ትስብእትም ፡ ግዘፉን ፡ ለቆ ፡ ሳይረቅ ፡ ውሱንነቱን ፡ ለቆ ፡ ምሉእ ፡ ስፉሕ ፡ ሳይኾን ፡ በተዐቅቦ ፡ ተወሐደ ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ ተለወጠ ፡ ወይም ፡ ተቀላቀለ ፡ አንልም ። እነሆ ፡ አሁን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ በመረመርነው ፡ አኳኋን ፡ በአካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ እንስማማ ፡ ይመስለኛል ።

## ደ ራ ሲ ።

### ፱ኛ ፡ ክርስቶስ ፡ ደሙን ፡ ስለማፍሰሱ ።

፳፪/ ጌታችን ፡ ስለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደሙን ፡ አፍሷል ፡ እኛም ፡ በደሙ ፡ ድነናል ። ይህ ፡ በክ ርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ባሕርየ ፡ ሥጋና ፡ ባሕርየ ፡ መለኮት ፡ መገኘታቸውን ፡ ያስተምረናል ።
እንዲህ ፡ ባይኾን፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፡ ደም ፡ የለውምና ፡ የተባሉት ፡ ምስክሮች ፡ የሚሰማ ፡ ትርጉም ፡ አይገኝላቸውም ፡ ነበረ ፡ ሲል ፡ መለሰ ፡ ያሉትን ፡ ቃል ፡ እንመርምር ።

## መ ላ ሽ ።

፳፪/ ይህ ፡ አነጋገር ፡ ደም ፡ ከአካለ ፡ ትስብእት ፡ ሳይኾን ፡ ከባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ፈሰሰ ፡ የሚያሳይ ፡ ነው ። የአካልንና ፡ የባሕርይን ፡ ነገር ፡ ዘርዝረን ፡ ባስረዳንበት ፡ በላይኛው ፡ መሥ መር ፡ ገልጸን ፡ ምሳሌ ፡ መስለን ፡ እንዳስረዳነው ፡ ባሕርይ ፡ አካል ፡ ሥራውን ፡ የሚሠራበት ፡ የአ ካል ፡ መሣሪያ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባሕርይ ፡ ከአካል ፡ ተለይቶ ፡ ብቻውን ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ አይችልም ። ስለዚህ ፡ መለኮት ፡ የተዋሐደው ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ አካለ ፡ ትስብእት ፡ ደሙን ፡ በመል ዕልተ ፡ መስቀል ፡ እንዳፈሰሰ ፡ እንናገራለን ፡ እንጂ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ብቻ ፡ ደም ፡ አፈሰሰ ፡ ማለ ትን ፡ ማንም ፡ አይቀበለውም ። እንግዲህ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጐን ፡ ደም ፡ መፍሰሱ ፡ ምንታዌን ፡ የሚያ መለክት ፡ ከኾነ ፡ ደም ፡ የፈሰሰ ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ካለው ፡ አካል ፡ እንጂ ፡ ከሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ አይደለምና ፡ እንደቁርሎስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ ቀርቶ ፡ እንደ ፡ ንስጥ ሮስ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የሚያሰኝ ፡ መኾኑን ፡ ይገንዘቡልኝ ። እኛ ፡ ግን ፡ ደም ፡ የፈሰሰ ፡ መለኮታዊ ፡ ባሕርይ ፡ የተዋሐደው ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ካለው ፡ አካለ ፡ ትስብእት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አምነን ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ብለን ፡ እንናገራለን ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የምንል ፡ አይደለንም ።

## ደ ራ ሲ ።

### ፲ኛ ስለጨዋው ፡ ንግግር ።

፳፫/ እዚያ ፡ ከነበሩ ፡ ጨዋዎች ፡ አንዱ ፡ ከትንሣኤ ፡ በኋላ ፡ የሚገኘው ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፡ ስለሚሉት ።

## መ ላ ሽ ።

፳፮/ ይህ ፡ ነገር ፡ በእውነት ፡ ተነግሮ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያልተማረ ፡ ማይምን ፡ ተናግሮት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፡ እንጂ ፡ ከተማሪ ፡ ቤት ፡ የዋለ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሊናገረው ፡ አይችልም ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መልስ ፡ የለውም ።

## ድ ራ ሲ ።

### ፩ኛ ፡ ስለ ፡ መላክተኛው ፡ መልስ ።

፳፯/ መላክተኛው ፡ ለዚህ ፡ መልስ ፡ ሲሰጥ ፡ ከኹለቱ ፡ ባሕርያት ፡ የትኛው ፡ ጠፋ ፤ የጠፋ ቢኖር ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ሊኾን ፡ ግድ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ከትንሣኤ ፡ በኋላ ፡ ለቶማስ ፡ ቍስሎቹን ፡ አሳይቶ ፡ እማኝ ፡ እንጂ ፡ ተጠራጣሪ ፡ አትኹን ፡ አለው ፡ የሚለውን ፡ የወንጌል ፡ ቃል ፡ የሚያፈርስ ፡ ስለኾነ ፡ ሊኾን ፡ አይችልም ፡ መለኮት ፡ የማይታይና ፡ የማይነካ ፡ ስለኾነ ፡ ያሳየውና ፡ ያስነካው ፡ ሥጋውን ፡ እንጂ ፡ መለኮትን ፡ አይደለም ። ከትንሣኤ ፡ በኋላ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ባሕርየ ፡ መለኮትና ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ እንዳሉት ፡ ይህ ፡ ያስረዳል ፡ ያሉትን ፡ እንመርምር ።

## መ ላ ሽ ።

፳፰/ መላክተኛው ፡ በዚህ ፡ አነጋገሩ ፡ ክርስቶስ ፡ ለቶማስ ፡ አሥረ ፡ ርግዘት ፡ ያሳየው ፡ ከአካሉ ፡ ላይ ፡ ሳይኾን ፡ ከባሕርዩ ፡ ላይ ፡ እንዳሳየው ፡ አድርጎ ፡ ተናግሯል ። ቊስል ፡ የሚገኝ ፡ ከአካል ፡ ላይ ፡ እንጂ ፡ ከባሕርይ ፡ ላይ ፡ አይደለም ፤ ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በጥይት ፡ ተመትቶ ፡ በጦር ተወግቶ ፡ ይሞታል ፡ ሲሞትም ፡ አራቱ ፡ ባሕርያት ፡ ይለያያሉ ፡ ፆ ፡ ከአራቱ ፡ ባሕርያት ፡ የነፋስ ፡ የእሳት ፡ የውኃ ፡ ባሕርይ ፡ የተለያየበት ፡ አካል ፡ በመሬትነቱ ፡ ብቻ ፡ በድን ፡ ኾኖ ፡ ይወድቃል ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የተመታው ፡ ቊስል ፡ በድን ፡ ኾኖ ፡ በወደቀው ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ይታያል ፡ እንጂ ፡ በተለያዩት ፡ ባሕርያት ፡ ላይ ፡ የሚታይ ፡ አይደለም ።

ስለዚህ ፡ ክርስቶስ ፡ ቊስሉን ፡ ለቶማስ ፡ ከባሕርዩ ፡ ላይ ፡ አሳየው ፡ በማለቱ ፡ መላክተኛው ፡ በጣም ፡ ተሳስቷል ። ክርስቶስስ ፡ ለቶማስ ፡ አሥረ ፡ ርግዘቱን ፡ ያስዳሰሰው ፡ አሥረ ፡ ቅንዋቱን ፡ ያሳየው ፡ አራቱ ፡ ባሕርያት ፡ ባልተለያዩበት ፡ መለኮት ፡ በተዋሐደው ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ባለው ፡ በሰብአዊ ፡ አካሉ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከአካሉ ፡ ለይቶ ፡ በባሕርዩ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ያሳየው ፡ አይደለም ።

ይህ ፡ ኹለት ፡ የሚያሰኝ ፡ ከኾነ ፡ ለምን ፡ ባሕርይን ፡ ብቻ ፡ ለይተው ፡ ኹለት ፡ ይላሉ ፡ እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ መልተው ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ይበሉ ፡ እንጂ ።

ኢትዮጵያውያን ፤ ካቶሊካውያን ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ ተከትለዋል ፡ የሚሉበት ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ነው ። እኛስ ፡ በማኅፀን ፡ የተዋሐደውን ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ ሰብአዊ ፡ አካልን ፡ በከዊን ፡ ከመለየቷ ፡ በቀር ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የምታደርግ ፡ መለኮታዊት ፡ ባሕርይ ፡ ያለችው ፡ አካለ ፡ ቃል ፡ ከትስብእቱ ፡ የተለየበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሌለ ፡ ተነሣ ፤ አረገ ፡ መባሉ ፡ ቅሉ ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እናምናለን ።

## ድ ራ ሲ ።

### ፪ኛ ፡ ሰውየው ፡ መልስ ፡ አጣ ፡ ስለሚሉት ።

## መ ላ ሽ ።

፳፱/ ሰውየው ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ መልስ ፡ አጣ ፡ ስለሚሉት ፡ በኢትዮጵያ ፡ የተጻፈው ፡ ታሪክ ፡ ደግሞ ፡ ካቶሊኩ ፡ ተከራካሪ ፡ መልስ ፡ አጣ ፡ ይላል ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ ተከራካሪ ፡ መልስ ፡ አጣ ፡ አይልም ። በእኛም ፡ አስተያየት ፡ ይህ ፡ አሁን ፡ የጻፍኩልዎ ፡ መልስ ፡ በኹሉ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ የጐላ ፡ ነገር ፡ ሲኾን ፡ መልስ ፡ አጣ ፡ ቢሉን ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ልንቀበለው ፡ አልቻልንም ። እንግዲህ ፡ ንግግርዎ ፡ ወገን ፡ ለማጕልመስ ፡ ብቻ ፡ የተጻፈ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አይተን ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ምርመራ ፡ እንለፍ ።

## ድ ራ ሲ ።

### ፫ኛ ፡ ስለፓድሬ ፡ ፓየዝ ፡ ንግግር ።

፴/ ፓድሬ ፡ ፓየዝ፡ንግግር ፡ እንዲያጥርልን ፡ ለዚሁ፡ሐተታ ፡ ብቻ ፡ መልስ ፡ ይስጡኝ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍጹም፡አምላክና ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ጠየቀ ።

ሲቄ ፡ ሌላ ፡ የማይረባ ፡ ነገር ፡ ቢያመጣ ፡ ንጉሡ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ አምላክና ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ መኾኑን ፡ ልትክደው ፡ ነህን ፡ ቢለው ፡ ይህስ ፡ የሚካድ ፡ አይደለም ፡ አለ ፡፡

ፓድረ ፡ ፓየዝ ፡ እንግዲያስ ፡ ለክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ የመለኮት ፡ ባሕርይና ፡ ፍጹም ፡ የሰው ፡ ባሕርይ ፡ አሉታ ፡ አለው ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ እንመርምር ፡፡

## መ ላ ሽ ፡፡

፴/ ፓድረ ፡ ፓየዝ ፡ ባነጋገሩ ፡ ኹሉ ፡ ባሕርይን ፡ እንጂ ፡ አካልን ፡ አያነሣም ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ የሚባል ፡ አካል ፡ የሌለው ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ ነውን ፡ ፍጹም ፡ ሰውስ ፡ የሚባል ፡ አካል ፡ የሌለው ፡ ባሕርየ ፡ ሰብእ ፡ ብቻ ፡ ነውን ፡፡

ፍጹም ፡ አምላክ ፡ የሚባል ፡ ሕያው ፡ ባሕርይ ፡ የኾነ ፡ ምሉእ ፡ ስፉሕ ፤ ረቂቅ ፤ አካል ፡ አይደለምን ፡ ፍጹም ፡ ሰውስ ፡ የሚባል ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ ግዙፍ ፡ አካል ፡ አይደለምን ፡ ለምን ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ ያልፈዋል ፡፡

ኹለት ፡ ማለትን ፡ ከፈለገ ፡ እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ አጕልቶ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አይልምን ፤ የጕላውን ፡ የአካልን ፡ ነገር ፡ በረቀቀው ፡ በባሕርይ ፡ እየሸፋፈነ ፡ ለምን ፡ ይናገራል ፡፡

እኛስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፤ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ነው ፡ የምንል ፡ የአምላክነትንም ፡ የሰውነትንም ፡ ሥራ ፡ ባንድ ፡ ፈቃድ ፤ ባንድ ፡ ሥልጣን ፡ ስለሠራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በየራሳቸው ፡ የቆሙ ፡ ያልተዋሐዱ ፡ በኹለትነት ፡ የሚቈጠሩ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ብለን ፡ አይደለም ፡፡ ይህንም ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ ጌታ ፡ በእኔ ፡ በኩል ፡ ካልኾነ ፡ ወደ ፡ አብ ፡ ሊመጣ ፡ የሚችል ፡ የለም ፡ እኔን ፡ ካወቃችሁኝ ፡ አብንም ፡ ባወቃችሁት ፡ ነበረ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ግን ፡ አብን ፡ አይታችሁታል ፡ አውቃችሁታል ፡ ቢላቸው ፡ ፊልጶስ ፡ የአብን ፡ ነገር ፡ መስማቱ ፡ ይበቃናል ፡ አብን ፡ አሳየን ፡ አለው ፡፡

ጌታም ፡ ይህን ፡ ያኸል ፡ ዘመን ፡ አብሬያችሁ ፡ ስኖር ፡ አላወቅኸኝምን ፡ እኔን ፡ ያየ ፡ አብን ፡ ማየቱ ፡ ነው ፡ እንዴት ፡ አሳየን ፡ ትላለህ ፡ አብ ፡ በኔ ፡ ህልው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እኔም ፡ በአብ ፡ ህልው ፡ እንደ ፡ ኾንኩ ፡ አታውቅምን ፡፡

ይህም ፡ የምነግራችሁ ፡ ቃል ፡ ከኔ ፡ የተገኘ ፡ አይደለም ፡ በኔ ፡ ህልው ፡ የኾነ ፡ አብ ፡ ይህን ፡ ሥራ ፡ ይሠራዋል ፡ እንጂ ፡፡ አብ ፡ በኔ ፡ ህልው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እኔም ፡ በአብ ፡ ህልው ፡ እንደኾንኹ ፡ እመኑ ፡ ብሎታል ፡፡

ይህን ፡ ነገር ፡ ሲናገር ፡ ባጭር ፡ ቁመት ፡ በጠባብ ፡ ደረት ፡ ተወስኖ ፡ በሰብአዊ ፡ አካል ፡ ተገልጾ ፡ በሰብአዊ ፡ አንደበት ፡ ነው ፡፡ የነገሩ ፡ ፍሬ ፡ ግን ፡ አምላክነትን ፡ እንጂ ፡ ሰውነትን ፡ አያሳይም ፡ ምሥጢሩን ፡ ብንመረምረው ፡ በከዊን ፡ ብቻ ፡ የምትለይ ፡ ከአብ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የምታደርግ ፡ ባሕርይ ፡ ያለችው ፡ አካለ ፡ ቃል ፡ በማኅፀነ ፡ ማርያም ፡ የተወለደውን ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ ሰብአዊ ፡ አካልን ፡ ገንዘብ ፡ እንዳደረገው ፡ በምንም ፡ በምን ፡ የሚለይበት ፡ ምክንያት ፡ አለመኖሩን ፡ ያስረዳናል ፡፡ ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፮-፲፩ ፡፡

በም ፡ ፲፯ ፡ በቊ ፡ ፷ም ፡ አማን ፡ አእመሩ ፡ ከመ ፡ እምኀቤከ ፡ ወፃእኩ ፡ ወአምኑ ፡ ከመ ፡ አንተ ፡ ፈነውከኒ ፡ ወአንሰ ፡ በእንቲአሆሙ ፡ እስእል ፡፡ ካንተ ፡ አካል ፡ ዘእምአካል ፡ ባሕርይ ፡ ዘእምባሕርይ ፡ እንደ ፡ ተወለድኩ ፡ አውቀዋል ፡፡ አንተ ፡ እንደላከኸኝም ፡ አምነዋል ፡፡ እኔም ፡ ስለነሱ ፡ እለምናለሁ ፡ ብሏል ፡፡ ካንተ ፡ ተወለድኩ ፡ በማለቱ ፡ ፍጹም ፡ አምላክነቱን ፡ ስለነርሱ ፡ እለምናለሁ ፡ በማለቱ ፡ ፍጹም ፡ ሰውነቱን ፡ አስረድቶናል ፡፡

እንደዚኸውም ፡ ያምላክነቱንም ፡ የሰውነቱንም ፡ ነገር ፡ አንድነትን ፡ በሚያሳይ ፡ ኹለትነትን ፡ በማያሳይ ፡ እኔ ፡ በሚል ፡ አነጋገር ፡ መናገሩ ፡ መለኮትና ፡ ትስብእት ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ፡፡

በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የተጻፈው ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምንታዌ ፡ ፍልጠት ፡ ያለበት ፡ መኾኑን ፡ የሚያመለክት ፡ በፍጹም ፡ አይገኝም ፡፡ መቸም ፡ መች ፡ ቢኾን ፡ በኹለትነት ፡ ጸንተው ፡ የሚኖሩ ፡ የአምላክነትን ፡ ሥራና ፡ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሠራቸው ፡ ኹለት ፡ ያሰኘዋል ፡ በማለት ፡ በያሰኛልና ፡ በይኾናል ፡ ብቻ ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የወሰነውን ፡ ውሳኔ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የማትቀበለው ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡፡

## ጥ ያ ቄ ።

## ፺ኛ ፡ ስለፓድሬ ፡ ፓየዝ ፡ ንግግር ።

፴፩/ ፓድሬ ፡ ፓየዝ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ አሉ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ የሉም ፡ ማለት ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ የሚፈራረስ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ በክርስቶስ ፡ የተዋሐዱ ፡ እንጂ ፡ ያልተደባለቁ ፡ ባሕርየ ፡ መለኮትና ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ በውነት ፡ የሚገኙ ፡ ከኾነ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ኹለት ፡ ሊባሉ ፡ ይቻላል ፡ አይቻልም ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ኹለት ፡ አይደለም ፡ ለማለት ፡ የፈለጋችሁ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ማን ፡ ይህ ፡ በፍጹም ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ አለውና ፡ አለ ፡ የሚሉትን ፡ እንመርምር ።

## መ ላ ሽ ።

፴፩/ አንድ ፡ አካል ፡ በማለት ፡ ተስማምተናል ። ይህም ፡ አካል ፡ በመለኮትና ፡ በትስብእት ፡ ተዋሐዶ ፡ አንድ ፡ የኾነ ፡ አካል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የመለኮት ፡ ብቻ ፡ ወይም ፡ የትስብእት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። የመለኮት ፡ ወይም ፡ የትስብእት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ያልን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ መቅረቱ ፡ ነውና ፡ ይህ ፡ አካል ፡ በመለኮትና ፡ በትስብእት ፡ ተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ የኾነ ፡ አካል ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ግድ ፡ ነው ። በላይኛው ፡ መሥመር ፡ ባሕርይ ፡ የአካል ፡ መግሪያ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ባሕርይ ፡ ያለ ፡ አካል ፡ አካልም ፡ ያለባሕርይ ፡ ሥራ ፡ ሊሠሩ ፡ የማይቻል ፡ መኾኑን ፡ መላልሰን ፡ አስረድተናል ።

እንግዲህ ፡ አካል ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ ባሕርይን ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ ከመኾን ፡ የሚከለክለው ፡ ምንድን ፡ ነው ።

የተዋሐዱ ፡ እንጂ ፡ ያልተደባለቁ ፡ በክርስቶስ ፡ የሚገኙ ፡ ባሕርየ ፡ መለኮትና ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ብቻ ፡ አይደሉም ፤ መለኮታዊ ፡ አካልም ፡ ሰብአዊ ፡ አካልም ፡ ናቸው ፡ ይህ ፡ ተዋሕዶ ፡ ባሕርያትን ፡ አንድ ፡ አያደርግም ፡ ምንታዌን ፡ ከባሕርያት ፡ አያጠፋም ፡ የሚባል ፡ ከኾነ ፡ ከአካላትም ፡ ምንታዌን ፡ አጠፋ ፡ ሊባል ፡ አይቻልምና ፡ እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ማለት ፡ ግድ ፡ ይኾናል ።

ከአካላት ፡ ምንታዌን ፡ አጥፍቶ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አሰኝቷል ፡ የሚባል ፡ ከኾነ ፡ ከባሕርያትም ፡ ምንታዌን ፡ አጥፍቶ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ያሰኛል ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አያሰኝም ።

## ጥ ያ ቄ ።

## ፹ ፡ ስለንግግሩ ፡ መረዳት ።

፴፪/ ፓድሬ ፡ ፓየዝ ፡ በተናገረው ፡ ንግግርና ፡ ባመጣቸው ፡ ማስረጃዎች ፡ ከሊቃውንቱና ፡ ከመነኰሳቱ ፡ ብዙዎቹ ፡ ከታላላቆቹ ፡ ንጉሡም ፡ ሳይቀር ፡ የካቶሊክን ፡ ትምርት ፡ እስከመቀበል ፡ ድረስ ፡ ተረዳቸው ፡ ያሉትን ፡ እንመርምር ።

## መ ላ ሽ ።

፴፪/ ይህ ፡ ክርክር ፡ ባ፲፯ ፡ ዘድንግል ፡ ዘመን ፡ የተደረገ ፡ መኾኑን ፡ አረጋግጠውልናል ፡ ያ፲፯ ፡ ዘድንግልን ፡ ታሪክ ፡ ስንመለከተው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሚሲዮናውያን ፡ ትምህርት ፡ ከፍተን ፡ ብዙ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ ካፖርቱጊዞች ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ደባልቀን ፡ እያስተማርን ፡ ለቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አገልጋይ ፡ የሚኾኑ ፡ ልጆች ፡ እናዘጋጅ ፡ የሚል ፡ አሳብ ፡ አቀረቡላቸው ።

ዐ፪ ፡ ዘድንግልም ፡ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ጉዳይ ፡ እስኪመከርበት ፡ ይቆይ ፡ አሉና ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ የሚያስተምሩ ፡ እስፓኞችና ፡ ፖርቱጊዞች ፡ እንዲላኩላቸው ፡ ወደ ፡ ሮማ ፡ ጳጳስ ፡ ክሊማንት ፡ (ቀሌምንጦስ) ወደ ፡ ተባለውና ፡ ወደ ፡ እስፓኙ ፡ ንጉሥ ፡ ፊልጶስ ፡ ወደተባለው ፡ በኒሁ ፡ በሚሲዮኖቹ ፡ አማካይነት ፡ የወዳጅነት ፡ ደብዳቤ ፡ ላኩ ።

ይልቁንም ፡ ዋናው ፡ ተስፋቸው ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የእስፓኝ ፡ መንግሥት ፡ በጣም ፡ የገነነ ፡ ኃይለኛ ፡ ስለነበረ ፡ በውስጥም ፡ በውጭም ፡ ጠላት ፡ ቢነሣብኝ ፡ ይረዳኛል ፡ ማለት ፡ ነበረ ።

ይህነኑም ፡ ተስፋቸውን ፡ ሚሲዮኖቹ ፡ በንግግራቸው ፡ ስላጸኑላቸው ፡ ሚሲዮኖቹን ፡ ወዳጅ ፡ አድርገው ፡ ለደብዳቢያቸው ፡ መልስ ፡ እየተጠባበቁ ፡ ቆዩ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ካቶሊኮቹንና ፡ ኮፕቶችን ፡ እያከራከሩ ፡ አሳባቸውን ፡ ከካቶሊኮቹ ፡ ጋራ ፡ አደረጉ ፡ ተብለው ፡ ታሙ ፤ ከጦር ፡ አለቃቸው ፡

ከደጃች ፡ ላእከ ፡ ማርያም ፡ ጋራ ፡ ተስማምተው ፡ ተዋሕዶ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ለውጠው ፡ ወደ ፡ ካቶሊክ ፡ ሃይማኖት ፡ ዞረዋል ፡ እየተባለ ፡ በቀሳውስቱም ፤ በሕዝቡም ፡ ዘንድ ፡ ተወራ ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ጳጳሱ ፡ ለዘድንግል ፡ የሚታዘዝ ፡ ገዝቻለሁ ፡ ብለው ፡ አወገዙ ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ራስ ፡ ዘሥላሴ ፡ የተባለው ፡ የጦር ፡ አዝማች ፡ የጎጃምን ፡ ሕዝብ ፡ ይዞ ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ተነሣ ፡ የቤተ ፡ ክህነትና ፡ የሃይማኖት ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ከራስ ፡ ዘሥላሴ ፡ ጋራ ፡ ኾነው ፡ ደንቢያ ፡ ውስጥ ፡ በርጫ ፡ ከሚባል ፡ ስፍራ ፡ ለጦርነት ፡ ተሰለፉ ። ፪፻ ፡ የሚሆኑ ፡ ብረት ፡ የያዙ ፡ ፖርቱጊዞችና ፡ ሚሲዮኖች ፡ ታማኝ ፡ ከኾኑ ፡ ከንጉሡ ፡ አሽከሮች ፡ ጋራ ፡ በንጉሡ፡ ጐን ፡ ተሰልፈው ፡ በፊትዎ ፡ እንሞታለን ፡ እያሉ ፡ ያደፋፍሯቸው ፡ ነበረ ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ጦርነቱ ፡ ሲጀመር ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ የነበረው ፡ እየከዳ ፡ ወደዚያ ፡ ዞረ ። ኹሉም ፡ በጀግንነት ፡ ሲዋጉ ፡ የንጉሡ ፡ ጦር ፡ አዛዥ ፡ ባንካሴ ፡ ተወግቶ ፡ ወደቀ ።

ንጉሡም ፡ የጦር ፡ አዛዣቸውን ፡ ዳጃች ፡ ላእከ ፡ ማርያምን ፡ የወጋውን ፡ ጠብቄ ፡ እወጋለሁ ፡ ብለው ፡ ሲጠባበቁ ፡ እርሳቸውንም ፡ ሌሎች ፡ በጦርና ፡ ባንካሴ ፡ ወጓቸውና ፡ ሞቱ ፡ ሲል ፡ እናገኘዋለን ። የአቶ ፡ ተክለ ፡ ጻድቅ ፡ መዝሙሮች ፡ ካ፪ ፡ ልብነ ፡ ድንግል ፡ ዐ፪ ፡ ቴዎድሮስ ፡ ተመልከት ።

ይህ ፡ ታሪክ ፡ የፓድሬ ፡ ፓየዝን ፡ ንግግር ፡ ንጉሡ ፡ ተቀበለው ፡ ያሉት ፡ እውነት ፡ ይኾናል ፡ የሚል ፡ ጥርጣሬ ፡ በተመልካች ፡ ልቡና ፡ ሳያሳይ ፡ አይቀርም ።

ከሊቃውንቱና ፡ ከመነኰሳቱ ፡ ከታላላቆችም ፡ አያሌዎቹ ፡ እስከመቀበል ፡ ድረስ ፡ ተረዱት ፡ ያሉት ፡ ቃል ፡ ግን ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ከተረዱት ፡ የንጉሣቸውንና ፡ የራሳቸውን ፡ ደም ፡ እስከ ፡ ማፍሰስ ፡ ምን ፡ አደረሳቸው ፡ አይቀበሉትም ፡ ኖሯልን ? ይህ ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ።

ስለኾነም ፡ ምንም ፡ ጊዜ ፡ ቢኾን ፡ የካቶሊክ ፡ ሰባኪዎች ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚመጡ ፡ ንጉሥንና ፡ ሕዝብን ፡ ለማለያየት ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ይህ ፡ በንጉሥ ፡ ዘድንግልና ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ የተደረገው ፡ ጦርነት ፡ እኒህ ፡ ሰባኪዎች ፡ ከመጡበት ፡ ጉዳይ ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ ፈጸሙ ፡ የሚያሰኝ፡ ነው ።

ወደ ፡ ሥር ፡ ነገራችን ፡ እንመለስ ፡

፱/ ስለሌሎች ፡ አስተያየት ።

ድ ራ ሲ ።

፴፫/ አብዛኛዎቹ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነውን ፡ በእውነት ፡ ቢታመኑበትም ፡ በአፍ ፡ በክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ አለ ፡ የሚለውን ፡ አነጋገር ፡ በመደገፍ ፡ ጸኑ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ እንመርምር ።

መ ላ ሽ ።

፴፫/ ምንም ፡ እንኳ ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነውን ፡ በእውነት ፡ ቢታመኑበት ፡ የሚለው ፡ አጠራጣሪ ፡ ቃል ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አልታመኑበትም ፡ ብዬ ፡ ከማስተባበሌ ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ በመደገፍ ፡ ጸኑ ፡ ያሉት ፡ እውነተኛ ፡ ንግግር፡ መኾኑን ፡ አረጋግጥልዎታለሁ ።

ድ ራ ሲ ።

፴፬/ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አነጋገር ፡ እውነተኛውን ፡ አሳባቸውን ፡ የሚያፈርስ ፡ ነበረ ፤ ምክንያቱም ፡ የባሕርይንና ፡ የአካልን ፡ አሳቦች ፡ ምንም ፡ ሳይለያይዋቸው ፡ በሚወራረሱ ፡ ቃሎች ፡ ይገልጿቸው ፡ ስለነበረ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የንስጥሮስን ፡ የኹለት ፡ አካላት ፡ ባህል ፡ ይክዱ ፡ ያሉ ፡ እየመሰላቸው ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ አይገኙም ፡ ሲሉ ፡ ይክዳሉ ፡ ያሉትን ፡ እንመርምር ።

መ ላ ሽ ።

፴፬/ ባሕርይና ፡ አካል ፡ የሚወራረሱበትንም ፡ የሚለያዩበትንም ፡ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ በቍ ፡ ፳፬ ፡ ለይተን ፡ አስረድተናል ፡ እንጂ ፡ ያለአገባብ ፡ የምናወራርስ ፡ አይደለንም ።

እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ያሰኛል ፡ ያልንበትንም ፡ ምክንያት ፡ በላይኛው ፡ አንቀጽ ፡ በቍ ፤ ፴፩ ፡ ለይተን ፡ አስረድተናል ፡ እንጂ ፡ አንዱን ፡ ካንዱ ፡ እያማታንና ፡ እያዘበራረቅን ፡ የምንናገር ፡ አይደለንም ።

ስለዚህ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊው ፡ ነገሩ ፡ ባይገባው ፡ ይህ ፡ አነጋገር ፡ እውነተኛውን ፡ አሳባቸውን ፡ የሚያፈርስ ፡ ነበረ ፡ እያለ ፡ ይጽፋል ፡ እንጂ ፡ ኢትዮጵያውያንስ ፤ ንግግራቸውን ፡ የሚያንጽ ፡ እንጂ ፡ የሚያፈርስ ፡ አይናገሩም ።

## ደ ራ ሲ ።

## ስለፓድሬ ፡ አማኑኤል ፡ ደልመይዳ ፡ ንግግር ።

፴፭/ ይህ ፡ ሰባኪ ፡ ሲናገር ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በአፍ ፡ የአውጣኪን ፡ የዲዮስቆሮስን ፡ ባህል ፡ ቢከተሉ ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ መኖራቸውን ፡ በመታመን ፡ ከባህሉ ፡ በደንብ ፡ የሚከተለውን ፡ ተገቢ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ስለማይቀበሉት ፡ እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከዚህ ፡ ኑፋቄ ፡ የራቁ ፡ ናቸው ፡ ሲል ፡ አሳቡን ፡ ገልጿል ፡ ያሉትን ፡ እንመርምር ።

## መ ላ ሽ ።

፴፮/ ዲዮስቆሮስና ፡ አውጣኪ ፡ በሃይማኖት ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ ማለትን ፡ እናንተ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ስታወሩ ፡ እንሰማለን ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ በባህል ፡ መስማማታቸውን ፡ አናውቅም ፤ እውነት ፡ ብለን ፡ አንቀበለውም ። ምክንያቱም ፡ የአውጣኪ ፡ ባህል ፡ ቃል ፡ የተዋሐደው ፡ ሥጋ ፡ ሕማም ፡ የማይስማው ፡ ሞት ፡ የማይስማማው ፡ ረቂቅ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ሲኾን ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ይህን ፡ የማይቀበል ፡ መኾኑን ፡ በመጽሐፉ ፡ ስለተረዳን ፡ ነው ።

ምን ፡ አለ ፡ የሚል ፡ ቢኖር ፡ በፈቃደ ፡ አቡሁ ፡ ወረደ ፤ ኀበ ፡ ማርያም ፡ ተአንገደ ፤ ወከመ ፡ ሕፃናት ፡ በከየ ፡ እንዘ ፡ ይስእል ፡ እምአጥባተ ፡ እሙ ፡ ሲሳየ ። እግዚአብሔር ፡ በሥላሴሁ ፡ እንዘ ፡ ነጋሢ ፡ ልሲሁ ፡ አርአየ ፡ ትሕትናሁ ፡ ከመ ፡ ገብር ። ሰፍሐ ፡ እደዊሁ ፡ ለሕማም ፡ ዘለሐኮ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ያግእዞ ፡ ለአዳም ፡ እምአርዑተ ፡ ኃጢአት ፡ አንዘዎ ፡ አይሁድ ፡ ወአቀምዎ ፡ ውስተ ፡ ዐውድ ፡ ለዘሎቱ ፡ ይቀውሙ ፡ ሠራዊተ ፡ መላእክት ፡ በፍርሃት ፡ ወበረዓድ ፤ ሰቀልዎ ፡ ዲበ ፡ ዕፅ ፡ ወቀነውዎ ፡ በቅንዋት ፡ ሞተ ፡ ዘኢይመውት ፡ ሞተ ፡ ከመ ፡ ያሕይዎሙ ፡ ለሙታን ፡ በከመ ፡ አሰፈዎሙ ፡ በቃለ ፡ ኪዳን ።

ባባቱ ፡ ፈቃድ ፡ ከሰማይ ፡ ወረደ ፤ ከድንግል ፡ ማርያም ፡ ተወለደ ፤ እንደሕፃናት ፡ ምግብ ፡ ሽቶ ፡ አለቀሰ ፤ በፀነቱ ፡ የሚኖር ፡ እግዚአብሔር ፡ የዘለዓለም ፡ ንጉሥ ፡ ሲኾን ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ ትሕትናውን ፡ ገለጸ ። ሰውን ፡ የፈጠረ ፡ እርሱ ፡ ሰውን ፡ ከኃጢአት ፡ ቀንበር ፡ ነፃ ፡ ያወጣው ፡ ዘንድ ፡ እጆቹን ፡ ለሕማም ፡ ዘረጋ ። የመላእክት ፡ ጭፍሮች ፡ በመፍራት ፡ በመንቀጥቀጥ ፡ በፊቱ ፡ የሚቆሙ ፡ እርሱን ፡ አይሁድ ፡ ይዘው ፡ ባደባባይ ፡ አቆሙት ። በዕንጨት ፡ ላይ ፡ ሰቀለው ፡ በችንካር ፡ ቸነከሩት ። ባም ስት ፡ ቀን ፡ ተከ·ል ፡ መጥቼ ፡ አድንሃለሁ ፡ ብሎ ፡ በአዳም ፡ የሰጣቸውን ፡ ተስፋ ፡ ለመፈጸም ፡ የማይሞት ፡ እርሱ ፡ ሞተ ፡ በማለቱ ፡ እነዮሐንስ ፡ አፈወርቅን ፡ ፤ እነቅዱስ ፡ ቄርሎስን ፤ እነአትናቴዎስን ፡ እነባስልዮስን ፡ እንጂ ፡ አውጣኪን ፡ መስሎ ፡ ስላላገኘነው ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ የዲዮስቆሮስን ፡ ባህል ፡ መከተላችን ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ያውጣኪን ፡ ባህል ፡ ተከተሉ ፡ ማለቱ ፡ ግን ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ።

በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ መኖራቸውን ፡ የምናምነው ፡ በምን ፡ ዐይነት ፡ እንደ ፡ ኾነና ፡ የማንቀበላቸው ፡ ፍሬ ፡ ነገሮች ፡ የትኞቹ ፡ እንደኾኑ ፡ ስላልተገለጸ ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ ሊሰጣቸው ፡ አልተቻለም ።

ከዚህ ፡ ኑፋቄ ፡ የራቁ ፡ ናቸው ፡ የተባልንም ፡ ከየትኛው ፡ ኑፋቄ ፡ እንደኾነ ፡ ስላልተገለጸልን ፡ ምስጋናውን ፡ ልንቀበለው ፤ ወይም ፡ ልንነቅፈው ፡ አልቻልንም ።

ምክንያቱም ፡ እኛ ፡ ርትዕት ፡ ሃይማኖት ፡ ብለን ፡ የያዝናትን ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ ሮማውያን ፡ ኑፋቄ ፡ ይሏታልና ፡ በከንቱ ፡ ውዳሴ ፡ ተጠልፈን ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ መስለን ፡ እንዳ ንገኝ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ ቀጥለው ፡ ያሉ ፡ ጽሑፎች ፡ ብዙዎች ፡ መልስ ፡ የተሰጠባቸው ፡ ስለኾኑ ፡ መልስ ፡ ያልተሰጠባቸውን ፡ ቃላት ፡ ለይተን ፡ እንጽፋለን ።

## ደ ራ ሲ ።

፴፯/ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እኛን ፡ ለማዳን ፡ ሞተ ፡ ወይ ፡ ብንላቸው ፡ አዎን ፡ ይላሉ ፡ የሞተው ፡ መለኮት ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ ትስብእት ፡ ስንላቸው ፡ ብዙዎች ፡ መለኮት ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ግማሾቹ ፡ መለኮት ፡ በማለታቸው ፡ ይቆጡባቸው ፡ ነበረ ። የሞተው ፡ ያለመለኮት ፡ ትስብእት ፡ ነው ፡ ቢሉም ፡ እንግዲያውስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ አሉት ፡ ስንላቸው ፡ የሚመልሱትን ፡ ያጡት ፡ ነበረ ፡ የሚሉትንና ፡ ንጉሡ ፡ ካቶሊኮች ፡ ባመጧቸው ፡ ምስክሮችና ፡ በንግግራቸው ፡ በጣም ፡ ተማርከ፡

የክርስቶስ ፡ ባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ሞቷል ፡ የሚለው ፡ ባህላቸው ፡ የማይሰማ ፡ መኾኑን ፡ እያስረዳ ፡ ይህ ፡ እንደምን ፡ ይሰማል ፤ የክርስቶስ ፡ የመለኮቱ ፡ ባሕርይ ፡ የሞተ ፡ ከኾነ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ናቸውና ፡ እነርሱም ፡ ሞተዋላ ፡ ሲል ፡ ሐተታ ፡ አጸናባቸው ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ እንመርምር ።

## መ ላ ሽ ።

፴፯/ በእውነቱ ፡ ዶክተር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ አስቀድመው ፡ የሀገርምን ፡ ታሪክ ፡ ተመልክተው ፡ ቢኾን ፡ መለኮት ፡ ሞተ ፡ ትስብእት ፡ ሞተ ፡ የሚለው ፡ ክርክር ፡ በዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በዕጩጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ አፈጉባኤነት ፡ የተፈጸመ ፡ መኾኑን ፡ ተረድተው ፡ ይህን ፡ ከመጻፍ ፡ በታገሡ ፡ ነበረ ፡ ታሪኩንም ፡ በ፭ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ በክፍል ፡ ፪ ፡ በቍጥር ፡ ፬ እናመጣዋለን ።

አሁንም ፡ ቢኾን ፡ የሚገባውን ፡ መልስ ፡ በሰፊው ፡ እንሰጣለን ፡ እንጂ ፡ ያለፈው ፡ ወይም ፡ ወደፊት ፡ የምናመጣው ፡ በቂ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ የምንራመደው ፡ አይደለንም ።

አሁን ፡ መርምረን ፡ መረጃ ፡ ልንሰጥባቸው ፡ የተዘጋጀንላቸው ፡ ነገሮች ፡ መለኮት ፡ ሞተ ፡ ማለትና ፡ ባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ሞተ ፡ ማለት ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ነገሮች ፡ መኾናቸውን ፡ አንዘንጋ ።

አስቀድመን ፡ መለኮት ፡ ሞተ ፡ የሚለውን ፡ እንመርምር ። አምላክ ፡ ሞተ ፡ ለማለት ፡ ጥንቱ ፡ መሠረቱ ፡ አምላክ ፡ ተፀነሰ ፡ አምላክ ፡ ተወለደ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ተፀነሰ ፡ ተወለደ ፡ ስንልም ፡ በሥጋ ፡ ነው ። በሥጋ ፡ እንደ ፡ ተፀነሰና ፡ እንደ ፡ ተወለደም ፡ ወንጌላውያን ፡ ፩ኛ ፡ ሉቃስ ፡ በም ፡ ፩ ፡ በቍ ፡ ፳፮ ፡ ወበሳድስ ፡ ወርኅ ፡ ተፈነወ ፡ ካለው ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፴፱ ። በም ፡ ፪ ፡ ከ፩ ፡ እስከ ፡ ፳ ።

ማቴ ፡ ከም ፡ ፩ ፡ ከቍ-፲፰ - ፳፭ ፡ ባለው ፡ ጽሑፋቸው ፡ አስረድተውናል ። ይልቁንም ፡ ዮሐንስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ብሎ ፡ ሥጋን ፡ የነሣ ፡ የተፀነሰ ፡ የተወለደ ፡ አንቀጽ ፡ ተቀባይ ፡ ባለቤት ፡ ቃል ፡ መኾኑን ፡ አረጋግጦ ፡ ጽፎልናል ።

ስለዚህም ፡ ዕሩቅ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ ዕሩቅ ፡ ሥጋ ፡ የማይጠራበት ፡ ቃል ፡ ሥጋን ፡ ቢዋሐድ ፡ የሚጠራበት ፡ የተዋሕዶ ፡ ስም ፡ አማኑኤል ፡ ክርስቶስ ፡ መባል ፡ ተሰጥቶታል ።

እመቤታችን ፡ ቅድስት ፡ ማርያምንም ፡ እመ ፡ አምላክ ፡ ወላዲተ ፡ አምላክ ፡ ብለን ፡ የምናከብራት ፡ አምላክን ፡ በሥጋ ፡ ስለወለደችልን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወለደች ፡ ብለን ፡ አይደለም ።

ርስዎም ፡ ራስዎ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በገጽ ፡ ፪፸፫ ፡ ለአምላክ ፡ እናት ፡ ሊያቀርቡላት ፡ ስለሚገባው ፡ አክብሮ ፡ ብለው ፡ እመ ፡ አምላክ ፡ መባሏን ፡ አረጋግጠዋል ።

እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ አነጋገር ፡ መለኮት ፡ በሥጋ ፡ ከማርያም ፡ ተወለደ ፡ በማለት፡ ተስማምተናል፡

ከዚህም ፡ ቀጥለን ፡ መለኮት ፡ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ሠራ ፡ እንመርምር ። እነሆ ፡ መለኮት ፡ በእደ ፡ ዮሐንስ ፡ በፈለገ ፡ ዮርዳኖስ ፡ መጠመቁን ፡ ማቴ ፡ በምዕ ፡ ፫ ፡ በቍ ፡ ፲፫ ፡ ማር ፡ በም ፡ ፩ ፡ በቍ ፡ ፱ ። ሉቃ ፡ በም ፡ ፫ ፡ በቍ ፡ ፳፩ ፡ ነግረውናል ።

የተጠመቀ ፡ መለኮት ፡ ለመኾኑም ፤ አብ ፡ ዝንቱ ፡ ውእቱ ፡ ወልድየ ፡ ብሎ ፡ መስክሯል ።

በሥጋ ፡ ለመኾኑም ፡ በዐጭር ፡ ቁመት ፡ በጠባብ ፡ ደረት ፡ ተወስኖ ፡ በዮሐንስ ፡ እጅ ፡ መጠመቁ ፡ በቂ ፡ መረጃ ፡ ነው ።

መጥምቀ ፡ መለኮት ፡ ዮሐንስም ፡ በቃሉ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በርግብ ፡ አምሳል ፡ ወርዶ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ሲቀመጥ ፡ አየሁ ። በውኑ ፡ እንዳጠምቅ ፡ የላከኝ ፡ እርሱ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚያጠምቅ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ሲቀመጥበት ፡ ያየኸው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ነገረኝ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አላውቀውም ፡ ነበረ ። እርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ እንደኾነ ፡ እኔ ፡ ምስክሩ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ነግሮናል ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፴፩ ።

እንደዚኹሁም ፡ በሥጋ ፡ የሞተ ፡ መለኮት ፡ መኾኑን ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወእመሰ ፡ ክርስቶስ ፡ ተሰቅለ ፡ በሥጋሁ ፡ ወአንትሙኒ ፡ ተወልተዉ ፡ በይእቲ ፡ ሕሊና ።

ክርስቶስ ፡ በሥጋው ፡ መከራ ፡ ተቀበለ ፡ እናንተም ፡ ይህችን ፡ መከራ ፡ መቀበልን ፡ እንደ ፡ ጋሻ፡ ልበሷት ፡ ብሎናል ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፬ ፡ ፩ ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ ወይደልዎ ፡ ለውእቱ ፡ ዘበእዴሁ ፡ ኵሉ ፡ ወዘእምኔሁ ፡ ኵሉ ፡ ወብዙኃነ ፡ ውሉደ ፡ አብአ ፡ ውስተ ፡ ስብሐት ፡ መልአከ ፡ ሕይወቶሙ ፡ ከመ ፡ ይፈጽም ፡ በሕማማት ።

ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ሥልጣን ፡ ለተፈጠረ ፡ ኹሉ ፡ ከእርሱ ፡ ለተገኘ ፡ ብዙ ፡ ምእመናንን ፡ ወደ ፡ ክብር፡ ሳደረስ ፡ የመዳናቸው ፡ መሠረት ፡ ለሚኾን ፡ ለርሱ ፡ ቸርነቱን ፡ በመስቀል ፡ በመሞት ፡ ሊፈጽም፡ ይገባዋል ፡ ብሎ ፡ ነግሮናል ። ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲ ።

እንግዲህ ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ሥልጣን ፡ የተፈጠረ ፤ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ የተገኘ ፡ መለኮት ፡ ቸርነቱን ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ የፈጸመ ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እናስተውል ።

ስለዚህ ፡ ይህንን ፡ የመምህሮቻችንን ፡ የሐዋርያትን ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ አድርገን ፡ መለኮት ፡ በሥጋ ፡ ተወለደ ፡ እንዳልን ፡ መለኮት ፡ በሥጋ ፡ ሞተ ፡ እንላለን ። መጻሕፍት ፡ እንዲህ ፡ አድርገው ፡ ጠንቅቀው ፡ በተዋሕዶ ፡ ስሙ ፡ ጠርተው ፡ እስመ ፡ ክርስቶስኒ ፡ ምዕረ ፡ ሞተ ፡ ወእመሰ ፡ ክርስቶስ ፡ ተሰቅለ ፡ በሥጋሁ ፡ እያሉ ፡ ከጻፉልን ፡ ከተዋሕዶ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ወጥቶ ፡ በጓደኝነት ፡ እንደሚ ኖሩ ፡ እንደ ፡ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ አድርጎ ፡ መለኮት ፡ ነው ፡ የሞተ ፡ ወይስ ፡ ትስብእት ፡ ብሎ ፡ መጠ የቅ ፡ የጠያቂው ፡ ግብዝነት ፡ ከማስገመት ፡ በቀር ፡ ተጠያቂዎችን ፡ የሚያሳፍራቸው ፡ አለመኾኑን ፡ ዐይነ ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ያመዛዝነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፴፯/ ፪ኛ ፡ ንጉሡ ፡ የመለኮቱ ፡ ባሕርይ ፡ ሞተ ፡ ካላችሁማ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ከርሱ ጋራ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ስለ ኾኑ ፡ ሞቱ ፡ ያሰኛል ፡ አላቸው ፡ የሚሉትን ፡ ቃል ፡ እንመርምር ።

## መ ላ ሽ ።

፴፯/ በቃልነቱ ፡ ከዊን ፡ ትስብእትን ፡ የተዋሐደ ፡ ፍጹም ፡ መለኮት ፡ በሥጋ ፡ ሞተ ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ መለኮት ፡ በባሕርዩ ፡ ሞተ ፡ የሚል ፡ የለም ።

መለኮት ፡ በባሕርዩ ፡ ሞተ ፡ እንዳንልስ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሞተ ፡ በሥጋ ፡ ወሐይወ ፡ በመንፈስ ። በሥጋ ፡ ሞተ ፡ በመለኮት ፡ ሕያው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ነግሮናል ፤ ፩ ፡ ጴጥ፡ ፫፡ ፲፱። ሊቁም፡ ለእመ፡ ትቤ ፡ መለኮት ፡ ሞተ ፡ አንተ ፡ ትከውን ፡ ቀታሊሆሙ ፡ ለሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ ብሎ ፡ አስጠን ቅቆናል ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መለኮተ ፡ ሥላሴ ፡ ባሕርየ ፡ ሥላሴ ፡ አንድ ፡ ከኾነ ፡ ፍጹም ፡ መለኮት ፡ በሥጋ ሞተ ፡ ከተባለ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አልሞቱም ፡ ማለት ፡ እንደምን ፡ ይቻላል ፡ የሚል ፡ ጥያቄ መቅረቡ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

ይህንን ፡ ለመረዳት ፡ ባለፈው ፡ ስለምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ስንናገር ፡ ስለከዊን ፡ የመሰልናቸውን ፡ ምሳሌዎች ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ መመርመር ፡ ይጠቅማል ።

ሥላሴን ፡ በነፋስ ፡ በፀሐይ ፤ በእሳት ፡ በቀላይ ፡ መስለናል ። ለነዚህም ፡ ለምሳሌዎች ፡ ሦስት ፤ ሦስት ፡ ከዊን ፡ እንዳላቸው ፡ አስረድተን ፡ ነበረ ፤ አሁንም ፡ ደግመን ፡ እናስረዳለን ።

## ፩ኛ ፡ ነ ፍ ስ ።

አንዲት ፡ ነፍስ ፡ ለባዊት ፡ ነባቢት ፡ ሕያዊት ፡ ትኾናለች ። በለባዊትነቷና ፡ በሕያዊትነቷ፡ ከዊን ፡ ሳይኾን ፡ በተለይ ፡ በቃልነቷ ፡ ከዊን ፡ ከሥጋ ፡ ምላስ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዳ ፡ ንባብን ፡ ትሰጣለች ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የልብነቷ ፡ ከዊንና ፡ የእስትንፋስነቷ ፡ ከዊን ፡ ከምላስ ፡ ጋራ ፡ ተዋሐዱ ፡ አይባልም ።

መለኮትም ፡ እንደዚሁ ፡ በልብነቱ ፡ ከዊን ፡ በእስትንፋስነቱ ፡ ከዊን ፡ ሳይኾን ፡ በቃልነቱ ፡ ከዊን ፡ ሥጋን ፡ ተዋሐደ ፡ ቢባል ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ ኾኑ ፡ አያሰኝም ።

## ፪ኛ ፡ ፀሐይ ።

ለፀሐይ ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ አለው ፡ ክበብ ፤ ብርሃን ፡ ዋዕይ ፡ ናቸው ። በክበቡ ፡ አብ ፤ በብርሃኑ ፡ ወልድ ፡ በዋዕዩ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመስላሉ ።

ፀሐይ ፡ በክበብነቱና ፡ በዋዕይነቱ ፡ ከዊን ፡ ሳይኾን ፡ በተለይ ፡ በብርሃንነቱ ፡ ከዊን ፡ ከብንተ ፡ ዐይን ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዶ ፡ ከጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡ ያያል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ክበብና ፡ ዋዕይ ፡ ከብንተ ፡ ዐይን ፡ ጋራ ፡ ይዋሐዳሉን ፡ አይዋሐዱም ።

እንደዚኹሉም ፡ መለኮት ፡ በልብነቱ ፡ በእስትንፋስነቱ ፡ ከዊን ፡ ሳይኾን ፡ በቃልነቱ ፡ ከዊን ፡ ትስብእትን ፡ ቢዋሐድ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ ኾኑ ፡ አያሰኝም ።

## ፫ ኛ ፡ እ ሳ ት ፡፡

ለእሳት ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ አለው ፡ ነበልባል ፤ ብርሃን ፡ ዋዕይ ፤ በነበልባሉ ፡ አብ ፤ በብርሃኑ ፡ ወልድ ፤ በዋዕዩ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመስላሉ ፡፡ እሳት ፡ በነበልባልነቱ ፡ በዋዕይነቱ ፡ ከዊን ፡ ሳይ ኾን ፡ በብርሃንነቱ ፡ ከዊን ፡ ከብንተ ፡ ዐይን ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዶ ፡ ከጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡ ያያል ፡፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ነበልባል ፡ ዋዕይ ፡ ከብንተ ፡ ዐይን ፡ ጋራ ፡ ይዋሐዳሉን ፡ አይዋሐዱም ፡፡

መለኮትም ፡ እንደዚሁ ፡ በልብነቱ ፡ በእስትንፋስነቱ ፡ ከዊን ፡ ሳይኾን ፡ በቃልነቱ ፡ ከዊን ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ ቢባል ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ ኾኑ ፡ አያሰኝም ፡፡

## ፬ ኛ ፡ ቀ ላ ይ ፡፡

ለቀላይ ፡ ፫ ፡ ከዊን ፡ አለው ፡ ስፍሐት ፡ ርጥበት ፡ ሑከት ፡፡ በስፍሐቱ ፡ አብ ፤ በርጥበቱ ፡ ወልድ በሑከቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመስላሉ ፡፡

ሰው ፡ ከባሕር ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ከአካል ፡ ላይ ፡ የሚገኝ ፡ ርጥበት ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ስፍሐትና ፡ ሑከትን ከአካል ፡ ላይ ፡ ሊገኝ ፡ አይቻልም ፡፡

እንደዚኹውም ፡ መለኮት ፡ በቃልነቱ ፡ ከዊን ፡ ትስብእትን ፡ ቢዋሐድ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ ኾኑ ፡ አያሰኝም ፡፡

እነሆ ፡ ሦስት ፡ ከዊን ፡ ያለው ፡ መለኮተ ፡ ሥላሴ ፤ ባሕርየ ፡ ሥላሴ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ በከዊን ፡ ሦስት ፡ የሚኾን ፡ ስለኾነ ፡ በልብነቱና ፡ በእስትንፋስነቱ ፡ ከዊን ፡ ሳይኾን ፡ በተለየ ፡ በቃልነቱ ከዊን ብቻ ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ ሥጋ ፡ ቢለብስ ፡ በልብነቱና ፡ በቃልነቱ ፡ ከዊን ፡ ያሉ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ ኾኑ ፡ አለማሰኘቱን ፡ በቂ ፡ በቂ ፡ የኾኑ ፡ ምሳሌዎች ፡ አምጥተን ፡ አስረድተናል ፡፡

እንግዲህ ፡ በቃልነቱ ፡ ከዊን ፡ ሰው ፡ የኾነ ፡ ሥጋን ፡ የለበሰ ፡ ወልድ ፡ በሥጋ ፡ ሞተ ፡ ቢባል ፡ በልብነትና ፡ በእስትንፋስነት ፡ ከዊን ፡ ያሉ ፡ ሥጋን ፡ ያልተዋሐዱ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሞቱ ፡ የማያሰኝ ፡ መኾኑን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ በግልጽ ፡ ሊረዳው ፡ ችሏል ፡፡

## ደ ራ ሲ ፡፡

፴፰/ መልእክተኞችና ፡ ኢትዮጵያውያኖቹ ፡ ያደርጉት ፡ የነበረው ፡ ክርክር ፡ የወዳጆች ፡ ጭውውት ፡ ይመስል ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ግጭት ፡ አይመስልም ፡ ነበረ ፡፡ ኢትዮጵያውያኖቹ ፡ መላክተኞችን ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ መምህራን ፡ ቈጥረዋቸው ፡ ሊጠይቋቸውና ፡ ሊያዳምጧቸው ፡ ወደነርሱ ፡ ይመጡ ፡ ነበረ ፡ ያሉትን ፡ እንመርምር ፡፡

## መ ላ ሽ ፡፡

፴፰/ የኢትዮጵያን ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ ስንመለከተው ፡ ባዬ ፡ ዘድንግል ፡ ጊዜ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ንጉሡን ፡ ሳይቀር ፡ ከሕዝቡ ፡ አለያይተው ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ እንዳፋሰሱ ፡ ንጉሡም ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ በጦርነት ፡ እንደሞቱ ፡ ተጽፎ ፡ እናገኛለን ፡፡

ባዬ ፡ ሱስንዮስም ፡ ዘመን ፡ ሮማውያን ፡ በሰባኪነት ፡ ገብተው ፡ የብዙ ፡ ሰው ፡ ደም ፡ ማፍሰሳቸውን ፡ ወበውእቱ ፡ ዕለት ፡ እለ ፡ ኮኑ ፡ ስምዐ ፡ እምሠራዊተ ፡ ዮልዮስ ፡ ፻ ፡ ወ፲፻ ፡ ፸ወ፩ ፡ ነፍሳት ፡ ወዕለተ ፡ ዕረፍቶሙ ፡ አመ ፡ ፯ ፡ ለግንቦት ፡፡

በዚያ ፡ ቀን ፡ ከዮልዮስ ፡ ሠራዊት ፡ ስለሃይማኖታቸው ፡ ብለው ፡ በሰማዕትነት ፡ የሞቱ ፡ ፩ሺ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ አምስት ፡ ናቸው ፡ ይህም ፡ የተደረገ ፡ ጸዳ ፡ ላይ ፡ ነው ፡፡

ወበውእቱ ፡ ዕለት ፡ እለ ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ ፪፻ ፡ ፲፴ወ፱ ፡ ወዕለተ ፡ ዕረፍቶሙ ፡ አመ ፡ ፲ ፡ ወ፱ ፡ ለጥቅምት ፡፡

በዚህ ፡ ቀን ፡ በሰማዕትነት ፡ የሞቱት ፡ ኹለት ፡ እልፍ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዘጠኝ ፡ ናቸው ፡ ቀኑም ፡ ጥቅምት ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ነው ፡ ይህም ፡ የተደረገው ፡ ጎጃም ፡ ዳሞት ፡ ላይ ፡ ነው ፡፡
ወበውእቱ ፡ ዕለት ፡ አመ ፡ ፳ኑ ፡ ለግንቦት ፡ እለ ፡ ኮኑ ፡ ሰማዕተ ፡ ፻ ፡ ወ፳፮ ፡፡

በግንቦት ፡ በ፳ ፡ ቀን ፡ እልፍ ፡ ከኹለት ፡ ሺ ፡ ሰዎች ፡ ሰማዕታት ፡ ኾኑ ፡ ይህም ፡ የተደረገ ፡ ሸዋ ፡ ወግዳ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ታሪክ ፡ እናገኛለን ፡፡

ምሥጢረ ፡ ሃይማኖት ፡ የተባለ ፡ የንእባ ፡ ዝክሬን ፡ መጽሐፍ ፡ ተመልከት ።

እርስዎ ፡ በዚሀ ፡ መጽሐፍዎ ፡ በገጽ ፡ ፻፺፭ ፡ የጠቀሱት ፡ ሰላም ፡ አልብነ ፡ ምስለ ፡ ሰብእ ፡ ሮሜ፡ ወለሰብእ ፡ ሮሜ ፡ ምስሌነ ፡ ኢሀለዎሙ ፡ ሰላም ፡ የሚለውም ፡ መወድስ ፡ ቅኔ ፡ የተደረሰ ፡ በዚያው፡ ዘመን ፡ ነው ።

ስንኳንስ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ደም ፡ መፋሰስ ፡ በነበረበት ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ ተስማምቶ ፡ ኹሉም ፡ እንደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ በየወደደው ፡ ይኑር ፡ በሃይማኖት ፡ ምክንያት ፡ መከራከር ፡ መጨቃ ጨቅ ፡ ይቅር ፡ ብሎ ፡ በወሰነበት ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ በፍቅር ፡ የሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ ለመረዳት ፡ ወደካቶሊካውያን ፡ ዘንድ ፡ የሚሔድ ፡ ኦርቶዶክሳዊ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ውስጥ ፡ አይገኝም ።

ይኸውም ፡ ሊታወቅ ፡ አሁን ፡ ባለንበት ፡ በ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ/ም ፡ በጐንደር ፡ ያሉ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሠርተው ፡ በሚያከብሩበት ፡ ቀን ፡ የጐንደር ፡ ሕዝብና ፡ ካህናቱን ፡ ሊቃውንቱን ፡ ጠሩ ፡ የመጥሪያውም ፡ ወረቀት ፡ ለክቡር ፡ ----የማክበር ፡ ሰላምታችንን ፡ እናቀርባለን ፡ በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መልካም ፡ ፈቃድ ፡ አልጋ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ በተሰጠን ፡ ቦታ ፡ የተሠራውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ቤት ፡ ጥር ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ/ም ፡ ስለምናስመርቅ ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ልክ ፡ በ፯ ፡ ሰዓት ፡ መጥተው ፡ የደስታችን ፡ ተካፋይ ፡ በመኾን ፡ ምሳ ፡ እንዲጋበዙልን ፡ በማክበር ፡ ጠር ተንዎታል ። ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ካንዳንድ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ካህናት ፡ ጋራ ፡ ኾነው ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ በማኻላችን ፡ የሚገኙ ፡ መኾናቸውን ፡ ስንገልጽ ፡ ደስታ ፡ ይሰማናል ። የጐንደር ፡ ካቶ ሊክ ፡ ማኅበር ፡ ጥር ፡ ፲ ፡ ፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የሚል ፡ ነው ።

አርቆ ፡ ተመልካቾችና ፡ አስተዋዮች ፡ የኾኑ ፡ የጐንደር ፡ ሊቃውንትና ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ ድሮ ፡ የፈሰሰውን ፡ ያባቶቻቸውን ፡ ደም ፡ ካለመዘንጋታቸውም ፡ በላይ ፡ ይህ ፡ ጥሪ ፡ ዛሬም ፡ የተሰበሰበውን ፡ ሕዝብ ፡ በፎቶግራፍ ፡ አንሥቶ ፡ የጐንደር ፡ ሕዝብ ፡ የካቶሊክን ፡ ሃይማኖት ፡ ተቀበለ ፡ ብሎ ፡ ወደሮ ማና ፡ ወደ ፡ ሌሎችም ፡ አገሮች ፡ ለመላክ ። ኋላም ፡ ለሚነሡ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ አባ ፡ አየለ ፡ ዐዲ ፡ ካሌብ ፡ ካቶሊክ ፡ ነበሩ ፤ ፀጋቱ ፡ ቅዱስን ፡ ካቶሊካውያን ፡ ነበሩ ፡ እያሉ ፡ ለሚጽፉት ፡ መሠረተ ፡ ቢስ ፡ ወሬ ፡ ማዳበሪያ ፡ እንዲኾን ፡ የተዘጋጀ ፡ ዘዴ ፡ መኾኑን ፡ በመገንዘብ ፡ ተማምለና ፡ ተገ ዛዝቶ ፡ ሳይሔድላቸው ፡ ቀረ ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ባለቤት ፡ መ ፡ ብ ፡ አ ፡ ለጐንደሮች ፡ የሚከተለውን ፡ መወ ድስ ፡ አበረከተ ።

እንትኩ ፡ በለሰ ፡ እመ ፡ በላዕክሙ ፡ ወተጋባእክሙ ፡ ደርገ ፡ ኀበ ፡ ሀለወ ፡ ገደላ ።

አንበርተ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ሊቅ ፡ ሊቃውንተ ፡ ጐንደር ፡ ገሊላ ። እሞትክሙ ፡ ሞተ ፡ ዘኢዮኤል ፡ ወእምየብሰት ፡ እስከ ፡ ፍጻሜነ ፡ ዜናክሙ ፡ ሰግላ ።

በሊዐ ፡ እክለ ፡ ባዕድ ፡ እስመ ፡ ውእቱ ፤
ዘበርእስ ፡ ነቢይ ፡ አብቆለ ፡ እፈ ፡ አንበሳ ፡ ሐቅል ፡ አሜከላ ።
ማዕዳኒ ፡ እንዘ ፡ ንወር ፡ በትፋዐ ፡ ጽልዕ ፡ መሐላ ።
በዐልተ ፡ በለስ ፡ እፎኑመ ፡ ጸውዐተክሙ ፡ ለበዐላ ።
ይገብሩኑ ፡ ኅቡረ ፡ በዓለ ፡ ሐሜት ፡ ወተድላ ።
ደዋርሀ ፡ (አርጋብ ፡ ) ምስለ ፡ አንቄ ፡ ወበግዕ ፡ ምስለ ፡ ተኵላ ።
የኢትዮጵያውያንና ፡ የሮማውያን ፡ መለያየት ፡ እስከዚሀ ፡ የደረሰ ፡ ሲኾን ፡ በዚሀ ፡ ቍጥር ፡ መልክ ተኞችና ፡ ኢትዮጵያውያኖች ፡ ያደርጉት ፡ የነበረው ፡ ክርክር ፡ የወዳጆች ፡ ጫውውት ፡ ይመስል ፡ ነበረ ፡ ያሉት ፡ ፍጹም ፡ ውሸት ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፩፱/ አንድ ፡ መነኩሴ ፡ ፓድሬ ፡ ፓየዝን ፡ ስለምንድን ፡ ነው ፡ ለክርስቶስ ፡ የመለኮትና ፡ የት ስብእት ፡ ኹለት ፡ ፈቃድ ፤ አሉት ፡ ብላችሁ ፡ የምታምኑ ፡ የትስብእትም ፤ ባሕርይ ፡ ከመለኮቱ ፡ ባሕርይ ፡ እኩል ፡ አይደለም ፡ እያላችሁ ፡ የምታስተምሩ ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ።

ፓድሬ ፡ ፓየዝም ፡ ክርስቶስ ፡ ራሱ ፡ በጌቴሴማኒ ፡ አትክልት ፡ ውስጥ ፡ ዘለዓለማዊ ፡ አባቱን ፡ ሲለምን ፡ ያንተው ፡ እንጂ ፡ የኔ ፡ ፈቃድ ፡ አይኹን ፡ ሲል ፤ እንዲሁም ፡ አብ ፡ ከኔ ፡ ይበልጣል ፡ ሲል ፡ በግልጥ ፡ ስላስተማረን ፡ ነው ፡ ሲል ፡ መለሰለት ። ሉቃ ፡ ፳፪ ፡ ፵፪ ። ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፳፰ ።

መነኩሴውም ፡ ክርስቶስ ፡ ይህን ፡ ማለቱ ፡ ስለትሕትና ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ ፈቃድ ፡ ኖሮት ፡ አይደለም ። ባሕርየ ፡ ትስብእትም ፡ ከባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ጋራ ፡ እኩል ፡ ያልኾነ ፡ ኾኖ ፡ አይደለም፡አለ።

ፓድረ ፡ ፓየዝ ፡ እንዲህ ፡ የኋላ ፡ ንግግር ፡ ትርጉም ፡ እንደማያስፈልገው ፡ ክርስቶስም ፡ ስለ ፡ ትሕትና ፡ ብቻ ፡ ብሎ ፡ ያልኾነውን ፡ ሊናገር ፡ ይቻል ፡ እንዳልነበረ ፡ እስረዳው ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ እንመርምር ።

## መ ላ ሽ ።

፴፱/ ይህ ፡ አነጋገር ፡ ትክ ፡ ብሎ ፡ ሲመለከቱት ፡ በፈቃድ ፡ ልዩ ፡ ናቸው ፡ የተባሉ ፡ ትስብእትና ፡ መለኮት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾኑ ፡ ሥላሴም ፡ በፈቃድ ፡ ልዩ ፡ ናቸው ፡ ወደ ፡ ማለትና ፡ ሞቱም ፡ በፈቃዱ ፡ ሳይኾን ፡ በአባቱ ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ በግድ ፡ ሞተ ፡ ወደ ፡ ማለት ፡ የሚያደርስ ፡ ንግግር ፡ ነው ።

ለዚህ ፡ መልስ ፡ ከመስጠቴ ፡ አስቀድሞ ፡ አንድ ፡ ጥያቄ ፡ ለማቅረብ ፡ እፈቅዳለሁ ። እነሆ ፡ጌታ ፡ በምኵራብ ፡ ሲያስተምር ፡ ሰምተው ፡ አይሁድ ፡ መጽሐፍን ፡ ያስተማረው ፡ ማንም ፡ ሳይኖር ፡ ይኽ መጽሐፍን ፡ እንዴት ፡ ያውቃል ፡ ቢሉት ፡ የማስተምራት ፡ ትምህርት ፡ የላከኝ ፡ የአብ ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ የኔ ፡ አይደለችም ፡ ብሏል ።

እንዲህ ፡ የኋላው ፡ ንግግር ፡ ትርጉም ፡ የማያስፈልገው ፡ ከኾነ ፡ ወንጌል ፡ የአብ ፡ ሕግ ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ የክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ አይደለችም ፡ ከማለት ፡ የሚያደርስ ፡ መኾኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

ደግሞ ፡ በሌላ ፡ አንቀጽ ፡ ከናንተ ፡ አስቀድመው ፡ ለነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ነፍስ ፡ አትግደሉ ፡ የተባለውን ፡ ሰምታችሁ ፡ ነበረ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ወንድሙን ፡ በከንቱ ፡ ያሳዘነ ፡ ሰው ፡ ኃጥእ ፡ ተብሎ ፡ ይፈረድበታል ፡ እላችኋለሁ ፡ እያለ ፡ በሰፊው ፡ ራሱን ፡ ባለቤት ፡ አድርጎ ፡ ሲናገር ፡ እናገኘዋለን ።

በዚህ ፡ አነጋገር ፡ እንደ ፡ ዐበይት ፡ ነቢያት ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ሳይል ፤ እንደ ፡ ደቂቀ ፡ ነቢያትም ፡ ሙሴ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ኢሳይያስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ሳይል ፡ ራሱን ፡ ባለቤት ፡ አድርጎ ፡ ተናግሯል ። ይህ ፡ አነጋገር ፡ ትርጉም ፡ የማያስፈልገው ፡ ከኾነ ፡ ወንጌልን ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ የሠራት ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ የአብ ፡ ሕግ ፡ እንዳይደለች ፡ ወደ ፡ ማሰብ ፡ ያደርሰናል ።

፫ኛም ፡ በሌላ ፡ አንቀጽ ፡ ወበዝኍ ፡ ሕዝብ ፡ በትምህርተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። ግብ ፡ ሐዋ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፴፪ ።

ሕዝቡ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ትምህርት ፡ በዙ ፡ የሚል ፡ ንባብ ፡ እናገኛለን ። ይኸም ፡ ንባብ ፡ ትርጕም ፡ የማያስፈልገው ፡ ከኾነ ፡ ወንጌል ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ትምህርት ፡ ብቻ ፡ እንደኾነች ፡ ያመለክተናል ።

እንግዲህ ፡ እኒኽን ፡ ንባቦች ፡ የሚያስማማቸውን ፡ መንገድ ፡ ተመልከተን ፡ ካላስማማናቸው ፡ ምሥጢረ ፡ ሥላሴም ፡ ምሥጢረ ፡ ሥጋዌም ፡ ከንቱ ፡ መኾኑ ፡ ነው ።

ይህንን ፡ ለማስማማት ፡ የፈለግን ፡ እንደኾነ ፡ ዮሐ ፡ ም ፡ ፲፬ ፡ ቍ ፡ ፳፫ ፡ ብንመለከት ፡ ዘያፈቅረኒ ፡ ይዕቀብ ፡ ቃልየ ፡ ወያፈቅሮ ፡ አቡየ ፤ ወንመጽእ ፡ አነ ፡ ወአቡየ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወንገብር ፡ ምዕራፈ ፡ ኀቤሁ ። ወዘሰ ፡ ኢያፈቅረኒ ፡ ኢየዐቅብ ፡ ቃልየ ፡ ወዝኒ ፡ ቃል ፡ ዘትሰምዑ ፡ ኢኮነ ፡ ቃለ ፡ ዚአየ ፡ አላ ፡ ቃሉ ፡ ውእቱ ፡ ለአብ ፡ ለዘፈነወኒ ፡ ወዘንተ ፡ ነገርኩክሙ ፡ እንዘ ፡ ሀሎኩ ፡ ምስሌክሙ ። ወባሕቱ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ መንፈሰ ፡ ጽድቅ ፡ ዘይፌኑ ፡ አብ ፡ በስምየ ፡ ውእቱ ፡ ይሜህረክሙ ፡ ኵሎ ፡ ወያዜክረክሙ ፡ ኵሎ ፡ ዘነገርኩክሙ ፡ አነ ።

እኔን ፡ የሚወደኝ ፡ ቃሌን ፡ ይጠብቅ ፡ አባቴ ፡ ይወደዋል ፡ እኔም ፡ አባቴም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ መጥተን ፡ እናድርበታለን ። ይህ ፡ የምትሰሙት ፡ ቃል ፡ የላከኝ ፡ የአብ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የኔ ፡ ቃል ፡ አይደለም ። ከናንተ ፡ ጋራ ፡ ሳለሁ ፡ ይኽን ፡ ነገርኋችሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ በኔ ፡ ስም ፡ አብ ፡ የሚልከው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እርሱ ፡ ኹሉን ፡ ያስተምራችኋል ፡ የነገርኋችሁን ፡ ኹሉ ፡ ያሳስባችኋል ፡ የሚል ፡ ንባብ ፡ እናገኛለን ።

ይህንንም ፡ ወደ ፡ ምሥጢሩ ፡ ገባ ፡ ብለን ፡ ብንመረምር ፡ ይህ ፡ የምትሰሙት ፡ የላከኝ ፡ የአብ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አብን ፡ ባለቤት ፡ አድርጎ ፡ ቢናገር ።

ይህን ፡ ነገርኋችሁ ፡ እኔን ፡ የሚወድ ፡ ቃሌን ፡ ይጠብቅ ፡ ብሎ ፡ ራሱን ፡ ባለቤት ፡ አድርጎ ፡ ቢናገር ።

ጳራቅሊጦስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ያስተምራችኋል ፡ ኹሉን ፡ ያሳስባችኋል ፡ ብሎ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ባለቤት ፡ አድርጎ ፡ ቢናገር ፡ ትምርቲቱ ፡ አንዲት ፡ ሕገ ፡ ወንጌል ፡ ብቻ ፡ ናት ።

በዚህ ፡ ንባብ ፡ ወንጌል ፡ የምስቱም ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ እንረዳበታለን ፡ እንጂ ፡ አብ ፡ ያስተማረው ፡ ሌላ ፡ ወልድ ፡ ያስተማረው ፡ ሌላ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያስተማረው ፡ ሌላ ፡ ነው ፡ የምንል ፡ አይደለንም ።

እንግዲህ ፡ ያንተ ፡ ፈቃድ ፡ እንጂ ፡ የኔ ፡ ፈቃድ ፡ አይኹን ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ሰባኪው ፡ የጠቀሰውን ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ነው ።

በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ፈቃድከ ፡ ይኩን ፡ ወአኮ ፡ ፈቃደ ፡ ዚአየ ፡ ቢል ፡ ደግሞ ፡ በሌላው ፡ አንቀጽ ፡ ነፍሴን ፡ እኔ ፡ በፈቃዴ ፡ እለያታለሁ ፡ እንጂ ፡ ሊቀማኝ ፡ የሚችል ፡ የለም ፡ ነፍሴን ፡ ከሥጋዬ ፡ እለያት ፡ ዘንድ ፡ ደግሞኤም ፡ አሥነሣት ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ አለኝ ፡ ሲል ፡ እናገኘዋለን ።

እንግዲህ ፡ የአብ ፡ ፈቃዱ ፡ ልጁን ፡ ለአዳም ፡ ቤዛ ፡ አድርጎ ፡ መስጠት ፡ እንደኾነ ፡ የወልድም ፡ ፈቃድ ፡ ራሱን ፡ ለአዳም ፡ ቤዛ ፡ አድርጎ ፡ ለሕማም ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ መስጠት ፡ መኾኑን ፡ ከተረዳን ፡ በፈቃድ ፡ አንድ ፡ ከማለት ፡ ወጥተን ፡ በፈቃድ ፡ ልዩ ፡ ናቸው ፡ ልንል ፡ እንዴት ፡ እንችላለን ፡ አንችልም ።

አብ ፡ የዐብየኒ ፡ ብሏል ፡ ሲሉትም ፡ በሥልጣን ፡ አንድ ፡ መኾናቸውን ፡ ሲያስረዳ ፡ አብ ፡ ሙታንን ፡ እንዲያሥነሣቸው ፡ ወልድም ፡ የወደደውን ፡ ያድናል ፡ ሥልጣኑን ፡ ኹሉ ፡ ለልጁ ፡ ሰጥቶታል ፡ እንጂ ፡ አብ ፡ በማንም ፡ በማን ፡ አይፈርድም ፡ ሲል ፡ እናገኛለን ። ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፳፩ ።

መለኮትና ፡ ትስብእትነት ፡ በፈቃድ ፡ ልዩ ፡ ናቸው ፡ ስለሚሉት ።

ያ ፡ ለምጻሙ ፡ ሰው ፡ መጥቶ ፡ አቤቱ ፡ ከወደድክስ ፡ ከለምጽ ፡ ልታነጻኝ ፡ ትችላለህ ፡ ብሎ ፡ ሰገደለት ። ጌታም ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ ዳሰሰውና ፡ ፈቅጃለሁ ፡ ንጻ ፡ ዳን ፡ አለው ፡ ከለምጹ ፡ ነጻ ፡ ይላል ፡ ማቴ ፡ ፰ ፡ ፩-፭ ።

ይህ ፡ ለምጻም ፡ ከፈቀድከ ፡ ልታነጻኝ ፡ ትችላለህ ፡ ብሎ ፡ የሰገደለት ፡ ባጭር ፡ ቁመት ፡ በጠባብ ፡ ደረት ፡ ተወስኖ ፡ በግዙፍ ፡ የሚያየውን ፡ ሰብአዊ ፡ አካል ፡ ነው ።

እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ የዳሰሰውና ፡ ፈቅጃለሁ ፡ ዳን ፡ ያለውና ፡ ያነጻውም ፡ የኸው ፡ ገዝፎ ፡ የሚታየው ፡ ሰብአዊ ፡ አካል ፡ ነው ።

መለኮት ፡ ግን ፡ ምሉእ ፡ ስፉሕ ፡ ረቂቅ ፡ ስለኾነ ፡ ሊያየው ፡ ሊነጋገረው ፡ አይችልም ። እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ፈቃድ ፡ የማን ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ ይሉታል ።

የትስብእት ፡ ብቻ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ እንዳይሉ ፡ ለትስብእት ፡ ብቻ ፡ ለዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ይህን ፡ ያኸል ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ።

የመለኮት ፡ ብቻ ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ እንዳይሉ ፡ ፈቀድኩ ፡ ንጻሕ ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ሰብአዊ ፡ አንደበት ፡ ነው ፡ የዳሰሰውም ፡ ሰብአዊ ፡ እጅ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ምሉእ ፡ ስፉሕ ፡ ረቂቅ ፡ መለኮት ፡ ውሱን ፡ ግዙፍ ፡ ሥጋን ፡ ተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኾኖ ፡ ባንድ ፡ ፈቃድ ፡ ባንድ፡ሥምረት ፡ የአምላክነትንም ፡ የሰውነትንም ፡ ሥራ ፡ እንደሠራ ፡ እናምናለን ፡ እንጂ ፡ ከመጻሕፍት ፡ ቃል ፡ ወጥተን ፡ ልብወለድ ፡ አነጋገር ፡ መለኮትና ፡ ትስብእት ፡ ኹለት ፡ ፈቃድ ፡ ናቸው ፡ ብንል ፡ ነገራችን ፡ ኹሉ ፡ ፈራሽ ፡ መኾኑን ፡ እንገነዘብ ።

## ደ ራ ሲ ።

፱/ እስመ ፡ ውእቱ ፡ አብ ፡ የዐብየኒ ፡ የሚለውን ፡ እንመርምር ።

## መ ላ ሽ ።

፱/ ይህን ፡ የተናገረ ፡ የመጣለትን ፡ ጽዋዐ ፡ ሞት ፡ ለመቀበል ፡ በሚዘጋጅበት ፡ በምሴተ ፡ ኀሙስ፡ነው ። እንዲህም ፡ ማለቱ ፡ በመለኮቱ ፡ ሕማም ፡ ሞት ፡ የሌለበት ፡ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ ሕማምን ፡ ሞትን ፡ ሲቀበል ፡ በአብ ፡ ሕማም ፡ ሞት ፡ የሌለበት ፡ ስለኾነ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሌላ ውስ ፡ ካባቱ ፡ የሚያንስበት ፡ ምክንያት ፡ አለመኖሩን ፡ አነ ፡ ወአብ ፡ ፩ ፡ ንሕነ ፡ ብሎ ፡ ነግሮናል ።

ይልቁንም ፡ አብ ፡ የዐብየኒ ፡ ካለው ፡ አነጋገር ፡ የበለጠ ፡ የሚያስገርም ፡ አነጋገር ፡ ቅዱስ ፡ ዳዊት፡ ሕቀ ፡ አሕጸጽኮ ፡ እመላእክቲከ ።

ከመላእክት ፡ ጥቂት ፡ አሳንስከው ፡ ብሏል ።

ይህም ፡ ትንቢት፡ ስለ፡ክርስቶስ ፡ የተነገረ ፡ መኾኑን ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በዕብራውያን ፡ ከታቦ ሰውን ፡ በቸርነትህ ፡ አስበህ ፡ በልጅህ ፡ ተዋሕዶ፡ ትጐበኘው ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ ምንድን ፡ ነው ። ሕማምን ፡ ሞትን ፡ ሰጥተህ ፡ ከመላእክት ፡ ጥቂት ፡ አሳንስከው ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ መሰከረ ፡ ብሎ ጠቅሶ ፡ ከመላእክት ፡ ጥቂት ፡ አሳንስከው ፡ ማለቱ ፡ ትንሣኤን ፡ ዕርገትን ፡ ባስከተለ ፡ በሕማሙ በሞቱ ፡ ከመላእክት ፡ ጥቂት ፡ ስላነሰ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እናውቃለን ፡ ብሎ ፡ ወስዶታል ።

ይህንንም ፡ የጳውሎስን ፡ ቃል ፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ለመኑ ፡ ይደሉ ፡ ሥርዓተ ፡ ሑጸጼ ፡ ሕቀ ፡ እኮኑ ፡ ለባሕቲቱ ፡ ለዘነበረ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል ፡ ሠሉስ ፡ መዋዕለ ፡ ህየንቴነ ፡ ለሙሱናን ።

ሙስና ፡ መቃብር ፡ ለሚገባን ፡ ለእኛ ፡ ሙስና ፡ መቃብርን ፡ ለማጥፋት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ ፫፡ ሌሊት ፡ ፫ ፡ መዓልት ፡ ሳደረ ፡ ለርሱ ፡ ብቻ ፡ ይገባል ፡ እንጂ ፡ ጥቂት ፡ አሳንስከው፡ መባል ፡ ለማን ፡ ይገባል ፡ ብሎ ፡ ተርጕሞታል ፡ ድር ፡ ፱ ።

የክርስቶስ ፡ ሕማሙ ፡ ሞቱ ፡ ለእኛ ፡ ክብር ፡ ስብሐት ፡ መባል ፡ የሚገባው ፡ መኾኑንም ፡ ወከመ ፡ ይሰመይ ፡ ሕማማተ ፡ መስቀል ፡ ክብረ ፡ ወስብሐተ ፡ ስማዕ ፡ ዘይቤ ፡ እግዚእነ ፡ ናሁ ፡ በጽሐ ፡ ከመ ፡ ይሰባሕ ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ወእግዚአብሔርኒ ፡ ይሴባሕ ፡ ቦቱ ፡ ያለውን ፡ ንባብ ፡ ከቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ ጠቅሶ ፡ አስረድቷል ። ዮሐ ፡ ፲፪ ፡ ፳፫ ።

አብ ፡ የዐብየኒ ፡ ያለበት ፡ ምሥጢሩ ፡ ይህ ፡ መኾኑን ፡ እነሆ ፡ በበቂ ፡ መረጃ ፡ ተረድተናል ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ አብ ፡ የዐብየኒ ፡ ያለ ፡ ክርስቶስ ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፡ ዕሩየ ፡ መንበር ፡ መኾኑን ፡ ሲያስረዳ ፡ እነ ፡ ወአብ ፡ ፩ ፡ ንሕነ ፡ እነ ፡ በአብ ፡ ወአብ ፡ ብየ ፡ ብሏል ።

እነዚህን ፡ ቃላት ፡ ከላይ ፡ አርእስታቸውን ፡ ከታች ፡ ኅዳጋቸውን ፡ ተመልክተን ፡ ምሥጢራቸውን ፡ በየረድፉ ፡ ተንትነን ፡ መረዳት ፡ አቅቶን ፡ አብ ፡ የዐብየኒ ፡ ያለ ፡ ትስብእት ፡ ነው ። እነ ፡ ወአብ ፡ ፩ ፡ ንሕነ ፡ ያለ ፡ መለኮት ፡ ነው ፡ እያልን ፡ ከመጻሕፍት ፡ ባልተገኘ ፡ በልብ ፡ ወለድ ፡ ንግግር ፡ አንድ ፡ ክርስቶስን ፡ ብንከፋፍለው ፡ ትምህርታችንም ፡ ሃይማኖታችንም ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ኾኖ ፡ መቅረቱን ፡ በመገንዘብ ፡ ያ ፡ መነኩሴ ፡ እንዲህማ ፡ ከኾነ ፡ የመለኮቱ ፡ ባሕርይ አንዱን ፡ ሲፈልግ ፡ የትስብእቱ ፡ ባሕርይ ፡ ሌላውን ፡ መፈለጉ ፡ ነው ፡ አንዱ ፡ ክርስቶስ ፡ ሊከፋፈል ፡ ነዋ ፡ ብሎ ፡ መቃወሙ ፡ የሚገባ ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፵፩/ መላከተኛው ፡ ኹለቱ ፡ ፈቃዶች ፡ እኮ ፡ አልተጣሉም ፡ መቸውንም ፡ አይጣሉም ፡ የትስብእቱ ፡ ባሕርይ ፡ ለመለኮቱ ፡ ባሕርይ ፡ መቸውንም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተገዛና ፡ እንደ ፡ ታዘዘ ፡ ነው፡ አሉ።

መነኩሴው ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ እኩል ፡ ናቸው ፡ ሲል ፡ ጠንክሮ ፡ ይቃወም ፡ ስለነበረ ፡ ሰባኪው ፡ የመነኩሴውን ፡ ባህል ፡ የሚያፈርሱ ፡ ማስረጃዎችንና ፡ ምስክሮችን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍትና ፡ ከቅዱሳን ፡ አበውም ፡ እየጠቀሰ ፡ የክርስቶስ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ፍጡር፡ ስለኾነ ፡ ከአምላክ ፡ ከፈጣሪው ፡ ጋራ ፡ እኩል ፡ ነው ፡ ለመባል ፡ አለመቻሉን ፡ አስረዳው ፡ ያሉትን እንመርምር ።

## መ ላ ሽ ።

፵፩/ ኹለት ፡ ፈቃዶች ፡ አልተጣሉም ፡ ማለት ፡ ቀድሞ ፡ ኹለት ፡ ፈቃድ ፡ መኖሩ ፡ ቢረጋገጥ፡ ነበረ ፡ ኹለት ፡ ፈቃዶች ፡ አለመኖራቸውን ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ፈቃድ ፡ ለመኾኑ ፡ ዘለምጃን ፡ በጠቀስንበት ፡ በላይኛው፡መሥመር ፡ የገለጽነው ፡ አስተያየት ፡ በቂ ፡ ነው ።

ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ በባሕርየ ፡ መለኮት ፡ እንደ ፡ ተገዛ ፡ ይናገራል ፡ ለሚሉትም ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ኹሉ ፡ መለኮት ፡ ትስብእትን ፡ ተዋሕዶ ፡ በሥጋ ፡ የአምላክነትንም ፡ የሰውነትንም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ሠራ ፡ ይነግሩናል ፡ እንጂ ፡ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ ባንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ምንታዌ፡ ኖሮበት ፡ ትስብእቱ ፡ ለመለኮቱ ፡ ተገዛ ፡ የሚል ፡ ንባብ ፡ በፍጹም ፡ አናገኝም ።

ይህንም ፡ ለመረዳት ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌልን ፡ ብንመለከት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከደቀ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋር ፡ በመርከብ ፡ ኾኖ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ሲሔድ ፡ ማዕበል ፡ ሞገድ ፡ ተነሥቶ ፡ መርከቡን ፡ ሊያሰጥመው ፡ ተቃረበ ። እርሱ ፡ ግን ፡ በመርከቡ ፡ ኋላ ፡ ተኝቶ ፡ ነበረ ። ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ አቤቱ ፡ ተነሥተህ ፡ አድነን ፡ ልናልቅ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቀሰቀሱት ።

እርሱም ፡ እናንተ ፡ ሃይማኖተ ፡ ጎደሎዎች ፡ ምን ፡ ያስፈራችኋል ፡ አለና ፡ ተነሥቶ ፡ ነፋሳቱንና፡ ማዕበለ ፡ ባሕሩን ፡ ጸጥ ፡ አትሉምን ፡ ብሎ ፡ ገሠጻቸው ፡ ማዕበሉም ፡ ጸጥ ፡ አለ ፡ ሲል ፡ እናገኘዋለን፡

ማቴ ፡ ፰ ፡ ፳፫-፳፯ ።

መተኛትና ፡ መቀስቀስ ፡ የሰውነት ፡ ሥራ ፤ ነፋሳትንና ፡ ማዕበላትን ፡ ገሥጾ ፡ ጸጥ ፡ ማድረግ ፡ የአምላክነት ፡ ሥራዎች ፡ መኾናቸው ፤ ሠሪያቸው ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ መኾኑ ፡ የማይካድ ፡ ነገር ፡ ነው ።

ካቶሊካውያን ፡ እንደሚሉት ፡ የመለኮትን ፡ ሥራ ፡ መለኮት ፡ የትስብእትን ፡ ሥራ ፡ ትስብእት ፡ ተከፋፍለው ፡ የሚሠሩት ፡ ኾኖ ፡ ቢኾን ፡ ነፋሳትንና ፡ ማዕበላትን ፡ መገሠጽ ፡ በተለይ ፡ የመለኮት ፡ ሥራ ፡ ስለኾነ ፡ ትስብእትን ፡ ባልቀሰቀሱትም ፡ ነበረ ።

እንግዲህ ፡ የተኛውና ፡ የተቀሰቀሰው ፡ ማዕበላትንም ፡ ጸጥ ፡ ያደረጋቸው ፡ ያው ፡ አንዱ ፡ ክርስቶስ ፡ ከኾነ ፡ አንድ ፡ እርሱን ፡ ኹለት ፡ አድርጎ ፡ ገዢና ፡ ተገዢ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ እንደምን ፡ ይቻላል ፡ አይቻልም ።

አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ መኾኑንም ፡ ሲያስረዳ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ባጭር ፡ ቃመት ፡ በጠባብ ፡ ደረት ፡ ተወስኖ ፡ ገዘፍ ፡ የሚያየውን ፡ አካል ፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልደ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ሕያው ።

የሕያው ፡ የእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ አንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ነህ ፡ ብሏል ።

በዚህም ፡ የዮና ፡ ልጅ ፡ ስምዖን ፡ ይህን ፡ ምሥጢር ፡ የሰማይ ፡ አባቴ ፡ እንጂ ፡ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ መምህር ፡ አልገለጸልህምና ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነህ ፡ ተብሎ ፡ ብፅዓን ፡ አገኘቶበታል ። ማቴ ፡ ፲፮ ፡ ፲፮—፲፯ ።

ናትናኤልም ፡ ረቢ ፡ አማን ፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወንጉሠ ፡ እስራ ኤል ፡ አንተ ፡ ብሎታል ፡ ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፶ ።

እርሱም ፡ ራሱ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘዕውሩን ፡ አይሁድ ፡ ካንድነታቸው ፡ እንደለዩት ፡ ሰምቶ ፡ ተገናኘውና ፡ አንተ ፡ በወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታምናለህን ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ፡ እርሱም ፡ አቤቱ ፡ አምንበት ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ማነው ፡ አለ ። ጌታም ፡ መልሶ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ይህ ፡ የምታየው ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ የሚነጋገረው ፡ ነው ፡ አለው ፡ ዘዕውሩም ፡ አቤቱ ፡ አመንኩ ፡ ብሎ ፡ ሰገደለት ። ዮሐ ፡ ፱ ፡ ፴፭-፴፱ ።

እንግዲህ ፡ በምራቁ ፡ ጭቃውን ፡ ለውሶ ፡ በደረቅ ፡ ግንባር ፡ ላይ ፡ ዐይን ፡ ሲቀርጽ ፡ በመታየቱ ፡ ሰው ፡ መኾኑን ፡ የገለጸ ፡ እርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ቢለን ፡ አይደለኽም ፡ ልንለው ፡ ይገባልን ፡ አይገባም ።

በሌላም ፡ አንቀጽ ፡ ወወሀቦ ፡ ሥልጣነ ፡ ከመ ፡ ይግበር ፡ ኰነኔ ፡ እስመ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ውእቱ ።

ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ነውና ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣንን ፡ ሰጠው ፡ ብሏል ። ዮሐ ፡ ፭-፳፯ ።

እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ መለኮቱን ፡ ከትስብእቱ ፡ ትስብእቱን ፡ ከመለኮቱ ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ አስተካክሎ ፤ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ወልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ሲነግረን ፡ እንቢ ፡ ብለን ፡ ትስብእቱን ፡ ለመለኮቱ ፡ ይገዛል ፡ የምንል ፡ ከኾነ ፡ አይሁድም ፡ ቢኾኑ ፡ መጻጕዕን ፡ በፈወሰ ፡ ጊዜ ፡ አባቴ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የአ ምላክነትን ፡ ሥራ ፡ እንዲህ ፡ ይሠራል ፤ እኔም ፡ እንደርሱ ፡ የአምላክነትን ፡ ሥራ ፡ እሠራለሁ ፡ ብሎ ፡ ቢነግራቸው ፡ ዓዲ ፡ አባሁ ፡ ይሬስዮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወያዔሪ ፡ ርእሶ ፡ ምስለ ፡ እግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ ይላል ፡ ራሱን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ያስተካክላል ፡ ብለው ታል ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ያሉት ፡ ነገር ፡ የለምና ፡ እኛም ፡ እንደነርሱ ፡ መኾናችን ፡ ነው ።

በዚህም ፡ ላይ ፡ በኔ ፡ ያመነ ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ የምሠራውን ፡ ይሠራል ፡ ከዚያም ፡ የበለጠ ፡ ያደር ጋል ፡ ብሎ ፡ ያመንበትን ፡ እኛን ፡ ለዚህ ፡ ለአምላካዊ ፡ ሥራው ፡ ተካፋዮች ፡ ሲያደርገን ፡ በተዋ ሕዶ ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገውን ፡ ራሱን ፡ ከራሱ ፡ ለይቶ ፡ ትስብእት ፡ ከአምላካዊ ፡ ሥራ ፡ ውጭ ፡ ልዩ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ለጆሮ ፡ ይቀፋል ።

## ደ ራ ሲ ።

፵፪/ የመነኩሴውን ፡ ባህል ፡ የሚያፈርሱ ፡ ማስረጃዎችና ፡ ምስክሮች ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕ ፍትና ፡ ከቅዱሳን ፡ አበው ፡ እየጠቀሱ ፡ ትስብእቱ ፡ ከመለኮቱ ፡ ጋራ ፡ እኩል ፡ ነው ፡ ማለት ፡ የሚ ይቻል ፡ መኾኑን ፡ አስረደ*ቸው ፡ ብለዋ እ ።

## መ ላ ሽ ።

፵፪/ ይህ ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ ቢኾን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍትም ፡ ኾነ ከቅዱሳን ፡ አበውም ፡ ኾነ ፡ ተጠቀሱ ፡ ካልዋቸው ፡ ቃላት ፡ አንዱ ፡ ይጠቀስ ፡ ነበረ ፤ አንድ ፡ ማስረጃ ሳይሰጡ ፡ አስረድቷል ፡ ማለት ፡ ማንም ፡ የማይቀበለው ፡ ፍጹም ፡ ውሸት ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፵፫/ ኢትዮጵያውያን ፡ በክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ የሰው ፡ ባሕርይና ፡ ፈቃድ ፡ መኖሩን ፡ የ ማያም ኑበት ፡ ምክንያት ፡ ካቶሊካውያን ፡ ኹለት ፡ ክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ወልድ ፡ ብለው ፡ ያምናሉ ፡ ሲሉ ፡ እንደሚያስቡት ፡ ባንድ ፡ ክርስቶስ ፡ መከፋፈል ፡ አለ ፡ ማለትን ፡ ያህል ፡ ኾኖ ፡ ስለሚሰማቸው ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፵፫/ ቃል ፡ ትስብእትን ፡ እንደ ፡ ተዋሐደ ፡ የተዋሕዶ ፡ ስሙም ፡ ክርስቶስ ፡ መባል ፡ አንድ ፡ ኾነና ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኾኖ ፡ የአምላክነትንም ፡ የሰውነትንም ፡ ሥራ ፡ ባንድ ፡ ፈቃድ ፡ ባንድ ፡ ሥምረት ፡ ባንድ ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ሠራ ፡ መጻሕፍት ፡ በያንቀጹ ፡ መናገራቸውን ፡ ባለፈው ፡ መሥመር ፡ መላልሰን ፡ አስረድተናል ።

የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መምህራን ፡ በየመጽሐፉ ፡ ከወሰኑት ፡ አልፉ ፡ የትስብእቱ ባሕርይ ፡ ለመለኮቱ ፡ ባሕርይ ፡ መቸውንም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተገዛና ፡ እንደ ፡ ታዘዘ ፡ ነው ፡ካለች የመለኮትንና ፡ የትስብእትን ፡ ተዋሕዶ ፡ ሽራ ፡ እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ ኀድረት ፡ ማለቷ ፡ እንደኾነ ግልጥ ፡ ነው ።

ኀድረትም ፡ ካለች ፡ በሙሴ ፡ አድሮ ፡ ኦሪትን ፡ እንደሠራ ፡ በትስብእት ፡ አድሮ ፡ ወንጌልን ፡ ሠራ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ የሚቈጠር ፡ ነገር ፡ ነው ።

እንዲህም ፡ ከኾነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ሙሴ ፡ ላደረበት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዲገዛ ፡ ትስብእትም ፡ ላደረበት ፡ ለመለኮት ፡ ተገዛ ፡ ማለቷ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተዋይ ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ያመዛዝነው ።

እኛ ፡ ግን ፡ ወልደ፡ ዕጓለ፡እመሕያው ፡ ኢመጽአ ፡ ከመ ፡ ይትለአክዎ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ ከመ ፡ ይትለአክ ።

ወልደ፡ ዕጓለ፡እመሕያው ፡ ክርስቶስ ፡ ሊላክ ፡ ሊያገለግል ፡ እንጂ ፡ ሊላኩት ፡ ሊያገለግሉት ፡ እንዳልመጣ ፡ እናውቃለን ። ተልእኮውም ፡ ከጸሎት ፡ ከሥዕል ፡ ጋራ ፡ ራሱን ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ ላባቱ ፡ ማቅረብ ፡ ነው ፤ በጠቅላላው ፡ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ መሥራትና ፡ ሕማማተ ፡ መስቀልን ፡ መቀበል ፡ ነው ። ይኸነንም ፡ ተልእኮ ፡ የፈጸመ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ አካላዊ ፡ ቃል ፡ ሥጋን ፡ ተዋሕዶ ፡ በሥጋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ትስብእት ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ አይደለም ።

ሥጋ ፡ ብቻውንስ ፡ እንዳይረባ ፡ እንዳይጠቅም ፤ መንፈስ ፡ ውእቱ ፡ ዘያሐዩ ፡ ወሥጋስ ፡ አልቦ ፡ ዘይበቍዕ ።

የሚያድን ፡ መንፈስ ፡ ነው ፤ ሥጋ ፡ ግን ፡ የሚረባው ፡ የሚጠቅመው ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ብሎ ፡ እርሱ ፡ ራሱ ፡ ነግሮናል ፡ ዮሐ ፡ ፮ ፡ ፷፫ ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ በፊልጵስዩስ ፡ ክታቡ ፡ ኵልክሙ ፡ ፍጹማን ፡ ዘንተ ፡ ሐልዩ ፡ ለነኒ ፡ ዘከመ ፡ ገብረ ፡ ለነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘውእቱ ፡ አርአያሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አኮ ፡ ሐይዶ ፡ ዘኮነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አላ ፡ አትሐቶ ፡ ርእሶ ፡ ነሥአ ፡ አርዓያ ፡ ገብር ፡ ወተመሰለ ፡ ከመ ፡ ብእሲ ፡ ወኮነ ፡ ከመ ሰብእ ፡ ሰምዐ ፡ ወተአዘዘ ፡ እስከ ፡ በጽሐ ፡ ለሞት ፡ ወሞቱኒ ፡ ዘበመስቀል ። ወበእንተዝ ፡ አዕበዮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥቀ ፡ ወጸገዎ ፡ ስመ ፡ ዘየዓቢ ፡ እምኵሉ ፡ ስም ፡ ከመ ፡ ለስሙ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይሰግድ ፡ ኵሉ ፡ ብርክ ፡ ዘበሰማያት ፡ ወዘበምድር ፡ ወዘበቀላያት ፡ ወእለ ፡ ታሕተ ፡ ምድር ፡ ወኵሉ ፡ ልሳን ፡ ይግነይ ፡ ከመ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ውእቱ ፡ እግዚእ ፡ በስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፊልጵ ፡ ፪ ፡ ፭ ፡ ፲፫ ።

ፍጹማን ፡ የኾናችሁ ፡ ኹሉ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያደረገልንን ፡ ይህነን ፡ አስቡ ። ይህም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብን ፡ በመልክ ፡ የሚመስለው ፡ በባሕርይ ፡ የሚተካከለው ፡ ነው ፤ እግዚአብሔርም ፡ የኾነ ፡ ራሱን ፡ ዝቅ ፡ አድርጎ ፡ የሰውን ፡ መልክ ፡ ነሥቶ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ቀምቶ ፡ አይደለም ።

ሰው ፡ ኾኖ ፡ ሰውን ፡ መስሎ ፡ እስከ ፡ መሞት ፡ ድረስ ፡ ደርሶ ፡ እሺ ፡ በጀ ፡ ብሎ ፡ ታዞዞ ፡ ሞቶም ፡ በመስቀል ፡ የኾነው ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈጽሞ ፡ እጅግ ፡ አከበረው ፡ (ማለት) ንበር ፡ በየማንየ ፡ አለው ።
ከስም ፡ ኹሉ ፡ የበለጠ ፡ ስምን ፡ ሰጠው ፡ (ማለት) ፡ አምላክ ፡ ወልድ ፡ እግዚእ ፡ መባልን ፡ ሰጠው ፡ ወልድየ ፡ አለው ።

በሰማይ ፡ በምድር ፡ በቀላያት ፡ ከምድር ፡ በታች ፡ ያለ ፡ ብርክ ፡ ጉልበት ፡ ኹሉ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ይንበረከክ ፡ ዘንድ ፡ (ማለት) ፡ ይሰግድ ፡ ዘንድ ፡ አንደበትም ፡ ኹሉ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ጌትነት ፡ ጌታ ፡ እንደኾነ ፡ ዐውቆ ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡ ከስም ፡ ኹሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ስምን ፡ ሰጠው ፡ ፈጽሞ ፡ እጅግ ፡ አከበረው ፡ ብሎ ፡ ይነግረናል ።

ይህ ፡ አነጋገር ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ በአብ ፡ ዕሪና ፡ የነበረ ፡ የአብ ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ድኅረ ፡ ዓለም ፡ ሥጋን ፡ ተዋሕዶ ፡ በሥጋ ፡ ሳባቱ ፡ እንደ ፡ ታዞዘና ፡ መከራ ፡ መስቀልን ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ በየማነ ፡ አብ ፡ የነበረ ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በሥጋ ፡ ነበረ ፡ በየማነ ፡ አቡሁ ፡ እንደ ፡ ተባለ ፡ ያስረዳናል ፡ እንጂ ፡ ትስብእቱ ፡ ከመለኮቱ ፡ ልዩ ፡ ኾኖ ፡ ለመለኮቱ ፡ ታዞዞ ፡ ተገዛ ፡ የሚል ፡ አናገኝም ።

ስለዚህ ፡ በልብ ፡ ወለድ ፡ ትስብእቱ ፡ ለመለኮቱ ፡ ዘወትር ፡ እንደ ፡ ተገዛ ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ ትምህርት ፡ ስንኳንስ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ልንቀበለው ፡ ስንሰማው ፡ ይቀፈናል ። ስለዚህ ፡ ካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ ፈቃድ ፡ ትስብእቱ ፡ ለመለኮቱ ፡ ይገዛል ፡ በማለቷ ፡ የክርስቶስን ፡ ተዋሕዶ ፡ አታምንም አካል ፡ የሌለው ፡ ባሕርይ ፡ የለምና ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ካለች ፡ እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ ኹለት ፡ አካልም ፡ ያስኘባታል ፡ በማለት ፡ ሐሳባችንን ፡ እንገልጻለን።

## ደ ራ ሲ ።


ጥ፩/ ሥዕለ ፡ ክርስቶስ ፡ ሲጠይቅ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ባታክልቱ ፡ ውስጥ ፡ ሲፈራ ፡ ጽዋው ፡ ሊያልፍ ፡ ሲጸልይ ፡ ደም ፡ ሲልብ ፡ በዕፀ ፡ መስቀል ፡ ተንጠልጥሎ ፡ አምላኬ ፡ አምላኬ ፡ ለምን ፡ ተውኸኝ ፡ ሲል ፡ ሲታመምና ፡ ሲሞት ፡ ኋላም ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ወደ ፡ አባቴና ፡ ወደ ፡ አባታችሁ ፡ ወደ ፡ አምላኬና ፡ ወደ ፡ አምላካችሁ ፡ ዓርጋለሁ ፡ ያላቸው ፡ ሰው ፡ በመኾኑ ፡ ነውን ወይስ ፡ አምላክ ፡ በመኾኑ ፡ ቢል ፡ ኢትዮጵያውያኖቹ ፡ ሰው ፡ በመኾኑ ፡ ነው ፡ አሉት ።
እርሱም ፡ እንግዲያስ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ አለው ፡ የመለኮትም ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ጊዜ፡ ከትስብእቱ ፡ ጋራ ፡ ከተዋሐደ ፡ በኋላ ፡ መቸውንም ፡ ከርሱ ፡ አልተለየም ፡ አላቸው ።
እነርሱም ፡ እውነት ፡ ነው ፡ አሉት ፡ እንግዲያስ ፡ በክርስቶስ ፡ የመለኮቱና ፡ የትስብእቱ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ይገኛሉ ፡ ቢላቸው ፡ የለም ፡ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ፡ አሉ ፡ ያሉትን ፡ እንመርምር ።

## መ ላ ሽ ።

ጥ፩/ ጠያቂው ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለሥጋ ፡ የሚገባውን ፡ መከራ ፡ የተቀበለ ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ አምላክ ፡ ቢኾን ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቃቸው ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ እንጂ ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ መስጠታቸው ፡ ጥያቄውም ፡ መልሱም ፡ የተካከለ ፡ ነው ።

ምክንያቱም ፡ የጠያቂው ፡ አነጋገር ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የሚያረጋግጥ ፡ እንጂ ፡ ምንታዌን ፡ የሚያመለክት ፡ ባለመኾኑ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ካቶሊካውያን ፡ አነጋገር ፡ ትስብእት ፡ ሞተ ፡ መለኮት ፡ አልሞተም ፡ በሚል ፡ ኹለትነትን ፡ በሚያሳይ ፡ አነጋገር ፡ አልተናገረም ፡ ማለት ፡ ነው ።
እንግዲያስ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ ያቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ ትክክለኛ ፡ አይደለም ። በላይኛውም ፡ መሥመር ፡ ሕማማተ ፡ መስቀልን ፡ የተቀበለ ፡ አምላክ ፡ ቢኾን ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ ሰው ፡ በመኾኑ ፡ ብሎ ፡ ጠይቆ ፡ ሰው ፡ በመኾኑ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ጠቅላላ ፡ መልስ ፡ አግኝቶ ፡ ነበረ ፡ ሰው ፡ መኾን ፡ ማለትም ፡ ነባቢት ፡ ነፍስ ፡ የተዋሐደችው ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ ሰብአዊ ፡ አካልን ፡ በከዊን ፡ መዋሐድ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ሰው ፡ ኾነ ፡ የሚል ፡ ጠቅላላ ፡ መልስ ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ባሕርይ ፡ ያለአካል ፡ ብቻውን ፡ የሚገኝ ፡ አስመስሎ ፡ እንግዲያስ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ መጠየቅ ፡ ጠያቂው የአካልንና ፡ የባሕርይን ፡ ኹናቴ ፡ ጠንቅቆ ፡ አላወቀም ፡ ብሎ ፡ ከማስገመት ፡ በቀር ፡ ጥያቄው ፡ የሚሰጠው ፡ ስሜት ፡ ስለሌለ ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ጥያቄ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ አልፈነዋል ።




ይህ ምስል መስቀሉ በሥጋ እንደ ተሰቀለ ያሳያል ፩ ጴጥ ፫ ፲፰—፲፱ ።

የመለኮቱ ፡ ባሕርይ ፡ ከትስብእቱ ፡ ጋራ ፡ ከተዋሐደ ፡ በኋላ ፡ መቸውንም ፡ ክርሱ ፡ አልተለየም ፡ የሚለውን ፡ ጥያቄ ፡ ካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትስብእቱ ፡ ለመለኮቱ ፡ መቸውንም ፡ እንደተገዛ ፡ ነው ፡ ትላለችና ፡ አትቀበለው ፡ እንደኾነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለሃይማኖቷ ፡ መሠረት ፡ አድርጋ ፡ የያዘችው ፡ ባህል ፡ ነው ።

እንግዲያስ ፡ በክርስቶስ ፡ የመለኮቱና ፡ የትስብእቱ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ይገኛሉ ፡ ማለት ፡ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ የመለኮቱ ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከትስብእቱ ፡ ጋራ ፡ ከተዋሐደ ፡ በኋላ ፡ መቸውንም ፡ አልተለየም ፡ የሚለውን ፡ ጥያቄ ፡ የሚያፈርስ ፡ ንግግር ፡ ነው ።

ምክንያቱም ፡ ተዋሕዶ ፡ ማለት ፡ ምንታዌ ፡ ጠፍቶ ፡ እንድነት ፡ ሲገኝ ፡ ነው ። ይህም ፡ ትምርት ፡ ካቶሊካውያን ፡ ሳይቀሩ ፡ የሚቀበሉት ፡ መኾኑ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ በማለታቸው ፡ ይታወቃል ። እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ ተዋሕዶ ፡ መሠረት ፡ አካልን ፡ አንድ ፡ ብለው ፡ ሲያምኑ ፡ ባሕርዩን ፡ ኹለት ፡ የሚሉበት ፡ ምክንያቱ ፡ ምንድን ፡ ነው ፧ ምንም ፡ ምክንያት ፡ አይገኝለትም ።

ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያውያኖቹ ፡ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ፩ ፡ ባሕርይ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ አይባልም ፡ ብለው ፡ የሰጡት ፡ መልስ ፡ ትክክለኛ ፡ መልስ ፡ ነው ።

ደ ራ ሲ ።

፶፩/ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ የሚፈራረሱ ፡ ኹለት ፡ ባህሎች ፡ እናንተ ፡ ትደግፋላችሁ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ በክርስቶስ ፡ ሳይደበላለቁና ፡ ሳይቀላቀሉ ፡ የመለኮትና ፡ የትስብእት ፡ ባሕርያት ፡ መገኘታቸውን ፡ ታምናላችሁ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ አለ ፡ ትላላችሁ ፡ ፩ ፡ ክርስቶስ ፡ ማለትን ፡ የፈለጋችሁ ፡ እንደኾነ ፡ ክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ፍጹማን ፡ ባሕርያት ፡ ያሉት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ ነውና ፡ እኛም ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ እናምናለን ፡ ኹለቱን ፡ ያሉትን ፡ እንመርምር ።

መ ላ ሽ ።

፶፩/ መለኮታዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ አካል ፡ መለኮትና ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ ሰብአዊ ፡ አካል ፡ እንደ ፡ ተዋሐዱና ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ እንደኾኑ ፡ እናምናለን ። ይህንንም ፡ እኛ ፡ ብቻ ፡ ሳንኾን ፡ ካቶሊካውያንም ፡ አንድ ፡ አካል ፡ በማለት ፡ ያምኑታል ።

ባንድ ፡ ወገንም ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ አለ ፡ ትላላችሁ ፡ ለሚለውም ፡ ኹለቱ ፡ ባሕርያት ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ ኾኑ ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ አንዱን ፡ ባሕርይ ፡ አጥፍተን ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ አለ ፡ የምንል ፡ አይደለንም ። ስለዚህ ፡ ባህላችን ፡ ኹሉ ፡ የተደጋገፈ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ የሚፈራርስ ፡ አይደለም ።

በእውነቱ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ የሚፈራረስስ ፡ የካቶሊክ ፡ ባህል ፡ ነው ። ሳይርቅ ፡ በቅርቡ ፡ አሁን ፡ ከዚህ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ በሚገኘው ፡ መሥመር ፡ የመለኮቱ ፡ ባሕርይ ፡ ከትስብእቱ ፡ ጋራ ፡ ከተዋሐደ ፡ በኋላ ፡ መቸውንም ፡ ከርሱ ፡ አልተለየም ፡ ብሎ ፡ ነበረ ። አሁን ፡ ደግሞ ፡ ባሕርዩን ፡ ከተዋሕዶ ፡ እውጭ ፡ ክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ፍጹማን ፡ ባሕርያት ፡ ያሉት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ የሚፈራርስ ፡ ነገር ፡ ነው ።

ኹለተኛም ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ትላላችሁ ፡ ይኸ ፡ አካል ፡ የማን ፡ ነው ፧ የቃል ፡ ብቻ ፡ ነው ፧ እንዳትሉ ፡ አካለ ፡ ቃል ፡ ምሉእ ፡ በሩሕ ፡ ረቂቅ ፡ ነው ፡ ሲታይ ፡ ሲዳሰስ ፡ ሲጨበጥ ፡ አይቻልም ። ደም ፡ የለውም ፡ ሕማም ፡ አይሰማውም ።

[illegible]

በመለኮትና ፡ በትስብእት ፡ [illegible] ፡ እንዳትሉ ፡ ባሕርይ ፡ አለ ፡ ተዋሕዶም ፡ ትላላችሁ ። [illegible]
ስለዚህ ፡ አካል ፡ የሌለው ፡ ባሕርይ ፡ ባሕርይ ፡ የሌለው ፡ አካል ፡ የለምና ፡ ይህ ፡ ተዋሕዶ ፡ [illegible] ፡ ባሕርይንም ፡ አንድ ፡ ያደርጋል ፡ ብላ ፡ እንደ ፡ ኦርቶዶክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባህል ፡ ካላመንኽ ፡ በቀር ፡ ነገሩ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ የሚፈራርስ ፡ መኾኑ ፡ እርግጠኛ ፡ ነገር ፡ ነው ።

ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ያላችሁ ፡ [illegible] ፡ ስለሚለውም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ በምትል ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ላይ ፡ ያላቸው ፡ ፍቅር ፡ ከንጉሡ ፡ ከንጉሥታቸው ፡ ፍቅር ፡ በላይ ፡ ስለኾነ ፡ ለንጉሡ ፡ የርሱን ፡ መለየት ፡ የንጉሣቸው ፡ የዘውድ ግልግ መለየት ከምንም አልቆጠሩትም ።

ደ ራ ሲ ።

፶፪/ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ዓይመልሱ ፡ ዝም ፡ አሉ ። ባህላቸው ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ መኾኑንም ፡ ተረድተው ፡ የካቶሊክን ፡ ትምህርት ፡ ወዳጅ ፡ የኾነውን ፡ ዘድንግልን ፡ ነገ

ሩን ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ እንዲተውላቸው ፡ ክርሱ ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ ንጉሥታት ፡ የተከላከሉለትንና ፡ የጠበቁትን ፡ ጥንታዊውን ፡ ሃይማኖት ፡ እንዳይሽረው ፡ አጥብቀው ፡ ስመኑት ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ እንመርምር ።

መ ላ ሽ ።

፺፮/ ይህንን ፡ እውነተኛውን ፡ ነገር ፡ [illegible] ፡ የዚ ፡ ዘድንገልን ፡ ታሪክ ፡ እንመልከት ። ብንመለከተውም ፡ በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ [illegible] ፡ ዘድንገል ፡ ሕዝቦቻቸው ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የጎደለባትን ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ የሚያስተምሩ ፡ መምህራን ፡ ለማግኘት ፡ ወደ ፡ ኤሲፓኛና ፡ ወደ ፡ ፖርቱጊዝ ፡ ላኩ ።
ይህንን ፡ ምክንያት ፡ አድርገው ፡ ሚሲዮኖች ፡ የማይረባ ፡ ቀስቀ ፡ እየሰጡ ፡ ከሚወዱትና ፡ ከሚወዳቸው ፡ ሕዝባቸው ፡ አለያዩዋቸው ። ሃይማኖቱን ፡ ወዳድ ፡ የኾነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ይል ቁንም ፡ የጎጃም ፡ ሕዝብ ፡ ራስ ፡ ዘሥላሴን ፡ የጦር ፡ መሪ ፡ አድርጎ ፡ ደንቢያ ፡ ውስጥ ፡ በርሜ ፡ ከሚ ባል ፡ ሥፍራ ፡ ጦርነት ፡ ገጠማቸው ። እርሳቸውም ፡ በአንካሴ ፡ ተወግተው ፡ ሞቱ ፡ ኪል ፡ እናገኘዋለን ።
እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ዝምታና ፡ ልመና ፡ እንዴህ ፡ እስኪኾን ፡ ድረስ ፡ ነው ። ሚሲዮናውያኑ ፡ ግን ፡ ምንጊዜም ፡ ቢኾን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መምጣታቸው ፡ ሰውና ፡ ሰውን ፡ ለማለያየት ፡ ደም ፡ ለማ ፋሰስ ፡ ብቻ ፡ ስለኾነ ፡ ፈቃዳቸው ፡ በመጠኑ ፡ ተፈጸመ ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ።

ደ ራ ሲ ።

፺፯/ ንጉሡ ፡ በካቶሊኮቹ ፡ ንግግር ፡ ተግርሰ ፡ መለኮት ፡ ሞተ ፡ ካላችሁ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሞቱ ፡ ያሰኝባችኋል ፡ እያለ ፡ በኢትዮጵያውያኖቹ ፡ ሐተታ ፡ አጸናባቸው ፡ ስለሚለው ፡ ንግግር ።

መ ላ ሽ ።

፺፯/ ይህ ፡ ንግግር ፡ መልሱ ፡ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ በቍጥር ፡ ፺፮ ፡ በሰፈረው ፡ መልስ ፡ የተ ሰጠበት ፡ ስለኾነ ፡ ከዚህ ፡ መድገም ፡ አላስፈለገም ፡ ደግኖ ፡ መመልከት ፡ በቂ ፡ ነው ።

ደ ራ ሲ ።

፺፰/ አንድ ፡ ሰባኪ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ከመልበሱ ፡ በፊት ፡ ባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ነበረው ፡ ኋላም ፡ ከድ ንግል ፡ ማርያም ፡ ሥጋን ፡ ወሰደ ፡ አሁን ፡ ይችን ፡ የወሰዳትን ፡ ኹለተኛዪቱን ፡ ባሕርይ ፡ ወዴት ፡ ትጥ ሏታላችሁ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቃቸው ፡ አንድ ፡ መነኩሴ ፡ ከኹለቱ ፡ ያለመከፈልና ፡ ያለመቀላቀል ፡ ዘእንበለ ፡ ፍልጠት ፡ ወኢቱሳሔ ፡ አንድ ፡ ኾነ ፡ እንላለን ፡ ሲል ፡ መለሰ ።
ሰባኪውም ፡ ያለመቀላቀል ፡ እንደሆነ ፡ ኹለት ፡ አንድ ፡ ይኾናል ፡ መቀላቀል ፡ የሌለ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግን ፡ ኹለቱ ፡ ባይቀላቀሉ ፡ በየባሕርያቸው ፡ ይኖራሉ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ቢለው ፡ መነኩሴው ፡ የለም ፡ አንድ ፡ ይኾናሉ ፡ እንጂ ፡ በኹለትነት ፡ አይኖሩም ፡ አለው ፡ የሚሉትን ፡ እንመርምር ።

መ ላ ሽ ።

፺፰/ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ከመልበሱ ፡ በፊት ፡ የነበረው ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ አካል ፡ መለኮ ትም ፡ ነበረው ፡ ኋላም ፡ ከድንግል ፡ ሥጋን ፡ እንደ [illegible] ፡ የማይከፈል ፡ የምናምነው ፡ ቃል ፡ ነው ።
ከአመቤታችንም ፡ የነሣው ፡ ሥጋ ፡ አካልና ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ በተዋሕዶ ፡ ምንታዌ ፡ የማይጠፋ ፡ ከኾነ ፡ ካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ የምትለው ፡ ከእመቤታችን ፡ የነሣውን ፡ ሥጋ ፡ ወዴት ፡ አድርሳው ፡ ነው ። ያለመለወጥ ፡ ያለመለየት ፡ በተዐቅቦ ፡ ተዋሕዶና ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኾኗ ፡ የማትል ፡ ከኾነ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ [illegible] ፡ ባለቤቶች ፡ በስተቀር ፡ እንደ ፡ ንስጥ ሮስ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ [illegible] ።
ቃል ፡ ሥጋን ፡ መዋሐዱን ፡ [illegible] ፡ በተዋሕዶ ፡ ምንታዌ ፡ ጠፋ ፡ የማትል ፡ ከኾነ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ የምትልበትን ፡ ምሥጢር ፡ ስትገልጽልን ፡ እኛም ፡ ያለመቀላቀል ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ ባሕ ርይ ፡ ኾነ ፡ የምንልበትን ፡ ምሥጢር ፡ ለመግለጽ ፡ ዝግጁዎች ፡ ነን ።

ደ ራ ሲ ።

፺፱/ ከርክሩን ፡ ይመራው ፡ የነበረው ፡ የንጉሡ ፡ እንደራሴ ፡ ወደ ፡ መነኩሴው ፡ ፊቱን ፡ አዙሮ ፡ እንዲህማ ፡ ከኾነ ፡ አውጣኪ ፡ እንዳለው ፡ ባሕርዮችን ፡ ተቀላቀሉ ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ አው ጣኪ ፡ አልተቀላቀሉም ፡ ቢል ፡ ያለመቀላቀል ፡ ከሁለት ፡ አንድ ፡ ሊኾን ፡ አለመቻላቸውን ፡ ኹሉም ፡ የሚገነዘበው ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ዘለፈው ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ እንመርምር ።

## መ ፋ ሽ ።

፺፱/ ምንም ፡ አውጣኪ ፡ አልተቀላቀለም ፡ ቢል ፡ አውጣኪ ፡ እንዳለው ፡ ባሕርያቸን ፡ ተቀላቀሏቸው ፡ ማለት ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ አነጋገር ፡ ነው ። ይህ ፡ ሰው ፡ በእውነት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አውጣኪ ፡ መናፍቅ ፡ ነው ፡ መባሉን ፡ ብቻ ፡ ሰምቶ ፡ መናፍቅ ፡ የተባለበትን ፡ ባሀል ፡ ሳያውቅ ፡ እንዲያው ፡ የሰው ፡ ስም ፡ ላጥፋ ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከመተው ፡ በቀር ፡ ቁራቱም ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ ድርሰቱን ፡ ያላወቀው ፡ ስለኾነ ፡ መልስ ፡ ሊሰጥበት ፡ አይገባውም ።

ሳይቀላቀል ፡ ከኹለት ፡ አንድ ፡ ሊኾን ፡ አለመቻሉን ፡ ኹሉም ፡ ይገነዘበዋል ፡ ለማለት ፡ ግን ፡ መልሱ ፡ ምሥጢረ ፡ ሥጋዌ ፡ በምሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቻለው ፡ የለምና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ኹሉ ፡ ይቻላል ፡ ብሎ ፡ ከማመን ፡ በቀር ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ አይቻልም ።

ለምሳሌ ፡ በኀቱም ፡ ድንግልና ፡ ተፀንሶ ፡ በኀቱም ፡ ድንግልና ፡ መወለድ ፡ ለሰው ፡ ይቻለዋልን ፡ አይቻለውም ። እንግዲያስ ፡ ይህም ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ባይቻል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይቻላል ፡ ብለን ፡ እንመልስለታለን ።

## ደ ራ ሲ ።

፻/ እንግዲያ ፡ ይህም ፡ መንፈሳዊ ፡ ባልቴት ፡ ክርክሮች ፡ የርሱ ፡ ወገን ፡ ይሉት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ዋንድ ፡ ጊዜ ፡ መከፈልና ፡ መደባለቅ ፡ አለመኖሩ ፡ እየታመነ ፡ በክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ብቻ ፡ አለ ፡ ይላል ፡ ከዚህም ፡ በፊት ፡ እንዳስረዳነው ፡ ያለመለማመቁ ፡ ምክንያት ፡ ባሕርይና ፡ አካል ፡ የሚሉትን ፡ ቃሎች ፡ ከማወራረስ ፡ ብቻ ፡ የተነሣ ፡ መኾኑ ፡ ያረዳናል ፡ ያሉትን ፡ ቃል ፡ እንመርምር ።

## መ ል ስ ።

፻/ እነሆ ፡ ጌታ ፡ አኔ ፡ ወአቡ ፡ ኅቡረ ፡ ሕይወት ፡ ዘወረደ ፡ እምሰማይ ፡ ብሏል ፡ ዮሐ ፡ ፲፥፴።
ኅቡረ ፡ ሕይወት ፡ ሲል ፡ ትስብእቱን ፡ ዘወረደ ፡ እምሰማይ ፡ ሲል ፡ ትስብእት ፡ ከሰማይ ፡ አል ወረደምና ፡ መለኮቱን ፡ አኔ ፡ ወአቡ ፡ ሲል ፡ በማያዊ ፡ መለኮት ፡ ምድራዊ ፡ ትስብእት ፡ ተዋሕዶ ፡ ሳይቀር ፡ አንድ ፡ መኾኑን ፡ ያስረዳናል ።

እንዲሁም ፡ ማለት ፡ ኅብስተ ፡ ሕይወት ፡ ብሎ ፡ ትስብእትን ፤ ዘወረደ ፡ እምሰማይ ፡ ብሎ ፡ መለኮትን ፡ ማመልከቱ ፡ ተፀቅበ ፡ መኖሩን ፡ መለኮትንም ፡ ትስብእትንም ፡ አዋሕዶ ፡ አኔ ፡ ወአቡ ፡ ማለቱ ፡ ተዋሕዶውን ፡ ያስረዳል ፡ ማለት ፡ ነው ።

፪ኛም ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሞተ ፡ በሥጋ ፡ ወሐይወ ፡ በመንፈስ ፡ ብሏል ። በሥጋ ፡ ብሎ ፡ ትስብእቱን ፡ በመንፈስ ፡ ብሎ ፡ መለኮቱን ፡ በመናገሩ ፡ ተፀቅቦ ፡ መኖሩን ፤ ሞተ ፡ ሐይወ ፡ ብሎ ፡ ዋንድ ፡ አንቀጽ ፡ በመናገሩ ፡ ተዋሕዶውን ፡ ያስረዳናል ።

፫ኛም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ለዕብራውያን ፡ እሬት ፡ በሞት ፡ ላይ ፡ መውደሙን ፡ ቢናገር ፡ ልጁን ፡ ኃጢአት ፡ በሚሰማማው ፡ ሰውነት ፡ አምሳል ፡ ላከ ፡ ይችንም ፡ ኃጢአት ፡ በሰውነቱ ፡ ቀጣት ፡ ብሏል ። ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፫ ።

ወልዶ ፡ ብሎ ፡ መለኮቱን ፡ ነፍስተ ፡ ኃጢአት ፡ ብሎ ፡ ትስብእቱን ፡ በመናገሩ ፡ ተፀቅቦ ፡ መኖሩን ፡ ኹለቱ ፡ ግብር ፡ ዋንድ ፡ አንቀጽ ፡ በመናገሩ ፡ ተዋሕዶውን ፡ ያስገነዝበናል ። መጻሕፍት ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ብንመረምራቸው ፡ በዚህ ፡ መንገድ ፡ የተመሩ ፡ ናቸው ።

፬ ፡ መነኩሴ ፡ ይህነን ፡ መሠረት ፡ አድርጎ ፡ ተፀቅቦ ፡ ሳይቀር ፡ መለኮትና ፡ ትስብእት ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ቢል ፡ ምንም ፡ የተሳሳተ ፡ ነገር ፡ የለም ።

ባሕርይና ፡ አካል ፡ የሚሉትን ፡ ቃሎች ፡ ከማወራረስ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ስለሚሉትም ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍም ፡ መልስ ፡ የካቶሊካውያን ፡ ቃሉ ፡ ከመዝገበ ፡ በቀር ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ልዩ ፡ ሰው ፡ ለአካልና ፡ ለባሕርይ ፡ ምንም ፡ ያስረዱት ፡ ነገር ፡ የለም ። በእኛ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ ስለአካልና ፡ ስለባሕርይ ፡ ባደረጉት ፡ በያንቀጹ ፡ መልሰን ፡ አስረድተን ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ መድገም ፡ አላስፈለገንም ፡ ብቻ ፡ ፪ ፡ የታዘዘውን ፡ መመልከት ፡ ነው ።

## ክ ፍ ል ፬ ።

### በኢትዮጵያ ፡ ስለሚታመነው ፡ ስለአንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባሀል ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ አሳቦችና ፡ ምስክሮች ።

## ደ ራ ሲ ።

፻፩/ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሕዶ ፡ ስለሚያምኑት ፡ ትምርት ፡ መርጃዎች ፡ ያሏቸው ፡ አስተያየት ፡ በ፫ ፡ ይመደባል ። ከነርሱም ፡ የጸናውን ፡ የአውጣኪን ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባሀል ፡ ያምናሉ ፡ የሚሉ ፡ አሉ ።

ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የሚያምኑት ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ መጠነኛ ፡ ወይም ፡ መካከለኛ ፡ ነው ፡ ይላሉ ። በመጨረሻም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ የሚያምኑት ፡ ትምህርት ፡ [illegible] ፡ የቀና ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ አይታጡም ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፺፭/ ታሪካቸው ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ [illegible] ፡ ይለያዩና ፡ መርማሪዎችን ፡ ቀክ ትለው ፡ ባልተረዱትና ፡ ባላወቁት ፡ [illegible] ፡ ትርጓሜ ፡ ያለት ፡ ኢትዮጵያን ፡ ስመንቀፍ ፡ መነቀቅም ፡ [illegible] ፡ ብሎ ፡ ከማለብ ፡ እርግጠኛ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ በመቸንም ፡ ካርቶች ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ እየመረ መሩ ፡ የኢትዮጵያን ፡ መምህራን ፡ ጠይቀው ፡ ቢኾን ፡ እውነተኛውን ፡ ባህል ፡ በተረዱት ፡ ነበረ ።

ኢትዮጵያ ፡ ያውጣኪን ፡ ባህል ፡ ይዛለች ፡ ብለው ፡ የጻፉ ፡ ሰዎች ፡ መቼም ፡ ቢኾን ፡ ሚሲዮና ውያን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚመጡ ፡ ለፖለቲካ ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ያንኑ ፡ የመጡበትን ፡ የፖ ለቲካ ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ ሲሠሩ ፡ ኖረው ፡ ሲመለሱ ፡ ምን ፡ እናውራ ፡ ብለው ፡ ከልባቸው ፡ ፈጥረው ፡ ተናግረውታል ፡ እንጂ ፡ ከሃይማኖቱ ፡ ምርመራ ፡ ከምንም ፡ አልደረሱም ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

፺፮ኛ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የሚያምኑት ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ መጠነኛ ፡ ወይም ፡ መካከ ለኛ ፡ ነው ፡ የሚሉት ፡ ካንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ የተያዘው ፡ የትኛው ፡ የተቀየው ፡ የትኛው ፡ መኾኑን ፡ የማይገልጽ ፡ የዝብዝብ ፡ ስለኾነ ፡ ምንም ፡ አስተያየት ፡ ሊሰጠው ፡ አይቻልም ።

ኢትዮጵያውያን ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ የሚያምኑት ፡ ትምርት ፡ ፈጽሞ ፡ የቀና ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የመሰከሩት ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ባህል ፡ በእርግጥ ፡ ተረድተዋል ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

## ደ ራ ሲ ።

፺፯/ እነሆ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ በኹለት ፡ ክፍል ፡ ይከፈላሉ ፡ አንደኛዎች ፡ የቤተ ፡ ክህነት ፡ ጸሐፊዎች ፡ ናቸው ፡ እነርሱ ፡ በዕውቀቱ ፡ የበሰሉ ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ በደንብ ፡ የተሰናዱ ፡ ስለኾኑ ፡ ጽፈው ፡ የሚወልደንንትልቅ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለው ፡ ነው ። ኹለተኞች ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ነገር ፡ በመመርመር ፡ ብዙ ፡ ዓመቶች ፡ ያሳለፉ ፡ ጨዋዎች ፡ ጸሐፊዎች ፡ ናቸው ፡ ጨዋ ዎች ፡ ስለኾኑ ፡ የሃይማኖቱን ፡ ነገር ፡ [illegible] ፡ አይገልጡም ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፺፰/ እኛ ፡ ይህን ፡ ጽሑፋቸውን ፡ መርምረን ፡ [illegible] ፡ የሃይማኖት ፡ ነገር ፡ የሚገልጡን ፡ ከትምህርት ፡ መጻሕፍት ፡ በቀጥታ ፡ [illegible] ፡ አሉበት ፡ ብቻ ፡ ከመጻፍ ፡ በቀር ፡ ከትምህርት ፡ መጻሕፍት ፡ ጠቅሰ ፡ እንዲህ ፡ ይላሉ ፡ ኃይል ፡ ቃል ፡ በሚገኝ ፡ [illegible] ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ [illegible] ፡ የሚያስረዳ ፡ አላገኘንም ። [illegible] ፡ በቀር ፡ የምናበላልጠው ፡ አላገኘንም ።

## ደ ራ ሲ ።

፺፱/ [illegible] ፡ ይህን ፡ [illegible] ፡ የኢትዮጵያ ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ እንደ ፡ [illegible] ፡ አሳብ ፡ [illegible] ፡ እንደዚሁ ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ ኢትዮጵያ ፡ ክርስትና ፡ [illegible] የተረጋገጠ ፡ ወረን ፡ የሰሙ ፡ እነርሱ ፡ [illegible] ፡ የኢትዮጵያን ፡ ክርስትና ፡ በሚያጠራ ጥር ፡ አንጋገር ፡ ተናግረውታል ።

## መ ላ ሽ ።

፻/ ኢትዮጵያ ፡ ከመላው ፡ ያውሮፓ ፡ ሀገሮች ፡ ቀድሞ ፡ አስቀድማ ፡ እምልኮተ ፡ እግዚአብሔ ር ፡ [illegible] ፡ መኾኗን ፡ የታሪክ ፡ መጻሕፍቶች ፡ ብቻ ፡ ሳይኾኑ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትም ፡ [illegible] እንቀድ ፡ ይመሰክሩላታል ። ይህንም ፡ ለመረዳት ፡ አባ ፡ ጋስፒረኒ ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ፡ ከገጽ ፡ ፲፱ ፡ —፲፪ ፡ መመልከት ፡ ይጠቅማል ።

አውሮፓውያን ፡ አለማወቃቸው ፡ ግን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ካለመቀበላቸው ፡ የተነሣ ፡ ባይኾን ፡ አይቀርም ። ስለዚህ ፡ አውሮፓውያን ፡ ሃይማኖታችንን ፡ ቢያውቁልን ፡ የምንወደው ፡ ባያውቁልን ፡ የማንጠላው ፡ ስለሌለ ፡ እነዚህን ፡ ጸሐፊዎች ፡ ኢትዮጵያን ፡ በሃይማኖት ፡ ለመታወቅ ፡ አበቁት ፡ ብለን ፡ የምናመሰግናቸው ፡ አይደለንም ።

## ደ ራ ሲ ።

፺፰/ እነርሱ ፡ ስለውጥናቸው ፡ ቋሚ ፡ የተውሉን ፡ ወሬ ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለ ፡ ኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ያላቸውን ፡ አስተያየትና ፡ ከኢጋገራቸውን ፡ መርምሬን ፡ ካገኘነው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ጋራ ፡ ፈጽሞ የተስማማ ፡ ነው ። ኢትዮጵያውያኖቹ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ በመሠረቱ ፡ ያምኑታል ፡ ማለት ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፺፰/ ይህ ፡ አነጋገር ፡ የተዘዋወረ ፡ አነጋገር ፡ ነው ፡ ምክንያቱም ፡ ኢትዮጵያ ፡ የያዘችው ፡ ያንድ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የቀወሰነው ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ከመመሥረቱ ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረ ፡ መኾኑን ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍም ፡ መላልሰው ፡ እያበረዱ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ግን ፡ ከ[illegible] ፡ ዓ/ም ፡ በኋላ ፡ የተመሠረተ ፡ መኾኑ ፡ ሲታወቅ ፡ የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ከርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረውን ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ፈጽሞ ፡ አለቀቀችውም ፡ ፈጽሞ ፡ አላጠፋችውም ፡ ብሟልት ፡ ፈንታ ፡ ፈቀኛይቱን ፡ መደበኛይቱን ፡ የኦርቶዶክስን ፡ ባህል ፡ ጥገኛ ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ጠፍ ፡ ታቦት ፡ በኋላ ፡ መጥቶ ፡ የተደረበውን ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ መደበኛ ፡ አድርጎ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ በመሠረቱ ፡ ያምኑታል ፡ ስለሚል ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ባህል ፡ መሠረቱ ፡ ከርሰቶስ ፡ ከኹለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ከኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኾኖ ፡ የሰወቀትንም ፡ የአምላክነትንም ፡ ሥራ ፡ ባንድ ፡ ፈቃድ ፡ በአንድ ፡ ሥምረት ፡ ሠራ ፡ ማለት ፡ ነው ።

የኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ ይህን ፡ የሚቀበል ፡ ከኾነ ፡ ኹለቱ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ፡ ይህ ፡ ካልኾነ ፡ ግን ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፺፱/ ሌቀ ፡ ጳጳሳቱ ፡ አሮንዮስ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እንደኛ ፡ ኹለት ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ባሕርይና ፡ አንድ ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ አይሉም ።

ይህም ፡ ከትዳሴ ፡ መጽሐፋቸው ፡ ወደ ፡ ላቲን ፡ ከተተረጐመው ፡ ጸሎት ፡ ይታወቃል ፡ ይላል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፺፱/ ወደ ፡ ላቲን ፡ ተተርጕሞ ፡ ያለው ፡ ከ[illegible] ፡ ቅዳሴያት ፡ የትኛው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አልተገለጸም ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ ቢኾን ፡ ፍሮ ፡ ወደ ፡ ላቲን ፡ የተተረጐመው ፡ ትዳሴ ፡ የትኛው ፡ እንደኾነ ፡ ኃይለ ፡ ቃሉም ፡ ተለይቶ ፡ በተጠቀሰ ፡ ነበረ ፡ ስለዚህ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ልንቀበለው ፡ አልቻልንም ።

## ደ ራ ሲ ።

፻/ [illegible] ፡ ቀጥለው ፡ ቀጥረቸው ፡ ካንድ ፡ አለ ፡ ሃያ ፡ የሚደርስ ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ [illegible] ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ባህል ፡ በመሠረቱ ፡ [illegible] ፡ ነው ፡ [illegible] ፡ ደግሞ ፡ ከካቶሊክ ፡ ባህል ፡ ይቃረባል ፡ ብኋል ፡ ሌላው ፡ ደግሞ ፡ [illegible] ፡ ባህል ፡ ተከትለዋል ፡ ብኋል ፡ እያሉ ፡ የጸሐፊዎችን ፡ ታሪክ ፡ በሰፊው ፡ ተናግረዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፻/ እነዚህ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ እየጠቀሱ ፡ እንዲህ ፡ የሚሉትን ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ለውጠውታል ፡ እንዲህ ፡ የሚሉትን ፡ ባህላቸውን ፡ እንዲህ ፡ የሚለው ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ያፈርስባቸዋል ፡ እያሉ ፡ ደራሲው ፡ ቢኾን ፡ ተገቢውን ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ዝግጁ ፡ ነበርን ፡ እንዲያ ፡ [illegible] ፡ እንዲፈረድ ፡ [illegible] ፡ ነገር ፡ [illegible] ፡ ለዚህ ፡ መልስ ፡ [illegible] ፡ ማለት ፡ መጸረሻው ፡ የማይታወቅ ፡ ንፋስን ፡ ልከተል ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ የሚቈጠር ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ብለን ፡ አልፈነዋል ።

## ክፍል ፡ ፮ ።

፮ በሥርዓት ፡ አምልኮና ፡ በሃይማኖት ፡ መጻሕፍታቸው ፡ የሚገኘው ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ትምህርት ።

### ደ ራ ሲ ።

፶፯/ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የካቶሊክ ፡ መልክተኞች ፡ ከኢትዮጵያውያኖቹ ፡ ጋራ ፡ ሲከራከሩ ፡ እንዚህን ፡ ለማስረዳት ፡ ከወንጌልና ፡ ከቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ መልእክቶች ፡ በሚያመጧቸው ፡ ጥቅሶች ፡ ላይ ፡ ከተ ከራካሪዎቻቸውም ፡ መጻሕፍት ፡ እየጠቀሱ ፡ ይረቱበት ፡ ነበረ ፡ ብለዋል ።

### መ ላ ሽ ።

፶፯/ ተጠቀሱ ፡ ከሚሏቸው ፡ መጻሕፍት ፡ አንድ ፡ እንኳን ፡ ለምልክት ፡ ተጠቅሶ ፡ ቢኾን ፡ የተመልካችን ፡ ልቡና ፡ ይኾን ፡ አይኾን ፡ በሚል ፡ አጠራጣሪ ፡ አሳብ ፡ ላይ ፡ በጣለው ፡ ነበር ፤ አንድ ፡ መረጃ ፡ ሳይኖር ፡ በቃል ፡ ብቻ ፡ ምኞትን ፡ ተናግሮ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብላችሁ ፡ ተቀበሉኝ ፡ ማለት ፡ ተገቢ ፡ አይደለም ።

### ደ ራ ሲ ።

፶፰/ የኢትዮጵያ ፡ የሥርዓት ፡ አምልኮና ፡ የሃይማኖት ፡ መጻሕፍት ፡ በመሠረታቸው ፡ በሌ ላም ፡ ባይኾን ፡ በምሥጢረ ፡ ሥጋዌ ፡ ምንም ፡ ስሕተት ፡ የለባቸውም ፡ ብለዋል ።

### መ ላ ሽ ።

፶፰/ ለዚህ ፡ አነጋገርዎ ፡ የሚሰጠው ፡ መልስ ፡ ሊቀ ካህናት ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በጲላጦስ ፡ ፊት ፡ በቆመ ፡ ጊዜ ፡ ጲላጦስ ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሣቸው ፡ አንተ ፡ ነህን ፡ ብሎ ፡ ሲጠይቀው ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ከልቡናህ ፡ አንቅተህ ፡ ተናገርህን ፡ ወይስ ፡ ስለእኔ ፡ የነገሩህ ፡ ሌላ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ የመለሰለትን ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ የመሰለ ፡ አነጋገር ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የማስታውሰው ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡ ባነጋገራቸው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እየተናገሩ ፡ ሰውን ፡ ኹሉ ፡ የሚያስቀይሙ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበሩ ። እኚያ ፡ ሰው ፡ ታመሙና ፡ ምላሳቸው ፡ ተዘጋ ፡ መነጋገር ፡ ቀረና ፡ ዐይናቸው ፡ ብቻ ፡ መቁለጭለጭ ፡ ኾነ ፡ ወትሮ ፡ ተናግረው ፡ ያስቀየሙት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሔዶ ፡ ጌታው ፡ እግዚአብሔር ፡ ይማርዎ ፡ ምነው ፡ ምን ፡ አገኘዎ ፡ አላቸው ። ምላሳቸው ፡ ተይዟልና ፡ ዐይናቸውን ፡ ከማቁለጭለጭ ፡ በቀር ፡ መልስ ፡ ሊሰጡ ፡ አልቻሉም ። ያ ፡ ሰው ፡ መልስ ፡ ሊሰጡት ፡ አለመቻላቸውን ፡ ካረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ አዬ ፡ ጌታው ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ውበት ፡ ካልዎ ፡ ከዘመድዎ ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ ሲጣሉ ፡ ይኖሩ ፡ አላቸው ፡ ይባላል ።

አሁንም ፡ እርስዎ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሥርዓት ፡ አምልኮ ፡ ምንም ፡ ስሕተት ፡ የሌለበት ፡ መኾኑን ፡ እያወቁ ፡ የሺህ ፡ ሕጅ ፡ መንገደኛ ፡ ሆኖ ፡ ይዘው ፡ ሀገርዎን ፡ ሲንቁ ፡ መኖርዎ ፡ ያስገ ርማል ፡ እንጂ ፡ ንግሩ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሥርዓት ፡ አምልኮ ፡ ምንም ፡ [illegible]

### ደ ራ ሲ ።

፶፱/ ከዚህም ፡ ቀጥለው ፡ አሁን ፡ እኛ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብለን ፡ የተቀበልነውን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሥ ርዓተ ፡ አምልኮ ፡ መጻሕፍት ፡ ስሕተት ፡ የለባቸውም ፡ የሚለውን ፡ ንግግር ፡ ለማጽናት ፡ ቢሉ ፡ ፩ኛ ፡ የካቶሊክ ፡ መልእክተኞች ፡ የሚያስተምሩትን ፡ ትምህርት ፡ በኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ ላይ ፡ አንብበዋለሁ ፡ ብሎ ፡ ንጉሥ ፡ ዘድንግል ፡ መመስከሩ ።

፪ኛም ፡ ሥዕለ ፡ ክርስቶስና ፡ ጓደኞቹ ፡ ከኢትዮጵያውያን ፡ ጋራ ፡ ሲከራከሩ ፡ ከሃይማኖተ ፡ አበው ፡ እየጠቀሱ ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ እንዳሉ ፡ ያላንዳች ፡ ችግር ፡ እንዳስረዷቸው ፡ ፓድሬ ፡ ፓየዝ ፡ ይናገራል ። ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያውያኖቹ ፡ መጻሕፍቶቻቸው ፡ በካቶሊካውያን ፡ እጅ ፡ ሲገቡ ፡ አይፈቅዱም ፡ ነበረ ።

ሌላም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ቄስ ፡ እንደ ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ አንድ ፡ መጽሐፈ ፡ ቅዳሴ ፡ እንደ ፡ ድጓ ፡ የመሰሉ ፡ ካቶሊኮች ፡ ምንም ፡ ሳይለውጡ ፡ እንዳሉ ፡ የተቀበሏቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ ዘንድ ፡ በትምህርት ፡ ፀኑል ፡ ክፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡ ያላቸው ፡ የሥርዓት ፡ አምልኮና ፡ የሃይማኖት ፡ መጻሕፍት ፡ ባነጋገራቸው ፡ ከካቶሊክ ፡ ትምርት ፡ ብዙ ፡ የራቁ ፡ አይደሉም ፡ ይላሉ ፡ ብለዋል ።

መ ሰ ፳ ።

፳፱/ ነገሩ ፡ እውነት ፡ ከኾነ ፡ ንጉሥ ፡ ዘድንግል ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ሥዕለ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፡ ብሎ ፡ ፓድረ ፡ ፓየዝ ፡ አወራ ፡ እያሉ ፡ የሰሚ ፡ ሰሚ ፡ ወሬ ፡ ከመንዛት ፡ መጻሕፍቱም ፡ አሉ ፡ እኛም ፡ አለን ፡ ንጉሥ ፡ ዘድንግልም ፡ ኾኑ ፡ ሥዕለ ፡ ክርስቶስ ፡ የጠቀሱትን ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ጠቅሶ ፡ ማስረዳት ፡ አይሻልም ፡ ነበረን ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ ባይመስልም ።

ስለኾነም ፡ ይህን ፡ ብለን ፡ ለነገሩ ፡ ተገቢ ፡ መልስ ፡ ሳንሰጠው ፡ አናልፍም ። ንጉሥ ፡ ዘድንግል ፡ እንደሚሉአለሁ ፡ አለ ፡ ለሚሉት ፡ ኾኖቻችንም ፡ በየበኩላችን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ትርጉም ፡ ከመስጠታችን ፡ በስተቀር ፡ በመሠረቱ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ መቀበላችን ፡ አይካድምና ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ በእኛም ፡ ዘንድ ፡ በካቶሊካውያንም ፡ ዘንድ ፡ በማየቱ ፡ ተናግሮ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ፡ ከዚህ ፡ አልፎ ፡ እንደ ፡ ካቶሊክ ፡ ባህል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ ሠረጸ ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ ውስጥ ፡ አየሁ ፡ ብሎ ፡ እንደኾነ ፡ ይህ ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፤ በኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ አይገኝም ።

ደግሞ ፡ ሥዕለ ፡ ክርስቶስና ፡ ጓደኞቹ ፡ ከሃይማኖቱ ፡ አቢው ፡ እየጠቀሱ ፡ አስረዱቸው ፡ ስለሚሉት ፤ ከላይ ፡ እንደ ፡ ገለጽኩት ፡ ኃይለ ፡ ቃሉ ፡ ተጠቅሶ ፡ ታውቆ ፡ ቢኾን ፡ መልሱን ፡ ለመስጠት ፡ መንገድ ፡ ይገኝለት ፡ ነበረ ፡ ፍሬ ፡ የገሩ ፡ ካልተገኘ ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ንግግር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከማለፍ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ ሊሰጠው ፡ አይቻልም ።

ከዚህ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የማስታውሰው ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለሃይማኖቷ ፡ ምስክር ፡ አድርጋ ፡ የምትቀበላቸውን ፡ መጻሕፍት ፡ ሊያውቋት ፡ ወደነርሱ ፡ ባህል ፡ ለመጠመ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ብለው ፡ ሊተረጉሟቸው ፡ መሞከራቸውንና ፡ መጻሕፍቱ ፡ እንቢ ፡ ብለው ፡ መቅረታቸውን ፡ ነው ።

ይህንም ፡ የሚያስረዳ ፡ [illegible] ፡ ቁጥር ፡ በሮማ ፡ በካቶሊክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ የታተመ ፡ ካልእ ፡ ተክለሉት ፡ ወአውሥአት ፡ በእንተ ፡ ነገረ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚል ፡ መጽሐፍ ፡ አይቻለሁ ።

የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ተርጓሚ ፡ ከሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ እትልተው ፡ የሚያሳዩትን ፡ ቃላት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ወደ ፡ ማለት ፡ ለመለወጥ ፡ ብዙ ፡ ታግሏል ።

መጻሕፍቱ ፡ግን ፡ እውነት ፡ በሐሰት ፡ አይለወጥምና ፡ በእንቢታቸው ፡ ጸንተው ፡ ቀርተዋል ። ጸሐፊው ፡ ግን ፡ ከብዙ ፡ ድካምና ፡ ትግል ፡ በኋላ ፡ መጻሕፍቱ ፡ ለፈቃዱ ፡ እንዳልተገዙለት ፡ ቁርጥ ፡ ሲያውቅ ፡ እንዲያውም ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ የተጠቀሰው ፡ ሊቅ ፡ ቃል ፡ አይደለም ፡ ወደ ፡ ማለት ፡ ሲመለስ ፡ ይታያል ፤ ይህንንም ፡ በሚከተሉት ፡ መሥመሮች ፡ እገልጻለሁ ።

፩ ኛ ።

ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ዘእንጾኪያ ፡ እግናጥዮስ ፡ ወለእመ ፡ ሰማዕት ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሐመ ፡ በእንቲአሁ ፡ መዋቲ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ቢጹ ፡ ሰበ ፡ አስመ፡ገረበየ ፡ ፩ ሀላዌ ፡ ለመለኮቱ ፡ ምስለ ፡ ትስብእቱ ፡ ያለውን ፡ ንባብ ፡ ሲተረጉም ፡ ሀላዌ ፡ ዘወትር ፡ ባሕርይ ፡ ተብሎ ፡ አይተረጎምም ፡ አካል ፤ ወይም ፡ አንዋወር ፡ ተብሎ ፡ ይተረጎማልና፡ ፩ ሀላዌ ፡ ለመለኮቱ ፡ ምስለ ፡ ትስብእቱ ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ እንድናደርገው ፡ አስተውል ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ ብሏል ።

ይህንም ፡ ሲመረምሩት ፡ ካቶሊካውያን ፡ አካል ፡ ያለው ፡ የቃል ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ለትስብእት ፡ አካል ፡ የለውም ፡ ይላሉ ፡ ይህን ፡ ሀላዌ ፡ አካል ፡ ብለው ፡ የሚተረጉሙት ፡ ከኾነ ፡ ሊቁ ፡ ለመለኮቱ ፡ ምስለ ፡ ትስብእቱ ፡ ብሎ ፡ መለኮትንም ፡ ትስብእትንም ፡ ጠርቷልና ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለታቸው ፡ ቀርቶ ፡ ከኹለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኾነ ፡ ማለት ፡ ግድ፡ ይኾንባቸዋል ።

ለትስብእትስ ፡ ባሕርይ ፡ እንጂ ፡ አካል ፡ የለውም ፡ ቢሉም ፡ ከኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ፡ ባሕርይ ፡ ኾነ ፡ ማለት ፡ ግድ ፡ ይኾንባቸዋል ።

ሀላዌን ፡ ለመለኮት ፡ ሲኾን ፡ አካል ፡ ለትስብእት ፡ ሲኾን ፡ ባሕርይ ፡ እንበለው ፡ ቢሉ ፡ግን፡ መጻሕፍት ፡ እኛ ፡ እንዳልናቸው ፡ ይኾናሉ ፡ አያዛዙንም ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግልጥ ፡ ነገር ፡ ነው ፡

ይህም ፡ ለጸሐፊው ፡ ግልጥ ፡ ኾኖ ፡ ታይቶት ፡ ከዚህ ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ በሚገኘው ፡ መሥመር ፡ ሊተአምርን ፡ ለእመ ፡ ትቤ ፡ ከመ ፡ መለኮት ፡ ሐመ ፡ እንተ ፡ ትከውን ፡ ቀታሊሆሙ ፡ ለሥዕለ ፡ ቅዱስ ፡ ይላልና ፡ ገለባው ፡ የጨመረው ፡ ወይም ፡ ከመ ፡ ንሬበየ ፡ ለቃል ፡ ፩ደ ፡ አካለ ፡ ምስለ ፡ ትስ

ብእቱ፡ በማለት ፡ ፈንታ ፡ ጣሬ ፡ መለኮቱ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ለወጠው ፡ ይታያል ፡ በማለት ፡ የሊቁን፡ ቃል ፡ ለመለወጥ ፡ ሞክሯል ።

ሊቁ ፡ ግን ፡ ከኹለት ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ከኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንዲ ፡ ኾነ ፡ በማንጸሪያ ፡ ሲያበረዳ ፡ በከመ ፡ እንተሂ ፡ ካዕበ ፡ እምኔሁ ፡ ህላዌያት ፡ ዘውእቱ ፡ ነፍስ ፡ ወሥጋ፡ ወትስመይ ፡ በዝንቱ ፡ ስም ፡ ፩ ፡ ዘይደሉ ፡ ለሰብእ ።

አንተ ፡ ከኹለት ፡ አካል ፡ ከኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ከነፍስና ፡ ከሥጋ ፡ ተገኝተህ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንድትባል ፡ መለኮቱን ፡ ከትስብእቱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንደኾኖ፡ እንደ[illegible] ፡ አስተውል ፡ ብሏል ።

፫ኛም ፡ ቅዱስ ፡ አግናጢዮስ ፡ በ፴ ፡ ክፍል ፡ ወለእለሂ ፡ ይከፍልዎ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ፡ወልድ፡ዋሕድ ፡ ወይሬስይዎ ፡ ክልኤተ ፡ ህላዌ ፡ እምድኅረ ፡ ኮነ ፡ አሐደ ፡ የትኅልዎ፡ ምስለ፡ አይሁድ ።

ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ የሚባል ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ከኾነ ፡ በኋላ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የሚሉት ፡ ሰዎች ፡ ከአይሁድ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አይ ሁድ ፡ ይቈጠራሉ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ለመለወጥ ፡ እሱ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድን ፡ ወደ ፡ ኹለት ፡ መና ፍያ ፡ ወደ ፡ ፪ ፡ አካላት ፡ የሚከፍሉ ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ አሉ ፡ አትበሉ ፡ ማለቱ ፡ አይደለም ፡ ብሏል ።

ይሆንንም ፡ ለማመን ፡ አንድ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገር ፡ አለበት ፡ በዚሁ ፡ በያዝነው ፡ በአባ ፡ እየሱ ፡ መጽሐፍ ፡ በ፲፭ኛው ፡ ገጽ ፡ እንደ ፡ ተመለከትነው ፡ ካቶሊካውያን ፡ ትስብእቱ ፡ ለመለኮቱ ፡ መቻ ውንም ፡ እንደተገጣና ፡ እንጂ ፡ ታዘዘ ፡ ነው ፡ ማለታቸውን ፡ ተረድተናል ። እንግዲህ ፡ የነገርና ፡ የተ ገዢ፡ያዛዥና፡የታዛዥ፡አንዋወር፡ልዩ፡የማይገናኝ፡መኾኑ ፡ ስለሚታወቅ ፡ እንደ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ባህል ፡ ትስብእት ፡ በተዋሕዶ ፡ ፅኑዕ ፡ መንበር ፡ ኾኑ ፡ ከሌለ ፡ በቀር ፡ ትስብእቱ ፡ ለመለኮቱ ፡ ተገዢ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ፩ህላዌ፡ ያለውን ፡ ትስብእቱን ፡ ከመለኮቱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አኳኋር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መተር ጐም ፡ የታዛዥ ፡ በፍጹም ፡ የማይቻል ፡ ነገር ፡ ነው ።

፫ኛ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ገባሬ ፡ መንክራት ። ወአካሉሰ ፡ ለወልድ ፡ ሱታፌን ፡ ውእቱ ፡ እስመ፡ ፩አምላክ ዘውእቱ ፡ መለኮት ፡ ወትስብእት ፡ ኅቡረ ፡ ህላዌ ፡ ረሰየ ፡ ክልኤሆሙ ፡ ፩ደ ፡ ወአልቦ ፡ በውስቴቱ ፡ ፍድፍድና ፡ ዘተወሰከ ፡ በመለኮት ፡ ወባሕቱ ፡ ፩ቱ ፡ እሙንቱ ፡ በአካል ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ለመለ ወጥ ፡ አበው ፡ ትስብእትና ፡ መለኮት ፡ በሚባሉ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ተዋሕዶ ፡ ያለ ፡ ኹለትነታቸ ውንም ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ባንድ ፡ አኳኋር ፡ ያኖረን ፡ የወልድ ፡ አካል ፡ ዘመዳችን ፡ ነው ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኾኗ ፡ ማለቱ ፡ አይደለም ። በተለየ ፡ አካሉ ፡ ዘመ ዳችን ፡ የኾነ ፡ ቃል ፡ የነሣው ፡ ባሕርይ ፡ አካል ፡ አይባልም ፡ ይህም ፡ ሊታወቅ ፡ ወአልቦ ፡ በውስቴቱ ፡ ፍድፋዴ ፡ ዘተወሰከ ፡ በመለኮቱ ፡ ወባሕቱ ፡ ፩ ፡ እሙንቱ ፡ በአካል ፡ ብሏል ፡ ይላል ።

ንስጥሮስ ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ አካል ፡ መኖሩን ፡ ሳይክድ ፡ በዚህ ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ባለው ፡ አካል ፡ መለኮት ፡ አደረበት ፡ እንጂ ፡ አልተዋሐደውም ፡ በማለቱ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ አለ ፡ ተብሎ ፡ በጉባኤ ፡ ኤፌሶን ፡ መወገዙ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

እውን ፡ ይህ ፡ ደራሲ ፡ የጠቀሰው ፡ እንደሚለው ፡ ወንጌላዊ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ባለው ፡ መሠረት ፡ ቃል ፡ የነሣው ፡ ሥጋ ፡ ባሕርይ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ አካል ፡ አይባልም ፤ ባሕርይም ፡ አልተዋሐደም ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ ካለ ፡ ቃል ፡ የነሣውን ፡ ሥጋ ፡ ንስጥሮስ ፡ አካል ፡ ካቶሊክ ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ከመ ለያየታቸው ፡ በቀር ፡ ምንታዌ ፡ አለመፋታ ፡ በአንድነት ፡ ይኖራል ፡ በማለት ፡ አንድ ፡ እንደኾኑ ፡ እናስተውል ።

በዚህም ፡ ላይ ፡ ሊቁ ፡ ለይቶ ፡ ጠንቅቆ ፡ የወልድ ፡ አካሉ ፡ ዘመዳችን ፡ ነው ፡ ብሏል ፤ ዘመዳ ችን ፡ መኾኑ ፡ ወልድ ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ የኛን ፡ አካል ፡ የኛን ፡ ባሕርይ ፡ በተዋሕዶ ፡ ገንዘብ ፡ ስላ ደረገው ፡ ነበረ ፤ እንደዚህ ፡ ሰው ፡ እንጋገር ፡ የኛን ፡ አንዱኾን ፡ አካላችንን ፡ በተዋሕዶ ፡ ገንዘብ ፡ አደረገው ፡ እንዳይባል ፡ ለትስብእት ፡ ባሕርይ ፡ እንጂ ፡ አካል ፡ የለውም ፡ ብሏል ፤ ባሕርያችንን ፡ ገንዘብ ፡ አደረገው ፡ እንዳይባል ፡ ባሕርይን ፡ አልተዋሐደም ፡ ይላል ፤ እንግዲህ ፡ በየት ፡ በኩል ፡ የወ ልድ ፡ አካሉ ፡ ዘመዳችን ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይችላል ፡ አይችልም ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የሰጠው ፡ ቃል ፡ በቋ ፡ አለመኾኑን ፡ ርሱው ፡ ራሱ ፡ ቃኘዝበት ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ የቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ቃል ፡ መኾኑን ፡ ለመረዳት ፡ በወጸያው ፡ ያለውን ፡ የተቀዳበትን ፡ መጽሐፉን ፡ ማየት ፡ ያስፈልገኛል ፡ ብሏል ።

፴ኛ፡ ቅዱስ ፡ በስልዮስ ፡ ወኢንሬስዮ ፡ ለዝንቱ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ፪ተ፡ ወኢንቤ ፡ ከመ ፡ ማለ ኮት ፡ በህላዌሁ ፡ ወትስብእቱሂ ፡ በህላዌሁ ፡ አላ ፡ ንብል ፤ ፩ ፡ ህላዌ ፡ ወ፩፡ አካል ። ወጴጥሮስሂ፡ ኢዘከረ ፡ ፪ተ ፡ ህላዌ ፡ አላ ፡ ባሕቱ ፡ አምኑ ፡ ወይቤ ፡ እስመ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐመ ፡ በእንቲአነ ፡ በሥጋ ።

ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ ክርስቶስን ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንለዋለን ፡ እንጂ ፡ ባሕርየ ፡ መለኮቱን ፡ ለብቻ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእቱን ፡ ለብቻ ፡ አድርገን ፡ ኹለት ፡ የምንለው ፡ አይደለንም ። ጴጥሮስም ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ መኾኑን ፡ አምኖ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለእኛ ፡ በሥጋ ፡ መከራ ፡ ተቀበለ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ መኾኑን ፡ በሚያስረዳ ፡ አነጋገር ፡ አልተ ናገረም ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ሊለውጥ ፡ አስቦ ፡ ይህንን ፡ ቃል ፡ ሲተረጒም ፤ ይህን ፡ አንድ ፡ የኾነ፡ ልጅን፡ ኹለት ፡ አናደርገውም ፡ አንድ ፡ አነዋወር ፡ አንድ ፡ አካል ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ መለኮትና ፡ ትስብእ ትን ፡ ለየብቻቸው ፡ ተለያይተው ፡ በኹለት ፡ አካላት ፡ አሉ ፡ አንልም ። ጴጥሮስም ፡ ስለእኛ ፡ በሥጋ ፡ ታመመ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ አካላትን ፡ ኹለት ፡ አነዋወርን ፡ አልጠራም ፡ አላመነም ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ ብሏል ።

ሊቁ ፡ ግን ፡ ጠንቅቆ ፡ ባሕርይንም ፡ አካልንም ፡ ለይቶ ፡ አላ ፡ ንብል ፡ ፩ ፡ ህላዌ ፡ ወ፩ ፡ አካል ፡ ብሏል ።

ይህ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ መለኮትን ፡ አንድ ፡ ኾነ ፡ የሚለው ፡ ከማን ፡ ጋር ፡ ነው ፡ ከነሣው ፡ ሥጋ ፡ አካል ፡ ጋር ፡ እንዳይኾን ፡ ለትስብእት ፡ ባሕርይ ፡ እንጂ ፡ አካል ፡ የለውም ፡ ብሏል ፤ ከባሕርየ ፡ ትስ ብእት ፡ ጋር ፡ እንዳይኾን ፡ ባሕርይ ፡ አልተዋሐደም ፡ ይላል ።

አንድ ፡ አነዋወር ፡ ለሚለውም ፡ ትስብእቱ ፡ ለመለኮቱ ፡ ተገዥ ፡ ነው ፡ ብሏልና ፡ የገዢና ፡ የተ ገዢ ፡ አነዋወር ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ። ስለዚህ ፡ እንደ ፡ ሊቁ ፡ አነጋገር ፡ ክርስቶስን ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እንለዋለን ፡ እንጂ ፡ ባሕርየ ፡ መለኮቱን ፡ ለብቻ ፡ ባሕሕርየ ፡ ትስ ብእቱን ፡ ለብቻ ፡ አድርገን ፡ ኹለት ፡ የምንለው ፡ አይደለም ፡ ካላለ ፡ በቀር ፡ ለዚሁ ፡ ንባብ ፡ ሌላ ፡ መንገድ ፡ ሊገኝለት ፡ አይቻልም ።

<u>፴፩ኛ ፡ ቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ እኁወ ፡ ባስልዮስ ፡</u> ወረሰዮሙ ፡ ምስሌሁ፡ ፩፡ህላዌ ፡ ወ፩ ፡ ሥም ረተ፡ ወ፩፡ ፈቃደ ፡ ወ፩ ፡ አካለ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ወልድ ፡ ዘቦቱ ፡ ኵሉ ፡ ዘመለኮቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወዓዲ ፡ ቦቱ ፡ ኵሉ ፡ ዘትስብእት ፡ ዘእንበለ ፡ ኃጢአት ፡ በሕቲታ ፡ በህላዌ ፡ ትስብእት ፡ ዘነሥአ ፡ እምኔነ ፡ ወኮነ ፡ ምስሌሁ ፡ ፩፡ህላዌ ፤ የሚለውን ፡ ንባብ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ወደ ፡ ማለት ፡ የሚለውጥበት ፡ መንገድ ፡ ቢያጣ ፡ ይህንን ፡ ለመረዳት ፡ መጀመሪያ ፡ በጻፈበት ፡ ቋንቋ ፡ የጻፈውን ፡ ማየት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ የቅዱስ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ቃል ፡ አይደለም ፡ ሲል ፡ ክዷል ፡ የጥንት ፡ ጽሑፉንም ፡ አይቶ ፡ ያመጣው ፡ መልስ ፡ የለም ።

<u>፴፪ኛ ፡ የሮሙ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ፊልክስ ፡</u> እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሐመ ፡ በሥጋ ፡ እንዘ ፡ ኢየሐምም ፡ በመለኮት ፡ ወሕማም ፡ በሥጋ ፡ ተኖለቈ ፡ ሎቱ ፡ በከመ ፡ ይቤሉ ፡ አበዊነ ፡ ንጹ ሐን ። ብሎ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ ለሠራው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ በሥጋ ፡ ማለትን ፡ መግለጫ ፡ እያደ ረጉ ፡ እንቀጽ ፡ ተቀባዩና ፡ ባለቤቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መኾኑን ፡ መጻሕፍት ፡ ኹሉ ፡ የሚና ገሩ ፡ መኾናቸውን ፡ መስከሯል ።

ደራሲው ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ከጌታ ፡ ምስሌኔ ፡ የወጣ ፡ አይመስለኝም ፡ ብሎ ፡ ክዶታል ።

ይልቁንም ፡ የሮሙ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡሊድስ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ መኾኑን ፡ በሚያረጋግጥ ፡ አነጋገር ፡ ወኢነሀቦሙ ፡ ምክንያተ ፡ ፍልጠት ፡ ለእለ ፡ ይብሉ ፡ ክልኤተ ፡ ህላዌ ፡ ወሥጋሂ ፡ ሥጋ ፡ ውእቱ ፡ አኮ ፡ ህላዊ ፡ በርእሱ ፡ ዘኮነ ፡ መድኃኒነ ፡ ወኢይደሉ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ፍሉጠ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ባህላዌ ፡ ርእሱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘእንበለ ፡ መድኃኒት ፡ ወኢይት ፈለጥ ፡ እምኔሁ ፡ ቃል ፡ በህላዌሁ ፡ ብሎ ፡ አጉልቶ ፡ መስክሮበታል ።

እርሱ ፡ ግን ፡ እንዲያውም ፡ በሮም ፡ አቡሊዲስ ፡ የሚባል ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ የለም ፡ ተሾሞ ፡ አያውቅም ፡ ሲል ፡ ክዷል ።

ከዚህም ፡ አያይዞ ፡ እስከ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ድረስ ፡ ያሉ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትና ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ፩፡ አካል ፡ ወ፩ ፡ ህላዌ ።

ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ በግልጽ ፡ የተናገሩትን ፡ ቃል ፡ ለውጦ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ብሎ ፡ ለመተርጐም፡ ብዙ ፡ ደክሟል ፡ መጻሕፍቱ ፡ ግን ፡ እንቢ ፡ ብለው ፡ ቀርተዋል ።

እንቢታቸውንም ፡ ባጭሩ ፡ እገልጣለሁ ፡ ፩፡አካል ፡ ወ፩ ፡ ህላዌ ፡ የሚለውን ፡ ንባብ ፡ ኹሉ ፡ መለኮቱ ፡ ከትስብእቱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ አኗኗር ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ባሕ

ርይ ፡ ማለት ፡ አይደለም ፡ ብሏል ። አንድ ፡ አካል ፡ ለሚለው ፡ አካል ፡ ለመለኮት ፡ እንጂ ፡ ለትስብ እት ፡ የለውም ፡ ብሏል ፡ ለትስብእት ፡ አካል ፡ ከሌለውና ፡ ትስብእትን ፡ ነሥቶ ፡ ካልተዋሐደ ፡ ዕሩቅ ፡ ቃል ፡ ያሰኘዋል ፡ እንጂ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ።

ከእመቤታችን ፡ የነሣው ፡ ሥጋ ፡ አካል ፡ ባይባልም ፡ ባሕርይ ፡ ይባላልና ፡ ስለዚህ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ መባልን ፡ አያስቀርም ፡ እንዳይባል ፡ ካቶሊክ ፡ ጠንቅቆ ፡ ባሕርይ ፡ አልተዋሐደም ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ይላል ፡ ስለዚህ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ የሚሉት ፡ ንግግር ፡ እንዲህ ፡ ፍርስርስ ፡ ያለ ፡ ኾኖ ፡ ይገኛል ።

አንድ ፡ አኗኗር ፡ የሚለውም ፡ ይህ ፡ አንድ ፡ አኗኗር ፡ አካለ ፡ ትስብእት ፡ ጋራ ፡ እንዳይኾን ፡ ለትስብእት ፡ ባሕርይ ፡ እንጂ ፡ አካል ፡ የለውም ፡ ተብሏል ፡ ከባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ጋራ ፡ እንዳይ ኾን ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ለባሕርየ ፡ መለኮት ፡ መቸም ፡ መች ፡ ቢኾን ፡ ተገዢ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አል ተዋሐደም ፡ በኹለትነት ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ ባይ ፡ ነው ። የገዢና ፡ የተገዢ ፡ አኗኗር ፡ ልዩ ፡ ስለኾነ ፡ ፩ ፡ ህላዌ ፡ የሚለውን ፡ ንባብ ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ አኗኗር ፡ እያልኩ ፡ ልተርጕመው ፡ ብሎ ፡ ያሰበው ፡ ሐሳብ ፡ ፈራሽ ፡ ኾኖበታል ።

ይህም ፡ ሐሳቡ ፡ ፈራሽ ፡ መኾኑን ፡ እርሱው ፡ ራሱ ፡ ተገንዝቦት ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ጣፊ ፡ የጨመ ረው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሊቁ ፡ ቃል ፡ አይደለም ፡ መጀመሪያ ፡ ሊቁ ፡ ይህነን ፡ ቃል ፡ ሊጽፍ ፡ በጻፈበት ፡ ቋንቋ ፡ የተጻፈውን ፡ ማየት ፡ ያስፈልገኛል ፡ ብሎ ፡ በሃይማኖት ፡ አበው ፡ የተጻፈው ፡ ቃል ፡ ለሐሳቡ ፡ ተስማሚ ፡ አለመኾኑን ፡ ካረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ የተመኘውን ፡ ጽሑፍ ፡ ተመልክቶ ፡ ያቀረበው ፡ ማስረጃ ፡ የለም ።

ከጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ የሮም ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳትም ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕ ርይ ፡ ማለታቸውን ፡ በጽሑፋቸው ፡ ስላረጋገጡበት ፡ ንግግራቸው ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ መኾኑን ፡ አረጋግጦ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ከጌታችን ፡ ምስለኔ ፡ የወጣ ፡ አይመስለኝም ። ወይም ፡ አቡሊድስ ፡ የሮም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አይደለም ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ንግግራቸውንና ፡ ባህላቸውን ፡ ሊለውጠው ፡ አልቻለም ።

ይኹን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ የተነሣበት ፡ መሠረቱ ፡ ሐሰት ፡ ኾኖ ፡ ሐሳቡ ፡ ሳይቃናለት ፡ ነገሩ ፡ ሳይገጣጠምለት ፡ ቢቀርም ፡ ከመጻሕፍቱ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ መፍጨርጨሩ ፡ የሚያስመሰግነው ፡ ነው ።

ዶክተር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ ግን ፡ ከመጻሕፍቱ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ አንድ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ መጥቀሳ ቸው ፡ ይቅርና ፡ መጽሐፉ ፡ የተከተተበትን ፡ ማኅደር ፡ እንኳን ፡ ሳያዩት ፡ በኢትዮጵያውያኖች ፡ ዘንድ ፡ ትልቅ ፡ ግምት ፡ ከሚያገኘው ፡ ከሃይማኖተ ፡ አበው ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ እየጠቀሱ ፡ ያላንዳች ፡ ችግር ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ መኖራቸውን ፡ ያስረዱቸው ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ መጻፍ ፡ ተናጋ ሪውንም ፡ ተቀባዩንም ፡ የሚያሳፍር ፡ ተወዳዳሪ ፡ የሌለው ፡ ውሸት ፡ ነው ።

ደ ራ ሲ ።

፹/ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ኢትዮጵያውያኖቹ ፡ መጻሕፍቶቻቸው ፡ ወደ ፡ ካቶሊኮች ፡ ሲወድቁ ፡ አይፈቅዱም ፡ ነበረ ፡ ያሉትን ፡ እንመርምር ።

መ ላ ሽ ።

፹/ ካቶሊካውያን ፡ እኒህ ፡ መጻሕፍቶች ፡ ስለመሰከሩባቸው ፡ በመናደዳቸው ፡ እየቀደዱ ፡ ይጥ ሉብናል ፡ ብለው ፡ በካቶሊካውያን ፡ እጅ ፡ እንዳይገቡባቸው ፡ ተጠንቅቀው ፡ እንደኾነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በተቀረጻ ፡ ምስክሮቻቸውን ፡ ቢመሰክሩላቸው ፡ ይደብቋቸዋልን ፡ አይደብቋቸውም ፡ ውሸት ፡ ነው ።

ደ ራ ሲ ።

፹፩/ ሌላም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ቄስ ፡ እንደ ፡ ሃይማኖተ ፡ አበው ፡ እንደመጽሐፈ ፡ ቅዳሴ ፡ እንደ ፡ ድጓ ፡ የመሰሉ ፡ ምንም ፡ ሳይለወጡ ፡ እንዳሉ ፡ ካቶሊካውያን ፡ የተቀበሏቸው ፡ የሥርዓተ ፡ አምል ኮና ፡ የሃይማኖት ፡ መጻሕፍት ፡ ባነጋገራቸው ፡ ከካቶሊክ ፡ ትምህርት ፡ ብዙ ፡ የራቁ ፡ አይደሉም ፡ ብሏል ። ስለሚሉት ።

መ ላ ሽ ።

፹፩/ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከ፬፻፶፩ ፡ ዓ/ም ፡ በኋላ ፡ ከጌታ ፡ ከሐዋርያት ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ያልተገኘ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ትምህርት ፡ አምጥታ ፡ እስከትለይ ፡ ድረስ ፡ የኹሉም ፡ ትም

ርታቸው ፡ በመሠረቱ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ ትምርቱ ፡ የተቀራረበ ፡ ነው ፡ ቢባል ፡ የሚያሳፍር ፡
ነገር ፡ አይደለም ፡፡

## ደ ራ ሲ ፡፡

፹፱/ ኢትዮጵያውያን ፡ እነዚህን ፡ በመሳሰሉ ፡ መጻሕፍት ፡ በክርስቶስ ፡ ህላዌያት ፡ ወይም ፡
ባሕርያት ፡ በሙሉነታቸው ፡ ኹለት ፡ ግብሮች ፡ አንድ ፡ አካል ፡ መገኘታቸውን ፡ አካለ ፡ ቃልም ፡
የማይለወጥ ፡ መኾኑን ፡ ይታመኑባቸዋል ፡ ብለው ፡ ለዚህ ፡ መረጃ ፡ ሲጠቅሱ ፡ አረጋኖን ፡ በመለኮ
ትህ ፡ የእምላክ ፡ የበኵር ፡ ልጅ ፡ መኾንህን ፡ በሥጋዌህም ፡ የድንግል ፡ ልጅ ፡ መኾንህን ፡ በትስብ
እትህም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መኾንህን ፡ እምናለሁ ፡ ይላል ፡፡

መጽሐፈ ፡ ስንክሣርም ፡ ቃሉ ፡ ወደ ፡ ሥጋ ፡ ሥጋውም ፡ ወደ ፡ መለኮት ፡ አልተለወጠም ፡
ኹለቱም ፡ በየባሕርያቸው ፡ በክርስቶስ ፡ ይኖራሉ ፡ ይላል ፡፡

በሃይማኖተ ፡ አበውም ፡ ባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ወደ ፡ ትስብእት ፡ አልተለወጠም ፡ ባሕርየ ፡ ትስ
ብእትም ፡ ወደ ፡ ባሕርየ ፡ ቃል ፡ አልተለወጠም ፡ ኹለቱም ፡ ያለመለዋወጥ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በየባ
ሕርያቸው ፡ ቆመው ፡ ይኖራሉ ፡ ተብሏል ፡ ይላል ፡፡

መጽሐፈ ፡ ሰዓታትም ፡ የማይታመመው ፡ ቃል ፡ በባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ታመመ ፡ ይላል ፡፡

እንዲሁም ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ መጽሐፍ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የአብ ፡ ቃል ፡ ስለእኛ ፡
ሰው ፡ የኾነ ፡ በፈቃዱ ፡ ሥጋን ፡ የለበሰ ፡ ኃጢአት ፡ የሌለበት ፡ በፈቃዱ ፡ በሥጋ ፡ የታመመ ፡ አም
ላክም ፡ ስለኾነ ፡ ያልታመመ ፡ የሚል ፡ ፈጽሞ ፡ የቀና ፡ ትምርት ፡ ያመጣል ፡ ብለዋል ፡፡

## መ ላ ሽ ፡፡

፹፱/ እነዚህ ፡ ቃሎችና ፡ የሚከተሉትም ፡ ቃሎች ፡ ውላጤን ፡ ቡዓዴን ፡ ቱሳሔን ፡ የሚመለከቱ ፡
ናቸው ፡ የዚህ ፡ መልስ ፡ የኬልቄዶን ፡ ውሳኔ ፡ ብለው ፡ ባቀረቡት ፡ ጥያቄ ፡ በተሰጠው ፡ መልስ ፡
ተጽፏልና ፡ ያነኑ ፡ መመልከት ፡ በቂ ፡ ነው ፡ ኹለተኛ ፡ መጻፍ ፡ አያስፈልግም ፡፡

## ደ ራ ሲ ፡፡

፺/ ኢትዮጵያውያን ፡ ያየነውና ፡ በእጃችን ፡ የዳሰስነው ፡ የሚለውን ፡ የዮሐንስን ፡
ቃል ፡ ሲተረጉሙ ፡ የሚታየውና ፡ የሚዳሠሠው ፡ ግዙፍ ፡ ነው ፡ ይህም ፡ ማለት ፡ የክ
ርስቶስ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ረቂቅ ፡ ባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ አይደለም ፡ ሲሉ ፡
በማስመር ፡ ይፈቱታል ፡ ብለዋል ፡፡

## መ ላ ሽ ፡፡

፺/ ይህ ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡፡ ንዜንወክሙ ፡ በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘሀሎ ፡ እምቅድም ፡ ሲል ፡
በቅድምና ፡ የነበረ ፡ የርሱን ፡ ነገር ፡ እንነግራችኋለን ፡፡

ውእቱ ፡ ዘሰማዕናሁ ፡ በእዘኒነ ፡ ሲል ፡ ቀዳማዊ ፡ አምላክ ፡ መኾኑን ፡ ለመግለጽ ፡ (እምቅድመ፡
ይትወለድ ፡ አብርሃም ፡ ሀሎኩ ፡ አነ ፡) እኔ ፡ አብርሃም ፡ ከመወለዱ ፡ አስቀድሜ ፡ ነበርኩ ፡ ሲል ፡
የሰማነው ፡ እርሱ ፡ ነው ፡፡

ወዘርኢናሁ ፡ በዕይንቲነ ፡ ሲል ፡ ቀዳማዊ ፡ አምላክ ፡ መኾኑን ፡ ለመግለጽ ፡ በደረቅ ፡ ግንባር
ዐይን ፡ ሲፈጥር ፡ ያየነው ፡ እርሱ ፡ ነው ፡፡

ወዘጠየቅናሁ ፡ ወዘገሠሣሁ ፡ እደዊነ ፡ በእንተ ፡ ነገረ ፡ ሕይወት ፡ ሲል ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡
መነሣቱንም ፡ ለመረዳት ፡ በእጃችን ፡ የዳሠሥነው ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ በቅድምና ፡ የነበረ ፡
እርሱ ፡ ሰውም ፡ ቢኾን ፡ ምንታዌ ፡ የሌለበት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ መኾኑን ፡ በሚያ
ስረዳ ፡ አነጋገር ፡ ይተረጕሙታል ፡ እንጂ ፡ መለኮቱን ፡ ከትስብእቱ ፡ ትስብእቱን ፡ ከመለኮቱ ፡ በሚ
ለይ ፡ አነጋገር ፡ የክርስቶስ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ረቂቅ ፡ የኾነው ፡ ባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡
አይደለም ፡ ብለው ፡ አይተረጕሙትም ፡ ፍጹም ፡ ውሸት ፡ ነው ፡፡

የኢትዮጵያ ፡ መምህራን ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ይተረጕሙታል ፡ ብሎ ፡ መናገርን ፡ ከፈቀዱ፡
አስቀድመው ፡ የሀገርዎን ፡ ባህልና ፡ ትምህርት ፡ መማር ፡ ያስፈልግዎ ፡ ነበረ ፡፡ ይህ ፡ ሳይኾን ፡ በተ
ወለዱ ፡ በ፲፩ ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ ካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን፡ ተሠማርተው ፡ ያደጉ ፡ ሲኾኑ ፡ የጠጡት
ተመልሰው ፡ የኢትዮጵያ ፡ መምህራን ፡ እንዲህ ፡ ብለው፡ ይተረጕማሉ ፡ እያሉ ፡ ማፈቸል ፡ ያላሳደ
ጉትን ፡ ተናካሽ ፡ ውሻ ፡ ጆሮ ፡ እንደ ፡ መቆንጠጥ ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ፡፡

## ደ ራ ሲ ።

፹፬/ በሃይማኖተ ፡ አበው ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በእውነት ፡ እንደ ፡ ታመመ ፡ የማያምኑትን ፤ ክርስቶስ ፡ ሲገርፉት ፡ አልታመመም ፡ ሲሰቅሉትም ፡ አልደከመም ፡ በመስቀልም ፡ ሥቃይ ፡ አልተሰማውም ፡ የሚሉትን ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ መናፍቃን ፡ እናወግዛቸዋለን ፡ ሲል ፡ ያወግዛቸዋል ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሲራብም ፡ ሲጠማም ፡ ሲደክምም ፡ ሲታመምም ፡ አንዳንዶቹ ፡ እንደሚሉት ፡ በምትሐት ፡ አይደለም ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ይገኝበታል ።

ኋላም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አውጣኪን ፡ የሚያወግዙት ፡ የጌታችን ፡ ሥጋ ፡ ረቂቅ ፡ ነው ፡ ሕማማትና ፡ ሥቃያት ፡ አልነኩትም ፡ ብሎ ፡ ያስተምር ፡ ስለነበረ ፡ መኾኑን ፡ ማወቅ ፡ ይበቃል ።

አውጣኪ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ መቸውንም ፡ ተከታይ ፡ አላገኘም ። አንዳንዶቹ ፡ የአውጣኪ ፡ ልጆች ፡ ባህሉን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለማግባት ፡ በሞከሩም ፡ ጊዜ ፡ ወዲያውኑ ፡ ተወግዘው ፡ ተባረሩ ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፹፬/ ይህ ፡ ቃል ፡ ሐሰት ፡ ያልተቀላቀለበት ፡ እውነተኛ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ኢትዮጵያ ፡ የምትከላከል ፡ የአውጣኪን ፡ ባህል ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ኹለት ፡ ልደት ፡ በተዋሕዶ ፡ ከበረ ፡ ከማለት ፡ የወጣውን ፡ ባህል ፡ ኹሉ ፡ የማትቀበል ፡ መኾኗ ፡ እርግጠኛ ፡ ንግግር ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፹፭/ ከዚህ ፡ ካልነው ፡ ኹሉ ፡ በኋላ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ጸሐፊዎች ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የክርስቶስን ፡ ሕማማትና ፡ ሞት ፡ በምትሐት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ያምናሉ ፡ ሲሉ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡ ደራሽ ፡ እንደ ፡ ወኀ ፡ ፈሳሽ ፡ ኾኖ ፡ ይሰማናል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፹፭/ ይህ ፡ አነጋገርዎ ፡ እውነተኛ ፡ ስለኾነ ፡ እውነት ፡ በመናገርዎ ፡ አመሰግንዎታለሁ ፡ በሌላውም ፡ ኹሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ቃል ፡ የወጣ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ባህል ፡ ያልያዘች ፡ መኾኗን ፡ የሚረዱበት ፡ ሰፊ ፡ አእምሮ ፡ እንዲሰጥዎ ፡ እመኝልዎታለሁ ።

## ደ ራ ሲ ።

፹፮/ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ከተባለው ፡ ባሕርይ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ለብቻው ፡ ሲነገር፡ በኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ መቸውንም ፡ በራሱ ፡ የቆመ ፡ ኋኝ ፡ አድራጊ ፡ ወይም ፡ የሚሠራ ፡ ባለቤት ፡ አካል ፡ ማለትን ፡ ያሰማል ፡ የሚሉትን ፡ ቃል ፡ እንመርምር ።

## መ ላ ሽ ።

፹፮/ ስለአካልና ፡ ስለባሕርይ ፡ መላልሰን ፡ በያንቀጹ ፡ እንዳስረዳነው ፡ አካል ፡ የሌለው ፡ ባሕርይ ፡ ባሕርይ ፡ የሌለው ፡ አካል ፡ የለም ። ስለዚህ ፡ መለኮታዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ አካለ ፡ ቃል ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ አካለ ፡ ትስብእትን ፡ ቢዋሐድ ፡ በተዋሕዶ ፡ ምንታዌ ፡ ጠፋ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኾኖ ፡ ባንድ ፡ ፈቃድ ፡ ባንድ ፡ ሥምረት ፡ የአምላክነትንም ፡ የሰውነትንም ፡ ሥራ፡ ሠራ፡እንላለን ፡ እንጂ ፡ ባሕርይን ፡ ከአካል ፡ ለይተን ፡ በራሱ፡የቆመ፡ኋኝ ፡ አድራጊ፡ ወይም ፡ የሚሠራ ፡ ባለቤት ፡ ፡ አካል ፡ የምንለው ፡ አይደለም ።

ባሕርይን ፡ ከአካል ፡ ለይታ ፡ በራሱ ፡ የቆመ ፡ ኋኝ ፡ አድራጊ ፡ የሚሠራ ፡ ባለቤት ፡ የምታደርገው ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ናት ፡ ምክንያቱም ፡ አካለ ፡ ቃል ፡ ከእመቤታችን ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእትን ፡ ነሣ ፡ ለትስብእት ፡ አካል ፡ የለውም ፤ ይኸውም ፡ የነሣው ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ከባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ሳይዋሐድ ፡ ተለይቶ ፡ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ብቻ ፡ እየሠራ ፡ ለባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ሲገዛ፡ ይኖራል ፡ ስለምትል ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፹፯/ ያልተደባለቁ ፡ ባሕርያት ፡ ለሚለውም ፡ ለኬልቄዶን ፡ አነጋገር ፡ የሚቃረን ፡ ወይም፡ የማይስማሙ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ኹለት ፡ አካላት ፡ የማለትን ፡ ትርጒም ፡ ስለዚህ ፡ ምንም ፡ ሳይደባለቁ ፡ የተዋሐዱ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ አሉ ፡ የሚለውን ፡ የካቶሊክ ፡ ትምርት ፡ ሲሰሙ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የሚቃወሙ ፡ ንስጥሮስ ፡ እንዳስተማረው ፡ በተቃርቦ ፡ አው ፡ በተላጽቆ ፡ (ማለት) ፡ በመቀራረብ ፡ ወይም ፡ በመጣበቅ ፡ የተፈጸመ ፡ መዋሐድ ፡ ኾኖ ፡ ስለሚሰማቸው ፡ ነው ፡ ያሉትን ፡ እንመርምር ።

## መ ላ ሽ ።

፳፯/ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ለሚለው ፡ ለኬልቄዶኑ ፡ አነጋገር ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ የማለትን ፡ ትርጕም ፡ የምንሰጠው ፤ ተዋሕዶውም ፡ ተላጽቆ ፡ ተቃርቦ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ የማንቀበልበት ፡ ምክንያት ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ከኬልቄዶን ፡ ውሳኔ ፡ በፊት ፡ ካቶሊካውያንም ፡ ኦርቶዶክሳውያንም ፡ ቃል ፡ ከእመቤታችን ፡ የነሣ ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ ሰብአዊ ፡ አካልን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያምኑ ፡ ነበረ ። ይህነንም ፡ ሰብአዊ ፡ አካል ፡ ሲነሣ ፡ በሕፃናት ፡ መጠን ፡ የዕለት ፡ ፅንስ ፡ ኾኖ ፡ ተሥዕሎተ ፡ መልክእ ፡ በ፵ ፡ ቀን ፡ ተፈጽሞለት ፡ በየጥቂቱ ፡ እያደገ ፡ አካል ፡ ዘየአከለን ፡ ቍመት ፡ አደረገ ፡ እንጂ ፡ ከተዋሕዶ ፡ በፊት ፡ አካል ፡ ዘየአክል ፡ ተገኝቶ ፡ ቃል ፡ ያነን ፡ ተዋሐደ ፡ ወይም ፡ በዚያ ፡ አደረ ፡ የሚል ፡ አልነበረም ።

ንስጥሮስ ፡ ከዚህ ፡ ወጥቶ ፡ ከተዋሕዶ ፡ በፊት ፡ አካል ፡ ዘየአክል ፡ ተገኝቶ ፡ ቃል ፡ ያነን ፡ ተዋሐደ ፡ ወይም ፡ በዚያ ፡ አደረ ፡ ስለዚህ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ያሰኛል ፡ ስላለ ፡ ሮምም ፡ እስክንድርያም ፡ አንጾኪያም ፡ ቍስጥንጥንያም ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አይደለም ፡ ብለው ፡ እንዳወገዙት ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ውሳኔ ፡ በቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ አፈ ፡ ጉባኤነት ፡ በጉባኤ ፡ ኤፌሶን ፡ ከተወሰነ ፡ በኋላ ፡ የኬልቄዶኑ ፡ ጉባኤ ፡ ቃል ፡ ከእመቤታችን ፡ የነሣው ፡ ሥጋ ፡ ባሕርይ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ አካል ፡ አይባልም ፤ ይኸውም ፡ የነሣው ፡ ባሕርይ ፡ በምንታዌ ፡ በኹለትነት ፡ ጸንቶ ፡ ለመለኮቱ ፡ እንደ ፡ ተገዛ ፡ ይኖራል ።

ሥራውንም ፡ መለኮት ፡ የመለኮትነትን ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ ትስብእትም ፡ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ ብሎ ፡ ስለወሰነ ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህልና ፡ የኬልቄዶንን ፡ ውሳኔ ፡ ስናመዛዝነው ፡ ንስጥሮስ ፡ ቃል ፡ ከእመቤታችን ፡ የነሣው ፡ ሥጋ ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ አካል ፡ ይባላል ፡ ቢል ።

ጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ ባሕርይ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ አካል ፡ አይባልም ፡ ቢል ፡ በተገናኝ ፡ ኹለቱም ፡ ቃል ፡ ከነሣው ፡ ሥጋ ፡ ጋራ ፡ በኹለትነት ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ ካሉ ፡ ኹሉም ፡ አንድ ፡ ናቸው ፤ በቃል ፡ ተዋሐደ ፡ ብለው ፡ ቢናገሩም ፡ ተዋሕዶ ፡ ምንታዌን ፡ የማያጠፋ ፡ ከኾነ ፡ ተላጽቆ ፡ ተቃርቦ ፡ ያሰኛል ፡ እንጂ ፡ ፍጹም ፡ ተዋሕዶ ፡ አያሰኝም ፡ የምንልበት ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፰/ ካቶሊክ ፡ ሥጋ ፡ ወይም ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ በተዋሕዶ ፡ ጊዜ ፡ ተደባለቀ ፡ እንጂ ፡ አልተዋሐደም ፡ ብለው ፡ ያስተምራሉ ፡ የሚለው ፡ ሐሜት ፡ በኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ ይገኛል ። የካቶሊክን ፡ እውነተኛውን ፡ አሳብ ፡ ባለማወቃቸው ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ንስጥሮሳውያን ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የአውጣኪ ፡ ተከታዮች ፡ ይሏቸዋል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፰/ መደባለቅ ፡ የሚመጣ ፡ ቀድሞ ፡ መዋሐድ ፡ ቢኖር ፡ ነበረ ፡ ካቶሊካውያን ፡ አካል ፡ ተዋሐደ ፡ እንዳይሉ ፡ አካል ፡ ለቃል ፡ እንጂ ፡ ለትስብእት ፡ የለውም ፡ ይላሉ ፤ ባሕርይ ፡ ተዋሐደ ፡ እንዳይሉ ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡ ባሕርይ ፡ ተዋሐደ ፡ ማለትን ፡ በፍጹም ፡ አይሞክሩትም ።

፪ኛም ፡ የቃል ፡ አካሉ ፡ ምሉእ ፤ ስፉሕ ፤ ረቂቅ ፤ ሕማም ፡ ሞት ፡ የማይስማማው ፡ በመኾኑ ፡ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ የሠራ ፡ የተሰቀለ ፤ የሞተ ፤ ግዙፍ ፡ በኾነ ፡ ሰብአዊ ፡ አካል ፡ መኾኑ ፡ ሲታወቅ ፤ አካል ፡ ለቃል ፡ እንጂ ፡ ለትስብእት ፡ የለውም ፡ ይላሉ ።

ይህን ፡ የሚሉበት ፡ አሳባቸው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አይታወቅም ። ስለዚህ ፡ ካቶሊካውያን ፡ አልተዋሐደም ፡ ይላሉ ፡ ማለታችን ፡ አሚታ ፡ ሳይሆን ፡ ግልጥ ፡ ነው ። ተደባለቀ ፡ ይላሉ ፡ ማለትን ፡ ግን ፡ የሚናገር ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ያለ ፡ አይመስለኝም ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፱/ ኢትዮጵያውያን ፡ በክርስቶስ ፡ ሳይቀላቀሉ ፡ ሳይደባለቁ ፡ እንደማይለያዩ ፡ ኾነው ፡ የተዋሐዱ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ወይም ፡ ህላዌያት ፡ መኖራቸውን ፡ ያምናሉ ። የኹለቱን ፡ ህላዌያት ፡ መለዋወጥና ፡ መቀላቀል ፡ ወይም ፡ ያንዱን ፡ ባንዱ ፡ መጥፋትና ፡ ክርስቶስ ፡ በምትሐት ፡ ታመመ ፡ ሞተ ፡ ማለትን ፡ አይቀበሉም ።

ባንዱ ፡ ክርስቶስ ፡ ለየብቻቸው ፡ የኾኑ ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ግብሮችና ፡ ጠባዮች ፡ መኖራቸውን ፡ ያምናሉ ፤ ከነዚህም ፡ ግብሮችና ፡ ጠባዮች ፡ ለይተው ፡ አንዳንዶችን ፡ ለባሕርየ ፡ መለኮት ፤ አንዳን ዶችን ፡ ለባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ይሰጣሉ ።

ስለዚህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚታመነው ፡ ፃንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ለስም ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ በግብር ፡ እንደሚቀበሉት ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፫፱/ ሳይቀላቀሉ ፡ ሳይደባለቁ ፡ የተዋሐዱ ፡ ባሕርያት ፡ አሉት ፡ ብለው ፡ ያምናሉ ፡ ለሚሉት ፡ የቱሳሔን ፤ የውላጤን ፡ ነገር ፡ በተናገርንበት ፡ አንቀጽ ፡ በሰፊው ፡ ዘርዝረን ፡ ያስረዳን ፡ ስለሆነ ፡ አሁን ፡ ኹለተኛ ፡ ከዚህ ፡ መጻፍ ፡ አላስፈለገም ።

የክርስቶስ ፡ ሕማሙ ፡ ሞቱ ፡ በምትሐት ፡ ነው ፡ ማለትን ፡ የማንቀበል ፡ መኾናችንም ፡ እርግ ጠኛ ፡ ነገር ፡ ነው ።

የክርስቶስ ፡ ሕማሙ ፡ ሞቱ ፡ በምትሐት ፡ ኾኖ ፡ ቢኾንስ ፡ የኛም ፡ ድኅነታችን ፡ እማናዊ ፡ ሳይኾን ፡ ምትሐት ፡ ኾኖ ፡ በቀረ ፡ ነበረ ።

ባንዱ ፡ ክርስቶስ ፡ ለየብቻቸው ፡ የኾኑ ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ግብሮችና ፡ ጠባዮች ፡ መኖራቸውን ፡ ያምናሉ ፡ ስለሚሉትም ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ግብራት ፡ መኖራቸው ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ከኹኹውም ፡ አንደኛው ፡ ግብር ፡ መራብ ፡ መጠማት ፡ መተኛት ፡ መነሣት ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ ቤት ፡ ተጠርቶ ፡ መሔድ በምራቅ ፡ ጭቃ ፡ መለወስ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ኹሉ ፡ ሰብአዊ ፡ ግብር ፡ ነው ።

ኹለተኛውም ፡ ኅብስት ፡ አበርክቶ ፡ ማብላት ፡ ወኃውን ፡ ወይን ፡ አድርጎ ፡ ማጠጣት፡ ነፋሳት፡ ንና ፡ ማዕበላትን ፡ መገሠጽና ፡ ጸጥ ፡ ማድረግ ፡ በደረቅ ፡ ግንባር ፡ ዐይን ፡ መፍጠር ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ኹሉ ፡ መለኮታዊ ፡ ግብር ፡ ነው ።

እነዚህ ፡ ኹለቱ ፡ ግብራት ፡ በኹለትነት ፡ ጸንተው ፡ መኖራቸው ፡ የማይካድ ፡ ነው ። ሠሪያቸው ፡ ግን ፡ ለኹለቱም ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ እናምናለን ፡ እንጂ ፡ የመለኮትን ፡ ሥራ ፡ መለ ኮት ፡ የትስብእትን ፡ ሥራ ፡ ትስብእት ፡ ሠራ ፡ ብለን ፡ በማካፈል ፡ የምንናገር ፡ አይደለንም ።

ይህንንም ፡ ስንል ፡ የአልዓዛር ፡ እኅት ፡ ማርያ ፡ ስታለቅስ ፡ አይቶ ፡ ተንሰቅስቆ ፡ ያለቀሰና ፡ አልዓዛርን ፡ ወዴት ፡ ቀበራችሁት ፡ ብሎ ፡ የጠየቀ ፡ ኋላም ፡ አልዓዛር ፡ አልዓዛር ፡ ነዐ ፡ ፃእ ፡ አፍኣ ፡ እመቃብር ፡ ብሎ፡ያሥነሣው ፡ አንድ ፡ ሥግው ፡ ቃል ፡ ክርስቶስ ፡ ከመኾኑ ፡ በቀር ፡ አይቴ፡ ቀበር ክምዎ ፡ ብሎ ፡ የጠየቀ ፡ ትስብእት ፡ ነው ፤ አልዓዛር ፡ አልዓዛር ፡ ነዓ፡ፃእ፡ ብሎ ፡ ያስነሣው ፡ መለ ኮት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ ስለሌለ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፮

፩/ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለሃይማኖት ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲከራከሩ ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ የገለጡት ፡ ትምህርት ።

፩ ፤ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የጸፉት ፡ ኸሉ ፡ አስፈላጊም ፡ አልነበረም ፡ ምክንያቱም ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ለመጻፍ ፡ ያሰቡበት ፡ ዋናው ፡ ዓላማ ፡ የሮማንና ፡ የኢትዮጵያን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አንድ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ በመቅድሙ ፡ ላይ ፡ ገልጸው ፡ ነበረ ። ለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ማቅረቢያ ፡ የጻፉልዎ ካርዲናል ፡ ኤውጀንዮስ ፡ ቲስራንም ፡ በዚሁ ፡ ጽሑፋቸው ፡ ውስጥ ፡ ክቡር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ የደረሱት መጽሐፍ ፡ ከረጅም ፡ ዘመናት ፡ ጀምሮ ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ሮማን ፡ ለያይቶ ፡ የሚገኘውን ፡ ዋና ፡ ክርክር ለማቆም ፡ በጣም ፡ እንደሚደግፍ ፡ እያጠራጥርም ። ስላንዳንድ ፡ ትንንሽ ፡ ጉዳዮች ፡ ያለ ፡ ልዩነትን ፡ አስቀርተው ፡ እንደገና፡ አንድነትን ፡ ለማግኘት ፡ በበለጠ ፡ የሚረዱ ፡ ዘዴዎችን ፡ ያመለክታሉ ፡ ብለው በሰፊው ፡ አስረድተውን ነበረ ።

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የጻፉት ፡ ግን ፡ በእርእሱ ፡ ከተመለከተው ፡ ግብ ፡ ወጥቶ ፡ ኤውሮፓውያን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘዴ ፡ ገብተው ፡ ብዙዎችን ፡ ሀገሮች ፡ ነፃነታቸውን ፡ አሳጥተው ፡ ከጫማቸው ፡ ሥር ፡ ረግጠው ፡ በሚገዙበት ፡ ጊዜ ፡ አለያይተህ ፡ ግዛ ፡ የሚሉትን ፡ ፖለቲካ ፡ ተከትለው ፡ አለያይ ተህ ፡ ግባ ፡ ለማለት ፡ የጻፉት ፡ መስሎ ፡ ስለሚታይ ፡ ነው ።

ኹለተኛም ፡ ምስክር ፡ አድርገው ፡ የጠቀስዋቸው ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የማይስማሙ ፡ ርስ ፡ በር ሳቸው ፡ የሚጣሉ ፡ መኾናቸውን ፡ ርስዎ ፡ ራስዎ ፡ እየመሰከሩ ፡ በነርሱ ፡ ምስክርነት ፡ የኢትዮጵያን ቤት ፡ክርስቲያንእርስ፡በርሷ፡ለማለያየት፡ስለሞከሩ ነው፡የጠቀሷቸው፡ታሪክጸሐፊዎችም፡ እርስበርሳቸው፡

ባንዱ ፡ ክርስቶስ ፡ ለየብቻቸው ፡ የኾኑ ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ግብሮችና ፡ ጠባዮች ፡ መኖራቸውን ፡ ያምናሉ ፤ ከነዚህም ፡ ግብሮችና ፡ ጠባዮች ፡ ለይተው ፡ አንዳንዶችን ፡ ለባሕርየ ፡ መለኮት ፤ አንዳንዶችን ፡ ለባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ይሰጣሉ ።

ስለዚህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚታመነው ፡ ፃንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ለስም ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ በግብር ፡ እንደሚቀበሉት ፡ የተረጋገጠ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፰፱/ ሳይቀላቀሉ ፡ ሳይደባለቁ ፡ የተዋሐዱ ፡ ባሕርያት ፡ አሉት ፡ ብለው ፡ ያምናሉ ፡ ለሚሉት ፡ የቱሳሔን ፤ የውላጤን ፡ ነገር ፡ በተናገርንበት ፡ አንቀጽ ፡ በሰፊው ፡ ዘርዝረን ፡ ያስረዳን ፡ ስለሆነ ፡ አሁን ፡ ኹለተኛ ፡ ከዚህ ፡ መጻፍ ፡ አላስፈለገም ።

የክርስቶስ ፡ ሕማሙ ፡ ሞቱ ፡ በምትሐት ፡ ነው ፡ ማለትን ፡ የማንቀበል ፡ መኾናችንም ፡ እርግጠኛ ፡ ነገር ፡ ነው ።

የክርስቶስ ፡ ሕማሙ ፡ ሞቱ ፡ በምትሐት ፡ ኾኖ ፡ ቢኾንስ ፡ የኛም ፡ ድኅነታችን ፡ እማናዊ ፡ ሳይኾን ፡ ምትሐት ፡ ኾኖ ፡ በቀረ ፡ ነበረ ።

ባንዱ ፡ ክርስቶስ ፡ ለየብቻቸው ፡ የኾኑ ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ግብሮችና ፡ ጠባዮች ፡ መኖራቸውን ፡ ያምናሉ ፡ ስለሚሉትም ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ግብራት ፡ መኖራቸው ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ከኒኽውም ፡ አንደኛው ፡ ግብር ፡ መራብ ፡ መጠማት ፡ መተኛት ፡ መነሣት ፡ ወደ ፡ ሠርግ ፡ ቤት ፡ ተጠርቶ ፡ መሔድ በምራቅ ፡ ጭቃ ፡ መለወስ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ኹሉ ፡ ሰብአዊ ፡ ግብር ፡ ነው ።

ኹለተኛውም ፡ ኅብስት ፡ አበርክቶ ፡ ማብላት ፡ ወኃውን ፡ ወይን ፡ አድርጎ ፡ ማጠጣት፡ ነፋሳትንና ፡ ማዕበላትን ፡ መገሠጽና ፡ ጸጥ ፡ ማድረግ ፡ በደረቅ ፡ ምንባር ፡ ዐይን ፡ መፍጠር ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ኹሉ ፡ መለኮታዊ ፡ ግብር ፡ ነው ።

እኒህ ፡ ኹለቱ ፡ ግብራት ፡ በኹለትነት ፡ ጸንተው ፡ መኖራቸው ፡ የማይካድ ፡ ነው ። ሠሪያቸው ፡ ግን ፡ ለኹለቱም ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ እናምናለን ፡ እንጂ ፡ የመለኮትን ፡ ሥራ ፡ መለኮት ፡ የትስብእትን ፡ ሥራ ፡ ትስብእት ፡ ሠራ ፡ ብለን ፡ በማካፈል ፡ የምንናገር ፡ አይደለንም ።

ይህንንም ፡ ስንል ፡ የአልዓዛር ፡ እኅት ፡ ማርያ ፡ ስታለቅስ ፡ አይቶ ፡ ተንሰቅስቆ ፡ ያለቀሰና ፡ አልዓዛርን ፡ ወዴት ፡ ቀበራችሁት ፡ ብሎ ፡ የጠየቀ ፡ ኋላም ፡ አልዓዛር ፡ አልዓዛር ፡ ነዐ ፡ ፃእ ፡ አፍዓ ፡ እመቃብር ፡ ብሎ፡ያሥነሣው ፡ አንድ ፡ ሥጋው ፡ ቃል ፡ ክርስቶስ ፡ ከመኾኑ ፡ በቀር ፡ አይቴ፡ ቀበርክምዎ ፡ ብሎ ፡ የጠየቀ ፡ ትስብእት ፡ ነው ፤ አልዓዛር ፡ አልዓዛር ፡ ነዓ፡ፃእ፡ ብሎ ፡ ያስነሣው ፡ መለኮት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ ስለሌለ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፮

ē/ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለሃይማኖት ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲከራከሩ ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ የገለጡት ፡ ትምህርት ።

፩ ፤ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የጸፉት ፡ ኸሉ ፡ አስፈላጊም ፡ አልነበረም ፡ ምክንያቱም ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ለመጻፍ ፡ ያሰቡበት ፡ ዋናው ፡ ዓላማ ፡ የሮማንና ፡ የኢትዮጵያን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አንድ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ በመቅድሙ ፡ ላይ ፡ ገልጸው ፡ ነበረ ። ለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ማቅረቢያ ፡ የጻፉልዎ ካርዲናል ፡ ኤውጀንዮስ ፡ ቲስራንም ፡ በዚሁ ፡ ጽሑፋቸው ፡ ውስጥ ፡ ክቡር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ የደረሱት መጽሐፍ ፡ ከረጅም ፡ ዘመናት ፡ ጀምሮ ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ሮማን ፡ ለያይቶ ፡ የሚገኘውን ፡ ዋና ፡ ክርክር ለማቆም ፡ በጣም ፡ እንደሚደግፍ ፡ አያጠራጥርም ። ስላንዳንድ ፡ ትንንሽ ፡ ጉዳዮች ፡ ያለ ፡ ልዩነትን ፡ አስቀርተው ፡ አንደገና፡ አንድነትን ፡ ለማግኘት ፡ በበለጠ ፡ የሚረዱ ፡ ዘዴዎችን ፡ ያመለክታሉ ፡ ብለው በሰፊው ፡ አስረድተውን ነበረ ።

በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ የጸፉት ፡ ግን ፡ በእርእሰቱ ፡ ከተመለከተው ፡ ግብ ፡ ወጥቶ ፡ ኤውሮፓውያን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዘዴ ፡ ገብተው ፡ ብዙዎችን ፡ ሀገሮች ፡ ነፃነታቸውን ፡ አሳጥተው ፡ ከጫማቸው ፡ ሥር ፡ ረግጠው ፡ በሚገዙበት ፡ ጊዜ ፡ አለያይተህ ፡ ግዛ ፡ የሚሉትን ፡ ፖለቲካ ፡ ተከትለው ፡ አለያይተህ ፡ ግባ ፡ ለማለት ፡ የጸፉት ፡ መስሎ ፡ ስለሚታይ ፡ ነው ።

ኹለተኛም ፡ ምስክር ፡ አድርገው ፡ የጠቀስዋቸው ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊዎች ፡ የማይስማሙ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ የሚጣሉ ፡ መኾናቸውን ፡ ርስዎ ፡ ራስዎ ፡ እየመሰከሩ ፡ በነርሱ ፡ ምስክርነት ፡ የኢትዮጵያን ቤተ ፡ክርስቲያንእርስ፡በርሷ፡ለማለያየት፡ስለሞከሩ ነው፡የጠቀሷቸው፡ታሪክጸሐፊዎችም፡ እርስበርሳቸው፡

ያልተስማሙ ፡ መኾናቸውን ፡ ከገጽ ፡ ፻፭፮—፻፹፩ ፡ ባለው ፡ ጽሑፍም ፡ ዘርዝረው ፡ ጎሚሶቹን ፡ በመን ቀፍ ፡ ጎሚሶቹን ፡ በመደገፍ ፡ ጽፈዋል ፡ ስለዚህ ፡ ይጠቅሙኛል ፡ ብሎ ፡ የጠቀሳቸው ፡ ሰው ፡ ቃላቸው ርስ ፡ በርሱ ፡ የተለያየ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሐሰተኝነታቸውን ፡ ለመሰከረባቸው ፡ ጽሑፎች ፡ መልስ ፡ እሰጣ ለሁ ፡ ብሎ ፡ መድከም ፡ እንደ ፡ ሥራ ፡ ፈት ፡ ያስቆጥራል ፡ እንጂ ፡ ጥቅም ፡ አይሰጥም ። ስለኾነም መልስ ፡ ሊሰጥባቸው ፡ የሚገባ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ነገሮች ፡ ስላሉ ፡ መልስ ፡ ሳንሰጥበት ፡ አናልፍም

## ክ ፍ ል ፮ ።

## ስለክርስቶስ ፡ ቅብዐት ፡ ክርክር

### ደ ራ ሲ ።

፩/ ኢትዮጵያውያን ፡ ከካቶሊክ ፡ ሰባክያን ፡ ጋራ ፡ መገናኘታቸው ፡ የሃይማኖትን ፡ ትምርት ፡ በበለጠ ፡ ለማጥናት ፡ አነቃቃቸው ፡ ስለዚህ ፡ ለትምርት ፡ አያያዛቸው ፡ የሚበቃ ፡ ማስረጃ ፡ ለመስጠት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ አንዳንድ ፡ የሃይማኖትን ፡ ጉዳይ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ እየተከራከሩበት ፡ ለመፍታትም፡ ትምርታቸውን ፡ እንደገና ፡ ሊመረምሩ ፡ ግድ ፡ ኾነባቸው ፡ ብለዋል ።-

### መ ላ ሽ

፩/ ሥጋዊ ፡ አርበኛ ፡ መንግሥት ፡ በጸናበት ፡ ጠላት ፡ በጠፋበት ፡ ወራት ፡ ትጥቁን ፡ ፈቶ ፡ ጋሻ ፡ ጦሩን ፡ ሰቅሎ ፡ ተዘልሎ ፡ ይቀመጣል ፡ ወደ ፡ ዕለት ፡ ተግባሩ ፡ ብቻ ፡ ይሠማራል ። ጠላት ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ጋሻ ፡ ጦሩን ፡ ከሰቀለበት ፡ አውርዶ ፡ ጋሻውን ፡ ይሰነግላል ፡ ጦሩን ፡ ይወለውላል ፡ ባጭር ፡ ታጥቆ ፡ ወደ ፡ ጦሩ ፡ ሜዳ ፡ ይገሠግሣል ።

መንፈሳውያን ፡ አርበኞች ፡ ሊቃውንትም ፡ በዚሁ ፡ አንጻር ፡ መናፍቃን ፡ ጠፍተው ፡ ምእመናን ፡ በዝተው ፡ ወንጌል ፡ በምትትነገርበት ፡ እግዚአብሔር ፡ በንጹሕ ፡ በሚመለክበት ፡ ጊዜ ፡ የክርክር ፡ ጠባይዕን ፡ የሚያሳዩ ፡ መጻሕፍትን ፡ በየማኅደራቸው ፡ ከተው ፡ ፍቅርንና ፡ ሰላምን ፡ ምግባርንና ፡ ትሩ ፋትን ፡ የሚሰብኩ ፡ መጻሕፍትን ፡ ዘርግተው ፡ በማስተማር ፡ የጸሎት ፡ መጻሕፍትን ፡ አብዝቶ ፡ በመጸ ለይ ፡ ይቀመጣሉ ። አንድ ፡ መናፍቅ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ መናፍቁ ፡ የተነሣበትን ፡ ሐሳብ ፡ የሚያፈ ርሱበትን ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ለማግኘት ፡ ዐይናቸው ፡ እስኪፈዝ ፡ መጻሕፍትን ፡ ይመለከታሉ ፡ እርስ ፡ በር ሳቸው ፡ ሐሳብ ፡ ለሐሳብ ፡ ይለዋወጣሉ ።

የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንትም ፡ በዚህ ፡ ልማድ ፡ የካቶሊክ ፡ ሰባኪዎች፡ መጥተው ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በሉ ፡ የሚል ፡ ብጥብጥ ፡ እስካነሡበት፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ከፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ ባገኙት በመሠረታዊ ፡ ትምርት ፡ ጸንተው ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ፡አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ተስማ ምተው ፡ ይኖሩ ፡ ነበረ ፡ እነዚህ ፡ ሰባኪያዎች ፡ መጥተው ፡ ከመሠረተ ፡ ትምርቱ፡ ወጥተው ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ትምርት ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ በሰበኩ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ኑፋቄ፡ ለመመለስ ፡ በበ ለጠ ፡ እኳኋን ፡ ታጥቀው ፡ መነሣታቸው ፡ አይከዶም ።

ይህነንም ፡ በማድረጋቸው ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወድልዋኒከሙ ፡ ሀልዉ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ከመ ፡ ታውሥእዎሙ ፡ ቃለ ፡ ለእለ ፡ ይሴአሉክሙ ፡ በእንተ ፡ ዛቲ ፡ ተስፋክሙ ።
የሃይማኖታችሁን ፡ ነገር ፡ ለሚጠይቋችሁ ፡ ሰዎች ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ትችሉ ፡ ዘንድ ፡ አንቀጽ፡ አውጥታችሁ ፡ እልባት ፡ አልባችሁ ፡ ተዘጋጅታችሁ ፡ ቆዩ ፡ ያለውን ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፭ ።

ቅዱስ ፡ ጳውሎስም ፡ ሑሩ ፡ በልቡና ፡ ኀበ ፡ ባዕዳን ፡ እምሃይማኖት ። ከሃይማኖት ፡ በአፍኣ ወዳሉ ፡ ሰዎች ፡ በምትሔዱበት ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ቢሉን ፡ ይህን ፡ እንመልሳለን ፡ ብላችሁ ፡ ተጠንቅቃ ችሁ ፡ ሒዱ ፡ ያለውን ፡ ፈጸሙ ፡ ያሰኛል ፡ እንጂ ፡ የሚያሳማቸውና ፡ የሚያስነቅፋቸው ፡ አይደለም ። ቆላስ ፡ ፬ ፡ ፮ ።

### ደ ራ ሲ ።

፪/ በኢትዮጵያ ፡ ሃይማኖት ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ የሃይማኖት ፡ ክርክሮች ፡ ሕዝቡን እርስ ፡ በርሱ ፡ እያጣላና ፡ እያፋጀ ፡ ወደኹለት ፡ ከፍሎች ፡ የነበረውስ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ቅብዐት የተደረገው ፡ ነው ፡ ጉዳዩ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሳይወሰንና ፡ የመጨረሻ ፡ ፍጻሜ ፡ ሳያገኝ ፡ እንደ ቀረ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ፡ ብለዋል ።

### መ ላ ሽ ።

፪/ የኢትዮጵያ ፡ ሃይማኖት ፡ በሕግ ፡ ተወስኖ ፡ ጳጳሳቱ ፡ ክህነት ፡ የሚሰጡበት ፡ ንጉሡ ፡ ተቀ ብቶ ፡ የሚነግሥበት ፡ ሕዝቡ ፡ ተስማምቶ ፡ የሚኖርበት ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ ኹለት ፡

ልደት፡በተዋሕዶ፡ከበረ ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በሕገ ፡ መንግሥት ፡ ተጽፎ ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ አንቀጽ፡ ይዞ ፡ ይገኛል ።

እርስዎ ፡ ግን ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ጠቀስኩት ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ አለያይቶ ፡ መግቢያ ፡ ለማግኘት ፡ ሲጣጣሩ ፡ ይታያሉ ። ኢትዮጵያዊ ፡ የኾነው ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ ባቀረቡለት ፡ ሰብቅ ፡ ተሳስቶ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ የሚቀበል ፡ አይገኝም ። እርስዎ ፡ ግን ፡ መንፈሳዊ ፡ መነኩሴ ፡ ሲኾኑ ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ሰይጣናዊ ፡ ተንኮል፡ ሲራመዱ ፡ መታየትዎ ፡ ያሳዝናል ።

## ፪ኛ ፡ ክፍል ፡ የክርክሩ ፡ ጉዳይ ።

### ደ ራ ሲ ።

፩/ ክርክሩ ፡ የተነሣው ፡ ስለመድኃኒታችን ፡ መቀባት ፡ የሚናገሩት ፡ የቅዱሳት ፡ መጻሕፍትን ፡ ቃሎች ፡ ለየብቻው ፡ የኾነ፡ ትርጒም ፡ ከመስጠት ፡ የተነሣ ፡ ነው ። ክርስቶስ ፡ የተቀባ ፡ ማለት ፡ ከኾነ እንዲህ ፡ ባለ ፡ ስም ፡ የመጠራቱ ፡ ምክንያት ፡ ሲመራመሩ ፡ ቀቢ ፡ ተቀቢ ፡ ቅቢዕ ፡ እነዚህን ፡ ፫ቱን ፡ ነገሮች ፡ ለመወሰን ፡ ሲሞክሩ ፡ ይህ ፡ የቅብዐት ፡ ክርክር ፡ ተነሣ ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እርስ ፡ በርሷ ፡ ስለሃይማኖት ፡ ስትከራከር ፡ ያደረገችው ፡ ትግል ኹሉ ፡ የተባሉትን ሦስት ፡ ነገሮች ፡ ለማወቅና ፡ ለመወሰን ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

ከዚህም ፡ አያይዘው ፡ ፩ኛው ፡ ክፍል ፡ የደብረ ፡ ሊባኖሶቹ ፡ ባህል ፡ ሦስት ፡ ልደት ፡ ወይም ፡ የጸጋ ፡ ልጅ ፡ ይላሉ ፤ የጎጃሜዎች ፡ ወይም ፡ የትግሮች ፡ ባህል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዕ ፡ ኹለት ፡ ልደት ይላሉ ፡ ካሮች ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ ኹለት ፡ ልደት ፡ ይላሉ ፡ የ፫ ፡ ልደቱ ፡ ባህል ፡ በመሠረቱ ፡ የቀና ፡ ነው ፡ የሌሎች ፡ ባህል ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ መለያየትን ፡ በሚፈጥር ፡ አነጋገር ፡ አሳፋፍተው ፡ ጽፈዋል ።

### መ ላ ሽ ።

፩/ በሰብቅ ፡ መንገድ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሊቃውንት ፡ ለማለያየትና ፡ መግቢያ ፡ በር ፡ ለማስከፈት ሣንቃ ፡ የሚመቱበት ፡ አንቀጽ ፡ ይህ ፡ ነው ። ይህም ፡ ሐሳብ ፡ ግልጽ ፡ ኾኖ ፡ የሚታይበትን ፡ መንገድ በሚከተሉት ፡ መሥመሮች ፡ ብሰፊው ፡ እንገልጻለን ።

የዶክተር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ ሐሳብ ፡ በመሠረቱ ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሮማ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የሃይማኖት ፡ መለያየት ፡ ለማራቅና ፡ አንድ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ነበረ ። ኹለቱ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሚለያዩበት ፡ ባህል ፡ ፩ኛ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ ሠረጸ ፡ ማለት ፡ ፪ኛ ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ቢማለት ፡ ነው ፡ ብለዋል ። ይህ ፡ እውነት ፡ ከኾነ ፡ እነዚህን ፡ የተጠቀሱትን ፡ ኹለቱን ባህሎች ፡ አርቆ ፡ አንድ ፡ የሚያደርግ ፡ መንገድ ፡ በመፈለግ ፡ ፈንታ ፡ በማያገባዎ ፡ ገብተው ፡ የእገሌ ፡ ባህል ፡ የቀና ፡ ነው ፡ የእገሌ ፡ ባህል ፡ የጠመመ ፡ ነው ፡ ምን ፡ ያሰኝ ፡ ነበረ ።

የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንትስ ፡ ሳይጣሉ ፡ የተጣሉ ፡ ሳይለያዩ ፡ የተለያዩ ፡ መስለው ፡ የሚታዩ ፡ ኹሉም ፡ በየበኩላቸው ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ለመሸሽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ማናቸውም ፡ ወገን ፡ ቢኾን ፡ የካቶሊክን ፡ ባህል ፡ ገድፎ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የሚል ፡ አይገኝም ።

ይልቁንም ፡ ትምህርቱ ፡ በመሠረቱ ፡ የቀና ፡ ነው ፡ ከካቶሊክ ፡ ትምርት ፡ የራቀ ፡ አይደለም ፡ እያሉ ፡ ከንቱ ፡ ውዳሴን ፡ የሚቀባቡት ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወገን ፡ ብለው ፡ የሚጠሩትን፡ ፫፡ልደት ፡ ወይም ፡ የጸጋ ፡ ልጅ ፡ ብለው ፡ የሰየሙትን ፡ ባህል ፡ ነው ።

ይህ ፡ እውነት ፡ ከኾነ ፡ የካቶሊክ ፡ ሰባኪዎች ፡ ዐፄ ፡ ሱስንዮስን፡ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ብለህ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ዐዋጅ ፡ ብታስነግር ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከእስክንድርያ ፡ለይተህ ፡ ከሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥር ፡ እንድትተዳደር ፡ ብታደርግ ፡ ከኢስፓኝ ፡ ንጉሥ ፡ ርዳታ ፡ ይደረግልሃል ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ይላክልሃል ፡ ብለው ፡ አታለው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ መነኰሳት ፡ ከሌሎቹ ፡ ምእመናን ፡ ጋራ ፡ የሚሞቱትም ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ የሚሰደዱትም ፡ እንደ ፡ ተሰደዱ በነርሱም ፡ ቦታ ፡ በአዘዞ ፡ የካቶሊክ ፡ ሰባኪዎች ፡ እንደ ፡ ገቡ ፡ ታሪክ ፡ ይነግረናል ።

በሃይማኖት ፡ የሚመስሏቸው ፡ ከኾነ ፡ ለምን ፡ ተሰደዱ ፡ አይቀበሏቸውም ፡ ኖሯልን ፡ ካቶሊካውያኖችስ፡የሃይማኖት ፡ ወንድሞቻቸውን ፡ አባርረው ፡ በነርሱ ፡ ቦታ ፡ ለምን ፡ ገቡ ፡ የወንድሞቻችንን ፡ ቦታ ፡ አንፈልግም ፡ ብለው ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ አይፈልጉም ፡ ነበርን ።

፪ኛም ፡ ዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ በተአምራት ፡ ምላሳቸው ፡ ተዘግቶ ፡ ፋሲል ፡ ይንገሥ ፡ አሚን ፡ ይመለስ ፡ ሃይማኖተ ፡ ሮም ፡ ይደምሰስ ፡ ብለው ፡ ዐዋጅ ፡ አናግረው ፡ ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ከነገሡ ፡ በኋላ ፡ ወሶበ፡ ነግሠ ፡ ፋሲለደስ ፡ ተስእሎሙ ፡ ለአፍርንጅያት ፡ ወይቤሎሙ ፡ ለምንት ፡ አስሐትክሙ ፡ ሰብአ ፡ በሃ

ይማኖትክሙ ፡ ርኩስት ። ወይቤልዎ ፡ ንሕነሰ ፡ ኢያስሐትነ ፡ እሳ ፡ መሐርነ ፡ ጽድቀ ። ወይቤሎሙ ፡ እመሰ ፡ ጽድቅ ፡ ነገርክሙ ፡ አመጽኡ ፡ ለክሙ ፡ ማእምራነ ፡ መጻሕፍት ፡ ወተዋሥኡ ፡ ምስሌሆሙ ። ወይቤልዎ ፡ ይኩን ፡ በከመ ፡ ትቤ ፡ ወአስተጋብኦሙ ፡ ንጉሥ ፡ ለካህናተ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ተሰአልዎሙ ፡ ለእሉ ፡ ሰብእ ፡ ሮምያ ፡ ነገረ ፡ ሃይማኖቶሙ ፡ ይላል ።

እነርሱም ፡ በዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ መሪነት ፡ ቀርበው ፡ ደማችን ፡ በከንቱ ፡ ፈሶ ፡ አይቀርምና ፡ ከአልፎንሱ ፡ ጋራ ፡ እከራከረን ፡ አሉት ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ደንቀዝ ፡ ላይ ፡ ጉባኤ ፡ ተደረገ ። ፡ የደብረ ፡ ሊባኖሱ ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ኢተአምንኑ ፡ ከመ ፡ አምላክ፡ኮነ፡ሰብአ ወአድኀነነ ፡ በሞቱ ።

አምላክ ፡ ሰው ፡ እንደኾነና ፡ ሞቶ ፡ እንዳዳነን ፡ አታምንምን ፡ አሉት ፡

አምላክሰ ፡ ኢይመውት ፡ አላ ፡ ሰበ ፡ ሞተ ፡ ሥጋ ፡ ዘኀደረ ፡ ቦቱ ፡ አምላክ ፡ ተብህለ ፡ ከመ ፡ አምላክ ፡ ሞተ ፡ ወአድኀነነ ።

አምላክ ፡ ያደረበት ፡ ሥጋ ፡ ቢሞት ፡ አምላክ ፡ ሞቶ ፡ አዳነን ፡ ተብሎ ፡ ተነገረ ፡ እንጂ ፡ አምላክስ፡ አይሞትም ፡ አለ ።

ዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ሞተ ፡ ዘኢይቀርቦ ፡ ሕማመ ፡ ሞት ፡ በህላዌሁ ፡ ይልብሃልሳ ፡ አሉት ።

እርሱም ፡ እነቄርሎስስ ፡ እንደኔ ፡ ያሉ ፡ ናቸው ፡ አልቀበልም ፡ አለ ።

የሐዋርያትንሳ ፡ መጽሐፍ ፡ አትቀበልምን ፡ ቢሉት ፡ እነርሱስ ፡ መምህሮች ፡ ናቸው ፡ እቀበላለሁ ፡ አለ ።

እንግዲያስ ፡ ጳውሎስ ፡ ወሰበ ፡ እንዘ ፡ ፀሩ ፡ ንሕነ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተዛሃለነ ፡ በሞተ ፡ ወልዱ፡ ይላል ፡ ሥጋኑ ፡ ወልዱ ፡ ለአብ ፡ ወሚመ ፡ አምላክ ፡ አኮኑ ፡ አምላክ ፡ ዘኮነ ፡ ሰብአ ።

እግዚአብሔር ፡ ጠላቶቹ ፡ ስንኾን ፡ በልጁ ፡ ሞት ፡ ይቅር ፡ አለን ፡ ይላል ። የእግዚአብሔር ፡ ልጁ ፡ ሥጋ ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ አምላክ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ የሚባል ፡ ሥጋን ፡ የተዋሐደ ፡ አምላክ ፡ አይደለምን ፡ ።

ኹለተኛስ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሞተ ፡ በሥጋ ፡ ወሐይወ፡በመንፈስ ፡ በሥጋ ፡ ሞተ ፡ በመለኮት ፡ ሕያው ፡ ነው ፡ ብሏል ።

መኑ ፡ ዘሐይወ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘሐመ ።

የተነሣው ፡ ማነው ፡ የሞተው ፡ ክርስቶስ ፡ አይደለምን ።

ዝኒ ፡ ያጤይቅ ፡ ተዋሕዶተ ፡ መለኮት ።

ይህም ፡ የመለኮትንና ፡ የትስብእትን ፡ ተዋሕዶ ፡ ያስረዳል ።

ዮሐንስኒ ፡ ይቤ ፡ ዝውእቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘሰማዕነ ፡ በእዘኒነ ፡ ዘርኢነ ፡ በአዕይንቲነ ፡ ወዘጠየቅነ ፡ ወዘገሠሣሁ ፡ እደዊነ ፡ በእንተ ፡ ነገረ ፡ ሕይወት ፡ መኑ ፡ ውእቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ወመኑ ፡ ውእቱ፡ ዘገሠሣሁ ፡ አኮኑ ፡ ውእቱ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘተንሥአ ፡ እሙታን ።

ዮሐንስም ፡ በጆሮዎችን ፡ የሰማነው ፡ ባይናችን ፡ ያየነው ፡ በእጃችን ፡ ዳሰን ፡ የተረዳነው ፡ እርሱ በቅድምና ፡ የነበረ ፡ መኾኑን ፡ እንነግራችኋለን ፡ ብሏል ።
የቅድምናውን ፡ ነገር ፡ እምቅድመ ፡ ይትወለድ ፡ አብርሃም ፡ ሀሎኩ ፡ አነ ፡ ሲል ፡ የሰማነው ፡ ሕያው ፡ ማሕየዊ ፡ አምላክ ፡ መኾኑንም ፡ በደረቅ ፡ ግንባር ፡ ዐይን ፡ ሲፈጥር ፡ ለምጽ ፡ ሲያነጻ ፡ ጋኔን ሲያስወጣ ፡ ያየነው ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ መነሣቱንም ፡ ዳሰሰን ፡ የተረዳነው ፡ ማነው ፡ ይህ ፡ ከሙታን ፡ ተለይቶ ፡ የተነሣው ፡ ክርስቶስ ፡ አይደለምን ፡ ፡ አሉት ።

ለዚሁ፡ ማፍረሻ ፡ የበቃ ፡ መልስ ፡ አጣ ፡ በዚህ ፡ ተረታ ። የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንትም ፡ ጠላቶቻቸው ካቶሊካውያንን ፡ በፈርዖንና ፡ በሠራዊቱ ፡ አፈ ፡ ጉባኤ ፡ ያደረጓቸው ፡ ዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስን ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ ኃይለ ፡ ቃላቸውን ፡ እንደ ፡ በትረ ፡ ሙሴ ፡ ራሳቸውን ፡ እንደ ፡ ሕዝበ ፡ እስራኤል ፡ በካቶሊካውያን ፡ ምክንያት ፡ በዐፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ዘመን ፡ የደረሰባቸውን ፡ ሥቃይ ፡ እሥራኤል ፡ በፈርዖን ፡ ቤት ፡ በተሠቃዩት ፡ ሥቃይ ፡ በዚህ ፡ ክርክር ፡ ያገኙትን ፡ እርታታ ፡ በሙሴ ፡ መሪነት ፡ የኤርትራን ፡ ባሕር ፡ ከፍለው ፡ በመሻገራቸው ፡ የጠላቶቻቸውን ፡ የነአልፎንሱን ፡ መረታት ፡ በፈርዖን ፡ ስጥመት ፡ መስለው ፡ ንሴብሖ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስቡሐ ፡ ዘተሰብሐ ፡ እያሉ ፡ በከበሮ ፡ በጽናጽል ፡ አሸበሸቡ ።

ሊቁም ፡ እምተበቅሎ ፡ ሰብእ ፡ ነውር ፡ እስከ ፡ ትኅጽሕ ።
ርእስ ፡ ትትቀባዕ ፡ በትረ ፡ እደ ፡ ሰብእ ፡ ዐበሜ ።

እርዌ ፡ ምድር ፡ ዘሰትየት ፡ ዐቂበ ፡ ሰኩና ፡ ከራሚ ።
ወእመ ፡ ይወፅኡ ፡ እስራኤል ፡ እምግብጽ ፡ ድኅረ ፡ ተፈጸመ ፡ ዘገዐር ፡ ዕድሜ ፡

በነፋስ ፡ በትረ ፡ ሙሴ ፡ ይቡስ ፡ ኮነ ፡ ዘባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ ልምላሜ ።
ንሕነሂ ፡ ዘዐገተነ ፡ ባህለ ፡ እለ ፡ ልዮን ፡ ጊሜ ።
በባህሎሙ ፡ ማዕበል ፡ ከመ ፡ ኢንሥጠም ፡ ልዳሜ ።
ረከብናሁ ፡ ለበትር ፡ ዘያጸክም ፡ ሰርሜ ።
ጽሩብ ፡ በንባብ ፡ ወቅሩጽ ፡ በትርጓሜ ።

የሚል ፡ መወድስ ፡ ቅኔ ፡ አበረከተ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሮማውያንን ፡ ጠራርገው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ አስወጥዋቸው ፡ ቤት ፡ ሠርተው ፡ ተክል ፡ ተክለው ፡ ይኖሩባት ፡ የነበረች ፡ አዘዞንም ፡ ንጉሡ ፡ ለደብረ ፡ ሊባኖሶች ፡ መለስላቸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሠርቶ ፡ ከአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መቃብር፡ ከሸዋ ፡ ያመጧትን፡ ታቦተ ፡ ማርያምን ፡ አኖረ ፡ የሚል ፡ ታሪክ ፡ እናገኛለን ።

ምንም ፡ ይህነን ፡ ስም ፡ የያዙ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖሶች ፡ ለመኾናቸው ፡ እርግጠኛ ፡ ባልኾን ፡ ፫ ፡ ልደቶች ፡ ወይም ፡ የጸጋ ፡ ልጆች ፡ የሚባሉት ፡ ወገኖች ፡ ባህል ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

እግዚአብሔር ፡ አዳምን ፡ ፈጥሮ ፡ በንፍሐት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አሳድሮ ፡ የጸጋ ፡ ልጅነትን ሰጥቶት ፡ ነበረ ። ዕፀ ፡ በለስን ፡ በበላ፡ጊዜ፡ይህችን፡ልጅነት፡አስወሰደ ፡ ንስሐ ፡ ቢገባ ፡ ይህችን ፡ ልጅነት ፡ ተመልሶ ፡ ማግኘት ፡ አልቻለም ፡ ስለዚህ ፡ ከ፫ቱ ፡ አካላት ፡ አንዱ ፡ አካል ፡ ቃል ፡ ሥጋን ፡ ተዋሕዶ አንድ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኾኖ ፡ በተዋሕዶ ፡ ምንታዌ ፡ ጠፋ ፡ በተዋሕዶ ፡ የባሕርይ ልጅ ፡ ኾነ ፡ ያችን ፡ አዳም ፡ ያስወሰዳትን ፡ ልጅነት ለመመለስ ፡ ሲል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በማኅፀን ፡ ተቀብሎ ፡ የአዳምን ፡ ልጅነት ፡ ገንዘብ ፡ ስላደረገ ፡ ዳግማይ ፡ አዳም ፡ ተባለ ፡ በኩረ ፡ ምእመናን ፡ ኾነ ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አይሉም ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ግንኙነት ፡ የሌላቸውን ፡ ወገኖች ፡ ከካቶሊክ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ መናገር አይገባም ።

፪ኛም ፡ እርስዎ ፡ ጎጃሚዎችና ፡ ትግሮች ፡ እያሉ ፡ የሚጠሩዋቸው ፡ ቅብዐቶች ፡ የሚባሉት ወገኖችም ፡ ቃል ፡ ሥጋን ፡ በተዋሐደ ፡ ጊዜ ፡ በተዋሕዶ ፡ ምንታዌ ፡ ጠፋ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኾነ ፡ ሲዋሐድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀብሎ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ ኾነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን፡ በመቀበሉ ፡ ንዴት ፡ ጠፋለት ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ካቶሊክ ፡ ባህል ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አይሉም ።

፫ኛም ፡ እርስዎ ፡ ካሮች ፡ እያሉ ፡ በሽሙጥ ፡ ቃል ፡ የሚጠርዋቸው ፡ ባህላቸው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ የታወቀላቸው ፡ ተዋሕዶዎችም ፡ ቃል ፡ ሥጋን ፡ ሲዋሐድ ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኾነ ፡ በተዋሕዶ ፡ ንዴትም ፡ ምንታዌም ፡ ጠፉ ፡ ቃል ፡ የነሣው ፡ ሥጋ ፡ የባሕርይ ፡ ክብርን ፡ በተዋሕዶ ፡ አገኘ ፡ እንጂ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አልከበረም ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ሦስቱም ፡ ወገኖች ፡ ከካቶሊክ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ኹለት ፡ ፈቃድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ ሠረጸ ፡ በማለት ፡ የሚተባበር ፡ የለም ።

እርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ሲከራከሩ ፡ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ይህማ ፡ እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ እንደ ፡ ልዮን ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ያሰኝብሃል ፡ እየተባባሉ ፡ ኹሉም ፡ በየበኩላቸው ፡ የንስጥሮስና ፡ የልዮን ፡ ተቃራኒዎች ፡ መኾናቸውን ፡ ይገልጻሉ ፡ እንጂ ፡ ከውስጣቸው ፡ የልዮንን ፡ ባህል ፡ የሚደግፍ ፡ አይገኝም ፡ ስለዚህ ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ራሱን ፡ ከሚቃወሙት ፡ ከ፫ ፡ ወንድማማቾች ፡ መካከል፡ በማያገባው ነገር ፡ ጥልቅ ፡ ብሎ ፡ ጉብቶ ፡ የማያውቁትን ፡ የእገሌ ፡ ባህል ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ የእገሌ ባህል ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ የእገሌ ፡ ባህል ፡ በመሠረቱ ፡ የቀና ፡ ነው ፡ የእገሌ ፡ ባህል ፡ የተሳሳተ ፡ ነው እያሉ ፡ ወንድማማቾችን ፡ በከንቱ ፡ ውዳሴ ፡ ለያይቶ ፡ ረዳትና ፡ ወገን ፡ ለማግኘት ፡ መሞከር ፡ አሲያይትሀ ፡ ግዛ ፡ የተባለውን ፡ ፖለቲክ ፡ የመሰለ ፡ ስብቅ ፡ ነው ፡ ቢባል ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ በቀር የማይገባ ፡ አነጋገር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሚቃወም ፡ አይገኝም ።

አሁን ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የነእገሌ ፡ ባህል ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የእነገሌ ፡ ባህል ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የ፫ቱንም ፡ ባህል ፡ ባጭሩ ፡ ለመግለጽ ፡ ያሳሰበኝ ፡ ኹሉም ፡ በየበኩላቸው ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን፡ ባህል ፡ ተቃዋሚዎች ፡ መኾናቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የተቀብዐን ፡ ምሥጢር ፡ ለካቶሊካውያን ፡ ለመግለጽ ፡ ብዬ ፡ አይደለም ። ምክንያቱም ፡ አባ ፡ እየለ ፡ ይህን ፡ ባህል ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ መጥቀሳቸው ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ዘረዘርኩት ፡ እርስ፡በርስ፡ለመለያየትና፡መግቢያ፡ለማግኘትእንጂ፡ነገሩ ፡

የሚያገባቸው ፡ ኹኖ ፡ የጸፉት ፡ አለመኾኑን ፡ በመረዳት ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ የግል ፡ ጉዳያችንን፡ ወደ፡ ጐን ፡ አኑረን ፡ በኦርቶዶክሳውያንና ፡ በካቶሊካውያን ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ወደ ፡ መመርመር ፡ እንመለስ ።

## ደ ራ ሲ ።

፭/ ለናዝሬቱ ፡ ኢየሱስ፡ቅብዕ፡የኾነው፡መንፈስ፡ቅዱስ ፡ ከአብና፡ከወልድ፡በአስትንፋስ፡ስለሚሠርጽ ፡ በጊዜ፡ሳይኾን፡በመሥረጹ፡ሲመለከቱት፡የቃል ፡ መወለድ፡ከመንፈስ፡ቅዱስ፡በአስትንፋስ ፡ መሥረጽ፡ እንደሚቀድም ፡ ግልጥ ፡ ነው ፡ እስዚያ ፡ የመለኮታውያን ፡ አካላት ፡ አወጣጥ ፡ ተርታ ፡ ማለት ፡ አብ ፡ ከማንም ፡ አለመውጣቱ ፡ ወልድ ፡ ከአብ ፡ መወለዱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብና ፡ ከወልድ ፡ መሥረጹ ፡ ይፋለስ ፡ ነበረ ፡ ካሉ ፡ በኋላም ፡ አብና ፡ ወልድ ፡ እንዳንድ ፡ ምንጭ ፡ ኹነው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ስለሚያሠርጹት ፡ በአሥራጺነታቸው፡ ከርሱ ፡ ይበልጡ ፡ ይቀድሙም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከቃል ፡ ሊበልጥ ፡ የማይቻል ፡ ነው ፡ ያሉትን ፡ እንመርምር ።

## መ ላ ሽ ።

፭/ ይህ ፡ አነጋገር ፡ አንደኛ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ እንደሠረጸ ፡ ኹለተኛ ፡ የወልድ ፡ ከአብ ፡ መመለድ ፤ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መሥረጽ፡ እንዲቀድም ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ መሥረጽ ፡ ከወልድ ፡ መወለድ ፡ ወደኋላ ፡ እንዲኾን ፡ ያመለክታል ።

ኹሉም ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ የማይገኝ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ አሳብ ፡ ነው ፡ መጻሕፍት ፡ ለወልድም ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ መሠረታቸው ፡ መገኛቸው ፡ አብ ፡ ብቻ ፡ እንደኾነ ፡ ሦስቱም ፡ በክብርም ፡ በዘመንም ፡ ዕሩያን ፡ መኾናቸውን ፡ በነፍስ ፡ በፀሐይ ፡ በእሳት ፡ በቀላይ ፡ መስለው ፡ ይነግሩናል ፡ በሥላሴ ፡ መቅደም ፡ መቀዳደም ፡ መብለጥ ፡ መበላለጥ ፡ እንዳለባቸው ፡ አይነግሩንም ።

## ፯ኛ ፡ ስለ ፡ አብ ፡ መሠረትነት ።

ለወልድና ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መገኛቸው ፡ መሠረታቸው ፡ አብ ፡ መኾኑን ፡ ሲያስረዳ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እስመ ፡ አነ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ወፃእኩ ፡ ወመጻእኩ ፡ ብሏል ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፵፪ ።

መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ከአብ ፡ ብቻ ፡ መሥረጹን ፡ ሲያስረዳ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ መንፈስ ፡ ጽድቅ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምኀበ ፡ አብ ፡ ውእቱ ፡ ሰማዕትየ ፡ ብሏል ፡ ዮሐንስ ፡ ፲፭ ፡ ፳፮ ፡ ከአብ ፡ እንደሠረጸ ፡ ከወልድም ፡ የሚሠርጽ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምኀበ ፡ አብ ፡ ብሎ ፡ ወእምኔየ ፡ ባለ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ እምኀበ ፡ አብ ፡ ማለቱ ፡ ብቻ ፡ ባልበቃውም ፡ ነበረ ።

ይህን ፡ የጌታን ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ሐዋርያት ፡ በጸሎተ ፡ እመክንዮ ፡ ወፈነወ ፡ ለነ ጰራቅሊጦስሃ ፡ መንፈሰ ፡ ጽድቅ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምኀበ ፡ አብ ፡ ወአድኀነ ፡ ኵሎ ፡ ዓለመ ፡ ብለዋል ።

፫፻፲፰ ፡ በጸሎተ፡ሃይማኖት፡ወነአምን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እግዚእ ፡ ማኅየዊ ፡ ዘሠረጸ ፡ እምአብ ብለዋል ፡ ከዚህ ፡ አያይዘው ፡ ልደተ ፡ ወልድ ፡ ወፀአተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እምአብ ፡ ይትነከር ፡ ወኢይትነገር ፡ እያሉ ፡ የተናገሩ ፡ ሊቃውንት ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። ከዚህ ፡ ወጥቶ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ፡ ሠረጸ ፡ የሚል ፡ አይገኝም ።

## ፰ኛ ፡ ስለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዕሪና ።

መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብ ፡ ከወልድ ፡ በክብር ፡ የማያንስ ፡ ወደኋላ ፡ የማይል ፡ መኾኑንም ፡ ይፌኑ ለከሙ ፡ ጰራቅሊጦስሃ ፡ ካልአ ፡ ዘከማየ ፡ ብሏል ፡ ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፲፮ ። ሕጸጽ፡ ቢኖርበት ፡ ዘከማየ ፡ ባላለም ነበርና ።

በማቴዎስም ፡ ወአንዘ ፡ ታጠምቅዎሙ ፡ በሉ ፡ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብሏል ፡ ማቴ ፡ ፳፰ ፡ ፳ ።

ከዚህ ፡ አያይዘው ፡ ሐዋርያት ፡ በጸሎተ ፡ አመክንዮ ፡ ዘህልው ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ብለዋል ፡ ለአውግዞ ፡ መቅዶንዮስ ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ የተሰበሰቡ ፡ ፻፶ ፡ ሊቃውንትም ፡ ምስለ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ዘነበበ ፡ በነቢያት ፡ ብለዋል ። ይህንም ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ አሐቲ ፡ ቅድምናሆሙ ፡ ለሥላሴ ፡ ወዕሩያን ፡ እሙንቱ ፡ በቅድምና ፡ እያሉ ፡ የጻፉ ፡ ሊቃውንት ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ።

## ፫ኛ ፡ የሥላሴ ፡ ምሳሌዎች ።

የሥላሴን ፡ አንድነት ፡ ፫ትነት ፡ በነፍስ ፡ በእሳት ፡ በፀሐይ ፡ በቀላይ ፡ የመሰሉልንን ፡ ምሳሌ ፡
እንመርምር ። ፩ኛ ፡ ሥላሴ ፡ በነፍስ ፡ ይመሰላሉ ፡ ነፍስ ፡ በአካልዋ ፡ አንድ ፡ ስትሆን ፡ በከዊን ፡ ፫ ፡
ናት ። ይኸውም ፡ ልብ ፡ መኾን ፡ ቃል ፡ መኾን ፡ እስትንፋስ ፡ መኾን ፡ ነው ። በልብነቷ ፡ አብ ፡
በቃልነቷ ፡ ወልድ ፡ በእስትንፋስነቷ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመሰላል ። ልብነቷ ፡ ቃልነቷን ፡ እስትን
ፋስነቷን ፡ ያስገኛል ፡ እንጂ ፡ ቃልነቷ ፡ ወይም ፡ እስትንፋስነቷ ፡ ልብነቷን ፡ አያስገኝም ።

እንደዚኹሁም ፡ ቃልነቷ ፡ እስትንፋስነትዋን ፡ እስትንፋስነቷ፡ቃልንትዋን ፡ ሊያስገኝ ፡ አይች
ልም ። እንዲህም ፡ ማለት ፡ ቃል ፡ እስትንፋስ ፡ ከልብ ፡ ይመነጫሉ ፡ እንጂ ፡ ልብ ፡ ከቃል ፡ ከእስትን
ፋስ ፡ አይገኝም ፡ ቃልም ፡ እስትንፋስን ፡ እስትንፋስ ፡ ቃልን ፡ ሊያስገኝ ፡ አይችልም ፡ ማለት ፡ ነው ።

እንደዚኹሁም ፡ በቃል ፡ የተመሰለ ፡ ወልድ ፡ በእስትንፋስ ፡ የተመሰለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በልብ
ከተመሰለ ፡ ከአብ ፡ ይገኛሉ ፡ እንጂ ፡ አብ ፡ ከወልድ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አይገኝም ። በቃል ፡ የተ
መሰለ ፡ ወልድም ፡ በእስትንፋስ ፡ የተመሰለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አያስገኝም ፡ በእስትንፋስ ፡ የተመ
ሰለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በቃል ፡ የተመሰለ ፡ ወልድን ፡ አያስገኝም ።

መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ ይሠርጻል ፡ ማለት ፡ እስትንፋስ ፡ ከቃል ፡ ይመነጫል ፡ ማለት ፡ ነው።

## በቅድምና ፡ ዕሩያን ፡ ስለመኾናቸው ።

ልብ ፡ ከቃል ፡ ከእስትንፋስ ፡ ጋራ ፡ ባንድነት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይገኛል ፡ እንጂ ፡ ከቃል ፡ ከእስት
ንፋስ ፡ ቀድሞ ፡ መገኘት ፡ የለበትም ፡ ቃልም፡ ከእስትንፋስ፡ከልብ ፡ እስትንፋስም ፡ ከልብ ፡ ከቃል ፡
ቀድሞ ፡ መገኘት ፡ የለባቸውም ፡ እንደዚኹሁም ፡ አብ ፡ ከወልድ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቀድሞ ፡ የተ
ገኘበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ፡ ወልድም ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ፡አይቀድምም፡ ቀድሞ ፡ የተገኘበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ፡
ወልድም ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አይቀድምም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ ወደኋላ ፡ አይኾንም ።

## ፪ኛ ፡ ሥላሴ ፡ በፀሐይ ፡ ይመሰላሉ ።

ለፀሐይ ፡ ክበብ ፡ ብርሃን ፡ ዋዕይ ፡ አለው ፡ በክበቡ ፡ አብ ፡ በብርሃኑ ፡ ወልድ ፡ በዋዕዩ ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ ይመሰላሉ ። ክበብ ፡ ዋዕይን ፡ ብርሃንን ፡ ያስገኛል ፡ እንጂ ፡ ብርሃን ፡ ዋዕይን ፡ ክበብን ፡ አያ
ስገኝም ፡ ዋዕይም ፡ ክበብን ፡ ብርሃንን ፡ አያስገኝም ።
እንደዚኹሁም ፡ በክበብ ፡ የተመሰለ ፡ አብ ፡ በብርሃን ፡ የተመሰለ ፡ ወልድን ፡ በዋዕይ ፡ የተመሰለ
መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ያስገኛል ፡ እንጂ ፡ በብርሃን ፡ በዋዕይ ፡ የተመሰሉ ፡ ወልድ፡ መንፈስ፡ቅዱስ፡በክ
በብ ፡ የተመሰለ ፡ አብን ፡ አያስገኙትም ።

ብርሃን ፡ ዋዕይን ፡ ዋዕይ ፡ ብርሃንን ፡ ሊያስገኝ ፡ እንደማይችል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወልድን ፡
ወልድም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ሊያስገኝ ፡ አይችልም ፡

ክበብ ፡ ሲገኝ ፡ ብርሃን ፡ ዋዕይ ፡ አብረው ፡ ይገኛሉ ፡ እንጂ ፡ ክበብ ፡ ቀድሞ ፡ ብርሃን ፡ ዋዕይ ፡
ኋላ ፡ የሚገኙ ፡ አይደሉም ።

እንደዚኹሁም ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደ ፡ አብ ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ህልዋን፡ናቸው
እንጅ ፡ አብ ፡ በዘመን ፡ ቀድሟቸው ፡ ኋላ ፡ የተገኙ ፡ አይደሉም። ክበበ ፡ ፀሐይ ፡ ብርሃንን ፡ ዋዕይን ፡
እየላከ ፡ መኖሩን ፡ ያስታውቃል ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡ ዋዕይ ፡ የሚላክ ፡ አይደለም ።
እንደዚኹሁም ፡ አብ ፡ ወልድን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ እየላከ ፡ ህልውናውን፡ይገልጻል ፡ እንጂ
ለማንም ፡ የታየና ፡ የተገለጸ ፡ አይደለም ። ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፲፰ ።

ስለዚህ ፡ መጻሕፍት ፡ አብን ፡ ፈናዊ ፡ ላኪ ፡ ወልድን ፡ ተፈናዊ ፡ ተላኪ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡
ተፈናዊ ፡ ተላኪ ፡ እያሉ ፡ ይነግሩናል ፡ እንጂ ፡ በክበብ ፡ በብርሃን ፡ በዋዕይ ፡ መቅደም ፡ መቀዳደም
መከተል ፡ መከታተል ፡ እንደሌለባቸው ፡ በሥላሴም ፡ መቅደም ፡ መቀዳደም ፡ መከተል ፡ መከታ
ተል ፡ የለባቸውም ።

## ፫ኛም ፡ ሥላሴ ፡ በእሳት ፡ ይመስላሉ ።

በነበልባሉ ፡ አብ ፡ በብርሃኑ ፡ ወልድ ፡ በዋዕዩ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመሰላሉ ፤ ነበልባል ፡ ብርሃ
ንን ፡ ዋዕይን ፡ ያስገኛል ፡ እንጂ ፡ ብርሃን ፡ ዋዕይ ፡ ነበልባልን ፡ አያስገኙትም ፡ ወይም ፡ ብርሃን ፡ ዋዕ
ይን ፡ ዋዕይ ፡ ብርሃንን ፡ አያስገኝም ። እንደዚኹሁም ፡ በነበልባል ፡ የተመሰለ ፡ አብ ፡ በብርሃን ፡ የተ
መሰለ ፡ ወልድን ፡ በዋዕይ ፡ የተመሰለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ያስገኛል ፡ እንጂ ፡ በብርሃን ፡ በዋዕይ ፡
የተመሰሉ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በነበልባል ፡ የተመሰለ ፡ አብን ፡ አያስገኙትም ።

እንደዚኹሙም ፡ ብርሃን ፡ ዋዕይን ፡ ዋዕይ ፡ ብርሃንን ፡ ሊያስገኝ ፡ እንደ ፡ ማይቻል ፡ በብርሃን ፡ የተመሰለ ፡ ወልድም ፡ በዋዕይ ፡ የተመሰለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ወይም ፡ በዋዕይ ፡ የተመሰለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በብርሃን ፡ የተመሰለ ፡ ወልድን ፡ አያስገኝም ።

ነበልባል ፡ ከብርሃን ፡ ከዋዕይ ፡ መቅደም ፡ መብለጥ ፡ እንደሌለበት፡ለብርሃንና ፡ ለዋዕይም ፡ ከነበልባል ፡ ማነስ ፡ ወይም ፡ ወደኋላ ፡ መኾን ፡ እንደሌለባቸው ፡ አብም ፡ ከወልድ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አይቀድምም ፡ አይበልጥም ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ከአብ ፡ አያንሱም ፡ በዘመን ፡ ወደ ፡ ኋላ አይሉም ፡ ወልድም ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አይበልጥም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ከወልድ ፡ አያንስም ፡ በዘመን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አይልም ።

አብ ፡ ፈናዊ ፡ ወልድ ፡ ተፈናዊ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተፈናዊ ፡ መባላቸውም ፡ ከላይ ፡ በፀሐይ ፡ ምሳሌነት ፡ እንደ ፡ ገለጥነው ፡ ነበልባል ፡ ብርሃኑን ፡ ፈንጥቆ ፡ ጨለማን ፡ በማራቁ ፡ ዋዕዩን ፡ ልኮ ፡ በመሞቁ ፡ ህልውናውን ፡ እንዲያሳውቅ ፡ የአብም ፡ ህልውናው ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስለተገለጸ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሥላሴ ፡ መቅድም ፡ መቀዳደም ፡ መብለጥ ፡ መበላለጥ ፡ ኖሮባቸው ፡ አይደለም ። እኛ ፡ ኦርቶዶክሳውያን ፡ ስለምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ ያለን ፡ አስተያየትና ፡ እምነት ፡ ይህ ፡ ነው ።

## እንግዲህ ፡ የካቶሊካውያንን ፡ ባህል ፡ ወደመመርመር ፡ እንመለስ ።

፩/ ዶክተር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ በዚህ ፡ በጽሑፍም ፡ ውስጥ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ ሠረጸ ፡ ማለትን ፡ ብቻ ፡ ይናገራሉ ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ የሰጡት ፡ መረጃ ፡ የለም ፡ አባ፡ ዮሐንስ፡ተክለ፡ሚካኤል የተባሉ ፡ የካቶሊክ ፡ መነኩሴ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ ሠረጸ ፡ የሚል ፡ ከምን ፡ መጽሐፍ፡ ይገኛል ፡ ብዩ ፡ ብጠይቃቸው ፡ ፩ኛ ፡ ከዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ም ፡ ፲፭ ፡ ቍ ፡ ፳፮ ፡ ም ፡ ፲፮ ፡ ቍ ፡ ፯ ፡ ም ፡ ፲፮ ፡ ቍ ፡ ፲፬ ፡ ም ፡ ፳ ፡ ቍ ፡ ፳፪ ፡ ጠቀሱልኝ ።

፪/ ከመጽሐፉ ፡ ገብቼ ፡ ብመረምር ፡ በም ፡ ፲፭ ፡ ቍ ፡ ፳፮ ፡ የጠቀሱት ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ወሶበ ፡ መጽአ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ ዘአነ ፡ እፌኑ ፡ ለክሙ ፡ መንፈሰ ፡ ጽድቅ ፡ ዘይወፅእ ፡ እምኀበ ፡ አብ ፡ውእቱ ፡ ሰማዕትየ ።

እኔ ፡ የምልክላችሁ ፡ ከአብ ፡ የሠረጸ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ ምስክሬ ፡ ነው፡ ብሎ ፡ ከአብ ፡ መሥረጹን ፡ ያስረዳል ፡ እንጂ ፡ ከወልድ ፡ እንደ ፡ ሠረጸ ፡ አያስረዳም ።

በም ፡ ፲፮ ፡ በቍ ፡ ፯ ፡ የጠቀሱትም ፡ እመ ፡ ኢሖርኩ ፡ አነ ፡ ኢይመጽእ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ ኀቤክሙ ወእመሰ ፡ ሖርኩ ፡ አነ ፡ እፌንዎ ፡ ለክሙ ።

እኔ ፡ ካልሔድኩ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ ወደናንተ ፡ አይመጣም ፡ እኔ ፡ የሔድኩ ፡ እንደኾነ ፡ ግን እሰድላችኋለሁ ፡ ብሎ ፡ በተነሣ ፡ በ፵ ፡ ቀን ፡ ባረገ ፡ በ፲ ፡ ቀን ፡ በጽርሐ ፡ ጽዮን ፡ የላከላቸውን ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተስፋ ፡ ያስረዳል ፡ እንጂ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ መሥረጹን ፡ አያስረዳም ።

በቍ ፡ ፲፬ ፡ የጠቀሱትም ፡ ወኪያየ ፡ ይሴብሕ ፡ ውእቱ ፡ እስመ ፡ እምዚአየ ፡ ይነሥእ ፡ ወይነግረ ክሙ ።

እርሱ ፡ እኔን ፡ ያመሰግናል ፡ ከእኔ ፡ ነሥቶ ፡ ይነግራችኋልና ፡ የሚል ፡ ነው ፡ ይህም ፡ ጥቅስ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ እርእስቱን ፡ ሲመለከቱት ፡ ውብየ ፡ ብዙኅ ፡ ነገር ፡ ዘእነግረክሙ ፡ ወባሕቱ ፡ ኢትክሉ ጸዊሮቶ ፡ ይእዜ ፡ ወመጺኦ ፡ ውእቱ ፡ መንፈሰ ፡ ጽድቅ ፡ ይመርሀክሙ ፡ ኀበ ፡ ኵሉ ፡ ጽድቅ ፡ እስመ ኢይነግር ፡ ዘእምኀቤሁ ፡ ወዘሰምዐ ፡ ዳዕሙ ፡ ይነግር ፡ ወዘይመጽእ ፡ ይነግረክሙ ።

ዛሬ ፡ ልትይዙት ፡ ልታጠኑት ፡ አትችሉም ፡ እንጂ ፡ የምነግራችሁ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ነበረኝ ፡ ነገር፡ ግን ፡ እርሱ ፡ የእውነት ፡ መንፈስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እውነት ፡ ኹሉ ፡ ይመራችኋል ፡ የሚሰማውን ፡ ኹሉ ፡ ይነግራል ፡ እንጂ ፡ ከራሱ ፡ አይነግርምና ፡ የሚመጣውን ፡ ይነግራችኋል ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ እርሱ ፡ እኔን ፡ ያከብራል ፡ ለእኔ ፡ ካለኝ ፡ ወስዶ ፡ ይነግራችኋል ፡ እላችኋለሁ ፡ ለአብ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ የእኔ ፡ ነውና ፡ ስለዚህ ፡ ለኔ ፡ ካለኝ ፡ ወስዶ ፡ ይነግራችኋል ፡ እላችኋለሁ ፡ ብሏል ።

ይህንንም ፡ ወደ ፡ ምሥጢሩ ፡ ገባ ፡ ብሎ ፡ ቢመረምሩት ፡ ለእኔ ፡ ካለኝ ፡ ወስዶ ፡ ይነግራችኋል ፡ ማለት ፡ ከርሱ ፡ የሚወስደው ፡ በእርእስቱ ፡ ዛሬ ፡ ልትይዙት ፡ አትችሉም ፡ እንጂ ፡ የምነግራችሁ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ነበረኝ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ ይነግራችኋል ፡ ያላቸውን ትምርቱን ፡ እንደኾነ ፡ በግልጥ ፡ ይረዳል ።

ለአባቴ ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ለእኔ ፡ አለኝና ፡ ከእኔ ፡ ወስዶ ፡ ይነግራችኋል ፡ ማለቱም ፡ በም ፡ ፯ ፡ በቍ ፡ ፲፮ ፡ ትምህርትየሰ ፡ ኢኮነት ፡ እንቲአየ ፡ አላ ፡ እንቲአሁ ፡ ለዘፈነወኒ ፡ ወዘሰ ፡ ይፈቅድ ፡ ይግበር ፡ ሥምረቶ ፡ ውእቱ ፡ የአምር ፡ ከመ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሐር ፡ ውእቱ ፡ ትምህርትየ ፡ ወእኮ ፡ ዘእምኀቤየ ፡ ዘእነግር ።

የማስተምራችሁ ፡ ትምርት ፡ ከላከኝ ፡ ከአብ ፡ የተገኘች ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ ከኔ ፡ የተገኘች ፡ አይደ ለችም ፤ ፈቃዱን ፡ ሊፈጽም ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ይህ ፡ የማስተምረው ፡ ትምህርት ፡ ከራሴ ፡ አንቅቼ ፡ የምናገረው ፡ እንዳይደለ ፡ ትምህርቴም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘ ፡ እንደኾነ ፡ ያውቃል ፡ ብሎ ፡ በም ፡ ፰ ፡ በቊ ፡ ፲፰ም ፡ ወእኮ ፡ ዘእምኀቤየ ፡ ዘእነግር ፡ አላ ፡ በከመ ፡ መሀረኒ ፡ አቡየ ፡ ከማሁ እነግር ።

አባቴ ፡ እንዳስተማረኝ ፡ አስተምራለሁ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ ከራሴ ፡ አንቅቼ ፡ አላደርግም ፡ አላስተም ርም ፡ ብሎ ፡ ለትምርቱ ፡ መደበኛ ፡ አብን ፡ አድርጎ ፡ እንደተናገረ ፡ ከዚህም ፡ ዕሪናውን ፡ ለመግለጽ ለአብ ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ለእኔ ፡ አለኝና ፡ ትምርቱን ፡ ከኔ ፡ ወስዶ ፡ ያስተምራችኋል ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከኔ ፡ ይሠርጻል ፡ ማለቱ ፡ አይደለም ።

ትምህርቲቱ፡ የፎቱም፡ መኾኗንም ፡ ይህ ፡ የምትሰሙት ፡ ቃል ፡ የላከኝ ፡ የአብ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የኔ ፡ ቃል ፡ አይደለም ፡ በማለቱ ፡ የአብ ፡ መኾኗን ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ ሳለሁ ፡ ይህንን ፡ ነገር ኳችሁ ፡ በማለቱ ፡ የወልድ ፡ መኾኗን ፡ አብ ፡ በኔ ፡ ስም ፡ የሚልከው ፡ እውነተኛ ፡ መንፈስ ፡ ጰራቅሊ ጦስ ፡ እርሱ ፡ ኹሉን ፡ ይነግራችኋል ፡ እኔ ፡ የነገርኳችሁን ፡ ኹሉ ፡ ያሳስባችኋል ፡ በማለቱ ፡ የመን ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ትምርት ፡ መኾኗን ፡ ገልጾልናል ።

ስለዚህ ፡ እምዚአየ ፡ ይነሥእ ፡ ያለ ፡ መምርነትን ፡ ትምህርትን ፡ እንደኾነ ፡ ያስረዳል ፡ እንጂ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ እንደ ፡ ሠረጸ ፡ አያስረዳም ፡

ሐዋርያትም ፡ በዕውቀት ፡ ፍጹማን ፡ ኾነው ፡ ወንጌልን ፡ አብራርተው ፡ ለማስረዳት ፡ የቻሉ ፡ በጽርሐ ፡ ጽዮን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡ መኾኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ።

ላባቴ ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ለእኔ ፡ አለኝ ፡ ብሏልና ፡ ለአብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ማሥረጽ፡ ገንዘቡ ፡ ከኾነ ፡ ለወልድም ፡ ገንዘቡ ፡ ይኾናል ፡ እንዳይባል ፡ ወላዲነትም ፡ ለአብ ፡ ገንዘቡ ፡ ነውና ፡ ወላዲ ነት ፡ ለወልድም ፡ ገንዘቡ ፡ ነው ፡ ማለትን ፡ ያስከትላል ፡ ወላዲነት ፡ ለወልድ ፡ ገንዘቡ ፡ ነው ፡ ከተባ ለም ፡ ራሱን ፡ ወለደ ፡ ከማለት ፡ ያደርሳል ።

<u>መውለድ፡ማሥረጽ</u>፡ለአብ፡በተለየ፡አካሉ ፡ የባሕርይ ፡ ግብሩ ፡ ነው ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚጨመሩበት ፡ አይደለም ። መወለድም ፡ ለወልድ ፡ በተለየ ፡ አካሉ፡ የባሕርይ፤ ግብሩ ፡ ነው ። አብ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚጨመሩበት ፡ አይደለም ።

<u>መሥረጽም</u> ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ የባሕርይ ፡ ግብሩ ፡ ነው ፤ አብ ፡ ወልድ ፡ የሚ ጨመሩበት ፡ አይደለም ። ይህንን ፡ የመሳሰለውን ፡ ነገር ፡ ለይቶ ፡ ጠንቅቆ ፡ ማወቅ ፡ ይጠቅማል፡ በም ፡ ፳ ፡ በቊ ፡ ፳፪ ፡ የጠቀሱትም ፡ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ነፍሐ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ንሥኡ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።

ይህንን ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀበሉ ፡ ብሎ ፡ እፍ ፡ አለባቸው ፡ ይላል ፡ ይህ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ በንፍሐት ፡ ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ እንዳሳደረባቸው ፡ ሢመተ ፡ ክህነትን ፡ እንደ ሾማቸው ፡ ያስረዳል ፡ እንጂ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ እንደ ፡ ሠረጸ ፡ አያስረዳም ።

ጌታ ፡ በሐዋርያት ፡ ላይ ፡ እፍ ፡ ብሎ ፡ ንሥኡ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ማለቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ ሠረጸ ፡ የሚያሰኝ ፡ ከኾነስ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ጳጳሳትን ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶሳትን ፡ ቀሳውስትን ፡ በንፍሐት፡ይሾሟቸዋል ፡ ምእመናንን ፡ ሲያጠምቁ ፡ ንሥኡ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብለው ፡ በንፍሐት ፡ ሀብተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ያሳድሩባቸዋልና ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከነርሱ ፡ ሠረጸ ፡ እንደማለት ፡ የሚቈጠር ፡ ነገር ፡ ነው ።

ስንኳን ፡ ዐዋቂ ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሊጠቅሰው ፡ አይገባም ።

፪ኛም ፡ ከሐዋርያት ፡ መጻሕፍት ፡ ናሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈነወ ፡ መንፈሰ ፡ ወልዱ ፡ ውስተ ፡ ልብከሙ ።

እግዚአብሔር ፡ የልጁን ፡ መንፈስ ፡ ወደ ፡ ልቡናችሁ ፡ ላከ ፡ ያለውን ፡ ገላ ፡ ፬ ፡ ፮ ።

ወኢያብሐሙ ፡ መንፈሱ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መንፈሱ ፡ አላሰናበታቸውም ፡ የሚለውም ፡ ጠቀሱልኝ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፮ ፡ ፯ ።

የዚህም ፡ ምሥጢሩ ፡ የሥላሴ ፡ አካላቸው ፡ የተለየ ፡ ሲኾን ፡ ባሕርያቸው ፡ ተከፍሎ ፡ የሌለበት ፡ አንድ ፡ ስለኾነ ፡ አብ ፡ ልብ ፡ ኾኖ ፡ አንድ ፡ ዕውቀት ፡ ያውቃሉ ፡ ወልድ ፡ ቃል ፡ ኾኖ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ይናገራሉ ። መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እስትንፋስ ፡ ኾኖ ፡ ሕያዋን ፡ ኾነው ፡ ይኖራሉ ፡ በሀልውና ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ የሚያሰኛቸውም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ ሀልውናቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ መንፈሰ ፡ ወልዱ፡ መንፈሱ ፡ ለኢየሱስ ፡ እያሉ ፡ ይናገራሉ ፡ እንጂ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ ሠረጸ ፡ ለማለት ፡ የተነገረ ፡ አይደለም ።

የሮሙ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አቡሊድስ ፡ ወልድኒ ፡ ቃሎሙ ፡ ለአብ ፡ ወለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ ቅዱስኒ ፡ መንፈሶሙ ፡ ለአብ ፡ ወለወልድ ፡ ብሂል ።

ይህ ፡ አነጋገር ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ገለጽነው ፡ ሀልወናቸውን ፡ የሚያስረዳ ፡ አነጋገር ፡ ነው ፡ እንጂ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብም ፡ ከወልድም ፡ ሠረጸ ፡ ለማለት ፡ አይደለም ።

መንፈሶሙ፡ ለአብ፡ ወለወልድ ፡ ብሎ ፡ ዝርዝሩን ፡ ለአብም ፡ ለወልድም ፡ ከሰጠ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ ሠረጸ ፡ የሚያሰኝ ፡ ከኾነ ፡ ወልድንም ፡ ቃሎሙ ፡ ለአብ ፡ ወለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይለዋልና ፡ ወልድም ፡ ከመንፈስ ቅዱስ ተወለደ ፡ የሚያሰኝ ፡ መኾኑን ፡ ተገንዝቦ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከወልድ ፡ ሠረጸ ፡ ማለትን ፡ መተው ፡ ትልቅ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለው ፡ አስተዋይነት ፡ ነው ።

የመለኮታውያን ፡ አካላት ፡ አወጣጥ ፡ ተርታ ፡ በተፋለሰ ፡ ነበረ ፡ ለሚሉትም ፡ ተርታ ፡ የሚያስፈልግ ፡ መቅደም ፡ መቀዳደም ፡ ቢኖር ፡ ነበረ ፡ አብ ፡ ወልድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብለን ፡ በተራ ፡ መጥራታችን ፡ ሦስቱን ፡ ስም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መጥራት ፡ ስለተሳነን ፡ የስዒን ፡ የድካም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አብ ፡ ይቀድማል ፡ ወልድ ፡ ይከተላል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ወደ ፡ ኋላ፡ ይኾናል ፡ ብለን ፡ አይደለም ።

ሳንድ ፡ ጊዜ ፡ ለመጥራት ፡ ስንፈልግ ፡ ግን ፡ አምላክ ፡ መለኮት ፡ ብለን ፡ እንጠራቸዋለን ፡ ከበብን ብርሃንን ፡ ዋዕይን ፡ አንድ ፡ ፀሐይ ፡ ብለን ፡ እንደምንጠራ ፡ ክበብ ፡ ብርሃን ፡ ዋዕይ ። እንዲሁም ፡ ነበልባል ፡ ብርሃን ፡ ዋዕይ ፡ መቅደም ፡ መቀዳደም፡መከተል ፡ መከታተል ፡ ሳይኖርባቸው ፡ አንድ ፡ ጊዜ እንዲገኙ ፡ የሥላሴም ፡ ሀልውና ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡ መቅደም ፡ መቀዳደም ፡ መከተል ፡ መከታተል ፡ የለባቸውም ።

## ፫ኛ ፡ የክርክሩ ፡ መነሣት ።

### ደ ራ ሲ ።

፩/ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ አስቀድሞ ፡ ክርክሩ ፡ እንዴት ፡ እንደ ተነሣና ፡ መቸ ፡ እንደተጀመረ ፡ ዶጎና ፡ እድርጎ ፡ ማወቅ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ተነሥተው ፡ የቅብዐቱ ፡ ክርክር፡ የተነሣው ፡ ያለቀርጥር ፡ የካቶሊክ ፡ መልእክተኞች ፡ በ፲፯ኛ ፡ ፻ ፡ ዓ/ም ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ኾነው ፡ ከኢትዮጵያኖቹ ፡ ጋራ ፡ ያደርጓቸው ፡ በነበሩት ፡ ክርክሮች ፡ ምክንያት ፡ ነው ።

ለዚሁም ፡ መሥራቹ ፡ ፖርቱጊዝ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ለዚሁም ፡ መረጃ ፡ ከሰጡ ፡ በኋላ ፡ አጠራጣሪ ታሪክ ፡ መዐልም ፡ ጴጥሮስ ፡ የተባለው ፡ በፋሲል ፡ መንግሥት ፡ በ፭ኛ ፡ ዓመቱ፡ (ማለት)በ፩ሺ፮፻፴፭ ግድም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የገባው ፡ ፔትር ፡ ሃይልንግ ፡ የተባለው ፡ የሰክሰን ፡ ዘር ፡ የኾነው ፡ ፕሮቶስታንቱ ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ አሉ ፡ ብለው ፡ ለዚኸውም ፡ ላጠራጣሪው ፡ አሳብ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ መረጃ ከሰጡ ፡ በኋላ ፡ አሳብዎን ፡ በካቶሊኩ ፡ በፖርቱጊዝ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አጽንተዋል ።

### መ ላ ሽ ።

፩/ ይህ ፡ ነገር ፡ በእኛም ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ዘንድ ፡ በቃልም ፡ በጽሑፍም ፡ ሲተረክ ፡ ካቶካዊው ፡ መዐልም ፡ ጴጥሮስ ፡ ቆረንጭ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ለተባለ ፡ ለአንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ በቅብዐት ፡ የጸጋ ፡ ልጅ ፡ በል፡ ብሎ፡ አስተማረው ፡ እርሱም ፡ ፫ት ፡ ልደት ፡ የጸጋ ፡ ልጅ ፡ የሚለውን ፡ ባህል ፡ አስተማረ ፡ ይህም ፡ በጻድቁ ፡ በአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ስም ፡ ተጠግቶ ፡ ቤተ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የሚባለውን ፡ ስም ፡ ለተከታዮቹ ፡ አተረፈ ።

፪ኛ ፡ ሳንኳ ፡ ኤዎስጣቴዎስ ፡ ለተባለ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሰው ፡ በቅብዐተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ ኾነ ፡ የሚለውን፡ ባህል፡ አስተማረ፡ ርሱም፡ በጻድቁ፡ በአቡነ፡ ኤዎስጣቴዎስ፡ስም ተጠግቶ ፡ ቤተ ፡ ኤዎስጣቴዎስ ፡ መባልን ፡ ለተከታዮቹ ፡ አተረፈ ። በዚህ ፡ ምክንያት ፡ መለያየት ፡ ተፈጠረ ፡ መምህራቸው ፡ መዐልም ፡ ጴጥሮስም ፡ ኢትዮጵያን፡ ለቆ ፡ በሚሔድበት ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ እሾህ ፡ ተከየባት ፡ መርዝ ፡ ነሰንሸባት ፡ መጣሁ ፡ አለ ፡ እየተባለ ፡ ይተረካል ።

ኹለተኛም ፡ ታሪክ ፡ ይኸው ፡ ካቶሊካዊው ፡ መዐልም ፡ ጴጥሮስ ፡ በዓፄ፡ ፋሲል ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮጵያን ፡ በግድ ፡ ለቆ ፡ ሲሔድ ፡ ዐፄ ፡ ፋሲል ፡ ሸኘታ ፡ ሰጥተው ፡ ሰደዱት ። ምጥዋ ፡ ሲደርስ ፡ እኒህ ፡ ደንቆሮዎች ፡ ነሥአ ፡ ተወክፈ ፡ ይላል ፡ መንፈስ ፡ቅዱስን ፡ ተቀብሎ ፡ ምን ፡ አደረገው ፡ ቢሏቸው ፡ አያውቁትም ፡ ብሎ ፡ የኢትዮጵያን፡ሊቃውንት ፡ ተሳድቦ ፡ ሔደ ። ሸኘዎችም ፡ ተመልሰው ፡ ይህን፡ የርሱን ፡ ንግግር ፡ ለዐፄ ፡ ፋሲል፡ ነገሯቸው ፡ ዐፄ ፡ ፋሲልም ፡ ሊቃውንቱን ፡ አሰብስበው ፡ መጻሕፍት፡ በብዙ ፡ አንቀጽ ፡ ነሥአ ፡ ተወክፈ ፡ ይላሉ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀብሎ ፡ ምን ፡ አደረገው ፡ ትላላችሁ ፡ ቢሏቸው ፡ ገሚሶቹ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀብሎ ፡ የጸጋ ፡ ልጅ ፡ ኾነ፡ አሉ፡እንዚህ ፡ የጸጋ ፡ ልጆች ፡ ተባሉ ፡ ገሚሶቹ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀብሎ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ ኾነ ፡ ብለዋል ፡ እነዚህ ፡

ትብዕቶች ፡ ተብለዋል ። ግሚሶች ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ጥምቀቱ ፡ እንደ ፡ ሕማሙ ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ስለእኛ ፡ ብሎ ፡ ለአብነትነትና ፡ ለበኵርነት ፡ ተቀበለ ፡ እንጂ ፡ በተዋሕዶ ፡ ከመክበሩ ፡ በቀር ፡ ይህ ፡ ንሥአት ፡ ለራሱ ፡ አልረባውም ፡ አልጠቀመውም ፡ ብለዋል ፤ እኒህ፡ ተዋሕዶዎች ፡ ተብለዋል ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ መለያየት ፡ መጣ ፡ እየተባለ ፡ ይተረካል ።

በዚያም ፡ ኾነ ፡ በዚህ ፡ ይህን ፡ ብጥብጥ ፡ የፈጠሩ ፡ ካቶሊካውያን ፡ መኾናቸው ፡ ቡርስታንቶች አለመኾናቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው፡ ይኸውም ፡ የቡርስታንቶች ፡ ሐሳብ ፡ ጽደቁ ፡ እንከ ፡ በአሚን ፡ ያለ ውን ፡ ንባብ ፡ ብቻ ፡ ይዘው ፡ በሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ እንጸድቃለን ፡ ምግባር ፡ አያሻንም ፡ አማላጅ ፡ አንሻም ፡ የራሳችን ፡ እምነት ፡ ብቻ ፡ ይበቃናል ።

ለሥዕል ፡ ለመስቀል ፡ መስገድ ፡ አይገባም ፡ እያሉ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ውን ፡ ጥቃቅን ፡ ነገር ፡ ከመ ስበክ ፡ በቀር ፡ ጥልቅ ፡ ከኾነው ፡ ኪቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ምሥጢር ፡ ባለመግባታቸው ፡ ይታወቃል ።

ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ብጥብጥ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የፈጠረ ፡ ካቶሊካዊው ፡ መዐልም ፡ ጴጥሮስ ፡ መኾኑ የማያጠራጥር ፡ ነገር ፡ ነው ። ይኸውም ፡ መቼም፡ መች፡ ቢኾን፡ ካቶሊካውያን፡ ወደ፡ ኢትዮጵያ፡ የሚመጡ ፡ ለተንኮልና ፡ ርስ ፡ በርስ ፡ ለማበጣበጥ ፡ እንጂ ፡ ለበጐ ፡ ነገር ፡ ለሰላም ፡ የማይመጡ ፡ መኾናቸውን ፡ ያስረዳል ።

ለሃይማኖት ፡ ተቆርቋሪዎች ፡ ለአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀናተኞች ፡ ሆነው ፡ ቢኾን ፡ አምል ኮተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመቀበል ፡ ከሮማ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ቅድሚያ ፡ ያላት ፡ ኢትዮጵያን፡ ላስተምር፡ ብሎ ፡ ከመድከም ፡ ባጠገባቸው ፡ ያሉትን ፡ ከአምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእፍአ ፡ ያሉትን ፡ ወገኖች ለማስተማር ፡ መድከም ፡ በተገባቸው ፡ ነበረ ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ ካቶሊካውያንን ፡ የሚያሳጣ ቸው ፡ እንጂ ፡ የሚያስመሰግናቸው ፡ አለመኾኑን ፡ ከመግለጥ ፡ በቀር ፡ ይህን ፡ ብጥብጥ ፡ የፈጠሩ ፡ ካቶሊካውያን ፡ አይደሉም ፡ ብዬ ፡ የምቃወምበት ፡ ነገር ፡ የለኝም ።

በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ሊዘለል ፡ የማይገባው ፡ አንድ ፡ አሳዛኝ ፡ ነገር ፡ ተናግረዋል ፡ ይኸውም ፡ መዓ ልም ፡ ጴጥሮስ ፡ ወይም ፡ ፓድረ ፡ ፓየዝ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጣና ፡ ካረቢኛ ፡ የሚወጡትን ፡ ኹለት፡ ቋንቋዎች ፡ አማርኛንና ፡ ግእዝን ፡ በፍጥነት ፡ ተማረ ፡ ብለው ፡ ግእዝን ፡ የዐረብ ፡ ዲቃላ ፡ ቋንቋ ፡ ነው ብለው ፡ የጻፉት ፡ ነው ።

አስቀድሞ ፡ የሀገርን ፡ ታሪክና ፡ ባህል ፡ ሳያጠኑ ፡ የባዕድን ፡ ታሪክና ፡ ባህል ፡ መቀላወጥ ፡ ከእ ንዲህ ፡ ያለ ፡ ስሕተት ፡ ላይ ፡ ይጥላል ፡ ለግእዝ ፡ መደበኛ ፡ ከኾነው ፡ ሀገር ፡ ከትግሬ ፡ ተወልደው ፡ ግእዝ ፡ የዐረቢኛ ፡ ዲቃላ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መጻፍዎ ፡ እጅግ ፡ የሚያሳዝን ፡ ነው ። ግእዝስ ፡ የባቢሎን ፡ ግንብ ፡ በፈረሰ ፡ ጊዜ ፡ ልሳናት ፡ ሲከፋፈሉ ፡ ቋንቋዎች ፡ ሲጎጣጠሉ ፡ ፊደሎች ፡ ሲደላደሉ ፡ እንደ ፀረብ ፡ እንደ ፡ ሱርስት ፡ እንደ ፡ ዕብራይስጥ ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፡ የያዘ ፡ ሴማዊ ፡ ፊደልና ፡ ቋንቋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የዐረብኛ ፡ ዲቃላ ፡ ቋንቋ ፡ አይደለም ፡ ይህንንም ፡ ለመረዳት ፡ ቢፈልጉ ፡ ሊቁ ፡ አለቃ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ የጻፉትን ፡ መጽሐፈ ፡ ግሥ ፡ ይመልከቱ ።

## ፬ኛ ፡ የክርክሩ ፡ መስፋፋት ።

### ድ ራ ሲ ።

፰/ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ካመነጩት ፡ ተገ ኮል ፡ የተነሣ ፡ በየጊዜው ፡ በኢትዮጵያ ሊቃውንት ፡ መካከል ፡ ጠብ ፡ ክርክር ፡ መደረጉን ፡ በሰፊው ፡ ጽፈዋል ።

### መ ላ ሽ ።

፰/ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ለመጻፍ ፡ ያሳሰበዎ ፡ ዋናው ፡ መሠረቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ እነዐፄ ፡ ካሌብ ፡ እንዲሁም፡የሃይማኖት ፡ መሪዎች ፡ የነበሩት ፡ ፱ ፡ ቅዱሳን ፡ ካቶሊካውያን ፡ ነበሩ እኛም ፡ ዛሬ ፡ ያለኖች ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ተስማምተን ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ ፡ ካቶሊካውያን ፡ እንኹን ፡ ለማለት ፡ ነበረ ።

ይህ ፡ አጻጻፍ ፡ ግን ፡ ከሐሳብዎ ፡ ግብ ፡ ወጥቶ ፡ የካቶሊካውያን ፡ ሐሳብ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሰላም ፡ እንዲጠፋ ፡ አውከት ፡ እንዲሰፋ ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ሐሳባቸው ፡ በየጊዜው ፡ ተፈጽሞላቸዋል ፡ ብሎ ፡ ለማስታወስ ፡ ያኽል ፡ እንደኾነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ፍሬ ፡ ያለው ፡ ኾኖ ፡ መልስ ፡ ልስጥበት ፡ የሚባል፡አይ ደለም ።

### ድ ራ ሲ ።

፱/ ይልቁንም ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወገን ፡ በዕጨጌያቸው ፡ በአባ ፡ ጌኖክ ፡ መሪነት ፡ ወደ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ በጣም ፡ የቀረበ ፡ ባህል ፡ ይዘው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተነሡ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የኹለት ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ተከታዮችና ፡ ደጋፊዎች ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ ከነአለቃቸው ፡ ተወገዙ ፡ ብለዋል

## መ ላ ሽ ፡

፱/ ፡ በዚህ ፡ አነጋገርም ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፈጽሞ ፡ የተጠላ ፡ መኾኑን ፡
መስክረዋል ። ስለዚህ ፡ አነጋገር ፡ እውነት ፡ ነው ፡ የኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፈጽሞ፡
የተጠላ ፡ ነው ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መልስ ፡ የለውም ።

## ደ ራ ሲ ፡

፲/ የካሮች ፡ ባህል ፡ የሥጋ ፡ ጠባዕያት ፡ ከቃል ፡ ጋራ ፡ በመዋሐዳቸው ፡ ጠፍተዋል ፡ ሰውና
አምላክ ፡ የኾነው ፡ የክርስቶስ ፡ ትስብእቱ ፡ የማይታመምና ፡ የማይሞት ፡ ኾኗል ፡ ይላሉ ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲/ ይህ ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ማናቸውም ፡ ወገን ፡ ቢኾን ፡ ሥጋው ፡ ቃል ፡
ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኾኖ ፡ እንደ ፡ አምላክነቱ ፡ ሕያው ፡ ሲኾን ፡ እንደ ፡ ሰው
ነቱ ፡ ለሰው ፡ የሚገባውን ፡ ሕማም ፡ ሞት ፡ በእውነት ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ ያምናል ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡
የሚል ፡ የለም ፡ ውሸት ፡ ነው ።

እንደ ፡ እውነቱ ፡ ከኾነ ፡ ካቶሊካውያን ፡ አካል ፡ ለቃል ፡ እንጂ ፡ ለትስብእት ፡ የለውም ፡ ስለሚሉ
አካለ ፡ ቃልም ፡ ሕማም ፡ ሞት ፡ የማይሰማው ፡ ረቂቅ ፡ ስለኾነ ፡ የሥጋ ፡ ጠባይዓት ፡ በተዋሕዶ ፡ ጠፍ
ተዋል ፡ ትስብእቱ ፡ የማይታመምና ፡ የማይሞት ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ መባል ፡ የሚገባቸው ፡ ለነርሱ ፡
ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፩/ እንደ ፡ እውነተኞቹ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ አሳብ ፡ በባሕርየ ፡ መለኮት ፡ ውስጥ ፡
ፈጽሞ ፡ ጠፍቷል ፡ የሚሉት ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ሳይጠፋ ፡ በክርስቶስ ፡ መገኘቱን ፡ በግድ ፡ ይታ
መኑበታል ። ስለዚህ ፡ የጠኑ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ የቶኑት ፡ ካሮች ፡ ፍጹም፡ አምላክና
ፍጹም ፡ ሰው ፡ በኾነው ፡ ባንዱ ፡ ክርስቶስ ፡ ከኹለት ፡ ልደት ፡ ከዘለዓለም ፡ ከመወለዱና ፡ ከድንግል፡
በጊዜ ፡ ከመወለዱ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሊያምኑ ፡ አይችሉም ፡ ነበረ ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፩/ ትስብእት ፡ ጠፍቷል ፡ ይላሉ ፡ ለሚሉት ፡ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ የጻፍኩት ፡ በቂ ፡ ነው ።
ከዘለዓለ ም ፡ ከመወለዱና ፡ ከድንግል ፡ በጊዜ ፡ ከመወለዱ፡በቀር ፡ ሌላ ፡ አያምኑም ፡ ስለሚሉት፡
ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ከአብ ፡ ያለእናት ፡ ድኅረ ፡ ዓለም ፡ ከእመቤታችን ፡ ያለአባት ፡ መወለዱን ፡ መጻ
ሕፍት ፡ አምልተው ፡ አስፍተው ፡ ሲነግሩን ፡ ፫ኛ ፡ በማኅፀን ፡ ተወለደ ፡ የሚል ፡ መጽሐፍ ፡ አይ
ገኝም ፡ ንባብ፡ ሳይገኝለት፡ በይኾናልና ፡ በይመስላል ፡ በያሰኛል ፡ ገምተን ፡ በማኅፀን ፡ ፫ኛ፡ ልደት፡
ተወለደ ፡ አለማለታችን ፡ እርግጥ ፡ ነው ።

## ፭ኛ/ የሚከራከሩት ፡ ወገኖች ፡ ባህል ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፪/ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ወገኖችን ፡ ባህል ፡ ጠንቅቀን ፡ ብንመረምረው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለአካ
ላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ የሚያምኑትንና ፡ የሚያስተምሩትን ፡ ትምርት ፡ በበለጠ ፡ ለመረዳት፡ እንችላለን
ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፪/ ይህ ፡ የማይቻል ፡ ውሸት ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ለማወቅ ፡ ከፈለጉ ፡ ከኢትዮጵያውያን ፡
መምህራን፡ እግር፡ሥር፡እንገትን፡አቀርቅሮ ፡ መጻሕፍትን፡መመርመርና ፡ መምህራንን ፡ ቃል ፡ ለቃል፡
በመጠየቅ ፡ ብዙ ፡ ቀኖችን ፡ ማሳለፍ ፡ ያስፈልጋል ፡ እንጂ ፡ ያልፎ ፡ ሐጆችን ፡ ወሬ ፡ በማጠራቀም፡
ለመረዳት ፡ አይቻልም ፡ ሊረዱት ፡ አለመቻልዎንም ፡ የደብረ ፡ ሊባኖሶች ፡ ባህል ፡ መግለጫ ፡ ለጎጃ
ሞች ፡ ባህል ፡ መግለጫ ፡ ብለው ፡ በጻፉት ፡ ሠንጠረዥ ፡ ልንረዳው ፡ እንችላለን ።

የጎጃሞች ፡ ባህል ፡ ብለው ፡ በጻፉት ፡ ሠንጠረዥ ፡ ውስጥ ፡ ከመለኮት ፡ ጋራ ፡ መዋሐዱ ፡ ለት
ስብእት ፡ እንደቅብዐት ፡ ኾነለት ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፡ በቅብዐት ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ ብለዋል ።

ከዚህም ፡ ቀጥለው ፡ ተዋሕዶ ፡ የተፈጸመ ፡ ወይም ፡ የተገኘው ፡ በቅብዐት ፡ ነው ፡ ክርስቶስ ፡
የአምላክ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ የሚኾነው ፡ በቅብዐት ፡ ነው ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፡ ክርስቶስ ፡ ራሱ ፡ ቅብዕ ፡
ቀቢና ፡ ተቀቢ ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አልተቀባም ፡ ብለዋል ።

ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ ማለትና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዕ ፡ ማለት ።

በተዋሕዶ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ኾነ ፡ ማለትና ፡ በቅብዐት ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ ኾነ ፡ ማለት ፡ መገናኘት ፡ የማይቻላቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገሮች ፡ መኾናቸውን ፡ ሊረዱ ፡ አልቻሉም ።

የነዚህን ፡ ባህሎች ፡ ጠባይና ፡ ስልት ፡ ለይቼ ፡ ዘርዝሬ ፡ እንዳላስረዳዎ ፡ እኒህን ፡ ባህሎች ፡ የሚፈልጓቸው ፡ ሰው ፡ ለሰው ፡ ለማበጣበጥና ፡ ወገን ፡ ለወገን ፡ ለማለያየት ፡ እንጂ ፡ ለሰላም ፡ ለበጐ፡ ነገር ፡ ስለማይፈልጓቸው ፡ ልገልጽልዎ ፡ አልፈቀድኩም ።

ይህን ፡ መጻፍ ፡ ለመጻፍ ፡ ያሳሰበዎ ፡ በካቶሊካውያን ፡ ዘንድ ፡ እንደተለመደው ፡ ኢትዮጵያ ውያንን፡ለማበጣበጥና፡ ለማለያየት ፡ መኾኑ ፡ የሚታወቀውም ፡ ንጉሡ ፡ ከሠራዊቱ ፡ ጳጳሱ ፡ ከነአር ድእቱ ፡ ዕጨጌው ፡ ከሊቃውንቱ ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ በቦሩ ፡ ሜዳ ፡ የወሰኑትን ፡ ውሳኔ ፡ አስታውሰው፡ በዚህ ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ የጎጃሞች ፡ ወይም ፡ የካሮች ፡ ወገን ፡ በደብረ ፡ ሊባኖሶች ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ ድል ማግኘቱ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ ጳጳሳት ፡ ስለደገፉትና ፡ ይልቁንም ፡ ከሺዎች ፡ ጋራ ፡ የሚጣሉት፡ የትግሬ ፡ ተወላጆች ፡ የመንግሥቱን ፡ ሥልጣን ፡ ስለያዙ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ በማያገባዎ ፡ ከመንግሥቱ፡ ፖለቲካ ፡ ሳይቀር ፡ ገብተው ፡ በመጻፍዎ ፡ ነው ።

ይልቁንም ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወገን ፡ ለኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ተቃዋሚ ፡ መኾኑ፡ በእነዕ ጨጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ክርክር ፡ የታወቀ ፡ ሲኾን ፡ በኹለት ፡ ወንድማማቾች ፡ መካከል ፡ ገብተው እንዲህ ፡ እያሉ ፡ መጻፍዎ ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ለማበጣበጥና ፡ ለማለያየት ፡ በዚሁም ፡ ምክንያት ፡ ወገን ፡ ለማግኘት ፡ ያሰቡ ፡ መኾንዎን ፡ በግልጽ ፡ ያስረዳል ። በዚህ ፡ አነጋገር ዎ ፡ ተስቦ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ የሚቀበል ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ አገኛለሁ ፡ ብለው ፡ እንዳይደክሙ ፡ አንድ ፡ ተረት ፡ ልጽፍልዎ ፡ እወዳለሁ ።

የነብር ፡ ግልገልና ፡ የፍየል ፡ ግልገል ፡ ተገናኝተው ፡ ሳይተዋወቁ ፡ ካንድ ፡ ላይ ፡ ሲጨዋወቱ ፡ ዋሉ ፡ ማታ ፡ በየቤታቸው ፡ ሲሔዱ ፡ የነብር ፡ ግልገል ፡ ለእናቷ ፡ የፍየሏን ፡ ግልገል ፡ መልክ ፡ እየዘረ ዘረች፡ዛሬስ ፡ እንዲህ ፡ ያለች ፡ ልጅ ፡ አግኝቼ ፡ ስጫወት ፡ ዋልኩ ፡ አለቻት ።

እናቲቱም ፡ በነገረቻት ፡ ምልክት ፡ የፍየል ፡ ግልገል ፡ መኾኗን ፡ ተረዳችና ፡ አንቺ ፡ ቂል ፡ እር ሷማ ፡ ምግባችን ፡ አይደለችም ፡ ለምን ፡ ለቀቅሻት ፡ አሁንም ፡ ያገኘሻት ፡ እንደኾነ ፡ እንዳትለቂያት፡ አለቻት ።

ልጅቷም ፡ እሺ ፡ ነገም ፡ ልንገናኝና ፡ ልንጫወት ፡ ተቃጥረናል ፡ አለቻትም ፡ አለቻት ።

የፍየልም ፡ ግልገል ፡ በበኩሏ ፡ ሔዳ ፡ ለናቷ ፡ እንዲህ ፡ ያለች ፡ መልኳ ፡ ሽልምልም ፡ የኾነች ልጅ ፡ አግኝቼ ፡ ስጫወት ፡ ዋልኩ ፡ አለቻት ፡ እናቲቱም ፡ የነብር ፡ ግልግል ፡ መኾኗን ፡ በነገረቻት ፡ ምልክት ፡ ዐውቃ ፡ አንቺ ፡ ቂል ፡ እርሷማ ፡ ዋንተ ፡ ጠላታችን ፡ ዘመዶቻችንን ፡ ኹሉ ፡ ስትፈጅ ፡ የኖ ረች ፡ አይደለችምን ፡ እንግዲህ ፡ ያገኘሻት ፡ እንደኾነ ፡ መሸሽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አትቅረቢያት ፡ ብላ ፡ መከረቻት ።

በማግስቱ ፡ ኹለቶችም ፡ ወደ ፡ ጨዋታው ፡ ቦታ ፡ ሔዱና ፡ ሲተያዩ ፡ ነብር ፡ አንቺ ፡ እንዴት ፡ አደርሽ ፡ እያለች ፡ ቀረብ ፡ ቀረብ ፡ ስትላት ፡ ፍየል ፡ ለመሮጥ ፡ ሽሽት ፡ ሽሽት ፡ አለች ፡ ነብር ፡ ምነዋ፡ ነይ ፡ እንጂ ፡ እንደትላንትናው ፡ እንጫወት ፡ አለቻት ፡ ፍየል ፡ የለም ፡ አይኾንም ፡ ከናንተ ፡ ቤት ፡ የተ መከረ ፡ ከኛም ፡ ቤት ፡ ተመክሯል ፡ አለቻት ፡ ይባላል ።

በካቶሊክና ፡ በኦርቶዶክስ ፡ መካከል ፡ ይልቁንም ፡ በኢትዮጵያና ፡ በሮማ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ ስለኾነ ፡ ምንም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወናሁ ፡ አነ ፡ እፌንወክሙ ከመ ፡ አባግዕ ፡ ማእከለ ፡ ተኵላት ፡ ቢለን ፡ የተቻለንን ፡ ያኽል ፡ መጠንቀቅ ፡ አለብን ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፫/ በዚህ ፡ ክፍል ፡ መጨረሻ ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ ባህል ፡ ጠንቅቆ ፡ ማወቅ ፡ ኢትዮጵያ ውያንንና ፡ ካቶሊካውያንን ፡ ለማቀራረብ ፡ ማናቸውንም ፡ ሥራ ፡ መሥራት ፡ የተፈለገ ፡ እንደኾነ ፡ ይጠቅማል ፡ የበለጠና ፡ የመቀራረብ ፡ የመተራረቂያ ፡ መንገድ ፡ ሊኾን ፡ ይችላል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፫/ የኢትዮጵያውያን ፡ ባህል ፡ በጥንቃቄ ፡ ከታወቀ ፡ ይህ ፡ እውነት ፡ ሳይኾን ፡ አይቀርም ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ በጥንቃቄ ፡ ሊያውቁት ፡ አልቻሉም የኢትዮጵያን ፡ ባህል ፡ በጥንቃቄ ፡ አው ቀውትስ ፡ ቢኾን ፡ ኢትዮጵያ ፡ የማትለውጥ ፡ ኹሉ ፡ ተለወጠ ፡ ትስብእት ፡ ጠፋ ፡ ቃል ፡ የነሣው ፡ ሥጋ ፡ ሕማም ፡ የማይስማማው ፡ ረቂቅ ፡ ነው ፡ ትላለች ፡ እያሉ ፡ ባላወሩባትም ፡ ነበር ።

አሁንም ፡ ኢትዮጵያውያንንና ፡ ካቶሊካውያንን ፡ ለማቀራረብ ፡ ከታሰበ ፡ በይመስላልና ፡ በያስ ኛል ፡ በፍልስፍናና ፡ በተራቀቀ ፡ የሚነገረውን ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ባህል ፡ ትቶ ፡ ቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡

በተናገሩት ፣ እስከ ፣ ጉባኤ ፣ ኬልቄዶን ፣ ድረስ ፣ የነበሩ ፣ አበው ፣ በጻፉት ፣ መጽናት ብቻ ፣ ነው ።
ስለኾነም ፣ ማናቸውንም ፣ ሥራ ፣ ለመሥራት ፣ የተፈለገ ፣ እንደኾነ ፣ ያሉት ፣ እነጋገር ፣ ደግሞ ፣ ከእንግዲህ ፣ ወዲያ ፣ በኢትዮጵያ ፣ ምን ፣ ሥራ ፣ ሊሠራባት ፣ ታስቦ ፣ ይኾን ፣ የሚል ፣ ሐሳብ ፣ ከተመልካች ፣ ልቡና ፣ ሳያሳድር ፣ አልቀረም ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፬/ የደብረ ፣ ሊባኖስን ፣ ባህል ፣ በበለጠ ፣ ማስረጃዎች ፣ አበርትቶ ፣ እላይ ፣ የተነገረውን ፣ ክርክር ፣ ከካቶሊክ ፣ ትምህርት ፣ ጋራ ፣ እንዲስማማ ፣ አድርጎ ፣ በመተርጐም፣ ቢደግፉትና ፣ ቢያስፋፉት የተሻለ ፣ ነው ፣ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፬/ ከላይ ፣ እንደ ፣ ተናገርነው ፣ ይህን ፣ መጽሐፍ ፣ ለመጻፍ ፣ ያሳሰበዎ ፣ አንዱን ፣ በመንቀፍ አንዱን ፣ በመደገፍ ፣ እርስ ፣ በርስ ፣ አለያይቶ ፣ በወንድማማቾች ፣ መካከል ፣ ጥልቅ ፣ ብሎ ፣ ለመ ግባት ፣ እንጂ ፣ ለአምልኮተ ፣ እግዚአብሔር ፣ ቀንተው ፣ እንዳልጻፉት ፣ እነሆ ፣ በዚህ ፣ አነጋገርዎ ፣ ታወቀ ፣ ተረዳ ።

ካቶሊካዊውን ፣ ተከራካሪ ፣ የደብረ ፣ ሊባኖሱ ፣ አበ ፣ ምኔት ፣ ዕጨጌ ፣ በትረ ፣ ጊዮርጊስ ፣ ተማሃለን በሞተ ፣ ወልዱ ፣ በሚል ፣ ፍላጻ ፣ ልብ ፣ ራሱን ፣ ወግተው ፣ የጣሉት ፣ በቀልና ፣ ደም ፣ በምን ፣ ደርቆ ፣ ነው ፣ ስምምነት ፣ የሚገኘው ፣ ይህ ፣ ከንቱ ፣ ምኞት ፣ ነው ። እንዲያውም ፣ በጠቅላላው ፣ ዛሬ ፣ በኢ ትዮጵያ ፣ ኹሉም ፣ ክርስቶስ ፣ አንድ ፣ አካል ፣ አንድ፣ ባሕርይ፣ ወልደ፣ አብ፣ ወልደ፣ ማርያም፣ ኹለት ፣ ልደት ፣ በተዋሕዶ ፣ ከበረ ፣ የሚል ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ከዚህ ፣ ወጥቶ ፣ አንድ ፣ አካል ፣ ኹለት ፣ ባሕርይ ፣ በቅብዐት ፣ የጸጋ ፣ ልጅ ፣ በቅብዐት ፣ የባሕርይ ፣ ልጅ ፣ የሚል ፣ አይገኝም ።

## ፯ኛ ፣ የልዩ ፣ ልዩ ፣ ወገኖች ፣ ቍጥርና ፣ ስለቅብዐቱ ፣ ክርክር ፣ የተገለጡ ፣ አስተያየቶች ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፭/ በዚህ ፣ ክፍል ፣ የጻፉት ፣ በጠቅላላው ፣ የውጭ ፣ ሀገር ፣ ታሪክ ፣ ጸሐፊዎች ፣ በኢትዮጵያ ፣ ምስት ፣ የሃይማኖት ፣ ባህሎች ፣ አሉ ፣ ይላሉ ፣ በማለት ፣ ነው ፣ ከውስጡም ፣ ገብቶ ፣ ሲመረምሩት ፣ ጎሚሶቹ ፣ ቅብዐቶችና ፣ ካራዎች ፣ አንድ ፣ ወገን ፣ ናቸው ፣ ሲሉ ፣ ጎሚሶቹ ፣ ቅብዐቶችና ፣ ካሮች ፣ በባ ህል ፣ አይገናኙም ፣ ይላሉ ። ጎሚሶቹ ፣ የደብረ ፣ ሊባኖሶች ፣ ባህልና ፣ የካቶሊክ ፣ ባህል ፣ የተቀራረበ ፣ ነው ፣ ሲሉ ፣ ጎሚሶቹ ፣ የተራራቀ ፣ ነው ፣ ይላሉ ፣ በማለት ፣ በሐሳብ ፣ አለመስማማታቸውን ፣ ከገለጡ በኋላ ፣ የራስዎን ፣ ሐሳብ ፣ ብቻ ፣ ለመደገፍ ፣ አንዱን ፣ ሲነቅፉ ፣ አንዱን ፣ ሲደግፉ ፣ አንዱን ፣ ሲያነሡ ፣ አንዱን ፣ ሲጥሉ ፣ ይታያሉ ።

## መ ላ ሽ ።

፲፭/ ኢትዮጵያዊ ፣ ሲኾኑ ፣ የኢትዮጵያን ፣ ታሪክና ፣ ባህል ፣ ከኢትዮጵያ ፣ መምህራን ፣ ጠይቆ ፣ እርግጡን ፣ በመረዳት ፣ ፈንታ ፣ የውጭ ፣ ሀገር ፣ አልፎ ፣ ሐጅ ፣ መንገደኞች ፣ የጻፉትን ፣ አገኝ ፣ አጣ ፣ ታሪክ ፣ በመመልከት ፣ እረዳለሁ ፣ ብለው ፣ መድከምዎ ፣ እጅግ ፣ ያሳዝናል ።

እኒህ ፣ ታሪክ ፣ ጸሐፊዎችስ ፣ የኢትዮጵያን ፣ ታሪክና ፣ ባህል ፣ ስለማያውቁ ፣ ለሀገራቸው ፣ ሰዎች ፣ የመሰላቸውን ፣ ቢጽፉ ፣ ተቀባዮች ፣ የሀገሩን ፣ ታሪክ ፣ አያውቁትምና ፣ እውነት ፣ ነው ፣ ብሎ ፣ የሚ ቀበላቸው ፣ ያገኙ ፣ ይኾናል ፣ እርስዎ ፣ ግን ፣ የኛን ፣ ታሪክ ፣ አበላሽተው ፣ ጽፈው ፣ ለኛ ፣ ማበርከትዎ እጅግ ፣ ይገርማል ፣ በዚህ ፣ አንቀጽ ፣ የጻፉት ፣ ኹሉ ፣ ከእውነት ፣ የራቀ ፣ የተዘበራረቀ ፣ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፮/ ይልቁንም ፣ ከትግሬ ፣ በሚበልጥ ፣ ክፍል ፣ መንፈስ ፣ ቅዱስ ፣ ከጌታችን ፣ ትስብእት፣ ጋራ ፣ ተዋሕዷልና ፣ ተደባልቋል ፣ ተብሎ ፣ ይታመናል ፣ (ገጽ ፣ ፻፳፬) ።

መንፈስ ፣ ቅዱስ ፣ ከቃል ፣ ትስብእት ፣ ጋራ ፣ ተዋሕዷልና፣ ተደባልቋል፣ ሲሉ፣ ያስተምራሉ ፣ ገጽ ፣ ፻፳፮፣ሥጋውም ፣ እንደኛው ፣ ሥጋ ፣ ያለ ፣ ከናቱም ፣ የተወሰደ ፣ ሳይኾን ፣ ባሕርይ ፣ በተባለው ፣ ልዩ ፣ ነገር ፣ የተሠራ ፣ ነው ፣ ይሉ ፣ ነበር ፣ (ገጽ ፣ ፻፳፱) ፣ እያለ ፣ ይነበባል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፮/ በኢትዮጵያ ፡ ማናቸውም ፡ ወገን ፡ ቢኾን ፡ ከኒህ ፡ ከተናገሩዋቸው ፡ ቃላት ፡ አንዱንም ፡ የሚያምን ፡ የሚያስተምር ፡ የለም ፡ ይህ ፡ አነጋገር ፡ በሐሰት ፡ የተጨማለቀ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ የሚጨበጥ ፡ እውነት ፡ ነገር ፡ የለበትም ። ይህን ፡ የተበላሸውን ፡ አቃንቼ ፡ በመልክ፡ በመልኩ ፡ አድርጌ ፡ እንዳልጽፍልዎ ፡ ይህነን ፡ ጽሑፍ ፡ የሚኾት ፡ ለበጐ ፡ ነገር ፡ ሳይኾን ፡ ወገንና ፡ ወገንን ፡ ለማለያየት ፡ ለተንኮል ፡ ስለኾነ ፡ ልጽፍልዎና ፡ ልገልጥልዎ ፡ አልወደድኩም ።

ስለዚህ ፡ ማናቸውንም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ባህል ፡ በደንብ ፡ አጥንተው ፡ አቃንተው ትክክለኛ ውን ፡ በጻፉ ፡ ጊዜ ፡ ትክክለኛውን ፡ መልስ ፡ እሰጥዎታለሁ ፡ ብዬ ፡ አስረድቼ ፡ አልፌዋለሁ ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፯/ ስለቅብዐት ፡ የሚከራከሩት ፡ ወገኖች ፡ የባህላቸው ፡ ትርጉም ፡ እንደዚያው ፡ እንዳስረዳነው ፡ መኾኑ ፡ የቅብዐቱ ፡ ክርክር ፡ ያስከተላቸውና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በተያያዙ ፡ አንዳንዶቹም ፡ ክርክሮች ፡ በበለጠ ፡ የጐላ ፡ ኾኖ ፡ ይታወቃል ፡ ካሉ ፡ በኋላ ።

(ሀ) በጸጋ ፡ ጥምቀት ፡ ዳግመኛ ፡ ስላልተወለደ ፡ ሰው ፡ ኹናቴ ፡ ክርክር ።
(ለ) ከሕልቀተ ፡ ዓለም ፡ በኋላ ፡ የክርስቶስ ፡ ትስብእት ፡ ስለሚያገኘው ፡ ኹናቴ ፡ ክርክር ።
(ሐ) ለአምላክ ፡ እናት ፡ ሊያቀርቡላት ፡ ስለሚገባው ፡ አክብሮ ፡ ክርክር ፡ ብለው ፡ በ፫ ፡ እርእስት ፡ ተንሥተው ፡ የደብረ ፡ ሊባኖሶች ፡ ባህል ፡ ወይም ፡ የቅብዐቶች ፡ ባህል ፡ እያሉ ፡ ጽፈዋል ፡ አልፈው ፡ አልፈውም ፡ የኹለቱ ፡ ወገኖች ፡ ባህል ፡ ከካቶሊኩ ፡ ትምርት ፡ ጋራ ፡ ቢያነጻጽሩት ፡ የወገኖቹ ፡ አያያዝ ፡ የተፋለሰ ፡ ኾኖ ፡ ይታያል ፡ እያሉ ፡ ባልጎላ ፡ አነጋገር ፡ ጽፈዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፯/ መልስ ፡ ሊሰጥበት ፡ የሚገባ ፡ ከካቶሊኩ ፡ ትምርት ፡ ጋራ ፡ ቢያነጻጽሩት ፡ ያሉት ፡ ብቻ ነበረ ፡ ይኸውም ፡ የሚቻል ፡ በነዚህ፡ እርእስቶች፡ ውስጥ ፡ የካቶሊኩ ፡ ባህል ፡ ምን ፡ እንደኾነ ፡ ገልጸው ፡ ጽፈው ፡ ቢኾን ፡ ነበረ ፡ ገልጸው ፡ የጻፉት ፡ ነገር ፡ ስለሌለ ፡ ለዚኸውም ፡ ምንም ፡ መልስ ፡ ሊሰጠው ፡ አይቻልም ። በጠቅላላው ፡ መልስ ፡ ሊሰጥበት ፡ የሚገባው ፡ በካቶሊካውያንና ፡ በኦርቶዶክሳውያን ፡ መካከል ፡ ስላለው ፡ ልዩነት ፡ ለሚጸፈው ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ይህም ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የጻፉት ፡ ኹሉ ፡ እርስዎን ፡ የማያገባዎት ፡ ስለሆነ ፡ አልፌዋለሁ ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፰/ በዚህ ፡ ክፍል ፡ አንድ ፡ የማይታለፍ ፡ ነገር ፡ አለ ፡ ይኸውም ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወገን የክርስቶስ ፡ ትስብእትና ፡ መለኮት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከተዋሐዱ ፡ በኋላ ፡ ሳይለያዩ ፡ እንደተዋሐዱ ፡ ይኖራሉ ፡ ሲሉ ፡ እንደ ፡ ካቶሊክ ፡ ያስተምራሉ ።

ጎጃሞች ፡ ግን ፡ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ አይናገሩም ፡ ይልቁንስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደሰማይ ፡ ሲያርግ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ትቷቸዋል ፡ ሲሉስ ፡ እንኳ ፡ በግልጥ ፡ ያስተምራሉ ፡ ብለው ፡ የጻፉት ፡ ቃል ፡ ነው ።

## መ ላ ሽ ።

፲፰/ (ሀ) ጎጃሚዎች ፡ ከተዋሐዱ ፡ በኋላ ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ አይናገሩም ፡ የሚሉት ፡ ውሸት ፡ ነው ። እንደ ፡ ካቶሊክ ፡ መለኮትንና ፡ ትስብእትን ፡ ለያይተው ፡ መለኮት ፡ በመለኮታዊ ፡ ፈቃድ ፡ የመለኮትን ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ። ትስብእትም ፡ በሰብአዊ ፡ ፈቃድ ፡ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ። አይሉም ፡ እንጂ ፡ ሥግው ፡ ቃል ፡ ክርስቶስ ፡ ባንድ ፡ ፈቃድ ፡ ባንድ ፡ ሥምረት አምላክ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ የአምላክነትን ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፡ እያሉ ፡ ያስተምራሉ ፡ እንጂ ፡ ትስብእት ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ ወይም እንደተለወጠ ፡ አድርገው ፡ ዝም ፡ አይሉም ። ይህም ፡ ባህል ፡ ኢትዮጵያ ፡ በመላዋ ፡ ወገን ፡ ሳትለይ ፡ የምታምነው ፡ እምነት ፡ ነው ።

(ለ) ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሲያርግ ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ ትቷቸዋል ፡ ብለው ፡ ያስተምራሉ ፡ የሚሉትም ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ በኢትዮጵያ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ የሚያስተምር ፡ የለም ።



ይህ ሥዕል አልዓዛርን ወዴት ቀበራችሁት ብሎ የጠየቀውና አልዓዛር አልዓዛር ብሎ ጠርቶ ያስነሣው ክርስቶስ አንድ እንደ ሆነ የጠየቀው ሌላ ያስነሣው ሌላ እንዳልሆነ ያሳያል። ዮሐ ፲፩ ፴፬—፵፫።

ዐርገ ፡ ነበረ ፡ መባሉ ፡ በሥጋ ፡ አይደለምን ፡ በመለኮቱማ ፡ ጥንቱንስ ፡ ንቡር ፡ አይደለምን ፡ ንቡሩንስ ፡ ነበረ ፡ ይለዋልን ፡ ይህ ፡ ባህል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በማንም ፡ ዘንድ ፡ በፍጹም ፡ የሌለ ነው ።

(ሐ) ለአምሳክ ፡ እናት ፡ ሊያቀርቡላት ፡ ስለሚገባው ፡ ክብር ፡ በሚለው ፡ አርእስትም ፡ በሌሎች ፡ ክርክሮች ፡ የደብረ ፡ ሊባኖሱ፡ ትምህርት፡ ወደ ፡ ካቶሊክ ፡ የቀረበ ፡ ነበረ ፡ በዚህ ፡ ክርክር ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ በግልጥ ፡ የኑፋቄ ፡ ባህል ፡ ሲኾን ፡ የጎጃሞቹ ፡ ትምርት ፡ ከካቶሊኩ ፡ ፈጽሞ ፡ የተስማማ ፡ ኾኖ ፡ ይገኛል ፡ ብለዋል ።

፳/ ሐሳብዎ ፡ በመሠረቱ ፡ ካቶሊካውያንንና ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ለማስማማት ፡ ከኾነ ፡ የእገሌ ፡ ባህል ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ የእገሌ ፡ ባህል ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ ለማለያየት ፡ ማሳበቁን ፡ ትቶ ፡ የካቶሊክንና ፡ የኦርቶዶክስን ፡ ባህል ፡ ብቻ ፡ እያነጻጸሩ ፡ መጻፍ ፡ ነበረብዎ ።

እርስዎ ፡ ግን ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ ባህል ፡ ባልተካከለ ፡ አነጋገር ፡ እየጻፉ ፡ ይህ ፡ ከካቶሊክውያን ፡ ትምርት ፡ ጋራ ፡ ይስማማል ፡ ይህ ፡ አይስማማም ፡ ከማለት ፡ በቀር ፡ የካቶሊካውያን ፡ ባህል፡ ምን ፡ እንደኾነ ፡ አልገለጡትም ።

ስለዚህ ፡ ከካቶሊካውያን ፡ ባህል ፡ ጋራ ፡ ይቀራረባል ፡ የሚሉትን ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ አልቻልንም ፡ የእኛን ፡ ባህል ፡ ለእኛ ፡ ለማስረዳት ፡ እንደኾነ ፡ ከእርስዎ ፡ ይልቅ ፡ የእኛን ፡ ባህል ፡ እኛ ፡ የምናውቀው ፡ ስለኾነ ፡ በከንቱ ፡ በመድከምዎ ፡ እያዘን፡ ዋጋ ፡ እንደ፡ ሌለው ፡ አድርገን ፡ አልፈነዋል ።

## ም ዕ ፍ ፍ ፯ ።

፩/ በቅኔዎቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ተገልጦ ፡ የሚገኘው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ የሚያምኑት ፡ ትምርት ።

፩/ ቅኔ ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ ለፍቶ ፡ ተምረውት ፡ እንኳ፡ ድርስ ፡ ምሥጢሩ ፡ አይገኝም ። ምክንያቱም፡ የሰው ፡ ኾዱን ፡ የወፍ ፡ ወንዱን ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ፡ እንደሚባለው ፡ የባለቅኔው ፡ ሐሳብ ፡ መነሻው መድረሻው ፡ በግልጥ ፡ ሊታወቅ ፡ የማይቻል ፡ ስለኾነ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ያልቆጠሩትን ፡ ቅኔ ፡ እፈታለሁ ፡ ማለት ፡ ያላሳደጉትን ፡ ውሻ፡ጀርባ መቆንጠጥ ፡ ነው ፡ ይባላል ። ምናልባት ፡ የነገሩ፡ አነሣሥና ፡ የባለቅኔው ፡ ጠባይ ፡ የታወቀ ፡ ሲኾን ፡ የቅኔን ፡ ጠባይዕ ፡ መርምረው ፡ ያወቁ ፡ ሊቃውንት ፡ ሳይደርሱበት ፡ አይቀሩም ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ እንደርስዎ ፡ በቅኔ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ሳይደክሙ ፡ በድፍረት ፡ ለቅኔው ፡ ባለቤቶች ፡ እንዲህ ፡ ማለታችሁ ፡ እንዲህ ፡ ማለታችሁ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መናገር ፡ ራስን ፡ አለማወቅ ፡ የድፍረት ፡ ድፍረት ፡ ነው ፡ ይኸውም ፡ በቅኔዎች ፡ አፈታት ፡ ላይ ፡ ይገለጣል ።

## ደ ራ ሲ ።

፪/ ከነዚሁ ፡ ቅኔዎች ፡ አንዳንዶቹ ፡ እላይ ፡ ስለተናገርንባቸው ፡ ክርክሮች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ወገኖች ፡ የገለጧቸው ፡ ባህሎች ፡ ትክክለኛውን ፡ ትርጕማቸውን ፡ ለመረዳት ፡ ስለሚያግዙን ፡ ከፍ ያለ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያላቸው ፡ ምንጮች ፡ ናቸው ።

ስለዚህ ፡ ምርመራችን ፡ የተሟላ ፡ የመጨረሻው ፡ ፍርዳችንም ፡ በበለጠ ፡ የተረጋገጠ ፡ ለማድረግ ፡ ይረዱናል ። የተከራካሪዎችን ፡ አሳብ ፡ በበለጠ ፡ ለማወቅ ፡ የምንችልባቸው ፡ ብዙዎች ፡ ምስክሮች ፡ ማስረጃዎች ፡ እናገኝባቸዋለን ።

የተከራካሪዎች፡ ወገኖች፡ ባለቅኔዎች ፡ ባህላቸውን ፡ ለማጽደቅ ፡ ወይም ፡ የጠላቶቻቸውን ፡ ባህል ለማፍረስ ፡ የሚያመጧቸውን፡ ማስረጃዎች ፡ ጠንቅቀን ፡ እየለየን ፡ ብንመረምራቸው ፡ ከሌሎቹ ፡ ምርመራችን ፡ ምንጮች ፡ ያገኘነው ፡ ፈጽሞ ፡ እውነት ፡ መኾኑን ፡ እንረዳዋለን ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፪/ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ፡ ባህላቸውን ፡ ለማጽደቅ ፡ ወይም ፡ የተቃዋሚዎቻቸውን ፡ ባህል ለማፍረስ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅኔዎች ፡ መድረሳቸው ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ ቅኔዎችም ፡ በሚገባ ፡ መርምር ፡ በየሚያቸው ፡ ቢያውቋቸው ፡ ጠቃሚዎች ፡ መኾናቸው ፡ አይካድም ። እርስዎ ፡ ግን ፡ ደንበኛ ፡ ሐሳባቸውን ፡ አስለቅቀው ፡ የራስዎን ፡ ሐሳብ ፡ ደጋፊዎች ፡ ለማድረግ ፡ ስለሞከሩ ፡ ራስዎን ፡ ከማስገመትና ፡ ከማስመዘን ፡ በቀር ፡ ሊጠቀሙባቸው ፡ የቻሉ ፡ አይመስለኝም ፡ ይኸውም ፡ በሚከተሉት ፡ በተጠቀሱት ፡ ቅኔዎች ፡ አገኘሁት ፡ በሚሉት ፡ ውጤት ፡ ይታወቃል ።

## ፭ኛ/ ፡ የተዋሕዶዎችን ፡ ባህል ፡ የሚደግፉ ፡ ቅኔዎች ።

### ጥ ያ ቄ ።

፫/ ኑርልኝ ፡ የተባለ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወገን ፡ ተከታይ ፡ የኾነ ፡ ባለቅኔ ፡ ጎሹ ፡ ከሚባለው ፡ ከቅባቶች ፡ ወገን ፡ ተከታይ ፡ ጋራ ፡ ሲመላለስ ፡ የክርስቶስን፡ ቅብዐት፡ በመተርጐም፡ ላይ ፡ የማይስማሙ ፡ ወገኖች ፡ የባህላቸውን ፡ መቃረን ፡ በሚከተለው ፡ ቅኔ ፡ ገልጦታል ፡ ብለው ፡ ኢየኀሥሥ ፡ ለአብርሆ ፡ የሚል ፡ ሥላሴ ፡ ቅኔ ፡ ጽፈዋል ።

### መ ል ስ ።

፫/ የባለቅኔው ፡ ሐሳብ ፡ መነሻውና ፡ መድረሻው ፡ ካልታወቀ ፡ የቅኔው ፡ ምሥጢር ፡ በርግጥ፡ ሊታወቅ ፡ አይቻልም ፡ ብዬ ፡ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ ያስታወስኩት ፡ አሁን ፡ ደረሰ ፡ የቅኔውን ፡ ምሥጢር ፡ በእርግጥ ፡ ደርሰውበት ፡ ቢኾን ፡ ለዚህ ፡ ቅኔ ፡ ተቀዳሚ ፡ እንዳለው ፡ አውቀው ፡ ተቀዳሚውን ፡ አስቀድመው ፡ ተከታዩን ፡ ባስከተሉ ፡ ነበረ ፤ ይህ አጻጻፍ ፡ ድር ፡ ሳያደሩ ፡ ማግ ፡ ላምግ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ያለ ፡ ነው ። ለዚህ ፡ ቅኔ ፡ ተቀዳሚ ፡ አለው ፡ ቅኔውም ፡ በ፻፹፩ ፡ ገጽ ፡ የተጻፈው ፡ የ፬ ፡ ዓይን ፡ ጉሹ ፡ ቅኔ ፡ ነው ፤ እርሳቸውም ፡ በቅብዐት ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ ባይ ፡ ነበሩ ፡ ይባላል ፡ ቅኔውም ፡ የሚከተለው ፡ ነው ።

ኢያጥፍዐ ፡ ንዴተ ፡ ሥጋ ፡ ተዋሕዶተ ፡ ቃል ፡ ምስለ ፡ ሥጋነ ፡ እመ ፡ ሐተትነ ፤ በልብ ፡ ይእዜ ፡ እንበለ ፡ ማኅየዊ ፡ ቅብዐት ። ወኢይኩን ፡ በዐውደ ፡ ሮምያ ፡ በይነዝ ፡ ሑከት ።

ይክልኑ ፡ በእግር ፡ ተሐውሶ ፡ ኅበ ፡ ፍኖተ ፡ ላዕል ፡ ወታሕት ።

ነፍስ ፡ ዘአልቦ ፡ ሥጋ ፡ ምውት ።

ወጽልመትኑ ፡ ያሴስል ፡ እምዓይን ፡ ማኅቶት ፡

ዘላዕሌሁ ፡ ኢፀለወ ፡ ዘይት ።

ወዳግርኛ ፡ ቢመልሱትም ፡ ዛሬ ፡ በልብ ፡ ብንመረምር ፡ ማኅየዊ ፡ ከኮነ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዐትነት ፡ ማለት፡ ክብርነት ፡ በቀር ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዐትነት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ቃል ፡ ከሥጋችን ፡ ጋራ ፡ መዋሐዱ ፡ የሥጋ ፡ ንዴትን ፡ አላጠፋም ።

ስለዚህም ፡ በሮማ ፡ ዐደባባይ ፡ ሑከት ፡ እንዳይኾን ፡ ነፍስ ፡ የሌለው ፡ የሞተ ፡ ሥጋ ፡ በእግር ፡ ከላይ ፡ ወደታች ፡ ሊመላለስ ፡ ይችላልን ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ዘይት ፡ የሌለበትስ ፡ መብራት ፡ ከዓይን፡ጨለማን ሊያርቅ ፡ ይችላልን ፡ ማለት ፡ ነው ።

ወደ ፡ ምሥጢሩም ፡ ገባ ፡ ብሎ ፡ ቢመረምሩ ፡ በምሥጢረ ፡ ሥላሴ ፡ አብ ፡ ልብ ፡ ወልድ ፡ ቃል መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እስትንፋስ ፡ ማለትን ፡ ኹላችን ፡ የምናምነው ፡ እምነት ፡ ነው ። ይህ ፡ ባለቅኔ ፡ ሕይወትነትን ፡ ከአብ ፡ ከወልድ ፡ ለይቶ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብቻ ፡ ሰጥቶ ፡ ተናግሯል ።

ምክንያቱም ፡ ሰው ፡ ልቡ ፡ ቢጠፋውና ፡ አእምሮው ፡ ቢናወጥ፡ አብድ፡ዝንጉዕ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ሕይወቱ ፡ ጠፋ ፡ ሞተ ፡ አይባልም ። ንግግርም ፡ ቢተው ፡ ዲዳ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ሞተ፡ አይባልም ፡ ሞተ ፡ የሚባል ፡ ትንፋሹ ፡ የጠፋ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ባህል ፡ በቅብዐቶች ፡ ቤት ፡ ስላለ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ባለቅኔ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ እንደ ፡ ነፍስና ፡ እንደ ፡ ዘይት ፡ አብንና ፡ ወልድን ፡ ነፍስ ፡ እንደተለየችው ፡ ሥጋና ፡ ዘይት ፡ ሳይኖረው ፡ በመቅረዝ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ፈትል ፡ አድርጎ ፡ አነጻጽሮ ፡ ነፍስ ፡ የተለየችው ፡ ሥጋ ፡ ሊንቀሳቀስ ፡ እንደማይችል ፡ ዘይት ፡ ያልተጨመረበትም ፡ መብራት ፡ ጨለማን ፡ ካይን ፡ ሊያርቅ ፡ እንደማይችል ፡ የቃል ፡ ከሥጋ ፡ ጋራ ፡ መዋሐድም ፡ መንፈስ ፡ ዱቅስን ፡ በመቀበል ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ የሥጋ ፡ ንዴትን ፡ ሊያጠፋ ፡ አይችልም ፡ ማለት ፡ ነው ።

ባለ ፡ ቅኔውን ፡ ይህን ፡ ቅኔ ፡ ለመጻፍ ፡ ያሳሰበው ፡ ርሱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዕ ፡ ብሎ ፡ ሲያስተምር ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ የሚል ፡ ተቃዋሚ ፡ እንዳለበት ፡ ስላወቀ ፡ ነው ።

ይህንንም ፡ ቅኔ ፡ ጽፎ ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ በተዋሕዶ ፡ ከበረ ፡ በማለት ፡ ለታወቀው ፡ ለዲማ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ማኅበር ፡ ልኮታል ፡ ከማኅበሩም ፡ አንዱ ፡ ቄስ ፡ ገበዝ ፡ ኑርልኝ ፡ ኻሉ ፡ የተባሉ ሊቅ ፡ ይህን ፡ በ፻፹፰ኛ ፡ ገጽ ፡ የጻፉትን ፡ ቅኔ ፡ መልሰዋል ፡ ቅኔውም ፡ የሚከተለው ፡ ነው ።

ኢየኀሥሥ ፡ ለአብርሆ ፡ ቅብዐ ፡ ዘይት ፡ ፀሐይ ፡ ዘላዕለ ፡ ኵሉ ።

መዘየዓቢ ፡ ፀሐይ ፡ ከማሁ ፡ ቅብዐ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ክብርነ ።

ኢየኃሥሥ ፡ አምጣነ ፡ ፀሐይ ፡ ዘያበርህ ፡ ለነ ።

ወኢይትሐወክ ፡ ብዙኅ ፡ በዝንቱ ፡ እርዮሳዊ ፡ ዘኮነ ።

ከመ ፡ ቃል ፡ ብርሃን ፡ ኅበ ፡ ኢአምነ ።

ዐይንት ፡ የኀሥሥ ፡ ካልአ ፡ ዐይነ ።

ወብርሃን ፡ ካልእ ፡ ብርሃን ፡ የሚል ፡ ነው ።

እርስዎ ፡ ግን ፡ ቅብዐ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ክብረን ፡ የሚለውን ፡ ክብርን ፡ ብለው ፡ በማሳሳት ፡ ጽፈውታል ፡ ክብርን ፡ ተብሎ ፡ የተነበበ ፡ እንደኾነ ፡ ኀቢርና ፡ ተገቢሮ ፡ ኾኖ ፡ የቅኔው ፡ መንገድ ፡ የሚጠፋ ፡ መኾኑን ፡ ይረዱልኝ ።

ቅኔውን ፡ ወደ ፡ አማርኛ ፡ ብንመልሰው ፡ ከኹሉ ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ፀሐይ ፡ ሳብሬ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ዘይቅን ፡ ለቅብዐትነት ፡ አይፈልግም ፡ እንደዚኸውም ። ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ፀሐይ ፡ የሚበልጥ ፡ ኢየሱስ ክርስቶስም ፡ ለእኛ ፡ የሚያበራ ፡ እውነተኛ ፡ ፀሐይ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን፡ለእኛ ፡ ክብር፡ የሚኾን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ አይሻም ።

በዚህም ፡ የአርዮስ ፡ ወገን ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ እንዳይታወክ ፡ ዐይን ፡ ልይ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ሌላ ፡ ዐይን ፡ ይሻልን ፡ ብርሃንስ ፡ ልገለጽ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ሌላ ፡ ብርሃን ፡ ይሻልን ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ወደ ፡ ምሥ ጢሩም፡ ገባ ፡ ብለን ፡ ብንመረምረው ፡ ሥላሴ ፡ በክብር ፡ መበላለጥ ፡ የሌለባቸው ፡ ዕሩያን ፡ መኾናቸው ፡ በክርስቲያን ፡ ደንብ ፡ ኹሉ ፡ የታመነ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ዐይን ፡ ልይ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ሌላ ፡ ዐይን ፡ እንደማይሻ ፡ ብርሃንም ፡ የብርሃንነቱን ፡ ሥራ ፡ ልሥራ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ሌላ ፡ ብርሃን ፡ እንዳይሻ ፡ ወልድም ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ ሥጋ ፡ ቢለብስ ፡ የተዋሐደውን ፡ ሥጋ ፡ በባሕርይ ፡ ክብሩ ፡ በተዋሕዶ ፡ አከበረው ፡ እንጂ ፡ እንደኛ ፡ እንደ ፡ ፍጡራን ፡ ክብርን ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አልሻም ፡ ሲሉ ፡ የደረሱት ፡ ቅኔ ፡ ነው ።

ይህንም ፡ ስገልጽልዎ ፡ ቅኔው ፡ ከተደረሰበት ፡ ከዲማ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተወልጄ ፡ አድጌ ፡ ቅኔው ፡ ሲደረስ ፡ በዕድሜ ፡ ከደረሱት ፡ ሊቃውንት ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ ጠይቄ ፡ ተረድቼም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ቅኔ ፡ በማወቄ ፡ በተረዳሁት ፡ ዕውቀት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ። የኹለቱም ፡ ባለቅኔዎች ፡ አሳብ ፡ እርግጠኛው ፡ አሁን ፡ እኔ ፡ እንደገለጽኩልዎ ፡ ነው ። እርስዎ ፡ ግን ፡ የኹለቱንም ፡ ባለቅኔዎች ፡ ሐሳብ ፡ ለውጠው ፡ ሌላ ፡ አስተያየት ፡ ሰጥተውታል ።

## ደ ራ ሲ ።

፬/ ባ፬፡ ዓይን ፡ ጎሹ ፡ ቅኔ ፡ የክርስቶስ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ወደ ፡ አምላክነት ፡ ባሕርይ ፡ የተ ለወጠ ፡ በቅብዐት ፡ ነው ፡ የክርስቶስን ፡ ኹለቱን ፡ ባሕርያት ፡ ያዋሐዳቸው ፡ ቅብዐት ፡ መኾኑ ፡ ነው፡ ሥጋዌም ፡ የተፈጸመው ፡ በቅብዐት ፡ ነው ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ የ/ሚል ፡ አስተያየት ፡ ሠለውበታል ።

## መ ላ ሽ ።

፬/ ፬ ፡ ዐይን ፡ ጎሹ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ወደ ፡ አምላክነት ፡ ባሕርይ ፡ በቅብዐት ፡ ተለወጠ፡ አይሉም ፡ ሥጋዌም ፡ የተፈጸመ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ ባለው ፡ በከዊን ፡ ተዋሕዶ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በቅ ብዐት ፡ ተፈጸመ ፡ አይሉም ፡ ፍጹም ፡ ውሸት ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፭/ ለቄስ ፡ ገበዝ ፡ ኑርልኝም ፡ ቅኔ ፡ ይህ ፡ ቅብዐት ፡ እንደ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ አሳብ ፡ ቀዳሹ ጸጋ ፡ ከነመንፈስ፡ ቅዱስ ፡ ስጦታዎች ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ቅብዐ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ክብርነ ፡ የተባለው፡ ቀብዐት ፡ ወይም ፡ ጸጋ ፡ በዐይነቱ ፡ ልክ ፡ በማናቸውም ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ነፍስ ፡ እንደሚገኘው ፡ ጸጋ ነው ፡ ተቀባዩም ፡ የቃል ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ነው ፡ በማለትዎ ፡ ባላቅኔው ፡ በመለኮትና ፡ በትስብ እት ፡ መካከል ፡ ምንታዌ ፡ አለ ፡ ያሉ ፡ ከማስመስልዎም ፡ በላይ ፡ ቅኔውን ፡ ኀቢርና ፡ ተገብሮ ፡ አድ ርገውታል ።

## መ ላ ሽ ።

፭/ ባለቅኔውስ ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ ባይ ፡ ስለኾነ ፡ ቃል ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ ሥጋ ፡ ቢለብስ ፡ ከእመ ቤታችን ፡ የነሣውን ፡ ሥጋ ፡ በተዋሕዶ ፡ አከበረው ፡ እንጂ ፡ ለእኛ ፡ ክብር ፡ የሚኾን ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ቅብዐት ፡ ወይም ፡ ጸጋ ፡ በማናቸውም ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ነፍስ ፡ እንደሚገኘው ፡ ጸጋ ፡ የቃል ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ተቀበለ ፡ ብለው ፡ መለኮትን ፡ ከትስብእት ፡ በሚለይ ፡ አነጋገር ፡ አልተናገሩም ።

ከባለቅኔዎች ፡ አሳብ ፡ ሳይደርሱ ፡ በመላ ፡ በድፍረት ፡ እንዲህ ፡ እያሉ ፡ ይተቻሉ ፡ እንጂ ፡ የባለ ቅኔዎቹስ ፡ ሐሳብ ፡ እኔ ፡ ከላይ ፡ እንደገለጽኩልዎ ፡ ነው ፡ ኹለቱም ፡ ባለቅኔዎች ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዕ ፡ በማለት ፡ ብቻ ፡ ይለያያሉ ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ በማ ለትስ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ አይለያዩም ።

## ዶ ራ ሲ ።

፩/ ያለቃ ፡ ተክለ ፡ ጽዮንን ፡ ቅኔ ፡ ጽፈዋል ፡ ቅኔውም ።

ኢዲኤይሱን ፡ ምንተ ፡ እለ ፡ ተሴሰዩ ፡ እማዕዳቲሁ ፡ ለፈርዖን ።
ፍርፋራተ ፡ ስሕተት ፡ ወዳጓዕ ፡
ወማየ ፡ ውሳጤ ፡ ዘሰትዩ ፡ እምዐይጋቲሃ ፡ ለግብጽ ።
ጎበ ፡ ተደለወ ፡ መቅሠፍቶሙ ፡ ሐጽ ።
አኮኑ ፡ እንበለ ፡ ድምፅ ።
ማዕበለ ፡ ጌጋዮሙ ፡ ባሕር ፡ በከተማ ፡ ርእሶሙ ፡ ይረውጽ ፡

እመሰ ፡ ማየ ፡ ውሳጤ ፡ በርእሰ ፡ አማኑኤል ፡ ሠርጽ ።
እስመ ፡ ባሕረ ፡ ግዘፍ ፡ ተቀንዎቱ ፡ በሐጋየ ፡ ርቀት ፡ ኢየሐጽጽ ።
አየ ፡ ገቦ ፡ ረገዙ ፡ ሐራ ፡ ጲላጦስ ፡ አብያጽ ።
ወ አይ ፡ ግዝፈ ፡ ሥጋ ፡ ተቀነወ ፡ ዲበ ፡ ዕፅ ፡ የሚል ፡ ነው ።

## መ ላ ሽ ።

ይህን ፡ ቅኔ ፡ ወደ ፡ አማርኛ ም ፡ ቢመልሱት ፡ ከፈርዖን ፡ ማዕድ ፡ ስሕተት ፡ እንፍርፋሪን ፡ የተመገቡ ፡ ከግብጽ ፡ ምንጭም ፡ ተለወጠ ፡ ማለት ፡ ውኀን ፡ የጠጡ ፡ ሰዎች ፡ ምንም ፡ አይነቅፉንም ።

መቅሠፍታቸው ፡ ፍላጻ ፡ ከተዘጋጀ ፡ ዘንድ ፡ ጥፋታቸው ፡ ማዕበል ፡ ሳይሰማ ፡ በራሳቸው ፡ መካከል ፡ ይሮጣልና ፡ መለወጥ ፡ ወኀ ፡ በአማኑኤል ፡ ቡቃያ ፡ ራስ ፡ ኖሮስ ፡ ቢኾን ፡ የግዘፍ ፡ ባሕር ፡ መቸንከሩ ፡ በርቀት ፡ በጋ ፡ አይደርቅምና ፡ የጲላጦስ ፡ ጭፍሮች ፡ ምን፡ ጐን ፡ ወጉ ፡ ምን ፡ ግዙፍ ፡ አካልስ ፡ በዕንጨት ፡ ቸነከሩ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ምሥጢሩም ፡ ባጭሩ ፡ አማኑኤል ፡ የነሣው ፡ ሥጋ ፡ ረቂቅ ፡ ነው ፡ ማለትን ፡ ከግብጻውያን ፡ የተማሩ ፡ ሰዎች ፡ እኛን ፡ ሊነቅፉን ፡ አይገባም ፡ አማኑኤል ፡ የነሣው ፡ ግዙፍ ፡ ሥጋ ፡ ተለውጦ ፡ ረቂቅ ፡ ከኾነ ፡ ረቂቅ ፡ ነገር ፡ ሊወጋ ፡ ሊቸነከር ፡ አይቻልምና ፡ የጲላጦስ ፡ ጭፍሮች ፡ ምን፡ ጐን ፡ ወጉ ፡ ምንስ ፡ አካል ፡ በዕንጨት ፡ ላይ ፡ ሰቀሉ ፡ ማለት ፡ ነው ።

፪/ የዚህ ፡ ቅኔ ፡ ባለቤት ፡ አለቃ ፡ ተክለ ፡ ጽዮን ፡ በአባ ፡ ማስያስ ፡ ስብከት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን በኑሩዋቸው ፡ ብስጭት ፡ ምክንያት ፡ ወደካቶሊካውያን ፡ መጠጋታቸው ፡ አይካድም ።

ይህን ፡ ቅኔ ፡ በካቶሊካውያን ፡ ዘንድ ፡ ታማኝነትን ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ ልባቸው ፡ እያወቀው ፡ መስሎ ፡ ለመታየት ፡ የደረሱት ፡ ቅኔ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በኢትዮጵያስ ፡ ተለወጠ ፡ ረቀቀ ፡ የሚል ፡ እንደ ሌለ ፡ ያውቁታል ።

ያውቁታል ፡ የምልበትም ፡ ምክንያት ፡ ከላይ ፡ በገለጽኩት፡ አኳኋን ፡ ወደካቶሊካውያን ፡ እስኪጠጉ ፡ ድረስ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ የሚተረጕሙትን ፡ ትርጓሜ ፡ የሚቀኙትን ፡ ቅኔ ፡ የሚያውቁ ፡ ስለኾነ ፡ ነው ።

ለዚህም ፡ መረጃ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ አባ ፡ ፍሬ ፡ የተባሉት፡ የጐንደሩ ፡ ሊቅ ፡ የተቀኙትን ፡ ቅኔ ፡ እጠቅሳለሁ ።

ሙሴ ፡ ለዕፀ ፡ እምነ ፡ መርገማ ፡ ተማይጠ ፡ ርእሱ ፡ ኢክህለ ፡ ወኢተረከበ ፡ ሥሉጠ ።
እመኒ ፡ በዕፅ ፡ ርእሰ ፡ ኤርትራ ፡ ቀጥቀጠ ።
ወእምኩሄሕ ፡ ሥጋ ፡ ነፍሰ ፡ ማይ ፡ ፈለጠ ።

ኀበሰ ፡ ኢተወለጠ ፡ ወእምያርብሐዊ ፡ ተምያጥ ፡ በፍና ፡ ጥበቡ ፡ ኀበ ፡ አምሠጠ ።
እብነ ፡ ካህድ ፡ ሆሣዕና ፡ ዘኢይሰምዕ ፡ ኀዳጠ ።
እመ ፡ ነገርዎ ፡ ሐራ ፡ ጥቃ ፡ ተምያጠ ፡ ወተውላጠ ።
ልብሰ ፡ ውስጥ ፡ ወአፍአ ፡ መርገመ ፡ በእካለ ፡ ርእሱ ፡ ሠጠጠ ።
ወበዕፅ ፡ እንበለ ፡ ወርቅ ፡ ዓለመ ፡ ተማየጠ ።

ወደአማርኛም ፡ ቢመልሱት ፡ ሙሴ ፡ ኤርትራን ፡ በበትሩ ፡ ቢከፍል ፡ ወኀንም ፡ ከደንጋይ ፡ ቢያፈልቅ ፡ ራሱን ፡ ከፍዳ ፡ ከመርገም ፡ ሊያድን ፡ አልቻለም ፡ ሐራ ፡ ጥቃ ፡ ተለወጠ ፡ ረቀቀ ፡ የሚሉት ፡ ሆሣዕና ፡ መለወጥ ፡ መርቀቅ ፡ የሌለበት ፡ ከኾነ ፡ ዘንድ ፡ መርገመ ፡ ሥጋ ፡ መርገመ ፡ ነፍስን ፡ አጠፋ። ዓለምን ፡ በወርቅ ፡ ሳይኾን ፡ በመስቀል ፡ ዋጀ ፡ ማለት ፡ አዳነ ፡ ብለዋል ።

ይህ ፡ ቅኔ ፡ በክርስቶስ ፡ ውሳጤ ፡ ቡዓዴ ፡ እንደሌለበት ፡ ኢትዮጵያም ፡ ተለወጠ ፡ ረቀቀ ፡ የማትል መኾንዋን ፡ በግልጥ ፡ ያስረዳል ። በእውነቱ ፡ ይህን ፡ ቅኔ ፡ ልብ ፡ ብለው ፡ ሲመለከቱት ፡ አለቃ ፡ ተክለ ፡ ጽዮን ፡ በካቶሊካውያን ፡ ዘንድ ፡ መታመንን ፡ ለማግኘት ፡ መስሎ ፡ ለመታየት፡ሲሉ፡ ወማየ ፡ ውሳጤ ፡ ዘሰትዩ ፡ እምዐይጋቲሃ ፡ ለግብጽ ፡ እመሰ ፡ ማየ ፡ ውሳጤ ፡ በርእሰ ፡ አማኑኤል ፡ ሠርጽ ፡ እያሉ



ይህ ሥዕል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት እያዩት በሥጋ ወደ ሰማይ እንዳረገ ያሳያል ። ማር ፲፮ ፲፱
ሉቃ ፳፬ ፶፩ ግብ ሐዋ ፩ ፱ ፲፱ ።

ንባብ ፡ ብቻ ፡ ቀብተውታል ፡ እንጂ ፡ አየ ፡ ዓፀ ፡ ፅፀዙ ፡ ሐራ ፡ ጲላጦስ ፡ አብያጽ፡ወአይ፡ግዘፈ ፡ ሥጋ ተቀነወ ፡ ዲበ ፡ ዕፅ ፡ በማለታቸው ፡ የካቶሊክን ፡ ባህል ፡ የነቀፉ ፡ ይመስላል ።

ምክንያቱም ፡ ካቶሊካውያን ፡ አካል ፡ ለቃል ፡ እንጂ ፡ ለትስብእት ፡ የለውም ፡ የሚሉ ፡ ስለኾ ነና ፡ የቃልም ፡ አካል ፡ ረቂቅ ፡ የማይሰቀል ፡ የማይወጋ ፡ ስለኾነ ፡ ነው ።

፪ኛም ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍዎ ፡ በ፪፻፩ ፡ ገጽ ፡ የተጻፈው ፡ የቃላቱ ፡ የአለቃ ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ ቅኔ ያስረዳል ።

ቅኔውም ፡ የሚከተለው ፡ ነው ፡

እምዐፀደ ፡ ትድምርት ፡ ወይን ፡ ላዕለ ፡ ሆማዕና ፡ ኀበ ፡ ሰብአ ፡ ሮሚ ፡ ይሰሐብ ፡ ባህለ ፡ ውላጤ ሐረግ ።

እስመ ፡ ክበበ ፡ ወርኀ ፡ ባህሎሙ ፡ ምስለ ፡ ባህለ ፡ ንስጥሮስ ፡ ዘውግ ።
ወነገር ፡ ዝንቱ ፡ ዘልዮን ፡ ምስሐግ ። ዘሰ ፡ ለኀዲግ ፡
እመ ፡ ማየ ፡ ምሥጢር ፡ ንቀድሕ ፡ እምነ ፡ መጻሕፍት ፡ አፍላግ ።
ኢይባእ ፡ ጽርሐ፡ውላጤ ፡ እስመ ፡ ተዋሕዶ ፡ መንሠግ ።
እምዐቅመ ፡ አቡሁ ፡ ኢይወርድ ፡ ወእምአቅመ ፡ እሙ ፡ ኢየዐርግ ፡
ወእንበለ ፡ ተውላጥ ፡ ንረክብ ፡ ከመ ፡ አስተዳለወት ፡ ሕግ ።
ዘባነ ፡ ኪሩብ ፡ ለመሬታዊ ፡ ወለሰማያዊ ፡ ዘባነ ፡ አድግ ።

<u>ትርጓሜውና ፡ ምሥጢሩ ፡ ባጭሩ</u>

ተለወጠ ፡ የማለት ፡ ባህል፡ ሐረግ ፡ በሆማዕና ፡ ላይ ፡ ከትድምርት ፡ ወይን ፡ ቦታ ፡ ወደሮም ፡ ሰዎች ፡ ይሳባል ፡ ማለት ፡ ወንጌላዊ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኮነ ፡ በማለቱ ፡ ቃል ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ ያለውን፡ ሰብአዊ ፡ አካል ፡ መዋሐዱ ፡ የታወቀ ፡ ሲኾን ፡ ሮማውያን ፡ አካል ፡ ለቃል ፡ እንጂ ፡ ለትስብእት ፡ የለውም ፡ ስለሚሉ ፡ ትስብእት ፡ ተለወጠ ፡ ወይም ፡ ጠፋ ፡ ያሰኛቸዋል ፡ ማለት ፡ ነው ።የጨረቃ ፡ ክበብ ባህላቸው ፡ ከንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ ጋራ ፡ [illegible] ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ አንድ ናቸውና ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ባህል ፡ ለመተው ፡ ከመጻሕፍት ፡ ወንዞች ፡ ምሥጢር ፡ ውኀን ፡ ብንቀዳ ፡ (ማለት ፡ መጻሕፍትን ፡ ብንመረምር ፡ ወደ ፡ መለወጥ ፡ አዳራሽ ፡ እንዳይገባ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቍልፍ ፡ ነውና (ማለት ) ፡ ተለወጠ ፡ እንዳይባል ፡ ተዋሕዶው ፡ በተፀቅቦ ፡ ነውና ፡ ለውም ፡ ቢኾን ፡ ከአባቱ ፡ ጋራ ፡ ዕሩየ ፡ መንበር ፡ ከመኾኑ ፡ አልተዋረደም ። አምላክም ፡ ቢኾን ፡ ከእናቱ ፡ መጠን ፡ አይወጣም ፡ (ማለት) ፡ ሰብአዊ ፡ ተግባርን ፡ አልተጸየፈም፡ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ሠራ ፡ ማለት ፡ ነው ።ሕግም ያለመለወጥ ፡ ለመሬታዊ ፡ ለትስብእት ፡ የኪሩብን ፡ ጀርባ ።

ለሰማያዊ ፡ ለመለኮትም ፡ የአኽያን ፡ ጀርባ ፡ እንዳዘጋጀች ፡ እናገኛለን ፡ ማለት ፡ ከአባቱ ፡ መጠን አይወርድም ፡ ከናቱ ፡ መጠን ፡ አይወጣም ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ መሬታዊ ፡ ትስብእት ፡ ሰማያዊ ፡ መለኮትን ፡ ስለተዋሐደ ፡ በዘባነ ፡ ኪሩብ ፡ ተቀመጠ ፡ ሰማያዊ ፡ መለኮትም ፡ ምድራዊ ፡ ትስብእትን ፡ ስለ ተዋሐደ ፡ በአኽያ ፡ ጀርባ ፡ ተቀመጠ ፡ ማለት ፡ ነው ።

በኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ የሚደረሱ ፡ ቅኔዎች ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ጠንቅቀው ፡ ክርስቶስ ፡ ውላጤ ቡዐዴ ፡ እደሌለበት ፡ የሚያስረዱ ፡ ናቸው ።

አለቃ ፡ ተክለ ፡ ጽዮን ፡ ወማየ ፡ ውላጤ ፡ ዘሰትዩ ፡ እምዐይጋቲሃ ፡ ለግብጽ፡ ያሉት ፡ በፍጹም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሌለ ፡ ነገር ፡ ነው ።

እርስዎም ፡ ለዚህ ፡ ለአለቃ ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ ቅኔ ፡ አስተያየት ፡ ሲሰጡ ፡ ይህ ፡ መወድስ ፡ ከካቶሊክ ትምህርት ፡ ብዙ ፡ ሩቅ ፡ ያልኾነውን፡ኢትዮጵያውያን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ የሚያምኑትን ፡ ትምህርት ፡ በማሳጠር ፡ ጠቅሎ ፡ የያዘ ፡ ነው ።

እንደ ፡ እውነቱም ፡ የክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ እንበለ ፡ ተውላጥ ፡ በሙሉነታቸው ፡ አሉ፡ ይባልበታል ። ክርስቶስ ፡ እምዐቅመ ፡ አቡሁ ፡ ኢይወርድ ፡ ወእምዐቅመ ፡ እሙ ፡ ኢየዐርግ ፡ በመባል፡ ፍጹም ፡ አምላክና ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ መኾኑ ፡ ተገልጧል ። ፍጹም ፡ ሰው ፡ ሲኾን ፡ የአምላክነት ፡ ሥራ ፡ መሥራቱን ፡ ፍጹም ፡ አምላክም ፡ ሲኾን ፡ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ መሥራቱን ፡ ለማስረዳት ፡ ደራሲው ዘባነ ፡ ኪሩብ ፡ ለመሬታዊ ፡ ወለሰማያዊ ፡ ዘባነ ፡ አድግ ፡ ይላል ፡ በማለትዎ ፡ ለአለቃ ፡ ተክለ ፡ ጽዮን ቅኔ ፡ አስተያየት ፡ ሲሰጡ ፡ የእስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምታስተምረውና ፡ ተከራካሪዎቹ ፡ የሚያምኑትን ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ተለወጠ ፡ ወይም ፡ በመለኮት ፡ ውስጥ ፡ ጠፋ ፡ የሚለውን ፡ የአንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮችን ፡ ባህል ፡ ነቀፈ ፡ የሚሉት ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ ዋጋ፡ ቢስ ፡ ንግግር ፡ መኾኑን ፡ ተረድተውታል ፡ ለማለት ፡ ቶችሏል ።

## ፫ኛ ፡ ዋዜማ ።

### ደ ራ ሲ ።

፯/ መንበረ ፡ ኪሩባዊ ፡ ለእመ ፡ በቅብዐት ፡ ወረሰ ፡ ፍሬ ፡ ክርሥኪ ፡ ዕጹብ ፡ ዘወርቀ ፡ ድንጋሌ ማርያም ፡ መሶብ ።
እስመ ፡ ከማሁ ፡ ዘልን ፡ ሱቱፋን ፡ ቅብዐት ፡ ሕዝብ ።
እስፍንተ ፡ ይጸውር ፡ መንበሩ ፡ ለአብ ።
ወእስፍንተ ፡ ያገምር ፡ ኪሩብ ፡ የሚል ፡ ቅኔ ፡ ጽፈዋል ።
ለዚህ፡ቅኔ፡አስተያየትም፡ሲሰጡ፡የመንፈስ፡ቅዱስ፡ቅብዐትን፡የተገባ፡ተቀባይ ፡ የሚኾን ፡ የሰውነት ፡ ባሕርይ ፡ በክርስቶስ ፡ መገኘቱንና ፡ ቃል ፡ የተባለው ፡ ቅብዐት ፡ ተቀባይ ፡ ሊኾን ፡ አለመቻሉን ፡ እንደማያከራክር ፡ በማሰብ ፡ ክርስቶስና ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ የኾኑ ፡ ቅብ ዐት ፡ ወይም ፡ ጸጋ ፡ ይቀበላሉ ፡ ማለትን ፡ መፈለጉ ፡ በግልጥ ፡ ይረዳ ል ፡ ብለዋል ።

### መ ላ ሽ ።

፯/ የዚህ ፡ ቅኔ ፡ ትርጓሜውና ፡ ምሥጢሩ ፡ ባጭሩ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ፡ በወርቅ ፡ መሶብ የተመሰልሽ ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ሆይ ፡ የማኅፀንሽ ፡ ፍሬ ፡ ክርስቶስ ፡ ኪሩቤል ፡ የሚሸከሙትን ዙፋን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በመቀበሉ ፡ የወረሰ ፡ ከኾነ ፡ ኹላችንም ፡ እንደ ፡ እርሱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱ ስን ፡ በመቀበል ፡ አንድ ፡ ነንና ፡ የአብ ፡ ዙፋን ፡ ስንቱን ፡ ይሸከማል ፡ ኪሩብስ ፡ ስንቱን ፡ ይችላል ፡ ማለት ፡ ነው ።

የዚህ ፡ ቅኔ ፡ ባለቤት ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ በተዋሕዶ ፡ ከበረ ፡ ከሚሉት ፡ ወገን ፡ ኾኖ ፡ በቅብዐተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ ኾነ ፡ የሚሉትን ፡ ወገኖች ፡ ለመንቀፍ ፡ የደረሰው ፡ መኾኑን ለማወቅ ፡ የሚያዳግት ፡ ነገር ፡ የለበትም ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

እርስዎ ፡ ግን ፡ ባለቅኔው ፡ ስንኳን፡ሊናገረው ፡ በሕሊናው ፡ ያላሰበውን ፡ ነገር ፡ ክርስቶስና ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ አይነት ፡ የኾነ ፡ ቅብዐት ፡ ወይም ፡ ጸጋ ፡ ይቀበላሉ ፡ ማለትን ፡ መፈለ ጉን ፡ በግልጥ ፡ ያስረዳል ፡ የሚል ፡ አስተያየት ፡ ጥለውብታል ።

ይህ ፡ አስተያየት ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ትምርት ፡ የሌላቸው ፡ ያላስተዋሉ ፡ ሰዎች ፡ መጻሕፍትን ለምኞታቸው ፡ እንደሚስማማ ፡ አድርገው ፡ ይለዋውጧቸዋል ፡ ብሎ ፡ ከተናገረባቸው፡ሰዎች ፡ ጋራ የሚያስቈጥርዎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሚያስመሰግንዎ ፡ አይደለም፡ ባለቅኔውም፡በሕይወት ፡ ሥጋ ፡ ኖሮ ቢኾን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ፩፻፸፪ ፡ ቍ ፡ በተጻፈው ፡ እንቀጽ ፡ በስም ፡ አጥፊነት ፡ ወንጀል ፡ በከሰስዎ ፡ ነበረ ።

### ደ ራ ሲ ።

፬ኛ፡ የጐንደሩን ፡ ሊቅ ፡ የክፍለ ፡ ዮሐንስን ፡ ቅኔ ፡ ጠቅሰዋል ።
፰ ፡ ሃይማኖት ፡ ቈርሎስ ፡ ኮነት ፡ ግማዳተ ፡ አብድ ፡
ውኊልቈ ፡ ተመትሮ ፡ አብዝኀት ፡ ኢምኀበ ፡ ኢኀሎ ፡ ንጉሥ ።
ካህነ ፡ ደብረ ፡ ኤፍሬም ፡ ቅድመ ፡ እምዘመተራ ፡ ነዐስ ።

ወእመ ፡ ኢዮርብዐም ፡ ለምሳሌ ፤ በእደ ፡ ነቢይ ፡ ዘተሠጠት ፡ ልብስ ፡
እምገዝኢ ፡ ዘይብእስ ፡ ወዘያንድድ ፡ ልቡና ፡ ኢትበሊ ፡ ኤዶምያስ ፡
ተቀብዐ ፡ ቅብዐ ፡ ውላጤ ፡ ጎሩመ ፡ ቅብዐት ፡ ክርስቶስ ፡
እምጣነ ፡ እኮ ፡ በተቀብዖቱ ፡ በዘረ ፡ ውሉዳ ፡ ለዮርዳኖስ ፡
ወእንዘ ፡ ትትናገሪ ፡ ዘንተ ፡ በአትሕቶ ፡ ክማድ ፡ ወርእስ ።
ከመ ፡ እነ ፡ ሰማዕኩኪ ፡ ኢይሰማዕኪ ፡ ጳውሎስ ።

ይህም ፡ ቅኔ ፡ ሐሳብዎን ፡ የማይገድፍ ፡ ኾኖ ፡ ቢያገኙት ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወገን ፡ ይሆን ፡ ለመ ሰሉ ፡ ተከራካሪዎቻቸው ፡ ትምርት ፡ ሲቃወሙ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ቅብዐት ፡ ወይም ፡ ለፍ ጡራን ፡ የሚሰጥ ፡ ተጨማሪ ፡ ጸጋ ፡ በቂ ፡ ተቀባይ ፡ የሚኾን ፡ በክርስቶስ ፡ የትስብእት ፡ ባሕርይ ፡ እስ ፡ ማለትን ፡ የሚያስከትል ፡ ትምርት ፡ ሲኖራቸው ፡ ግድ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ከደራሲው ፡ አሳብ ፡ ውጭ ፡ የኾነ ፡ ብይን ፡ ሰጥተዋል ።

ቀጥሎም ፡ ደራሲው ፡ ሊያስረዳ ፡ የፈለገ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ ባሕርየ ፡ መለኮት ፡ መኾኑን ፡ ሳይተው መቸም፡ መቼ፡ የፍጡራን ፡ መቀባት ፡ ያስፈልገው ፡ አልነበረም ፡ ክርስቶስም ፡ አምላክ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ መኾኑ፡ መጠን ፡ የፍጡራን ፡ በኩር ፡ ኾነ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብለዋል ።



ይህ ሥዕል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ደቂቅ አእሩግ ሕፃናት አንድ ኾነው ሆሣዕና በኣርያም እያሉ እንደተቀበሉት ያሳያል ። ማቴ ፳፩ ፩ ፲፯ ። ስለዚህ ሰማያዊ መለኮት በሥጋ በአህያ ጀርባ ላይ ተቀምጦ ሆሣዕና በኣርያም ተብሎ ስለተመሰገነ በስቅለቱ ዘባን ኪሩብ ለመሬታዊ ወለሰማያዊ ዘባን አድግ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፰/ የባለቅኔው ፡ ሐሳብና ፡ የቅኔው ፡ መንገድ ፡ እንደዚህ ፡ አይደለም ፡
የቅኔውስ ፡ ትርጓሜ ፡ ከነምሥጢሩ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

የሚሠራ ፡ የሚቀጣ ፡ ንጉሥ ፡ ከሌለ ፡ ዘንድ ፡ የቁርሎስ ፡ ሃይማኖት ፡ የእብድ ፡ ጨርቅ ፡ ኾነች ። ቀጥሯም ፡ የደብረ ፡ ኤፍሬም ፡ ካህን ፡ ፲፪ አድርጎ ፡ ከቀራረጣት ፡ ሴትና ፡ በኢዮርብዓም ፡ ጊዜ ፡ ለምሳሌ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ በነቢይ ፡ እጅ ፡ ፲፪ ፡ ኾና፡ ከተቀደደች ፡ ልብስ ፡ ይልቅ ፡ እየበዛ ፡ ሔደ ፡ በማለቱ ፡ ሃይማኖት ፡ አንዲት ፡ ስትኾን ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ካቶሊክ ፡ ቡርስታንት ፡ በመባባል ፡ ከብዙ ፡ መከፋፈሏን ፡ አስረድቷል ።

ቀጥሎም ፡ ኤዶምያስ ፡ ሆይ ፡ መለወጥ ፡ መቀባት ፡ የሌለበት ፡ ክርስቶስ ፡ ለምእመናን ፡ በኲር ፡ መኾኑ ፡ በመቀባቱ ፡ አይደለምና ፡ የመለወጥ ፡ ቅብዐትን ፡ ተቀባ ፡ አትበይ ፡ በማለቱ ፡ ደራሲው ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ፡ ከሚሉት ፡ ወገን ፡ ኾኖ ፡ በቅብዐተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ የሚሉትን ፡ ወገኖች ፡ ለመንቀፍ ፡ ቢል ፡ የደረሰው ፡ መኾኑ ፡ ይረዳል ።

ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ የሚሉትም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዕ ፡ የሚሉትም፡ወገኖች፡ብቻ፡ለብቻ፡በኾኑ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ በመሰለ ፡ ነገር ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ቢከራከሩም ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የሚል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ ዘሠረጸ ፡ እምወልድ ፡ የሚል ፡ ካቶሊካዊ ፡ ሲመጣ ፡ ተባብረው ፡ የሚመከቱ ፡ ናቸው ፡ የሚነጣጠሉ ፡ አይደሉም ።

እርስዎ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ በሚመክቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ መካከል ፡ ገብቶ ፡ ለማለያየት ፡ ስለተመኙ ፡ በማያገባዎ ፡ ነገር ፡ ገብተው ፡ ሲዘበርቁ ፡ ይታያሉ ።

መዘባረቅም ፡ ያልኩት ፡ ቃል ፡ ማለት ፡ የመለኮት ፡ ብቻ ፡ ስም ፡ ነው ፡ ትስብእትም ፡ ማለት ፡ የዕውነት ፡ ብቻ ፡ ስም ፡ ነው ፡ ክርስቶስ ፡ ማለት ፡ ግን ፡ ቃል ፡ ሥጋን ፡ ቢዋሐድ ፡ የወጣለት ፡ የተዋሕዶ ፡ ስም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ቃል ፡ ብቻውን ፡ ክርስቶስ ፡ አይባልም ፡ ትስብእትም ፡ ብቻውን ፡ ክርስቶስ አይባልም ፡ ባለቅኔውም ፡ ጠንቅቆ ፡ በተዋሕዶ ፡ ስሙ ፡ ኅሩመ ፡ ቅብዐት ፡ ክርስቶስ ፡ ቢል ፡ መለኮትን ከትስብእት ፡ በሚለያይ ፡ ስም ፡ ጠርተው ፡ ፪ ፡ ባሕርይ ፡ ለማለት ፡ እንዲመች ፡ ቃል ፡ ቀዳሹን ፡ ጸጋ፡ ተቀበለ ፡ የሚለውን ፡ ባህል ፡ በፍጹም ፡ እንደማይቀበሉት ፡ እንረዳለን ። ደራሲው ፡ ሊያስረዳ ፡ የፈለገ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ ባሕርየ ፡ መለኮት ፡ መቸም ፡ መች ፡ የፍጡራን ፡ መቀባት ፡ ያስፈልገው ፡ አልነበረም ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ቅብዐት ፡ ተቀባይ ፡ የትስብእት ፡ ባሕርይ ፡ ሊኖረው ፡ ግድ ፡ ነው ፡ እያሉ ከደራሲው ፡ ሐሳብ ፡ የወጣ ፡ አነጋገር ፡ ስለተናገሩ ፡ ነው ።

በዚህ ፡ አኳኋን፡ በቅኔው ፡ መንገድ ፡ ሲደርሱበት ፡ አልቻሉምና ፡ የሊቃውንቱን ፡ ቅኔ፡አያበላሹ።

## ደ ራ ሲ ።

፱/ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ የጸጋ ፡ ልጅ ፡ ወገን ፡ የኾነ ፡ አለቃ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ የተባለው ፡ ከደረሰው ፡ ቀጥሎ ፡ ካለው ፡ ሥላሴ ፡ ያልነውን ፡ ባህል ፡ የሚደግፍ ፡ አሳብ ፡ ይገኛል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፱/ በቅኔው ፡ መንገድ ፡ ሳይደርሱበት ፡ የደረስኩበት ፡ መስሎዎ ፡ ምኞትዎን ፡ ይተቻሉ ፡ እንጂ ፡ የቅኔው ፡ መንገድና ፡ የርስዎ ፡ አስተያየት ፡ እንደ ፡ ሰማይና ፡ እንደ ፡ ምድር ፡ የተራራቀ ፡ ነው ደራሲው ፡ አለቃ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስም ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ ባይ ፡ መኾናቸው ፡ የተረጋገጠ ፡ ሲኾን ፡ የጸጋ ፡ ልጅ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፡ ያሉትም ፡ ፍጹም ፡ ውሸት ፡ ነው ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ ባይ ፡ መኾናቸው በቅኔው ፡ ይታወቃል ።

## ደ ራ ሲ ።

## ሥላሴ ፡ ዘአለቃ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ።

፲/ በጸዊረ ፡ ስም ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ኢኮነ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡
ከመስ ፡ ኢይኅሥሥ ፡ ለጽምዑ ፡ ጠለ ፡ ተቀብዖ ፡ ዝናም ፡
በፈለገ ፡ ዘይት ፡ ክርስቶስ ፡ ቅውም ፡
አርአያ ፡ መልክኡ ፡ ለቄሳር ፡ ነጋሢ ፡ እመ ፡ ይጸውር ፡ ማኅተም ፡
ማኅተም ፡ ኢኮነ ፡ ንጉሠ ፡ ሮም ።
ወእንዘ ፡ ቅብዐ ፡ ላሕም ፡ ያከብር ፡ ሥእርተ ፡ ዓለም ፡
በተቀብዖ ፡ ኢትከብር ፡ ላሕም ፡
ከዚህም ፡ ሥላሴ ፡ ደራሲው ፡ ስለቅብዐትና ፡ ስለኹለቱ ፡ የክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ የቀና ፡ አሳብ ፡ በግልጥ ፡ ይታያል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

ሰው ፡ በልቡ ፡ የተመኘውን ፡ ወይም ፡ ቀን ፡ ሊያገኘው ፡ የሚፈልገውን ፡ ሌሊት ፡ በሕልሙ ፡ እየታየው ፡ ሲታዥ ፡ የሚያድረውን ፡ ያህል ፡ ምኞትምን ፡ እንደልብዎ ፡ ይናገራሉ ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ ቅኔ ፡ ውስጥ ፡ ክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በግልጥ ፡ የምጣድ ፡ ብልጭልጭታ ፡ ያህልም ፡ አይታይበትም ።

## ድ ራ ሲ ።

፲፩/ ድራሲው ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ የቅባቶችን ፡ ባህል ፡ ይገድፍ ፡ የነበረው ፡ የበጌምድር ፡ ጥንታዊ ገዳም ፡ የቅባቶችን ፡ ትምርት ፡ በመደገፉ ፡ ስሙንና ፡ ባሕርዩን ፡ ለውጦ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ተብሎ ፡ እንደ ማይጠራ ፡ እንዲሁም ፡ ቅብዐት ፡ ክርስቶስን ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ መኾን ፡ ከፍ አላደረገውም ፡ ወይም ፡ አላከበረውም ፡ ይላል ።

ይህም ፡ ክርስቶስ ፡ ቅብዐትን ፡ ተቀብሎ ፡ ሲያበቃ ፡ የተቀበለው ፡ ቅብዐት ፡ የመለኮት ፡ ባሕርዩንና አካሉን ፡ ፈጽሞ ፡ የማይነካ ፡ ነው ፡ ማለቱ ፡ ነው ። ክርስቶስ ፡ በአካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ የተቀበለውና ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ መኾን ፡ ከፍ ፡ ያደረገው ፡ ጸጋ ፡ ተዋሕዶ) ፡ ዝናም ፡ ከጤዛ፡ የሚበልጠውን ፡ ያህል ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዐት ፡ ከቀዳሽ ፡ ጸጋ) ፡ ይበልጣል ፡ ክርስቶስ ፡ ማለት የተቀባ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አንድ ፡ ማኅተም ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ በሚገኘው ፡ መልክና ፡ ቅርጽ ፡ የማን ፡ ንጉሥ ፡ መኾኑ ፡ እንደ ፡ ሚታወቅ ፡ እንዲሁም ፡ ክርስቶስ ፡ በቅብዐት ፡ መሲሕ ፡ መኾኑ ፡ ይታወቃል ፡ ክርስቶስ ፡ ሲቀባ ፡ የቅብዐቱ ፡ (የቀዳሹ ፡ ጸጋ) ፡ ተቀባይ ፡ የሚኾነው ፡ ሥጋ ፡ በለበሰ ፡ ጊዜ ፡ የወሰደው ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አካለ ፡ ቃል ፡ ሊኾን ፡ አይችልም ፡ ምክንያቱም ፡ እርሱ የተቀበለውና ፡ እኛ ፡ የምንቀበለው ፡ ጸጋ ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ ስለኾነ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፩/ ለዚህ ፡ ቅኔ ፡ የሰጡት ፡ አስተያየት ፡ ኹሉ ፡ ከባለ ፡ ቅኔው ፡ ያልመጣ ፡ ከዘይቤ ፡ የወጣ ልብ ፡ ወለድ ፡ ንግግር ፡ ነው ፡ የቅኔውስ ፡ ትርጓሜውና ፡ ምሥጢሩ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

አስቀድሞ ፡ ይህን ፡ ቅኔ ፡ የተቀኙበትን ፡ ምክንያት ፡ ማወቅ ፡ ይገባል ፡ ይህን ፡ ቅኔ ፡ የተቀኙት ፀበዓለ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ነው ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ብርሃነ ፡ መለኮቱ ፡ የተገለጸበት ፡ እምላክነቱ ፡ የታወቀበት ፡ ቦታ ፡ ነው ።

በደብረ ፡ ዘይት ፡ ደግሞ ፡ ምሥጢረ ፡ ምጽአቱን ፡ አስተማረበት ፡ እንጂ ፡ ብርሃን ፡ አልታየበትም ፡ እንደ ፡ ስሙ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ መብራት ፡ ብርሃኑን ፡ የሚሰጥ ፡ በዘይት ፡ ስለኾነ ፡ ብርሃን ፡ ማሳየት ፡ ለደብረ ፡ ዘይት ፡ በተገባው ፡ ነበረና ፤ ብርሃን ፡ ባለማሳየቱ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ የዘይት ፡ ተራራ ፡ በመባሉ ፡ ደብረ ፡ ታቦርን ፡ አልኾነም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በበጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የሚገኘውን ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ የሚባለውን ፡ ገዳም ፡ የሚመለከት ፡ አይደለም ።

ይህንንም ፡ በአንጻር ፡ ሲያስረዱ ፡ ማኅተም ፡ የንጉሡን ፡ የቄሣርን ፡ መልክ ፡ ቢይዝ ፡ የሮም ፡ ንጉሥ ፡ ሊኾን ፡ እንደማይችል ፡ የላም ፡ ቅቤም ፡ የዓለምን ፡ ኹሉ ፡ ጠጕር ፡ ሲያከብር ፡ ላም ፡ በቅቤዋ እንደማትከብር ፡ ደብረ ፡ ዘይትም ፡ የዘይት ፡ ተራራ ፡ በመባሉ ፡ እንደ ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ ብርሃን ፡ ሊሰጥ አልቻለም ፡ ማለት ፡ ነው ።

ከመስ ፡ ኢይኀሥሥ ፡ ለጽምፁ ፡ ጠለ ፡ ተቀብዖ ፡ ዝናም ፡ በፈለገ ፡ ዘይት ፡ ክርስቶስ ፡ ቅውም ፡ ያለውም ፡ ንባብ ፡ ሲተረጐም ፡ ክርስቶስ ፡ ግን ፡ ለጥማቱ ፡ የመቀባት ፡ ዝናም ፡ ጠልን ፡ እንዳይሻ ፡ በዘይት ፡ ወንዝ ፡ የቆመ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ስለኾነ ፡ ቅብዐትን ፡ ክብርን ፡ ከሌላ ፡ እንዳይሻ ፡ ራሱ ፡ ቅብዕ ፡ ክብር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ ባይ ፡ መኾናቸውን ፡ ይገልጻሉ ። እውነተኛው ፡ የቅኔው ፡ ትርጓሜና ፡ ምሥጢር ፡ ይህ ፡ ነው ። እርስዎ ፡ የሰጡትንስ ፡ አስተያየት ፡ ስንኳንስ ፡ እንደርስዎ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ሊናገረው ፡ የሀገሬ ፡ መበለቶች ፡ አይናገሩትም ።

ደግሞ ፡ የቅኔውን ፡ አፈታትና ፡ ምሥጢር ፡ ከማበላሸትዎ ፡ በላይ ፡ ተራራ ፡ የሚያኽሉ ፡ ኹለት ፡ ሐሰቶች ፡ ተናግረዋል ። ፩ኛ ፡ በበጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የሚገኘው ፡ ደብረ ፡ ታቦር ፡ የቅባቶችን ፡ ትምህርት ፡ የሚገድፍ ፡ ነው ፡ ብለዋል ፡ ይህ ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ አንድ ፡ መረጃ ፡ ሊያቀርቡ ፡ አይችሉም ፡ ሐሰት ፡ እውነት ፡ ላይኾን ፡ አሰቱን ፡ እውነት ፡ አስመስላለሁ ፡ ብሎ ፡ የሰው ፡ ስም ፡ ማጥፋት ፡ አይገባም ።

## ድ ራ ሲ ።

፲፪/ ኹለተኛም ፡ እኒህ ፡ ወገን ፡ በሃይማኖታቸው ፡ ቅንነትና ፡ እውነተኛነት ፡ በጣም ፡ ከመረዳታቸው ፡ የተነሣ ፡ በአርኅ ፡ እመከባከል ፡ ሲሉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሰደቶችን ፡ በደስታ ፡ ተቀብለዋል ። ያሉት ፡ ነው ።



ይህ ሥዕል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ታቦር ብርሃን መለኮቱን እንደገለጸ ። ማቴ ፲፯ ፩—፱ ። ማር ፱ ፪ — ፲ ።

### መ ላ ሽ ፡፡

፲፪/ እኒህ ፡ ደፀን ፡ ቅኔ ፡ የተቀኙ ፡ ሊቅ ፡ አለቃ ፡ ተክሌ ፡ ኢያሱስ ፡ ይህን ፡ ቅኔ ፡ በመቀኘታቸው ፡ ስንኳ ፡ ስደት ፡ የቃል ፡ ተግሣጽም ፡ አልደረሰባቸውም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡፡

### ደ ራ ሲ ፡፡

፲፫/ ይህን ፡ ነገር ፡ የሚያስረዳ ፡ ቀጥሎ ፡ ያሉትን ፡ የደብተራ ፡ ካሣ ፡ ጕንደሬን ፡ መወድስ ፡ እናገኛለን ፡ ብለው ፡ የደራሲውን ፡ ስም ፡ አጠራር ፡ ክብር ፡ በሚቀንስ ፡ አነጋገር ፡ ተናግረዋል ፡፡

### መ ላ ሽ ፡፡

፲፬/ እኒህ ፡ በንቀት ፡ አነጋገር ፡ ደብተራ ፡ ካሣ ፡ ብለው ፡ የጠሯቸው ፡ ሊቅ ፡ የብሉይ ፡ የሐዲስ ፡ መምህር ፡ የታወቁ ፡ ታላቅ ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ሊቅ ፡ ናቸው ፡ ይህን ፡ ቅኔ ፡ ያገኙበት ፡ መጽሐፍም ፡ መምህር ፡ ካሣ ፡ ዘጐንደር ፡ ብሎ ፡ አክብሮ ፡ ይጠራቸዋል ፡ እንጂ ፡ ደብተራ ፡ ካሣ ፡ ብሎ ፡ አይጠራቸውም ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያለትን ፡ ሊቃውንት ፡ ደብተራ ፡ እገሌ ፡ እያሉ ፡ ቢጽፉ ፡ እርስዎ ፡ ራስዎ ፡ አለቃ ፡ የሚባል ፡ በምን ፡ ደረጃ ፡ ያለ ፡ ደብተራ ፡ የሚባል ፡ በምን ፡ ደረጃ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ መኾኑን ፡ የማያውቁ ፡ መኾንዎን ፡ ያስገምታሉ ፡ እንጂ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ በዚህ ፡ የሚዋረዱ ፡ አይደሉም ፡፡

### ቅ ኔ ው ፡፡

### ደ ራ ሲ ፡፡

፲፭/ ጥይቅት ፡ ጽእቲ ፡ ለዘይብሬዊ ፡ እምደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ዘወዕአት ፡ መርዓት ፡ ሃይማኖትነ ፡
ወሐራውያ ፡ ካልእ ፡ ከመ ፡ ኢይስብር ፡ ፍጡሩ ፡፡
ኪያሃ ፡ ዕንቈ ፡ ባሕርይ ፡ ማርቆስ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘአጥረየ ፡ ለነ ፡
መኃትዊሆን ፡ መጻሕፍት ፡ በቃለ ፡ ተፍሥሕት ፡ ነሥአ ፡ ጠባባት ፡ ከናፍሪነ ፡፡
ዓዲ ፡ ኢታንክርዋ ፡ ለዘትመጽእ ፡ ኀቤነ ፡፡
መከራ ፡ ዘሃይማኖት ፡ እስመ ፡ ፍዳ ፡ ዕሴት ፡ እኃዊነ ፡፡
ወቃለ ፡ ግብጻዊ ፡ ነቢይ ፡ ከመ ፡ ኢይስማዕ ፡ እዝንነ ፡
ስሙ ፡ እንዘ ፡ ብርሃን ፡ መንገለ ፡ ጽልመት ፡ ይመርሀነ ፡፡

### መ ላ ሽ ፡፡

፲፮/ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ለመጻፍ ፡ ያሳሰበዎ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ፩ ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ መኾኗን ፡ ከሊቃውንቶቿም ፡ መንበረ ፡ ማርቆስ ፡ የኾነች ፡ የእስክንድርያን ፡ ባህል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ ንቀፎ ፡ መንበረ ፡ ጴጥሮስ ፡ የተባለች ፡ የሮማን ፡ ባህል ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለትን ፡ የሚደግፍ ፡ እንዳለ ፡ ለማስረዳት ፡ ነው ፡፡

የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ግን ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዕ ፡ ፩ ፡ ልደት ፡ ፫ ፡ ልደት ፡ በመባባል ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይከራከሩ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ቢነገርም ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ ሲመጣ ፡ ኹሉም ፡ ባንድነት ፡ ከመንበረ ፡ ማርቆስ ፡ ሥር ፡ ተገኝተው ፡ ባንድነት ፡ ተሠልፈው ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ባለማፈግፈግ ፡ ሲመለከቱ ፡ ይገኛሉ ፡ እንጂ ፡ ከቶ ፡ የልዮንን ፡ ባህል ፡ ደግፎ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ አይገኝባቸውም ፡፡ ይኸውም ፡ ግብጽንና ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለማለያየት ፡ ይጠቅመኛል ፡ ብለው ፡ የጠቀሱት ፡ ቅኔ ፡ ኪያሃ ፡ ዕንቈባሕርይ ፡ ማርቆስ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘአጥረየ ፡ ለነ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ዕንቍ ፡ የጠራች ፡ የሃይማኖቱ ፡ ባህል ፡ ከመንበረ ፡ ማርቆስ ፡ የተገኘች ፡ መኾኗን ፡ በመግለጹ ፡ ይታወቃል ፡፡

በፍቅርም ፡ ቢኾን ፡ በጥል ፡ ኹለት ፡ መንድማሞቾች ፡ የግል ፡ ጉዳያቸው ፡ ለሚያደርጉት ፡ ንግግር ፡ መካከል ፡ የኹለቱም ፡ ባላጋራ ፡ የኾነ ፡ ፫ኛ ፡ ሰው ፡ ገብቶ ፡ ሲያሳብቅ ፡ ቢገኝ ፡ ኹለቱም ፡ ወገኖች ፡ በስብቅ ፡ እንርሱን ፡ አለያይቶ ፡ ከመካከላቸው ፡ ገብቶ ፡ ሊጎዳቸው ፡ ታጥቆ ፡ የተነሣ ፡ ጠላት ፡ መኾኑን ፡ በመቀው ፡ ውሻ ፡ ውሻ ፡ ብለው ፡ አሳፍረው ፡ ይመልሱታል ፡ እንጂ ፡ ነገሩን ፡ እውነት ፡ ብለው ፡ አይቀበሉትም ፡፡

ስለዚህ ፡ እርስዎም ፡ ለዚህ ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ምን ፡ የሚያገባዎ ፡ የሌለ ፡ ፫ኛ ፡ ትርፍ ፡ ሰው ፡ ስለኾኑት ፡ ይህ ፡ አሳብዎ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ትርፍ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ብለን ፡ አልፈነዋል ፡፡

## ደ ራ ሲ ።

፲፩/ ኢያጥፍዐ ፡ ንጹሐ ፡ ሥጋ ፡ የሚለውን ፡ የ፩ ፡ ዐይን ፡ ጕሹን ፡ ቅኔ ፡ ጽፌዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፩/ ይህ ፡ ቅኔ ፡ የተደረሰበትን ፡ ምክንያትና ፡ የተሰጠውን፡መልስ፡እንደ፡ድርና፡ እንደ፡ ማግ ፡ አስማምቼ ፡ በቅኔዎች ፡ በመጀመሪያ ፡ ላይ ፡ በገጽ ፡ ፫፻፫ና፡ ፫፻፬ ፡ ጽፌልዎታለሁ ፡ ያንን፡ይመልከቱ ኹለተኛ ፡ መጻፍ ፡ አያስፈልግም ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፭/ የክርስቶስ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ተለወጠ ፡ ወይም ፡ ጠፋ ፡ የሚለውን ፡ የአውጣኪን ፡ ባህል ፡ የኹለት ፡ ልደትና ፡ የቅብዐት ፡ ወገን ፡ ይቀበሉታል ፡ ሲል ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወገን ፡ የኾነው ፡ አለቃ ፡ ተክለ ፡ ጽዮን ፡ ይከሳቸዋል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፭/ አለቃ ፡ ተክለ ፡ ጽዮን ፡ በአባ ፡ ማስያስ ፡ ፍቅር ፡ ተስበው ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ መኾ ናቸው ፡ የታወቀ ፡ ነው ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ተክለልዮን ፡ የሚባል ፡ ስም ፡ ወጥቶላቸዋል ፡ ስለ ዚህ ፡ ካቶሊካዊ ፡ ይባላሉ፡እንጂ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወገን ፡ ከመባል ፡ ተሠርዘዋል ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ተለወጠ ፡ ጠፋ ፡ ይላሉ ፡ እያለ ፡ ይከሣቸዋል ፡ ለሚሉትም ፡ አለቃ ፡ ተክለ ፡ ጽዮን ፡ ለካቶሊክ ፡ ባህል ሐዲስ ፡ አማኒ ፡ በመኾናቸው ፡ እታመናለሁ ፡ ሲሉ ፡ የተናገሩት ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ባህል ፡ የሚቀበል ፡ በኢትዮጵያ ፡ የለም ። የዚህንም ፡ መረጃ ፡ ኢይጌይሱን ፡ ምንተ ፡ እለ ፡ ተሴሰዩ፡ የሚለውን ፡ ቅኔ ፡ በጸፋበት ፡ በገጽ ፡ ፫፻፮ ፡ አብራርቼ ፡ ጽፌልዎታለሁ ፡ ያንን ፡ ይመልከቱ ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፪/ ይህም ፡ እውነት ፡ እንደሆነ ፡ ቀጥሎ ፡ ባለው ፡ አቤቶ ፡ ተክለ፡ሃይማኖት ፡ ጎጃሜ ፡ በደረሰው ፡ ሥላሴ ፡ ይታወቃል ፡ ብለዋል ።

፲፪/ አቤቶ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጎጃሜ ፡ አለመኾናቸው፡ ጕንደሬ ፡ መኾናቸው ፡ በኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ጎልቶ ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ ነው ። ይህ ፡ ነገር ፡ በተመልካች ፡ ዘንድ ፡ ዘራቸው ፡ ሀገራቸው ፡ በግልጽ ፡ የሚታወቀውን ፡ የኢትዮጵያውያንን ፡ ብሔረ ፡ ሙላድ ፡ ሐረገ ፡ ትውልድ ፡ እንዲህ ፡ የለዋወጡት ፡ ዘልቀው ፡ ከተማሩ ፡ አጥብቀው ፡ ከተመራመሩ ፡ ሊቃውንት ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ በግልጽ ፡ ሊረዳው ፡ የማይችለውን ፡ የመጻሕፍትን ፡ ምሥጢርማ ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ለዋውጠዋቸው ፡ ይኾን ፡ የሚል ፡ አሳብ ፡ አሳድሯል ።

## ቅኔው ፡ የሚከተለው ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፫/ ክራማተ ፡ ፰ ፡ ሐሰወ ፡ ኖኅ ፡ ነቢየ ፡ ጊዜ ፡ ወትትገፈታዕ ፡ በነድ ፡ ማዕደ ፡ መወልጥ ፡ነነዌ ።
ጽድቀ ፡ ብሂሎቱ ፡ ለዮናስ ፡ ሕሳዌ ።
ከመ ፡ ትኩኑ ፡ እምላከ ፡ ባሕቱ ፡ ሀለወከሙ ፡ ሀላዌ ።
ዘይቤ ፡ ዕቤረ ፡ ወአረጋዌ ።
እስመ፡ኮነ ፡ ሥጋ ፡ እምላከ ፡ ማኅየዌ ።
ኢሐሰወ ፡ ነቢይ ፡ አርዌ ፡ የሚል ፡ ነው ።

ይህንንም ፡ ቅኔ ፡ ሲተረጕሙ ፡ ጠቅለል ፡ ባለ ፡ አነጋገር ፡ ደራሲው ፡ ኹለት ፡ ነገሮችን ፡ ያስታው ሳል ፡ አንዱ ፡ በቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ የናስ ፡ ነነዌ ፡ ከ፵ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ትጠፋ ለች ፡ ብሎ ፡ የተናገረውና ፡ ሳይፈጸም ፡ የቀረው ፡ ትንቢት ፡ ነው ። ሌላውም ፡ በመጽሐፈ ፡ አዋልድ ፡ የሚገኘው ፡ ኖኅ ፡ ማየ ፡ አይኅ ፡ ከ፷፰፡ዓመት፡ በኋላ ፡ ይመጣል ፡ ብሎ ፡ በትንቢት ፡ ተናግሮ ፡ ሲያ በቃ ፡ የጥፋቱ ፡ ወኀ ፡ ከ፻፡ዓመት፡ በኋላ ፡ መጣ ፡ የሚለው ፡ ተረት ፡ ነው ። ደራሲው ፡ እነዚህን ፡ ነገ ሮች ፡ ካስታወሰ ፡ በኋላ ፡ እነዚህ ፡ እውነተኞች ፡ ነቢያት ፡ ሲሳሳቱ ፡ ሳይጣን ፡ ውሸታም ፡ ሳለ ፡ ለአ ዳምና ፡ ለሔዋን ፡ በእባብ ፡ አድሮ ፡ እንደ ፡ አማልክት ፡ ትኾናላችሁ ፡ ሲል ፡ የተናገራቸው ፡ በሥጋዌ ፡ የሰው ፡ ባሕርይ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ኾኗልና ፡ አልተሳሳተም ፡ ሲል ፡ ነገሩን ፡ ያቆማል ፡ ብለዋል ።



ይህ ሥዕል ሄሮድስ በዓል በሚያደርግበት ቀን የዮሐንስን ራስ ቈርጦ ለወለተ ሄሮድያዳ በጻሕል እንደ ሰጣት ያሳያል ። ማቴ ፲፬ ፩—፲፪ ። ማር ፮ ፲፬ — ፴

## መ ላ ሽ ።

፲፰ ከዮናስ ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ያለውን ፡ እስከ ፡ ፺ ፡ ቀን ፡ በማለት ። ፪ኛ ፡ ሐዋርያት ፡ የተቀበሉትን ፡ የጌናክን ፡ ትንቢት ፡ ተረት ፡ በማለት ፡ ፫ኛ ፡ እስመ ፡ ኮነ ፡ ሥጋ ፡ ያለውን ፡ ንባብ ፡ ሥጋ ፡ ማለት ፡ አካል ፡ ዘየአክልን ፡ የሚያሳይ ፡ አነጋገር ፡ ሲኾን ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ከመሳሳትም ፡ በቀር ፡ የቅኔው ፡ መንገድ ፡ ግቡን ፡ አልለቀቀም ፡ ይኸው ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ ከዚህ ፡ ቅኔ ፡ ውስጥ ፡ ሊነቅፉት ፡ የሚያስቡት ፡ ሥጋ ፡ ማኅየዊ ፡ አምላክ ፡ ኾነ ፡ ማለትን ፡ ነው ፡ እኒህ ፡ ሊቅ ፡ ይህንን ፡ ቃል ፡ የተናገሩ ፡ አዳም ፡ ዕፀ ፡ በለስን ፡ በበላ ፡ ጊዜ ፡ አዳም ፡ ኮነ ፡ ከመ ፡ ፩ ፡ እምኔነ ።

አዳም ፡ ከእኛ ፡ እንደ ፡ አንዳችን ፡ ኾነ ፡ ያሉትን ፡ ቃል ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከልባቸው ፡ አንቅተው ፡ አልተናገሩም ፡ ዘፍ ። ፫ ፡ ፳፪ ።

ይህ ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ መሠረት ፡ የያዘ ፡ ከኾነ ፡ ያንን ፡ መሠረቱን ፡ በኦሪት ፡ የተጻፈውን ፡ ካልነቀፉ ፡ በቀር ፡ ይህንን ፡ ቃል ፡ ሊነቅፉ ፡ አይችሉም ።

## ድ ራ ሲ ።

፲፱/ የደብረ ፡ ሊባኖሱ ፡ መነኩሴ ፡ አለቃ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ ዓፄ ፡ ዮሐንስ ፡ በሸዋ ፡ ላይ ፡ የቅባቶች ፡ ባህል ፡ በዐዋጅ ፡ እንዲነገር ፡ ባስገደዱ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቅባቶች ፡ ወገን ፡ ያለፈ ፡ የቅባቶችን ፡ ወገን ፡ እንደሚከተለው ፡ አድርጎ ፡ ይገድፈዋል ፡ ብለው ፡ ዋዜማ ፡ ቅኔ ፡ ጽፈዋል ። ቅኔውም ፡ ኢነግእከ ፡ እምካልእከ ፡ ለአብርሆ ፡ ገጽ ፡ ቅብዐ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ነግድ ።
እስመ ፡ ቅብዕ ፡ ለሊሁ ፡ መሬትከ ፡ ወልድ ።
ቅብዐ ፡ ካልእስ ፡ ይንሥኡ ፡ አራዛተ ፡ ሰርጉ ፡ ነገድ ።
ኀበ ፡ ኀበ ፡ አንጸረ ፡ ቅድመ ፡ ልሳንከ ፡ ነድ ።
የሐውሩ ፡ በሠናይ ፡ ልማድ ፡ ነው ።

## መ ላ ሽ ።

፲፱/ ከዚህ ፡ ላይ ፡ የተናገሩት ፡ ኹሉ ፡ በፍጹም ፡ ውሸት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ አንድ ፡ እውነት ፡ የለበትም ፡ ፩ኛ ፡ ዓፄ ፡ ዮሐንስ ፡ በሸዋ ፡ የቅባቶችን ፡ ባህል ፡ ባዋጅ ፡ አላናገሩም ።
፪ኛ ፡ አለቃ ፡ ገብረ ፡ ኢየሱስ ፡ ከመሠረታቸው ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ ባይናቸው ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ቅባቶች ፡ ባህል ፡ ባዋጅ ፡ ያለፉ ፡ አይደሉም ፡ ይኸውም ፡ እስመ ፡ ቅብዕ ፡ ለሊሁ ፡ መሬትከ ፡ ወልድ ፡ በማለታቸው ፡ ይታወቃል ።

ይህን ፡ ያህል ፡ ውሸት ፡ ከመናገር ፡ ያደረሰዎ ፡ አስቀድመው ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ በማለትና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዕ ፡ በማለት ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ባለማወቅዎና ፡ ወልድ ፡ ቅብዕ ፡ የሚሉ ፡ እነማን ፡ እንደኾኑ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅብዕ ፡ የሚሉ ፡ እነማን ፡ እንደኾኑ ፡ የቅባቶችን ፡ ባህል ፡ ምን ፡ እንደኾነ ፡ የተዋሕዶችም ፡ ባህል ፡ ምን ፡ እንደኾነ ፡ ሳያውቁ ፡ በድፍረት ፡ ልጻፍ ፡ ማለትዎ ፡ ነውና ፡ አስቀድመው ፡ ይህንን ፡ የዘረዘርኩልዎን ፡ ጠንቅቀው ፡ አውቀው ፡ ሲጽፉ ፡ መልሱን ፡ አጽፍልዎታለሁ ፡ ይህ ፡ ንግግር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ቅዠት ፡ ያለ ፡ ስለሆነ ፡ ለዚህ ፡ መልስ ፡ ልስጥ ፡ ማለት ፡ ተኝቶ ፡ በዕንቅልፍ ፡ ልቡ ፡ ለሚቃዥ ፡ ሰው ፡ ሕጋዊ ፡ መልስ ፡ ልስጠው ፡ እንደማለት ፡ የሚቈጠር ፡ ነው ።

## ድ ራ ሲ ።

፳/ መምህር ፡ ዜና ፡ የተባሉትን ፡ የመርጡለ ፡ ማርያምን ፡ መምህር ፡ ቅኔ ፡ ንባቡን ፡ በመለዋወጥ ፡ ጽፈውታል ፡ ቅኔውም ፡ የሚከተለው ፡ ነው ።
ናስተሐምም ፡ ንስተይ ፡ ማየ ፡ ፈለግኪ ፡ ወኢናስተሐምም ፡ ንስተይ ፡
ዘበዓለ ፡ መርቅያን ፡ ወይነ ።

በፈለግኪ ፡ ዮሐንስ ፡ እስመ ፡ አጥመቀ ፡ ብርሃነ ፡
ወከመ ፡ ለዮሐንስ ፡ ተበቀሎ ፡ ሄሮድስ ፡ በወይነ ፡ በዓሉ ፡ አኮኑ ፡ ሰማዕነ ።
ወእመ ፡ ንስጥርስ ፡ ይሁብነ ፡ ወርቀ ፡ ኬልቄዶን ፡ ጽሩየ ፡ ወብሩረ ፡ ሮሜ ፡ ፍቱነ ።
ለንስጥሮስ ፡ ኢንሁብ ፡ ዘምሥያጥኪ ፡ አእባነ ።
መርጡለ ፡ ማርያም ፡ ደብረ ፡ ተሰምዮ ፡ ምስካየ ፡ ወጸወነ ።
በነግሊአ ፡ ሠላስ ፡ አእባን ፡ እስመ ፡ ነፍሰ ፡ ዳዊት ፡ ድኅነ ።
ወነፍሰ ፡ ይሁዳ ፡ አስቆሮታዊ ፡ በነግሊአ ፡ ብሩር ፡ ተኰነነ ። ነው ።

እርስዎ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ቅኔ ፡ ሲጽፉ ፡ ወርቀ ፡ ኬልቄዶን ፡ ያለውን ፡ ወርቀ ፡ ሰማርያ ፡ ወይም ፡ ሀገ ደኬ ፡ ብለው ፡ ለውጠው ፡ ጽፈውታል ። ባለቅኔው ፡ ወርቀ ፡ ኬልቄዶን ፡ አሉ ፡ እንጂ ፡ ወርቀ ፡ ሠማ ርያ ፡ አላሉም ።

ሠማርያ ፡ ሲልም ፡ ለንስጥሮስ ፡ የመወለጃው ፡ አገር ፡ የመሰለው ፡ ይመስላል ፡ ብለው ፡ ምኞት ዎን ፡ ተናገረዋል ። እንጂ ፡ የባለቅኔው ፡ ሐሳብ ፡ አይደለም ።

ደራሲውስ ፡ ጠንቅቀው ፡ የኬልቄዶንን ፡ ወርቅ ፡ የሮማን ፡ ብር ፡ ቢሰጡን ፡ ማለት ፡ በኬል ቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በተወሰነው ፡ በሮማ ፡ ጳንቶ ፡ በሚኖረው ፡ በኹለት፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ አንድ ፡ ባሕ ርይ ፡ የሚል ፡ ባህላችንን ፡ እንለውጥም ፡ ብለው ፡ ተናግረዋል ።

ቀጥለውም ፡ የንስጥሮስንና ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስን ፡ የካቶሊክንም ፡ ባህል፡አንድ፡ላይ ፡ ጨምሮ ፡ በወይን ፡ ጠጅ ፡ በወርቅና ፡ በብር ፡ መስለ ፡ የሚሉት ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ። ባለቅኔው ፡ ጠንቅ ቀው ፡ ባህሉን ፡ ያነቁትንና ፡ የተቀበሉትን ፡ ሰዎች ፡ ንስጥሮስ ፤ መርቅያን ፡ ብለው ፤ ባህሉ ፡ የተወ ሰነባቸውንና ፡ የጸናባቸውንም ፡ ሀገሮች፡ ኬልቄዶን ፤ ሮሜ ፡ ብለው ፡ ስማቸውን ፡ ጠርተው ፡ ተናግረ ዋል ። ደብረ ፡ ሊባኖስን ፡ ያነሡበት ፤ ቦታ ፡ የለም ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስን ፡ ከንስጥሮስና ፡ ከካቶሊክ ፡ ጋራ ፡ አጣምረው ፡ የሚያነሡበት ፡ ምክንያቱ ፡ ምንድን ፡ ነው ። ይህ ፡ አሠራርዎ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ተለመደው ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ለማለያየት ፡ የሚገቡበት ፡ ዘዴ ፡ ለማግኘት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የኾነ ፡ የስብቅ ፡ መንገድ ፡ የሚጠርጉ ፡ መኾንዎን ፡ ከሚገልጽ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ እውነት ፡ የሌለበት ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፩/ ከዚሀ ፡ ቅኔ ፡ ይሀ ፡ ወገን ፡ የሚያስተምረው ፡ የአንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ምሥጢሩ ፡ ምን ፡ እንደኾነ ፡ በቀጥታ ፡ ለመረዳት ፡ የሚረዱ ፡ በቂዎች ፡ ማስረጃዎች ፡ እንደማይገኙ ፡ ግልጽ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የጎጃሙ ፡ ደራሲ ፡ የካቶሊክን ፡ ትምህርትና ፡ የንስጥሮስን ፡ ኑፋቄ ፡ ቀላቅሎ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ በማለቱ ፡ ባሕርይ ፡ ለሚለው ፡ ቃል ፡ የሚሰጠው ፡ ትርጉም ፡ በኬልቄዶኑ ፡ ጉባኤ ፡ ከተወ ሰነው ፡ ልዩ ፡ መኾኑን ፡ እንዲሁም ፡ ባሕርይና ፡ አካል ፡ የሚሉትን ፡ ቃሎች ፡ እንደሚያወራርሳ ቸው ፡ ያስረዳል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፩/ እኒህ ፡ ባለቅኔ ፡ ከዝርዝር ፡ ነገር ፡ ሳይገቡ ፡ ድፍን ፡ ባለ ፡ አነጋገር ፡ የሐንስ ፡ በወንዝ፡ ወኃ ፡ ብርሃን ፡ ክርስቶስን ፡ እንዳጠመቀ ፤ እናውቃለንና ፡ የወንዛችንን ፡ ወኃ ፡ እንጠጣለን ፡ እንጂ ፡ ሄሮ ድስ ፡ በዓል ፡ ባደረገበት ፡ ቀን ፡ ወይን ፡ ጠጥቶ ፡ የሐንስን ፡ እንደ ፡ ተበቀለው ፡ ስለሰማን ፡ የመርቅ ያንን ፡ ወይን ፡ አንጠጣም ።

እንደዚኹሉም ፤ ዳዊት ፡ ሦስት ፡ ደንጋዮች ፡ አንሥቶ ፡ ከጎልያድ ፡ እንደ ፡ ዳነ ፤ የአስቆሮቱ ፡ ይሁዳም ፡ ብር ፡ ተቀብሎ ፡ እንደ ፡ ተጎዳ ፡ እናውቃለንና ፡ ንስጥሮስ ፡ የኬልቄዶንን ፡ ወርቅና ፡ የሮ ምን ፡ ብር ፡ ቢሰጠን ፡ የገበያችንን ፡ ደንጋይ ፡ እንሰጠውም ፡ ብለዋል ፡ እንጂ ፡ ከዝርዝሩ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ ባሕርይን ፡ አካልን ፡ አላነሱም ።

እርስዎም ፡ ይህንኑ ፡ ተረድተውት ፡ በዚህ ፡ ቅኔ ፡ የአንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ ምሥጢሩ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በቀጥታ ፡ ለመረዳት ፡ የሚረዱ ፡ መረጃዎች ፡ አይገኙበትም ፡ ብለዋል ። ይህንን ፡ በእር ግጥ ፡ ከተረዱት ፡ በኋላ ፡ ባሕርይ ፡ ለሚለው ፡ ቃል ፡ የሚሰጠው ፡ ትርጉም ፡ በኬልቄዶኑ ፡ ጉባኤ ፡ ከተወሰነው ፡ ልዩ ፤ መኾኑን ፡ ያስረዳል ፡ እንዲሁም ፡ ባሕርይና ፡ አካል ፡ የሚሉትን ፡ ቃሎች ፡ እን ደሚያወራርሳቸው ፡ ያስረዳል ፡ ብለው፡ የግል ፡ ሐሳቡዎን ፡ ተናግረዋል ።

ቅኔዎችን ፡ ጽፈው ፡ በመጨረሻ ፡ ላይ ፡ የሚሰጡት ፡ መረጃ ፡ ከቅኔዎች ፡ ያልተያያዘ ፡ የግል ፡ ሐሳብዎን ፡ ከኾነ ፡ የሊቃውንቱን ፡ ቅኔ ፡ ለምን ፡ ይጠቅሱታል ፡ ለማስመሰል ፡ ለማጭበርበር ፡ ነውን?።

## ደ ራ ሲ ።

፳፪/ ከዚህም ፡ ቀጥለው ፡ የአለቃ ፡ ሣህለ ፡ ሚካኤልን ፡ መወድስ ፡ ጽፈዋል ፤ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ነገረ ፡ ጸብእሙ ፡ ለዘተዋሕዶ ፡ ወጸጋ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እምሃይማኖቱ ።

በእንተ ፡ እሉ ፡ ግብራት ፡ እስመ ፡ ተብህለ ፡ እምጥንቱ ።

ይቁም ፡ ኵሉ ፡ ለነገር ። ማኅለቅቱ ።

በስምዐ ፡ ክልኤቱ ፡ ወበ፫ቱ ፤ ወበእንተዝ ፡ ነገር ፡ ኢይደልዎሙ ፡ ይትሐተቱ ።

ሥርዓትሂ ፡ እመ ፡ ተጽሕፈ ፡ ወእመ ፡ ከመዝ ፡ ሥርዓቱ ።

ኢንሑር ፡ በትምይንት ፡ ፍናወ ፡ ግብራት ፡ ጾታ ፡ ሠለስቱ ።

ውፁአን ፡ እምጽድቅ ፡ እምጣነ ፡ ልደታት ፡ ክልኤቱ ።

ለእልፍ፡ ሕዝበ ፡ ጸጋ ፡ ይሰድድዎሙ ፡ እስከ ፡ ታሕቱ ።

## መ ላ ሽ ።

፳፪/ ይህ ፡ ቅኔ ፡ ፱ ፡ ልደት ፡ በሚሉና ፡ ፫ ፡ ልደት ፡ በሚሉ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ባህል ፡ የሚመለከት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባንድ ፡ ባሕርይና ፡ በኹለት ፡ ባሕርይ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ባህል ፡ የሚመለከት ፡ አይደለምና ፡ ርስዎን ፡ የሚያገባዎ ፡ አይደለም ፡ ስለዚህ ፡ የዚህ ፡ ጠቅላላ ፡ መልሱ ፡ በ፲፩ኛው ፡ ቍጥር ፡ የተጻፈው ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፫/ የቅብዐቱን ፡ ክርክር ፡ በወገኑ ፡ ትተው ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ መዋሐድ ፡ እምነት ፡ ብቻ ፡ የሚናገሩ ፡ ሊቃውንት ፡ አይታጡም ። እነዚሁም ፡ ኹላቸው ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ መገኘታቸውን ፡ እንደማያከራክር ፡ እውነት ፡ አድርገው ፡ ያስቡታል ፡ ለካቶሊክም ፡ ትምህርት ፡ የሚቃወሙት ፡ እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ እንዳይኾን ፡ ስለሚያሰጋቸው ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፫/ የቅብዐቱን ፡ ክርክር ፡ ትተው ፡ ስለ ፡ ባሕርየ ፡ መለኮትና ፡ ስለ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ተዋሕዶ ፡ የሚናገሩ ፡ ሊቃውንት ፡ መኖራቸው ፡ እርግጥ ፡ ነው ፡ እነርሱም ፡ ኹለቱ ፡ ባሕርያት ፡ በተዋሕዶ ፡ ምንታዌ ፡ ጠፍቶ ፡ አንድ ፡ እንደኾኑ ፡ ይናገራሉ ፡ እንጂ ፡ በምንታዌ ፡ ጸንተው ፡ እንደሚኖሩ ፡ አይናገሩም ፤ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ ኹለቱ ፡ ባሕርያት ፡ በኹለትነት ፡ መገኘታቸውን ፡ እንደማያከራክር ፡ እውነት ፡ አድርገው ፡ አያስቡትም ።

የካቶሊክንም ፡ ባህል ፡ የሚቃወሙት ፡ እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ ኾኖ ፡ ቢያገኙት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ገና ፡ ይኾንብናል ፡ ብለው ፡ ሰግተው ፡ አይደለም ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፬/ ለዚህ ፡ መረጃ ፡ ሊኾንዎ ፡ የሚከተለውን ፡ ቅኔ ፡ ጽፈዋል ።
ለማየ ፡ ሕይወት ፡ ቃለ ፡ አብ ፡ በማኅየበ ፡ ሙሴ ፡ ትንቢት ፡ እመ ፡ ቀድሐቶ ፡ ድንግል ።
ኢሐጸ ፡ እምነ ፡ ምልእቱ ፡ መለኮት ፡ ማዕበል ።
እመ ፡ ተኀየለሰ ፡ ይጽብት ፡ ዕመቀ ፡ ምሥጢሩ ፡ ለቃል ።
ንስጥሮስ ፡ ወድቀ ፡ በፍኖተ ፡ ኀጕል ።
አምጣኒሁ ፡ አኮኑ ፡ ኢይክል ።

ይህንንም ፡ ሊተረጕሙ ፡ ሲሞክሩ ፡ ወርቅ ፡ የሚኾነው ፡ ከቅድስት ፡ ንጽሕት ፡ ድንግል ፡ ማርያም ፡ ማኅፀን ፡ ሥጋ ፡ የለበሰው ፡ ቃል ፡ በተለይም ፡ ባሕርየ ፡ መለኮቱ ፡ ነው ። ሰም ፡ የሚኾነውም ፡ የሚቀዳው ፡ ወኀ ፡ ነው ። ደራሲው ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ ሲያፈርስ ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለቱ ፡ ባሕርያት ፡ ሳይቀላቀሉ ፡ ሳይለወጡና ፡ ሳይደባለቁ ፡ መገኘታቸውን ፡ በኹለቱ ፡ ፊተኞች ፡ ቤቶች ፡ ያስረዳል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፬/ የዚህ ፡ ቅኔ ፡ ትርጓሜውና ፡ ምሥጢሩ ፡ የሕይወት ፡ ወኀ ፡ ቃለ ፡ አብን ፡ ድንግል ፡ በሙሴ ፡ ማድጋ ፤ ትንቢት ፡ ብትቀዳው ፡ መለኮት ፡ ማዕበል ፡ ከምላቱ ፡ አልጎደለም ፡ ማለት ፡ ምሉእ ፡ ስፉሕ ፡ የኾነ ፡ ምስት ፡ ከዊን ፡ ያለው ፡ መለኮት ፡ በቃልነቱ ፡ ከዊን ፡ ከእመቤታችን ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ ሥጋ ፡ ቢለብስ ፡ በልብነቱ ፡ በእስትንፋስነቱ ፡ ከዊን ፡ ሰው ፡ አልኾነም ፡ ሥጋ ፡ አለበሰም ፡ ከምልአቱ ፡ ከስፍሐቱ ፡ አልተወሰነም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኹለቱ ፡ ባሕርያት ፡ በምንታዌ ፡ ይኖራሉ ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ይኸውም ፡ በሚከተሉት ፡ በ፫ቱ ፡ ቤቶች ፡ ንስጥሮስ ፡ የማይቻለውን ፡ ምሥጢረ ፡ ተዋሕዶውን ፡ እመረምራለሁ ፡ ብሎ ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ቢል ፡ በጥፋት ፡ ጕዳና ፡ ወደቀ ፡ በማለቱ ፡ ይታወቃል ።

የቅኔው ፡ ትርጓሜውና ፡ ምሥጢሩ ፡ ይህ ፡ ሲኾን ፡ ኹለቱ ፡ ባሕርያት ፡ በምንታዌ ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ፡ ያለ ፡ አስመስለው ፡ የሚናገሩት ፡ ንግግር ፡ ከርስዎ ፡ አንጎል ፡ የመነጨ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባለ ቅኔው ፡ ስንኳን ፡ ሊናገረው ፡ አላሰበውም ። ይህንንም ፡ የቅኔን ፡ ጠባይ ፡ አጣርተው ፡ አንጠርጥረው ፡ አበጥረው ፡ የሚያውቁ ፡ ሊቃውንት ፡ ይመስክሩ ።

## መ ላ ሽ ።

፳፯/ የዚህ ፡ ቅኔ ፡ ትርጓሜውና ፡ ምሥጢሩ ፡ ባጭሩ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ፡ መላእክት፡ ዙሪ ያውን ፡ ከበውት ፡ የሚቆሙ ፡ አማኑኤል ፡ ከዕንበረም ፡ ቤት ፡ ሙሴን ፤ ከሐዶ ፡ ቤት ፡ ዘካርያስን ፡ አሥነሥቶ፡ የሥጋዌውን ፡ የተዋሕዶውን ፡ ነገር ፡ በሐመልማልና ፡ በነበልባል ፤ በመቅረዝ ፡ ላይ ፡ ባለ ፡ ፈትልና ፡ ነበልባል ፡ መስሎ ፡ ካመለከተን ፡ ዘንድ ፡ ከዊን ፡ ተዋሕዶ ፡ ሳይኖር ፡ ያለከዊን ፡ ያለ ተዋሕዶ ፡ ቀምቶ ፡ እግዚአብሔር ፡ የኾነ ፡ አይደለምና ፡ በአብ ፡ ልዕልና ፡ እሳት ፤ ኃጢአት ፡ እሾ ኽን ፡ አቃጠለው ። ተጥርዶንም ፡ ሳይንቅ ፡ ሳያቃልል ፡ በእኖት ፡ ትሕትና ፡ ተዋረደ ፡ ማለት ። በጠ ቅላላው ፡ ክርስቶስ ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኾኖ ፡ የአምላክነትንም ፡ የሰው ነትንም፡ሥራ ፡ ሠራ ፡ ማለት ፡ ነው ። በሚከተሉትም ፡ ኹለት ፡ ቤቶች ፡ ምንም ፡ ኹለቱም ፡ የሚያዛ ምድ፡አንድ ፡ ልጅን ፡ ቢወልዱ ፡ እመቤታችን ፡ አብ ፡ በወለደበት ፡ በመለኮቱ ፡ አልወለደችውም ፡ አብም ፡ እመቤታችን ፡ በወለደችበት ፡ በሥጋ ፡ አልወለደውም ፡ ብለው ፡ ወላጆቹ ፡ አብና ፡ እመ ቤታችን ፡ ኹለት ፡ ሲኾኑ ፡ ተወላጁ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ መኾኑን ፡ አስረድተዋል ፡ እንጂ ፡ በክርስ ቶስ ፡ ምንታዌ ፡ ያለበት ፡ መኾኑን ፡ አላመለከቱም ።

እኒህ ፡ ባለቅኔ ፡ ካቶሊካውያን ፡ እንደሚሉት ፡ ክርስቶስን ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የሚሉትስ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ክልኤቱን ፡ ለአብና ፡ ለእመቤታችን ፡ እንደቀጠሉት ፤ ለክርስቶስም፡ በቀ ጠሉለት ፡ ነበረ ፡ ስለዚህ ፡ የባለቅኔዎቹን ፡ ድርስ ፡ ዕውቀት ፡ ጥልቅ ፡ ሐሳብ ፡ ሳይደርሱበት ፡ እንዲ ያው ፡ በከንቱ ፡ ያንንም ፡ ያንንም ፡ ይጨብጣሉ ፡ እንጂ ፡ ሐሳብምን ፡ የሚደግፍ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የሚል ፡ ቅኔ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ዘንድ ፡ አይገኝም ።

## ዶ ራ ቢ ።

፳፰/ ቄስ ፡ ዘሩፋኤል ፡ የተባሉትን ፡ ሊቅ ፡ ቅኔ ፡ ጽፈዋል ፡ ቅኔውም ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሰብእ ፡ እግዚአብሔር ።

ዘላዕለ ፡ መቃብር ፡ እንተ ፡ ወውስተ ፡ መቃብር ፡ ሕትጽ ።
ከመ ፡ ኪያከ ፡ አግመረ ፡ ወከመ ፡ኢያግመረከ ፡ ዕፀ ።
በአፍአ ፡ ብሔሮሙ ፡ ሰቀሉከ ፤ ወኢሰቀሉከ ፡ በካልእ ፡ አንቀጽ ።
መግብተ ፡ እንታክቲ ፡ አድልዎ ፡ ገጽ ፡ ምሳሌ ፡ ዝኒ ፡ ንጠይቅ ።
ዘኢሀለዎ ፡ ግብረ ፡ ሕጸጽ ፡

መሰሎሙ ፡ ዘቀተልዎ ፡ እመ ፡ ቀዳሚ ፡ ተግሣጽ ፡
እንዘ ፡ በቅድሜሆሙ ፡ ኤርምያስ ፡ ማኅለቅተ ፡ ነገር ፡ ያስተሐይጽ ፡
ዮሴፍኒ ፡ ዘጸረ ፡ ግፍዓ ፡ መሪራን ፡ አብያጽ ፡
ምውት ፡ በከነዓን ፡ ወሕያው ፡ በምድረ ፡ ግብጽ ። የሚል ፡ ነው ፤

## መ ላ ሽ ።

፳፰/ እንግዲህ ፡ የሚናገሩትን ፡ ያስተውሉት ፡ ጠቅላላ ፡ ሐሳብዎ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት፡ በቅኔያቸው ፡ ክርስቶስን ፡ ኸለት ፡ ባሕርይ ፡ ይሉታል ፡ ለማለት ፡ ነው ።

ይህ ፡ ባለቅኔ ፡ ጠንቅቆ ፡ ዮሴፍ ፡ በከነዓን ፡ ሞተ ፡ ሲባል ፡ በግብጽ ፡ ሕያው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፤ ኤርምያስም ፡ በመካከላቸው ፡ ቆሞ ፡ የነገሩን ፡ ፍጻሜ ፡ ሲመለከት ፡ ለጠላቶቹ ፡ ገደልነው ፡ እንደ ፡ መሰላቸው ፡ ከመቃብር ፡ በአፍኣና ፡ ከመቃብር ፡ ውስጥ ፡ ያለህ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሥጋ ፡ ብትሞት ፡ በመለኮት ፡ ሕያው ፡ ነህ ፡ ብሏል ።

እርስዎም ፡ ደራሲው ፡ ሊያስረዳው ፡ የፈለገ ፡ አንዱ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚታመምና ፡ የማይታመም ፡ ኾነ ፡ ማለትን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መስክረዋል ። አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ ሞተ ፡ በመለኮት ፡ ሕያው ፡ ነው ፡ ማለት ፡ አባቶቻችን ፡ ሐዋርያት ፡ ፫፻፲፰ ፡ ያስተማሩን ፡ እውነተኛ ፡ ትምህርታችን ፡ ነው ። የሚ ያጣላን ፡ ላንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ክልኤቱ ፡ የሚል ፡ ቅጽል ፡ ሰጥተው ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ከተዋሕዶ ፡ በአፍኣ ፡ በምንታዌ ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ፡ ስለዚህ ፡ መለኮት ፡ ሕያው ፡ ነው ፡ ትስብእት ፡ ሞተ ፡ ማለትዎ ፡ ነው ።

ትስብእት ፡ ሞተ ፡ መለኮት ፡ አልሞተም ፡ በማለትና ፡ በሥጋ ፡ ሞተ ፡ በመለኮት ፡ ሕያው ፡ ነው ፡ በማለት ፡ መካከል ፡ ምን ፡ ያህል ፡ መራራቅ ፡ እንዳለ ፡ ልብ ፡ ብለው ፡ ያስተዎሉት ።

መለኮት ፡ አልሞተም ፡ ትስብእት ፡ ሞተ ፡ ማለት ፡ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ ኹለት ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎ ችን ፡ እንደ ፡ ሠሩ ፡ ያመለክታል ።

ምክንያቱም ፡ መሞትና ፡ አለመሞት ፡ የማይገናኙ ፡ ኹለት ፡ ነገሮች ፡ እንደኾኑ ፡ ሞተ ፡ የተባለ ፡ ትስብእትንና ፡ አልሞተም ፡ የተባለ ፡ መለኮትን ፡ የማይገናኙ ፡ ኹለት ፡ ባለቤቶች ፡ አድርጎ ፡ የሚያሳይ ፡ ስለኾነ ፡ ነው ።

በሥጋ ፡ ሞተ ፡ በመለኮት ፡ ሕያው ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ግን ፡ መሞትና ፡ አለመሞት ፡ የማይገናኙ ፡ ኹለት ፡ ሥራዎች ፡ ሲሆኑ ፡ ሠሪያቸው ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ መኾኑን ፡ ያሳያል ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ባለ ቅኔ ፡ እንድ ፡ ዮሴፍ ፡ በከንዓን ፡ ሞተ ፡ ሲባል ፡ በግብጽ ፡ ሕያው ፡ እንደ ፡ ኾነ ።

አንድ ፡ ኤርምያስም ፡ ለጠላቶቹ ፡ የገደልነው ፡ የሞተ ፡ ሲመስላቸው ፡ ሕያው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አንድ ፡ ክርስቶስም ፡ በሥጋ ፡ ቢሞት ፡ በመለኮት ፡ ሕያው ፡ ነው ፡ ብኋል ፡ ከመቃብር ፡ ውስጥ ፡ሲኾን፡ ከመቃብር ፡ በአፍዓ ፡ ነው ፡ እርስዎም ፡ ደራሲው ፡ ሊያስረዳ ፡ የፈለገ ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚታመምና ፡ የማይታመም ፡ ኾነ ፡ ማለትን ፡ ነው ፡ በማለትዎ ፡ በባለቅኔው ፡ ሐሳብ ፡ ደርሰውበታል ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ።

ይህን ፡ ቅኔ ፡ ለመጥቀስ ፡ የበቁበትም ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ባለቅኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሰብእ ፡ በማለቱ ፡ ፪ ፡ ያለ ፡ መስሎዎ ፡ ነው ፡ ባለቅኔው ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሰብእ ፡ ያለው ፡ ኹለት ፡ እንዳያሰኝበት ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያለውን ፡ ንባብ ፡ ይመልከቱ፡ ይህን ፡ ቃልዎን ፡ እንደማይለውጡ ፡ ከኾነ ፡ በዚህ ፡ አነጋገር ፡ እንስማማበታለን ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፱/ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ በሙሉነት ፡ መገኘታቸውን ፤ እንዲሁም ፡ መታመሙና ፡ መሞቱ ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የንጉሥ ፡ ተክለሃይማኖት ፡ ቅኔ ፡ ያስረዳል ፡ ብለው ፡ የሚከተለውን ፡ ሥላሴ ፡ ቅኔ ፡ ጽፈዋል ።

ሩፋኤል ፡ መልአከ ፡ ራማ ፡ ባሕረ ፡ ሥጋዌ ፡ አመ ፡ ፀበጠ ።
እንዘ ፡ እምነ ፡ ቆጽል ፡ ይነሥእ ፡ አርዓያ ፡ ወእምነ ፡ ሐመር ፡ አምሳለ ።
ለባሕረ ፡ ሥጋዌ ፡ ላዕሌሁ ፡ ጸለለ ።
ዕመቀ ፡ ባሕርዩስ ፡ (ባሕሩስ) ፡ ያርኢ ፡ ፈጣሪ ፡ አመ ፡ በእንቲአነ ፡ ክህለ ።
ወረደ ፡ ታሕተ ፡ ወተቆልቆለ ።
ወከመ ፡ እማእከል ፡ ኢተርፈ ፡ ወኢተሰዐለ ።
አርአየነ ፡ ኖጻሁ ፡ መስቀለ ፡ የሚል ፡ ነው ።

የዚሁ ፡ አስቸጋሪ ፡ ቅኔ ፡ ምሥጢር ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ። ሊቀ ፡ መላእክቱ ፡ ሩፋኤል ፡(ገብርኤል) ፡ ምሥጢረ ፡ ሥጋዌን ፡ ሲያበሥር ፡ ባሕረ ፡ ሥጋዌ ፡ አመ ፡ ፀበጠ ፡ ሰው ፡ የኾነው ፡ በአምሳል ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ቅጠልና ፡ እንደመርከብ ፡ በምሥጢሩ ፡ ተንሳፎ ፡ ቀረ ።

ለባሕረ ፡ ሥጋዌ ፡ ላዕሌሁ ፡ ጸለለ ።

ቃል ፡ ግን ፡ ሥጋን ፡ በለበሰ ፡ ጊዜ ፡ ቅጠልና ፡ መርከብ ፡ በባሕሩ ፡ ላይ ፡ እንደሚቀሩት ፡ በባሕረ ፡ ምሥጢሩ ፡ ላይ ፡ ተንሳፎ ፡ አልቀረም ፡ ማለት ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሊቀ ፡ መላእክቱ ፡ ሩፋኤል ፡ (ገብርኤል) ፡ በአምሳል ፡ ብቻ ፡ ሰው ፡ አልኾነም ።

ይህንም ፡ የሚያስረዳ ፡ እስከ ፡ ባሕሩ ፡ አሸዋ ፡ መውረዱ ፡ ማለት ፡ የሰውነቱ ፡ መጨረሻ ፡ ማስረጃ ፡ እስከ ፡ ኾነው ፡ እስከ ፡ መስቀል ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ መድረሱ ፡ ነው ።

ከዚህም ፡ የባሕርያተ ፡ ክርስቶስን ፡ ኹለትነት ፡ ማመናቸው ፡ በግልጥ ፡ ይረዳል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፱/ እውነትም ፡ ይህ ፡ ቅኔ ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ኾኖብዎታል ። አስቸጋሪነቱም ፡ ላለዐዋቂ ፡ ፎገራ ፡ ዱሩ ፡ እንደተባለው ፡ በርስዎ ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ አይደለም ፡ ስለዚህ ፡ አስቸጋሪ ፡ የኾነብዎን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አቃንቼና ፡ አብራርቼ ፡ ልጽፍልዎ ፡ እወዳለሁ ።

፩ኛ/ ንባቡን ፡ ባሕረ ፡ ሥጋዌ ፡ አመ ፡ ፀበጠ ፡ በማለትዎ ፡ ተሳስተዋል ፡ ንባቡ ፡ አመ ፡ ፀበተ ፡ ነው ፡ አፈታታቸውም ፡ የፀበጠ ፡ ጨበጠ ፡ የፀበተ ፡ ዋኘ ፡ ነው ። የባለቅኔውም ፡ አሳብ ፡ ሥጋዌ ፡ ባሕርን ፡ በዋኘ ፡ ጊዜ ፡ በላይ ፡ ተንሳፈፈ ፡ ለማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሥጋዌ ፡ ባሕርን ፡ በጨበጠ ፡ ጊዜ ፡ ለማለት ፡ አይደለም ።

ኹለትኛ ፡ ባለቅኔው ፡ ጠንቅቆ ፡ ሩፋኤል ፡ መልአከ ፡ ራማ ፡ ቢል ፡ ሩፋኤልን ፡ ገብርኤል ፡ ብሎ ፡ መተርጐም ፡ ገብርኤል ፡ ምሥጢረ ፡ ሥጋዌን ፡ ሲያበሥር ፡ ብለው ፡ የሰጡት ፡ አስተያየት ፡ ተራራ ፡ የሚያህል ፡ ስሕተት ፡ ነው ። ባለቅኔው ፡ ገብርኤልን ፡ ከፈለገ ፡ ገብርኤል ፡ መልአከ ፡ ራማ ፡ ማለት ፡



ይህ ሥዕል ፫ቱ ደቂቅን መልአከ እግዚአብሔር ከእሳተ ባቢሎን እንዳዳና
ቸው ያሳያል ዳን፥፫ ፲፫ — ፳፫ ። ፳፬ — ፳፰ ። በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ
ሥላሴ መልካም ፈቃድ ታርሞና ተዘጋጅቶ የታተመውን መጽሐፍ ቅዱስ
ተመልከት ።

አቃተው ፡ መሰለዎትን ፡ ስለዚህ ፡ በጣም ፡ ተሳስተዋል ። እውነተኛው ፡ የቅኔው ፡ ትርጓሜና ፡ ምሥጢሩ ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

ይህ ፡ ቅኔ ፡ የተደረሰ ፡ የቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡ በዓል ፡ በሚከበርበት ፡ ቀን ፡ ነው ። መልአኩ ፡ ቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡ በሰው ፡ ተመስሎ ፡ ለጦቢት ፡ እንደ ፡ አሽከር ፡ ኾኖ ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ አገለገለ ፡ በ፯ኛው ፡ ዓመት ፡ በዓሣ ፡ ሐሞት ፡ የጦቢትን ፡ ዐይን ፡ አብርቶለት ፡ መልአክነቱን ፡ ገለጸ ፡ ወደሰማይ ፡ ዐረገ ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ በጦቢት ፡ መጽሐፍ ፡ ይገኛል ። ለቅኔው ፡ መነሻ ፡ የኾነው ፡ ምሥጢር ፡ ይህ ፡ ነው ።

ስለዚህ ፡ የራማ ፡ መልአክ ፡ ሩፋኤል ፡ ሥጋዌ ፡ ባሕርን ፡ በዋኘ ፡ ጊዜ ፡ ከቅጠልና ፡ ከመርከብ ፡ ምሳሌ ፡ ነሥቶ ፡ በባሕር ፡ ሥጋዌ ፡ ላይ ፡ ተንሳፈፈ ፡ ማለት ፡ ቅጠልና ፡ መርከብ ፡ ወደውስጥ ፡ ሳይጠልቁ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ እንዲንሳፈፉ ፡ ሩፋኤልም ፡ በጦቢት ፡ ቤት ፡ አዛርያስ ፡ የምባል ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ፯ ፡ ዓመት ፡ ቢያገለግል ፡ ሰው ፡ መስሎ ፡ ከመታየት ፡ በቀር ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ አልኾነም ።
ፈጣሪ ፡ ክርስቶስ ፡ ግን ፡ ስለእኛ ፡ ብሎ ፡ የባሕሩን ፡ ጥልቅነት ፡ ሊያሳይ ፡ በቻለ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ቅጠልና ፡ እንደ ፡ መርከብ ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ሳይንሳፈፍ ፡ ከላይ ፡ ወርዶ ፡ እታች ፡ ድረስ ፡ ጠለቀ ። ማለት፡ ፈጣሪ ፡ ሰው ፡ መኾኑ ፡ በከዊን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡ መስሎ ፡ በመታየት ፡ አይደለም ።

ከባሕሩ ፡ ሥር ፡ መሠረት ፡ ሳይደርስ ፡ ቀርቶ ፡ ከመካከል ፡ የተመለሰ ፡ አለመኾኑንም፡ እናውቅ፡ ዘንድ ፡ አሽዋው ፡ መስቀልን ፡ አሳየን ፡ ማለት ፡ ሰው ፡ መኾኑ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡ መስሎ ፡ በመታየት ፡ ነው ፡ እንዳንል ፡ ሰው ፡ የመኾንን ፡ የመጨረሻውን ፡ ነገር ፡ መከራ ፡ መስቀልን ፡ ተቀብሎ ፡ አሳየን ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህ ፡ ቅኔ ፡ በጠቅላላው ፡ የሚያስረዳን ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ መኾኑንና ፡ መከራ ፡ መስቀልን ፡ መቀበሉ ፡ በምትሐት ፡ መስሎ ፡ በመታየት ፡ ሳይኾን ፡ በእውነት ፡ መኾኑን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

የባለቅኔው ፡ ሐሳብ ፡ የቅኔው ፡ ትርጓሜና ፡ ምሥጢር ፡ ይህ ፡ ሲኾን ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ባሕርያት ፡ በሙሉነታቸው ፡ መገኘታቸውንና ፡ የባሕርያተ ፡ ክርስቶስን ፡ ኹለትነት ፡ ማመናቸውን ፡ ያስረዳል ፡ ብለው ፡ የሰጡት ፡ ትችት ፡ ጸበተ ፡ ያለውን ፡ ንባብ ፡ ፀበጠ ፡ ብለው ፡ እንዳነበቡት ፡ ሩፋኤል ፡ ያለውን ፡ ንባብ ፡ ገብርኤል ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ተረጐሙት ፡ ያለ ፡ ስሕተት ፤ ማሻሻያ ፡ የሌለው ፡ ውሸት ፡ ነው ። ንባብን ፡ አበላሽቶ ፡ ምስጢሩን ፡ አጥፍቶ ፡ የእኛን ፡ ቅኔ ፡ ለእኛ ፡ ልተርጕምላችሁ ፡ ማለት ፡ እርስዎን ፡ ከማስገመት ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ጥቅም ፡ የሚያስገኝ ፡ ነገር ፡ አይደለም ።

## ደ ራ ሲ ።

፴/ ሌላም ፡ ደራሲ ፡ ያለጥርጥር ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ባህል ፡ ተከታይ ፡ የኾነ ፡ ከተዋሕዶም ፡ በኋላ ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ በሙሉነታቸው ፡ ስለመገኘታቸው ፡ ሲናገር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ።

ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነግደ ፡ ተሠግዎ ፡
ዘአብጽሐከ ፡ ዕለት ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሥጋ ፡ ኅሡር ፡
እንዘ ፡ ሕጹረ ፡ ነድ ፡ ምውቅ ፡ ቤተ ፡ አቡከ ፡ መንበር ።
እፎ ፡ ኀደርከ ፡ ከመ ፡ ሰራቂ ፤ በመስቀል ፡ አፍዓ ፡ ዘአልቦ ፡ ሐጹር ።
ምስለ ፡ አራዊት ፡ ውሉደ ፡ ነውር ።
ወእፎ ፡ ኀጣእከ ፡ ምጽላለ ፡ ጥዒና ፡ ምልአ ፡ ስዝር ፡
እንዘ ፡ አንተ ፡ ታወርሶሙ ፡ ብሔረ ፡ ጥዒና ፡ መንክር ፡
ዘይኢድም ፡ አርዓያሁ ፡ ወልምላሜሁ ፡ ዘይትፈቀር ፡
ለዕውረ ፡ እግር ፡ ሐንካስ ፡ ወለሐንካሰ ፡ ወይን ፡ ዕውር ፡
እምሐዊረ ፡ ፍና ፡ ገጸ ፡ ብእሲ ፡ ወእምነጽሮ ፡ ገጽ ፡ ፍና ፡ ብሔር ።

ከዚህም፡በክርስቶስ ፡ ኹለቱ ፡ ባሕርያት ፡ መገኘታቸውን ፡ እንደሚታመኑበት ፡ በግልጥ ፡ ይረዳል ። ደራሲው ፡ ክርስቶስ ፡ ሥጋን ፡ በለበሰ ፡ ጊዜ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ኾነ ፡ ተዋረደ ፡ እንደ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ በእውነት ፡ ታመመ ፡ ስለዚህ ፡ ባሕርየ ፡ ትሰብእት ፡ አለው ። ነገር ፡ ግን ፡ ሥጋ ፡ በመልበሱ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ መኾኑንም ፡ አልተወምና ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ አለው ፡ ይላል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፴/ ይህ ፡ ባለቅኔ ፡ ጠንቅቆ ፡ ክርስቶስን ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ አድርጎ ፡ አዋሕዶ ፡ በየማን ፡ አብ ፡ በዘባን ፡ ኪሩብ ፡ ያለህ ፡ አምላክ ፡ ስትኾን ፡ እንደ ፡ ሌባ ፡ ከሽፍቶች ፡ ጋራ ፡ እንዴት ፡ ተሰቀልክ ። ለዕውር ፡ ዐይንን ፡ ለአንካሳ ፡ እግርን ፡ ሰጥተህ ፡ ጤናን ፡ የምታወርሳቸው ፡ ስትኾን ፡ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ ጤናን ፡ እንደምን ፡ አጣህ ፡ እያለ ፡ ያደንቃል ።

ይህ ፡ አነጋገር ፡ በየማን ፡ አብ ፡ በዘባን ፡ ኪሩብ ፡ ያለው ፤ በመልዕልተ ፡ መስቀልም ፡ የተሰቀለው ፡ ያው ፡ አንዱ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያስረዳል ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ካቶሊካውያን ፡ አነጋገር ፡ አንድ ፡ ክርስቶስን ፡ ከኹለት ፡ ከፍሎ ፡ በየማን ፡ አብ ፡ በዘባነ ፡ ኪሩብ ፡ ያለ ፡ መለኮት ፡ ነው ፤ በመልዕልተ ፡ መስቀል ፡ የተሰቀለ ፡ ትስብእት ፡ ነው ፡ አይልም ። እንዲህ ፡ ጎልቶ ፡ የሚታየውን ፡ ነገር ፡ ክልኤ ፡ ባሕርይ ፡ ለማለት ፡ መረጃ ፡ አድርጎ ፡ መጥቀስ ፡ እንደ ፡ ማጭበርበር ፡ የሚቈጠር ፡ ነገር ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፴/ ኢትዮጵያውያን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ እንዲህ ፡ ቢያምኑ ፡ ቢጽፉ ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ አሉ ፡ የሚለውን ፡ የካቶሊክ ፡ አነጋገር ፡ አይቀበሉትም ፡ ምክንያቱም ፡ ለክርስቶስ ፡ አካል ፡ አንድነት ፡ የሚቃወም ፡ ስለሚመስላቸው ፡ ነው ። ይህንም ፡ የሚያስረዳ ፡ አንድ ፡ ስሙ ፡ ያልታወቀ ፡ ደራሲ ፡ የጻፈው ፡ ሥላሴ ፡ አለ ። ቅኔውም ።

ቃለ ፡ እምነ ፡ ሥጋ ፡ በሮሜ ፡ ፈለጡ ፡ ውሉደ ፡ ሮሜ ፡
ዘንተኒ ፡ ልማደ ፡ ዘሮሜ ፡ ከመ ፡ ኢንግበር ፡ ልማደ ፡
ዋሕድና ፡ ክልኤቱ ፡ በታቦር ፡ ተግህደ ።
ዘሰገደኒ ፡ ለቃል ፡ በሥጋ ፡ እንዘ ፡ ይፌሲ ፡ አሐደ ፡
ለሥጋ ፡ ሰገደ ፡ ኅበ ፡ ሰገደ ፡
ባዕደ ፡ አብ ፡ እስመ ፡ ኢወለደ ፡
ወድንግል ፡ ኢወለደት ፡ ባዕደ ። የሚል ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፴/ ይህን ፡ ቅኔ ፡ ለተመልካቾች ፡ አብራርቼና ፡ ገላልጬ ፡ ላቀርብላቸው ፡ እወዳለሁ ። ቃለ ፡ እምነ ፡ ሥጋ ፡ በሮሜ ፡ ፈለጡ ፡ ውሉደ ፡ ሮሜ ።

የሮም ፡ ልጆች ፡ በሮም ፡ ቃልን ፡ ከሥጋ ፡ ለዩት ፡ (ማለት) ፡ በኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነው ፡ ውሳኔ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ማለት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ አካል ፡ የሌለው ፡ ባሕርይ ፡ የለምና ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ ከማለት ፡ የሚያደርስ ፡ ነው ፡ ማለቱ ፡ ነው ።

ዘንተኒ ፡ ልማደ ፡ ዘሮሜ ፡ ከመ ፡ ኢንግበር ፡ ልማደ ። ዋሕድና ፡ ክልኤቱ ፡ በታቦር ፡ ተግኅደ ፡ ማለት ይህንም ፡ የሮማን ፡ ትምርት ፤ ትምርት ፡ አድርገን ፡ እንዳንቀበለው ፡ የቃልና ፡ የሥጋ ፡ ተዋሕዶ ፡ በደብረ ፡ ታቦር ፡ ተገለጸ ፡ (ማለት) ።

እንደ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ትምርት ፡ መለኮት ፡ ከትስብእት ፡ ተለይቶ ፡ የአምላክነትን ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፡ ትስብእትን ፡ የሚገዛ ፡ ቢኾን ፤ ትስብእትም ፡ ከመለኮት ፡ ተለይቶ ፡ የትስብእትን ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፡ ለመለኮት ፡ ሲገዛ ፡ የሚኖር ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ከኋሀ ፡ ከኹለቱ ፡ ከመለኮትና ፡ ከትስብእት ፡ አንዱ ፡ መለኮት ፡ ወይም ፡ በትስብእት ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ መለኮት ፡ ልጂ ፡ ነው ፡ ባለ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ መለኮቱን ፡ ከትስብእቱ ፡ ትስብእቱን ፡ ከመለኮቱ ፡ ሳይለያይ ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ባጭር ፡ ቁመት ፡ በጠባብ ፡ ደረት ፡ ተወስኖ ፡ የሚታየውን ፡ አካል ፡ ይህ ፡ ልጂ ፡ ነው ፡ ባላለም ፡ ነበረ ፡ ማለቱ ፡ ነው ።

ዘሰገደኒ ፡ ለቃል ፡ በሥጋ ፡ እንዘ ፡ ይፌሲ ፡ አሐደ ።
ለሥጋ ፡ ሰገደ ፡ ኅበ ፡ ሰገደ ።
ባዕደ ፡ አብ ፡ እስመ ፡ ኢወለደ ።
ወድንግል ፡ ኢወለደት ፡ ባዕደ ።

አብ ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ በመለኮቱ ፡ የወለደው ፡ ድኅረ ፡ ዓለምም ፡ እመቤታችን ፡ በሥጋ ፡ የወለደችው ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አብ ፡ የወለደው ፡ እመቤታችን ፡ ከወለደችው ፡ ሌላ ፤ እመቤታችንም ፡ የወለደችው ፡ አብ ፡ ከወለደው ፡ ሌላ ፡ አይደለምና ፡ ለቃል ፡ በሥጋ ፡ የሰገደ ፡ ትስብእትን ፡ ከመለኮት ፡ መለኮትን ፡ ከትስብእት ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ አዋሕዶ ፡ ለሥጋ ፡ ሰገደ ፡ (ማለት) ፡ ዘለምጽ ፡ ባጭር ፡ ቁመት ፡ በጠባብ ፡ ደረት ፡ ተወስኖ ፡ በአካለ ፡ ሥጋ ፡ ሲያየው ፡ አምላክነቱን ፡ አምኖ ፡ አቤቱ ፡ ከፈቀድክስ ፡ እኔን ፡ ከለምጽ ፡ ልታድነኝ ፡ ትችላለህ ፡ ብሎ ፡ በሰገደለት ፡ ጊዜ ፤ ዘዕውሩም ፡ እንደዚሁ ፡ አምንበት ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ ማነው ፡ ብሎ ፡ ጠይቆ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የምታየው ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ የሚነጋገረው ፡ ነው ፡ ቢለው ፡ አምላክነቱን ፡ አምኖ ፡ በሰገደ ፡ ጊዜ ፡ ለሥጋም ፡ ሰገደ ፡ እንጂ ፡ መለኮቱን ፡ ከትስብእቱ ፡ ለይቶ ፡ ለመለኮት ፡ ብቻ ፡ የሰገደ ፡ አይደለም ፡ ማለቱ ፡ ነው ።

የሌሎችም ፡ ቅኔዎች ፡ ኹሉ ፡ ምሥጢር ፡ ከዚህ ፡ የተለየ ፡ አይደለም ፡ የዚህን ፡ ቅኔ ፡ ድርስ ፡ ምሥጢሩን ፡ እንደተረዱት ፡ የሌሎችንም ፡ ምሥጢር ፡ የዚህን ፡ ያህል ፡ ተረድተውት ፡ ቢኾን ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ነበረ ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ምን ፡ ይደረጋል ፡ ሳይኾን ፡ ቀረ ።

ይህን ፡ ቅኔ ፡ ካነሡ ፡ ዘንድ ፡ ለዚህ ፡ ቅኔ ፡ ደጋፊ ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ መወድስ ፡ ልጠቅስልዎ ፡ እወዳለሁ ፡ ቅኔውም ፡ የሚከተለው ፡ ነው ።

በዘሞተ ፡ ወልድ ፡ ወበዘኢሞተ ፡ ፪ቲ ፡ አንስት ፡ ለእመ ፡ አንሥኣ ፡ ቅሰተ ፡
ወለእመ ፡ ለፍትሕ ፡ ሖራ ፡ እንተ ፡ ሰሎሞን ፡ አብያተ ።
ሰሎሞን ፡ ይቤ ፡ ይግበራ ፡ ክልኤተ ፡
ወልደ ፡ ዘኢሞተ ፤ ከመ ፡ በዝንቱ ፡ ያጠይቅ ፡ ጽድቀ ፡ ወሐሰተ ፡
አብሰ ፡ ወማርያም ፡ እንዘ ፡ ኢይትኃፀፉ ፡ ዘንተ ፡
ወእንዘ ፡ ጸብአ ፡ ልብ ፡ ኢያነሥኡ ፡ በዘሞተ ፡ ወኢሞተ ፡
እስመ ፡ እምንእስከ ፡ ልዮን ፡ መፍቀሬ ፡ ነገር ፡ አንተ ።
ከፈልከ ፡ ኀበ ፡ ክልኤ ፡ ሥግወ ፡ መለኮተ ።
የሚል ፡ ነው ።

ትርጓሜውና ፡ ምሥጢሩም ፡ ባጭሩ ፡ ሰሎሞን ፡ ኹለት ፡ ሴቶች ፡ በሞተ ፡ ልጅና ፡ ባልሞተ ፡ ልጅ ፡ የሞተው ፡ ያንች ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ያልሞተ ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ በመባባል ፡ ጥል ፡ አንሥተው ፡ ሔደው ፡ ፍርድ ፡ ስጠን ፡ ቢሉት ፡ በዚህ ፡ እውነቱንና ፡ ሐሰቱን ፡ ለማወቅ ፡ ሲል ፡ ያልሞተውን ፡ ልጅ ፡ በሰይፍ ፡ ቆርጣችሁ ፡ ተካፈሉት ፡ አለ ።

ልዮን ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ከትንሽነትህ ፡ ጀምረህ ፡ ነገር ፡ ወዳጅ ፡ ስለኾንክ ፡ እመቤታችን ፡ ማርያምና ፡ አብ ፡ በሞተውና ፡ ባልሞተው ፡ በክርስቶስ ፡ ሳይጣሉ ፡ ፍረድልን ፡ ሳይሉህ ፡ ሰው ፡ የኾነ ፡ መለኮትን ፡ ከኹለት ፡ ከፈልከው ፡ ማለት ፡ ነው ።

የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ እንዲህ ፡ ጠንቅቀው ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ የኾነ ፡ ቃል ፡ በተዋሕዶ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ኾኖ ፡ ያምላክነትንም ፡ የሰውነትንም ፡ ሥራ ፡ እንደሠራ ፡ ያምናሉ ፡ ያስተምራሉ ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ እርስዎ ፡ እየፈጠሩ ፡ እንደሚያወሩት ፡ መለኮትና ፡ ትስብእት ፡ በምንታዌ ፡ በኹለትነት ፡ ጸንተው ፡ በኀገርና ፡ በተገገር ፡ ደረጃ ፡ እየኖሩ ፡ መለኮት ፡ የመለኮትን ፡ ሥራ ፡ ትስብእት ፡ የትስብእትን ፡ ሥራ ፡ ይሠራሉ ፡ አይሉም ፡ በየቅኔዎች ፡ የሰጡት ፡ አስተያየት ፡ ኹሉ ፡ ፍጹም ፡ ውሸት ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፴፭/ እላይ ፡ ከተነገሩት ፡ ምክንያቶች ፡ በስተቀር ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ሮማን ፡ የሚያራርቁ ፡ ሌሎችም ፡ የሥርዓት ፡ አምልኮ ፡ ምክንያቶች ፡ አሉ ። ከነርሱም ፡ ለምሳሌ ፡ በሮም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኩል ፡ ምእመናቹን ፡ በኹለት ፡ መልክ ፡ ማቁረብን ፡ እንደ ፡ ማስቀረት ፡ የመሰሉ ፡ ናቸው ። ስለዚሁ ፡ በሚከተለው ፡ መወድስ ፡ የሚለውን ፡ እንስማ ።

ሰላም ፡ እልብነ ፡ ምስለ ፡ ሰብአ ፡ ሮሜ ፡ ወለሰብአ ፡ ሮሜ ፡ ምስሌነ ፡ ኢሀለዎሙ ፡ ሰላም ።
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘመደ ፡ ሥጋ ፡ ወዐፅም ።
እስመ ፡ ከተረነ ፡ ደምከ ፡ ቀለም ።
እ፡ዘትሠይም ፤ ቀስተ ፡ ሕይወታ ፡ ለንፍስ ፡ በደመና ፡ ገቦ ፡ ንዝኀተ ፡ ደም ።
አንተሰ ፡ ታስተዱሉ ፡ በውስተ ፡ ዛቲ ፡ ዓለም ።
ኪያሆሙ ፡ ለጥኂና ፡ ወኪያነ ፡ ለሕማም ።
እንዘ ፡ እምፍጥረትነ ፡ ጴጥሮስ ፡ በተዐድዎ ፡ ሕግ ፡ ፍጹም ።
ለዘተጸብአከ ፡ ንጸብአ ፡ ወዘተቃወመከ ፡ ንትቃወም ።

## መ ላ ሽ ።

፴፭/ እርግጥ ፡ ነው ፡ ከላይ ፡ እንዳመለከቱት ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ ከሚለያዩበት፡ ባህል፡ሌላ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ሮማ ፡ የሚለያዩበት ፡ ባህል ፡ መኖሩ ፡ አይካድም ፡ ከነዚያውም ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ አሁን ፡ የጠቀሱት ፡ የሥጋ ፡ ወደሙ ፡ አቀባበል ፡ መኾኑ፡ አይካድም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ቅኔውን ፡ እፈታለሁ ፡ ብለው ፡ ሲሞክሩ ፡ ተሳስተዋል ፡ ይህንንም ፡ በሚከተሉት ፡ መሥመሮች ፡ እገልጻለሁ ።

## ደ ራ ሲ ።

፴፮/ ከኹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ኢትዮጵያውያኖቹ ፡ በዚህ ፡ መወድስ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘመደ ፡ ሥጋ ፡ ወዐፅም ፡ ሲል ፡ እንደኛ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ የኾንክ ፡ ማለቱ ፡ ነውና ፡ የክርስቶስ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ በሙሉ ፡ መጠበቁን ፡ ደጋግመው ፡ መታመናቸውን ፡ ማስተዋል ፡ ነው ፡ ብለው ፡ የማንጣላበትን ፡ ነገር ፡ ከምንጣላበት ፡ ውስጥ ፡ አግብተው ፡ አዳብለው ፡ ተናግረዋል ።

መ ላ ሽ ።

፵፪/ ኢትዮጵያውያንና ፡ ካቶሊካውያን ፡ የምንለያይ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ባሕርየ ፡ መለኮትና ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ አልተዋሐዱም ፡ በምንታዌ ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ፡ ሲሉ ፡ እኛ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምንታዌ ፡ የለበትም ፡ በማለታችን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ቃል ፡ ከእመቤታችን ፡ በነሣው ፡ ሥጋ ፡ ወገናችን ፡ ዘመዳችን ፡ ኾነ ፡ አልኾነም ፡ በመባባል ፡ አይደለም ። ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በቅዱስ ፡ ዳዊት ፡ አድሮ ፡ አየድዮሙ ፡ ስመከ ፡ ለአኃውየ ፡ ያለውን ።

በኢሳይያስም ፡ እስመ ፡ ደቂቅ ፡ ተሳተፉ ፡ በሥጋ ፡ ወደም ፡ ውእቱኒ ፡ ተሳተፎሙ ፡ በዝንቱ ፡ ወከመ ፡ ቢጸሙ ፡ ኮነ ፡ ሎሙ ፡ ያለውን ።

በጳውሎስም ፡ ኢየኀፍር ፡ ብሂሎቶሙ ፡ ለነዳያን ፡ አኃውየ ፡ ያለውን ።
በወንጌልም ፡ እምእሉ ፡ ንኡሳን ፡ አኀውየ ፡ ያለውን ፡ የማናውቅ ፡ የማናምን ፡ አስመስለው ፡ ዘመደ ፡ ሥጋ ፡ ወዐፅም ፡ ማለቱ ፡ እንደኛ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ የኾንክ ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በማዳነቅ ፡ መናገርዎ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ባህል ፡ ገና ፡ ያላወቁ ፡ በነገሩ ፡ ያልደረሱበት ፡ መኾንዎን ፡ በግልጥ ፡ ያስረዳል ። ዕብ ፡ ፪ ፡ ፲፩ - ፲፰ ።

ደ ራ ሲ ።

፵፫/ እስመ ፡ ከተረነ ፡ ደምከ ፡ ቀለም ፡ ሲል ፡ የሮምያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለምእመናን ፡ የማታቁርበው ፡ ደምህ ፡ ያለመስማማት ፡ ምክንያት ፡ ኾኖ ፡ እኛን ፡ ከነርሱ ፡ እነርሱን ፡ ከኛ ፡ ለያይቶናል ፡ ይላል ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፵፬/ ይህ ፡ አፈታት ፡ ከቅኔው ፡ ምሥጢር ፡ እጅግም ፡ የራቀ ፡ አይደለም ፤ ስለኾነም ፡ አፈታቱ ፡ ቀጥታ ፡ እንዲያገኝ፡ እ፡ ዘትሠይም ፡ ቀሥተ ፡ ሕይወታ ፡ ለነፍስ ፡ በደመና ፡ ገቦ ፡ ንዝኀተ ፡ ደም ፡ ያለውን ፡ ንባብ ፡ ጨምሮ ፡ መፍታት ፡ ይጠቅማል ።
የነፍስ ፡ ሕይወት ፡ ቀሥትን ፡ ከጐንህ፡ በፈሰሰ ፡ ደም ፡ ደመና ፡ ስትሾም ፡ ደምህ ፡ ቀለም ፡ ለይቶናልና ፡ ማለት ፡ ደኅነተ ፡ ነፍስ ፡ የሚገኝ ፡ ደምህን ፡ በመቀበል ፡ እንዲኾን ፡ ስታደርግ ፡ ሮማውያን ፡ ደምህን፡ለምእመናን፡ከልክለዋልና፡ለሮም፡ሰዎች፡ከእኛ ፡ ጋራ፡ፍቅር፡አንድነት ፡ የላቸውም ፡ ለእኛም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ የለንም ፡ ማለት ፡ ነው ።

ደ ራ ሲ ።

፵፭/ አባቡንም ፡ በምጸት ፡ እነጋገር ፡ ሲፈጽም ፡ አንተ ፡ ደምህን ፡ መጠጣት ፡ ያዘዝህ ፡ እነርሱን ፡ ለጤንነት ፡ እኛን ፡ ለሥቃይ ፡ ስለመደብከን ፡ ነው ፡ አለ ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፵፮/ የለም ፡ እንዲህም ፡ አይደለም ፡ ተሳስተዋል ፡ ይህ ፡ ባለቅኔ ፡ ባዬ ፡ ሱስንዮስ ፡ ጊዜ ፡ የነበረ ፡ ነው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ካቶሊካውያን ፡ በገዛ ፡ ሀገራቸው ፡ ገብተው ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ስላሠቃይዋቸው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እነሱን ፡ ለዕረፍት ፡ እኛን ፡ ለመከራ ፡ አዘጋጅተኸናል ፡ በማለት ፡ ሮማውያንን ፡ ለዚህ ፡ ዓለም ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ራሱን ፡ ለዕረፍተ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እንዳዘጋጀ ፡ አድርጎ ፡ በግልጽ ፡ ተናግሯል ፡ እንጂ ፡ የምጸት ፡ አነጋገር ፡ አይደለም ።

ደ ራ ሲ ።

፵፯/ ነገር ፡ ግን ፡ ከጥንት ፡ ጀምረን ፡ ሕግህን ፡ በመተላለፍ ፡ አንተን ፡ የካደውን ፡ ፍጹም ፡ ጴጥሮስን ፡ የምንመስል ፡ ነንና ፡ የሚወጋህን ፡ እንወጋዋለን ፡ ለሚቃወምህም ፡ እንቃወመዋለን ፡ እንጂ ፡ በኹለቱ ፡ መልኮች ፡ የማቍረብ ፡ ልማዳችንን ፡ አንተውም ፡ ይላል ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፵፰/ ከዚህ ፡ ላይ ፡ ትርጓሜው ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ከንባቡም ፡ ተሳስተዋል ፡ ንባቡ ፡ እስመ ፡ እምፍጥረትነ ፡ ጴጥሮስ ፡ በተዐድዎ ፡ ሕግ ፡ ፍጹም ፡ ለዘተጸብአከ ፡ ንጸብእ ፡ ወዘተቃወመከ ፡ ንትቃወም ፡ ነው ።



ይህ ሥዕል መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሴተ ኀሙስ ይሁዳ ሳይቀር ባለመለያየት ለደቀመዛሙርቱ ሥጋውንም ደሙንም እንደ ሰጣቸው ያሳያል ማቴ ፳፮ ፳፮—፳፱ ።

ትርጓሜውም ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሕግን ፡ በመቃወም ፡ ፍጹም ፡ ነውና ፡ ዛሬም ፡ የሚ ጣላህን ፤ እንጣላዋለን ፡ የሚቃወምህን ፡ እንቃወመዋለን ፡ ነው ። ምሥጢሩም ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስን ፡ ሕግን ፡ በመተላለፍ ፡ ፍጹም ፡ ነው ፡ ያለበት ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በፍኖተ ፡ ቂሳርያ ፡ አይሁድ ፡ ይይዙኛል ፡ ይሰቅሉኛል ፡ ቢላቸው ፡ ሐሰ ፡ ለከ ፡ ይህ ፡ ባንተ ፡ አይደረግም ፡ ብሎ ፡ የጌ ታን ፡ ቃል ፡ ተቃወመ ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ሕግ ፡ ስለኾነ ፡ ይህን ፡ ንግግሩን ፡ ሕግን ፡ እንደመጣስ፡ ቈጥሮበት ፡ ሑር ፡ እምድኅሬየ ፡ ሰይጣን ፡ እስመ ፡ ኮንከኒ ፡ ማዕቀፍየ ፡ ሊተ ፡ እስመ ፡ ኢትሔሊ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ዘእንበለ ፡ ዘሰብእ ።

ሰውሰውኛ ፡ ነገር ፡ ትናገራለህ ፡ እንጂ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ስለማታስብ ፡ ዕንቅፋት ፡ ኾነኸኛልና ፡ አንተ፡ ሰይጣን ፡ ከኋላየ ፡ ወግድ ፡ ብሎታልና ፡ በተዐድዎ ፡ ሕግ ፡ ፍጹም ፡ ያለበት ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፤ ነው ፡ ማቴ ፡ ፲፮ ፡ ፳፩-፳፬ ። ለዘተጻብአከ ፡ ንጻብእ ፡ ወዘተቃወመከ ፡ ንትቃወም ፡ ያለበትም ፡ ምክንያት ፡ በጴጥሮስ ፡ ወንበር ፡ የተቀመጠው ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ።

ስትዩ ፡ እምኔሁ ፡ ኵልክሙ ፡ ዝ ፡ ውእቱ ፡ ደምየ ፡ ዘሐዲስ ፡ ሥርዓት ፡ ዘይትከዐው ፡ በእንተ ፡ ብዙኃን ፡ ከመ ፡ ይትኀደግ ፡ ኃጢአት ።

ሐዲስ ፡ ሕግ ፡ ወንጌል ፡ የምትጸናበት ፤ ኃጢአት ፡ ይሰረይ ፡ ዘንድ ፡ የሚፈሰው ፡ ደሜ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ኹላችሁም ፡ ከርሱ ፡ ጠጡ ፡ ብለህ ፡ የሠራኸውን፡ ሕግ ፡ ተላልፎ ፡ ደምህን ፡ ምእመናን ፡ አይ ቀበሉ ፡ ካህናት ፡ ብቻ ፡ ይቀበሉት ፡ ብሎ ፡ በመበየን ፡ ቢቃወምህ ፡ እኛ ፡ እንጣላዋለን ፡ እንቃወመ ዋለን ፡ እንጂ ፡ አንቀበለውም ፡ ማለት ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ካነሣት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ ገባ ፡ ብለን ፡ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያን ፡ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፡ እንደ ፡ ትእዛዙ ፡ ለካህናት ፡ ብቻ ፡ ስታቀብል ፡ ለምእመናን ፡ ሥጋ ውን ፡ ብቻ ፡ አቀብላ ፡ ደሙን ፡ የከለከለችበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድን ፡ ነው ፤ ከሥጋውና ፡ ከደሙ ፡ የሚበላለጥ ፡ አለ ፡ ለማለት ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥጋውን ፡ የቈረሰ ፡ ለም እመናኑ ፡ ኹሉ ፡ ሲኾን ፡ ደሙን ፡ ያፈሰሰ ፡ ለካህናት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይኾን ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለምእመናን ፡ ኹሉ ፡ ሥጋውንም ፡ ደሙንም ፡ መቀበል ፡ እንዲገ ባቸው ፡ በቃልም ፡ ነግሮናል ፡ በሥራም ፡ አሳይቶናል ።

በቃል ፡ ዘበልዐ ፡ ሥጋየ ፡ ወሰትየ ፡ ደምየ ፡ ይሄሉ ፡ ምስሌየ ። እመ ፡ ኢበላእክሙ ፡ ሥጋሁ ፡ ለወ ልደ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ወኢሰተይክሙ ፡ ደሞ ፡ አልብክሙ ፡ ሕይወት ።

ሥጋየን ፡ ካልበላችሁ ፡ ደሜን ፡ ካልጠጣችሁ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ሥጋዬን ፡ ካልበላችሁ ፡ ብቻ ፡ አላለም ።

በገቢርም ፡ በምሴተ ፡ ኀሙስ ፡ ኅብስቱን ፡ አከብሮ ፡ ለውጦ ፡ ፍጹም ፡ ሥጋውን ፡ አድርጎ ፤ እንኩ ፡ ብሉ ፡ ብሎ ፡ ከሰጣቸው ፡ በኋላ፡ ወይኑንም ፡ አከብሮ ፡ ለውጦ ፡ ፍጹም ፡ ደሙን ፡ አድርጎ ሰጣቸው ፡ እንጂ ፡ ሥጋውን ፡ ብቻ ፡ አልሰጣቸውም ።

ስላቀባበሉም ፡ ይሁዳ ፡ ሳይቀር ፡ ለኹሉም ፡ በትክክል ፡ ሥጋውንም ፡ ደሙንም ፡ ሰጣቸው ፡ እንጂ ፡ ለይቶ ፡ የተወው ፡ የለም ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ይህ ፡ ብያኔ ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ መኾኑ ፡ ነው ።

አንድ ፡ የካቶሊክ ፡ መነኩሴ ፡ የዚህን ፡ ነገር ፡ እንዲያስረዱኝ ፡ ብጠይቃቸው ፡ ደሙ ፡ የሚሰጥ ፡ ባንድ ፡ ዕርፈ ፡ መስቀል ፡ ነው ። የያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ከንፈር ፡ ዕርፈ ፡ መስቀሉን ፡ መንካቱ ፡ የማይ ቀር ፡ ነው ።

ምናልባት ፡ ከምእመናን፡ደዌ፡ያለበት፡ቢኖር፡ደዌ ፡ በዕርፈ ፡ መስቀሉ ፡ ወደሌሎች ፡ የሚናኝ ፡ ስለኾነ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ደዌ ፡ እንዳይናኝ ፡ ደም ፡ የሌለው ፡ ሥጋ ፡ የለምና ፡ ለምእመናን ፡ ሥጋው ፡ ብቻ ፡ ይበቃቸዋል ፡ ካህናት ፡ ግን ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ደዌ ፡ የማይጠረጠሩ ፡ ሕያዋን ፡ ስለኾኑ ፡ ሥጋው ንም ፡ ደሙንም ፡ ይቀበሉ ፡ ተብሎ ፡ የተበየነ ፡ ብያኔ ፡ ነው ። ለዚኸውም ፡ መሠረቱ ፡ በመጽሐፈ ፡ ቅዳሴ ፡ ወኢይምሰሎ ፡ ለ፩ ፡ እምኔነ ፡ ዘይበልዕ ፡ ሥጋ ፡ ባሕቲቶ ፡ ዘእንበለ ፡ ደም ፡ ወመ ንፈስ ፡ ይላል ፡ አሉኝ ።

እውነት ፡ ነው ፤ በመጽሐፈ ፡ ቅዳሴ ፡ ይህን ፡ ኅብስት ፡ በተቀበለ ፡ ጊዜ ፡ ከእኛ ፡ ሳንዱ ፡ ደም ፡ መንፈስ ፡ የተለዩት ፡ ሥጋን ፡ ብቻ ፡ የምቀበል ፡ አይምሰለው ።

ይህንንም ፡ ጽዋዕ ፡ በተቀበለ ፡ ጊዜ ፡ ሥጋና ፡ መንፈስ ፡ የተለዩትን ፡ ደም ፡ ብቻ ፡ የምቀበል ፡ አይምሰለው ፡ መለኮቱ ፡ ከትስብእቱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እንደኾነ ፡ ሥጋ ፡ ደም ፡ መንፈስም ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ የሚል ፡ ንባብ ፡ መገኘቱ ፡ አይካድም ፡ ይኸውም ፡ ንባብ ፡ የሚገኘው ፡ በእስክንድ ርያው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ በዲዮስቆሮስ ፡ ቅዳሴ ፡ ነው ።

የዚህ ፡ ንባብም ፡ ምሥጢሩ ፡ ሰው ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ አራቱ ፡ ባሕርያት ፡ ይለያዩበታል ፡ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ የወጉ ፡ ባሕርይ ፡ ስለተለየው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሬሳውን ፡ ቢወጉት ፡ ደም ፡ አይ ወጣውም ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ግን ፡ በመልዕልተ ፡ መስቀል ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ ነፍሴን ፡ በእጅህ ፡ አደራ ፡ እሰጣለሁ ፡ ብሎ ፡ ነፍሱን ፡ ከሥጋው ፡ ከለየ ፡ በኋላ ፡ አራቱ ፡ ባሕርያት ፡ አልተለያዩበትም ። ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፵፮ ።

ስለዚህ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሐራዊ ፡ ቀኝ፡ ጐኑን ፡ በቀጭን ፡ ጦር ፡ ቢወጋው ፡ ትኩስ ፡ ደም ፡ ጥሩ ፡ ወኀ ፡ ፈሰሰው ። ዮሐ ፡ ፲፱ ፡ ፴፬ ።

ይህ ፡ ሊኾን ፡ የቻለው ፡ አራቱ ፡ ባሕርያት ፡ ባይለያዩበት ፡ ነው ፡ ይህም ፡ ንባብ ፡ ይህ ፡ የምን ቀበለው ፡ ሥጋው ፡ ደሙ ፡ ባራቱ ፡ ባሕርያት ፡ ያልተለያዩበት ፡ መኾኑን ፡ ያስገነዝበናል ፡ እንጂ ፡ ካህናት ፡ ሥጋውንም ፡ ደሙንም ፡ ይቀበሉ ፡ ምእመናን ፡ ሥጋውን ፡ ብቻ ፡ ይቀበሉ ፡ ደሙን ፡ አይ ቀበሉ ፡ ማለትን ፡ የሚያመለክት ፡ አነጋገር ፡ አይደለም ።

ይህን ፡ ንባብ ፡ የጠቀሱልኝም ፡ መነኩሴ ፡ ለሐሳባቸው ፡ ተመሳሳይ ፡ መስሎ ፡ ስለታያቸው፡ በራሳቸው ፡ ሐሳብ ፡ የጠቀሱት ፡ እንጂ ፡ የሮማ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ በእውነት ፡ ይህን ፡ መሠረት ፡ አድርገው ፡ የወሰኑት ፡ አይመስልም ።

ምክንያቱም ፡ ሮማውያን ፡ ዲዮስቆሮስን ፡ የአውጣኪ ፡ ሴረኛ ፡ መናፍቅ ፡ እያሉ ፡ ስሙን ፡ ከማ ጥፋትና ፡ ሥራውን ፡ ትምርቱን ፡ ከመንቀፍ ፡ በቀር ፡ የማይቀበሉት ፡ ስለኾነ ፡ ነው ። ተቀብለውትስ ፡ ቢኾን ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ መለያየትና ፡ መበጣበጥ ፡ ባልተፈጠረም ፡ ነበረ ። በጠቅላላው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያሉ ፡ ፲፬ቱ ፡ ቅዳሴያት ፡ በሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያሉ ፡ አይመስለኝም ፡ ስለዚህ ፡ የሮም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይህን ፡ ውሳኔ ፡ የሰጠች ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ደዌ ፡ ይናኛል ፡ በማለት ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግልጥ ፡ ነገር ፡ ነው ። ምእመናን ፡ ደሙን ፡ በዕርፈ ፡ መስቀል ፡ ሲቀበሉ ፡ ደዌ ፡ ይተላ ለፍባቸዋል ፡ ብሎ ፡ መጠራጠር ፡ ካለ ፡ መድኃኒተ ፡ ሥጋ ፡ መድኃኒተ ፡ ነፍስ ፡ ይኾነናል ፡ ብለን ፡ አምነን ፡ የምንቀበለውን ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ የደዌ ፡ መተላለፊያ ፡ ይኾናል ፡ ብለው ፡ በሚያስቡና ፡ በሚጠራጠሩ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ የሥጋ ፡ ወደሙ ፡ መድኃኒትነት ፡ ገና ፡ አልታወቀም ፡ አልታመነም ፡ ቢባል ፡ እርግጠኛ ፡ ነገር ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፴፮/ እላይ ፡ ከጠቀስናቸው ፡ ቅኔዎች ፡ ግማሾቹ ፡ የደራሲያቸው ፡ ስም ፡ አይታወቅም ፡ የተደ ረሱበት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የኹሉም ፡ አይታወቅም ። እርግጠኛ ፡ ኾኖ ፡ የሚታየን ፡ ግን ፡ ከ፲፰ኛ ፡ ፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ የተደረሱ ፡ አለመኾናቸው ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፴፮/ ይህን ፡ ያሉበት ፡ ምክንያት ፡ ገብቶናል ። ከ፲፰፻ ዓ/ም ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቃ ውንት ፡ ካቶሊካውያን ፡ ስለነበሩ ፡ ይህን ፡ የመሳሰለ ፡ ድርሰት ፡ አይደርሱም ፡ ለማለት ፡ ነው ።

ይህ ፡ አሳብዎ ፡ እኒህ ፡ የጠቀሱዋቸው ፡ ቅኔዎች ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ይደግፋሉ ፡ እያሉ ፡ የሰጡት ፡ አስተያየት ፡ ኹሉ ፡ ከልብ ፡ ያልመነጨ ፡ ካንገት ፡ በላይ ፡ የተነገረ ፡ መኾኑን ፡ አረጋገጡ ፡ ማለት ፡ ነው ። የተደረሱበትም ፡ ጊዜ ፡ አይታወቅም ፡ ማለትዎ ፡ ለሀገርዎ ፡ ታሪክና ፡ ባህል ፡ እንግዳ ፡ ባይታዎር ፡ በመኾንዎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሊቃውንቱ ፡ በነበሩበት ፡ ዘመን ፡ ሊታወቅ ፡ ይቻላል ። እነሆ ፡ በ፻፹፩ ፡ ገጽ ፡ የተጻፈው ፡ ሃይማኖተ ፡ ቄርሎስ ፡ ኮነት ፡ ግማዳተ ፡ አብድ ፡ የሚ ለው ፡ መወድስ፡ የጐንደሩ ፡ ሊቅ ፡ የክፍለ ፡ ዮሐንስ ፡ ነው ። ክፍለ ፡ ዮሐንስም ፡ በአድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱ ፡ ጊዜ ፡ የነበረ ፡ ሊቅ ፡ ነው ። አድያም ፡ ሰገድ ፡ ኢያሱም ፡ ከ፲፮፻፸፬ - ፲፮፻፺፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ - ወይም ፡ እንደርስዎ ፡ አቆጣጠር ፡ ከ፲፮፻፹፪ - ፲፯፻፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የነገሡ ፡ ናቸው ። ገጽ ፡ ፻፺፩ ፡ የከ ቡር ፡ ብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይን ፡ መጽሐፍ ፡ ዋዜማ ፡ ተመልከት ።

በ፻፺፩ ፡ ገጽ ፡ የተጻፈው ፡ ቃለ ፡ እምነ ፡ ሥጋ ፡ የሚለውም ፡ ሥላሴ ፡ ቅኔ ፡ ቸርደሞ ፡ የተባለው ፡ እርቶዶክሳዊ ፡ ሊቅ ፡ የተቀኘው ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ሊቅ ፡ የካቶሊካውያንና ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ክርክር ፡ ተፋፍሞ ፡ በነበረበት ፡ ባፄ ፡ ሱስንዮስ ፡ ዘመን ፡ የነበረ ፡ ነው ።

አቤቶ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የተባሉትም ፡ ከ፲፮፻፺፰ - ፲፯፻፪ ፡ የነገሡት ፡ መናኔ ፡ መንግሥት ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ናቸው ። የብላቴን ፡ ጌታ ፡ ኅሩይ ፡ ዋዜማ ፡ ተመልከት ።

እንአለቃ ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ እንቁስ ፡ ዘሩፋኤል ፡ የተባሉትም ፡ በጐንደር፡ መንግሥት ፡ የነበሩ ፡ ሊቃውንት ፡ ናቸው። የጐንደር ፡ መንግሥትም ፡ በ፲፭፻፸፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከነገሡ ፡ ከዓፄ ፡ ሠርጸ ፡ ድንግል ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ መንግሥት ፡ ተክለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ነው ። ፍጻሜ ፡ መንግሥት ፡ ተክለ ፡ ጊዮር

ጊስም ፡ ከ፲፯፻፹፪ ፡ እስከ ፡ ፲፯፻፹፯ ፡ ነው ። እንዲህ ፡ በግልጥ ፡ የታወቀውን ፡ ነገር ፡ አስተባብለው ፡ ከ፲፰፻ ዓ ፡ ም ፡ በፊት ፡ አለመደረሳቸው ፡ በግልጥ ፡ ይታየኛል ፡ ሲሉ ፡ የሚታየዎ ፡ እርግጠኛ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ የመሰለ ። መኾኑ ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፴፯/ በተለይም ፡ በገጽ ፡ ፻፹፰ ፡ ፻፺፪ ፡ ፻፺፫ - ፬ ላይ ፡ ያሉ ፡ ቅኔዎች ፡ በሙዚዮ ፡ ቦርጃና ፡ ውስጥ ፡ ባለ ፡ ብራና ፡ ኢ ፡ ጉዲ ፡ ያገኛቸው ፡ ናቸው ፡ የተጻፉበት ፡ ብራና ፡ በ፲፬፻ ዓ/ም ፡ አኩል ፡ የተጻፈ ፡ ይመስላል ፡ ብለው ፡ ቅኔዎቹ ፡ ከ፲፰ኛ ፡ ፻ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ወዲህ ፡ የተጻፉ ፡ መኾናቸውን ፡ ለማስረዳት ፡ ሞክረዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፴፯/ እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ አያያዝ ፡ ከ፲፱፻ ዓ ፡ ም ፡ ወዲህ ፡ የተጻፈ ፡ አረት ፡ ቢገኝ ፡ ስለብራናው ፡ አዲስነት ፡ አረት ፡ የተደረሰች ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ይቻላል ፡ ማለትዎ ፡ ነው ። የተጨበጠና ፡ የተረጋገጠ ፡ ነገር ፡ ሳይዙ ፡ መረጃ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ማስተባበል ፡ ደግ ፡ ነገር ፡ አይደለም ።

## ክ ፍ ል ፫ ።

## የመጨረሻ ፡ ፍርድ ።

፩/ ፍርድ ፡ ማለት ፡ ዳኛ ፡ ለከሣሽና ፡ ለተከሣሽ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ የከሳሽን ፡ ክሱን ፡ የተከሳሽን ፡ መልሱን ፡ ሰምቶ ፡ ያኑም ፡ በምስክሮች ፡ ቃል ፡ አጣርቶ ፡ ነገሩን ፡ አበጥሮ ፡ አንጠርጥሮ ፡ ከተረዳው ፡ በኋላ ፡ የሚሰጠው ፡ አስተያየት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ከሳሽ ፡ ራሱ ፡ ተከሳሽ ፡ ራሱ ፡ አስረጅ ፡ ራሱ ፡ ፈራጅ ፡ ኾኖ ፡ ሊፈርድ ፡ አይገባውም ፡ ። ባባቶቻችንም ፡ ተረት ፡ ብቻውን ፡ የሮጠ ፡ የሚቀድመው ፡ የለም ፡ ይባላል ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ራስዎ ፡ ከሳሽ ፡ ራስዎ ፡ መላሽ ፡ ራስዎ ፡ ተከራካሪ ፡ ራስዎ ፡ መስካሪ ፡ ኾነው ፡ የሰጡት ፡ እውነተኛ ፡ ፍርድ ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ።

## ደ ራ ሲ ።

፪/ እንደሚታየው ፡ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ የመረመርናቸው ፡ ምንጮች ፡ ካለፉት ፡ ምርመራዎቻችን ፡ ያገኘነውን ፡ ኹሉ ፡ በፍጹም ፡ የሚያጸድቁ ፡ ናቸው ። በጠቅላላው ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህልን ፡ በሚያይ ፡ በእነዚሁ ፡ ምንጮች ፡ መሠረት ፡ እነርሱ ፡ በክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካልና ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አለ ፡ የሚለውን ፡ የሃይማኖት ፡ ትምርት ፡ በመሠረቱ ፡ እንደሚቀበሉት ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡ ደርሰናል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፪/ በዚህ ፡ ምዕራፍ ፡ ውስጥ ፡ የመረመርዋቸው ፡ ጽሑፎች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ የደረስዋቸው ፡ ቅኔዎች ፡ መኾናቸው ፡ ግልጥ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እኒህ ፡ ቅኔዎች ፡ ባለፈው ፡ ምርመራዎ ፡ እንዐጼ ፡ ካሌብ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ነበሩ ፤ ኢትዮጵያ ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ተቀብላ ፡ ነበረ ፡ እያሉ ፡ የሚያወሩትን ፡ መሠረተ ፡ ቢስ ፡ ወሬ ፡ የማያጸድቁ ፡ መኾናቸውን ፡ በየቅኔዎቹ ፡ መልስ ፡ ላይ ፡ ጽፌ ፌልዎታለሁ ።

ኢትዮጵያውያን ፡ በክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካልና ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ አለ ፡ የሚለውን ፡ ትምርት ፡ በመሠረቱ ፡ እንደሚቀበሉት ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡ ደርሰናል ፡ ስለሚሉትም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የማይቀበሉት ፡ መኾኑን ፡ በም ፡ ፩ ፡ በቍ ፡ ፯ ፡ በሰፊው ፡ ጽፈናል ። ያንን ፡ መመልከት ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፫/ ኢትዮጵያውያን ፡ በቃል ፡ ብቻ ፡ የካቶሊክን ፡ ትምርት ፡ አንቀበለውም ፡ የሚሉበትና ፡ የሚቃወሙበት ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ ስለሚመስላቸው ፡ መኾኑን ፡ አይተናል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፫/ ኢትዮጵያውያን ፡ የካቶሊክን ፡ ትምርት ፡ የማይቀበሉት ፡ ከንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ከመኾኑም ፡ በላይ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ከነን ፡ የሚያስተባብል ፡ ኾኖ ፡ ስላገኙት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ መስሏቸው ፡ አይደለም ። ምክንያቱም ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ።

፩ኛ ፡ ኹለቱም ፡ ወገኖች ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ በማለት ፡ አንድ ፡ ስለኾኑ ፡ የንስጥሮስና ፡ የካቶሊክ ፡ ትምርት ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ቢባል ። ብዙ ፡ ሐተታ ፡ የሚያስፈልገው ፡ አይደለም ።

ኹለተኛም፡ የካቶሊክ ፡ ትምርት ፡ ከንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ አልፎ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኾነ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ያስተባብላል ፡ ያልንበት ፡ ምክንያት ፡ ንስጥሮስ ፡ ለመለኮትም ፡ ለትስብእትም ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ አካል ፡ እንዳላቸው ፡ አምኖ ፡ ባሕርይ ፡ ያለው ፡ አካለ ፡ መለኮት ፡ ባሕርይ ፡ ባለው ፡ አካለ ፡ ሰብእ ፡ አደረ ፡ እንጂ ፡ አልተዋሐደም ፡ ብሎ ፡ ነበረ ።

የካቶሊክ ፡ ትምህርት ፡ ግን ፡ አካልም ፡ ባሕርይም ፡ ያለው ፡ ለመለኮት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለትስብእት ፡ ከባሕርይ ፡ በቀር ፡ አካል ፡ የለውም ፡ ይልና ፡ የክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ ፡ ይላል ። አካል ፡ ተዋሐደ ፡ እንዳይባል ፡ ለትስብእት ፡ ባሕርይ ፡ እንጂ ፡ አካል ፡ የለውም ፡ ይላል ፤ ባሕርይ ፡ ተዋሐደ ፡ እንዳይባል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ ነው ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ አካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ የሚለው ፡ አነጋገር ፡ የቃል ፡ ብቻ ፡ መኾኑ ፡ ነው ።

አካላዊ ፡ ተዋሕዶ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በከዊን ፡ ሳይኾን ፡ በአነጋገር ፡ ብቻ ፡ ከኾነ ፡ ወንጌላዊ ፡ ቃል ፡ ሥጋ ፡ ኾነ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ የካቶሊክ ፡ ትምርት ፡ ያስተባብለዋል ፡ የሚያሰኝ ፡ ስለኾነ ፡ ነው ።

፬/ በተለይም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ስለቅብዐቱ ፡ ክርክር ፡ ባህል ፡ የማይስማሙ ፡ ወገኖች ፡ ኹለት ፡ ብቻ ፡ መኾናቸውን ፡ እነርሱም ፡ እኛ ፡ የጎጃምና ፡ የትግሬ ፡ ኹለት ፡ ልደት ፡ ቅብዐት ፡ ወይም ፡ ካራ ፡ የተባለው ፡ ወገን ። ፪ኛ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ፫ ፡ ልደት ፡ ተዋሕዶ ፡ ወይም ፡ የጸጋ ፡ ልጅ ፡ የተባለው ፡ ወገን ፡ መኾናቸውን ፡ በመረመርናቸው ፡ ምንጮች ፡ መሠረት ፡ ተረድተናል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፬/ በቅብዐቱ ፡ ባህል ፡ ምክንያት ፤ የማይስማሙትን ፡ ወገኖች ፡ በእውነት ፡ እንዳላወቋቸው ፡ ግልጥ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ ቢያውቁትም ፡ ባያውቁትም ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነገር ፡ ስለኾነ ፡ ይህንን ፡ ወደ፡ ጐን ፡ ትተን ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የምንሰጠው ፡ መልስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ማንኛውም ፡ ወገን ፡ ቢሆን ፡ የካቶሊክን ፡ ትምርት ፡ የኹለት ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ተቀባይ ፡ አለመኖሩን ፡ ብቻ ፡ ነው ። ም ፡ ፩ ፡ ክፍል ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፩ ፡ ተመልከት ።

## ደ ፉ ሲ ።

፭/ የደብረ ፡ ሊባኖስ፡ ባህል ፡ ከካቶሊክ ፡ ትምርት ፡ ጋራ ፡ ፈጽሞ ፡ የተስማማ ፡ መኾኑ ፡ የባህል ፡ መግለጫቸውን ፡ በቀጥታ ፡ በመመርመር ፡ እንዲሁም ፡ ተከራካሪዎቻቸው ፡ ካቶሊክ ፡ ናቸው፡ ብለው ፡ በሚያሟቸው ፡ መሠረት ፡ ይታወቃል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፭/ የደብረ ፡ ሊባኖስና ፡ የካቶሊክ ፡ ትምህርት ፡ የተስማማ ፡ አንድ ፡ ከኾነ ፡ ባዜ ፡ ሱስንዮስ ፡ ጊዜ ፡ የካቶሊክ ፡ ሰባኪዎች ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስን ፡ መነኮሳት ፡ ለምን ፡ አስደበደብዋቸው ፡ ባዜ ፡ ፋሲልስ ፡ ጊዜ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖሱ፡ አበ ፡ ምኔት ፡ ዕጨጌ ፡ በትረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ተከራክረው ፡ ረተው ፡ ከሀገር ፡ አስወጥተው ፡ ለምን ፡ ሰደድዋቸው ፡ ይህ ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ተከራካሪዎቻቸው ፡ ካቶሊካውያን ፡ ናቸው ፡ እያሉ ፡ ያምዋቸዋል ፡ ለሚሉትም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲከራከሩ ፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ ኹለተኛውን ፡ ወገን ፡ አንተ ፡ ካቶሊክ ፡ ብሎ ፡ ቢሰድበው ፡ ያም ፡ መልሶ ፡ ካቶሊክ ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አይደለሁም ፡ እያሉ ፡ መነቃቀፊያ ፡ አድርገው ፡ ሲነጋገሩበት ፡ ይታያሉ ፡ እንጂ ፡ የማንኛቸውንም ፡ ወገን ፡ ቢኾን ፡ የያዘ ፡ ባህል ፡ ለካቶሊክ ፡ ባህል ፡ በእርግጥ ፡ ተስማሚ ፡ ኾኖ ፡ ተገኝቶ ፡ በዚህ ፡ ስም ፡ የሚጠራ ፡ የለም ።

ፍርድ ፡ መባልስ ፡ የሚገባው ፡ ከኹለታችንም ፡ ወገን ፡ ፍርዱ ፡ ያልተስማማው ፡ ቢኖር ፡ ይግባኝ ፡ ይጠይቃል ፡ እንጂ ፡ እርስዎ ፡ የጸፉትን ፡ እኔ ፡ የመለስኩትን፡ በሚዛናዊ ፡ አስተያየት ፡ ተመልክቶ ፡ የሚጽፍ ፡ ሌላ ፡ ፫ኛ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ያ ፡ ነው ። ከላይ ፡ እንደገለጽኩት ፡ እርስዎ ፡ ከሣሽ ፡ እርስዎ ፡ መላሽ ፡ እርስዎ ፡ ዳኛ ፡ ኾነው ፡ የሰጡት ፡ ፍርድ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነውና ፡ ፍርድ ፡ የሚለውን ፡ እርኅስት ፡ ሊሠርዙት ፡ ይገባል ።

## ጠቅላይ ፡ መደምደሚያ ።

### ደ ራ ሲ ።

ጠቅላይ ፡ መደምደሚያ ፡ በሚል ፡ አርእስት ፡ ተንሥተው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ አዋሐድ ፡ የሚያምኑትና ፡ የሚያስተምሩት ፡ ምን ፡ እንደኾነ ፡ በበለጠ ፡ አኳኋን ፡ ለመረዳት ፡ ለመጽሐፉ ፡ ጠቅላይ ፡ መደምደሚያ ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። አሁን ፡ የምንፈልገው ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹን ፡ ጉዳዮች ፡ ባጭሩ ፡ በመጠቅለል ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የኾኑትን ፡ ማስረጃዎች ፡ አስማምቶና ፡ አንድ ፡ ላይ ፡ አደራጅቶ ፡ ማቅረብ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

፩/ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ የጻፉት ፡ ያነኑ ፡ ያለፈውን ፡ መልስ ፡ የተሰጠበትን ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ነው ። ለኹሉም ፡ ተገቢ ፡ መልስ ፡ የተሰጠበት ፡ ስለኾነ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ መልስ ፡ የሚያስፈልጋቸው ፡ ነገሮች ፡ ካልተገኙ ፡ በቀር ፡ ያለፈውን ፡ መልስ ፡ ከማስታወስ ፡ በቀር ፡ ኹለተኛ ፡ ሌላ ፡ መልስ፡ መስጠት ፡ አስፈላጊ ፡ ኾኖ ፡ አላገኘሁትም ።

### ደ ራ ሲ ።

፪/ ይህን ፡ ምርመራቸውን ፡ ሲያነቡት ፡ ፈጥኖ ፡ የሚረዳው ፡ ነገር ፡ የኢትዮጵያና ፡ የሮም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ አለመስማማት ፡ በእስላሞችና ፡ በእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ምክንያት ፡ የደረሰው ፡ የረዥም ፡ ጊዜ ፡ መለየት ፡ ያስከተለው ፡ መዘዝ ፡ እንጂ ፡ በሃይማኖት ፡ ትምርት ፡ በኩል ፡ ከመራራቅ ፡ የተነሣ ፡ አለመኾኑ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

### መ ላ ሽ ።

፪/ ይህ ፡ ነገር ፡ ለርስዎ ፡ ስለመሰለዎ ፡ ለሌላውም ፡ የሚመስለውና ፡ የሚረዳው ፡ መስሎዎ ፡ እንዲህ ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡ ሮማና ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተለያዩ ፡ በሃይማኖት ፡ አይደለም ፡ እስላሞችና ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ባመጡት ፡ መዘዝ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሚያምን ፡ የለም ። የተለያዩበትን ፡ ምክንያት ፡ በም ፡ ፩ ፡ በቍ ፡ ፱ ፡ ጽፌአለሁ ፡ ያነን ፡ ይመልከቱ ።

### ደ ራ ሲ ።

፫/ እንደ ፡ እውነቱም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከግብጽ ፡ ጋራ ፡ አብራ ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ የመሸፈቷን ። ዓላማ ፡ አምርታ ፡ አልተነሣችም ፡ የጉባኤውንም ፡ ትምርት ፡ አልተቃወመችም ፡ ብለዋል ።

### መ ላ ሽ ።

፫/ ትምህርቱን ፡ ካልተቃወመች ፡ ባ፬ ፡ ሱስንዮስ ፡ ጊዜ ፡ በብዙ ፡ ሽህ፡ የሚቆጠሩ ፡ ልጆቿን ፡ ለምን ፡ አሳረደች ፡ ባ፮ ፡ ፋሲል ፡ ጊዜ ፡ ተከራክራ ፡ ረትታ ፡ የካቶሊክን ፡ ሰባኪዎች ፡ ጠራርጋ ፡ ለምን ፡ አስወጣች ፡ ተስማምታ ፡ አትኖርም ፡ ኖሯልን ፡ ይህ ፡ ፍሬ ፡ ቢስ ፡ ምኞት ፡ ነው ፡ ጠቅላላው ፡ መልሱ ፡ በም ፡ ፮ ፡ በገጽ ፡ ፪፻፱ ፡ በቍ ፡ ፳ ፡ ተጽፏል ፡ ያን ፡ ይመልከቱ ።

### ደ ራ ሲ ።

፬/ ከመረመሯቸው ፡ ምንጮች ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የአውጣኪን ፡ ባህል ፡ የሚከተሉ ፡ እውነተኞች ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ አለመኾናቸውን ፡ እንረዳለን ፡ ፩ ፡ ባሕርይ ፡ ሲሉም ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ህልው ፡ መኾኑን ፡ ለማስረዳት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በእሱ ፡ ኹለት ፡ ያልተደባለቁ ፡ ባሕርያት ፡ መገኘታቸውን ፡ ለመካድ ፡ አይደለም ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የሚሉትም ፡ ኹለት ፡ አካላት ፡ የሚለውን ፡ የንስጥሮስን ፡ ባሀል ፡ ለመቃወም ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

### መ ላ ሽ ።

፬/ የአውጣኪን ፡ ባህል ፡ የማንቀበል ፡ መኾናችንን ፡ ስላወቁልን ፡ እናመሰግንዎታለን ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የሚሉ ፡ በክርስቶስ ፡ ኹለት ፡ ያልተደባለቁ ፡ ባሕርያት ፡ መገኘታቸውን ፡ ለመካድ ፡ አይደለም ፡ ስለሚሉት ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የምንልበትን ፡ ምክንያት ፡ የቱሳሔን ፡ የውላጤን ፡ ነገር ፡ በጻፍንበት ፡ አንቀጽ ፡ በሰፊው ፡ የዘረዘርነው ፡ ስለኾነ ፡ አኹን ፡ ደግሞ ፡ መጻፍ ፡ አላስፈለገም ።

አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ማለታቸው ፡ ኹለት ፡ አካል ፡ የሚለውን ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ ብቻ ፡ ለመቃወም ፡ ነው ፡ ያሉትም ፡ ፍጹም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ በእርግጥ ፡ የምንቃወም ፡ በአንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የሚለውንም ፡ ባህል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የንስጥሮስን ፡ ባህል ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

### ደ ራ ሲ ።

፩/ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባይ ፡ ተብላ ፡ የመጠራትዋ ፡ በቂ ፡ ምክ
ንያት ፡ በኬልቄዶኑ ፡ ጉባኤ ፡ ተሻሽሎ ፡ የተወሰነውን ፡ አነጋገር ፡ ትታ ፡ ከኬልቄዶኑ ፡ ጉባኤ ፡ በፊት ፡
በቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ይነገርበት ፡ የነበረውን ፡ አነጋገር ፡ በመያዝዋ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

### መ ላ ሽ ።

፩/ ይህ ፡ አነጋገር ፡ ምንም ፡ ሐሰት ፡ ያልተቀላቀለበት ፡ እውነተኛ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ወደፊትም ፡
ቢኾን ፡ እስከ ፡ ቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ድረስ ፡ ጸንቶ ፡ የኖረውን ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የሚ
ለውን ፡ ባህል ፡ ልንለውጠው ፡ አንፈቅድም ። ምክንያቱም ፡ የመንፈሳዊ ፡ አስተዳደር ፡ ምግባር ፡
እንደ፡ጊዜው ፡ አኳኋን ፡ አይቶ ፡ ቢሻሻል ፡ ይቻላል ፡ እንጂ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ቃል ፡ ተመሥርቶ ፡ በሐዋርያት ፡ ስብከት ፡ ጸንቶ ፡ በሊቃውንት ፡ ጉባኤ ፡ ተስፋፍቶ ፡ የቆየውን ፡
ሃይማኖት ፡ ላሻሽል ፡ ማለት ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ወካልአሰ ፡ መሠረተ ፡ አልቦ ፡ ዘይክል ፡ ሣርሮ ፡ ዘእ
ንበለ ፡ ዘተሣረረ ፡ ወመሠረቱሂ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ውእቱ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፲፩ ።

አነክረክሙ ፡ እፎ ፡ ከመዝ ፡ ፍጡነ ፡ ትፈልሱ ፡ እምሃይማኖተ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘጸውዐክሙ ፡ በጸ
ጋሁ ፡ ውስተ ፡ ካልእ ፡ ትምህርት ፡ ዘኢኮነ ፡ ህልወ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘየሀውኩክሙ ፡ ወይፈቅዱ ፡ ይዕልዉ ፡
ትምህርቶ ፡ ለክርስቶስ ፡ አንትሙሰ ፡ ዐሠረ ፡ ዚአነ ፡ ትልዉ ፡ አንትሙሰ ፡ መልአክ ፡ እምሰማይ ፡
ለእመ ፡ መሀረክሙ ፡ ካልአ ፡ እምዘ ፡ መሀርናክሙ ፡ ውጉዘ ፡ ለይኩን ፡ ብሎ ፡ ያወጀልንን ፡ ዐዋጅ ፡
ማፍረስ ፡ ስለሆነ ፡ ነው ። ገላ ፡ ፩ ፡ ፮ ።

ይህ ፡ የሚመኙት ፡ አንድነትም ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ ያመጣችውን ፡
ማሻሻል ፡ ትታ ፡ አባቶቻችን ፡ እነቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ በሔዱበት ፡ ጥንታዊ ፡ መንገድ ፡ ካልገቡ ፡ በቀር ፡
የሚገኝ ፡ አይመስለኝም ።

### ደ ራ ሲ ።

፪/ በግብር ፡ ግን ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሕዶ ፡ የሚያምኑት ፡ ትም
ርት ፡ የቀና ፡ መኾኑ ፡ በፍጹም ፡ የማያጠራጥር ፡ ነው ፡ ይህም ፡ የሚታወቀው ፡ ባህላቸውንና ፡ ለካ
ቶሊክ ፡ ትምህርት ፡ የሚቃወሙትን ፡ ምክንያት ፡ በመመርመር ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

### መ ላ ሽ ።

፪/ ይህ ፡ የሚመኙት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድነት ፡ እኛም ፡ የምንመኘው ፡ ታላቅ ፡ ቁም ፡
ነገር ፡ ነው ። እኛ ፡ ካባቶቻችን ፡ ያገኘነውን ፡ ጥንታዊ ፡ ባህል ፡ ትተን ፡ ወደዚያ ፡ እንዳንመጣ ፡ ይህ ፡
የተሻሻለው ፡ የካቶሊካውያን ፡ ባህል ፡ ከመጻሕፍት ፡ ግብ ፡ የወጣ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ በመኾኑ ፡ ልንቀ
በለው ፡ አልቻልንም ።

እርስዎ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ እኛ ፡ የያዝነው ፡ ባህል ፡ በመሠረቱ ፡ ከጉባኤ ፡ ኬልቄዶን ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡
አባቶች፡እነቅዱስ ፡ ቄርሎስ ፡ ይዘውት ፡ የነበረው ፡ ባህል ፡ ምንም ፡ ያልተሻሻለ ፡ መሆኑን ፡ የካቶ
ሊክ ፡ ባህል ፡ ግን ፡ አሁን ፡ የቀና ፡ መኾኑ ፡ በፍጹም ፡ የማያጠራጥር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከተረዱት ፡ ወደ
ዚሁ ፡ ተመልሰው ፡ ካባቶቻችን ፡ የተገኘ ፡ የቀና ፡ መኾኑ ፡ ያለጥርጥር ፡ በታወቀበት ፡ ባህል ፡ አንድ ፡
ብንኾን ፡ ምን ፡ የሚያስቸግርዎ ፡ ነገር ፡ አለ ፡ በእውነቱ ፡ እንዲህ ፡ እየታወቀዎ ፡ እልክ ፡ ይዞዎ ፡
እንቢ ፡ ቢሉ ፡ ያዋቂ ፡ አጥፊ ፡ ተብለው ፡ እንደሚፈረድብዎ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

### ደ ራ ሲ ።

፫/ የሥርዓት ፡ አምልኮንና ፡ የሃይማኖት ፡ ትምርት ፡ መጻሕፍቶቻቸውን ፡ እንዲሁም ፡ ሌሎች ፡
ጽሑፎቻቸውን ፡ ብንመለከት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በክርስቶስ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ልዩ ፡ የኾኑ ፡ ከተዋ
ሕዶም ፡ በኋላ ፡ ሳይቀላቀሉ ፡ የሚቀሩ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ የማይታመም ፡ መለኮትና ፡ የሚታመም
ትስብእት ፡ መገኘታቸውን ፡ እንደሚያምኑ ፡ እናገኛለን ፡ ብለዋል ።

### መ ላ ሽ ።

፫/ የሥርዓት ፡ አምልኮና ፡ የሃይማኖት ፡ ትምርት ፡ ያሏቸውን ፡ መጻሕፍቶች ፡ ገልጠዋቸው ፡
ቢኾን ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ በተመቸ ፡ ነበረ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ስላልገለጿቸው ፡ አስቸጋሪ ፡ ኾኗል ፡
ከተዋሕዶ ፡ በኋላ ፡ ሳይቀላቀሉ ፡ የሚቀሩ ፡ ፪፡ ባሕርያት ፡ ስለሚሉት ፡ መልሱን ፡ በም፡፩፡ በቍ፡፵፡
፵፩ ፡ ይመልከቱ ።

ደ ራ ሲ ።

፰/ ባሕርይ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ዘንድ ፡ የካቶሊክ ፡ መምህራን ፡ ከሚሰጡት ፡ ትርጉም ፡ ልዩ ፡ የኾነ ፡ አሳብ ፡ ያሰማል ፡ ደሞ ፡ አካል ፡ ወይም ፡ ኳኝ ፡ ከሚለው ፡ ጋራ ፡ ያወራርሱታል ፡ ስለዚህ ፡ በክርስቶስ ፡ ፪ ፡ ባሕርያት ፡ አሉ ፡ ሲባል ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ፪ ፡ አካላት ፡ አሉ ፡ እንደሚለው ፡ እንደ ፡ ንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ ኾኖ ፡ ይሰማቸዋል ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፰/ ስለባሕርይና ፡ ስለአካል ፡ በም ፡ ፬ ፡ በቍ ፡ ፳፰ ፡ በሰፊው ፡ ስለተጻፈ ፡ ያነን ፡ ይመልከቱ።

ደ ራ ሲ ።

፱/ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ፩ ፡ ባሕርይ ፡ የሚለው ፡ የኢትዮጵያኖቹ ፡ አነጋገር ፡ ጠንቅቀን ፡ ብናስተውልበት ፡ ፪ ፡ ባሕርያት ፡ ለሚለው ፡ ለካቶሊክ ፡ አነጋገር ፤ ተቃራኒ ፡ አይደለም ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፱/ ፩ ባሕርይ ፡ የሚለው ፡ አነጋገር ፡ ለካቶሊኮች ፡ ባህል ፡ ተቃራኒ ፡ ካልኾነ ፡ እንደ ፡ ቀደሙ ፡ አባቶቻችን ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ አይሉምና ፡ እንስማማምን ፡ ምን ፡ ያጣላናል ።

ደ ራ ሲ ።

፲/ በጣም ፡ የታወቀውን ፡ የቅብዐትን ፡ ክርክር ፡ ስንመረምር ፡ ብለው ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ በሚለያይ ፡ ስሜት ፡ ለመጻፍ ፡ ሞክር ፡ አድርገዋል ።

መ ላ ሽ ።

፲/ ይህ ፡ አነጋገር ፡ እርስዎን ፡ የሚያገባዎ ፡ አይደለም ፡ ብዬ ፡ እንደገለጽኩልዎ ፡ አሁንም ፡ እንደዚያው ፡ ነው ።

ደ ራ ሲ ።

፲፩/ ኢትዮጵያውያን ፡ እውነተኛውን ፡ ያንድ ፡ ባሕርይን ፡ ባህል ፡ ያምናሉ ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ፡ ምክንያቱም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተለየችበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ምክንያት ፡ የሚገልጥ ፡ ደንበኛ ፡ ጽሑፍ ፡ በታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የማይገኝ ፡ በመኾኑ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፲፩/ የዚህም ፡ መልሱ ፡ ባለፈው ፡ በም ፡ ፫ ፡ በገጽ ፡ ፳፯ና ፡ ፳፰ ፡ በቍ ፡ ፳ና ፡ ፳፪ ፡ ስለተጻፈ ፡ ያነኑ ፡ መመልከት ፡ ነው ።

ደ ራ ሲ ።

፲፪/ ፪ኛውም ፡ ምክንያት ፡ ያንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባህል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሊስፋፋ ፡ አለመቻሉ ፡ ነው ። ሊስፋፋ ፡ አለመቻሉም ፡ ከግብጽ ፡ ተሾመው ፡ የሚመጡትን ፡ ጳጳሳት ፡ ስለሚቈጣጠሩዋቸው ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲገቡ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ባህል ፡ ጋራ ፡ የሚስማማ ፡ ተአምኖተ ፡ ሃይማኖት ፡ ሊደግሙ ፡ ይገደዱ ፡ ነበረ ፡ በኢያሱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ዘመን ፡ መንግሥትም ፡ አባ ፡ ሲኖዳ ፡ የሚባለውን ፡ ግብጻዊ ፡ ጳጳስ ፡ የደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ወገን ፡ ያምኑት ፡ የነበረውን ፡ ባህል ፡ አልቀበልም ፡ በማለቱ ፡ እንዳባረሩት ፡ በታሪክ ፡ ይነገራል ፡ ብለዋል ።

መ ላ ሽ ።

፲፪/ ይህም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ መላልሼ ፡ እንዳስረዳሁት ፡ ኢትዮጵያ ፡ አሁን ፡ ይዛው ፡ የምትገኘውን ፡ አንድ ፡ አካል ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ የሚለውን ፡ ባህል ፡ ይዞ ፡ ተገኝቶ ፡ የተነቀፈና ፡ የተባረረ ፡ የለም ።

ደ ራ ሲ ።

፲፫/ እኒህ ፡ ከግብጻውያን ፡ ጳጳሳት ፡ ለመጠንቀቂያና ፡ ለመጠባበቂያ ፡ ተብለው ፡ የተደረጉ ፡ ሥራዎች ፡ ከየት ፡ ዘመን ፡ እንደጀመሩ ፡ በእርግጥ ፡ ልናውቀው ፡ አልተሰጠንም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የካቶ

ሊክ ፡ ጳጳስ ፡ መምጣት ፡ አቋርጦ ፡ ቆይቶ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዩ ፡ የእስክንድርያው ፡ ጳጳስ ፡ ከገባበት ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ የተለመደ ፡ ይኾናል ፡ ተብሎ ፡ ቢታሰብ ፡ ከእውነት ፡ የራቀ ፡ አይመስልም ፡ ብለዋል ፡

## መ ላ ሽ ።

፲፫/ ኢትዮጵያ ፡ በእስክንድርያ ፡ መንበረ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ስትመራ ፡ መቆየቷን፡ይኸውም፡ የተጀመረ ፡ በ፫፻፴፩ ፡ ዓ/ም ፡ ግድም ፡ በፍሬምናጦስ ፡ መኾኑን ፡ እርስዎ ፡ ራስዎ ፡ በዚሁ፡ መጽሐፍ ፡ በገጽ ፡ ፵፫ ፡ አረጋግጠው ፡ ጽፈዋል ፡ የሮም ፡ ካቶሊክ ፡ ጳጳሳት ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ፤ መግባት ፡ በሕግ ፡ መብት ፡ ያላቸው ፡ ለመኾኑ ፡ ስንኳን፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ርስዎ ፡ ራስዎም ፡ ቢኾኑ ፡ የተናገሩበት፡ አንቀጽ ፡ የለም ።

በ፱፻ ፡ ሱስንዮስም ፡ ጊዜ ፡ መጥቶ ፡ የነበረው ፡ አልፎንሱ ፡ የተባለው ፡ አመጣጡ ፡ ከሕግ፡ ውጭ ስለኾነ ፡ በሕግ ፡ ተባሮ ፡ የሔደ ፡ መኾኑ ፡ ግልጽ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ በጉልህ ፡ በግልጥ ፡ የሚታወቀውን፡ ነገር ፡ ሲደረግ ፡ የኖረ ፡ አስመስሎ ፡ የካቶሊክ ፡ ጳጳስ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መምጣት ፡ አቋርጦ ፡ ቆይቶ ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዩ ፡ የእስክንድርያ ፡ ጳጳስ ፡ ከገባባት ፡ ጊዜ ፡ ወዲህ ፡ የተለመደ ፡ ይኾናል ፡ ብሎ ፡ መናገር ፡ አያሳፍርምን ፡ እኔስ ፡ እንኳን፡ መናገሩ ፡ ማሰቡም ፡ ያሳፍረኛል ፡ በጠቅላላው ፡ ይህ ፡ አነጋ ገር ፡ እንኳንስ ፡ ራሱ ፡ እውነተኛ ፡ ኾኖ ፡ ተቀባይ ፡ ሊያገኝ ፡ ሌላውንም ፡ የእውነት ፡ መሠረት ፡ ሳይ ኖረው ፡ በይኾናልና ፡ በይመስላል ፡ ብቻ ፡ የመሠረተውን ፡ ንግግር ፡ ኹሉ ፡ የሚንድ ፡ ሐሰት ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፬/ ይህ ፡ ባህል ፡ የሚያስተምረውና ፡ የሚሰብከው ፡ ካላገኘ ፡ እንደምን ፡ ሊስፋፋ ፡ ይችላል፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የግብጽን ፡ ትምህርት ፡ ከተቃወሙት ፡ የ፪ቱ ፡ ትምርት ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ሊባል፡ እንደምን ፡ ይቻላል ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፬/ ግብጽና ፡ ኢትዮጵያ ፡ የተለያዩበት ፡ የሃይማኖት ፡ ምክንያት ፡ ሳይኖር ፡ እንዲህ ፡ እያሉ ፡ ማውራት ፡ ልክስክስ ፡ ሰው ፡ የሚያወራው ፡ የሰብቀ ፡ መንገድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ንግግር፡ አይደለም ፡ እውነትማ ፡ ከኾነ ፡ ከእኛ ፡ አንደበት ፡ ይገኝ ፡ አልነበረምን።

## ደ ራ ሲ ።

፲፭/ ኢትዮጵያውያን፡ለካቶሊክ ፡ ክርስቶስ፡ባሕርያት ፡ አዋሕድ ፡ ትምርት ፡ የሚቃወሙት፡ እንደ፡ንስጥሮስ ፡ ባህል ፡ ስለሚመስላቸው ፡ ነው ፡ የኢትዮጵያና ፡ የካቶሊክ ፡ ትምርት ፡ በመሠረቱ ፡ አንድ ፡ ሲኾን ፡ ለያይቷቸው ፡ ያለው ፡ ያነጋገር ፡ ልዩነት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሃይማኖት ፡ ትምርት ፡ አለመስማማት ፡ አይደለም ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፭/ ይህ ፡ ኹሉ ፡ የነገር ፡ አካባቢ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከእስክንድርያ ፡ ለይቶ ፡ ከሮማ ፡ ቤተ፡ ክር ስቲያን ፡ ሥር ፡ ለመጣል ፡ ነው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሃይማኖቷን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ጠንቅቃ ፡ የተረዳችው ፡ ስለኾነ ፡ በይመስላልና ፡ በይኾናል ፡ የምትለወጥ ፡ አይደለችምና ፡ በከንቱ ፡ አይድከሙ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፮/ በጠቅላላው ፡ በኢትዮጵያ፡ ስለ፡ክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ የሚታመነው ፡ ትምህርት፡በእስክ ንድርያ ፡ ከሚያስተምሩት፡ ባህል ፡ ጋራ ፡ ማናቸውም ፡ ተመሳሳይነት ፡ የለውም ፡ ብሎ ፡ መካድ ፡ አይቻልም ፡ ምክንያቱም ፡ የእስክንድርያ ፡ ሊቃውንት ፡ ክርስቶስን ፡ ይበልጥ ፡ በትስብእቱ፡በኩል ፡ መመልከት ፡ ከመውደዳቸውም ፡ የተነሣ ፡ በእርሱ ፡ ሁለት ፡ አካል ፡ አሉ ፡ ወደማለት ፡ ፡ ለደረሱት፡ ለአንጾኪያ ፡ ሊቃውንት ፡ ተቃራኒ ፡ ለመኾን ፡ ክርስቶስን ፡ በመለኮቱና ፡ ባንድነቱ ፡ በኩል ፡ ብቻ ፡ መመልከት ፡ ይመርጡ ፡ ስለነበር ፡ ትስብእቱን ፡ ቸል ፡ በማለትና ፡ በማጥፋት ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ እስከ ማለት ፡ ድረስ ፡ ደርሰው ፡ ነበርና ፡ እንዲህ ፡ ካለ ፡ ባህላቸው ፡ ምናምን ፡ ትንሽ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሳይዘልቅ ፡ አልቀረም ፡ ይኾናል ፡ ስለሚያሰኝ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፮/ ሐሰት ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ ቢኾን ፡ ቀዋሚ ፡ ኾኖ ፡ ሊቀር ፡ የማይችል ፡ ስለኾነ ፡ እነሆ ፡ በላ ይኛው ፡ መሥመር ፡ በ፲፩ኛው ፡ ቍጥር ፡ የተናገሩትን ፡ ርስዎ ፡ ራስዎ ፡ አፍርሰው ፡ የእስክንድርያና፡

የኢትዮጵያ ፡ የሃይማኖት ፡ ትምርት ፡ አንድ ፡ መኾኑን ፡ መሰከሩ ፡ ትስብእቱን ፡ ቸል ፡ በማለትና ፡ በማጥፋት ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ወደማለት ፡ ደርሰዋል ፡ ስለሚሉት ፡ ትስብእቱን ፡ ቸል ፡ የማንልና ፡ የማናጠፋ ፡ መኾናችንና ፡ አንድ፡ባሕርይ ፡ የምንልበትን ፡ ባለፈው ፡ ጽሑፋችን ፡ በሰፊው ፡ ዘርዝረን ያስረዳን ፡ ስለኾነ ፡ ከዚህ ፡ መድገም ፡ አያስፈልግም ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፯/ ኢትዮጵያውያኖቹ ፡ የእስክንድርያ ፡ መምህራን ፡ እንደሚያደርጉት ፡ ዘለዓለማዊውን ፡ ቃል ፡ በመለኮቱ ፡ በኩል ፡ መመልከትን ፡ በመምረጥ ፡ ከባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ጋራ ፡ ከመዋሐዱ፡በፊትም ፡ ኾነ ፡ ወይም ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ኋኝ ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ሕልው ፡ መኾኑን ፡ ወደ ፡ ማሳየት ፡ ያዘንብላሉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በምሥጢረ ፡ ሥጋዌ ፡ ከመዋሐዱም ፡ በኋላ ፡ ለባሕርየ፡ ትስብእት፡ እንደታማሚነት ፡ ያለ ፡ የሰውነትን ፡ ሥራዎች ፡ ወይም ፡ ግብሮች ፡ ስለሚሰጡት ፡ በክርስቶስ ፡ ባሕርየ ፡ ትስብእት ፡ ጠፋ ፡ እንደሚሉ ፡ የሚያስረዳ ፡ ምስክር ፡ ምንም ፡ አይገኝም ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፯/ እርግጥ ፡ ነው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ክርስቶስ ፡ በመለኮቱ ፡ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ የነበረ ፡ አምላክ ፡ መኾኑን ፡ ድኅረ ፡ ዓለም ፡ ከእመቤታችን ፡ በነሣው ፡ ሥጋ ፡ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ሠራ ፡ ከተዋሕዶም ፡ በኋላ ፡ ተፈልጦ ፡ እንደሌለበት ፡ እናምናለን ።

፲፰/ ከዚህም ፡ በላይ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ቃልና ፡ ትስብእት ፡ ከተዋሐዱ ፡ በኋላ ፡ ኹለቱ፡ባሕርያት ፡ ሳይለወጡና ፡ ሳይቀላቀሉ ፡ አንዱም ፡ ባንድ ፡ ውስጥ ፡ ሳይጠፉ ፡ በየራሳቸው ፡ ይኖራሉ ፡ ይላሉ ፡ ስለዚህ ፡ በክርስቶስ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የተዋሐዱ ፡ ቢኾኑ ፡ ምንም ፡ ሳይደባለቁ ፡ የቆሙ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ መኖራቸውን ፡ እንደሚያምኑ ፡ የማያጠራጥር ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፰/ የዚህ ፡ መልስ ፡ የውላጤ ፡ የቱሳሔ ፡ ነገር ፡ በተጻፈበት ፡ አንቀጽ ፡ ተብራርቶ ፡ የተጻፈ ስለኾነ ፡ ከዚህ ፡ መድገም ፡ አላስፈለገም ።

## ደ ራ ሲ ።

፲፱/ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ካልነው ፡ በክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፡ አዋሐድ ፡ ትምርት፡ በኢትዮጵያና፡በሮምያ ፡ መካከል ፡ የሚገኘው ፡ የመለያያ ፡ መጋረጃ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ የረቀቀ ፡ መኾኑ፡ ይረዳል ይህን ፡ መጋረጃ ፡ ቀዶ ፡ ለማስወገድ ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ሮማንም ፡ ለማስታረቅ ፡ ባለፈው ፡ ዶጋግመን፡ የገለጥነውን ፡ አሳብ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ብናስታውሰው ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ፡ ካሉ፡ በኋላ፡ ይህን፡ሲተረጕሙ፡ ባሕርይና ፡ አካል ፡ የሚሉትን ፡ የተራቀቁ ፡ ቃላት ፡ በወገናቸው ፡ ትተው ፡ ክርስቶስ ፡ ፍጹም፡ አምላክና ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ክርስቶስ፡የመለኮትና ፡ የትስብእት ፡ ባሕርያት ፡ አሉት ፡ ብለው፡ የትምህርቱን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ቢያቀርቡላቸው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የካቶሊክን ፡ የክርስቶስ፡ ባሕርያት አዋሐድ ፡ ትምርት ፡ ያላንዳች ፡ መቃወም ፡ ይቀበሉት ፡ ነበረ ፡ ማለታችን ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፲፱/ እርስዎ ፡ በሐሳብዎ ፡ እኛ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ በአባባና ፡ በሻንጉሊት ፡ እንደሚታለሉ ፡ ሕፃናት ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ መገመትዎን ፡ ባነጋገርዎ ፡ ተረድተናል ፡ እኛ ፡ ግን ፡ እርስዎ ፡ እንደሚገምቱን ፡ አይደለንምና፡ክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ቢሏቸው ፡ ያላንዳች፡ መቃወም ፡ ይቀበሉታል ፡ ለሚሉት ፡ ሐሳብ ፡ መልሱን ፡ የኬልቄዶንን ፡ ውሳኔ ፡ በጠቀሱበት ፡ በ፫ኛው ምዕራፍ ፡ በ፪ኛው፡ክፍል ፡ በ፳ኛው ፡ ቍጥር ፡ በንኡስ ፡ ቍ ፡ ፪ ፡ ጽፈንለዋልና ፡ ያንን ፡ ይመልከቱ ።

ኢትዮጵያውያን፡ክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ካሏቸው ፡ የአካልንና ፡ የባሕርይን ፡ ምሥጢር ፡ ሊደርሱበት ፡ አይችሉም ፡ ብለው ፡ ማሰብዎ ፡ እርስዎ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሊቃውንት ፡ መጠን ፡ ለማወቅ ፡ ያልቻሉ ፡ መኾንዎን ፡ ከማስገመቱ ፡ በቀር ፡ የነገሩ ፡ ውጤት ፡ እንዳሰቡት ፡ ኾኖ ፡ አይገኝም ።

## ደ ራ ሲ ።

፳/ ይኸ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ለመቀራረብና ፡ ለመግባባት ፡ ይልቅ ፡ ያጠረ ፡ መንገድ፡ እንደመኾኑ ፡ መጠን ፡ በሥራ ፡ እንዲውል ፡ ዐደራ ፡ እንላለን ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳/ ኢትዮጵያውያን ፡ ክርስቶስ ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ነው ፡ ማለትና ፡ ለክርስቶስ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ አሉት ፡ ማለት ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ንግግር ፡ መኾኑን ፡ አያውቁትም ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ አሉት ፡ ቢሏቸው ፡ ይታለላሉ ፡ ብሎ ፡ ከመገመት ፡ የበለጠ ፡ የሚያናድድ ፡ ነገር ፡ ስለሌለ፡ አደራዎን ፡ በከንቱ ፡ ጥለውታል ፡ ይህ ፡ አነጋገር ፡ የተናጋሪውንም ፡ አስተያየት ፡ ግምት ፡ በጣም፡ ዝቅ ፡ የሚያደርግ ፡ መኾኑን ፡ በተጨማሪ ፡ ሳላሳስብ ፡ አላልፍም ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፩/ በፕሮፓጋንዳ ፡ ፊደ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ አንድ ፡ ትልቅ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ያለውና ፡ እሳ ብችንንም፡የሚደግፍ ፡ ጽሑፍ ፡ ይገኛል ፡ እርሱም ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ነገሩን ፡ ሲዘረ ዝሩ ፡ ለኢትዮጵያውያን ፡ ስለ ፡ ባሕርያት ፡ ምንም ፡ ሳያነሡ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ወይም ፡ ክርስቶስ ፡ የሰው ፡ ባሕርይ ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ ማስተማር ፡ ይቻላልን ፡ ለሚል ፡ ሐተታ ፡ ማኅበሩ ፡ አዎን ፡ ሲል ፡ መልስ ፡ ሰጥቷል ።

እንዲሁም ፡ የመለኮት ፡ ባሕርይ ፡ አለው ፡ ብሎ ፡ ስለዚህ ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ አሉት ፡ ማለትን፣ ሳያስከትሉስ ፡ ለሚል ፡ ሐተታም ፡ ኹለት ፡ ባሕርያት ፡ ተቀላቀሉ ፡ ወይም ፡ ተደባለቁ ፡ አይበሉ፣ እንጂ ፡ አዎን ፡ ሃይማኖት ፡ ሳይበላሽ ፡ እንዲሁ ፡ ማስተማር ፡ ይቻላል ፡ ብሎ ፡ መልስ ፡ ሰጥቷል ብለዋል ።

፳፪/ ይህ ፡ የጠቀሱት ፡ ቃል ፡ በላይኛው ፡ መሥመር ፡ እኛ፡ስለተቃወምነው ፡ ስሕተታዊ ፡ አስተያየት ፡ ነቁ ፡ ምንጭ ፡ እኔ ፡ አይደለሁም ፡ ይህ ፡ ጉባኤ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ዋቢ ፡ ለማሳለፍ ፡ ይረዳ እንደኾነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ አስተያየት ፡ እውነተኛ ፡ ሕጋዊ ፡ አስተያየት ፡ ሊያደርገው ፡ አይች ልም ፡ ምክንያቱም ፡ ያስተያየቱ ፡ ውጤት ፡ በ፳ኛው ፡ ቍ ፡ እንደገለጽነው ፡ ስለኾነ ፡ ነው ።

እንግዲህ ፡ የጉባኤውን ፡ አስተያየት ፡ ወደ ፡ መመርመር ፡ እንመለስ ፡ እውነተኛ ፡ መምህር ፡ ተማሪዎቹ ፡ እርሱ ፡ ከደረሰበት ፡ እውቀት ፡ እስኪደርሱለት ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ የተደበቀ ፡ ነገር ፡ ሳይ ኖር ፡ በተቻለው ፡ መጠን ፡ ግልጥ ፡ አድርጎ ፡ ያስተምራል ። እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ያስተማረ ፡ መምህር ፡ ፀሩን ፡ ከመልካም ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ የጣለ ፡ ገበሬ ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ትምህርት ፡ ተምሮ ፡ ያመነ ፡ ደቀ ፡ መዝሙርም ፡ መናፍቃንን ፡ ተከራክሮ ፡ ይረታል ፡ በሃይማኖቱ ፡ ምክንያት ፡ መከራ ፡ ቢመጣበት ፡ ይመክታል ። ማቴ ፡ ፲፫ ፡ ፳ ፡ ፱ ።

ከዚህ ፡ በወጣ ፡ አኳኋን፡ የትምህርቱን ፡ ስሕተትነት ፡ ራሱ ፡ ተረድቶት ፡ ምሥጢሩ ፡ እንዳይዋ ለጽበት ፡ እውነት ፡ በማስመሰል ፡ ተንኮል ፡ ሸፋፍኖ ፡ አስተምሮ ፡ ያሳመነ ፡ መምህር ፡ መርዙን ፡ በማር ፡ ለውሶ ፡ እንደሚያውጥ ፡ ጠላት፡ ይቆጠራል።እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ መምህር ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ በምዕራፍ ፡ ፳፫፡ቍ፡፳፩፡ቍ፡፳፱፡ያለውን፡ኃይለ፡ ቃል ፡ ያወጀባቸው ፡ ወይም ፡ ያዳኘባቸው ፡ መምሀራን ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ትምርት ፡ ያመነ ፡ ደቀ ፡ መዝሙርም ፡ ሃይማኖቱን ፡ በሚገባ ፡ ስላልተረዳው ፡ መከራ ፡ ቢመጣበት ፡ ፈጥኖ ፡ ይክዳል ፡ ተከራካሪ ፡ ቢነሣበት ፡ ፈጥኖ ፡ ይረታል ፡ እንጂ ፡ መከራ ፡ ቢመጣበት ፡ ሊታገሥ ፡ ክርክር ፡ ቢቀርብለት ፡ ሊመልስ ፡ አይችልም ። ማቴ ፡ ፲፫ ፡ ፳ ።

እንግዲህ ፡ የጠቀሱት ፡ ጉባኤ ፡ የትምርቱን ፡ አሰጣጥ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የሚመራው ፡ ከኾነ ፡ ያታላዮች ፡ ጉባኤ ፡ ሊባል ፡ ይገባዋል ፡ እንጂ ፡ የእውነተኞች ፡ መምሀራን ፡ ጉባኤ ፡ ሊባል ፡ አይገ ባውም ።

## ደ ራ ሲ ።

፳፫/ ስለዚህ ፡ ኢትዮጵያውያንና ፡ ካቶሊክ ፡ በዚሁ ፡ በረዥም ፡ ዘመናት ፡ ለመለያየታቸው ፡ ዋና ፡ ምክንያት ፡ በኾነው ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ መስማማትን ፡ ለማግኘት ፡ በጣም ፡ አስቸጋሪ ፡ ወይም ፡ የማይቻል ፡ አይመስለንም ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፳፬/ ይህ ፡ መስማማት ፡ ያለችግር ፡ ሊገኝ ፡ ይቻል ፡ የነበረው ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ዕውቀት፣ እርስዎ ፡ ከሰጡት ፡ አስተያየት ፡ ግምት ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ በታች ፡ ኹኖ ፡ ቢገኝ ፡ ነበረ ። አሁን ፡ ግን ከላይ ፡ እንደገለጽኩሉዎ ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ዕውቀት ፡ እርስዎ ፡ ከሰጡት ፡ አስተያየት ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ኾኖ ፡ ስለሚገኝ ፡ ምኞትዎ ፡ ከንቱ ፡ ምኞት ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፹፫/ ይህ ፡ አለመስማማታቸው ፡ ካንጋገር ፡ ልዩነት ፡ ብቻ ፡ የተነሣ ፡ ስለኾነ ፡ እርሱን ፡ ለማጥፋት ፡ ካቶሊኮችም ፡ ኢትዮጵያውያኖችም ፡ አብረው ፡ በማጥናት ፡ ምሥጢረ ፡ አካላዊ ፡ ተዋሕዶን፡ ለመግለጥ ፡ የሚበቁና ፡ ትክክለኛ ፡ የኾኑ ፡ ቃሎችን ፡ የሚወስኑበት ፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ ቢቋቋም ፡ የክርስቲያኖች ፡ መቀራረብ ፡ ተብሎ ፡ ቢጠራ ፡ የተሻለ ፡ ነገር ፡ ኾኖ ፡ ይታየናል ።

ነገር ፡ ግን ፡ ወደሚፈለገው ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ የእርስ ፡ በርስ ፡ ፍጹም ፡ መግባባት ፡ እንዲኖር ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ እንዲሁም ፡ የተለመደው ፡ የእርስ ፡ በርስ ፡ መተማማትና ፡ ባልኾነው ፡ መነቃቀፍ ፡ ቀርቶ ፡ እንደ ፡ ሥርዓት ፡ አምልኮና ፡ እንዳገሩ ፡ ልማዶች ፡ እንደ ፡ አባቶችም ፡ ወጎች፡ያሉ፡ ከሃይማኖት ፡ ትምርት ፡ ጋራ ፡ በጥብቅ ፡ የተያያዙ፡ ካልኾኑ ፡ ጥቃቅን ፡ ነገሮችን ፡ በወገናቸው ፡ ትቶ ፡ በመሠረታዊው ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ መስማማት ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፹፫/ ምናልባት ፡ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘይፈቅድ ፡ እምኔክሙ ይኩን ፡ ሊቀ ፡ ይኩንክሙ ላእከ ፡ ያለውን ፡ በመዘንጋት ፡ ከኹሉ ፡ በላይ ፡ መኾኗን ፡ አጥብቃ ፡ ስለምትፈልገው ፡ በሮማ ፡ መንበር ፡ የተቀመጠውን ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ዳግማዊ ፡ ክርስቶስ ፡ እስከ ፡ ማለት ፡ ደርሳለች ።

ከሊቃነ ፡ ጳጳሳቱም ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰማይንና ፡ የምድርን ፡ መንግሥት ፡ ሰጠን ፡ እያሉ ፡ ተውሀበ ፡ ሊተ ፡ ኵሉ ፡ ሰማይ ፡ ወምድር ፡ ያለውን ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ የመሰለ ፡ እንጋገር ፡ ለመናገር ፡ የደፈሩ ፡ አሉና ፡ የሮሙ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ከሌሎች ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ጋራ ፡ ተባብሮ ፡ መሥራቱ ቀር ፡ ያሰኘት ፡ እንደኾነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዚህ ፡ ሐሳብ ፡ ፈጽማ ፡ የምትስማማበት ፡ መኾኑን ፡ ስገልጽልዎ ፡ በውነቱ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

## ደ ራ ሲ ።

፹፬/ ከመ ፡ ኵሎሙ ፡ ይኩኑ ፡ ፩ደ ፡ በከመ፡እንተ ብየ ፡ ወአነሂ ፡ ብከ ፡ ሲል ፡ ክርስቶስ ፡ የተመኘው ፡ አንድነት ፡ ተገኝቶ ፡ ፩ ፡ መርዔት ፡ ለ፩ ፡ ኖላዊ ።

ባንድ ፡ እረኛ ፡ የሚጠበቅ ፡ አንድ ፡ መንጋ ፡ ለመኾን ፡ ተስፋ ፡ ልናደርግ ፡ የምንችለው ፡ እንዲህ ቢደረግ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

፹፬/ አንድ ፡ ኖላዊ ፡ የተባለ ፡ ቸር ፡ ጠባቂ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አብ ፡ እኔን ፡ እንደሚያውቀኝ ፡ እኔም ፡ አብን ፡ እንደማውቀው፡በጐች ፡ እኔን ፡ ያውቁኛል ፤ እኔም ፡ በጐቼን ፡ አውቃቸዋለሁ ፤ ስውነቴን ፡ ልበጐቼ፡ቤዛ ፡ አድርጌ ፡ ለሕማም ፡ ለሞት ፡ እሰጣለሁ ፡ ያለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

፭/ መርዔት ፡ የተባሉም ፡ ከዚህ ፡ ቦታ ፡ ያልኾኑ ፡ ሌሎች ፡ በጎች ፡ አሉኝ ፡ እነዚያንም ፡ አመጣቸው ፡ ዘንድ፡አለኝ ፡ የተባሉ ፡ ባራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ያሉ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ናቸው ። ባራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ያሉ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ኹሉ ፡ ባንድ ፡ አነጋገር ፡ የተለያዩ ፡ ቢመስሉም ፡ ኹሉም ፡ በየበኩላቸው ፡ አንድ ፡ ክርስቶስን ፡ አምነው ፡ በስሙ ፡ ተጠርተው ፡ የሚኖሩ ፡ ስለኾነ ፡ ወይከውና ፡ ፩ደ ፡ መርዔተ፡ ለ፩ ፡ ኖላዊ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ተፈጻሚ ፡ ኾኖ ፡ ይታያል ። ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፲፩-፲፯ ። እርስዎ ፡፡ ግን ፡ ተስፋ የሚያደርጉ ፡ ኖላዊ ፡ ኄር ፡ መባልን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አውጥተው ፡ ለሮም ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ሰጥተው ፡ ባራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ያሉ ፡ ክርስስቲያኖች ፡ ኹሉ ፡ ከሮሙ፡ ርእሰ፡ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ እግር ፡ ሥር ፡ እንዲንበረከኩ ፡ መኾኑን ፡ ገልጸዋል ። ምናልባት ፡ የገለጹት ፡ ሐሳብ፡ ተቀባይ፡ አግኝቶ ስብሰባው ፡ ቢጀመር ፡ የሚሰ ጠው ፡ ውጤት ፡ ገሚሱ ፡ ፩ ፡ አካል ፡ ፩ ፡ ባሕርይ ፡ ሲል ፡ ገሚሱ ፡ ፪ ፡ አካል ፡ ፪ ፡ ባሕርይ ፡ ገሚሱም ፡ ፩ ፡ አካል ፡ ፪ ፡ ባሕርይ ፡ የሚለውንና ፡ ሌላውንም ፡ የተለያየ ፡ አነጋገር ፡ ደምሶ ፡ ለክርስቲያን ፡ ኹሉ ፡ ለሃይማኖቱ ፡ መግለጫ ፡ አንድ ፡ አነጋገር ፡ ይፈጥርለት ፡ እንደኾነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ኹሉም ፡ ተስማምቶ ፡ የሮሙን ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ያመልካል ፡ ብለው ፡ የሚጠባበቁት ፡ ተስፋ ፡ ምንም ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ተስፋ ፡ ነው ።

## ደ ራ ሲ ።

፹፭/ እግዚአብሔር ፡ ይህ ፡ ተስፋ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ተፈጽሞ ፡ ክርስ ቲያኖች ፡ ኹሉ ተባብረውና ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ለማየት ፡ ያብቃን ፡ ብለዋል ።

## መ ላ ሽ ።

ከላይ ፡ እንደ ፡ ገለጽኩልዎ ፡ ተስፋዎን ፡ እንዲያሻሽሉት ፡ አሳስብዎታለሁ ፡ እንጂ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ኹሉ ፡ ተባብረውና ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ለማየት ፡ ያብቃን ፡ ብሎ ፡ በመመኘት ፡ ኹላችንም ፡ ተባባሪዎች ፡ ነን ።

አ ሜ ን ያ ብ ቃ ን ።

## የክርስቲያኖች ፡ መቀራረብ ፡ ተብሎ ፡ ለሚቋቋመው ፡ ማኅበር ፡

## ማጠቃለያ ፡ አሳብ ።

ከመ ፡ ብ ፡ አ ፡

ማንም ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ሲናገር ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ሲጽፍ ፡ መነሻውና መድረሻው ፡ ሳይቃወስ ፡ የነገሩ ፡ አመራር ፡ ሳይልከሰከስ ፡ በሰማዕያኑ ፡ ዘንድ ፡ ባለመስልቸት ፡ ተደማጭነትን ፡ አግኝቶ ፡ መልካም ፡ ውጤትን ፡ እንዲያስገኝለት ፡ መጠንቀቅ ፡ አለበት ።
ሐሳቡ ፡ አልጠቃለልለት ፡ ብሎ ፡ አንዱን ፡ ነገር ፡ አንዱ ፡ እየጐተተው ፡ ከግቡ ፡ የወጣ ፡ እንደኾነ ፡ ግን ፡ ተመልካቹን ፡ አሰልችቶ ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ኾኖ ፡ ይቀራል ።

በዚሁ ፡ መሠረት፡ ዶክተር ፡ አባ ፡ አየለም ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ሲጽፉ ፡ የተነሡበት ፡ ዋናው ፡ ዓላማ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድነት ፡ መኾኑን ፡ ሲገልጹ ፡ መጻሕፍት ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ አንድ ፡ ሃይማኖት ፡ አንድ ፡ ጥምቀት ፡ ብቻ ፡ መኖራቸውን ፡ ሲያስተምሩን ፡ ክርስቲያኖች ፡ እርስ በርሳቸው ፡ ኅብረት ፡ አለማግኘታቸው ፡ ያሳዝናል ።

የክርስቶስ ፡ ተከታዮች ፡ ለኾኑ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ኹሉ ፡ መለዮ ፡ እንዲኾን ፡ የፈለገውና ፡ ያማጠነው ፡ አንድነት ፡ ይህም ፡ በመሳሰሉ ፡ በማይረቡ ፡ ነገሮች ፡ ተባታትና ፡ ማየት ፡ በጣም ፡ የሚያሳዝን ፡ ነው ። የዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ዋና ፡ ዓላማው ፡ ይህን ፡ ኹላችን ፡ የምንመኘውን ፡ አንድነት ፡ ማስገኘት ፡ ነው ።

ዛሬ ፡ የወንጌልን፡መንፈሳዊ ፡ ሀብት ፡ ለመጠበቅና፡ወደሚያመለክተው ፡ ከፍተኛ፡ ዓላማ ፡ ለመድረስ ፡ ክርስቲያኖች ፡ እንዲያብሩና ፡ ኃይላቸውን ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ እንዲያደርጉ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ በመቅድሙ ፡ ገልጸው ፡ ነበረ ።

በመጽሐፋቸው ፡ መጨረሻ ፡ በ፪፻፫ ፡ ገጽ ፡ ላይ ፡ ካቶሊኮችም ፡ ኢትዮጵያውያኖቹም ፡ አብረው ፡ በማጥናት ፡ ምሥጢረ ፡ አካላዊ ፡ ተዋሕዶን ፡ ለመግለጥ ፡ የሚበቁና ፡ ትክክለኛ ፡ የኾኑ ፡ ቃሎች የሚወሰኑበት ፡ አንድ ፡ ማኅበር ፡ ቢቋቋም ፡ የክርስቲያኖች ፡ መቀራረብ ፡ ማኅበር ፡ ተብሎ ፡ ቢጠራ ፡ የተሻለ ፡ ነገር ፡ ኾኖ ፡ ይታየናል ፡ ብለው ፡ ነበረ ።

ይህም ፡ ሐሳብ ፡ የዶክተር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ ሐሳብ ፡ ብቻ ፡ ኾኖ ፡ እንዳይቀር ፡ ጥቀ ፡ ልዑል ፡ የሚል ፡ ቅጽል ፡ የተሰጣቸው ፡ ክርዲናል ፡ ኤውጀንዮስ ፡ ቲሰራንም ፡ ይኸ ፡ ክቡር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የደረሱት ፡ መጽሐፍ ፡ ከረዥም ፡ ዘመናት ፡ ዠምሮ ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ሮማን ፡ ለያይቶ ፡ የሚገኘውን ፡ ዋና ፡ ክርክር ፡ ለማቆም ፡ በጣም ፡ እንደሚረዳ ፡ ስለማያጠራጥር ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ አሳብ ፡ ማበራታታትና ፡ ርዳታ ፡ ሊያገኝ ፡ በእውነት ፡ የሚገባው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ለነገሩ ፡ ድጋፌ ፡ መኾናቸውን ፡ ገልጸዋል ።
ይህ ፡ ሐሳብ ፡ በዚህ ፡ አያያዝ ፡ የሚዘልቅ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ማንንም ፡ ክርስቲያን ፡ የኾነን ፡ ሰው ኹሉ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ተናፋቂ ፡ ሐሳብ ፡ ነበረ ።

በእውነቱ ፡ ይህ ፡ መልካም ፡ ሐሳብ ፡ ከግቡ ፡ እንዲደርስ ፡ ከልብ ፡ አስበውበት ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ የኢትዮጵያንም ፡ መብትና ፡ ክብር ፡ እንደሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ክብር ፡ ጠብቀው ፡ የኢትዮጵያና የሮማ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሚለያዩባቸውን ፡ ባህሎች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እየለዩ ፡ የሮማ ፡ ቤተ ክርስቲያን ፡ እንዲህ ፡ ያለውን፡ባህል፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ምዕራፍ ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ቊጥር ፡ አግኝታ ፡ ይዛዋለች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይህን ፡ የማትቀበልበት ፡ ምክንያት ፡ ምንድነው ፡ በሚል ፡ አስተያየት ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ የሚለውን ፡ ባህል ፡ ከምን ፡ አገኘችውና ፡ ያዘችው ፡ በሚል ፡ አኳኋን ፡ ጥያቄዋን ፡ እንድታቀርብ ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም፡እንደዚሁ፡የራሷ፡ባህል ፡ የተመሠረተበትን ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ እየጠቀሰች ፡ በማስረዳት ። የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባህሏን ፡ የመሠረተችበትን ፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት ፡ ጠቅሳ ፡ እንድታስረዳት፡በመጠየቅ፡ግራ ፡ ቀኙም ፡ ሐሳባቸውን ፡ ከዚያም፡ከዚያም፡ተወጣጥቶ ፡ ለተቋቋመው ፡ የክርስቲያኖች ፡ መቀራረብ ፡ ማኅበር ፡ ተብሎ ፡ እንዲጠራ ፡ ለተመኙለት ፡ ጉባኤ እንዲቀርብና ፡ ጉባኤው ፡ በመንፈሳዊ ፡ ዳኝነት ፡ ወይም ፡ በሰላማዊ ፡ ሽምግልና ፡ የሚወስንበትን ፡ መንገድ ፡ በጠረጉ ፡ ነበረ ።

ነገር፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሐሳብ ፡ ካንገት ፡ በላይ ፡ እንጂ ፡ ልባዊ ፡ ስላልኾነ ፡ ይህን ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ የሚገኝበትን ፡ ሰላማዊ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ ትተው ፡ ለዶክተር ፡ አባ ፡ አየለ፡ረዳትና፡ አበረታች የኾኑት ፡ ካርዲናል ፡ ኤውጀንዮስ ፡ ቲሰራን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከእመቤትዋ ፡ ኰበሳ ፡ ጠፍታ ፡ ስንብታ

መታረቅ ፡ እምሯት ፡ አማላጅ ፡ እንደምትልክ ፡ ገረድ ፡ ቆጥረዋት ፡ ኢትዮጵያ ፡ በበኩልዋ ፡ ከሮማ ፡ ጋራ ፡ ለመታረቅ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በልብ ፡ ተመኝታለች ፡ ብለዋል ።

የሮማንም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጠፍታ ፡ ለተገኘች ፡ ገረዷ ፡ ይቅርታ ፡ እንደምታደርግና ፡ በበጐ ፡ አስተያየት ፡ እንደምትመለከት ፡ ርኅርኅት ፡ እመቤት ፡ አድርገዋት ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ በመልካም ፡ ዐይንና ፡ በልዩ ፡ ፍቅር ፡ እንደ ፡ ተመለከተቻት ፡ ናት ፡ እያሉ ፡ ተናግረዋል ።

ዶክተር ፡ አባ ፡ አየለም ፡ ይህንኑ ፡ ሐሳብ ፡ በመደገፍ ፡ ኢትዮጵያና ፡ ግብጽን ፡ ለሰላማዊ ፡ ንጉሥ ፡ አልገዛም ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ሸፈተ ፡ ወንበዴ ፡ ቆጥረዋቸው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ የተለየችው ፡ ሳታውቀውና ፡ ሳትፈልገው ፡ ነው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከግብጽ ፡ ጋራ ፡ ኾና ፡ ዓላማዋን ፡ አምርታ ፡ ያመፀችበት ፡ የሸፈተችበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ በኋላ ፡ የእስክንድርያን ፡ ጳጳሳት ፡ መቀበሏ ፡ የቅዱስ ፡ ፍሬ ፡ ምናጦስ ፡ የተገቡ ፡ ወራሾች ፡ የትምርቱና፡የስብከቱ ፡ ቀጣዮች ፡ መስለዋቸው ፡ በልበ ፡ ገርነት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከግብጽ ፡ ጋራ ፡ አብረው ፡ ለማመጥ ፡ አይደለም ።

ኢትዮጵያ ፡ ለጥፋትዋ ፡ ምክንያት ፡ የሚኾናት ፡ አለማወቋ ፡ አላት ፡ ግብጽ ፡ ግን ፡ አውቃ ፡ ያደረገችው ፡ ስለኾነ ፡ ለጥፋትዋ ፡ ምንም ፡ ምክንያት ፡ አይገኝላትም ፡ እያሉ ፡ ጽፈዋል ።

የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታትም ፡ እነ ፡ ዓፄ ፡ ካሌብና፡ሌሎችም፡ኢትዮጵያ፡ውያን፡ካቶሊካውያን ፡ ነበሩ ፡ ምሥጢሩን ፡ ባያውቁት ፡ አንድ ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ ነን ፡ ይላሉ ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ ባዮች ፡ ናቸው ፡ ይኸውም ፡ በቅኔያቸው ፡ ይታወቃል ፡ ብለው ፡ የብዙ ፡ ሊቃውንት ፡ ቅኔ ፡ ንባቡንም ፡ ምሥጢሩንም ፡ እያበላሹ ፡ ጽፈዋል ።

ከዚህም ፡ ሌላ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱና ፡ በቤተ ፡ ክህነቱ ፡ አስተዳደር ፡ ገብተው ፡ ቤተ ፡ መንግሥትንና ፡ ቤተ ፡ ክህነትን ፡ ለማለያየት ፡ ሊቃውንቱን ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ለማበጣበጥ ፡ ሞክረዋል ።

ይህ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ አመራር ፡ መልስ ፡ ስጪውንም ፡ በዚሁ ፡ መንገድ ፡ እንዲራመድ ፡ አስገድደው ፡ ስለዚሁ ፡ በያንቀጹ ፡ ሲያንዳንዱ ፡ ኃይለ ፡ ቃል ፡ ተገቢውን ፡ መልስ ፡ አዘጋጅቶ ፡ አቅርቧል ፡ ተመልካች ፡ ባስተዋይ ፡ ልቡናው ፡ አመዛዝኖ ፡ እውነት ፡ ከማንላቸው ፡ ወገን ፡ እንዳለች ፡ ይመስክር ።

እንግዲህ ፡ ይህች ፡ እግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ የሚሰኝባት ፡ እኛ ፡ የምንጠቀምባት ፡ ዶክተር ፡ አባ ፡ አየለ ፡ በምላሳቸው ፡ ቀምሰው ፡ ወደጉሮሯቸው ፡ ሳትወርድ ፡ እክ ፡ እንትፍ ፡ ብለው ፡ የተፉት ፡ የክርስቲያንነታችን ፡ ምልክት ፡ የኾነች ፡ አንድነት ፡ በዚህ ፡ ባረባ ፡ ነገር ፡ ወድቃና ፡ ተዘንግታ ፡ እንዳትቀር ፡ እርሷ ፡ የምትገኝበትን ፡ መንገድ ፡ እንፈልግ ።

አስቀድሞ ፡ የሮማ ፡ ካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንንና፡የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚለያዩባቸውን ፡ ባህሎች ፡ ለይቶ ፡ ማወቅ ፡ ያስፈልጋል ፡ እነኸውንም ፡ ምንም ፡ አባ ፡ አየለ ፡ በመጽሐፋቸው ፡ በቂ ፡ መረጃ፡እየሰጡ ፡ አብራርተው ፡ ባይገልጧቸው ፡ በመጠኑ ፡ ለምልክት ፡ ያህል ፡ የገለጹልን ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

፩ኛ/ የሮማ ፡ ካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብም ፡ ከወልድም ፡ እንደ ፡ ሠረጸ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መሥረጽም፡ ከወልድ ፡ መወለድ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በሥላሴ ፡ መቅደም ፡ መቀዳደም ፡ መብለጥ ፡ መበላለጥ ፡ እንዳለ ፡ የምታስተምር ፡ መኾኗን ፡ በገጽ ፡ ፪፴፯ ፡ ገልጸው ፡ ጽፈዋል ፡ መረጃ ፡ ግን ፡ አልሰጡም ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብ ፡ ብቻ ፡ መሥረጹን ፡ ከወልድ ፡ አለመሥረጹን ፡ በሥላሴም ፡ መቅደም ፡ መቀዳደም ፡ መብለጥ ፡ መበላለጥ ፡ የሌለባቸው ፡ ዕሩያን ፡ መኾናቸውን ፡ ከቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ ጠቅሰን ፡ ሊቃውንት ፡ ከመሰሏቸው ፡ ምሳሌዎች ፡ አምጥተን ፡ በበቂ ፡ መረጃ ፡ አስረድተናል ፡ መድ ፡ አሚ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፳፬—፪፻፳፯ ቍ ፡ ፩ ተመልከት ።

እንዲሁም ፡ በገጽ ፡ ፪፭፱ ፡ በሠ ፡ ፊደል-፪፳፪ ፡ ተመልከት ።

፪ኛ/ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ክርስቶስን፡፩ ፡ አካል ፡ በ፪ኤ ፡ ባሕርያት ፡ የምትል ፡ መኾኗን ፡ የኬልዶን ፡ ውሳኔ ፡ ብለው ፡ በጸፉት ፡ በ፪፺፪ ፡ ገጽ ፡ ጽፈዋል ። ኹለት ፡ ባሕርይ ፡ የሚሉበትን ግን ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የጠቀሱት ፡ መረጃ ፡ የለም ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ ክርቶስን ፡ አንድ፡አካል፡አንድ፡ ባሕርይ ፡ የምትልበትን ፡ ምክንያትና ፡ የኬልቄዶንም ፡ ጉባኤ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ግብ ፡ ሳይወጣ ፡ የወሰናቸውን ፡ ውሳኔዎች ፡ በማስማማት ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ የወሰናቸውንም ፡ ለይቶ ፡ በማስረዳት ፡ የቱሳሔና ፡ የውላጤ ፡ የቡዓዴ ፡ ምሥጢር ፡ ሳይቀር ፡ በሰፊው ፡ ዘርዝረን ፡ አስረድተናል ፡ ገጽ ፡ ፪፺፪—፪፺፯ ፡ ቍ ፡ ፭ ።

፫ኛ/ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በአካለ ፡ ቃል ፡ የሚገኘውን ፡ ባሕርየ ፡ ሰብእ ፡ እንደ ፡ ኾነ ሰብአዊ ፡ አካል ፡ እንዳይደለ ፡ ባሕርይም ፡ እንዳልተዋሐደ ፡ የምታስተምር ፡ መኾኗን ፡ በገጽ ፡ ፹፯ ።

ባሕርይ ፡ ያለአካልነቱ ፡ ሊገኝ ፡ መቻሉን፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አያምኑም ፡ በአካለ ፡ ቃል ፡ የሚገኘውን ም ፡ ሰብአዊ ፡ ባሕርይ ፡ አካል ፡ ብለው ፡ ይሰይሙታል ፡ ብለው ፡ ጽፈዋል ፡ ለዚህም ፡ የጠቀሱት ፡ መረጃ ፡ የለም ።

የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ አካል ፡ ያለባሕርይ ፡ ብቻውን ፡ ሊገኝ ፡ አይችልም ፡ ባሕርይም ፡ ያለአካል ፡ ብቻውን ፡ ሊገኝ ፡ አይችልም ፡ ይህ ፡ ግዙፍ ፡ አካለ ፡ ሰብእም ፡ አካል ፡ እንዲባል፡ ማመኗ፡ተገቢ፡ነገር፡መኾኑን፡ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ጠቅሰን ፡ ምሳሌ ፡ መስለን ፡ አስረድተናል ፡ ገጽ ፡ ፻፶፰ ፡ ፻፷፱ ፡ ፪፻፷፩—፪፻፷፮ ፡ ተመልከት ።

፩ኛ/ ካቶሊካውያን ፡ አንድ ፡ ክርስቶስን ፡ ከፍለው ፡ መለኮት ፡ አልሞተም ፡ ትስብእት ፡ ሞተ ብለው ፡ የሚናገሩበት ፡ ምክንያት ፡ መለኮት ፡ ሞት ፡ ያልን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ሥላሴ ፡ በባሕርይ ፡ አንድ ናቸውና ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ሞቱ ፡ ያሰኝብናል፡በማለት ፡ ፈርተው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በገጽ ፡ ፪፲፱ ፡ አመልክተዋል ። ገጽ ፡ ፪፻፴፮ ።

የኢትዮጵያውያን ፡ አነጋገር ፡ እንደ ፡ ካቶሊክ ፡ አነጋገር ፡ ምንታዌን ፡ በሚያሳይ፡ አኳኋን ፡ መለኮት ፡ አልሞተም ፡ ትስብእት ፡ ሞተ ፡ የሚል ፡ ሳይኾን ፡ መለኮት ፡ በሥጋ ፡ ሞተ ፡ ማለት ፡ እንደ ኾነ፡ ይኸውም ፡ ቃል ፡ በተለየ ፡ አካሉ ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ ሥጋ ፡ ቢለብስ ፡ አብ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ የማያሰኝ ፡ መኾኑን ፡ የከዊንን ፡ ምሥጢር ፡ በጻፍንበት ፡ አንቀጽ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ጠቅሰን ፡ በነፋስና ፡ በፀሐይ ፡ በእሳትና ፡ በቀላይ ፡ መስለን ፡ አስረድተናል ። ገጽ ፡ ፪፻፴፯—፪፻፵፩

፩ኛ/ የሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለሥጋ ፡ ወደሙ ፡ አቀባበል ፡ በካህናትና ፡ በምእመናን ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ መኖሩን ፡ ሰላም ፡ አልብነ ፡ ምስለ ፡ ሰብአ ፡ ሮሜ ፡ የሚለውን ፡ መወድስ ፡ በጻፉበት ፡ አንቀጽ ፡ በገጽ ፡ ፻፺፫ና ፡ ፻፺፯ ፡ ገልጸውልናል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ማድረግ ፡ የሚገባ ፡ መኾኑን ፡ የሚያስረዳ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት፡ የጠቀሱት ፡ መረጃ ፡ የለም ።

ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ሥጋ ፡ ወደሙ ፡ አቀባበል ፡ የምትፈጽመው ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ልብ ወለድ ፡ አለመኾኑን ፡ ከቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ እየጠቀስን ፡ አስረድተናል ፡ ገጽ ፡ ፫፻፴፩—፴፮፡ ተመልከት፡

እኒህ ፡ ከምሉ ፡ በክፍሉ ፡ ከብዙ ፡ በጥቂቱ ፡ ከዶክተር፡አባ፡አየለ፡መጽሐፍ፡የተገለጹ፡ ናቸው ።

ደግሞ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ያልተጠቀሰ ፡ በኢትዮጵያ ፡ መጻሕፍት ፡ ተጽፎ ፡ የተገኘ ፡ ሌላም ፡ የምንለያይበት ፡ ባህል ፡ አለ ። ምናልባት ፡ ይህ፡ምኞት ፡ ከቁም ፡ ነገር ፡ ደርሶ ፡ የመቀራረብ ፡ በር ፡ ቢከፈት ፡ ይህም ፡ አብሮ ፡ መታየት ፡ የሚገባው ፡ ስለኾነ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥዬ ፡ እገልጠዋለሁ ።

ይኸውም ፡ ስለነፍስ ፡ ተፈጥሮ ፡ ነው ፡ ካቶሊካውያን ፡ የነፍስ ፡ ተፈጥሮዋ ፡ እንደ ፡ መላእክት ፡ ተፈጥሮ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ነው ፡ የሚካኤል ፡ ከገብርኤል ፡ የገብኤል ፡ ከሚካኤል ፡ ልዩ ፡ እንዳይደለ ፡ የነፍሳትም ፡ እንደዚሁ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ መላእክት ፡ ሲፈጠሩ ፡ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ እንዳይከፈል ፡ ማለት ፡ ሚካኤል ፡ ከገብኤል ፡ ገብርኤል ፡ ከሩፋኤል ፡ እንደማይገኙ ፡ እንደማይከፈሉ ፡ ነፍሳትም ፡ እንደዚሁ ፡ ከአባት ፡ ከእናት ፡ አይከፈሉም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ይገኛሉ ፤ ካባት ፡ ዘር ፡ ከናት ፡ ደም ፡ ተከፍሎ ፡ ረግቶ ፡ ተሥዕሎተ ፡ መልክእ ፡ ከተፈጸመለት ፡ በ፵ ፡ በ፹ ፡ ቀን ፡ ከአዳም ፡ ያልተከፈለች ፡ ሌላ ፡ ነፍስ ፡ አምጥቶ ፡ ያሳድርበታል ፡ እንጂ ፡ ነፍስ ፡ ከአባት ፡ ከእናት ፡ አትከፈልም፡ ይላሉ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ይህንንም ፡ ባህል ፡ አባ ፡ ጽጌ ፡ ማርያም ፡ አንዳርጌ ፡ የተባሉት ፡ ካቶሊካዊ ፡ መነኩሴ ፡ ባለሥዕል፡ ትምህርተ ፡ ክርስቲያን ፡ በተባለው ፡ መጽሐፋቸው ፡ በ፳፭ኛው ፡ ገጽ ፡ እግዚአብሔር ፡ መዠመሪያይቱን ፡ ሴት ፡ ለመፍጠር ፡ በፈቀደ ፡ ጊዜ ፡ በመዠመሪያው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ምሥጢራዊ ፡ ዕንቅልፍ ፡ ላከበት ። ተኝቶ ፡ ሳለ ፡ መዠመሪያይቱን ፡ ሴት ፡ የፈጠረበትን ፡ አንድ ፡ ጎድን ፡ ወሰደ ፡ ከዚህ፡ ገላ፡ ጋራ ፡ ነፍስን ፡ አዋሐዳት ፡ ብለው ፡ እጅግ ፡ ባልጎላ ፡ አነጋገር ፡ መልክት ፡ አርገው ፡ አልፈውታል ።

ስለኾነም ፡ አተኩሮ፡ ሲመለከቱት፡ከአዳም ፡ ጐን፡ አንድ ፡ አጥንት ፡ ወስዶ ፡ ከዚህ ፡ ገላ ፡ ጋራ፡ ነፍስን ፡ አዋሐዳት ፡ ማለት ፡ ነፍስ ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ ከአዳም ፡ ሳትከፈል ፡ ከአፍአ ፡ መጥታ ፡ ተዋሐደች ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በግልጥ ፡ ይታወቃል ።

ይህንም ፡ ለማለት ፡ የሚረዳቸው ፡ ምስክር ፡ ሲጠቅሱ ፡ አዳም ፡ ሔዋንን ፡ ምሉእ ፡ ሴት ፡ ኾና ባያት ፡ ጊዜ ፡ ዛቲ ፡ ዓፅም ፡ እምዐፅምየ ፡ ወሥጋ ፡ እምሥጋየ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ወነፍስ ፡ እምነፍስየ ፡ አላለም ፡ ማለትን ፡ ይጠቅሳሉ ፡ ማለትን ፡ እንሰማለን ።

የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ለዚህ ፡ መልስ ፡ ሲሰጡ ፡ በአዳም ፡ አቅዋም ፡ ያሉ ፡ ሥጋና ፡ አጥንት ብቻ ፡ አይደሉም ። ደም ፡ ጅማት ፡ ወይም ፡ አሥራው ፡ ጠጉርም ፡ አሉ ፡ እንግዲህ ፡ አዳም ፡ ደም ፡ እምደምየ ፡ ወጸጉር ፡ እምጸጉርየ ፡ ወአሥራው ፡ እምአሥራውየ ፡ አላለምና ፡ ሔዋን ፡ ከአዳም ፡ ደምን ጅማትን ፡ ጠጉርን ፡ አልነሣችም ፡ እንላለን ? እንልም ።

እንግዲያስ ፡ ሔዋን ፡ ከእርሱ፡የነሣቻቸውን ፡ በሰውነት ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ነገሮች ፡ ኹሉ ፡ አጠቃሎ ፡ ሥጋ ፡ ዓፅም ፡ በማለት ፡ ከተናገራቸው ፡ ነፍስንም ፡ እንደዚሁ ፡ ሥጋ ፡ ዓፅም ፡ ባለው ፡ አነጋገር ፡ ውስጥ ፡ አጠቃሎ ፡ ተናገራት ፡ ይላሉ ።

በነፍስና ፡ በሥጋ ፡ ተዋሕዶ ፡ የቆመ ፡ ሰውም ፡ ሥጋ ፡ ወይም ፡ ነፍስ ፡ ተብሎ ፡ እንደሚጠራ መጻሕፍት ፡ በብዙ ፡ አንቀጽ ፡ ይመሰክራሉ ። እነሆ ፡ ዳዊት ፡ ስማዕ ፡ ጸሎተ ፡ ዦሉ ፡ ዘሥጋ ፡ ዘመጽአ ፡ ኀቤከ ።

አንተ ፡ ጸሎትን ፡ ሰሚ ፡ ነህና ፡ ወዳንተ ፡ የቀረበ ፡ የሥጋውያንን ፡ ጸሎት ፡ ኹሉ ፡ ስማ ፡ ወዳንተ ይመጣል ፡ ይላል ፡ መዝ ፡ ፷፭ ፡ ፪ ።

በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ነፍስ ፡ የተለየች ው ፡ ሥጋ ፡ ብቻ ፡ ወዳንተ ፡ ይቀርባል ፡ እለ ፡ እንላለን ? ።

አፌ፡የእግዚአብሔርን ፡ ምስጋና ፡ ይናገራል ፡ ሥጋዊም ፡ ኹሉ ፡ ለዘለዓለም ፡ የተቀደሰውን ፡ ስሙን ፡ ይባርክ ፡ ይላል ። መዝ ፡ ፻፵፭ ፡ ፳፩ ።

እንግዲህ ፡ ሥጋ ፡ ኹሉ ፡ የተባለ ፡ ነፍስ ፡ የተለየችው ፡ ሥጋ ፡ ማለቱ ፡ ነውን ? አይደለም፡ነፍስን፡ በሥጋ ፡ ህልው ፡ አድርጎ ፡ መናገሩ ፡ ነው ።

ደግሞ ፡ ያዕቆብ፡፸፭ ፡ ነፍስ፡ኾኖ ፡ ምድረ ፡ ግብጽ፡ወረደ ፡ ይላል ፡ ዘፍ ፡ ፵፮ ፡ ፳፯ ፡ ፯ ። ግብ ፡ ሐዋ፡ ፯ ፡ ፲፬ ። እንግዲህ ፡ ሥጋቸው ፡ በከነዓን ፡ ቀርቶ ፡ ነፍሳት ፡ ብቻ ፡ ወረዱ ፡ ማለቱ፡ነውን ፡ አይደለም ።

ኢትቅትል ፡ ነፍሰ ፡ ይላል ፡ ዘፀአ ፡ ፳ ፡ ፲፪ ። ማቴ ፡ ፭—፳፩ ።

ነፍስ ፡ በባሕርይዋ ፡ የማትሞት ፡ መኾኗ ፡ ሲታወቅ ፡ ነፍስ ፡ ሞተች ፡ እንላለን ፡ የምትሞት ፡ የምትፈርስ ፡ የትምበሰብስማ ፡ ሥጋ ፡ አይደለችምን ።

እነሆ ፡ በነፍስና ፡ በሥጋ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቆሞ ፡ የሚገኝ ፡ ሰው ፡ በጠቅላላው ፡ ሥጋ፡ ወይም ፡ ነፍስ ፡ ተብሎ ፡ እንዲጠራ ፡ ከመጻሕፍት ፡ ጠቅሰን ፡ አስረድተናል ።

ስለዚህ ፡ አዳም ፡ ሔዋንን ፡ ዛቲ ፡ ዓፅም ፡ እምዓፅምየ ፡ ወሥጋ ፡ እምሥጋየ ፡ ቢልም ፡ ወነፍስ ፡ እምነፍስየ ፡ ካላለ ፡ ነፍስን ፡ ከአዳም ፡ ነሣች ፡ ለማለት ፡ አይቻልም ፡ የሚሉት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ አይደለም ።

በዚህም ፡ አኳኋን ፡ ከሥጋው ፡ ሥጋ ፡ ከነፍሱ ፡ ነፍስ ፡ ነሥታ፡ ምሉ፡ሴት ፡ ኾና ፡ የተፈጠረች ፡ ሔዋንን ፡ ዛቲ ፡ ዓፅም ፡ እምዓፅምየ ፡ ወሥጋ ፡ እምሥጋየ ፡ ለትኩነኒ ፡ ብእሲትየ ፡ ብሎ ፡ ሚስት ፡ አደረጋት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ብዝኁ ፡ ወተባዝኁ ፡ ወምልእዋ ፡ ለምድር ፡ ብሎ ፡ ባዘዛቸው ፡ መሠረት ፡ አዳም ፡ ሔዋንን ፡ በግብር ፡ ባወቃት ፡ ጊዜ ፡ ከአዳም ፡ ዘርዕ ፡ ከሔዋን ፡ ደም ፡ ሲከፈል ፡ ነፍስም ፡ አብራ ፡ ተከፈለች ፡ ደምና ፡ ዘርዕ ፡ ተቀላቅለው ፡ ተዋሕደው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ሥጋ ፡ አጥንት ፡ ጅማት፡ ጠጉር ፡ ጥፍር ፡ ወደ ፡ መኾን ፡ ሲራመዱ ፡ ነፍስም ፡ በበኩሏ ፡ ቁስ ፡ በቀስ ፡ ሥጋዊ ፡ አካል ፡ ወይም ፡ ገላ ፡ ወደ ፡ መኾን ፡ መራመድ ፡ የጀመረውን ፡ ፅንስ ፡ በማንቀሳቀስ ፡ የሕይወትነት ፡ ሥራዋን ፡ ትሠራለች።

ይህ ፡ ከእናት ፡ አባት ፡ ተከፍሎ ፡ የዕለት ፡ ፅንስ ፡ የኾነው ፡ ዘርዕና ፡ ደም ፡ በዚያኑ ፡ ጊዜ ፡ነፍስ ፡ አብራው ፡ የተከፈላች ፡ ባትኾንስ ፡ በገበታ ፡ ላይ ፡ እንደተቀበሉት ፡ ደም ፡ ለጊዜው ፡ ቢረጋም ወደ ፡ መድረቅ ፡ ይራመድ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ሕያው ፡ ወደ ፡ መኾን ፡ ሊራመድ ፡ ባልቻለም ፡ ነበረ ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ይህ ፡ ዕንስ ፡ በነፍስ ፡ ሕይወትነት ፡ እየተረዳ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ አካል ፡ ዘየአክልን ፡ ግን ዘብ ፡ አድርጎ ፡ መዋዕለ ፡ ፅንሱን ፡ ሲፈጽም ፡ ተወለደ ፡ ቃየል ፡ ተባለ ፡ ዘፍ ፡ ፬ ፡ ፩ ።

ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ የሚፈጠር ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ነው ።

ይህንንም ፡ የሚያስረዳ ፡ ነገር ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘይቤ ፡ ይሠርቅ ፡ ብርሃን ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ውእቱ ፡ አብርሀ ፡ ውስተ ፡ ልብነ ፡ ብርሃነ ፡ አእምሮ ፡ ስብሐቲሁ ፡ በገጹ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ።

በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ብርሃን ፡ ይውጣ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጌትነቱን ፡ የምናውቅበትን ፡ እውቀት ፡ በልቡናችን ፡ ሥሎብናል ፡ ያለውን ፡ ንባብ ፡ ሲተረጕም ፡ በሚቀጥለው ፡ መሥመር ፡ ወብነ ፡ ዝንቱ ፡ መዝገብ ፡ ውስተ ፡ ንዋየ ፡ ልሕኩት ።

ይህ ፡ መዝገብ ፡ በሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ውስጥ ፡ አለን ፡ ማለት ፡ ጌትነቱን ፡ የምናውቅባት ፡ ነፍስ ፡ ከመሬት ፡ በተፈጠረ ፡ በሥጋችን ፡ አለችን ፡ ብሎ ፡ ተርጕሞታል ። ፪ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፭ ፡ ፯ ።

ልሕኲት ፡ የተባለ ፡ ከ፬ቱ ፡ ባሕርያት ፡ የተፈጠረ ፡ ሥጋ ፡ መዝገብ ፡ የተባለችም ፡ ነፍስ ፡ እንደ ኾነች ፡ መዝገብነቷም ፡ ለማሰብ ፡ ለመናገር ፡ ለመተንፈስ ፡ በጠቅላላው ፡ ለዕውቀትና ፡ ለሕይወት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ።

ይህንንም ፡ ፫፻ ፡ በቅዳሴ ፡ ወእምአሐቲ ፡ መዝግብ ፡ ዘበእስትንፋስ ፡ አፉሁ ፡ ይሠርጽ ፡ ወያሕመለምላ ፡ ነፍሳት ፡ እለ ፡ ይትወለዱ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚወለዱ ፡ ነፍሳት ፡ ባፉ ፡ ትንፋሽ ፡ ከተገኘች ፡ ካንዲት ፡ መዝገብ ፡ ይበቅላሉ ፡ ያድጋሉ ፡ ብለው ፡ ወስደውታል ።

ነፍሳት ፡ ኹሉ ፡ ከርሷ ፡ የተገኙ ፡ ባፉ ፡ ትንፋሽ ፡ የተገኘች ፡ አንዲት ፡ መዝገብ ፡ የተባለች ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ ከምድር ፡ ዐፈር ፡ ፈጥሮ ፡ ባፍንጫው ፡ የሕይወት ፡ እስትንፋስን ፡ እፍ ፡ አለበት ፡ የተባለችቱ ፡ ሰውም ፡ ሕያው ፡ ነፍስ ፡ ያለው ፡ ኾኑ ፡ ያሰኘችው ፡ ነፍስ ፡ እንደኾነች ፡ እንዘንጋ ፡ ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፯ ።

እንደ ፡ ካቶሊካውያን ፡ ባህል ፡ ነፍስ ፡ ከእናት ፡ ካባት ፡ አትከፈልም ፡ በየቀኑ ፡ ለያንዳንዱ ሰው ፡ ትፈጠርለታለች ፡ ያልን ፡ እንደኾነ ፡ አስቸጋሪ ፡ አስቸጋሪ ፡ የኾኑ ፡ ነገሮች ፡ ይገጥሙናል ።

፭ኛ/ መጽሐፍ ፡ ከእሑድ ፡ እስከ ፡ ዐርብ ፡ ፍጥረቱን ፡ ሲፈጥር ፡ ሰንብቶ ፡ ዐርብ ፡ በነግህ ፡ አዳምን ፡ ፈጥሮ ፡ ሥራውን ፡ ጨርሶ ፡ ዐረፈ ፡ ይላል ፡ ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፪ ።

እንዲህ ፡ ማለቱ ፡ እስከ ፡ ምጽአት ፡ ድረስ ፡ የሚፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ያው ፡ ከእሑድ ፡ እስከ ፡ ዐርብ ፡ የተፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ እርሱ ፡ በርሱ ፡ እየተባዛና ፡ እየተራባ ፡ የሚገኝ ፡ ነው ፡ እንግዳ ፡ ፍጥረት ፡ አይፈጥርም ፡ ማለቱ ፡ ነው ። ይህን ፡ አልፈን ፡ ከአዳም ፡ ያልኾነች ፡ በየጊዜው ፡ ልዩ ፡ ነፍስ ፡ ይፈጥራል ፡ የምንል ፡ ከኾን ፡ ፈጽሞ ፡ አዕረፈ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ታብለ ፡ ማለቱ ፡ ነው ።

፮ኛ/ ነፍሳትን ፡ እየፈጠረ ፡ በያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ አዳም ፡ በንፍሐት ፡ ያሳድርበታል ፡ እንዳይባል ፡ ይህን ፡ የሚያስረዳ ፡ መጽሐፍ ፡ አይገኝም ፡ ይህ ፡ የሚደረግ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ከአዳም ፡ ተከፍሎ ፡ መፈጠር ፡ የተጀመረ ፡ በሔዋን ፡ ስለኾነ ፡ ስለአዳም ፡ ባፍንጫው ፡ የሕይወት ፡ እስትንፋስ እፍ ፡ አለበት ፡ እንዳለ ፡ ስለ ፡ ሔዋንም ፡ የሕይወት ፡ እስትንፋስ ፡ እፍ ፡ አለባት ፡ ባለ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ከአዳም ፡ የወሰዳትን ፡ አጥንት ፡ ሴት ፡ አድርጎ ፡ ሠራት ፡ ወደ ፡ አዳምም ፡ አመጣት ፡ ብሎ ፡ ባልቀረም ነበረ ፡ ዘፍ ፡ ፪ ፡ ፳፪ ።

፯ኛ/ በየቀኑ ፡ የሚፈጠሩ ፡ ነፍሳት ፡ እንደ ፡ አዳም ፡ በንፍሐት ፡ ሳይኾን ፡ በአርምሞ ፡ ይፈጠራሉ ፡ እንዳይባልም ፡ የአዳም ፡ ነፍስ ፡ በንፍሐት ፡ ተፈጥራ ፡ የሌሎች ፡ ነፍስ ፡ በአርምሞ ፡ ስትፈጠር ፡ አንዲ ፡ በንፍሐት ፡ የተፈጠረች ፡ ሌሎች ፡ ደግሞ ፡ በአርምሞ ፡ የተፈጠሩ ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ፍጥረቶች ፡ መኾናቸው ፡ ነው ። እንዲህም ፡ ከኾነ ፡ መላእክት ፡ በተፈጥሮአቸው ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ነፍሳትም ፡ በተፈጥሮአቸው ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ ተብሎ ፡ በአርእስቱ ፡ የተወሳው ፡ አነጋገር ፡ ሐሰት ፡ ኾነ ፡ ማለት ፡ ነው ።

በዚያውም ፡ ላይ ፡ በአርምሞ ፡ ከተፈጠረው ፡ በነፋሕ ፡ የተፈጠረው ፡ መብለጥ ፡ አለበትና ፡ ነፍሳት ፡ በተፈጥሮ ፡ መበላለጥ ፡ አለባቼው ፡ ማለት ፡ በግድ ፡ ይመጣል ።

ምናልባት ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍጥረትን ፡ በዕለተ ፡ ዐርብ ፡ ፈጽሞ ፡ ዐርፏል ፡ በየቀኑ ፡ እንግዳ ፡ ፍጥረት ፡ አይፈጥርም ፡ ለተባለው ፡ አስተያየት ፡ አቡየ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ፡ ይገብር ፡ ወአነሂ ፡ ከማሁ ፡ እገብር ፡ ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፲፯ ።

አባት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያደርጋል ፡ እኔም ፡ እንደርሱ ፡ አደርጋለሁ ፡ ያለውን ፡ ንባብ ፡ ለዚህ አስተያየት ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ የሚታያቸው ፡ ሰዎች ፡ ይኖሩ ፡ ይኾናል ።

አይሁድ ፡ ጌታን ፡ በሰንበት ፡ ድውይ ፡ ፈወስክ ፡ ተአምራት ፡ አደረግህ ፡ ብለው ፡ ተቃወሙት ፡ እንጂ ፡ እንግዳ ፡ ፍጥረት ፡ ፈጠርክ ፡ ብለው ፡ አልተቃወሙትም ፡ እርሱም ፡ አባቴ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ተአምራት ፡ ያደርጋል ፡ እኔም ፡ እንደርሱ ፡ ተአምራት ፡ አደርጋለሁ ፡ ሲል ፡ መለሰላቸው ፡ እንጂ ፡ አባቴ ፡ ሌላ ፡ እንግዳ ፡ ፍጥረት ፡ ይፈጥራል ፡ እኔም ፡ እንደርሱ ፡ እንግዳ ፡ ፍጥረት ፡ እፈጥራለሁ ፡ ሲል ፡ የተናገረው ፡ አይደለም ።

ይኸውም ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ በሚገኘው ፡ መሥመር ፡ አብ ፡ ልጁን ፡ ይወደዋልና ፡ የሚያደርገውን ፡ ኹሉ ፡ ያሳየዋል ፡ እናንተ ፡ ታደንቁ ፡ ዘንድ ፡ ከዚህም ፡ የሚበልጥ ፡ ሥራ ፡ ያሳየዋል ። አብ ፡ ሙታንን ፡ እንዲያስነሣ ፡ እንዲሁ ፡ ወልድም ፡ የወደደውን ፡ ያድናል ፡ ብሎ ፡ የተአምራት ፡ መኾኑን ፡ በማያጠራጥር ፡ አኳኋን ፡ ገልጦታል ፡ ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፳ ፡ ፳፩ ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ጥቅስ ፡ ለዚህ ፡ ሐሳብ ፡ የማይጠቅም ፡ መኾኑን ፡ እናስረዳለን ።

፰ኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነፍሳትን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፈጥሮ ፡ መዝገበ ፡ ነፍሳት ፡ አለ ፡ ከዚያ ፡ አስቀምጧቸዋል ፡ ከአባት ፡ ዘር ፡ ከእናት ፡ ደም ፡ ተከፍሎ ፡ የዕለት ፡ ፅንስ ፡ ኾኖ ፡ ተሥዕሎተ ፡ መልክእ ፡ ሲፈጸምለት ፡ አንድ ፡ አንዷን ፡ ነፍስ ፡ እያመጣ ፡ ያሳድርበታል ፡ ይላሉ ፡ የሚል ፡ ታሪክ ፡ እንሰማለን ፡ ምንም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በእርግጥ ፡ ይላሉ ፡ ብሎ ፡ ያስረዳኝ ፡ ባይኖር ፡ ምናልባት ፡ እውነት ፡ እንደ ኾነ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ እውነት ፡ ብለን ፡ ልንቀበለው ፡ አንችልም ፡ ምክንያቱም ፡ መጽሐፍ ፡ ለነፋሳት ፡ መዝገብ ፡ እንዳላቸው ፡ ዘያወፅእሙ ፡ ለነፋሳት ፡ እመዛግብቲሆሙ ፡ ብሎ ፡ መዝ ፡ ፻፴፭ ፡ ፯ ።

ለበረድም ፡ መዝገብ ፡ እንዳለው ፡ በጸሕከኑ ፡ ኀበ ፡ መዛግብ ፡ በረድ ፡ ብሎ ፡ ነግሮናል ፡ ኢዮ ፡ ፴፰ ፡ ፳፪ ። ነፍስ ፡ ግን ፡ ራሷ ፡ ለዕውቀት ፡ መዝገብ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ ከላይ ፡ የጠቀስነው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ወብነ ፡ ዝንቱ ፡ መዝገብ ፡ ብሎ፡ ፪ቆ፡፬ም ፡ በቅዳሴያቸው ፡ ወእምአሐቲ ፡ መዝገብ ፡ ዘበእስትንፋስ ፡ አፉሁ ፡ ብለው ፡ ይነግሩናል ፡ እንጂ ፡ ለርሷ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተፈጥራ ፡ ተከማችታ ፡ የምትገኝበት ፡ መዝገብ ፡ እንዳለ ፡ አይነግሩንም ፡ የርሷስ ፡ መዝገቧ ፡ ንዋየ ፡ ልሕኩት ፡ የተባለው ፡ የአዳም ሥጋ ፡ ነው ። ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ በባሕርይዋ ፡ ዐዋቂ ፡ የኾነች ፡ ነፍስ ፡ ዕውቀትን ፡ ከምታተርፍለት ፡ ከሥጋ ፡ ጋራ ፡ ከመዋሐዷ፡ በፊት ፡ ፍጹምት ፡ ኾና ፡ ተፈጥራ ፡ ከሥጋ ፡ ጋራ ፡ እስክትዋሐድ ፡ ድረስ ፡ ብቻዋን ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ የምትኖር ፡ ከኾነ ፡ ከሥጋ ፡ ጋራ ፡ ከተዋሐደች ፡ በኋላ ፡ ባለ ፡ ዘመኗ ከመዋሐዷ ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ አኗዋወሯና ፡ ሥራዋ ፡ ለምን ፡ ትዝ ፡ አይላትም ፡ የሚል ፡ አሳብ ፡ ይመጣብናል ፡ ይህንንም ፡ አሳብ ፡ የምናሳርፍበት ፡ ምንም ፡ ምክንያት ፡ አናገኝለትም ፡ ስለዚህ ፡ በማናቸውም ፡ አስተያየት ፡ ልንቀበለው ፡ የምንችለው ፡ አይደለም ።

፪ኛ/ ካቶሊካውያን ፡ ካባት ፡ ዘር ፡ ከናት ፡ ደም ፡ ሲከፈል ፡ ነፍስም ፡ የምትከፈል ፡ ከኾነ ወንዶች ፡ በሕልመ ፡ ሌሊት ፡ ዘር ፡ ይከፍላሉ ፡ ሴቶችም ፡ በየወሩ ፡ ደም ፡ ያያሉና ፡ ያ ፡ ኹሉ ፡ ነፍስ ፡ አለው ፡ ማለት ፡ ነዋ ፡ ብለው ፡ ይቃወማሉ ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ አይቻለሁ ።

የኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡ ለዚህ ፡ መልስ ፡ ሲሰጡ ፡ እንዲህ ፡ ይላሉ ፡ እነሆ ፡ እሳት ፡ በዕንጨት ፡ ውስጥ ፡ መኖሩ ፡ የታወቀ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ አንድ ፡ ዕንጨት ፡ ብቻውን ፡ ሳለ ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ እሳት ፡ አውጥቶ ፡ ሊያሳይ ፡ አይችልም ።

በዕንጨቱ ፡ ውስጥ፡ ያለው ፡ እሳትም ፡ ከዕንጨቱ ፡ ተከፍሎ ፡ ሊወጣና ፡ ሊታይ ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ አይችልም ፡ እንደዚኹውም ፡ ሴቶች ፡ በብቻቸው ፡ የሚያስገኙት ፡ ደም ፡ ወንዶችም ፡ በብቻቸው ፡ የሚያስገኙት ፡ ዘርዕ ፡ ሥጋ ፡ አጥንት ፡ ሊኾን ፡ እንደማይችል ፡ ነፍስም ፡ ሊኾን ፡ አይችልም ።

፪ቱን ፡ ዕንጨቶች ፡ አገናኝቶ ፡ ቢሰብቋቸው ፡ ግን ፡ ተረዳድተው ፡ በውስጣቸው ፡ ያለውን ፡ በተፈጥሮው ፡ የማይመስላቸውን ፡ እሳትን ፡ ሊያስገኙ ፡ እንደሚችሉ ፡ ወንድና ፡ ሴትም ፡ ተራክቦ ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፡ ከወንድ ፡ የሚገኝ ፡ ዘርዕና ፡ ከሴቷ ፡ የሚገኝ ፡ ደም ፡ በጠባብ ፡ ማኅፀን ፡ ተገናኝተው ፡ የማትመስላቸው ፡ የማትሞት ፡ ረቂቅ ፡ ነፍስን ፡ ያስገኛሉ ።

የነፍስ ፡ ተከፍሎዋም ፡ እንደ ፡ ፋና ፡ ብርሃን ፡ ተከፍሎ ፡ ነው ፡ ካንድ ፡ ፋና ፡ ብዙ ፡ መብራት ፡ ቢያቀጣጥሉለት ፡ ሕጸጽ፡ አያገኘውም ፡ ከቀድሞ ፡ መጠኑ ፡ አይቀነስለትም ።

ከሴትና ፡ ከወንድም ፡ ነፍስ ፡ በተከፈለች ፡ ጊዜ ፡ በነፍሳቸው ፡ ሕጸጽ፡ የለበትም ። ከፋናው ፡ ለሚቀጣጠሉ ፡ መብራቶችም ፡ ከፋናው ፡ የሚወስዱት ፡ ብርሃን ፡ ፍጹም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በከፊል ፡ በመጠን እንዳይደለ ፡ ከእናት ፡ ካባት ፡ የተከፈለችዋም ፡ ነፍስ ፡ ፍጽምት ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ ሕጽጽት፡ጐደሎ ፡ አይደለችም ፡ ብለው ፡ በቂ ፡ ምሳሌ ፡ ሰጥተው ፡ ያስረዳሉ ።

ደግሞ ፡ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ይህች፡ነፍስ ፡ ከእናት ፡ ካባት ፡ አትከፈልም ፡ የሚለው ፡ አሳብ ፡ ቃል ፡ ከእመቤታችን ፡ ሥጋን ፡ እንጂ ፡ ነፍስን ፡ አልነሣም ፡ ከማለት ፡ የሚያደርስ ፡ ጥርጊያ፡ ጐዳና ፡ ነው ።

በጠቅላላው ፡ ሥጋ ፡ እንጂ ፡ ነፍስ ፡ አልነሣም ፡ እንዳይባል ፡ ርሱው ፡ ራሱ ፡ ተከዘት ፡ ነፍስየ እስከ ፡ ለሞት ፡ ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፴፰ ። ማር ፡ ፲፬ ፡ ፴፬ ።

እስመ ፡ አነ ፡ እሜጡ ፡ ነፍስየ ፡ ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፲፯ ፡ ፲፰ ።

አባ ፡ አመሐፅን ፡ ነፍስየ ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፡ ሉቃ ፡ ፳፫ ፡ ፵፮ ። እያለ ፡ መላልሶ ፡ ነግሮናል ።

በመጽሐፈ ፡ ኪዳንም ፡ ሥጋሁ ፡ ለአዳም ፡ ምስለ ፡ ነፍሱ ፡ ብሎ ፡ ሥጋንም ፡ ነፍስንም ፡ እንደ ነሣ ፡ ነግሮናል ። በሌላም ፡ አንቀጽ ፡ ለብሶ ፡ ለዘአበሰ ፡ የሚል ፡ ንባብ ፡ እናገኛለን ።

እንግዲህ ፡ የበደለች ፡ ዕውቀት ፡ ያላት ፡ ነፍስ ፡ አይደለችምን ፡ ሥጋማ ፡ ብቻውን ፡ ምን ፡ ዕውቀት ፡ አለውና ፡ ይበድላል ፡ ቃል ፡ የተዋሐዳት ፡ ነፍስ ፡ ከበደለችቱ ፡ ከአዳም ፡ ነፍስ ፡ የተከፈለች ፡ ካልኾነች ፡ ወገኛቿ ፡ ላልኾኑ ፡ ለማይመስሏት ፡ ነፍሳት ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ወርዳ ፡ ግዕዛንን ፡ እንደምን ፡ ሰበከችላቸው ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ።

ቃል ፡ ከእመቤታችን ፡ ሥጋንም ፡ ነፍስንም ፡ ነስቶ ፡ በሥጋም ፡ በነፍስም ፡ ክሶ ፡ አዳነን ፡ ብለን የማናምን ፡ ከኾነ ፡ እምነታችን ፡ ኹሉ ፡ ከንቱ ፡ ኾነ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ምናልባት ፡ ይህ ፡ ስለነፍስ ፡ ተፈጥሮ ፡ የጻፍኩት ፡ በሮማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትምርት ፡ ኾኖ ፡ የማይነገር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይቅርታ ፡ እለምናለሁ ፤ ትምርት ፡ ኾኖ ፡ ይነገር ፡ እንደኾነ ፡ ግን ፡ ይፀም ፡ አብሮ ፡ ታስቦበት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድነት ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የሚፈጸም ፡ ቢኾን ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ የማትጠላ ፡ መኾኗን ፡ እገልጻለሁ ።

ይህ ፡ ኹላችን ፡ የምንጠቀምበት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድነት ፡ በዘመናችን ፡ ተፈጽሞ ፡ ለማየት ፡ ያብቃን ።

አ ሜ ን ።

# ማ ው ጫ


መቅድም ፲፯
መግቢያ ፳፪
ማቅረቢያ ፳፫
የደራሲው ፡ ዐጭር ፡ የሕይወት ፡ ታሪክ ፳፯
መልስ ፡ የሚሰጥበት ፡ መቅድም ፳፰
ደራሲው ፡ የጠቀሷቸው ፡ መጻሕፍት ፴፩
በኢትዮጵያ ፡ የሚታመነው ፡ ባህል ፴፯
እውነተኛው ፡ ምክንያት ፵፭
ኢትዮጵያ በእስክንድርያ ፡ ስለመመራቷ ፵፱
ስለግብጻዊው ፡ ጳጳስ ፡ ሥራና ፡ ሥልጣን ፵፱
ነገሥታቱ ፡ በሃይማኖት ፡ ስላላቸው ፡ ሥልጣን ፶፭
ስለ ፡ ዕጨጌው ፡ ሥልጣን ፶፰
ኢትዮጵያ ፡ ከሮማ ፡ የተለየችው ፡ መቼ ፡ ነው ፷፪
ልዩ ፡ ልዩ ፡ አስተያየቶች ፷፫
በይቅናል ፡ የሚገለጹ ፡ አሳቦች ፷፱
ስለ ፡ ፱ ፡ ቅዱሳን ፡ አመጣጥ ፸፭
የኬልቄዶንን ፡ ጉባኤ ፡ የመቃወም ፡ ምልክት ፹፪
ስለኬልቄዶን ፡ ጉባኤ ፡ አስተያየት ፺፯
በጉባኤ ፡ ስለተደረገው ፡ ታሪክ ፡ ስሕተት ፻
አካላዊ ፡ ተዋሕዶን ፡ ሲተረጕሙ ፡ የሚያገቧቸው ፡ ቃላት ፻፲፭
የቃሎች ፡ ምርመራ ፻፲፰
የኬልቄዶኑን ፡ ውሳኔ ፡ ይቀበላሉ ፡ ስለሚሉት ፻፳፭
የኢትዮጵያውያንና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሰባኪዎች ፡ ክርክር ፻፴፯
የካቶሊክ ፡ ሰባኪዎች ፻፴፱
የመጀመሪያ ፡ ክርክሮች ፻፵፪
በ፲፮ና ፡ በ፲፯ኛ ፡ ፻ ፡ የተደረጉ ፡ ክርክሮች ፻፵፰
አሳቦችና ፡ ምስክሮች ፻፷፯
በአምልኮና ፡ በሃይማኖት ፡ የሚገኝ ፡ ትምርት ፻፸
ስለክርስቶስ ፡ ቅብዐት ፡ ክርክር ፻፸፱
ስለክርስቶስ ፡ ባሕርያት ፻፸፱
የተገለጡ ፡ አስተያየቶች ፻፺፭
የርስ ፡ በርስ ፡ ክርክሮች ፻፺፮
ስለቅኔዎች ፻፺፰
የመጨረሻ ፡ ፍርድ ፪፻፲፭
ጠቅላይ ፡ መደምደሚያ ፪፻፲፯
ማጠቃለያ ፡ አሳብ ፪፻፳፩

# ማ ረ ሚ ያ

| ገጽ | መስመር | ግድፈት | እርም |
|---|---|---|---|
| ፲፯ | ፲፯ | እትባበር | እተባበር |
| ፵፭ | ፳፱ | ዲዮስቅሮስን | ዲዮስቆሮስ |
| ፹፪ | ፴፪ | በግልም | በግልጥ |
| ፷፯ | ፰ | ባህርይ ትስብእትን | ባሕርየ ትስብእት |
| ፩፻፲፭ | ፳ | ያለው ባሕርይ | የሰው ባሕርይ |
| ፩፻፲፮ | ፰ | የሥላሴ ባህርይ ያለ— | የሥላሴ ባህርዩ ነው ያለ |
| ፩፻፴፰ | ፲፪ | ኮነ | ኾነ |
| ፩፻፵፰ | ፴ | ፍጹሜነ | ፍጸሜሃ |
| ፩፻፰ | ፲፰ | ትስብእትነት | ትስብእት |
| ፩፻፷፭ | ፴፪ | ይትረጕሙታል | ይተረጐሙታል |
| ፩፻፹፩ | ፵፰ | ርዕስ | ርእሳ |
| ፩፻፹፮ | ፲፩ | መመለድ | መወለድ |
| ፪፻፲፯ | ፳፱ | ፪፷፱ | ፪፻፷፱ |

1. አለ: ማሥሙር: ሥላሴ 78. 183–185
2. አለ: ቀዋሚነ: ማሥሙር " 171
3. ዶ/ዲዮስቆሮስ: [illegible] " 91